21000

# ቆንጆዎቹ

ከ ሠርቅ ዳ.

አሳታሚ፡- ሜጋ አሳታሚ ድርጅት (ሜ.አ.ድ)
1989

በሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ታተመ
Printed by Mega Printing Enterprise

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

(c)ሜጋ አሳታሚ ድርጅት (ሜ.አ.ድ)
Mega Publishing Enterprise (M.P.E)

የመጀመሪያ እትም- 1988
ሁለተኛ እትም -1989

ሦስተኛ እትም 1990

ሽፋን

ዲዛይነር:- ሠዓሊ መስፍን ሃብተማርያም
ፎቶግራፈር:- ኢዮቤል ዘርፉ

ለ-አስቀያሚዎቹ

# ቅድመ ታሪክ

እሪ! እሪ! ይላል አምቡላንሱ። ከፊቱ ያለውን ሁሉ እያተራመሰ፣እየደረማመሰ በጭለማው ውስጥ እንደ ቀስት ወደፊት ይወነጨፋል። ቦግ-እልም-ቦግ-እልም የሚሉትና የሚንቀለቀሉት ቀያይ የአደጋ መብራቶቹ የሚተፉት ቀይ ብርሃን በጨረቃ የለሹ ምሽት እየተወራጨ በዝናቡ ጎርፍ በተዘፈቀው አስፋልት ላይ ሲያርፍ ዙሪያው የደም ኩሬ ይመስላል። እሪ! እሪ! እሪ! ይላል አምቡላንሱ፣ በደሙ ኩሬ ውስጥ እየተንቦራጨቀ እሪ! እንደ መብረቅ ሲወረወር በሩቅ ያዳመጡት አሽከርካሪዎች ጥግ ጥግ ይይዛሉ። እግረኞች ከመኪናው መንገድ ይሸሻሉ፤ በሩቅ ቆመው በምሽት ከዱር በርግጎ እንደወጣ ጎሽ አፍጥጠው ይመለከቱታል። ከአራት ኪሎ አቅጣጫ የመጣው አምቡላንስ መሃል ለመሃል ተርትሯት ሲገባ ካዛንቺስ ተሸበረች።

መንገድ ዳር የቆመችው የዲፕሎማቲክ መለያ ታርጋ የለጠፈችው መኪና ፊንጂ እንደተጠመደባት ሁሉ ብትት በሕዝብ ተከባለች። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በየመኪናዎቻቸው አናት ላይ የተገጠመላቸውን ሰማያዊ መብራት ብልጭ ድርግም ብልጭ ድርግም እያደረጉ የደረሱት ፖሊሶች ሕዝቡን ለማበታን ይጥራሉ። ከዚህ ሲበትኑት ከወዲያ ይጠራቀማል። የደንብ ልብስ የለበሱ ሁለት የፖሊስ መኮንኖች ከመኪናዋ ጎን እንደቆሙ የአምቡላንሱን ድምፅ ሲሰሙ ተቁነጠነጡ። ጠና ያለው ወደ መኪናዋ ተጠጋ። በመሪው በኩል ያለው በር ተከፍቷል፤ መስታወቱ አስፋልቱ ላይ ረግፏል። በሹፌሩ መቀመጫ ላይ የተቀመጠው የሞርኮው ወታደራዊ አታሼ ወደኋላ ተንጋሎ ዓይኖቹን ገርበብ አድርጓቸዋል። በስተግራ ከማጅራቱ ስር ጥይቱ ከገባበት ጠባብ ቀዳዳ በቀጭኑ የሚንቆረቆረው ደም ግራ ትከሻውን አበሰብሶታል። ፖሊሱ ጠጋ ብሎ አጠናው፤ ግራ እጁን አንስቶ የልቡን ምት አዳመጠ። አለ። አልሞተም። ደም የምትረጭ ልቡ የቀራትን እንጥፍጣፊ እየጨመቀች ትር-ትር ትላለች።

የአምቡላንሱ እዩዩ እየቀረበ መጣ። ፖሊሱ ትከሻው ሲነካ ተሰማው። ቀና ብሎ ተመለከተ። ከጀርባው ከቆመው ጓደኛው ጋር ተያዩ። በመላ ተነጋገሩ። የአምቡላንሱ ድምፅ ቀረበ። ትር-ትር ትላለች ልቡ። ዋይ! ዋይ! ይላል አምቡላንሱ። ፖሊሶቹ ተያዩ። የተሰጣቸው ትዕዛዝ ቁርጥ ያለ ነው። ጠና ያለው ፖሊስ እጁን ሰደደና ከመሪው ጀርባ ጋለል ያለውን ቁስለኛ አፍና አፍንጫ ጥርቅም አድርጎ አፈነው። ትር-ትር አለች ልቡ። ትንሽ ተፈራገጠ። ትር-ትር ወዲያው ዝም አለ። ቀና አለ ፖሊሱ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እርጋታ እየታየበት።

# I

## "ቆንጆዎቹ ገና አልተወለዱም"

\- ኤ.ኬ.አርማህ

-1-

...አዲስ አበባ... የአፍሪካ መዲና... እሁድ ሐምሌ 21...199...
...ማለዳ ... ያነባል... በርኖሱን ደርቦ፤ አንገቱን ቀልሶ... እንባውን ያወርዳል ሰማዩ:: ምድርን ከምድር ሲያይ፤ ሲያዝን፤ ሲተክዝ... ሲባባ፤ ሲመረው... ሰማዩ ከሰማይ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል:: እረፍ፡ አልኮ ሲል በርኖሱ ይተክዛል:: ዳግም ሆዱ ሲርድ... አንጀቱ ሲላወስ... ሆድ ዕቃው ሲታሸስ... መንፈሱ ሲታመስ... እዬዬ!... እህህ! ... ነፍሱ ስታቃስት... ዳግም ይጀምራል ሲያለቅሰው፤ ሲያነባ... ሰማዩ... ማለዳ...

... ክረምቱ ጨክኗል... ዓለም... ምድር... ማማ...ክል ለብሳለች... ትንፋሿ ቆሟል.. ጥላሸት? .... እንፋሎት? ጭጋግ ነው! ... ባዘቶ!...

በአፓርትመንቱ ሶስተኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው በጣም በተሸፈነው የመኝታ ቤቱ መስኮት ቁልቁል የሚታየው ድብዝዝ ያለ ትርዒት አላጠግብህ ቢለው እጁን [illegible] መጋረጃ ውስጥ አሾልኮ ቀዝቃዛውን መስታወት በመዳፉ ወለወለው:: [illegible] ቅዝቃዜ እንደመርፌ ጠቅ አደረገው.. እጁን ግን አልሰበሰበም::

ከመንገዱ ባሻገር ያለው መናፈሻ ጭር እንዳለ ነው... ቢሆንም... እየነጋ ነው... ሌላ ቀን [illegible] አዲስ ቀን...

ባዶ እግሩን ምንጣፉ ላይ እንደቆመ ራቁት ደረቱን አከክ አከክ አደረገና ሰዓቱን ተመለከተ::

አንድ ሲሆን ነው .... አንድ... አንድ ቀን::

ፊቱን ወደ አልጋው መልሶ ቆመ :: እንደ ሁሌው እግሮቿን ዘና አድርጋ እጆቿን እዚያና እዚያ አመናቅራ በጀርባዋ ተንጋላ ተኝታለች:: ከላይዋ ላይ ተንሸራቶ አንድ ጠርዙ ከመሬት ሌላው ጠርዙ ከአልጋው መሃል የደረሰው የብርድ ልብስ ከፋኛ አጋልጧታል:: የተመነቃቀረውንና የተበታተነውን አልጋ ሲመለከት ሰውነቱ ተፍታታበት::

ቶሎ ብሎ ዓይኖቹን ከተጋለጠው ሰውነቷ ላይ ነቀለና ወደ መታጠቢያ ቤት አመራ::

ሰውነቱን በሙቅ ውሃ ተጣጥቦ በሰፊ ፎጣ አካላቱን እያደራረቀ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ:: ፈገግ አለ ሲመለከታት:: ከእንቅልፏ ተነስታ ሰፊው አልጋ መሃል ተቀምጣለች፤ እንቅልፍ ያሳበጠው ትኩስ ፊቷ ገና ወደ ቀድሞ ቅርጹ አልተመለሰም:: በዘዝ ያሉ ጥቋቁር ዓይኖቿ ገና ማየት የጀመሩ አይመስሉም:: ብትንትን ብሎ ትከሻና ደረቷ ላይ የተዘራው ፀጉሯ የደነበሩ መንታ ሚዳቆዎች የሚመሳሰሉ ራቁት ጡቶቿን መሸፈን መሸሸግ አቅቶት ግራ ተጋብቷል::

"እንዴት አደርሽ እንዳትለኝ::" አለች እንቅልፍ ባጎረነነው ድምጿ ተሽቀዳድማ::

"ለምን?" ፈገግ አለ::

"ደህና አልልህማ! እብደት ነበርኮ... ናቲ ሙት እብደት ነው:: አንዳንዴኮ ሰው መሆንህ ያጠራጥረኛል:: አውሬ!" አለች ድንገት በሁለት እጆቿ ጭንቅላቷን ያዝ አድርጋ::

"አዳም ካደረገው የተለየ ምን ሳደርግ ተገኘሁ?" አለ ናትናኤል እየሳቀ:: አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጦ ጎተት አደረጋት:: ተጎተተችለት:: እጆቹን በብብቶቿ አሳልፎ እቅፍ ያዛት:: ሳመችው::

"አዳም እንዳንተ ከቀበጠ ሄዋን ብትጮህም የማደርስላት የለም ብሎ ነው:: አንተ ግን ድገመኝና አሳይሃለሁ...ጎረቤቶችህን ነው የምቀሰቅስልህ::"

"ሀ! ሀ! ሀ! ጎረቤቶቼ ከእኔ ተሽለው? ርብቃ፤ ሁሉም በየጓዳው አውሬ ነው:: ፊት ከሰጡት ሁሉም አንድ ነው:: ፊጥ ካለበት አይወርድም::" እጆቹ በአንሶላው መሀል ዋኝተው እልፊው ጭኖቿ መሃል ገቡ::

"እረፍ! እየው ደሞ ጀመረህ... ቆይ! ናቲ!"

ሳይታወቀው ተመልሶ ገባበት:: ስህተት:: ዛሬ አልጋ ላይ መዋል የለበትም:: በፍጹም! ምን ማድረጉ ነው ታዲያ? ድንገት ከአልጋው ላይ ተፈናጥሮ ተነሳ:: ሳይታወቀው ፕሮግራሙን አበላሽቶ ነበር:: ከርብቃ ጋር እንዲህ ጨዋታ ከጀመረ፤ ልፊያ ከቀመሰ ቀኑ እንደማይበቃው ያውቀዋል:: አሽቶቶ፤ ልሶ፤ ገምጦ፤ አኝኮ፤ ውጦ አይጠግባትም:: ድጋሚ እንደ አዲስ ሊያሽታት ይጀምራል:: ሳይወድ በግድ ራሱን ተቆጣጥሮ ፊቱን መለሰና ማበጠሪያውን አንስቶ ፀጉሩን ያበጥር ጀመር:: 'እናቷን! ይቺ ልጅ ሳይታወቀኝ መዳፏ ውስጥ ልትከተኝ ነው...' አለ::

"ለምን ተነሳህ ግን በጠዋት?" በጀርባዋ ተንጋላለችበት ሳትነሳ ሽቅብ እያየች ጠየቀችው::



"ቀጠሮ" በመስታወቱ ውስጥ እየተመለከታት::

"በእሁድ!"

"አምን ርብቃ::" አለ በለሆሳስ::

"ምንድንነበር ያልከኝ?...አበዛኸው! ናትናኤል ሙት አበዛኸው...እሁ ንስ የቤትህ ቁሳቁስ መሰልኩህ መሰለኝ..." አለች እንደተከፋ ሕፃን እግሮቿን አመናጭራ ከአልጋ እየወረደች:: "...በሳምንት ሁለት ቀን ብቻ መገናኘታችን በዛና በእሁድም ቀጠሮ ትይዝ ጀመር...አልታወቀህም እንጂ በጣም ነው የተዘባነንከው::" ከአልጋው ግርጌ የተቀመጠውን ነጭ የጠዋት ልብስ አንስታ ሳትደርበው መሬት ለመሬት እየጎተተችው እራቁቷን የመታጠቢያ ቤቱን በር በርግዳ ገባችና ከውስጥ ጠረቀመችው::ደቂቃም ሳትቆይ ጮሃ ስትሳደብ ተሰማው-"አንተ ብሽቅ!... እርኩስ!..":: ብቻዋን ትጮሃለች:: ፈገግ አለ የጥርስ ሳሙና የተቀባውን የሽንት ቤት መቀመጫ አስታውሶ ስትናደድ፤ ስትቆጣ፤ 'ግስላ ስትሆን ይበልጥ ታምረዋለች::ተራ ህይወታቸው ብቻ አይደለም፤ ፍቅራቸውም ትግል ነው፤ ንክሻ፤ ቡጭሪያ... እሷም ብትሆን ጠዋት ጠዋት ትነጫነጭ እንጂ የአፈቃቀር ዘዬውን ተላምዳዋለች::ጠዋት 'አውሬ' ብትለው ውም ማታ አትፈራውም::ሲነጋ 'ጭራቅ' ብትለውም ሲመሽ አትሸሸውም ...አላይዋ ላይ እንደ መዥገር ተጣብቆ አልነቀል ሲላት፤እንደ ቅንቅን በሰራ አካላቷ ሲፍለከለክ፤ እንደ አልቅት ደሟን ሲመጠምጥ፤እንደሞያሌ አካሏን ሲቦረቡር፤ እንደምስጥ በአጥንቷ ሲያስኬድ 'ያሳንተ'...ትለዋለች... ሌላ ፀሐይ ስትወጣ ደግሞ... ሌላ ነገ ሲተካ... 'አውሬ' ... 'ሰው በላ'::

የእንግሊዝ ቅርፅ ባለው መስታወት ፊት ቆሞ ክራባቱን ያስር ጀመር::ከፊቱ የተደቀነውን ቀን እንዴት እንደሚገፋው እርግጠኛ አይደለም:: በትክክል የት ሊሄድ እንዳለበት ለራሱም ግልፅ አልሆነለትም:: እውነቱን ለመናገር እርሱ ራሱም ቢሆን ምን ለመስማት እንደጠበቀ አያውቅም:: ጥያቄውን ማቅረቡ ራሱ አስቸጋሪ ነው:: ቢሆንም ለጥርጣሬው አንድ መልስ እስካላገኘ ድረስ ለእረፍት የሚያቀርበው ያልተሟላ ብቻ ሳይሆን ባዶ ቀፎ እንደሚሆን ተሰምቶታል:: የትም ይሂድ የት ብቻ ለጥርጣሬው በቂ መልስ ማግኘት አለበት::ለዚህ ነው እሁድን ሲሰዋ ደሟን ሊያፈስ የቆረጠው:: ጥርጣሬውን ያገነነበት የላይቤርያው ወታደራዊ አታሼ የገባበት መጥፋት ነው:: በአንድ ሳምንት ሶስተኛ ጥያቄ:: ሊሆን የማይችል ተራ አጋጣሚ:: ሰውየው ቀደም ሲልም በዚሁ የስራ መደብ ላይ ለስድስት ዓመታት ሲሰራ እንደቆየና ለአዲስ አበባም እንግዳ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ታዲያ ድንገት መሰወሩን ምን አመጣው? የላይቤርያ ኤምባሲ ባለሥልጣኖችስ ያሳዩት ለዘብተኝነት እንዴት ጤነኛ ሊሆን ይችላል?የወታደራዊ አታሼውን መጥፋት ችላ ማለቱ ለነገሮች ተገቢ አትኩሮት አለመስጠት መስሎ ታየው::

በመጀመሪያ ደረጃ በሳምንቱ መጀመሪያ በአዲስ አበባ የተከሰቱት የጊኒና የሞሮኮ ወታደራዊ አታሼዎች ግድያ የምን ውጤት ነበረ? የወታደራዊ አታሼዎቹ ሬሳ በተለያዩ ቦታዎች የተጣለ ቢሆንም በተመሳሳይ ሁኔታ

በየመኪናዎቻቸው ውስጥ ነበር የተገኘው። ለሁለቱም ሰዎች ሞት ምክንያት የሆኑት ጥይቶች ከአንድ ሽጉጥ ለመተኮሳቸው የቀረበው ሪፖርት በዝርዝር ያስቀመጠው ጉዳይ ነው። በሬሳዎቹም ላይ የተገኙት ቁስሎችና ሌሎችም የአካባቢና የቴክኒክ ማስረጃዎች የሚያመለክቱት በሁለቱ ሰዎች ላይ የተፈፀሙት ግድያዎች በተመሳሳይ መሳሪያ፣ በተመሳሳይ ርቀት፣ በተመሳሳይ ማዕዘን ምናልባትም በአንድ ሰው መሆኑን ነው። ያ ሰው ማነው? መልስ ሊያገኝ የቻለ ጥያቄ አይደለም። ሳምንቱ ከመገባደዱ በፊት ደግሞ ሌላ ሁኔታ ተፈጠረ - የላይቤሪያው ወታደራዊ አታሼ ድንገት የገባበት ጠፋ።

ታዲያ ይህን እንዴት 'ተራ አጋጣሚ' ብሎ ማለፍ ይቻላል? በእርግጥ የሰዎቹ አሟሟት በየተራ ነው። ነገር ግን የናትናኤልን ጭንቅላት እረፍት የነሳው የወታደራዊ አታሼዎቹ ሞትና መሰወር ምናልባት ባለፉት ጥቂት ወራት በአዲስ አበባ ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ኤምባሲዎች ያልተለመደ እንቅስቃሴ ጋር ዝምድና አለው ብሎ መጠርጠሩ ብቻ አልነበረም። ባለፉት ወራት በተለያዩ የአፍሪካ አገሮችና በአውሮፓም ያጋጠሙ ድንገተኛ አደጋዎች ያለወትሮው በርካታ ብቻ ሳይሆኑ ምክንያተ ቢስም ነበሩ። ቢሮው ውስጥ ቁጭ ብሎ ደጋግሞ ካነበባቸው የውጭ ዘገባዎች ጥቂቶቹ ታወሱት።

ጅብራልተር- መጋቢት ሃያ-ዘጠኝ ከምትባል የሞሮኮ የወደብ ከተማ ተነስታ ካዲስክ ወደምትባል የስፔይን የወደብ ከተማ በመጓዝ ላይ የነበረች አንድ የሞተር ጀልባ የገባችበት ጠፋ። የታመኑ የወሬ ምንጮች በጀልባዋ ላይ የሞሮኮው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በምስጢር ተሳፍረው ነበር ይላሉ።የሞሮኮ መንግሥት ጉዳዩን በተመለከተ ያለው የለም...(ዘ ኢንዲፐንደንት)

ካሜሩን - ሚያዝያ ሁለት-የአገሪቱን ኤታማዦር ሹምና የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩን አሳፍራ ከያውንዴ ወደ ዱዋላ ትበር የነበረች የካሜሩን የጦር ሄሊኮፕተር በአየር ላይ እንዳለች ስትቃጠል በውስጧ በካሜሩን የእሥራኤል አምባሳደርን ጨምሮ ስድስት ባለሥልጣኖች አለቁ... (ካሜሩን ትሪቡን)

ያውንዴ - ሚያዝያ ስምንት- የካሜሩን የአየር ሃይል አዛዥ መኖሪያ ከተማዋ ወጣ ብሎ በሚገኝ የገጠር ቤታቸው ሬሳቸውን ገደሉ ቀባለ።የውስጥ አዋቂዎች እንደሚሉት የጄኔራሉ ቤት ለአራት ቀናት በልዩ ኮማንዶ ሃይል ተከቦ የቆየ ሲሆን የባለሥልጣኑ ስልክም ተቆርጦ ነበር... (ዴይሊ ቴሌግራፍ)

ኤፕልስ- " ግንቦት አስር-ከአልጀርስ ተነስተው ወደ ፓሊያን ያልተጠበቀ በረራ ያደረጉት የአልጄሪያ መከላከያ ሚኒስትር ኔፕልስ አውሮፕላን ማረፊያ ባረፉ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ህይወታቸው ባልታወቀ አሸባሪ ጥይት አለፉ...(አልሞጃሂድ)



አጋጣሚ? ይህ ሁሉ ተራ አጋጣሚ?አዲስ አበባ ውስጥ የሚፈፀመው ግድያና መሰወርስ? ይህም አጋጣሚ? ከአራት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይህ ሁሉ አጋጣሚ?...

በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ነበር አለቃው ወደ ቢሮአቸው ያስጠሩት።

"ደውለው ፈልገውህ ነበር።" ብላው ነበር ፀሃፊው ያን ዕለት ጠዋት እርፍዶ ቢሮው ሲገባ። ማን? አላላትም። እሱ በሚሰራበት ሁለተኛ ፎቅ ላይ 'አንቱ'፣ 'እርስዎ'፣ 'እርሳቸው' ... እየተባለ የሚነገርላቸው የሱ አለቃ ብቻ ናቸው።የተረፈው በዕድሜም በሥልጣንም ተቀራራቢ ነው - 'አንተ' እንዳንዴም 'አንቺ' ነው የሚባባለው:

"ይሄ ጭን ይገጥም ሰምሪ።" አላት ናትናኤል ወደ ቢሮው በር ሲያመራ ፈርከክ ያደረገቻቸውን ጭኖቿን እየተመለከተ።

"ተወው ባክህ 'እሱ የከፈቱውን ሳይዘጋው አይቆርም' ተብሏል።" አለች ሳምራዊት ፈረግ ብላ።

"አዲስ የመጣ ሪፖርት አለ?" አላት እየሳቀ የቢሮውን በር ከፍቶ ከመግባቱ በፊት።

"ሁለት።" አለችው የታች ከንፈሯን በምላሷ አርጥባ። ልማዷ ነው።

ሳምራዊት ቆንጆዬ ልጅ ነች። የምትፈልገውንና የምትመኘውን ትዳር እንዴት ሳታገኝ እንደዘገየች ሁሌ ይገርመዋል። ምናልባት በጣም ስለምትጓጓና ስሜቷንም ስለማትደብቅ ይሆናል። ናትናኤል ገና ከጠዋቱ ነው የሸሻት። ሌላ ወሬ የላትማ! ባል፣ ጋብቻ ትዳር። ሸሻት። ጎመን በጤና።

ቢሮው ገብቶ ከወንበሩ ላይ ከመቀመጡ በፊት ጠረጴዛው ላይ የተቀመጡትን ሁለት ወረቀቶች አንስቶ ዋጣቸው። የጠበቀው ነበር - አንደኛው ወረቀት ስለ አልጄርያ ወታደራዊ አታሼ፣ሁለተኛው ደግሞ ስለሞዛምቢክ ወታደራዊ አታሼ የቀረበ ሪፖርት። ሁለቱም ሰዎች ወደ አገራቸው ሄደዋል - የሰሞኑ ተደጋጋሚ ዜና።

ወረቀቶቹን በነበሩበት አስቀምጦ ለአፍታ ዓይኖቹን ጨፍኖ ከሰላሳ የሚበልጡ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ኤምባሲዎች የሚሰሩ ወታደራዊ አታሼዎች እየተጠሩ ወደየአገሮቻቸው ሄደዋል። ጥቂቶቹ ሲመለሱ በተቀሩት ሌሎች ተተክተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለነዚህ ሁሉ ወታደራዊ አታሼዎች መጠራት ከሚወክሏቸው መንግሥታትም ሆነ ከሌላ አካል የተሰጠ ምክንያታዊ ፍንጭ የለም።

በየመኪናዎቻቸው ውስጥ ነበር የተገኘው። ለሁለቱም ሰዎች ሞት ምክንያት የሆኑት ጥይቶች ከአንድ ሽጉጥ ለመተኮሳቸው የቀረበው ሪፖርት በዝርዝር ያስቀመጠው ጉዳይ ነው። በሬሳዎቹም ላይ የተገኙት ቁስሎችና ሌሎችም የአካባቢና ያቴክኒክ ማስረጃዎች የሚያመለክቱት በሁለቱ ሰዎች ላይ የተፈፀሙት ግድያዎች በተመሳሳይ መሳሪያ፣ በተመሳሳይ ርቀት፣ በተመሳሳይ ማዕዘን ምናልባትም በአንድ ሰው መሆኑን ነው። ያ ሰው ማነው? መልስ ሊያገኝ የቻለ ጥያቄ አይደለም። ሳምንቱ ከመግባደዱ በፊት ደግሞ ሌላ ሁኔታ ተፈጠረ - የላይቤርያው ወታደራዊ አታሼ ድንገት የገባበት ጠፋ።

ታዲያ ይህን እንዴት 'ተራ አጋጣሚ' ብሎ ማለፍ ይቻላል? በእርግጥ የሰዎቹ አሟሟት በየተራ ነው። ነገር ግን የናትናኤልን ጭንቅላት እረፍት የነሳው የወታደራዊ አታሼዎቹ ሞትና መሰወር ምናልባት ባለፉት ጥቂት ወራት በአዲስ አበባ ከሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ኤምባሲዎች ያልተለመደ እንቅስቃሴ ጋር ዝምድና አለው ብሎ መጠርጠሩ ብቻ አልነበረም። ባለፉት ወራት በተለያዩ የአፍሪካ አገሮችና በአውሮፓም ያጋጠሙ ድንገተኛ አደጋዎች ያለውትሮው በርካታ ብቻ ሳይሆኑ ምክንያተ ቢስም ነበሩ። ቢሮው ውስጥ ቁጭ ብሎ ደጋግሞ ካነበባቸው የውጭ ዘገባዎች ጥቂቶቹ ታወሱት።

ጅብራልተር- መጋቢት ሃያ-ዘጠኝ የር ከምትባል የሞሮኮ የወደብ ከተማ ተነስታ ካዲስክ ወደምትባል የስፔይን የወደብ ከተማ በመጓዝ ላይ የነበረች አንድ የሞቶር ጀልባ የገባ ችበት ጠፋ። የታመኑ የወሬ ምንጮች በጀልባዋ ላይ የሞሮኮው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በምስጢር ተሳፍሬው ነበር ይላሉ።የሞሮኮ መንግሥት ጉዳዩን በተመለከተ ያለው የለም...(ዘ ኢንዲፔንደንት)

ካሜሩን - ሚያዝያ ሁለት-የአገሪቱን ኢታማዦር ሹምና የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩን አሳፍራ ከያውንዴ ወደ ዱዋላ ትበር የነበረች የካሜሩን የጦር ሄሊኮፕተር በአየር ላይ እንዳለች ስትቃጠል በውስጧ በካሜሩን የእሥራኤል አምባሳደርን ጨምሮ ስድስት ባለሥልጣኖች አለቁ... (ካሜሩን ትሪቡን)

ያውንዴ - ሚያዝያ ስምንት- የካሜሩን የአየር ሃይል አዛዥ ከቤት ከተማዋ ወጣ ብሎ በሚገኝ የገጠር ቤታቸው ራሳቸውን ገደሉ ተባለ።የውስጥ አዋቂዎች እንደሚሉት የጄነራሉ ቤት ለአራት ቀናት በልዩ ኮማንዶ ሃይል ተከቦ የቆየ ሲሆን የባለሥልጣኑ ስልክም ተቆርጦ ነበር... (ዴይሊ ቴሌግራፍ)

ኔፕልስ- " ግንቦት አስር-ከአልጀርስ ተነስተው ወደ ጣሊያን ያልተጠበቀ በረራ ያደረጉት የአልጀሪያ መከላከያ ሚኒስትር ኔፕልስ አውሮፕላን ማረፊያ ባረፉ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ህይወታቸው ባልታወቀ አሸባሪ ጥይት አለፈች...(አልሞጃሂድ)



አጋጣሚ? ይህ ሁሉ ተራ አጋጣሚ?አዲስ አበባ ውስጥ የሚፈፀመው ግድያና መሰወርስ? ይህም አጋጣሚ? ከአራት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይህ ሁሉ አጋጣሚ?...

በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ነበር አለቃው ወደ ቢሮአቸው ያስጠሩት።

"ደውለው ፈልገውህ ነበር።" ብላው ነበር ፀሃፊው ያን ዕለት ጠዋት እርፍዶ ቢሮው ሲገባ። ማን? አላላትም። እሱ በሚሰራበት ሁለተኛ ፎቅ ላይ 'አንቱ'፣ 'እርስዎ'፣ 'እርሳቸው' ... እየተባለ የሚነገርላቸው የሱ አለቃ ብቻ ናቸው።የተረፈው በዕድሜም በሥልጣንም ተቀራራቢ ነው - 'አንተ' አንዳንዴም 'አንቺ' ነው የሚባባለው:

"ይሄ ጭን ይገወም ብሞራ።" አላት ናትናኤል ወደ ቢሮው በር ሲያመራ ፈርከክ ያደረገቻቸውን ጭኖቿን እየተመለከተ።

"ተወው ባክህ 'እሱ የከፈተውን ሳይዘጋው አያቆርም' ተብሏል።" አለች ሳምራዊት ፈረግ ብላ።

"አዲስ የመጣ ሪፖርት አለ?" አላት እየሳቀ የቢሮውን በር ከፍቶ ከመግባቱ በፊት።

"ውሸት።" አለችው የታች ከንፈሯን በምላሷ እርጥባ። ልማዷ ነው።

ሳምራዊት ቀንጆዬ ልጅ ነች። የምትፈልገውንና የምትመኘውን ትዳር እንዴት ሳታገኝ እንደዘገየች ሁሌ ይገርመዋል። ምናልባት በጣም ስለምትጓጓና ስሜቷንም ስለማትደብቅ ይሆናል። ናትናኤል ገና ከጠዋቱ ነው የሸሻት። ሌላ ወሬ የላትማ! ባል፣ ጋብቻ ትዳር። ሽሻት። ጎመን በጤና።

ቢሮው ገብቶ ከወንበሩ ላይ ከመቀመጡ በፊት ጠረጴዛው ላይ የተቀመጡትን ሁለት ወረቀቶች አንስቶ ዋጣቸው። የጠበቀው ነበር - አንደኛው ወረቀት ስለ አልጀርያ ወታደራዊ አታሼ፣ሁለተኛው ደግሞ ስለሞዛምቢክ ወታደራዊ አታሼ የቀረበ ሪፖርት። ሁለቱም ሰዎች ወደ አገራቸው ሄደዋል - የሰሞኑ ተደጋጋሚ ዜና።

ወረቀቶቹን በነበሩበት አስቀምጦ ለአፍታ ዓይኖቹን በዘዝ አድርጎ ቆመ። 'ምን ማለት ነው?' ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ከሰላሳ የሚበልጡ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ኤምባሲዎች የሚሰሩ ወታደራዊ አታሼዎች እየተጠሩ ወደየአገሮቻቸው ሄደዋል። ጥቂቶቹ ሲመለሱ በተቀሩት ሌሎች ተተክተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለነዚህ ሁሉ ወታደራዊ አታሼዎች መጠራት ከሚወክሏቸው መንግሥታትም ሆነ ከሌላ አካል የተሰጠ ምክንያታዊ ፍንጭ የለም።

ናትናኤል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመድቦ ሲሰራ ስምንት ዓመት ሆኖታል:: በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን እንደያዘ የተመደበው አሁን በሚገኝበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአፍሪካ ጉዳይ በተለይ በምዕራብ አፍሪካ ክፍል ነበር:: ለአራት ዓመታት ካገለገለ በኋላ ወደሰሜን አፍሪካ እንዲዛወር ተደረገ:: ካለፈው ዓመት ጀምሮ ደግሞ የአእምሮውን ፈጣንነት የተገነዘቡ አለቆቹ የአፍሪካ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ አድርገው ባይሾሙትም ቢሮውንና ጠረጴዛውን ጭነው እየጋለቡት ነው::

አእምሮው እውነትም ፈጣን ነው:: አዳዲስ ሁኔታዎች ቶሎ ይገቡታል:: አንዳንዴም የመቸኮል ባህርይው እልህ ውስጥ የሚያስገባውም ቢሆን የነገሮችን ሂደት ከአጀማመራቸው የመከታተል ትዕግሥቱ ያመዝናል:: አስተሳሰቡ ቀናና ቀጥተኛ ነው:: ጠማማ መስመሮች ካጋጠሙት በጠማማ መስመር መሄድም አያቅተውም:: ልብ ብሎ የተከታተለውን ጉዳይ እዳር ሳያደርስ ሠላማዊ እንቅልፍ የማያገኝ መሆኑ ደግሞ ዋናው ባህሪው ነው:: ናትናኤል ፍቅር አዋቂ የመሆኑን ያህል ቶሎ የሚወድቁለትን እፍቃሪዎቹን ሰብዓዊ አመለካከት የሚነፍግ አይደለም:: እርግጥ አንዳንዴ ዓላማውን ሲያዘናጉት ፀፀት ላይ ይወድቃል:: ሆኖም ሰብዓዊነቱም ቀራጥነቱም አይከዱትም:: መልከ-መልካም ነው የቀይ ዳማ-ረዘም ያለ::

ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ ይህን ያህል የተቸገረበት ጥያቄ! ሊዘለው ያልቻለው ዲብ አላጋጠመውም:: የሰሞኑን ሁኔታ ግን ትርጉም ሊሰጠው ተቸግሯል:: በየአቅጣጫው ከተለያዩ ቢሮዎች የሚመጡ ሪፖርቶች የሚሉት ነገር ቢኖር 'የዚህ አገር ኤምባሲ ወታደራዊ አታሼ ወደ አገሩ ተጠርቶ ሄዷል' ... 'የዚያኛው አገር ወታደራዊ አታሼ ወደ አገሩ ተጠርቶ ከሄደ በኋላ በምትኩ እገሌ የሚባል ሰው ተተክቷል..' አለቃው

በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠው ቀይ የውስጥ ስልክ ሲጮኸ ከሄደበት የሃሳብ ጉዞ ተመለሰ::

"ይፈልጉሃል::" አለችው ፀሃፊው::

"ይፈልጉሃል" -እሳቸው- አለቃው - ቦርጫሙ አለቃው:: ከጠረጴዛው ላይ ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን ይዞ ከቢሮው ወጣ::

"ኖር! ኖር!" ከተቀመጡበት ለመነሳት ሳይሞክሩ በትሁትና ተቀበሉት::

"እንደምን አደሩ::" አለ በአክብሮት::

ከአፋቸው ላይ የማይለየው የፒፖቸው ጠረን ክፍሉን አጨናንቆታል:: ለምን እንደሆነ ባይገባውም ናትናኤል ቆዳ ቆዳ የሚለውን ትንባሆ ጠረን ይወደዋል:: ቢሮአቸው እለትጥ ሰፊ ነው:: ከጀርባ በስተቀኝ በኩል ያሉት ሰፋፊ መስኮቶች የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንን ውብ ህንፃ በሩቅ



ያሳያሉ:: በስተግራ ከግርግዳው ጋር ሲስተካከል ጥቂት ያቀረው ሰፊ የአፍሪካ ፖለቲካዊ ካርታ ተዘርግቷል:: በስተቀኝ የቢሮ ውስጥ ስብሰባ ማካሄጃ ጥቁር ጠረጴዛና በዙሪያውም አስራ ሁለት ወንበሮች አሉ:: በሰፊው ክፍል ከጥግ እስከ ጥግ የተንጣለለው ቀይ ወፍራም ምንጣፍ የአለቅየውን ቢሮ ቁጡ አስመስሎታል::

"ቁጭ በል! ቁጭ በል!" አሉ ወፋፍራም ጣቶቻቸውን ከጠረጴዛቸው ፊት ለፊት ወደ አንደኛው ጥቁር የቆዳ ሮቱ ዘርግተው::

ተቀመጠ::

"ትናንት የሞሪቴንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመከላከለኛውን ምሥራቅ በተለይ የአረቦችን እንቅስቃሴ በተመለከተ የቀሰጠውን የሬድዮ ቃለ ምልልስ ሪፖርት አየኸው?" አለቃው በቀጥታ ወደ ቁም ነገሩ ገቡ::

ሰውየው ሃይለኛ አንባቢ ናቸው:: ያነባሉ ሳይሆን ያጋብሳሉ ማለት ይቀላል:: በአፍሪካ ትራንኮር የተፈጸመው ሁሉ እሳቸው ትላንት ማታ ያነበቡት ነው::

"እ... እ... አላየሁትም::" አለ ናትናኤል እንደማፈር ብሎ::

"አንብበው! አንብበው!... እጅግ አስገራሚ ነው... 'ሰሜን አፍሪካ - አረባዊት ወይስ አፍሪካዊት? በሚለው ሃሳብ ላይ በሳል አስተያየት ሰንዝሯል ሰውየው:: ትዝ ይልሃል...ከጥቂት ዓመታት በፊት በሞሪቴንያና በሴኔጋል መሃል ተፈጥሮ በነበረው መቃቃር 'የአረቦችና የአፍሪካውያን ቅራኔ ናሙና ነበር ወይ?' በሚለው ጥያቄ ላይ አስገራሚ ሃሳብ አለው... አንብበው..." አሉ ከጠረጴዛቸው ላይ የተለያዩ ወረቀቶች እያነሱ እየጣሉ:: "... በአፍሪካ ጎዳ እያንዛረጠ ፤ የአረቦችን ቀዝቃዛ ውሃ እየተጎነጨ ባዳ ነን ለሚሉ አስሉዮች ጥሩ መልዕክት ይዟል:: አሁን እንኳን የፈለግሁህ ለዚህ ሳይሆን ሰሞኑን በተደጋጋሚ ስለሚመጡ ሪፖርቶች ጉዳይ ነበር::" አለቃው የፈለጉትን ወረቀት ያጡ ይመስል ጠረጴዛቸው ላይ የተከመረውን ሰነድ ያምሱት ጀመር::

ናትናኤል ለምን ወደ ቢሮአቸው እንዳስጠሩት ገባው:: ስለወታደራዊ አታሼዎቹ ጉዳይ መሆን አለበት፣ሰሞኑን በተደጋጋሚ የሚመጡ ሪፖርቶች የሚጠቁሙት ያንን ብቻ ነው:: ቢሆንም እርሳቸው ራሳቸው እስኪነግሩት በትዕግሥት ተጠባበቃቸው::

"እ...ም" አሉ ፈልገው ያገኙትን ወረቀት ከፊታቸው ራቅ አድርገው ይዘው የማንበቢያ መነጽራቸውን በወፍራም አፍንጫቸው ላይ እያስተካከሉ:: "...ነገሩን እንኳን አንተም ሳትታዘበው እንዳልቀረህ እርግጠኛ ነኝ" አሉ ቀና ብለው እየተመለከቱት:: "ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ በአፍሪካ ኤምባሲዎች

ናትናኤል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመድቦ ሲሰራ ስምንት ዓመት ሆኖታል። በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን እንደያዘ የተመደበው አሁን በሚገኝበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአፍሪካ ጉዳይ በተለይ በምዕራብ አፍሪካ ክፍል ነበር። ለአራት ዓመታት ካገለገለ በኋላ ወደሰሜን አፍሪካ እንዲዛወር ተደረገ። ካለፈው ዓመት ጀምሮ ደግሞ የአእምሮውን ፈጣንነት የተገነዘቡ አለቆቹ የአፍሪካ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ አድርገው ባይሾሙትም ቢሮውንና ጠረጴዛውን ጭምር እየጋለቡት ነው።

አእምሮው እውነትም ፈጣን ነው። አዳዲስ ሁኔታዎች ቶሎ ይገቡታል። አንዳንዴም የተቸከል ባህርይው እልህ ውስጥ የሚያስገባውም ቢሆን የነገሮችን ሂደት ከአጀማመራቸው የመከታተል ትዕግሥቱ ያመዝናል። አስተሳሰቡ ቀናና ቀጥተኛ ነው። ጠማማ መስመሮች ካጋጠሙት በጠማማ መስመር መሄድም አያቅተውም። ልብ ብሎ የተከታተለውን ጉዳይ እዳር ሳያደርስ ሁላማዊ እንቅልፍ የማያገኝ መሆኑ ደግሞ ዋናው ባህሪው ነው። ናትናኤል ፍቅር አዋቂ መሆኑን ያሁሉ ቶሎ የሚወድቁለትን አፍቃሪዎቹን ሰብዓዊ አመለካከት የሚነፍግ አይደለም። እርግጥ አንዳንዴ ዓላማውን ሲያዘናጉት ፀፀት ላይ ይወድቃል። ሆኖም ሰብዓዊነቱም ቀራጥነቱም አይክዱትም። መልከ-መልካም ነው፣ የቀይ ዳማ-ረዘም ያለ።

ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ ይህን ያህል የተቸገረበት ጥያቄ! ሊዘለው ያልቻለው ዲብ አላጋጠመውም። ያለውን ሁኔታ ግን ትርጉም ሊሰጠው ተቸግሯል። በየእትጣጫው ከተለያዩ ቢሮዎች የሚመጡ ሪፖርቶች የሚሉት ነገር ቢኖር 'የዚህ አገር ኤምባሲ ወታደራዊ አታሼ ወደ አገሩ ተጠርቶ ሄዷል' ... 'የዚያኛው አገር ወታደራዊ አታሼ ወደ አገሩ ተጠርቶ ከሄደ በኋላ በምትኩ እገሌ የሚባል ሰው ተተክቷል..' እለቀው።

በጠረጴዛው ላይ የተቀመጠው ቀይ የውስጥ ስልክ ሲጮኽ ከሄደበት የሃሳብ ጉዞ ተመለሰ።

"ይፈልጉሃል።" አለችው ፀሃፊው።

"ይፈልጉሃል" -አሳቸው- አለቃው - ቦርጫሙ አለቃው። ከጠረጴዛው ላይ ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን ይዞ ከቢሮው ወጣ።

"ኖር! ኖር!" ከተቀመጡበት ለመነሳት ሳይሞክሩ ተቀበሉት።

"እንደምን አደሩ።" አለ በአክብሮት።

ከአፋቸው ላይ የማይለየው የፒፖቸው ጠረን ክፍሉን አጨናንቆታል። ለምን እንደሆነ ባይገባውም ናትናኤል ቆዳ ቆዳ የሚለውን ትንባሆ ጠረን ይወደዋል። ቢሮአቸው አለቅጥ ሰፊ ነው። ከጀርባ በስተቀኝ በኩል ያሉት ሰፋፊ መስኮቶች የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንን ውብ ህንፃ በሩቅ



ያሳያሉ። በስተግራ ከግርግዳው ጋር ሲስተካከል ጥቂት ያቀረው ሰፊ የአፍሪካ ፖለቲካዊ ካርታ ተዘርግቷል። በስተቀኝ የቢሮ ውስጥ ስብሰባ ማካሄጃ ጥቁር ጠረጴዛና በዙሪያውም አስራ ሁለት ወንበሮች አሉ። በሰፊው ክፍል ከጥግ እስከ ጥግ የተንጣለለው ቀይ ወፍራም ምንጣፍ የአለቅየውን ቢሮ ቁጡ አስመስሎታል።

"ቁጭ በል! ቁጭ በል!" አሉ ወፋፍራም ጣቶቻቸውን ከጠረጴዛቸው ፊት ለፊት ወደ አንደኛው ጥቁር የቆዳ ፎቴ ዘርግተው።

ተቀመጠ።

"ትናንት የሞሪቴንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመከላከለኛውን ምሥራቅ በተለይ የአረቦችን እንቅስቃሴ በተመለከተ የተሰጠውን የሬድዮ ቃለ ምልልስ ሪፖርት አየኸው?" አለቃው በቀጥታ ወደ ቁም ነገሩ ገቡ።

ሰውየው ሃይለኛ አንባቢ ናቸው። ያነባሉ ሳይሆን ያጋብሳሉ ማለት ይቀላል። በአፍሪካ ጉራንጉር የተፈጸመው ሁሉ እሳቸው ትላንት ማታ ያነበቡት ነው።

"እ... እ... አላየሁትም።" አለ ናትናኤል እንደማፈር ብሎ።

"[illegible]ንብበው! አንብበው!... እጅግ አስገራሚ ነው... 'ሰሜን አፍሪካ - አረባዊት [illegible] አፍሪካዊት? በሚለው ሃሳብ ላይ በሳል አስተያየት ሰንዝሯል ሰውየው። [illegible] ይልሃል...ከጥቂት ዓመታት በፊት በሞሪቴንያና በሴኔጋል መሃል ተፈ[illegible] በነበረው መቃቃር 'የአረቦችና የአፍሪካውያን ቅራኔ ናሙና ነበር ወይ?' [illegible] ጥያቄ ላይ አስገራሚ ሃሳብ አለው... አንብበው..." አሉ ከጠረጴዛቸው [illegible]የተለያዩ ወረቀቶች እያነሱ እየጣሉ። "... በአፍሪካ ጓዳ እያንዛረጠ ፣ የ[illegible]ን ቀዝቃዛ ውሃ እየተጉነጩ ባዳ ነን ለሚሉ እስስቶች ጥሩ መልዕክት [illegible]። አሁን እንኳን የፈለግሁህ ለዚህ ሳይሆን ሰሞኑን በተደጋጋሚ ስለሚ[illegible] ሪፖርቶች ጉዳይ ነበር።" አለቃው የፈለጉትን ወረቀት ያጡ ይ[illegible] ጠረጴዛቸው ላይ የተከመረውን ሰነድ ያምሱት ጀመር።

ናትናኤል ለምን ወደ ቢሮአቸው እንዳስጠሩት ገባው። ስለወታደራዊ አታሼዎቹ ጉዳይ መሆን አለበት ብሎ ገመተ። በተደጋጋሚ የሚመጡ ሪፖርቶች የሚሉት ያንን ብቻ ነው። ቢሆንም እርሳቸው ራሳቸው እስኪነግሩት በትዕግሥት ተጠባበቃቸው።

"እ...ም" አሉ ፈልገው ያገኙትን ወረቀት ከፊታቸው ራቅ አድርገው ይዘው የማንበቢያ መነጽራቸውን በወፍራም አፍንጫቸው ላይ እያስተካከሉ። "...ነገሩን እንኳን አንተም ሳትታዘበው እንዳልቀረህ እርግጠኛ ነኝ" አሉ ቀና ብለው እየተመለከቱት። "ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ በአፍሪካ ኤምባሲዎች

የሚሰሩ ሰላሳ ስድስት ወታደራዊ አታሼዎች ወደ አገራቸው ተጠርተው ሄደዋል::"

"ሰላሳ ስምንት" አለ ናትናኤል ከተቀመጠበት ወንበር ላይ እየተመቻቸ:: "ከቀድሞዎቹ በተጨማሪ ትናንት የአልጀሪያና የሞዛምቢክ ወታደራዊ አታሼዎች ተጠርተው ወደየአገሮቻቸው ሄደዋል::"

"በጣም ግሩም" አለቃው ፈገግ አሉ:: ይህ ነው የሚያረካቸው:: ፈጣንነቱ፤ ቀልጣፋነቱ፤ የሚያስቡትን ቀድሞ አስቦ መገኘቱ:: "ጉዳዩን ተከታትለኸዋል ማለት ነው::"አሉ የያዙትን ወረቀት ወደ ጎን እያስቀመጡ::

"አዎ" አለ ናትናኤል እየመነቃቃ:: እርግጥ ሪፖርቶቹን በሙሉ በጥንቃቄ ተመልክቷቸዋል:: ሆኖም ለሁኔታው ትርጉም ሊያገኝለት አልቻለም::

"እንግዳ አልሆነብህም?" [illegible]ፓቸውን አንስተው ከውስጥ ያለውን አመድ በነሃሱ የሲጋራ መተርከሻ[illegible] ውስጥ እያራገፉ ጠየቁት::

"እርግጥ..." ናትናኤል ግራ ተጋባ:: "ሁኔታው ለማንም ቢሆን እንግዳ ነው:: ግን..."

"አዎ እንግዳ ነው" አሉ አለቃየው ሃሳቡን የተረዱ ይመስል ሽበት የተንጠባጠበበትን ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ:: "ከአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ጋር የተገናኘ ምክንያት ይኖረዋል ትላለህ?" ፒፓቸውን እየጠቀጠቁ ጠየቁት::

"እ?" ጭንቅላቱን በፍጥነት ለማሰራት ሞከረ::

"አዎ አስቸጋሪ ነው ለመናገር" ፒፓቸውን አፋቸው ውስጥ ሻጥ አደረጉና የጫሩትን ክብሪት አስጠግተው ማግ... ቡልቅ...ማግ... ቡልቅ.... እያደረጉ አያይዘው ሲያበቁ የያዙትን እሳት ሳያጠፉ ክብሪቱን በጥንቃቄ በመተርከሻው ውስጥ አስቀመጡና "ናትናኤል እስቲ አንድ መላምት ላይ ለመድረስ ሞክር::" ነበር ያሉት የአለቃ ሳይሆን የባልደረባነት ቃና ባለው ድምፅ::

"አንተ ብሽቅ! አንትኔን በኮልጌት አጨማለቅኸው አይደል... እናቴ ትሙት ብድሬን ባልመልስ! ለመሆኑ ከማን ጋር ነው ቀጠሮህ?" አለች ርብቃ እየሳቀች ከመታጠቢያ ቤት ወደ መኝታ ክፍሉ እየገባች::



"እኔም" ራሴ እርግጠኛ አይደለሁም ርብቃ" አለ ናትናኤል:: "እውነቱን ለመናገር ቀጠሮ ማለቱ አዚያው በየቢሮአቸው እየሄድኩ የማነጋግራቸው ሰዎች ናቸው::" አላት::

"ይሻላል! ማን በእሁድ ቢሮው ይገባልሃል? የማይመስል ነገር ለእንትንህ አትንገር::" አለች ሌሊቱን በርቶ ያደረውን የራስጌ መብራት እያጠፋች::

"ሙች እውነቴን ነው::"

"ተው እንጂ ናቲ... እንድምትታመን ሁን::"

"ይልቅ አሁን እሱን ተይውና..." አለ ናትናኤል ክርክሩ እንደማያዋጣው ሲረዳ ቁጢጥ ብሎ የጫማውን ክር ከሚያስርበት ተነስቶ [illegible]ና ጉንጯን በሁለት እጆቹ ይዞ እያባበላት:: "ማታ እንገናኛና..."

"አ! አ! አ!" አቋረጠችው:: "ስንት ጊዜ ልንገርህ እሁድ ሌሊትን ማሳለፍ [illegible]ፈልገው ተኝቼ ነው:: ሰኞ ጠዋት ስራ ገቢ ነኝ:: ገባህ? ካንተ ጋር [illegible] ማደር አልችልም::"

"[illegible]:: እራት አጋብዝሽና ቤት አደርስሻለሁ::"

"[illegible]" ተንጠራርታ ቅንድቡን ሳመችው::

ወ[illegible] ማዘጋጃው ክፍል ገባ ብሎ ከማቀዝቀዣው ውስጥ በጠርሙስ [illegible] አጠጣና በቁሙ ወደ ሆዱ ደፋው - ቁርስ:: የአፓርትመንቱ[illegible]መዝግዛ ደረጃዎች በሩጫ ወረዳቸው:: ወደ ውጭ የሚያስወጣውን [illegible]ታወት በር ገፋ አድርጎ ሲወጣ ቁና ቁና እየተነፈሰ ነበር:: የውጭው [illegible] ሰውነቱን አቀራመደው:: የመኪናውን በር ከፍቶ ከመግባቱ በፊት [illegible] ተመለከተ:: የመኝታ ቤቱን መጋረጃ ወደጎን ሰብሰብ አድርጋ ቁል[illegible]ትመለከተዋለች::

[illegible]ጁን አወዛ[illegible]ለት:: ጠጋ ብላ ከንፈሮቿን ቀዝቃዛው መስታወት ላይ አጣበቀቻቸው! ሳመቻቸው - በስሜት:: ከራሱ ጋር እየተከራከረ የመኪናውን በር ከፍቶ ገባ::

"ግን ለምን?"

መኪናውን አስነስቶ ከአፓርትመንቱ ግቢ ወጣ:: ከጎኑ ተሰባጥረው ከተደረደሩት የሙዚቃ ክሮች አንዱን አነሳና ማዘፈኛው ውስጥ ከተተው:: ለስላሳ ሙዚቃ:: ወደ ቀኝ ታጥፎ ወደላይኛው ቤተመንግሥት አቀና::

ግን ለምንድነው ስሜቱን የሚደብቃት? መውደድን እምኖ መቀበል ደካማነት ነው እንዴ? ከአንቺ ስለይ አእምሮዬ ይረበሽ ጀምሯል፤ ካንቺ ተለይቼ ሳድር በስጭትጭት ያደርገኝ ጀምሯል ብሎ ተሸናፊነትን መግለጽ ደካማነት ነው እንዴ? ለምንድነው ዛሬም እንደድሮው ቀዝቃዛና ግድ የለሽ መስሎ ለመቅረብ የሚጥረው? ወደዳም ጠላ የድሮው አይደለም:: ርብቃን ካገኘ ወዲህ ከቀን ወደ ቀን የገዛ ራሱን ለውጥ ተገንዝቦታል:: ታዲያ ተሸነፍኩልሽ ወደድኩሽ ብሎ ማለቱ ምኑ ላይ ነው ስህተቱ? የመኪናውን ቤንዚን መስጫ አጎነው::

በመናፈሻው ውስጥ ተሰጥረው በተተከሉት ዛፎች መሃል ገባ:: ሽሽግ ብላ ቆማ የነበረች ጥቁር 504 ፔጆ በእርጋታ ተነስታ በርቀት ከጀርባው ስትከተለው አላስተዋለም::

-3-

ለምን እንደምትወደው ገጹም አይገባትም::እርግጥ መውደድ ያውቃል፤ ከዛ ውጪ ግን በሰዎች ልብ ጓዳ ውስጥ የሚፈላና የሚገነፍል የሚንተከተክ ትኩስ ስሜት እንደሌለው ከተረዳች ቆይታለች:: ግን ትወደዋለች::

"ብሽቅ!"

ወደጎን ሰብሰባ የያዘችውን የመኝታ ቤቱን መጋረጃ ለቅቃ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ገባች:: በአራት ማዕዘን ቆርቆሮ ውስጥ ከተቀመጠው የቡና ዱቄት ሁለት ማንኪያ ቀንሳ ጀበና ውስጥ ከጨመረች በኋላ በላዩ ላይ አንድ ብርጭቆ ውሃ ከለሰችበትና ምድጃው ላይ ጣደችው:: ውሃ እስኪፈላ ማን ይጠብቃል... እብረው ይንተከተክ ዳቦ በስሱ መቁረጥ ጀመረች::

ቁርስ ትወዳለች:: በተለይ ከዚያ አውሬ ጋር ያደረች ሌሊት ደንደን ያለ ቁርስ ከጥቁር ቡና ጋር አለበለዚያ ከሁለት የአስፕሮ እንክብል ጋር እጅግ አስፈላጊ ነው:: አለበለዚያ ራስ ምታቱም አይቻል:: ሰውነት ሲነሳ ያደረ ገላም ይጎሳቆላል:: የገበታ ቅቤ የያዘውን ማቅረቢያ ከማቀዝቀገርው ውስጥ አውጥታ ትሪ ላይ አስቀመጠችውና ቡናው ደጋግሞ በኀ እስኪል ታግሳ፤ ከምድጃው ላይ አውጥታ ወደ መኝታ ቤት ተመለሰች:: አልጋው ውስጥ ገብታ፤ ትራሱን ከጀርባዋ አደላድላ ትሪውን በጭንና በጭኗ መሃል አስቀመጠችና የቆረጠችውን ዳቦ ቅቤ ትቀባ ጀመር::

ቁርስ ሳይበላ አንድ ብርጭቆ ወተት ብቻ ጠጥቶ እስከ ምሳ ሰዓት ሲቆይ ድንቅ ይላታል፤ ናቲ:: እሷ ብትሆን ፍርክስክስ ብላ ከመሬት በተቀለ ለች:: ነገረ ስራውና መላ አፈጣጠሩ ሁሉ ግራ ግብት ነው የሚላት:: ይሄን



ያህል ጊዜ አብራው ስትቆይ አሁንም ቢሆን 'ናትናኤልን አውቀዋለሁ::' ብላ ለመናገር ትፈራለች:: ግን ትወደዋለች:: ለምን እንደሆነ ባይገባትም ሳታስበው፤ ሳትጠብቀው ከልቧ ወዳዋለች፤ ጭራው የማይያዝ፤ የማይጠመድ፤ ከእጅ የማይገባ ጋማውን እያመሰ የሚፈነጭ የዱር ፈረስ ነው የሆነባት:: ይህን እያወቀች የመጨረሻ ውሳኔዋ ላይ መድረሷ እብደት መሰላት:: 'ገደል ግቢ' ብሎ ቢተዋትስ? "እፍ...ፍ" በረጅሙ ተነፈሰች::

በወፍራሙ ቅቤ የቀባቸውን ዳቦ ያለርህራሄ ግምጥ አደረገችና ከትኩስ ወፍራም ቡና በረጅሙ ፉት አለችበት:: ነፍሷ መለስ አለች::

ከናትናኤል ጋር እንዴት እንደተገናኘች ስታስታውስ፤ ግንኙነታቸው ሲጀመር የነበራት ዓላማና የአሁኑን ስሜቷን ስታስብ ድንቅ ይላታል:: ልታጠምደው ተዘጋጅታ ቀርባ እሷ ራሷ እንዴት ልትጠመድ እንደቻለች ጭራሽ አይገባትም:: ያደረገችውን ሁሉ 'የግል ጉዳይ ነው' እያለች ራሷን ለማሳመን ብትታገልም ህሊናዋ ሊያርፍ አልቻለም::ቀድማ የዘረጋችውን መረብ ሳትሰበስብ ሌላ መረብ መጣሏ ለራሷም አስፈርቷታል::

ሶስና ባዘጋጀችው የልደት በዓሏ ላይ ነበር ከናትናኤል ጋር የተዋወቀችው እርፍዶ ነበር የመጣው:: ወደ ውስጥ እንደገባ በግራው ያንጠለጠለውን በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ እቃ ለሶስና አቀብሎ ግራ ጉንጯን ሳም አድርጎትና ተያይዘው ወደ ውስጥ ዘለቁ:: ዓይኗ የገባውና ለይታ ያወቀችው ግን ከበር ነበር:: መረቧን ጣለች:: ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ነው - እንደነገሩ ለቀቅ ስልክክ ያለ ፊቱ ቅንድቦቹና ሽፋሽፍቶቹ እንደጎርፍ በአገጩ ያለ ፏ ብሎ ግጥም ያለው ጥቁር ጺሙ በሩቅ ሳቧት።

"ሶስና እውነቷን ነው..." አሰበች ርብቃ:: "ደስ የሚል ልጅ ላይ ነው የጣላት እግዜሩ... አስደናቂ ፍጡር ቢሆንም ኖሮ ... ገብሬልዬ!"

ሶስና ግራ እጁን ይዛ እየጎተተች ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል መሃል ወሰደችው:: በክፍሉ ውስጥ የሚተራመሰው እንግዳ አይተያይም፤ ሁሉም ቡድን በቡድን ጨዋታውን ያቀልጠዋል:: ናትናኤል ብዙ የሚያውቀው ሰው ያለው አይመስልም:: ቢሆንም የመደናገር ፤ ግራ የመጋባት መልክ አልታየበትም::

ሶስና እጁን ይዛ እየጎተተች ከጓደኞቿ ጋር ስታስተዋውቀው ዞሮ ዞሮ የሚመጣው እሷጋ መሆኑ ታሰባትና ፈገግ አለች ርብቃ::

ኬክ ከተቆረሰ በኋላ ነበር የተዋወቁት::

"ተዋወቃት፡፡ ርብቃ ትባላለች፡፡ ጓደኛዬ ናት፡፡ ርብቃ አብሬው ነው የምሠራው፡፡ ናትናኤል ይባላል፡፡" አለቻት ሶስና አሁንም እጁን እየጎተተች አምጥታው፡፡

"ናትናኤል ግርማ፡፡" አላት እጁን ዘርግቶ፤ አስቂኝ ወሬ እንደሰማ ሁሉ ፈገግ ብሎ፡፡ በትክክል የተደረደሩ የሚያማምሩ ትናንሽ ነጫጭ ጥርሶች አሉት፡፡

"ርብቃ ዮሃንስ፡፡" እጁን ዘረጋችለት፡፡ ጠበቅ አድርጎ ጨበጣት፡፡

ሶስና ድንገት ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብላ "ተጠንቀቂ ታዲያ ዱርዬው ነው" አለቻትና "በሉ ተጫወቱ፡፡" ብላቸው ከሰው መሃል ተደባልቃ ተሰወረች፡፡

"ዱርዬው!" ይህ ነበር የምትፈልገው የሚያጠንቀቂያ ቃል፡፡ ፈገግ አለች ርብቃ፡፡

"ስምሽን ከዚህ በፊት የማውቀው መሰለኝ፡፡" አላት ድንገት፡፡
"እ... በሬድዮ ሰምተኸው ይሆናል... ጋዜጠኛ ነኝ፡፡"
"እ! ... የአፍሪካ ምጣኔ ሀብት የምታዘጋጂው" እጇን ጠበቅ አድርጎ ጨበጠ፡፡

"አዎ፡፡" አለች ፈገግ ብላ በሬድዮ የምታዘጋጀውን የፕሮግራም ስም ያለስህተት በመጥራቱ ኩራ ብላ፡፡

"በጣም ነው የምወደው እሱን ፕሮግራም፡፡"

የሰማችውን ማመን አልቻለችም፡፡ እንዲህ ዓይነት ድፍረት ሲያጋጥማት የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር፡፡ መልስ አልሰጠችውም፡፡ እጇን ከእጁ ውስጥ መንጭቃ ማውጣት ፈለገች፡፡ ነገር ግን ትዝ ብለው የሚያይዋት ዓይኖቹ አልሰበር፤ አፍታ አልሰጥ አሏት፡፡

'ብሽቅ' አለች በልቧ፡፡

"ትዝ ይለኛል... በአንድ ወቅት ዋብዞህን ፓርቲ ስርዓትና የኢኮኖሚ እድገት በአፍሪካ በሚል ርዕስ አንድ ተከታታይ ዝግጅት አቅርበሽ ነበር...መላቅጡ የጠፋው ዝግጅት ነበር፡፡" አላት ናትናኤል፡፡ ርብቃ ንዴቷን ልትቋቋመው አልቻለችም፡፡



"ካልወደድከው ለምን ትከታተለዋለህ ታዲያ?" አለች ደርዝ ባለው ድምፅ፡፡

"ድምፅሽን ስለምወደው ይሆናል..." አለና ድንገት ከት ብሎ ሳቀ፡፡ ወዲያውኮስተር አለና "ስራዬ ከአፍሪካ አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የሚያገናኘኝ ነው፡፡ ስለዚህ ወደድኩትም አልወደድኩትም ፕሮግራምሽ እንዲያመልጠኝ አልፈልግም፡፡ በተለይ እንግዶች ጋብዘሽ ቃለ ምልልስ በምታደርጊበት ወቅት፡፡" አለ ከጎናቸው ካለ ጠረጴዛ ላይ ከተደረደሩት በመጠጥ ከተሞሉት ብርጭቆዎች ሁለቱን አንስቶ አንዱን እያቀበላት፡፡ "የሚሰማኝን በግልፅ በመናገሬ እንዳልተቀየምሽኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡"

"እህእ..." ትከሻዋን ነቅንቃ፡፡ "ግድ የለኝም የፈለከውን ብትቀባጥር ለማለት፡፡"

"የምታዘጋጂያቸው ፕሮግራሞች እንደተረዳሁት በአመዛኙ ለአፍሪካ ማንሠራራት ዋነኛ ተስፋ አድርገሽ የምትወስጂው በአፍሪካ አገሮች መሀል ያለውን [illegible] ነው፡፡ አገሮች በተናጠል ለሚያደርጉት ጥረት ቦታ የሰጠሽው [illegible]ለይም፡፡"

"ት[illegible]ነህ፡፡ እውነቱ መራራ ቢሆንም ልቀበለው ስለደፈርኩ ነው፡፡" አለች ር[illegible] ለዘብ ብላ፡፡

"ምንድነው [illegible]ነቱ?"

"የአፍሪካ አ[illegible] ተስፋ የለሽ መሆናቸው፤ ከገቡበት አዘቅት መቼም ቢሆን ሊወጡ [illegible]መቻላቸው፤ ተስፋ ያላት አንድ አፍሪካ ብቻ መሆኗ ነው እውነቱ፡፡"

"አልገባኝም!" አለ ናትናኤል ቅንድቦቹን አጠጋግቶ፡፡

"ብሥጭሩ በኤሬል አፍ እንደተባለው የአፍሪካ ነፃነት የሚገኘው በተዋሀደ እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡"

"ጨርሽዋ!" አለ ናትናኤል ፈገግ ብሎ "ኤሬል ያለው ያንን ብቻ አይደለም፡፡ ውህደቱ ሊጠናከር የሚችለው በኢኮኖሚያዊ መተባበር የግንኙነት መስመሮችን በማሻሻል በመጨረሻም በፖለቲካ ውህደት ነው... መሠለኝ ያለው ኤሬል፡፡ ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ የአፍሪካ አገር በተናጠል የሚያደርገው ጥረት ዋጋ ሊሠጠው ይገባል፡፡"

"የትኛው ይቅደም መሠለኝ ጥያቄው::" አለች ርብቃ በስሱ የገጠመቻቸውን ከንፈሮቿን እላቃ::

"ከምኑና ከምኑ?" ጠየቃት ናትናኤል::
"ከኢኮኖሚው ትብብርና ከፖለቲካው ውህደት::"

"ይህማ ግልፅ ነው:: የፖለቲካ ውህደት በኢኮኖሚና በሌሎችም ትብብሮች ላይ የሚገነባ ነው:: ስለዚህ ፀው ኢኮኖሚያዊ ትብብር ይቀድማል::"

"እንደ መጽሐፍ ከሆነ ልክ ነህ መሠለኝ:: ኢኮኖሚያዊ ጥንካሬና ትብብር ለፖለቲካ ውህደት እንደ መሠረት መሆኑ አያጠራጥርም:: ጥያቄው ግን መጽሀፍ ላይ የተጻፈው ሳይሆን ሲቀርስ? የፖለቲካ አቋም ልዩነት በራሱ ለኢኮኖሚው ጥንካሬና ለትብብሩም እንቅፋት ሆኖ ሲገኝስ መድሃኒቱ ምን ይሆናል የሚለው ነው:: በአፍሪካ የሚታየው ችግር ይህ ይመስለኛል::" አተኩራ ተመለከተችው:: "መሰለኝ እንጂ::" አለች ናትናኤል ያመነታ ሲመስላት::
"ይገባኛል! ይገባኛል! እርግጥ የፖለቲካ አለመጣጣም..." ናትናኤል እያመነታ ጀመረ::

"እንዴ የአፍሪካ አገር" [illegible]ችው:: "ለውጭ አራዊቶች ቅጥረኛ እየሆነ የጎረቤቶቹን ሰላም ሲያውክ ኢኮኖሚ ሲያደቅስ እልፍ ተርፎ በገዛ አፍሪካውያን ወንድሞቹ ላይ ጦር ሲሰብቅ መድሐኒቱ ምን ይሆናል? የተማሩ የተመራመሩ ቅምጥል የአፍሪካ ልጆች የአፍሪካ ጥቁር አፈር ሲገለማቸውስ? ነጭ አፈር ፍለጋ ሲዘምቱስ? ጋሻ መከታ መኩሪያ መመኪያ መሪዎቻቸውን፤ በአፍሪካ በሀቃ የጠለቁትን ሊጥ በስዊዝ ባንክ ካልጋገርነው ሲሉስ? ፖለቲካ መድሀኒት መሆኑ ቀርቶ የነአብላቢ ጭልፊት፤ የነጎርሶ አይጠግቡ፤ የነውጦ አይጠረቁ ጋሻ ጃግሬ አጋፋሪ ሲሆንስ? መድሀኒቱ ምን ይሆናል? መጽሐፉ እንደሚለው ትብብር ይሆን?" አፈጠጠችበት::

"ይገባኛልካ ችግሮች መኖራቸውማ ያለ ነገር ነው:: ግን..." አለ ናትናኤል::

"በማን ጀርባ ላይ እየተጨፈረ ያለ ነገር ነው? ወንድም ወንድሙን እያስማማ፤ ከነጭ ውል እየተጋባ፤ ወንድም ወንድሙን እየተበቀለ ከባዕድ ውጉ እየተጣባ፤ አፍሪካ የሁሉ ቅምጥ እንደ ባቢሎን ግንቦኞች ሁምሳ ቋንቋ ስታንቀረቅር አሽቃባጮች የባዕድ ሊጋግ እየላሱ ከርዳታው ከዳረጎቱ ሲሻሙ፤ ሲስገበገቡ ነገ በዕዳ ማንቁርታቸው ሲፈጠረቅ፤ ነገ ያጠለቁት ቁምባ ሲበጣጠስ በላሌ ውርደት ሲያጠልቁ፤ ነገ ደንቆሮ ጥቁር ሲባሉ ዛሬ በገዛ ወንድሞቻቸው ላይ ሲያቀጥሩ ነው 'ያለ ነገር ነው' ብለን የምናልፈው?!"



"ርብቃ..." አለ ናትናኤል:: "መቼም አፍሪካዊ ሆኖ የአፍሪካን አንድነት፤ የአፍሪካውያንን ልምላሜና እድገት የማይመኝ ያለ ኖሮ አይመስለኝም:: አፍሪካ ብትበለፅግ፤ አፍሪካ ብትለመልም፤ የእያንዳንዳችን ጓዳ የእያንዳንዳችን ጎተራ ሞላ ማለት ነበረ! ይህኮ የሁላችንም ምኞት ነው::"

"ምንድን ነው ምኞት?" ፊቷን አጠቀረችበት::"ወይስ ምኞት በዘር በሰፈር የተከፋፈለች አፍሪካችንን አንድ ያደርጋት ይሆን? የተራቆተ ገላችንን ይሸፍንልን፤ በረሃብ የተቆዘረ ሆዳችንን ይሞላልን፤ ወይስ የሸተተ የከረፋ ስማችንን ፍቆ እንደገዘንጀር ከመታየት ያድነን ይሆን?!"

"ርብቃ አንጎሌን እየቀጠቀጠሽው ነው::" አለ ናትናኤል ፈገግ ብሎ:: "አፍሪካዊ የሆነ ሁሉ ቁጭት ሳይሰማው ቀርቶ አይምሰልሽ:: ድህነቱ ድንቁርናው፤ ውርደት እስከ አጥንቱ የማይጠዘጥዘው፤ እስከ ድማቱ የማይነዝረው ኖሮ አይምሰልሽ:: ማጡጫው፤ መፍትሄው ጠፍቶት ነው ማዶ ማዶ የሚያየው:: ይህ የእኔ ስሜት ብቻ አይምሰልሽ:: የእያንዳንዱ አፍሪካዊ ስሜት ነው:: ምክንያቱም ድህነት በወረቀት ላይ በሰንጠረዥና በካርታ የሚታይ ሳይሆን በየጓዳችን እሸሩሩ የምንለውና የምናሞላቅቀው ነው:: ምናልባት እኔ ጠግቤ አድር ይሆናል ግን ወንድሜ ወይ እህቴ አለዛም ጎረቤቴ ጾሙን እንደሚያድር አውቃለሁ:: አፍሪካ ውስጥ ነው ያለነው:: በአንድ ጨረቃ ሁላችን ጠፍተን ማደር እንደምንችል አውቃለሁ:: ታዲያ ጠግቤ የምተኛው እንቅልፍ የሰላም ይመስልሻል? ድህነቱን ተሸክሜው ስኖር [illegible]ሻዬ የማይላጥ ህሊናዬ የማይኮላሽ ይመስልሻል? ጠግቤ መብላት እሻለሁ [illegible]ርበኛል ድሀ ነኝ:: ጥሩ መልበስ እፈልጋለሁ፤ አራቆታለሁ መና[illegible]ኛ:: ወንድ ልጄ በስልጣኔ እንዲያድግ እጥራለሁ፤ ይደንቁራል አልታደ[illegible]ም:: ሴት ልጄ በእውቀት እንድታብብ አልማለሁ፤ ትሸረሙጣለች ተረግ[illegible]ቧ:: ይህ ነው እጣዬ፤ አፍሪካዊ ነኝ:: ይሄ አይቆረጥምም ትያለሽ? [illegible]ህ አይጠዘጥዝም ትያለሽ? ይህ አያንገበግብም ትያለሽ? አፍሪካዊ ደን[illegible] ሆኖ ይሆን? ነጮች እንደሚሉት አፍሪካዊ የማይገባው አፍር ጭንቅላት ሆኖ ይሆን? በልቶ መጸዳዳት ይሆን ዕድሉ? ቢከፍቱት የሚሸት እበት ይሆን አንጎሉ? በስባሳ መረቅ መግል ይሆን ሁሞቱ? አይመስለኝም:: አፍሪካ በጊዜዋ የስልጣኔ ጫፍ ነበረችኮ:: የግብፅና የማሊ፤ የጋና የዚምባብዌ፤ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔዎችኮ ተበድረን ያመጣናቸው አምጡ መልሱ ስንባል የመለስናቸው አልነበሩም:: የኛው የራሳችን አፍሪካውያን ነበሩ:: የጥቁር ንጥር ስልጣኔ ነበሩ:: ታዲያ ዛሬ ምን ነካን? እንዲያ ከሆነ እኛም ሰው ነን ማለት ነዋ! ... ዛሬም ብንማር የምናውቅ ብንሰራ የምናድግ ነን ማለት ነዋ! ... ታዲያ ምን ነካን? ምንድነው እንቅፋቱ? ማነው ጠላታችን ርብቃ? አፍሪካውያን ጠላታቸው ማን እንደሆነ አጥተውት ይመስልሻል? እርዳታ እያሉም ሲያሸቀጡብን፤ ሆ! ሻሞ እያሉም ሲያናክሱን፤ እኔ እሻል እኔ እሻል እወደድ ባይ አሽቃባጭ ሲያደርጉን፤ ብድር ብድር እያሉም በዕዳ ሲዘፍቁን፤ዕዳችሁን ውሰዱ እያሉ ሀብታችንን ሲገዙ፤ ወገባችንን ሲያደቁን፤ ዘር እያቋጠሩ ጦር እያስታጠቁ

እርስ በራስ ሲያናቁሩን፤ መልሰው 'ዲሞክራሲ ላይ ቆማችሁ ተጫናችሁት' ሲሉ፤ ሲዘባበቱብን፤ ማንም ጥቃውን ሲሰድፍብን፤ የገበያ ድንጋይ ሲያደርገን የማይቆረቁረኝ ይመስልሻል?"

ናትናኤል ቀጠለ።

"ርብቃ አፍሪካውያን ጠላታቸው ማን እንደሆነ አጥተውት ይመስልሻል? ማርና ወተት ከአንደበታቸው እያንጠባጠቡ፤ በጉቦና በምልጃ ማብሰያ ድስት ጥደው ሲያቁላሉን፤ ነጭ አትያቸው፤ ጥቁር አትያቸው፤ ቡራቡሬ ኬክ ገላ ተንባኬዎች ከእምብርታችን ቆመው ሲበጠቡጡን፤ የባዕድ አትያቸው የኛ! የኛ አትያቸው የባዕድ ፤ ሽለምጥማጥ እስስቶች ከኛው ዘርፈው ነጭ ሲሆኑብን፤ በስልጣን ዙፋቸው፤ በፖለቲካ ልምጫቸው፤ ሲከረክሩን፤ 'ጭ' እያሉ ሲጋልቡን፤ ውስጥ እግራችንን የማያቃጥለን፤ ውስጥ እጃችንን የማይለበልበን ይመስልሻል? መውጫው ስለጠፋብን ነው። ቢያስምጡን፤ ከአንደበታችን ቢደርቅ ዙሪያው ቢጨቀይ ነው ባሻገር ማተኮራችን፤ የቆምንለትን አላማ እያየ እንዳለየ እየሰማ እንዳልሰማ መምሰላችን!"

ለአንድ አፍታ አተኩሮ ተመለከታት። "ማነሽ? ርብቃ ለምን የዚህ አይነት ርዕስ አንስተሽ ሰላም ታደፈርሻለሽ?"

"መድሐኒቱን ንገረኝና ርዕስ እቀይር።" አለች ርብቃ ፈገግ ብላ።

"ለአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ ውድቀት መልስ ቅንጅት ያለው እንቅስቃሴ መሆኑኮ እርግጥ ነው። ግን ይህን ቅንጅት እንዴት ልንፈጥረው እንደምንችል አላውቅም። ይሁን እንጂ ይህን ቅንጅት አንቺ እንደምታስቢው በአንድ ጀንበር መዳፋችን ውስጥ ልናስገባው የምንችለው አይመስለኝም። ጊዜ... ጊዜ እንላለን። ዲሞክራሲና ጊዜ እንፈልጋለን። ይበልጥ መማር፤ ይበልጥ ማወቅ አለብን። አገሮች በተቻላቸው ግንኙነታቸውን ማዳበር አለባቸው። እርግጥ ለዚህ የጋራ መድረክ ያስፈልጋል ፦ ብቻ አይደለም፤ አገሮች ጥቃቅንና ግዙፍ ቅራኔዎቻቸውንም ማቻቻል ይኖርባቸዋል። እንዴት አትበይኝ። አላውቅም። እውነቱን ንገረኝ ካልሽ በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ማውራት አልወድም።ምክንያቱም መልስ የማይገኝላቸው በርካታ ጥያቄዎች ያፋጥጡኛል። ስለዚህ ጉዳዩ እንደማይነካኝ ሁሉ ትከሻዬን ነቅንቄ ማለፉን እመርጣለሁ። እንጂ ብዥ ምን ማድረግ እንዳለብን አላውቅም። ወደ አንቺ የሬዲዮ ፕሮግራም የመጣሁ እንደሆነ ደግሞ አሁንም ተረዳዬቱ ቅንጅት ባለው መልክ መስራት ነው። በኔ በኩል አለፍ አለፍ እያልን እየተገናኘን እንዲህ ብንወያይ መቼም ያቅሜን ከማድረግ አልቆጠብም። ለምሳሌ ነገ ማታ እራት ብጋብዝሽና..." ፈገግ አለ ናትናኤል።

"ሁ..ሁ..ሁ.." ከት ብላ ሳቀችበት። "ኮሚክ ነህ"



እንዳለው በማግስቱም ባይሆን በሳምንቱ ተገናኝተው እራት ጋበዛት። ስለምታዘጋጀው የሬድዮ ፕሮግራም ግን ብዙም አልተወያዩም። ሳይታሰብ ሌሎች በርካታ የመወያያ ነጥቦች ተፈጠሩ - አስቸኳይ ጉዳዮች። ከዚያ ወዲያም ቢሮዋ ድረስ ስልክ እየደወለ ቀጠሮ እየያዘ ግንኙነታቸውን ቀጠሉ። ርብቃ እንዳጠመደችው የተረዳው ወዲያው ነበር። መቼ እንደተጠመደች ግን ጭራሽ አታስታውስም። እርግጥ መጀመሪያ ባየችውም ሰዓት ደስ ብሏታል። ናትናኤል ዓይን የሚገባ ወንድ ነው። ግን ዓላማዋ ሌላ ሆኖ ሳለ አሁን የሚሰማት ጥልቅ ስሜት እንዴትና መቼ ሊፈጠርባት እንደቻለ አይገባትም። እሷ ማመን የማትፈልገውን ያህል እያፈቀረችው መጥታለች። እሱን መውደዷ ከአላማዋ ጋር ሊጋጭ ይችላል የሚል ስጋት ቢያድርባትም እራሷን ለመቆጣጠር አልቻለችም።

የሚጨንቃትና የሚረብሻት ነገር ቢኖር የናትናኤል ግድየለሽነት ነው። እርግጥ አልጋ ውስጥ የሚወዳደረው የለም። ግን ሰው አልጋ ውስጥ አይኖርም። ናትናኤል ደግሞ ከዛ ውጪ የሌላን ፍጡር ወዳጅነትና አርነት የሚሻ ሰው አይመስልም። እንዳልተገራ ፈረስ ያንን አሞሌ ይዞ ስታባብለው ይቀርባታል። ጋማህን ልጨብጥ ስትለው ይደነብራል። ከሱ ጋር መስማማት ብትችል እንኳን እነሱስናን የሚያመነ ጥያቄ ቀላል አይደለም።

ከመጨረሻ ውሳኔዋም የደረሰችው ለዚህ ነው።በየትኛውም አቅጣጫ ተጠያቂ ወይም ተወቃሽ አትሆንም። መቼስ አጋጣሚ ሆኖ ሆነ... ስለዚህም መጋባታቸውም ምርጫ የሌለው መፍትሄ ሆኖ ተገኘ። ስለሆነም ያላትን ብቸኛ ምርጫ ወሰደች። የሁሉንም ወገን እፎ ሊዘጋ ይችላል ብላ ያሰበችውን እርምጃ ነበር የወሰደችው፤ ናትናኤልንም ጨምሮ። አለበለዚያ ሲጋብቻ ያለውን ጥላቻ ስታጤን...

"ርብቃ ከዚህ በፊት የተናገርኩ መሰለኝ። ጋብቻ ጊዜው ያለፈበት ጥንታዊ ልማድ ነው፤ ጎጂ ባህል።" አላት አንድ ቀን እንደቀልድ ለምን እንደማይጋቡ ስትጠይቀው።

"እና እስከመቼ እንዝላዘል ነው የምትለው?" ቆጣ ለማለት ሞከረች።

"የተጋቡ ምን ያደርጉ መሰለሽ? ያው እንደኛው መንዘላዘል ነውኮ።"

"ናትናኤል እኔ ትዳር ይዤ ልጆች ወልጄ መኖር ነው የምፈልገው።"

"ታዲያ ለምን ባል አታገቢም?"

"አንተ ባል መሆን አትችልም? አባት መሆን አትችልም?!"

"ርብቃ እኔ ወደዚች ጨካኝ ዓለም ምንም የማያውቁ ህፃናትን የሚያመጣ ድፍን ልብ የለኝም። ልጅ መውለድ አልፈልግም።"

በመጀመሪያ እንደ ብዙ ወንዶች ነፃነቱን ከመውደድና በትዳር ዓለም የሚገጥመውን ሀላፊነት ከመፍራት የመነጨ ይመስላት ነበር። በኋላ ግን ትዳርን ከልቡ እንደሚጠላ እየተረዳች መጣች። ታማኝ ነው። ለዚህ ደግሞ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነች። ነገር ግን በፊርማና በድግስ ከእርሷ ጋርም ሆነ ከሌላ ሴት ጋር መተሳሰር እንደማይፈቅድ እየተገለጸላት መጣ። ፍቅሯ ፍርሀትና ስጋት እየወለደ የመጣው ከዚያ በኋላ ነው።

ተጨማሪ ጭንቀት የሚፈጥርባት ደግሞ ከናትናኤል ጋር ያገናኛት ምክንያት ነው። "ምን ይሉኛል አነሶስና? ሁሉም የፈለጉትን ይበሉ። ወደድኩት፤ ወደደኝ ተጋባን፤ በቃ።" ብላ ስታስበው ነገሩ ጭንቅ ጥብብ ያደርጋታል።

ርብቃ ከአልጋዋ ላይ ተነስታ ቁርስ የበላችበትን ትሪ ይዛ ወደ ወጥቤት ገባች። ትሪውን ማጠቢያው ላይ አስቀምጣ ወደ መኝታ ቤት ተመለሰች። የቤት ልብሷን ብትቀይር ይሻላል። ተመላላሿ ቤት አጽጂ ሴት ከመጡ ማጽዳታቸውም አይቀርም። አቤት ጥድፊያቸው የቤቱን ወለል ነካ ነካ አድርገው አፀዳሁ ለማለት የተጠሩ ይመስል በተኛችበት እስር ጊዜ የመኝታ ቤቱን በር እየከፈቱ እየገቡ "ቤቱን ላፀዳ ብዬ..." የሚሉት ፈሊጣቸው ታወሳት። "በመጡበት የማይመቸው አብዛኛ" ቶሎ ለባብሳ ብትቀይ ይሻላታል።

አላይዋ ላይ የደረበችውን ሌሊት ልብስ አውልቃ ወደ አልጋው ግርጌ ወርወር አደረገችውና እራቁቷን ወደ ፊት ራመድ ብላ መስታወቱ ፊት ቆመች።

ፍረደኝ!

አንተ እዚህ ጠብቀኝ ደርሼ እመለሳለሁ የሚለው ነገር እድሜዋም አብሯት ይቆሰቁሳል። ዘልዛላ። እያንዳንዷ ሀሳብ ወጥታ በጠለቀች ቁጥር አንድ ቀን እንዳረጀች ይሰማታል። ፊቷን ከሰላሳ ሰላሳኛ አመቷን ልትቀበለው የቀሯት ሁለት ጥቃቅን ዓመታት ብቻ ናቸው። ስታስበው ይዘገንናታል።

እራቁት ገላዋን በመስታወት ውስጥ ተመለከተችው። ያው የድሮው ይመስላል። ጥምጥም ያለ ገላ፤ ቀና፣ ቀጥ ያለ ትከሻ፤ ሽለግ ያለ ሆድ፣ ሞላ ያሉ ጭኖች... ድንገት ጡቶቿን በሁለት እጆቿ ያዝ አደረገቻቸው። ከወትሮው ይልቅ ለስለስ ያሉ መሰላት። ምናልባት መስሏት ይሆናል። ግን ደግሞ ሊሆንም ይችላል። ወሳኙ ጊዜ ነው። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጭራሹን ይሞቀሙቃሉ። የገዛ ሃሳቧ አሸማቀቃት። ጡቶቿን ቶሎ ለቀቅ አደረገችና ቀኝ እጇን ወደታች ሰደደችው። ዙሪያውን ዳበሰችው። ሆዷ ከፊት ባይገፋም ጎንና ጎኗ ደንደን ያለ መሀላት። "እስካሁንም አለማስታወቁ ቁመት ስላለኝ ነው።" ብላ አሰበች።



"ግን ትክክል ውሳኔ ነው ያደረኩት?" ራሷን ጠየቀች። "የራስሽ ጉዳይ፤ እየነገርኩሽ በገዛ እጅሽ የመጣሽው ነው ቢለኝስ?" ፊቷ ቅጭም አለ። "የፈለገውን ያህል ግድየለሽ ይሁን፤ ግን ጨካኝ አይደለም ናቲ። አይጨክንም በፍጹም ብትነግረው ነው የሚሻለው። አውቃ እሱን ለማጥመድ እንዳደረገችው ማወቅ የለበትም። እሷ እራሷ እንደተደናገጠች እንዳዘነች ሆና ነው መቅረብ ያለባት። ከቻለች ማልቀስ። አስወርደው እንደሚላት በፊቱንም አውቃለች። ይህን ያህል ጊዜ ደብቃው የቆየችውም ለዚህ ብላ ነው። ከአሁን በኋላ ግን ምኑን ትደብቀዋለች? ውሎ አድሮ ራሱ እዚህ ነው ያለሁት ማለቱ አይቀር፤ ያበጠው ይፈንዳ! እሺ ብሎ ከተቀበላትም ተመስገን። አንጋባም ልጃችንም ዲቃላ ይሁን ነው..."

"አይልም! በፍጹም አይልም!" አለች ርብቃ ሳይታወቃት ጮሃ።
የመኝታ ቤቱ በር ሲከፈት ደንግጣ ዞረች።
"ሳሊስነ ቅድስት!» ራቁቷን ሲያይዋት ፊታቸውን ወደኋላ መንጭቀው ተመለሱና የበረገዱትን መዝጊያ ዘጉት... ተመላላሽ ቤት አጽጂዋ።

-3-

ሁለቱ ቦታዎች ለመሄድ አቅዷል። ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያና በመረጃው መሰረት ቤት ውስጥ በሀረ ከለላ ክፍል ባልደረባ የሆነው ጓደኛው አብርሃም ጋ። ትናንት ደውሎ ሲያናግረው አብርሃም እያቅማማ ነበር ቀጠሮውን የተቀበለው።

"ግን እንደዚህ ብዙ ሃሳብ ልሰጥህ የምችል አይመስለኝም።" ብሎት ነበር አብርሃም ስለ ሊቤርያዊው አታሼ አንስቶ ናትናኤል ጫፍ ጫፉን ሲነካካለት።

"ቆይ! ቆይ! አብርሃም ለማንኛውም እንገናኝና የምታውቀው ነገር ካለ ታካፍለኛለህ። ያም ባይሆን ችግር የለም። እ! በነገራችን ላይ ለምን ምሳ አልጋብዝህም?"

"ግን አንተ ለምንድነው በነገሩ የተሳበከው? አንድ የውጭ ዜጋ ጠፋና የውጭ ጉዳይ ምን አገባው?"

"እንዴት? ምን ማለትህ ነው? ያገባዋል እንጂ። ሰውየው እኮ የውጭ ዜጋ ነው - በዛም ላይ ዲፕሎማት።"

"ገባኝ! ገባኝ። ነገሩማ በቀጥታ ነው የሚነካችሁ። ቢሆንም ሁኔታውን ፖሊስ እየተከታተለው ሳይሆን አይቀርም። የእኛ መሥሪያ

ቤትም ቢሆን መቼም እጁን አጣጥፎ አይቀመጥም:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ አይዘናጉም ለማለት ነው:: ስለዚህ ችግሩን ለምን ለባለቤቶቹ አትተወውም? ናትናኤል:: ለማለት የፈለግሁት አንተ የውጭ ጉዳይ ባልደረባ እንጂ ወንጀል መርማሪ መኮንን አይደለህም ነው:: ተግባባን?"

"አብርሃም እኔ በሰውየው ላይ የተለየ አትኩሮት ኖሮኝ አይደለም:: ጉዳዩ በተዘዋዋሪ ከምሠራው ሥራ ጋር ዝምድና አለው ብዬ በማሰብ ብቻ ነው:: እንዴት አድርጌ ላስረዳህ...አየህ ብንገናኝ እኮ..."

"ጥሩ! ጥሩ!" አለ አብርሃም ተቆጥቶ በመቁረጥ:: "ስማንኛውም ተገናኝተን እንነጋገራለን::"

"በስንት ሰዓት? የት?" ጠየቀ ናትናኤል::
"እሁድ አይደል ነገ? ሙሉ ቀን ነጻ ነኝ::"
"ደግ... በስድስት ተኩል ላይ ኢትዮጵያ ሆቴል!"

"አ! አ!" ድንገት አብርሃም ቀዝቀዝ አለ:: "ናትናኤል አንዳችን ቤት ብንገናኝ የተሻለ ይመስለኛል:: ባይሆን ከዚያ በኋላ የት እንደምንሄድ እንወስናለን::"

"ግሩም... መጀመሪያ ለዚህ ጉዳይ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ ሊሰጡኝ የሚችሉትን ሃሳብ እሰበስባለሁ ብያለሁ:: ከዚያ በኋላ እንደጨረስኩ አራት ወይም አምስት ላይ አንተ ቤት መጥቼ አብረን እንወጣለን::"

"ጥሩ እጠብቅሃለሁ::" የአብርሃም አነጋገር የመስማማት ሳይሆን የመሸነፍ ስሜትን የተላበሰ ነበር።

ናትናኤል ከአብርሃም ጋር ከመገናኘቱ በፊት ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ሊሰጡት ፈቃደኛ የሚሆኑትን ማናቸውንም መረጃ ለመሰብሰብ ወስኗል:: የገባ ያገለግላል::

ወደ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ወደሚያስገባው ጠባብ አስፋልት መንገድ እጥፍ ሲል ከኋላው በተመሳሳይ ፍጥነት ትከተለው የነበረችው ጥቁር 504 ፔጆም ታጠፈች:: ከውስጥ ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል:: መሪውን የያዘው ሰው ኢትዮጵያዊ አለመሆኑ መልኩን በማየት በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል:: ከሰሃራ በታች ከሚገኙት ጥቁር አፍሪካ አገሮች ከአንደኛው የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው:: መልኩ ብጣም ጠቆር ያለ፤ አፍንጫው ደፍጣጣና ወፋፍራም ከናፍር አሉት:: የደረበውን ፀጉራም ካፖርት አንገትዬ ወደ ላይ ቀልብሶታል::አይኖቹ ክፉኛ ደፍርሰዋል:: ሌሊቱን በቂ እንቅልፍ ያገኘ አይመስልም:: ሆኖም ቅልጥፍናና እርጋታ በተሞላው



እንቅስቃሴ ከፊት ለፊቱ የምትሄደውን ብርማ 131 ፊያት ይከታተላታል:: መሪ የያዘበት እጁ ከመሪው ጋር ወደ ግራ ሲንቀሳቀስ ጥቁር አረንጓዴ ንቅሳት ከእጁ አንጓው በላይ ብቅ አለ፤ የቀንዳም በሬ ምስል:: መኪናዋ ወደ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታጠፈች።

አጠገቡ የተቀመጠው ሰው ኢትዮጵያዊ ገጽታ ያለው ነው:: ጠየም ያለና ረዘም ብሎ ቀጠን፤ መጠጥ ያለ ሰውነት ያለው:: ግራ ጉንጩ ከላይ ከጎድኑ ሥር ጀምሮ ስከታች ከንፈሩ ጫፍ የሚደርስ አስፈሪ ጠባሳ ተጋድሞበታል:: ትናንሽ ዓይኖቹ ባሉበት ጉድጓድ ውስጥ ሆነው ትክ ብለው ሲመለከቱ ከወዲያ ወዲህ ውር ውር ሲሉ ፊቱን የጨካኝ ገጽታ ያላብሱታል::

"እዚሁ ልቁም ወይስ ልለፈው ኮሎኔል?" አለ መሪ የያዘው ሰው በፈረንሳይኛ::

"እልፈኸው ቁም!" አለ ከጎኑ የተቀመጠው ሰው በፈረንሳይኛ ቋንቋ- ይከታተሏት የነበረችው 131 ፊያት ፊት ለፊት ካለው የፖሊስ ጣቢያ ደጃፍ ስትቆም ሲያዩ ፊቱ ላይ የተጋደመውን ጠባሳ ፈተግ አድርጎ:: መኪናዋ እንደቆመች ከጎን ተቀምጦ የነበረው ሰው በሩን ከፍቶ ወረደ።

መሪውን የያዘው ሰው ከተቀመጠበት ወንበር ሥር የተነጠመውን መገናኛ ሬዲዮ ተጫነው::

"ሌ ገሮሌ...! ሌ ገሮሌ....! ቀንጆዎቹ....! ቀንጆዎቹ....!" በፈረንሳይኛ መልዕክት ያስተላልፍ ጀመር።

የስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ሕንፃ ጥንታዊ መልክ ያለው ነው:: ሰዓቱ ቢረፋፍድም የጠዋቱ ቅዝቃዜ ቦታውን ጭል ጭል ለምትለው ለጋ ፀሐይ ሳለመልቀቅ የቆረጠ ይመስላል:: ናትናኤል ወደ ግቢው የሚያስገባውን መዝጊያ አልፎ ወደ ውስጥ ዘለቀ::

"ምንድነው?" አለችው አንድ ወጣት ሴት ዳሌዋን እየነቀነቀች እየተጠጋችው::

ናትናኤል ዞር ብሎ ተመለከታት:: ጥፋት አጥፍታ ጣቢያ ያደረች መሆን አለባት ብሎ አሰበ::

"ሴሽ ይዘሃል? ይቅርታ ሃርድ ሲሰጡኝ ነው ያደሩት::" አለችው አንገቷን ወደ ጣቢያው መታ አድርጋ:: ፀጉሯ ግማሽ ጥቁር፣ ሌላው ቀይ የቀረው ብርማ ተቀብቷል:: ከአይኗ በላይ በተላጩትው ቅንድቧ ምትክ፣ በቀጭኑ የተሰመረው እርሳስ ክፉኛ ደብዝዞ ያለ ቅንድብ የተፈጠረች አስመስሏታል:: ከገላዋ የሚነሳው ጠረን የምን እንደሆነ ለመረዳት ናትናኤል

ተቸረገ:: አለቅጥ ተጠግታው ስለቆመች በተቻለው ብዙ አየር ላለመሳብ ጣረ::

"ይቅርታ በጠዋት ነጀስኩህ አይደል? ሴሽ ይዘሃል?" እጇን ወደፊት ዘርግታ ፈገግ ስትል የሚታዩት ጥርሶቿ ንጫጭ ናቸው::

"ምን?" አለ የምትለው አልገባ ሲለው::

"እ ...ማለቴ ሲጋራ አለህ?...." ጡቶቿን ወደፊት ገፋ ዳሌዋን ነቅነቅ አደረገችለት ይበልጥ ጠጋ ብላው::

ናትናኤል ከደረት ኪሱ ውስጥ ሲጋራ ሲያወጣ ተሽቀዳድማ ከእጁ ላይ ቀማችውና የያዘውን ጎን መታ መታ አድርጋ አንድ ሲጋራ አውጥታ አፏ ላይ ከሰካች በኋላ "አንድ ሀባ ልጨምር?" አለችው በቀኝ አይኗ ጠቀስ አድርጋው::

"ውሰጅ::" አላት ናትናኤል ትዕግሥቱ እየተሰጠጠበት::

አንድ ጭማሪ ሲጋራ አውጥታ ሰታበቃ ሳትጋበዝ ቀልጠፍ ባለ ሁኔታ ኮቱን መለስ አደረገችና የሲጋራውን ፓኮ ከውስጥ በኩል ኪሱ ውስጥ ሻጠችለት::

"ብድር መላሽ ያድርገኝ::" አለችው ፈገግ ብላ የጎንት ሕይወት አጥተው ስልምልም ባሉ ቅንድብ የለሽ አይኖቿ እያባበለች::

"ችግር የለም::" አለ ናትናኤል እልፏት ለመሄድ እየሞከረ::

"ካዛንችስ ሞቢሉጋ 'ስርጉት ቤት' ብለህ ጠይቅ በል ቆንጆ ሌሊት እናሳልፋለን.... እ.... አትጥፋ::" አለችው በሚያምርበት ትቷት ሲሄድ ጀርባውን ቸብ አድርጋ::

"ዘልዛላ .... ዘልዛላ ሽርሙጣ::" አለ ናትናኤል በልቡ:: ቢሆንም ዞር ብሎ አልተመለከታትም:: ራመድ እያለ ወደ ጣቢያው ህንፃ አመራ::

"እንደምን አደርክ...." አለ ናትናኤል ፊቱን በፈገግታ አስውቦ ከጠረጴዛው ኋላ ተቀምጦ በቀኝ እጁ የስልክ እጀታ በግራው ደግሞ የመስክ መገናኛ ሬዲዮ ይዞ ሥራ የበዛበት ለመምሰል የሚጥረውን ወጣት የፖሊስ መኮንን::



መኮንኑ በተቻለው መጠን ፊቱን አኮሳትሮ በቀኝ የያዘውን የስልክ እጀታ ወደጎን ዞር አድርጎ "ምንድን ነበር?!" አለ እንደማመናጨቅ እየቃጣው::

"ይቅርታ አድርግልኝ አቋረጥኩህ ...አባክህ የጣቢያውን ኃላፊ ለማነጋገር ፈልጌ ነበር::" በተቻለው ትህትና ተላብሶ ለመቅረብ ሞከረ ናትናኤል::

መኮንኑ በተሰላቸ ሁኔታ በአገጩ በስተቀኝ በኩል ወዳለ በር አመለከተው::

ናትናኤል በምሥጋና ራሱን አነቃንቶ በስተቀኝ ያለውን በር ሁለቴ ካንኳኳ በኋላ መዝጊያውን ከፍቶ ገባ::

ናትናኤል በሩን ከፍቶ ወደውስጥ እንደገባ ከውጭ ክበሩ ቆም ብሎ ሁኔታውን ይከታተል የነበረ አንድ ሰው ወደ ወጣቱ መኮንን ጠጋ አለ::

"ምንድን ነበር?" ወጣቱ መኮንን የነኑ ቅጭም ያለ ፊቱን ቀና አድርጎ እንግዳውን ገረመመው::

እንግዳየው እጁን ወደ ደረት ኪሱ ሰዶና አነስተኛ የመታወቂያ ወረቀት አውጥቶ ለአንድ አፍታ ብልጭ አደረገለትና መልሶ ከኪሱ ከተተው::

"አቤት ጌታዬ!?" አለ ወጣቱ መኮንን በቀኝና በግራው የያዘውን የስልክ እጀታና መገናኛ ሬዲዮኑን በጥድፊያ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ከወንበሩ እየተነሳ::

"ቁጭ በል...!" እንግዳው የተለየ እርጋታ ይታይበታል:: ፊቱ ላይ ከተጋደመው ጠባሳ ጋር ሲታይ ከእንጨት ተፈልፍሎ የወጣ እንጂ ከደምና ከስጋ የተፈጠረ አይመስልም:: "ምንድን ነው የጠየቀህ?"

"ማን ጌታዬ?" ወጣቱ መኮንን በተቀመጠበት አይኖቹን በተጠንቀቅ ከጎንና ከጎን ለጥፎ ከፊቱ ያጎነበሰውን እንግዳ ሽቅብ እየተመለከተ ጠየቀ::

እንግዳው ጭንቅላቱን በስተቀኝ ወዳለው በር መታ አድርጎ አመለከተው::

"አሁን የገባውን ሰውዬ ነው ጌታዬ?"
"ቀስ ብለህ ተናገር!" እንግዳው ጥርሱን ገጥሞ ነው የሚናገረው::

"...የጣቢያውን አዛዥ ነው የፈለገው ጌታዬ::" መኮንኑ እንደተቆጣት ሀሳን ጉንጮቹ ተንጠለጠሉ::

እንግድየው ምንም መልስ ሳይሰጠው ፊቱን ወደ ግራ መልሶ ግድግዳው ላይ የተለጠፈውን የአዲስ አበባን ከተማ ካርታ ያጠና ጀመር::

ናትናኤል ወደ አዛዡ ቢሮ እንደገባ በሩን ዘግቶ ቆመ:: ከጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠው ሲቪል የለበሰው ሰው ግን ካቀረቀረበት ቀና አላለም:: እህህ... ጉሮሮውን አፀዳ ናትናኤል:: ሰውየው ለአንድ አፍታ ቀና ብሎ ካየው በኋላ በግራ እጁ አንድ ወንበር አመለከተውና እንደገና አቀረቀረ::

ናትናኤል በፀጥታ ወደፊት ተራመደና አዛዡ ባመለከተው የእንጨት ወንበር ላይ ተቀምጦ በትዕግሥት መጠባበቅ ያዘ:: የአዛዡ ቢሮ ይቀዘቅዛል:: በጠባቧ መስኮት የሚገባው አነስተኛ ብርሃንና ሙቀት ለትንሿ ክፍል ህይወት ለመስጠት የሚበቃ አይመስልም::

የጣቢያው አዛዥ የጠረጴዛ መሳቢያውን ስቦ ከውስጥ ዕቃ እንደሚፈልግ አይነት ሲጎረጉር ቆየና "ምን ልርዳህ?" አለ ድንገት ቀና ብሎ ይዞት የነበረውን ብዕር ጠረጴዛው ላይ ጣል እያደረገ::

"እ..." ናትናኤል እንዴት መጀመር እንዳለበት ግራ ተጋባ:: የደረት ኪሱ ውስጥ ገባና የገንዘብ ቦርሳውን አወጣ:: ከውስጥ የመሥሪያ ቤቱን መታወቂያ ወረቀት አውጥቶ ለሰውየው ዘረጋለት:: ሰውየው በቸልታ መታወቂያ ወረቀቱን ተቀብሎ ከተመለከተ በኋላ መልሶ ከጠረጴዛው ላይ ወርወር አደረገለት:: ናትናኤል ቀልጠፍ ብሎ ጀመረ::

"እ... ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር... እ...ባለፈው ሳምንት አንድ የውጭ ዜጋ ለጊዜው ተሰውሮ ነበር:: በጊዜው መኪናውን በመቻበት ያገኟት የዚህ ጣቢያ አባላት ነበሩ:: እና የምትችሉ ከሆነ አንዳንድ ሃሳብ እንድትሰጡኝ ነበር::"

"በጉዳዩ ላይ በወቅቱ ተገቢውን ዘገባ አቅረብን መሰለኝ::" አለ የጣቢያው አዛዥ ቀዝቀዝ ብሎ::

"እ... ይሆናል! ይሆናል! ግን ሳስቸግርህና እንደው ስለሰውየው ማንኛውንም ዓይነት ሃሳብ ባገኝ...መኪናው የተገኘችው መጠጥ ቤቶች በብዛት በሚገኙበት አካባቢ ነበር...ማለቴ ከዚህ ቀደም ሰውየው ወደዚሁ ቦታ ይመጣ እንደሆነ::"

"ወንጀል አልተፈጸመም::" የጣቢያው ኃላፊ ድንገት አቋረጠው "መኪናዋ በእኛ ክልል መገኘቷ ግልፅ ነው:: ያንን ደግሞ ወዲያውኑ ለተገቢው አካል አስተላልፈናል:: ከዚህ ውጪ ምንም የምናውቀው ነገር የለም::"



"ምን መሰለህ..." ናትናኤል ተስፋ ሳይቆርጥ ሁኔታውን ለማስረዳት ጀመረ::

"ይቅርታ ወንድም!" ድንገት አቋረጠው የጣቢያው ኃላፊ ከመቀመጫው እየተነሳ "ምንም ልሰጥህ የምችለው ሃሳብ የለም::"

ናትናኤል ተስፋ ቆረጠ:: ሰውየው ሊረዳው ፈቃደኛ አይደለም:: ከዚህ በኋላ አጥብቆ መጨቅጨቅ ምንም የሚጨምረው ነገር አይኖርም::

"አመሰግናለሁ:: ይቅርታ የሥራ ሰዓትህን ስለተሻማሁ::" ንዴቱን ውጦ የአዛዡን ደረት እጅ ጨብጦ ከቢሮው ወጣ::

ናትናኤል ከአዛዡ ቢሮ እንደወጣ ከውጭኛው ክፍል ግድግዳ ላይ የተለጠፈውን የአዲስ አበባ ካርታ ያጠና የነበረው ሰው ቀልጠፍ ባለ ሁኔታ የአዛዡን ቢሮ በር ከፍቶ ገባ:: ለአንድ አፍታ ከአዛዡ ጋር ተያዩ:: የጣቢያው አዛዥ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመ::

"ቀንደምቹ::" አለ ፊቱ ላይ ጠባሳ ያለው ሰው እንደ ቆርቆሮ በሚንኳኳ ድምፁ::

አዛዡ ከተሳበው የጠረጴዛ ኪስ ውስጥ የተቀመጠውን ክር የጎረሰውን አነስተኛ የድምጽ መቅጃ መሣሪያ አውጥቶ አቀበለው:: እንግዳው ሰው በጭንቅላቱ ሠላምታ ሰጥቶ ፈጠን ብሎ ወጣ::

ናትናኤል ከአዛዡ ቢሮ ሲወጣ ተበሳጭቶ ነበር:: የጣቢያው አዛዥ በበጎ አመለካከት ተቀብሎ ሊረዳው አልተቻለውም:: ሁኔታውን በረጋ መንፈስ አስረድቶት ሊረዳው አለመቻሉን ሊነግረው ሲችል እንዲያ እንደ ጠላት በጥርጣሬና በጥላቻ ለምን እንደተመለከተው ሊገባው አልቻለም:: «ደደብ» አለ ንድድ ብሎት::

ከሕንፃው እንደወጣ ዝናብ ብን ብን እያለ መውረድ ስለጀመረ ቀልጠፍ ብሎ ወደ መኪናው አመራ::

"ሄይ!" መኪናውጋ ደርሶ በሩን ሊከፍት ሲል ከኋላው ሲጠራ ተሰማው:: ፊቱን ሲያዞር አያት:: ወደ ጣቢያው ሲገባ ሲጋራ የጠየቀችው ሴት እየተውረገረገች ስትመጣ ተመለከተ:: "ወደ ፒያሳ ነው የምትሄደው? ወደዛ ከሆነ የምትሄደው...?"

"አይደለም! ወደዛ አይደለም ይቅርታ::" ናትናኤል ቀልጠፍ ብሎ የመኪናውን በር ከፍቶ ገባና በሩን ሊዘጋ ሲል ተሽቀዳድማ ግራ ትከሻውን ያዝ አድርጋ ተጠጋችው::

"ሳስቸግርህና የኔ ጌታ ሌላ ሲጋራ ትሰጠኝ?" እነዛኑ ቅንድብ የለሽ አይኖቿን አስለመለመችለት:: የዝናቡ ማካፋት የተሰማት አትመስልም::

በጣም ተናደደ። በተለይ ያንን ቁናስ ገላዋን ደፍራ ወደ አፍንጫው ማስጠጋቷ ክፉኛ አበሳጨው። ፈጠን ብሎ ከደረት ኪሱ ውስጥ ያለውን የሲጋራ ፓኮ አውጥቶ ወረወረላትና እየናገረችው ሳለች የመኪናውን በር ዘግቶባት ሞተሩን አስነስቶ ወደ መንገድ ገባ።

ልጅቷ በቆመችበት ፈገግ ብላ እጇን አወዛወዘችለት። ከፓኮው ውስጥ አንድ ሲጋራ አውጥታ ለኮሰች። አንድ ሰማያዊ ቢ.ኤም.ደብሊው ከጀርባዋ መጥታ አጠገቧ ስትቆም የመኪናውን በር ከፍታ ገባች።

“ብራቮ!” አላት መሪውን የያዘው ሰው ፈገግ ብሎ እየተመለከታት። “የቀኑን ኃላፊነታችንን ተወጥተሻል። የቀረው የቦብ ኃላፊነት ነው።” አለ በዕብራይስጥ ቋንቋ።

ነጭ ቢሆንም በብዙ ሀሩር የተቃጠለና የተጠበሰ የሚመስለው ፊቱ ብዙ ውጣ ውረድ ያለፈ ጠንካራ መሆኑን ያሳያል። ዛሬ እንደ አስፈላጊነቱ ስለሚቀያየር ይህ ነው ተብሎ የሚጠራ ቋሚ ስም የለውም። ሆኖም የጦር አውሮፕላን አብራሪነቱን አቁሞ ስለላን ሙያው፣ ሞሳድን ቤቱ ከማድረጉ በፊት አሃሮን አይተን በመባል ነበር የሚታወቀው። የተወለደውም ያደገውም ከቴልአቪቭ አቅራቢያ በምትገኝ ሆሎን በምትባል ከተማ ነው፤ እናቱን አያውቅም። የልጅነት አለሙ በአባቱ የተጣበበ ነበር።

አሃሮን አይተን በእሥራኤል አየር ሃይል ውስጥ ማገልገል ከጀመረ በኋላ እጅግ ዝነኛ ከሆኑት ጥቂት አብራሪዎች ጋር አብሮ ለመቆጠር ረጅም ጊዜ አልወሰደበትም። የመጀመሪያ ሲሳዩ ኢራቅ ነበረች። ሰኔ 7 ቀን 1981 ባግዳድ አካባቢ የሚገኝ የኢራቅን የኒውክሌር ማመንጫ እንዲደመስሱ ከተላኩት አውሮፕላኖች የአንዱ አብራሪ ሆኖ ሲመረጥ ገና የ23 ዓመት ወጣት ነበር። የኢራቅ የኒውክለር ማመንጫ ወደመ፤ የአሃሮን ደረት በኒሻን አጌጠ። በአመቱ ሁለተኛ ሲሳዩ እጁ ገባች - ሊባኖስ። በእንግሊዝ የነበሩት የእሥራኤል አምባሳደር አርጎብ በመሃል ለንደን በጠራራ ፀሐይ በአሸባሪዎች ጥይት ቆሰሉ። ተከትሎም የ1982 አምስተኛ የአረብና የእሥራኤል ጦርነት ተጀመረ። የእሥራኤል የጦር አውሮፕላኖች የጠቅላይ ሚኒስቴር ቤጊንን ቁጣ እውን ለማድረግ በሊባኖስ አየር ላይ አንዣበቡበት፤ ፈነጩበት። ድል በድል የሆነው የእሥራኤል ጦር ሲመለስ የአሃሮን ደረት ድጋሚ በኒሻን ተሽሞነሞነ።



ገና በወጣትነቱ በሯን ከፍታ ያቀማጠለችው ዕድሉ በዛው ዓመት ድንገት ፊቷን አዞረችበት። ከገሊላ ወጣ ብሎ ከሚገኝ የአየር ሃይል ጦር ሰፈር ተነስቶ የልምምድ በረራ እያደረገ ሳለ የያዛት አውሮፕላን ተከሰከሰች። ረዳቱ ወዲያውኑ ሲሞት አሃሮን ሞተ ከተባለ በኋላ በሐኪሞች ብርታት ተመልሶ ሰው ሆነ። ከደረሰበት ጉዳት አገግሞ ከሐኪም ቤት የወጣው ግን ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ነበር። የቀድሞ ሥራውን የመቀጠል ዕድሉን ከጥያቄ ውጪ ሆኖ አገኘው።

ሞሳድ እጆቹን ዘርግቶ ተቀበለው።

በስለላው ድርጅት ውስጥ ሲገባ ባጋጠመው ሁኔታ መንፈሱን የተሰበረ ቢሆንም በውትድርናው ዓለም ውስጥ የነበረውን ዓይነት ዝና መልሶ የተጎናፀፈው ገና ድርጅቱ ውስጥ በገባ በሁለተኛው አመት ነበር። በጥር ወር 1985 በተካሄደው ኦፕሬሽን ሞሴስ በመባል የሚታወቀው እሥራኤል በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ በከሰላና በአላታርች የስደተኛ ሠፈሮች ውስጥ የነበሩ በሺህ የሚቆጠሩ ፈላሻዎችን ከፖርት ሱዳን በስተሰሜን 120 ኪሎ ሜትር ርቆ ከሚገኝ የቀይ ባህር ጠረፍ በስውር ወደ እሥራኤል ባጓጓዘችበት ኦፕሬሽን ውስጥ ያሳየውን ችሎታ የተመለከቱ የሞሳድ ባለሥልጣናት ዓይናቸውን ጣሉበት።

ከዚህ ኦፕሬሽን በኋላ አሃሮን በተለይ በአፍሪካ ውስጥ የመረጃ ሥራ ለመሥራት የሚያበቃውን ልዩ ሥልጠና እንዲወስድ ተደርጎ ሥራውን በጥልቀት ቀጠለ። በሰሜን ከሚገኙ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች ውጪ በተቀሩት የአረብ አገሮች ተዘዋውሮ ሰርቷል። ዛሬ እድሜው በአርባዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ላይ የሚገኘው አሃሮን አብዛኛውን የአዋቂ አለሙን በአፍሪካ ውስጥ በመረጃ ሥራ በመሥራት በማጥፋቱ አፍሪካን በተመለከተ በሞሳድ ውስጥ ተለዋጭ ሊገኝላቸው ከማይችሉት ሁለትና ሶስት ኤክስፐርቶች አንዱ ለመሆን በቅቷል።

ባለፈው ሚያዚያ አጋማሽ ላይ ነበር ከነበረበት ከጆሃንስበርግ በአስቸኳይ ወደ ቴልአቪቭ እንዲመለስ ትዕዛዝ የተላለፈለት። በዛኑ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ቴልአቪቭ ተመልሶ በመሃል ከተማ በሚገኘው የሞሳድ ዋና ጽህፈት ቤት ሪፖርት ሲያደርግ ወዲያውኑ የሩቅ ምሥራቅና የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊ ወደሆነው የበላይ ሹም ቢሮ አጣደፉት።

“አይተን ...” አለ በስልሳዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኘው በሳል የመረጃ ሰው ከተቀመጠበት ተነስቶ ጠረጴዛውን ዞሮ ወጥቶ ከአሃሮን ፊት ለፊት ወንበር ስቦ እየተቀመጠ። ሰውየው በሞሳድ ቀጭን የሥልጣን ገመድ ላይ ተረማምደው ቆጥ ላይ ከሰፈሩት በጣት የሚቆጠሩ ባለሥልጣናት አንዱ ቢሆንም እያንዳንዱን የበታች ሠራተኛ የሚያቀርበው እንደ ታናሽ ወንድም እንጅ እንደ ታዛዥ የሥራ ባልደረባ አይደለም። ከከፍተኛ ችሎታው ውጪ ፍቅርንና ከበሬታን ያተረፈለት ነገር ቢኖር ይኸው ነበር። “... አይተን

እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ ለጊዜው ልሰጥህ የምችለው መረጃ እንስተኛ ነው:: ያም-ቢሆን ከሞላ ጎደል በዚህ ተካቷል::" አለ አነስተኛ ጥራዝ ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ እያቀበለው:: "ይህን ጊዜ ወስደህ አንብበው! አብላላው:: በተረፈ ግን ሁኔታው ግልፅ እንዲሆንልህ ዋና ፍሬ ሃሳቡን እገልጽልሃለሁ::" በሩ ተከፍቶ የአስቃው ፀሐፊ በትሬ ላይ ቡናና ብስኩቶች ይዛላቸው ገባች:: አስቅየው ለአንድ አፍታ ወሬውን ገታ:: ፀሐፊው ተመልሳ ስትወጣ የቀረበውን ቡናና ብስኩት ቾላ ብሎ ንግግሩን ቀጠለ::

"የአፍሪካ አገሮች በ1994 ላይ ከሱማሊያና ከሩዋንዳ የእርስ በርስ እልቂት በኋላ ካይሮ ውስጥ ተሰብስበው አፍሪካ የራሷን የሠላም አስከባሪ ግብረሃይል ልታዋቅርበት የምትችልበትንና በአገሮች ውስጥ ሁከቶች ሲከሰቱ ያለ ባዕድ ጣልቃ ገብነት ልትፈታቸው የምትችልበትን ሁኔታ አንስተው እንደተወያዩ ታስታውሳለህ::"

"አዎ ትዝ ይለኛል" አለ አሃሮን:: "ዝርዝር ሪፖርቱን ያዘጋጀሁት እኔው ነኝ::"

"በጊዜው እንደምስጢር አልያዙትም ነበር:: ነገር ግን ባለፈው ወር..." ቀጠለ አለቅየው "አፍሪካን ዲፌንስ የተባለ መጽሄት ከዓመታት በፊት የጻፈውን ጽሁፍ ጠቅሶ በድጋሚ አፍሪካ ይህንኑ ዕቅድ በተግባር እየተረጎመችው መሆኑን ሲጽፍ መላው አፍሪካ አስተባበለ::"

አሃሮን ጭንቅላቱን በመስማማት ነቀነቀ፤ ሁኔታውን እሱም የተከታተለው መሆኑን በሚገልፅ መልክ::

"ለጊዜው ሁኔታው የዚያን ያህል ባያሳስበንም አንድ ተጨባጭ ነጥብ ላይ ለመድረስ ስንል በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ ወታደራዊ ባለሥልጣናትን ቀርበን መረጃ ለማግኘት ሞከርን:: የሚገርምህ ነገር ሶስት ወር ሙሉ በያለበት ብንዳክርም ትንሽ ፍንጭ እንኳን ለማግኘት ተሳነን:: በመጨረሻም ሳይታሰብ ፈረንሣዮች ቀዳዳ እንዳገኙ ደረስንበት::"

"የት?" አለ አሃሮን ከወንበሩ ላይ ወደፊት ፎቀቅ ብሎ::

"ሞሮኮ ውስጥ" አለ አለቃው የቡና ስኒው ውስጥ ስኳር ጨምሮ እያማሰለ:: "ለጊዜው በተደራቢነት በመለመልናቸው የፈረንሣይ የመረጃ መኮንኖች በኩል ሁኔታውን ስንከታተል ፈረንሣዮች የሞሮኮን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደመለመሉ ደረሥንበት:: ይህ በእርግጥ ግሩም ተስፋ ነበር:: ሆኖም ከሁለት ሣምንታት ቆይታ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግል ጀልባቸው በሜድትራንያን ላይ ሲዝናኑ ድንገት የገቡበት ጠፋ:: የተለያዩ ጋዜጦች የተለያዩ ጽሁፎችን አወጡ:: ግማሾቹ ታፍነዋል አሉ፤ ሌሎች እራሳቸውን አጥፍተዋል አሉ..."



"እም እኔም በርካታ ጽሁፎች አንብቤአለሁ::" አለ አሃሮን ያጋባውን የቡና ስኒ እያስቀመጠ::

"በዚህ ተደናግጠን እንዳለን የኛው ልጆች ካሜሩን ውስጥ መረጃ ለመሸጥ ፈቃደኝነትን ያሣዩ ሁለት ባለሠልጣናትን አገኙ:: የገንዘቡ መጠን የሚያስደነግጥ ነበር:: ሆኖም ምርጫ ስላልነበረን የተጠየቅነውን ሁሉ ከፈልን:: ከመረጃው በፊት ክፍያ መፈጸም ከደንብ ውጪ ቢሆንም ባለሥልጣናቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ስለነበሩና እኛም ጉጉት ላይ ስለነበርን ገንዘቡን ከፈልን::"

"እና ምስጢሩ ተገኘ?" አለ አሃሮን::

"አዎ::"

"ምንድነው?"

"እሱን ነው እኔም ያልመለስኩት ጥያቄ!" አለ አለቃው::

"እንዴት ...?" አለ አሃሮን ምሥጢሩ ከተገኘ በኋላ ዳግመኛ ሊከሰት የቻለው ችግር አልገለጽልህ ብሎት::

"ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ በሁለተኛው ቀን ማለት ከትላንት ወዲያ ረቡዕ ያወንዴ ያለው አምባሳደራችን አንደኛ ፀሃፊውን መልዕክት አሲዞ ወደዚህ ሰደደው:: በላከው መልዕክት ውስጥ ምሥጢሩን ማግኘቱንና እጅግ አደገኛ የሆነ እንቅስቃሴ በመላው አፍሪካ በተቀናጀ መልኩ እየተካሄደ መሆኑን፤ አናቱም ያለው አዲስ አበባ ውስጥ እንደሆነ ጠቅሶ ዝርዝር መረጃውን በተመለከተ ግን እርሱ እራሱ ይዞት በማግሥቱ ወደዚህ እንደሚበር ገለጸልን::"

"የእርሱ እዚህ ድረስ መምጣት ለምን አስፈለገ? እንደማንኛውም ምሥጢር በዲፕሎማቲክ ቦርሳ ሊልከው ሲችል" አለ አሃሮን አለቃውን አቋርጦት::

"አላውቅም፤ ምናልባት ያገኘው ምስጢር ከፍተኛነት ከራሱ ውጪ ማንንም እንዳይተማመን የፍርሃት ሥሜት አሳድሮበት ይሆናል::"

"እ... ሺ" አለ አሃሮን መጨረሻው ናፍቆት::

"የአምባሳደራችንን መምጣት ስንጠባበቅ ትላንት ምሽት ላይ የካሜሩን ኢታማዦር ሹምንና የአገሩን አስተዳደር ሚኒስቴር እንዲሁም የኛን አምባሳደር በአንድነት ጭና ትበር የነበረች የጦር ሄሊኮፕተር በአየር ላይ እንዳለች መቃጠሏን የካሜሩን የውጭ ጉዳይ እዚህ ባለው አምባሳደሩ በኩል አስታወቀን::"

"ሊሆን አይችልም!"

"ሆነ።" አለ አሰቃው የተቀመጠበትን ወንበር ድጋፍ በቡጢ "መትቶ። እጃችን የገባውም ምሥጢር ከሸጡልን ሁለቱ ባለሥልጣኖች ጋር አብሮ በእሣት ጋየ።"

"እስካሁን ወሬውን እንዴት አላገኘሁትም?...ማለቴ ያውንዴ ጆሮዎች አሉኝ...ደግሞም"

"የሚገርምህ ነገር" አለቃው አቋረጠው "የካሜሩን መንግሥት አደጋ መድረሱን ከገለፀልን ከሰባት ሰዓታት በኋላ ነው እዚያው ያሉ የኤምባሲያችን አባላት የደረሱበት። አደጋው ካሜሩን ውስጥ በምሥጢር ተይዞ ነበር ማለት ነው።"

"አሁን ምን ላይ ነው ያለነው?" አለ አሃሮን በተቀመጠበት እየተቁነጠነጠ።

"በበኩላችን ማብራሪያ ጠይቀናል-የካሜሩንን መንግሥት። በተጨማሪም የአደጋውን መነሻ የሚያጠና ቡድን ትናትና ሌሊቱን ወደዚያው በሯል። ሆኖም ዋናው ነጥብ ይህ አይደለም። አደጋው ሆን ተብሎ የተፈጸመ ለመሆኑ ጥርጥር የለኝም። ግድያው የሞሮኮው ጠቅላይ ሚኒስትር ከተሰወሩበት ምክንያት ጋር በተዛመደ መልኩ የተቀነባበረ ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም። ይህ ደግሞ አምባሳደራችን እጅ ገብቶ የነበረው መረጃ በእርግጥም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነበር ማለት ነው።" አለቅየው ከተቀመጠበት ተነስቶ ከጠረጴዛው ጀርባ ከቦታው ተመልሶ በገዛ ወንበሩ ላይ ተቀመጠና መሳቢያውን ስቦ የታሸገ ፖስታ አወጣ።

"አሃሮን" አለ ፖስታ የያዘበትን እጁን ወደፊት ዘርግቶ "...ከጆሃንስበርግ ባስቸኳይ ያስጠራሁህ ወደ አዲስ አበባ ሄደህ የዚህን እንቅስቃሴ አናት ሽምቀቆ ውስጥ እንድታስገባልኝ ነው... ይህ ትኬትህና ፓስፖርትህ ነው።" የታሸገውን ፖስታ አቀበለው።

የዛኑ ለሊት ከቴልአቪብ ተነስቶ በአቴንስ አድርጎ አዲስ ደበባ ገባ። በፓስፖርቱ ላይ ያለው ስሙ ካሚል ጀማል ጀማየል ይላል። ዜግነት ሊባኖሳዊ፤ ሥራ ንግድ።

አዲስ አበባ ከገባ ሶስተኛ ወሩን ጨርሶ አራተኛውን ሊይዝ የቀሩት ጥቂት ቀናት ናቸው። ጨለማው ግን አሁንም አልገፈፈለትም። አዲስ አበባ እንደደረሰ ቴልአቪብ ያለው አለቃው በቅድሚያ ባመቻቸለት መሠረት ከእንግሊዝ ኤም.አይ. ስድስት ሰዎች ጋር በቅንጅት በመሥራት መረቡን በስፋት ዘረጋ። መረቡ ውስጥ የገባ የተጠመደ አሳ ግን አልነበረም።



አሃሮን ሊክደው ያልቻለው ነጥብ አዲስ አበባ ውስጥ ከሞሳድና ከሲ.አይ.ኤ. ይልቅ ኤም.አይ.ስድስት ቀድሞ ምሥጢሩን ማነፍነፍ መጀመሩን ነበር። ሆኖም እንግሊዞች የመለመሏቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያንን በመሆኑና እነዚህም ከሞላ ጎደል በኢትዮጵያ የስለላ መዋቅር ውስጥ የታቀፉ ለገንዘብ ሲሉ በተደራቢነት ለኤም.አይ. ስድስት የሚሰሩ በመሆናቸው የመሥክ ሥራ በስፋት ለመሥራት የማያመቹና አመኔታም የማይጣልባቸው ሆነው አገኛቸው።

ይህን ችግር ለማስወገድ አሃሮን ቴልአቪብ የሚገኙ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ወደ እሥራኤል የተመለሱ አይሁዶችን በብዛት ወደ አዲስ አበባ አስመጥቶ አሰማራቸው።ይህ አዲስ አበባ ውስጥ በርካታ ጆሮዎችና ዓይኖች እንዲኖሩት ከመርዳቱም በላይ የእንግሊዝ ኤም አይ. ስድስት ለሚያደርግለት ድጋፍ ወሮታውን ለመመለስ አብቅቶታል።

በአዲስ አበባ ውስጥ በአጭር ጊዜ ከእንግሊዞች የተሻለ ሰፊ መረብ ዘርግቻለሁ ብሎ ቢያምንም የመጀመሪያውን በር የከፈቱት እንግሊዞች ነበሩ።

ሰኔ መጨረሻ ላይ አዲስ አበባ በገባ በሶስተኛ ወር በአዲስ አበባ የኤም. አይ. ስድስት ቡድን የሚመራው ሮበርት ፋረል ዜናውን አበሰረለት። ፋረል የሰላሳ ስምንት አመት ጎልማሳ ነው። ፈጣንና ቀልጣፋ ጭንቅላት ስላለው አሃሮን ያከብረዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁት በ1991 ሶማሊያ ውስጥ ሁለቱም የመረጃ ሥራ ሲሰሩ ነበር።

"እርግጠኛ ነህ?" አለ አሃሮን በመቀደሙ የተሰማውን ብሽቀት አምቆ ይዞ።

"ይመስለኛል።" አለ ፋረል በቀኙ የያዘውን የሸረ ጠርሙስ እየከተፈ። የተከፈተውን ጠርሙስ በቀኝ ይዞ በእርጋታ ሁለት መለኪያዎች ከመደርደርሪያው ውስጥ አወጣና ለሁለቱም ከቀዳ በኋላ "ለስፔይን ወይን ጠጅ ጠማቂዎች! ብሎ መለኪያውን አነሳ። "ዓለም ሁሉ የፈረንሣዮችን ወይን ጠጅ ያደንቃል። የኔ ልብ ግን ጥንትም ዛሬም ወደፊትም ያለው ከስፔይን ጠማቂዎች ጋር ነው!" አለ ፈገግ ብሎ።

"ቦብ ... ይቅርታ አድርግልኝና የመጣሁት ለሼሪ ያለህን ታማኝነት ለማረጋገጥ አይደለም!" አለ አሃሮን በስጨት ብሎ "ለማወቅ የምፈልገው በእርግጥ ቀዳዳ ማግኘትህን ነው።"

"አትቸኩል።" አለ ፋረል ፈገግ ብሎ አሃሮንን ይበልጥ ማበሳጨት የፈለገ ይመስል። "ልጅ ሆኜ አባቴ ሁሌ የሚነግረኝ ተረት ነበር...የስፔይን ወይን ጠጅ ጠማቂዎች..."

"የፈጣሪ ያለህ!" አሃሮን ተነስቶ ቆመ "...እመነኝ ካሁን በኋላ ስለ ሼሪ ወይ ስላባትህ ልትቀባጥር ብትሞክር..." አለ አሃሮን ቡጢ ጨብጦ።

"ደህና...ደህና" አለ ፋረል እየሳቀ ቶሎ ተቀመጠና "ቁጭ ብለህ ብትሰማኝ አይሻልም?" አለ በንዴት ቡጢ ጨብጦ ቁልቁል የሚመለከተውን አሃሮንን እያየ።

"በል ቀጥል ምን ታየኛለህ...ምንድነው አገኘሁት የምትለው?"
"መረጃ ያለው ሰው ያጠመድኩ ይመስለኛል።" አለ ፋረል ለመጀመሪያ ጊዜ ኮስተር ብሎ

"ማነው እሱ?"
"እ..ለጊዜው ማንነቱን እናቆየው.."
"ቦብ! ...ምሥጢር መደበቅህ ነው?" አለ አሃሮን በስጨት ብሎ
"ዲፕሎማት ነው።" አለ ፋረል ትንሽ ካቅማማ በኋላ።
"ኢትዮጵያዊ?"
"አይደለም..ላይቤሪያዊ ነው።"
"እንዴት መለመልከው... ስለፈጣሪ ብለህ ሁሉን በግልጽ አስረዳኝ።"

ፋረል መለኪያውን አንስቶ ከጨለጠው በኋላ "... ዝርዝር ነጥብ ውስጥ እንድገባ አታስገድደኝ.. አልገባም። ዋናው ነጥብ ሰውየው ሚስጥሩን እንደሚያውቅ ደርሰንበታል። ከአሁን በኋላ የጊዜ ጉዳይ ነው። ብዙ እንደማይዘገይ እርግጠኛ ነኝ... የፈለግነው ምሥጢር በጃችን ይገባል" አለ ፋረል በተቆራረጠ አረፍተ ነገር።

"በምን መንገድ ልረዳህ እችላለሁ እኔ? " አለ አሃሮን መቀደሙ አንጀቱን እየበላው፡

"አመሰግንሃለሁ...ግን ለጊዜው እርዳታ አያሻኝም።" አለ ፋረል ዘብነን እያለ በምሥጢሩ ላይ ያለውን ባለቤትነት ለማሳየት እንደፈለገ ሁሉ።

በሣምንቱ ሁኔታዎች ሁሉ ተቀያየሩ።ተስፋ የተጣለበት የላይቤሪያው ዲፕሎማት የገባበት ጠፋ።

"አሃሮን!" አለ ፋረል ፀጉሩን እየነጨ "እርዳታህን እፈልጋለሁ።" ይሄን ሰው የገባበት ገብተን ማግኘት አለብን። ምሥጢሩን ይዞ ነው የተሰወረው።

የተባለው የላይቤሪያ ዲፕሎማት መጥፋት ሁለቱን የመረጃ ቤቶች በአዲስ አበባ ውስጥ ይበልጥ አስተሳሰራቸው። ያላቸውን የሰው ሃይልና



የገንዘብ ብርታት ሁሉንም በቅንጅት ለመጠቀም ዝግጁ ሆኑ። ዲፕሎማቱ... የላይቤሪያው ወታደራዊ አታሼ በፍጥነት በእጃቸው መግባት አለበት! በፍጥነት።

***

ልጅቷ የያዘችውን የሲጋራ ፓኮ ቁልቁል ቀደደችና ከውስጥ ባቄላ የምታክል የድምፅ ማስተላለፊያ መሣሪያ አውጥታ ለአሃሮን አቀበለችው።

"በጣም አደገኛ ዘዴ ነው የተጠቀምነው ግን ውስጥ ከገባ በኋላ ሊያጨስ ፓኮውን ቢያወጣ ኖሮ !" አለ አሃሮን።

"ፓኮውን ቀድዶ ውስጡን እስካላየ ድረስ አያገኛትም። ደግሞ ይህን ይህን እየተሸተትኩ የደባበስኩትን ሲጋራ አውጥቶ ከአፉ ከሰካው ሰውየው ጤነኛ አይደለም ማለት ነው... እስቲ አሽትተው።" አለች እሷን እሷን የሚሸተውን የሲጋራ ፓኮ ወደ አፍንጫው እያስጠጋች።

"ቦብ ምን ያህል እንደሚደሰት አላውቅም።" አለ አሃሮን ፊቱን ከሲጋራው ፓኮ እያሸሸ።

"ተደሰተም አልተደሰተም ሥራዬን ጨርሻለሁ... ቃልህን ማክበር አለብህ... በሚቀጥለው አውሮፕላን ወደ ቴልአቪቭ መመለስ እፈልጋለሁ።"

"ያንን መወሰን የሚችል አሮን እራሱ ነው። እኔ ላደርግ የምችለው ነገር ብሶትሽን ማሳወቅ ብቻ ነው።" አለ አሃሮን ዓይኖቹን ከፊት ለፊት ካለው መንገድ ላይ ተክሎ። "ያንን ደግሞ አደርጌዋለሁ።"

"እንግዲያው ልትረዳኝ ከልቻልክ ከአሮን ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ።"

"ሞኝ አትሁኝ። አንድ ጊዜ አዲስ አበባ ከደረስሽ በኋላ በምንም መንገድ ከአሮን ጋር መገናኘት እንደማትችይ ገና ከቴልአቪቭ ስትነሽ የተገለፀልሽ መሰለኝ።" አለ አሃሮን ዞር ብሎ ተመልክቷት።

"ከቴልአቪቭ ስንነሳ የተነገረኝ ሚሽኑ ከአንድ ወር በላይ የማይወስድ ስለመሆኑ ነው! አሁን ግን ሁለተኛ ወሬን ይዣለሁ። አይገባችሁም እንዴ የሰው ችግር? ስንት ጊዜ ልንገርህ? ሕፃን ልጄ የልብ ቀዶ ጥገና ሊደረግላት ስትዘጋጅ ነው አሮን አቻኩሎ ቶሎ እንደምመለስ አግባብቶ ወዲህ እንድመጣ ያደረገኝ። ይገባሃል? ሌላው ቢቀር በዚህ ጊዜ ህፃን ልጄን ልንከባከባት እፈልጋለሁ። የተሰጠኝን ስራ ጨርሻለሁ።"

"እዬው" አለ አሃሮን የመኪናውን ፍጥነት ቀንሶ:: "ይቅርታ አድርጊልኝና እኔ ስለሀገን ልጅና ስለሴላው ችግርሽ ሁሉ የማውቀው ነገር የለም:: እኔ የማውቀው ለሥራዬ የምጠቀምበት አማርኛ አማርታ የምትናገር የአዲስ አበባን ጉራንጉር የምታውቅና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ጠንቅቃ የጠናች ልምድ ያላት የመስክ ሠራተኛ እንድትላክልኝ መጠየቄንና በማምነት ውስጥ አንቺ መምጣትሽን ብቻ ነው:: ከዚህ ውጪ ማሽኑ እስከልተጠናቀቀ አለበለዚያም በአንቺ ምትክ ሌላ ሴት እስካልተተካችልኝ ድረስ ሳደርግ የምችለው ነገር ቢኖር ችግርሽን በሰሁፍ ማሳወቅ ብቻ ነው:: ተግባባን?"

"ሰምን ቀስ ብለህ አሮንን ልታግባባልኝ አትሞክርም አንተ?" ክርክር መግጠሙ እንደማያዋጣት ስትረዳ ለዘብ አለች::

"አላመንሽኝም" ማለት ነው ያለፈው ጊዜ ስነግርሽ» አለ አሃሮን በረጅሙ ተንፍሶ:: «እኔ ራሴ አሮንን በአካል ላገኘው አልችልም:: አየሽ...እሱ የኤምባሲያችን አባል ስለሆነ ክትትል ሊደረግበት ይችላል:: ስለዚህ እኔ ራሴ ትዕዛዙ ደርሶኝ ከቴልአቪብ ስነሳ የተገለፀልኝ ነገር ቢኖር አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላ ከማንኛውም የኤምባሲያችን አባል ጋር መገናኘት እንደማልችልና ማንኛውንም ግንኙነት በምሥጢር በተዘረጉ አቀባባይ ወኪሎች አማካኝነት ብቻ እንድፈጽም ነው:: ከዚህ ውጪ በቀጥታ ላገኛቸው የምችለው ለዚሁ ጉዳይ አብረውኝ የመጡ ክቡታቹ ያሉ ሠራተኞችን ብቻ ነው:: ቤታ:: ደግሞ እውነቱን ንገረኝ ካልሽ አሮንም ቢሆን ሊመልስሽ አይችልም:: እንድትመለሺ ፈቃድ ሊሰጥሽ የሚችለው ሰው ያለው እዛው ቴልአቪብ ነው::"

" እና የኔ ችግር መቼ ነው የሚፈታው?"

" ማሽኑ ዳር ሲደርስ"

" አብደሃል እንዴ! ይህ ነገርኮ ለወራት ሊቆይ ይችላል!" በጭንቀት አፈጠጠችበት::

"በወራት ጊዜ እንቆቅልሹን ክፈታነው እድለኞች ነን:: እውነቱን ንገረኝ ካልሽ ቀናት በተቆጠሩ ቁጥር ፍርሃቴ እየጨመረ ነው የመጣው:: በተለይ ከሶስት ሣምንታት በፊት ካዛንቺስ ውስጥ በጥይት ቆስሎ የነበረው የሞሮኮ ወታደራዊ አታሼ አምቡላንሱ ደርሶ ሊያተርፈው ሲችል በጥታ አስከባሪ ተብለው የመጡ ፖሊሶች ራሳቸው አፍነው ሲገድሉት የእንግሊዝ ስድስቶች ያነሱትን ፎቶግራፍ ካየሁ ወዲህ...እንጃ...እነዚህ አፍሪካውያን የሚሰሩትን ጠንቅቀው የተረዱት ይመስለኛል:: እያንዳንዱ እርምጃቸው ማሰሪያ ያለው ነው የሆነብኝ:: እነዚህ ባሪያዎች ፈንቅለው የተነሱ ዕለት ዓለም ወዮለት!" ፈገግ አለ::

"አፍሪካውያን ባሪያዎች አይ...አይደሉም::" አለች ኮስተር ብላ::



"ኢትዮጵያዊነቱ አገረሸብሽ እንዴ? " ፈገግ አለ አሃሮን ፊቱን መልሶ እየተመለከታት::

"እየው... እሥራኤላዊነቴ ጥያቄ ውስጥ አይገባም" አፈጠጠችበት:: "ግን ይህ የተወለድኩባትና ያደኩባትን አገር እንድጠላ አያደርገኝም:: እውነቱን ንገረኝ ካልክ ደግሞ ሰላይ ሆኜ ወደ ኢትዮጵያ መመለሴ ያቅለሸልሸኛል::"

"ኡፍ! አንቺ ሴትዮ መኪናውን አገማሽው::" አለ አጠገቧ የተቀመጠው አሃሮን መስኮቱን ዝቅ እያደረገ:: ሣቃብ ገባው:: "እስቲ ለማንኛውም ድጋሚ አሳውቀዋለሁ ችግርሽን::"

አሃሮን እውነቱን ሊገልጽላት አልፈለገም::ተለዋጭ የመስክ ሠራተኛ ቢጠይቅ የቴልአቪብ ቢሮ በሰዓታት ውስጥ እንደሚልክለት ልቡ ያውቀዋል:: ሆኖም ይህችን ልጅ መመለስ አልፈለገም:: ፍጥነቷን ድፍረቷንና የመሣሪያ አጠቃቀም ችሎታዋን እምነት እንዲጥልባት አድርጎታል:: እሷን መልሶ ምናልባት ብቁ ያልሆነ የመስክ ሠራተኛ ላይ መውደቅ አልፈለገም:: ያለው ምርጫ በተቻለው ሁኔታው ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ እንደሆነ ልጅቷን ማሳመንና አዲስ አበባ እንድትቆይ ማስገደድ ብቻ ነው::

## -5-

"አብርሃም አለ?" አላት የመኪናውን መስኮት ዝቅ አድርጎ::

የግቢውን በር የከፈተችው ሴት መልስ ሳትሰጠው የብረት በሩን ወለል አድርጋ ከፈተችለት:: የአብርሃም ገረዶች መምጫና መሄጃቸው አይታወቅም:: እንደ አሸን ይፈላሉ፤ እንደ ጤዛ ይበናሉ:: ሁሌ አዲስ ፊት! ሁሌ አዲስ ገረድ::

ናትናኤል ፈረግ እንዳለ መኪናውን በእርጋታ እያሽከረከረ ወደ ግቢ ገባ:: ናትናኤል የአብርሃምን ግቢ በተመለከተ ቁጥር የሚታወሰው ካመት በፊት ቤቱ ሲሰራ የነበረ አቧራና ጭቃ ነው:: ያ ሁሉ አልፎ የዛሬውን አረንጓዴ መስክ ሲመለከት ይገርመዋል::

ከሁለት ዓመት በፊት አብርሃም ቤቱን ለመሥራት ከባንክ ሊበደር ማሰቡን ሲያማክረው ያከላከለው ታሰበው::

"አብርሃም ምን አስቸኮለህ... ገና ምንንም ሳትይዘው ቤት መሥራትን ምን አመጣው?" ነበር ያለው::

"ናትናኤል ከአሁን በኋላክ ህፃናት አይደለንም። ፈጠነም ዘገየ ቤተሰብ መክተሉ አይቀርም።" አብርሃም ሊያስረዳው ሞከረ።

"ቢሆንም...በኋላ ከፍለህ የማትጨርሰው ዕዳ ውስጥ ከምትገባ ለምን ትንሽ አትታገስም..."

"በታገስ ምን ይመጣልኛል...ናትናኤል ከትምህርት ቤት ከተለየንና ሥራ ከጀመርን እንኳን አራት አመታት አለፉንኮ... ጊዜውኮ ይሄዳል። አንተ እራስህ ካልተንቀሳቀስክ ነገም ከዛሬ አይለይም። ዛሬ የከበደህ ነገም ይከብድሃል። ዛሬ አልገፋ ያለህ ነገም አልገፋ ይልሃል። ጨክነን መግባት ነው እንጂ።"

"እንጃ... ብድር ውስጥ ገባ ብዬ አልመክርህም።" ናትናኤል እስከመጨረሻው በአብርሃም ሃሳብ አልተስማማም ነበር።

አብርሃም በሃሳቡ ጠንክሮ ከባንክ ተበድሮ ቤቱን ሠራ። ቤቱ ካለቀ በኋላ ናትናኤል ከራሱ ስንፍና ጋር እየነፃፀረ አብርሃምን አደነቀው፣ ዛሬ የመጣበት ትዝታ ይሄ ነበር።

"አብርሃም አለ? " ብሎ ጠየቃት ድጋሚ የግቢውን በር ከፍታ ያስገባችውን የቤት ሠራተኛ፤ የመኪናውን በር ከፍቶ እየወረደ።

"አለ።" አለችው ሁለት እጆቿን እያፍተለተለች። ከግራ አይኗ በላይ ግማሽ ግንባሯን የሸፈነው የሽታ ምልክት ፊቷን አበላሽቶታል።

"ሳጥናኤል!" አለ አብርሃም የቤቱን በር ከፍቶ ወጥቶ ናትናኤልን ሲያይ። በተማሪነት ዘመናቸው በናትናኤል ሸርና ተንኮል ዘወትር መሳቂያ ይሆን የነበረ አንድ ጓደኛው ናትናኤልን አሻሽሎ ሳጥናኤል ካለው ወዲያ የቅርብ ጓደኞቹ በዚያው ስም ነው የሚጠሩት።

"ፕስ" አለ ናትናኤል ከአብርሃም ጋር ወደቤት እየገባ።

"ምነው?"

"አዲስ ገረድ!" አለ ናትናኤል እያሾፈ።

"ተወኝ ባክህ.. አሁንስ ራሴን እየተጠራጠርኩት ነው። ከራሴው ሳይሆን አይቀርም ችግሩ። ምሥራቅንም ሰለቻት አሁንስ ..እሷ ታመጣለች እኔ አባርራለሁ። እሷ ታመጣለች እኔ አባርራለሁ..."

"እኔኮ ብዬሃለሁ.. ውቃቢህ ገረድ አይወድም!" ናትናኤል ሳቀ።



"አፈር የበላ ውቃቢ... ወይ ወጥ አይሠራ... እንጀራ አይጋግር... በቻ ገረድ ያባርራል!"

"ምሥራቅ ደህና ነች ለመሆኑ?"

"ደህና ነች!" አለ አብርሃም እንደፀባያቸው ለናትናኤል የበረዶ እንኳሮች የገቡበት ለራሱ ደገሞ እምቦ ውሃ ጠብ ያለበት ውስኪ ይዞ እየተመለሰ።

"አሁን ነውኮ የሄደችው።ጠብቃህ ነበር ይመጣል ብያት። አብረን ልንነግርህ ነበር ውሳኔያችንን።"

"የምን ውሳኔ?"

"ልንጋባ ነው"

"ውሸትክን ነው!" አለ ናትናኤል ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ወደፊት ፎቀቅ ብሎ። "አባቷን አሳመነቻቸው? ወይስ..."

"ምን ታሳምናቸዋለች... የደረቁ ሽማግሌ። አታምንም እንዴት እንደጠሏኋቸው።"

"እና ምን ይሁን ነው የሚሉት። ከሆነ በኋላ? "

"እ..እ... አንተ ስለማርገዟ ነው የምታወራው። እሳቸውን ስንለማመጥ ልጁ ሊወለድ ነው፣ አስበው እስቲ እራት ወር አለፈው ኮ ... ችኮ ሽማግሌ!"

"አትፍረድ አብርሃም...ሰውየውኮ ቅደም ተከተሉ ጠፍቷቸዋል። እንደነሱ ጊዜ ዛሬም እርግዝና ከጋብቻ በኋላ እየመሰላቸው ነውኮ ተደፈርኩ የሚሉት። ልጃቸው መሆኗን አትርሳ..."

"እና ምን ላድርግ ...ይቅርታ ጠየቅኩ! ሽማግሌ ላኩሁ!" አብርሃም እጆቹን አወናጨፈ።

"ታዲያ አባቷ ሳይስማሙ ነው ልትጋቡ የቆረጣችሁት?"

"አሁንማ እሺ አሉ። ስታስፈራራቸው፤ 'እምቢ ካልክ ያለሠርግ ቤቱ እገባለሁ' ስትላቸው ያኔ ጭንቅላታቸው መስራት ጀመረ" አለ አብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ ብሎ "ጥቅምት ላይ ልንጋባ ነው።"

"ተመስገን ነው!" አለ ናትናኤል ወደኋላ ደገፍ ብሎ እየተነፈሰ "ወንድ ሽማግሌ ናቸው ግን አራት ወር ሙሉ አቃዢሀ።" አለ ናትናኤል ፈገግ ብሎ።

"ትላንትኮ ደውዬ እነግረዋለሁ እያልኩ ሳስብ ነው ቀድመህ የደወልከው። አንተ!" አለ አብርሃም ድንገት ሌላ ትዝ ያለው ነገር እንዳለ ሁሉ "በነገራችን ላይ በስልክ ውስጥ እንዲያ ተዝናንተህ አታውራ።፡ አፍህን የምይዝበት መንገድ ጠፍቶኝ ነው አንጀ.. አየህ የኔ አካባቢ.. ማለቴ ሥራዬ ጥንቃቄ ይፈልጋል። ስልክ ጥሩ'ነባ ነው። ሁሉ ያዳምጠዋል። ደግሞስ ስለ ሞንሮቪያው አታሼ የማውቀው ነገር መኖሩን በምን አወቅህ?"

"ዝም ብዬ በግምት ነው። መቼም ፀረስለላ ውስጥ እየሰራህ አንዳንድ ነገር አታጣም።"

"ብቻ ለሁለተኛው ስልክ ይዘህ አትዝፈን።"

"ያወራነውኮ ምሥጢር አልነበረም። የሰውየው መሰወር ከማንም የተደበቀ አይደለም። የጠየኩህ ደግሞ የምታውቀው ነገር እንዳለ ነው። ይሄ ደግሞ ተራ ነገር ነው።"

"ናትናኤል..ነገሩ እንተ የምታስበውን ያህል ተራ ነገር አይመስለኝም። ብቻ እስቲ ቀጥል።" አብርሀም የሚያውቀውን ከመዘርዘሩ በፊት ጓደኛው የሚለውን መስማት መምረጡ ግልጽ ነበር።

"በቃ..ይኸው ነውኮ አብርሃም። ሰውዩው እንዴት ተሰወረ? ለምን ተሰወረ? ያንን ያንን ነው ለማወቅ የምፈልገው። ማለቴ... የምታውቀው በመሥሪያ ቤታችሁ በኩል የደረሳችሁበት ምሥጢር እንዳለ..." ናትናኤል ጓደኛውን ትኩር ብሎ ተመለከተው።

"ይኸው ነው?" የአብርሃም ድምፅ ማሾፍ የተቀላቀለበት ነበር።

"አየው አብርሃም..." ናትናኤል ነገሩን ከሥር መሠረቱ መጀመር እንዳለበት ተረዳ። "ባለፉት ወራት ከሰላሳ የሚበልጡ ወታደራዊ አታሼዎች ወደየአገሮቻቸው እየተጠሩ ሄደዋል፤ ይህ በራሱ ያልተለመደ ክስተት ነው። ባለፈው ሳምንት ደግሞ የጊኒና የሞሮኮ ወታደራዊ አታሼዎች ወደየአገሮቻቸው ሄደው በተመለሱ በጥቂት ቀናት ውስጥ ተገድለው ተገኙ። የሚገርምህ ነገር የሁለቱም አሟሟት ተመሳሳይ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ጉዳዩ ወይንም ጉዳዩቹ ግንኙነት ያላቸው ያስመስለዋል፤ ሊሆንም ይችላል። ይህ ሁሉ የነሰ ይመስል አሁን ደግሞ የላይቤሪያው አታሼ ድንገት ተሰወረ።"



"ስለዚህ ናትናኤል የጠፋ የሰው አገር ሰው ሊያፈላልግ ቤቱን ቆልፎ ወጣ! ለምን?" አብርሃም ጥርጣሬ የወረሰው መሰለ።

"አይደለም!" ናትናኤል በስጨት አለ። "የሰውየው መጥፋት አይደለም ያን ያህል ያሳሰበኝ። ነገር ግን የሰውየው መሰወር ባለፈው ሳምንት ከተገደሉት ሁለት ዲፕሎማቶችና ባለፉት ጥቂት ወራት ከተደረጉት የአፍሪካ አገር ኤምባሲዎች እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አለው ብዬ ስላመንኩኝ ነው። ይህ ብቻ አይደለም አብርሃም። በተለያዩ የአፍሪካ ባለሥልጣናት ላይ ባለፉት ወራት የደረሱ አደጋዎች አጋጣሚዎች ናቸው ማለት ይከብደኛል።"

አብርሃም ቁጎ ካለ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ የሲጋራ ፓኮ አንስቶ ለናትናኤል አንድ ሲጋራ ከጋበዘው በኋላ ለራሱም አንድ አወጣና በእርጋታ የለኮሳትን ሲጋራ ሁለቴ ስቦ ናትናኤልን ትኩር ብሎ ተመለከተው።

"ናትናኤል" አለ ድንገት። "በጣትህ ልትጠነቁለው የማይገባህን በክንድህ እየቦካህ ነው።"

"ምን ማለትህ ነው?"

"ምን እያደረግህ እንደሆነ አለቆችህ ያውቃሉ?"

"በደንብ። እንደውም አለቃዬ ናቸው ከዚህ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አንድ ወረቀት እንዳዘጋጅ የጠየቁኝ። እንቆቅልሹን እንድፈታው ይፈልጋሉ።"

ፈገግ አለ አብርሃም

"ናትናኤል...እንቆቅልሹን እንኳን አንተ ተከታትለህ የምትፈታው ዓይነት አይመስለኝም።"

"ለምን?" ናትናኤል አይኖቹን አጥብቦ ጓደኛውን ተመለከተው። "ሰውየው ሞቷል አይደል?"

"አልሞተም። ቢሞት ይቀል ነበር ለሁላችንም። ግን አልሞተም። አለመሞቱም ነው ሁሉን እረፍት የነሳው።" አለ አብርሃም የሲጋራውን ጭስ ከተናገራቸው ቃላት ጋር እየለቀቀው።

"አልገባኝም።" ናትናኤል ትዕግሥት አጣ።

"ናትናኤል...በተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ስለደረሱ አደጋዎች ለመተንተን በቂ መረጃ የለኝም። ወደኛዋ አዲስ አበባ ስንመለስ ደግሞ ቀደም ሲል የተለያዩ የአፍሪካ ኤምባሲዎች ለምን የወታደራዊ አታሼዎቻቸውን ወደየአገሮቻቸው እንደጠሩ አላውቅም። ባለፈው ሣምንት ስለሞቱትም የጊኒና የሞሮኮ አታሼዎች ቢሆን ከሬሳዎቻቸው አጠገብ ከተገኙት ቀለሆችና ጥይቶች ከፈጠሩት ቁስል ተነስተን ሁለቱንም ሰዎች የተገደሉበት መሣሪያ

በግብጽና በታንዛኒያ ውስጥ ከሚሠሩ ሁለት ተዛማጅ ባለ 7.ሚ.ሜ ሽጉጦች የተተኮሱ ናቸው ብለን ስላመንን ግድያዎቹ የተያያዙ ቢመስሉም ምክንያቱ ለኛም ገና ግልጽ አልሆነልንም:: ስለ ላይቤርያው አታሼ ግን መጠነኛ ዕውቀት አለኝ:: ቢሆንም የምነግርህ ሁሉን አይደለም:: የምነግርህም ቢሆን ላንተ እንጅ ለአለቃህ በምታቀርበው ሪፖርት ውስጥ የሚገባ አይደለም::"

ናትናኤል በመስማማት እራሱን ነቀነቀ::

"ሰውየው አዲስ አበባ በሚገኘው የላይቤርያ ኤምባሲ እንዲሰራ ተመድቦ ከመጣ ስድስት ዓመት ሆኖታል::" ናትናኤል በመስማማት ጭንቅላቱን ነቀነቀለት አብርሃም ቀጠለ:: "እና...ከሶስት አመታት በፊት ነበር ሰውየው የአገሩን ምሥጢር ለእንግሊዝ የስለላ ድርጅት አሳልፎ እንደሚሰጥ የደረስንበት:: በጊዜው የሚያስተላልፋቸውን መረጃዎች በመሃል እየጠለፍን እየቀዳን እናስተላልፍ ስለነበርና መረጃዎቹ ፀረ ኢትዮጵያ ገጽታ የሌላቸው መረጃዎች ስለነበሩ በተለይም ሰውየው በገዛ አገሩ ሁኔታ ላይ ያተከረ ስለነበረ ማስረጃዎች ብቻ እየሰበሰብን የምንጠቀምበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ በትዕግሥት መጠባበቅን መረጥን::"

"እንዴት ደረሳችሁበት?» ናትናኤል ጠየቀ አሳስችል ብሎት::

"የቅብብሎሹን ሠንሠለት መስበር ነው ዋናው ነገር:: አየህ ሰውየው ለጥቅም ሲል በገዛ አገሩ ላይ የሚሠልል ስለሆነ በአገሩ ኤምባሲ ውስጥ ከሚሰሩ የአገሩ ሰዎች ራሱን መጠበቅ ነበረበት:: ይህ ደግሞ በዙሪያው ባሉ ጥቂት ኢትዮጵያን ላይ እንዲደገፍ ገፋፍቶታል::" አብርሃም የጨረሰውን ሲጋራ በመተርኮሻው ውስጥ አጠፋና ንግግሩን ቀጠለ "እ..ና የሰረቀውን መረጃ ከቀረጥ ነፃ ከሆኑ ሱቆች በሚገዛቸው የውስኪ ጠርሙሶች ውስጥ እየደበቀ በኤምባሲው ውስጥ በሾፌርነት ለሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ያቀብላል:: በርካታ ዲፕሎማቶች ሕገወጥ ንግድ መፈጸማቸው የተለመደና ያደባባይ ምስጢር በመሆኑ ለሰውየው ጥሩ ከለላ ነበር::"

"ሾፌሩ ሁኔታውን አያውቅም?" ናትናኤል ጠየቀ

"ለእሱማ 'ውስኪ' ብሎ ነው ጠርሙሶቹን የሚሰጠው:: መረጃ እንደያዙ አይነግረውም:: ግን ሾፌሩ ያውቃል! ማወቅ ብቻ ሳይሆን የኛ ሰው ነው:: በሱ በኩል ነበር መረጃዎቹን የምንጠልፈው::"

"እ...ሽ." አለ ናትናኤል በመቀመጫው ላይ ወደፊት ፎቀቅ ብሎ እየተቀመጠ::



"እና ሹፌሩ የውስኪዎቹን ጠርሙሶች በታዘዘው መሠረት ወስዶ ቤላ የመጠጥ ቤት ላላት ሴት ያስረክባል:: እሷ ደግሞ የተለየ ምልክት ያለበትን መረጃ የያዘውን የውስኪ ጠርሙስ ለይታ ታስቀምጥና የእንግሊዝ ስለላ ሰዎች እንደመጡ ታስረክባለች::"

"ሴትየዋም ታውቃለች ማለት ነው?"

"አሳምራ:: ማወቅ ብቻ አይደለም ከዛም ታልፋለች:: አየህ ሴትየዋ ፈላሻ ነች:: ከጥቂት ዓመታት በፊት ኢትዮጵያና እሥራኤል የዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸውን እንዳደሱ በየጊዜው ፈላሾች የኢትዮጵያ አይሁድ እየተባሉ ወደ እሥራኤል እንዲሄዱ ተፈቅዶላቸው ስለነበር እሷም ወደ እስራኤል ሄዳ ነበር:: ነገር ግን ብዙ ሳትቆይ በአመቷ የእሥራኤል ፓስፖርቷን ይዛ ተመለሰችና ቤላ መጠጥ ቤት ከፍታ ተቀመጠች:: ስለዚህ ከላይቤርያው ሰላይ የምታገኘውን መረጃ ለእንግሊዙ ኤም.አይ. ስድስት. ከማሳለፏ በፊት የእሥራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ ሳያገኘው የሚቀር አይመስለኝም::"

"ታዲያ ምንድን ነበር የምትጠብቁት? አትይዙትም ነበር እጅ ከፍንጅ?" ናትናኤል ኮስተር አለ::

"ለምን? ምን አደረገና? አንድን ሰላይ ስለላ ስላካሄደ ብቻ ተንደርድረህ አትይዘውም:: በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስተላልፋቸው መረጃዎች ኢትዮጵያን የሚጠቅሱ አልነበሩም:: እርግጥ አልፎ አልፎ ብቻ አዎ ...ግን ጉዳት የሚያደርሱ አልነበሩም:: ሁለተኛ ነገር ሰውየው ሳንጠይቀው የሚያጎርፍልንን መረጃ የእሱንም መኖር እንፈልገዋለን:: አየህ እሱን ማስያዝ ወይም መያዝ ማለት የምትታለብ ላምህን አርደህ መብላት ማለት ነው ገና ብዙ ልታልብት ስትችል::"

"እሺ. በል ቀጥል::" አለ ናትናኤል ሁኔታው ከጠበቀው በላይ እየተወሳሰበበት ሲመጣ ዝም ብሎ ማዳመጡን መርጦ::

"እንዳልኩህ ሁኔታውን መሃል ላይ በሰነቀርነው ሾፌር አማካኝነት እየተከታተልን ተጠባብቀን:: ታዲያ ባለፈው ወር አታሼው ወደ አገሩ ሲጠራ ተጋልጦ እንደሆን ብለን ስጋተን ስለነበር ብዙ ጥያቄዎች ተከተሉ:: አንደኛ በሰውየው ምትክ ሌላ ሰው ከተተካ የእሱ ጠቃሚነት ሊቀር ሆነ:: በግልጽ ካስፈራራነው ደግሞ ምናልባት ተመልሶ ቢመጣ እንኳን ለመለመሉት የእንግሊዝ ሰዎች መጋለጡን ስለሚያሳውቅ አሁንም ጠቃሚነቱ ሊደርቅ ነው:: ከብዙ ውጣ ውረድና ክርክር በኋላ ሰውየውን ቀርበን ላለማነጋገርና ከተመለሰ ሥራችንን እንደቀድሞው ለመቀጠል አገሩ እንደሄደ ከቀረም ሞኖሮቪያ ባሉ የኛ ሰዎች አማካኝነት ቀርበን ስለፈጸመው ወንጀል የምናውቅ መሆናችንን ገልጸን ግንኙነታችንን በማስገደድና በማስፈራራትም ቢሆን ለመቀጠል ወሰንን::"

"ለምንድነው ግንኙነቱን የፈለጋችሁት? ከሄደ ሄደ፤ ግልግል...!" ናትናኤል ጠየቀ።

"የቱን ግንኙነት?"
"ከሰውጋ ያላችሁን ነዋ ከላይቤርያው አታሼ?"

"እህ... " ተገረመ አብርሃም። "ይጠቅመናላ። ሰውየውን መዳፋችን ውስጥ ማቆየታችን። አየህ...የአንድን የሰላ ድርጅት ወኪል በስውርም ሆነ በማስገደድ ተቆጣጠርከው ማለት በኋላው ያለውን የሰላ ድርጅት በተወሰነ ደረጃ ተቆጣጠርከው ማለት ነው። ጆሴፍ ካልቨርትን፤ በነገራችን ላይ ስሙ 'ካልቨርት' ነው፤ እና ካልቨርትን ተቆጣጠርን ማለት ስለሞንሮቪያ ሊሰጠን የሚችለውን ሁሉ ከማግኘታችን በተጨማሪ የእንግሊዝን ኤም.አይ.ስድስት ምናልባትም የእሥራኤልን ሞሳድ እንቅስቃሴ ጫፍ ያዝን ማለት ነው።"

"ገባኝ...ገባኝ።" ናትናኤል ራሱን በመስማማት እየነቀነቀ ሰዓቱን ተመለከተ - ስድስት ሰዓት ከአሥር። "አብርሃም ለምን ወጥተን ምሳችንን እየበላን አንጫወትም? "

"ጥሩ።" አለ አብርሃም ከመቀመጫው እየተነሣ።

ከቤት ወጥተን በናትናኤል መኪና ከግቢ ሲወጡ አብርሃም የመኪናውን መስኮት ዝቅ አደረገና-

"የሚፈልገኝ ሰው ከደወለ ነጋውን እየታጠበ ነው በይ ወጥቷል አትበይ።" አላት የግቢውን መዝጊያ ከፍታ የያዘችውን ሠራተኛ።

"እሺ." አለች የግቢውን በር በሁለት እጆቿ እንደያዘች።

* * *

ናትናኤልና አብርሃም ከግቢ እንደወጡ የአብረሃም ሠራተኛ የግቢውን በር ዘግታ በጥድፊያ ወደ ዋናው ቤት ተመለሰች። ወደ መኝታ ክፍሏ ገብታ አነስተኛ ሻንጣ መሰል የሬዲዮ መልዕክት ማስተላለፊያ መሣሪያዋን ከፈተችት...ቲ...ቲቲ... ሃሎ... ሃሎ..ቲቲ..ቲ ቲቲ..ቲ.. ቲቲ..ቲ ሃሎ... ሃሎ ቆንጆዎቹ...ቡድን 'ረ'... ዜሮ ሶስት... ስድስት ሰዓት ከአስራሶስት... ናትናኤል ከሚባል ሰው ጋር ወጥቷል። ከአምስት ከሃያ ጀምረው ሲያወሩ ነው የቆዩት። ቅጅውን በሰዓቱ እልካለሁ... ጨርሻለሁ።" የሬዲዮ ማስተላለፊዋን ዘግታ ከቦታው መልሳ ወደ ሳሎኑ ክፍል ተጣደፈች ጥግ



ወዳለው አረንጓዴ ሶፋ ሄደችና በርከክ ብላ ከወንበሩ ስር አነስተኛ የድምፅ መቅጃ አውጥታ ወደ መኝታ ቤቷ ተመለሰች።

* * *

ናትናኤልና አብርሃም ከልደታ ተነስተው ሜክሲኮ አደባባይ እስኪደርሱ አልተነጋገሩም። ፖሊስ ሆስፒታልን አለፍ እንዳሉ አብርሃም የኋላ መመልከቻ መስተዋቱን ወደ ራሱ እያስተካከለ

"ብጠቀምበት ይከፋሃል? " አለ።
"ለምን? ምን ይሠራልሃል? " አለ ናትናኤል ጓደኛውን ሳንዳፍታ ተመልክቶ።

"የመረጃው መሥሪያ ቤት አባል ከሆንኩ ጀምሮ የምሄድበትን ብቻ ሳይሆን የመጣሁበትንም መንገድ መመልከት ተምሬአለሁ" አለ አብርሃም እየሳቀ "እንደ አሣ።"

"እንዴት? ምኑን ታየዋለህ የመጣህበትን መንገድ?" ናትናኤል የጓደኛው ነገረ ሥራ ሁሉ አለወትሮው ግራ የሚያጋባ ሆነበት።

አብርሃም አልተመለሰም። ብቻ ፈገግ አለ - ፈገግ። አይኖቹ ግን ገና ከቤት ሲወጡ ራቅ ብሎ ከመንገድ ዳር ቆሞ በነበረው በኋላም በሩቅ እርቀት በሚከተላቸው ነጭ ሲትሮይን መኪና ላይ ነበሩ።

ሜክሲኮ አደባባይን ዞረው ወደ ብሔራዊ ትያትር ሲያቀኑ አብርሃም አሁንም በኋላ መመልከቻው መስታወት ተመለከተ። ነጩ ሲትሮይን በተመጣጣኝ ርቀት ተከትሏቸዋል። ናትናኤል መኪናውን ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ለማቆም በረድ ሲያደርግ

"ቀጥል-ቀጥል ናትናኤል ትንሽ ዞር ዞር እንበል። መቀመጡ ሰልችቶኛል።" አለ አብርሃም አይኖቹን ከኋላ ከሚከታተላቸው ነጭ ሲትሮይን ላይ ሳይነቅል።

"በል ቀጥልልኝ እንጂ።" አለ ናትናኤል ጓደኛውን ዞር ብሎ እየተመለከተ።

"እ..?...እ..." አብርሃም ልቡ ሌላ ቦታ የሄደ መሰለ። "አዎ... ምን ብዬ ነበር ያቆምኩት? እ... "

"ሰውየው ወደ አገሩ ተጠራ' ብለህ ነበር::" አለ ናትናኤል ቀልጠፍ ብሎ::

"እ...አዎ... እና ሰውየው ወደ አገሩ ሲጠራ እንዳልኩህ ፈርተን ነበር:: ግን ብዙም ሳይቆይ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ መደበኛ ሥራውን ቀጠለ:: እኛም እንደወትሮው ክትትላችንን ተያያዝነው:: ሆኖም አንድ አዲስ ነገር ተፈጠረ:: ሰውየው እንደበፊቱ መረጃዎችን በውስኪ ጠርሙሶች ውስጥ እየደበቀ ማስተላለፉን ትቶ በተደጋጋሚ በሚከራያቸው የሆቴል ክፍሎች ውስጥ ከእንግሊዝ የስለላ ሰዎች ጋር በቀጥታ መገናኘቱን ተያያዘ::"

"ከሰዎቹ ጋር በቀጥታ መገናኘቱ ለእርሱ አደገኛ አይሆንም? " ናትናኤል በመገረም ጠየቀ

"ለእኛም አንቀቅልሽ የሆነብን ይህ ነበር:: ለወትሮው ጠንቃቃ የነበረ ሰው መንቀዥቀዥ አበዛ:: አልፎ ተርፎ በስልክ ቀጠሮ እስከመለዋወጥ ደረሰ:: አንድ ዓይነት ጭንቀት ውስጥ እንደ ወደቀ ከሁኔታው ለመረዳት ከባድ አልነበረም:: አለቅጥ መጠጣቱም ሌላ አዲስ ፀባዩ ነበር:: መሽ አልመሸ ብሎ ቤቱ ይገባ የነበረ ሰው ከዛንቺስ አንድ ሆቴል ካላት ወዳጁ ቤት ሲጠጣ አምሽቶ እዛው ያድር ጀመር:: ሁኔታው ግራ አጋብቶን ይበልጥ ተደራጅተን ሁኔታውን ስመከታተል ስንዘጋጅ ድንገት ተሰወረ:: አብርሃም ከደረት ኪሱ ሲጋራ አውጥቶ አፉ ውስጥ ሻጠና ለናትናኤል እየጋበዘው የመኪናውን የሲጋራ ማያያዣ ተጫነው::"

"በቃ?!" አለ ናትናኤል አብርሃም ከዘረጋለት የሲጋራ ፓኮ ውስጥ አንድ ሲጋራ መዞ አፉ ውስጥ እየሰካ::

"በቃ::" አብርሃም ፍም በመሰለው የሲጋራ መለኮሻ ሲጋራውን እየለኮሰ በኋላ መመልከቻው መስታወት ውስጥ ተመለከተ:: ነጩ ሲትሮን አሁንም እየተከተላቸው ነው::

"እና ተሰወረ ብላችሁ ተዋችሁት ማለት ነው ናትናኤል አብርሃም ባቀበለው እሳት ሲጋራውን እየቀጣጠለ ተገርሞ ጠየቀ::"

"የነገሩን ክብደት ይበልጥ እየተረዳን የመጣነው እጅግ ዘግይቶ ነበር::" አለ አብርሃም በረጅሙ ተንፍሶ::

"እንዴት?"ናትናኤል ትዕግሥት አጣ::

"ቆይ...እየነገርኩህኮ ነው:: ሰውየው እንደተሰወረ በመጀመሪያ 'ሞቷል' ማለቱ 'ተገድሏል' የሚለው መላምት ነበር ጠንክሮ የታየን:: ስለዚህ በተለይ ማን ሊገድለው ይችላል በሚለው ጥያቄ ላይ አተኮርን:: የሱንም



ጉዳይ ቀደም ሲሉ ተገድለው ከተገኙት ከጊኒና ከሞሮኮ ወታደራዊ አታሼዎች ጋር ደመርነው::"

"አልሞተም... አይደል?" ናትናኤል ፊቱን መልሶ ጠየቀ::
"አልሞተም::" አብርሃም ሲጋራውን ማግ አድርጎ ጭሱን በረጅሙ ለቀቀው::
"እንዴት? ምን ማረጋገጫ አገኛችሁ?"
"እዛው አካባቢ ያለ ወኪላችን አየው::"
"የት?"
"ከዛንቺስ ከወዳጁ ቤት የሴት ልብስ ለብሶ ድሪያ ተከናንቦ በስርቆሽ በር ሲወጣ አየው::"
"ከዛስ?" ናትናኤል መኪናውን በቸርችል ሽቅብ እያሽከረከረ ጠየቀው::

"ወኪላችን ሪፖርቱን እንዳቀረበ ሰዎች አሰማርተን ሃያ አራት ሰዓት አካባቢውን መከታተል ያዝን:: እሱን ብቻ ሳይሆን ወዳጁንና መጠጥ ቤቱ ውስጥ የሚሰሩትን ሁሉ አንድም ሳይቀር የማያቋርጥ ክትትል እናደርግባቸው ጀመር::"
"እ...ሺ::"

"ያለማቋረጥ ለሣምንት ያህል ስንከታተል ቆየን:: ግን ምንም ፍንጭ ማግኘት አልቻልንም:: ሆኖም ሰውየው አለመሞቱን ሁላችንም ተማምነንበት ስለነበር ክትትላችንን ለማጠናከር ወሰንን:: ያን ጊዜ ድንገት ክትትሉን እንድናቋርጥና ሰውየው ስለመሞቱ የሚገልጽ ሪፖርት እንድናቀርብ ከበላይ ታዘዝን::"

"ሰውየው ሳይሞት?"
"ያ ነውኮ የሚገርምህ:: ሁኔታውን ለማስረዳት ብንሞክርም ትዕዛዙ በድጋሚ ከማስጠንቀቂያ ጋር ተላለፈልን:: ለጊዜው ጭቅጭቅ መፍጠር ስላልፈለግን የተጠየቅነውን ሪፖርት አስተላለፍን::"

"ሞተ ብላችሁ?!"
"የፈለጉት እሱን ነዋ!...ሞተ ብለን አስተላለፍን:: ግን የሚያሳዝን ሌላ ስህተት ፈጸምን::"
"ምን?"

"ሞቷል የሚለውን ሪፖርት ካስተላለፍን በኋላ በግላችን ሁለት ሰዎች ክትትሉን እንዲቀጥሉ አሰማራን::" አለ አብርሃም በኋላ

መመልከቻውን መስተዋት እየተመለከተ:: ሲትሮይን ተከትላቸዋለች:: ፈገግ አለ::

"እና ስህተቱ ምኑ ላይ ነው?" ናትናኤል ጠየቀው::

"ሁለቱን የክትትል ሰዎች ባሰማራን በሰስተኛው ቀን አንደኛው ሰዋችን በስለት ታርዶ እዛው ካዛንችስ ቱቦ ውስጥ ተጥሎ ተገኘ::

ናትናኤል በድንጋጤ ፊቱን አጨማዶ ጓደኛውን ተመለከተው::

"ሰዋችንን አርዶ የጣለው ሰው ወይም ቡድን ማን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንልንም ግድያው ከክትትሉ ጋር የተያያዘ እንደነበረ ስለተረዳን ያሰማራነውን ሁለተኛ ሰው ክትትሉን በፍጥነት እንዲያቋርጥ አደረግን::"

"እሺ::" ናትናኤል ፊቱን እንዳጨማደደ ጓደኛው ፊት ላይ አፍጥጦ ቀረ::

"እያየህ ንዳ እንዳንጋጭ:: በቃ ይኸው ነው::" አለ አብርሃም ሌላ ሲጋራ ባለቀች ሲጋራው እያያያዘ::

"እና በቃ ተዋችሁት.... ተዋችሁት? የገዛ ሠራተኛችሁ ተገድሎ!"
"አንተ ብትሆን ምን ውሣኔ ትሰጥ ነበር?"
"ሰው ጨምሮ መከታተል ነዋ!"ናትናኤል በስጨት አለ::
"በማን ትዕዛዝ? በገዛ ራስህ?" አብርሃም የብስጭት ሳቅ ሳቀ::
"ሁኔታውን በሚገባ የተረዳነው አይመስለኝም እንጅ ናትናኤል በእሳት እየተጫወትን ነው:: የተሻለው ምርጫ ምን እንደሆነ ልንገርህ?"

"ምንድነው?"

"መተው ነው:: አንተንም የምመክርህ ነገር ቢኖር ይህን ነገር ማነፍነፍህን ትተህ በሰላም ስራህን እንድትሠራ ነው:: የተለመደው ግትርነትና ቅልጥፍና እዚህ ላይ የሚጠቅምህ አይመስለኝም::"

"አብርሃም እየሰራሁ ያለሁትኮ ሥራዬን ነው:: አንተ ነገሩን አርግፍ አድርገህ ልትተው የወሰንከውኮ አለቆችህ ስላስፈራሩህ ነው:: የኔ አለቃ ግን የሚገፋፋኝ ፍሬ ያለው ነገር ይገኝ እንድመለስ ነው:: ገባህ?"

"እንግዲያው አለቃህም እንዳንተ አይናቸው ተሸብቧል::"



"ማነው አይናችንን የሸበበው?" ናትናኤል የጓደኛውን አነጋገር አልወደደውም::

አብርሃም አልመለሰለትም:: አይኖቹን በኋላ መመልከቻው መስተዋት ላይ ተክሎ ፈገግ አለ:: ነጯ ሲትሮይን...

"ናትናኤል እውነቱን ልንገርህ?...በጣም ነው የራበኝ እጋብዝሃለሁ ያልከኝ ምሳ እንደ ሰማዩ ነው የራቀኝ::"

-6-

የተወለደው መሃል መርካቶ ነው:: የት እንዳደገ ለመናገር ግን እሱም ይቸገራል:: በተወለደ በዓመቱ አባቱ ሲሞቱ እናቱ የአራት አመት ታላቅ ወንድሙንና እሱን ይዘው ቤተሰቦቻቸው ጋ ደብረማርቆስ ገቡ:: ማርቆስ ብለው ስም ያወጡለትም እዚያው የነበሩት ሴት አያቱ ነበሩ::ወላጅ እናቱም ብዙ ሳይቆዩ የአምስት ዓመት ልጅ ሳለ ሞቱበት:: አዲስ አበባ የነበሩት የእናቱ ታላቅ ወንድም እሱንና ወንድሙን መልሰው አዲስ አበባ ሊያሳድጓቸው ወሰዷቸው:: እኚሁ አጎቱ በስድስተኛው አመት በሥራ ተቀይረው ወደ ድሬዳዋ ሲሄዱ እሱና ወንድሙም ተከተሉ:: ያኔ አስራ አንደኛ አመቱን ይዞ ነበር::

አጎቱ አምስት ዓመታት ድሬዳዋ ውስጥ አገልግለው በጡረታ ሲገለሉ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ - ወንድማማቾቹን ይዘው:: የተከተሉትን ሶስት አመታት አዲስ አበባ ውስጥ ቆየና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በአስራዘጠኝ አመቱ ሐረር ሄዶ የጦር መኮንንነት ስልጠናውን ጀመረ:: ያን ጊዜ ታላቅ ወንድሙ በዚያን ጊዜው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሁለተኛ ዓመት የህግ ተማሪ ነበር::

ማርቆስ በትምህርቱ እጅግ ጥሩ ውጤት እንደነበረው የሚያውቁ ሁሉ ትምህርቱን ዩኒቨርስቲ ገብቶ እንዲቀጥል ቢገፋፉትም የእርሱ ምርጫ ሌላ ነበር:: አጎቱ ወታደር ይሁን አስተማሪ፤ ዳኛ ይሁን አናጢ ግድ አልነበራቸውም:: ዋናው ነገር ሥራ ይዞ ራሱን መቻሉ ነበር የሚያሳስባቸው:: ያ ነበር በሰማይ ቤት የሚያስጠይቃቸው::

በሐረር የጦር ትምህርት ቤት የወታደራዊና የቀለም ትምህርቱን በከፍተኛ ማዕረግ አገባደደ:: በመጀመሪያ ማስተማር ልቡ ባይፈቅደውም ተሰጥኦውን የተገነዘቡ መምህራኑና የማሰልጠኛው ባለሥልጣን አባብለውትና ገፋፍተውት በተማረበት ማሰልጠኛ ረዳት መምህር አድርገው ቀጠሩት:: አመቱ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ከሰለሞን ሥርወ መንግሥት ሥልጣን ለመረከብ ሽርጉድ የሚልበት፤ ተማሪዎችና ምሁራን ሠራዊቱን የጎሪጥ እያዩ በፊንታቸው ወገባቸውን ያጠባበቁበት፤ በዙሃኑ ኢትዮጵያዊ በመጪው

ሶሻሊስታዊ ገነት በአንድ ምሽት ባለመኪናና ባለቤት ሊሆን ተስፋ ያደረገበት፤ አለም ፊቷን ወደ ኢትዮጵያ መልሳ ትንፋሽዋን የያዘችበት ዓመት ነበር- 1966 በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር::

በተከተሉት አራት አመታት ውስጥ በሕይወቱ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ አንኳሮች ተከታትለው አለፉ:: ሚስት አገባ:: በአመቱ ወንድ ልጅ ወለደ:: በ1978 ሙሉ ኮለኔል ሆነ:: በ1981 ጥር ላይ 'ጋሼ' እያለ የሚጠራቸው እንደ አባት ያሳደጉት አጎቱ ሞቱ:: በዛው ዓመት ግንቦት በኢትዮጵያ ተደርጎ በነበረው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ውስጥ እጁ ገባ! ሁሉ ነገር አበቃ::

በመንግሥት ግልበጣ ንቅናቄ ውስጥ የገባው በአንድ ወቅት አስተማሪው በነበረው በኋላም በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ አለቃው ሆኖ በሠራው ብርጋድዬር ጀነራል አብይ ሰናይ ገፋፊነት ነበር:: የሃሣቡን ትክክለኛነት ከጅምሩ ቢቀበለውም የግልበጣው ተካፋይ ለመሆን ብዙም አልዳዳውም:: ሆኖም ከሁለት ወር የአለቃው ውትወታ በኋላ ከጊዜው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እራሱን ማግለል እንደማይችል በመረዳት ራሱን ሰጠ:: በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ የመንግሥት ግልበጣው ቀንደኛ ተዋንያን ከነበሩት መሃል ራሱን አገኘው::

በወቅቱ በአዲስ አበባና በአሥመራ ተራርቀው የነበሩት የመፈንቅለ መንግሥቱ ጠንሳሾች ተከታታይ ዕቅዶችን እያወጡ በተለያዩ ሳንካዎች የተወጠነው መፈንቅለ መንግሥት ቢዘገይም በመጨረሻ ግንቦት ላይ አብዛኛው ኢትጵያዊ ሳያስብና ሳይገምት ከብሪቱ ተጫረ::

ከጅምሩ የተወለካከፈው መፈንቅለ መንግሥት በአሥመራ ለቀናት በአዲስ አበባ ደግሞ ለሰዓታት ሲንገዳገድ ቢቆይም ኮለኔል ማርቆስ ዕቅዱ መክሸፉን የተረዳው ገና ጠዋት በአምስት ሰዓት አብዛኛዎቹ የመንፈንቅለ መንግሥት ጠንሳሽ ጀነራሎች በመሀል አዲስ አበባ መከላከያ ሚኒስቴር ቅጥር ግቢ ውስጥ በተሰበሰቡበት በታማኝ የመንግሥት ሃይሎች በታንክ ሲከበቡና የአንዳንድ የንቅናቄውን አባላት ክህደት እንደተረዳ ነበር::

ጊዜ አላጠፋም:: ከበባው ከመግጠሙ በፊት ከግቢው ሾልክ ብሎ ወጣ:: ከዚያ በኋላ ያደረገው ግን ለእርሱ ለራሱም እንቆቅልሽ ነው:: እጁ ንጹህ እንደሆነ ሁሉ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲቀመጥ በእርግጥ እተርፋለሁ ብሎ እንዳልነበር ግልጽ ነበር:: ባለቤቱንና ልጁን ትቶ ጨክኖ ከአገር ለመጥፋት ቢሞክር ምናልባት ይሳካለት ነበር:: ኮሎኔል ግን ያንን አልመረጠም:: ከቤቱ ተመልሶ ይጠብቀኛል ብሎ የፈራውን ስቃይና ውርደት ላለመቀበል በምትኩ የመጨረሻውን መራራ ጽዋ ለመጨለጥ ወሰነ::

ማዕረጉን ገፈው ስሙን በድምጽ ማጉያ እየጠሩ ወጥቶ እጁን እንዲሰጥ ያለበለዚያ ግን እንደሚደመሰስ ሲዝቱ ከቆዩ በኋላ ከምሽቱ ለሁለት ሰዓት ሃያ ጉዳይ ላይ መጠነኛ የሽፋን ተኩስ አስቀድመው የግቢውን የአጥር



በር ገርስሰው ከሰፊ ግቢው ሲፈሱ ዙሪያው በአንድ አፍታ በፈንጅ ነበልባል ጋየ:: በተኩሱ ልውውጥ ሚስቱና ልጁ ተገደሉ:: ራሱን ለመግደል ሞክሮ ቆሰለና ተያዘ::

እራሱን ሲያውቅ ሆስፒታል አልጋ ላይ ነበር:: ግማሽ ፊቱ በፕላስተር ታሽጓል:: ሁኔታውን ሲያገናዝብ መልሶ ራሱን ሳተ:: የዚያ ቁስል ውጤት ፊቱ ላይ ጠባሳ ትቶበት አልፏል::

ከሃኪም ቤት እንደወጣ ወደእስር ቤት ወሰዱት:: ግድ አልነበረውም:: በ1983 ግንቦት ላይ የመንግሥት ለውጥ ሲደረግ ከእሥር ቤት ተፈቶ ካናዳ ሄደ::

ካናዳ ከወንድሙና ከሜክሲካዊ ሚስቱ ጋር የቆየው ለአራት ወራት ነው:: በአራተኛው ወር በአንድ የህፃናት ሆስፒታል በአፀድነት ተቀጥሮ ሁለት ክፍል አፓርታማ ተከራይቶ ወጣ:: የአፀድነት ሥራውን ያልወደደለት ወንድሙ ታክሲ ገዝቶ ሊሰጠው ቢጠይቀውም ማርቆስ ፈቃደኛ አልነበረም:: ለእርሱ ሕይወት እራሷ ትርጉም አልነበራትም:: ማግኘትና ማደግ ሃብትና ክብር ለእሱ የቁል ጌጦች ነበሩ:: በዛን ወቅት የእርሱ ምኞት ያለፈውን ሁሉ ባለበት ትቶ የተቀሩትን ዓመታት በአንድ የዓለም ጥግ ድምጽ ሳይሰማ ማሳለፍና ድምፅ ሳያሰማ ማለፍ ነበር:: ሩጫና ትግል ለእሱ የተሰበረ መንፈስ የሚመች አልነበረም:: ያንን ነበር የፈለገው ጸጥታ::

ካናዳ በገባ በሁለተኛው ዓመት ከአዲስ አበባ ቀንስቶ እሱን ፈልጎ እቤቱ ድረስ የመጣው እንግዳ ግን ይዞለት የመጣው ጸጥታ አልነበረም::

ማርቆስ የሁለት ክፍል አፓርትመንቱን የተሳሳጠ የእንጨት በር ከፍቶ ሲመለከት ከመተሳለፊያው ላይ ቆሞ የሚያየው ሰው በቅዠቱ እንደሆነ አልተጠራጠረም:: እንግዳው "ማርቆስ" ብሎ በተከፈተው በር ገብቶ አቅፎ ሲስመው ሁኔታን እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ተቸገረ::

በ1981 የመፈንቅለ መንግሥት ጠንሳሾች መሃል ከመደገፍ ከመታሰርና ከሞት ካመለጡት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች መሃል የነበረ እራሱን አለቃ ብርጋዴል ጀነራል አብይ ሰናይን በሆች ትንሽ ክፍሉ ሲያየው ማመን አቃተው::

ያለፉትን በርካታ ዓመታት በስደት ያሳለፈው አለቃው ከእርሱ በእጅጉ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዳለ ግልጽ ነበር:: አለቃው ዞር ዞር ብሎ የማርቆስን የተሳሳጠች፤ የተጋጋጠች ክፍል አዩና "እዚህ ነው የምትኖረው...?" አለ የተሻለ ነገር መናገር ያቃተው ይመስል፤ ድንገት እንባ ያቀረሩትን አይኖቹን በማርቆስ ላይ ተክሎ:: ለአንድ አፍታ ሳይናገር በገዝምታ የቆመውን ማርቆስን ትክ ብሎ ሲመለከት ቆየና የጠፋ ወንድሙን እንዳገኘ ሁሉ መልሶ ተጠመጠመበት::

ለሰዓታት ቀጭ ብለው አወጉ:: በመጨረሻ ብርጋድየር ጀነራሉ እሱን ፍለጋ እስከ አሰም ጥግ የተጓዘበትን ምክንያት ሲገልጽለት ማርቆስ ፈገግ ብሎ ተመለከተው::

"ጀነራል እኔ እኮ ሙት ነኝ::" አለ ማርቆስ ባጭሩ::

"ማርቆስ አድምጠኝ" አለ ጀነራሉ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከማርቆስ ጎን እየተቀመጠ:: "እያንዳንዳችን የምንወዳቸውን አጥተናል:: እርግጥ በአሳዛኝ አጋጣሚ ውስጥ እንዳለፍክ ይገባኛል! ግን ለሆነው ነገር እራስህን ተጠያቂ ማድረግ የለብህም..."

የተከተሉት ሶስት ሳምንታት ኮሎኔል ማርቆስ ከቀፎው ላለመውጣት ብርጋድዬር ጀነራሉ ደግሞ ቀፎውን ለማፈራረስ ሲታገሉ ቆዩ:: በመጨረሻ ማርቆስ ለሁለተኛ ጊዜ ተሸነፈ::

"ነገርኩህ ማርቆስ...ይህች ዓለም መጥፎም ጥሩም የምትሆነው በእኛ ተግባር ነው:: የተሳሳተ ነገር ካለ ያንን የማስተካከል ኃላፊነት የኛው ነው:: ሌላ ማን ይደርስልናል...?"

"ከእኔ የሚጠበቀው ምንድነው?" አለ ማርቆስ አለቃውን አቋርጦት::

"ወደ አዲስ አበባ ትመለሳለህ:: ለጊዜው በአፍሪካ ሠላም አስከባሪ ግብረኃይል የምሥራቅ አፍሪካ ክንፍ የቡድን - ለ ወታደራዊ ደህንነት ኃላፊ ሆኜ ነው የምሠራው:: ረዳቴ እንድትሆን ነው የምፈልገው::"

በሁለተኛው ወር አዲስ አበባ ተመለሰ፤ ማርቆስ::

የአፖርታማው የፊት በር ሲንኳኳ የመታጠቢያ ቤቱን መብራት አጠፋና ወደ ሳሎን ገባ:: ከጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ሽጉጥ አንስቶ ወደ በሩ ሄዶ ቁልፉን አዙሮ በሩን በቀጭኑ ከፍቶ ተመለከተ::

ፒተር ነበር:: ፒተር አዱዋ በአንድ ወቅት በኬንያ መንግሥት ወታደራዊ ደህንነት ውስጥ የነበረና በአሁኑ ወቅት ለኮሎኔል ማርቆስ በረዳትነት የተመደበ፤ የቁመቱ እርዝመትና የትከሻው ስፋት አስፈሪ ገጽታ የሰጠው ሰው ነው::

"ሰዓቱ ደርሷል..." አለ ፒተር እጆቹን ከለበሰው ረጅም የሸራ የዝናብ ልብስ ኪሶች ውስጥ እንደከተተ፤ ጥያቄ ይሁን ዓረፍተ ነገር ባልለየ አነጋገር::



"ጨርሻለሁ::" አለ ማርቆስ:: ወደ ሳሎኑ ተመልሶ ጥቁር የቆዳ ጃኬቱን አጠለቀና ሽጉጡን በጀርባው ሽጦ ፒተርን ተከትሎ ከክፍሉ ወጣ::

"የመጀመሪያውን አሳ እግኝተውታል::" አለ ፒተር ከፊት ለፊት የአፓርታማውን ደረጃ እየወረደ::

ማርቆስ መልስ ሳይመልስ ሰዓቱን ተመለከተ:: ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ይላል ሰዓቱ:: በረጅሙ ተነፈሰና ምንም ሳይናገር ፒተርን ተከተለው:: የአፓርትመንቱን የፊት በር ከመውጣታቸው በፊት ብን ብን የሚለውን ዝናብ ሲመለከት የቆዳ ኮቱን ኮሌታ ወደላይ ቀለበሰና ሲጋራ ፍለጋ የደረት ኪሱ ውስጥ ገባ::

ሀሲናው ሊያርፍለት አልቻለም:: በሱ አመለካከት ግድያውን መፈጸም ፍጹም ወቅታዊ አይደለም::

"ይቅርታ አድርጉልኝና... ለጊዜው የውጭ ጉዳዩ ሰው መገደል ቢዘገይ እመርጣለሁ" ነበር ያለው:: በዛኑ ቀን ከሰዓት በአሥር ሰዓት ላይ በተደረገው የምሥራቅ አፍሪካ ደህንነት ቡድን ስብሰባ ሁለት ሪፖርቶች ከቀረቡ በኋላ ኮሎኔል ሃሳቡን ሲሰጥ:: በክፍሉ ውስጥ የተሰበሰቡት ባለሥጣናት ለአንድ አፍታ ከራሳቸው ጋር ሙግት ያዙ:: ወዲያው በስተቀኝ የተቀመጠው የአጥቂ ስለላ ኃላፊ የሆነው የኬንያው ሰው ዣክ ዊልያም የያዘውን እስክሪፕቶ በፊቱ ካለው ፋይል ላይ አስቀመጠና "ጥያቄው ነው" አለ በተቀመጠበት ወንበር ላይ ወደኋላ እየተደገፈ "ጥያቄውኮ የመረጃው ቤት ሰው ለውጭ ጉዳዩ ምን ያህሉን ምስጢር ገልጾለታል የሚለው ነው:: እኔ የምፈራው የሚያውቀውን ሁሉ ዘክዝኮለት ከሆነ ማንኛቸውንም ቢሆን ማቆየቱ በኋላ ልናርመው ከማንችለው ስህተት ውስጥ ይከተናል ብዬ ነው::"

"ከቤት ከመውጣታቸው በፊት..." አለ በስተግራ የተቀመጠው ሩዋንዳዊ ሻለቃ አንድሬ አማሪ:: በንቅናቄው የእዝ ሠንሠለት ከብርጋዴር ጀነራል አብይ ሰናይ ቀጥሎ የቡድን -ለ የፀጥታ ክፍልን የሚመራ ሰው ነው:: "...የቲነጋገሩት ቅጅ ነው ለጊዜው በእጃችን የሚገኘው:: ቢሆንም ከዝርዝር ነጥቦች አገነባቡ ስንሰሳ እያንዳንዱን ነጥብ ዘክዝኮ ሳይነግረው የሚቀር አይመስለኝም:: ሆኖም ኮሎኔል ማርቆስ እንዳለው ለጊዜው የመረጃው ሰው ብቻ እንዲወገድ ተደርጎ የውጭ ጉዳዩን ሰው በቋሚ ክትትል..."

"እዚህ ላይ ተቃውሞ አለኝ!" አለ ኬንያዊው ዣክ ዊልያም "ስላቋረጥኩህ ይቅርታ አድርግልኝ:: ነገር ግን እያንዳንዳችሁ ልትገነዘቡት የሚገባችሁ ነጥብ ስህተት ለመፈጸም ጊዜ እንደሌለን ነው::"

ክርክሩ ለበርካታ ደቂቃዎች ቢካሄድም የመጨረሻው ውሣኔ የኮሎኔልን ሀሊና የረበሸ ነበር።

"ጥሩ..." አለ ብርጋዴር ጄነራል አብይ ሰናይ "ዝርዝር ነጥቦችን አንስተን የተከራከርን ይመስለኛል። ሆኖም ከኮሎኔል በስተቀር የቀረነው የተስማማንበት ነጥብ የሁለቱም ሰዎች መወገድ ምናልባት ዘግይቶ ሊጸጽተን ከሚችል ስህተት ሊያድነን እንደሚችል ነው። የመረጃው ሰው ካዘንቺስ ያለችውን ሴት ለማግኘት መሞከሩ በራሱ ሰውየው ምን ያህል አደገኛ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይ ነው። የውጭ ጉዳዩን ሰው በተመለከተ ምንም እንኳን ሰውየው ጠለቅ ያለ እውቀት ባይኖረውም ምናልባት ካገኛቸው ጥቃቅን ነጥቦች ተነስቶ ችግር ሊፈጥር የሚችል ነው። ስለዚህ..."

ኮሎኔል ስብሰባው ተበትኖ ከክፍሉ ሲወጣ ህሊናው እየተረበሸበት ነበር።

* * *

መንገድ ዳር ከቆመችው ነጭ ሲትሮይን መኪና ሲደርሱ ሁለቱም ተከታትለው በስተቀኝ ያለውን የኋላ በር ከፍተው ገቡ።

"እሺ?" አለ ማርቆስ ከፊት ተቀምጦ መሪውን የጨበጠውን አልጀርያዊ መከንን እየተመለከተ።

"የመጀመሪያውን አጠናቅቀዋል።" አለ አልጀርያዊው አፉ ውስጥ የሰካትን የጥርስ መጎርጎሪያ ስንጥር ከአፉ ሳያወጣ እያላመጣት።

"ጥሩ" አለ ኮሎኔል በረጅሙ ተንፍሶ ሰአቱን ለሁለተኛ ጊዜ እየተመለከተ። "ሁለተኛውን እንደጨረሳችሁ ሪፖርት ታዘጋጃላችሁ... የሁለቱንም በአንድ ላይ። ቢሮዬ ነኝ።" አለ የሲትሮይኗን በር ከፍቶ እየወረደ። ፒተር ተከተለው።

የቆዳ ጃኬቱን ኮሌታ ወደላይ እንደመለስ በረጃጅም እርምጃ መንገዱን ተሻገረና ጥግ ይዞ ወደቆመች መርሰዲስ አመራ። ፒተር ቀልጠፍ ብሎ በመሪው በኩል ያለውን በር ከፍቶ ከገባ በኋላ ባሻገር ያለውን በር ከፈተለትና ኮሎኔል ገብቶ ከፒተር ጎን ተቀመጠ።

"ፒተር" አለ ማርቆስ በዝናቡ ካፊያ በስብሶ ከፊት ለፊቱ ያለውን ሰባብሮና አወላግዶ በሚያሳየው የመርሰዲስ የፊት መስተዋት ላይ አይኖቹን አቦዝዞ "..ሁኔታዎች አስገድደውህ የምታደርገውንና ያደረከውን ህሊናህ



መሳልሶ መሳልሶ ሲፀየፈው ምን ታደርጋለህ?" አለ ጉንጩ ላይ ያለውን ጠባሳ በጣቱ እየዳሰሰ።

"ህሊናዬን እፀየፈዋለሁ።!" አለ ፒተር ለማሰብ እንኳን ጊዜ ሳይወስድ "ወደ ቢሮ?" አለ አከታትሎ።

"አዎ ወደ ቢሮ እንሂድ።" አለ ማርትቆስ አይኖቹን ጨፍኖ።

-7-

"ቆንጆዬ... ለምን አብረን አናድርም?"
"ቆንጆዬ ለምን ቤቱ አታደርሰኝም?"
"አትቀልጅ እንጂ እውነቴንኮ ነው።"

"አንተ አትቀልድ...ጠዋቱኑ ነግሬሃለሁ። በሰላም መተኛት ነው የምፈልገው። ጠዋት ሥራ ገቢ ነኝ።" የያዘችውን ሹካና ቢላ ከሳህኖቹ ላይ አስቀመጠችና ከጎን የተቀመጠውን ወረቀት አንስታ አፏን መጠራረግ ያዘች።"

"ስለምንሽ?" እጁን ዘርግቶ ቀኝ እጇን ያዝ አደረገና አይኖቹን አቁለጨለጨላት።

"እራት ጋብዤሽ እቤት አደርስሻለሁ ነው ያልከው። አሁን አዲስ ፋይል አትክፈት።"

"ምን ነካሽ ርብቃ! አልረብሽሽም እርፌ እተኛለሁ...ሙች።"
"እርፌህ አትተኛም! ናቲ... እንተዋወቃለንኮ። አሁን ይልቅ እንሂድ።" ቦርሣዋን አነሳች።
"ርብቃ በናትሽ አትድረቂ።" በተቀመጠበት እጆቿን ይዟት ቆየ።

"ብቻዬን ማደር አልፈልግም። በቃ። አቅፌሽ እንቅልፋችንን መለጠጥ በቃ።" ናትናኤል የገዛ እራሱ መቀየር አሳፈረው።

"ሚስት አግባና አቅፈሃት እንቅልፍህን ለጥጥ። ይልቅ አትቀልድ ሂሳቡን ክፈልና እንሂድ...መሸኮ።" ሀዓቷን እየተመለከተች። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት።

ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት። እጉል መሸፋፈኑን ትቶ ፍቅሩን መግለጽ አለበት። ግን እንዳፈቀራት ካወቀች ትጫነዋለች...እንጋባ አለበለዚያ

ብትልስ? መከራ ጣጣ! ይሄ ጋብቻ የሚሉትን ነገር የፈጠረው ወፈፌ ማን ይሆን? የተዋደዱ ሁሉ መጋባት አለባቸው ያለው ማነው? ጭቅጭቅ! አስተናጋጁን ጠቀሰው።

ናትናኤል ድፍን ሃምሣ ብር አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ። አስተናጋጁ ብሩን አንስቶ በትሪ ላይ ኮፍሶ ካመጣው የዋጋ ማቅረቢያ ወረቀት ጎን አስቀመጠውና ተመልሶ ሄደ።

"ርብቃ...እንደዛሬው ችክ ብዬብሽ አውቃለሁ?" ፈገግ ብሎ ተመለከታት።

"በፍፁም!" አለች ርብቃ እየሳቀች።

"በቃ እንግዲያው 'እሺ' በይኝ።" ናትናኤል ብቻውን ቤቱ ገብቶ አልጋው ውስጥ ጥቅልል ማለቱን እንደሞት ፈራው። ለወትሮው ግድ የለሽ ነው። ዛሬ ግን ብቻውን ወና ቤቱ ውስጥ መግባቱ ቀፈፈው... ምክንያቱ ለራሱ ባይገባውም።

አስተናጋጁ ተመልሶ መጣ። ናትናኤል መልሱን ተቀብሎ ወፈር ያለ ጉርሻ ትቶለት ተነሳ። አስተናጋጁ ፊቱ በፈገግታ ረስርሶ በግራው ትሪውን እንደያዘ ክወገቡ ጎንበስ አለና ቀኙን ደረቱ ላይ ጭኖ ተሰናበታቸው "ደህና እደሩልኝ።"

"አላበዛኸውም?"

"ምኑን?"

"ጉርሻውን።" አለች ክንዱን ያዝ አድርጋ።

"ቢቀናኝ ብዬ ነው ባክሽ።" አለ ናትናኤል ፈገግ ብሎ።

"ምንድነው የሚቀናህ?" የሆቴሉን የፊት አዳራሽ አቋርጠው ወደ ፊተኛው በር ሲወጉ በረኛው በሩን ከፍቶ፤ ጎንበስ ብሎ ተሰናበታቸው።

"እሺ እንድትይኝ ነዋ። እኔ ጋ እንድታድሪ።" እየሳቀ ተመለከተት።

"በሽት!" አለች አብረው እየሳቀች።

ርብቃ አብረው ሊታድር የወሰነችው ገና ከሆቴሉ ሳይወጡ ነበር። ነገር ግን መኪናው ውስጥ ከገቡም በኋላ-

"አሃ! የት ነው የምትሄደው? ናቲ ሙት አይሆንም ብዬሃለሁ። ቤት ታደርሰኝ እንደሆን አድርሰኝ። አይሆንም። ነገርኩህ እንግዲህ።" እያለች ተግደረደረችበት።



ይሄኔ ነው መናገር ያለባት። የፍቅር ጨዋታዋን ብቻ ሳይሆን ተራ ሙቀቷን፣ ቅርበቷን፣ እሷነቷን በፈለገ ሰዓት ነው መናገር ያለባት - "ናቲ...አረገዝኩልህ' ከ አ!አ! እንደዛ አይደለም..." ናቲ... ዛሬ ሃኪም ቤት ሄጄ ነበር... እና..." እንደዛም አይደለም... ፀጥ ብላ ማልቀስ። እሱ ራሱ ደንግጦ "ምንሆንሽ?" ይላት የለ... ያን ጊዜ ማልቀሷን ሳታቋርጥ አንገቱ ስር ገብታ በአንባዋ አንገቱን እያረጠበች፤ ደረቱን እያባበሰች፤ ጣቶቿን ከጀርባ ፀጉሩ ውስጥ ከትታ እያፍተለተለች መነፋረቅ... "ና...ቲዬናቲ... አንድ ነገር ብነግርህ አትቆጣም አይደል ...እ ...ናቲ ...የኔ ጌታ...ሙች በለኝና ትወደኛለህ አይደል..." መነፋረቅ "...ናቲ..."... መነፋረቅ...

"እሺ፤ ግን ቃል ገብተህልኛል... አትረብሸኝም አይደል?" አለች የሌባ ጣቷን አፍንጫው ሥር ቀስራ።

"አልረብሽሽም አልኩኝኮ ርብቃ።" በመጨረሻ ማሸነፉ ደስ አለው ናትናኤል። ከዚህ ቀደም ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲሆን ተሰምቶት የማያውቅ ልዩ ስሜት እንደሽረሪት ድር በዙሪያው ሲቃበተብ ተሰማው። ፈራ።

ቤቱ ደሢት ሄደ።

የአፓርትመንቱን በር ከፍቶ እንደገቡ ናትናኤል መብራቱን አብርቶ ኮቱን ፎቴ ላይ ወርወር አድርጎ ወደ መጠጥ መደርደሪያው ሄደ።

"ናትናኤል ቁጭ አድርገኸኝ ልትጠጣ አይደለም ያመጣኸኝ!"

ወደ መኝታ ቤት ከሚያስገባው በር ስትደርስ ፊቷን መልሳ ገረመመችው።

"ትንሽ ማሰብ ስለፈለኩኝ ነው።" አለ ናትናኤል የጠርሙሱን መክደኛ እየከፈተ።

"እንግዲህ ጀመረህ..." አለች ራመድ ራመድ ብላ ከእጁ ውስጥ ጠርሙሱን ወስዳ መልሳ መደርደሪያው ላይ እያስቀመጠችው። "አቅፈሽ ስጥ ነው ብለህ ነው ያመጣኸኝ? ማሰብ ከሆነ የምትፈልገው የእኔ እዚህ መምጣት አስፈላጊ አይመስለኝም።" ተከሳተረችበት።

ናትናኤል በረጅሙ ተነፈሰና ትከሻዋን እቀፍ አድርጓት ወደ መኝታ ቤት ገቡ። ርብቃ ቀዩን የራስጌ መብራት ስታበራ መኝታ ቤቱ ደም መሰለ። ታኮ ጫማዋን አውልቃ ከአልጋው ግርጌ አስቀመጠችና ልብሷን ማውለቅ ጀመረች። ናትናኤል ወደ መስኮቱ ሄዶ ወፍራሙን መጋረጃ ከመዝጋቱ በፊት ድቅድቅ ጨለማ በተከናነበው ከተማ ላይ አይኑን አፈጠጠ። ርብቃ የሌሊት ልብሷን ለብሳ ወደ መታጠቢያ ቤት ስትገባ-

"ምንድን የምታየው በጨለማ? ይልቅ ልብስህን ቀይር።" አለችው። መታጠቢያ ቤት ገብታ ተጣጥባ ስትመለስም ናትናኤል እዛው መስኮቱ አጠገብ እንደቆመ ነበር።

"ምን ሆነሃል?" ጠጋ ብላ ፀጉሩን እያሻሸች ፊቱን ወደራሷ መልሳ ጠየቀችው።

"እኔ እንጃ።"

"ምንድነው?"

"ምኑ?"

"የምታስበው።"

ናትናኤል አመነታ። ውሳኔውን ራሱ መውሰድ አለበት። ለርብቃ የሚያማክራት ነገር አይደለም። የግል ህይወቱ ቢሆን... አዎ ግን ይሄ ከሥራው ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። ያንን ደግሞ ራሱ ሊወስነው የሚገባ ነገር ነው።

ቀን ምሳ ላይ ከአብርሃም ጋር አጥብቀው ተከራክረውበታል። ለጊዜው ባይሸነፍለትም የአብርሃም አመለካከትም መሠረት ያለው መሆኑን ሊክድ አልቻለም።

"አየው ናትናኤል... እኔ ይህን ስራ ያንን አትስራ እያልኩኝ አልመራህም ግን ደግሞ እንደ እሳት እራት መጥፊያህን ስታሳድድ ዝም ማለት አልችልም።" ነበር ያለው አብርሃም።

"ምንድነው መጥፊያዬን የማሳድደው? እኔ'ኮ መደበኛ ሥራዬን ነው እያሰራሁ ያለሁት። በማንም ጉዳይ አልገባሁም።"

"ናትናኤል - የኛን ሰው አርደው ድልድይ ሥር የጣሉት ሰዎች ለምን ያንን ዓይነት አሰቃቂ እርምጃ የወሰዱ ይመስልሃል? ባጭሩ የጆሴፍ ካልሸርትን አድራሻ ሲያነፈንፍ ስላገኙት ብቻ ነው። አሁን አንተ እያደረግህ ያለኸው እሱ ሲያደርግ የተገኘውን ነገር ነው። ናትናኤል አንድ ምክር ብቻ ነው የምሰጥህ...ተጠንቀቅ!"

"ለምን ታስፈራራኛለህ?" በስጨት አለ ናትናኤል።

"አላስፈራራሁህም!" ለመጀመሪያ ጊዜ የተናደደ መሰለ አብርሃም "የማስፈራራበትም ምክንያት የለኝም። የሚያስፈራራስ አላወቅኸውም እንጂ አንተ ራስህ ፈቅደህ የገባህበት አለም ነው።"

"ሥራዬን ነው እየሰራሁ ያለሁት'ኮ አብርሃም።"

"የኛም ሰው ሥራውን ሲሰራ ነው እንደ ዶሮ ታርዶ የተጣለው፤ በድኑ ድልድይ ስር የተሸጎጠው፤ ደሙ ከወንዝ የተደባለቀው...



ትሰማኛለህ?!" አብርሃም ፊቱን ወደ ናትናኤል አዙሮ አፈጠጠበት። "ያው የድሮው ጋዜን አሁንም እየጋለበህ መሰለኝ።" ነበር አብርሃም ያለው የናትናኤልን የወትሮ ግትርነት አስታውሶ።

"እ...? ንገረኝ እንጂ ምን ሆነሃል?" ርብቃ ፀጉሩን እያሻሸች ጠየቀችው።

"ዝም ብዬ ነው ርብቃ።" አለ ናትናኤል ጀርባዋን እያሻሸ።

እጁን ይዛ ወደ አልጋው ወሰደችው። አልጋው ላይ ቁጭ ብለው ልብሱን አወለቀችለት። አንድ በአንድ ኮቱን፣ ሸሚዙን፣ ሱሪውን፣ ጫማውንና ካልሲውን ስታወልቅለት በዝምታ አይን አይኗን ሲመለከታት ቆየ። እንደ ህፃን ልጅ ፒጃማውን ካለበሰችው በኋላ ተነስቶ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ።

በተቻላት መጠን ሃሣቡን መሰብሰብ አለባት። አለበለዚያ ልትነግረው የፈለገችውን መናገር አትችልም። ምንድነው ግን የሚያስበው... አንድ ያስጨነቀው ነገር እንዳለ እርግጠኛ ነች። ማርገዟን ተጠራጥሮ ይሆን እንዴ? ወይኔ ገብሬልዬ! ሆዷ ባይገፋም ወገቧ አካባበ....ጡቶቿም...። ሃሣብ ገባት ርብቃ። ያበጠው ይፈንዳ ዛሬ ታወጣዋለች። ሳይቀድማት መቅደም አለባት። ዛሬ ነገ ስትል ዘጠኝ ወር ደርሶ ወልዳ ሳታርፈው አትቀርም። አሁኑኑ ተናግራ ካልወጣላት ከጥቂት ጊዜ በኋላ በደንብ ነው የምታስታውቀው። የመጣው ይምጣ ዛሬ...

ናትናኤል የመታጠቢያ ቤቱን መብራት አጥፍቶ በሩን ሲከፍት ስትሰማ ርብቃ ቶሎ ብላ በጀርባዋ ተንጋላ በተቻላት ዘና ብላ ጠበቀችው። በሩን ዘግቶ ወደ መኝታ ቤት ዘለቀ። ወደ አልጋው ሄዶ ብርድ ልብሱን ገልጦ አልጋው ውስጥ ሲገባ ርብቃ አልተነቃነቀችም። አልጋው ውስጥ ከገባ በኋላ ዞር ብሎ ከራስጌ ያስቀመጠውን ጀምሮ ያቋረጠውን መጽሐፍ አነሳ።

"ናትናኤል...አሁን ማንበቢያ ሰዓት አይደለም።" አለች ድንገት ቀና ብላ መጽሐፉን ከእጁ ላይ እየወሰደችበት።

ናትናኤል አልተከራከራትም። አንድ ዓይነት ጭንቀት እንደወረረው ግን ፊቱ ላይ በግልጽ ይነበብ ነበር። ሸርተት ብሎ አልጋ ውስጥ ገባ። ርብቃ ጠጋ ብላው ተኛች። ትኩስ ገላዋ መጥቶ ልጥፍ ሲልበት እጁን ሰዶ በስሱ የሌሊት ልብስ ውስጥ ያለውን መግቢያ መውጫውን የሚያውቀውን ገላ ያሻሽ ጀመር። በየት እንደሆነ ባይገባውም እጆቹ የሌሊት ልብሷን አልፈው የሚፋጅ ገላዋ ላይ መቅለጥ ጀመሩ። ትኩስ ትንፋሽዋ አንገቱን ሲለበልበው የሚወደው ፀጉሯ ደረቱ ላይ ብትን አለ።

...ያ ሁሉ ፋክራ ለዚህ ነው? አሁን ነው ማልቀስ ያለባት! እጆቹ እየዳሰሷት እያሉ፤ ደረቱ ላይ ተኝታ እያለች... ምን ይመጣል...? አውቀሽ ነው ያረገዝሽው ብሎ ቢያመርስ? ያምርራ! ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለች... ከአሁን በኋላ አንዴ ሆኗል! መናገርና የሚመጣውን መቀበል። ገብሬልዬ!

"ናትናኤል..." ከደረቱ ላይ ቀና አለች ርብቃ።
"ናትናኤል..." በተቻላት ድምጿን አለስልሳ ስሙን ጠራችው።

"እ..."

"ናትናኤልዬ..." ድምጿ በጭንቀት ተንቀጠቀጠ።

"ምነው?" ጣቶቹን ልኮ ፀጉሯን እየተለተለው ግራ እጁን በጀርባዋ ቁልቁል ሰዶ የሚወደውን ገላ ሳብ አቀፍ አደረገው። ቀኝ እጁን መለስ አድርጎ የለሊት ቀሚሷን ወደላይ ሰበሰበው። ቀሚሷ ጭኖቿን አልፎ ወገቧ ዙሪያ አሰፈሰፈ።

"ናትናኤል አንድ የ...ምነግርህ ነገር ነበር።" ድምጿ እንደቢራቢሮ ክንፍ ተርገበገበ።

"ምንድነው? ንገሪኝ።" አለ ናትናኤል ድምጿ አለቅጥ ሲለሰልስበት ፀጉሯን ከራሷ ላይ ወደኋላ እየመለሰ በደረቱ ቁልቁል እየተመለከታት።

"እስካሁንም ያልነገርኩህ ፈርቼህ ነው። ናቲዬ..." እንባዋን ለማምጣት ታገለች። የጠፈራት ድንጋጤ ምራቋን ከአፏ ውስጥ አደረቀው።

"ለምን...ምንድነው?" እጆቹ በታቻውን ያዙ-ጭኖቿ ውስጥ...

"ናትናኤል የኔ ጌታ..." ሳታውቀው አይኖቿ በእንባ ግጥም አሉ። "ገና! ገና! ምኑ ተይዞ ተንሰቅስቃ ካላለቀሰች ካልተነፋረቀች በዚህ ጨለማ አይኗ ስር ያቆረዘዘው እንባ የት ታይቶ!" አሰበች።

"ምንድነው የሆንሽው?" ሁኔታዋ ግራ ሲገባው ድንገት በሁለት እጆቹ ሁለት ጉንጮቿን ይዞ ቀና አደረጋት።

"ናቲዬ...ና..." ድምጿ እንደ ወፍ ትንፋሽ ሳሳ።
"ምንድነው ንገሪኝ ርብቃ።" ጉንጮቿን እንደያዘ ደግሞ ጠየቃት።
"ናቲዬ..."
"ኪርርር___ር!"
ከተዘጋው የመኝታ ቤት በር ወዲያ የስልክ ጥሪ ተሰማቸው።
"ስልክ ነው...አይደል?" ናትናኤል ከተኛበት ቀና አለ።
"ኪርርር___ር!"



ናትናኤል ቀልጠፍ ብሎ ከአልጋው ላይ ተነሳና ነጠላ ጫማውን አጥልቆ የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ።

"ሃሎ" አለ እንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ያለውን ስልክ አንስቶ።
"ሃሎ...ናትናኤል?" አለ የታፈነ የሚመስል ጎርነን ያለ ድምጽ።
"ነኝ...ማን ልበል?"

"አብርሃም ነኝ። እንድንገናኝ እፈልጋለሁ። አሁን በአስር ደቂቃ ውስጥ እንድትደርስ። ሆቴል ዲ-አፍሪክ ነው ያለሁት... ትሰማኛለህ? የመኪናህን ትንሽን መብራት ሳታጠፋ በሩ ላይ መኪናህን አቁም። እጠብቅሃለሁ..."

"ሃሎ... ሃሎ" ናትናኤል ተጣራ። ስልኩ ግን ተዘግቶ ነበር።
ለጥቂት ሴኮንዶች የስልኩን መነጋገሪያ እንዳንጠለጠለ አመነታ።
ሰዓቱን ተመለከተ። ለሶስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ። አብርሃም ውጪ የማምሸት ፀባይ የለውም። እስከሚያውቀው ድረስ። ደግሞስ ቀን ያልተነጋገሩት አሁን የሚነግረው ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? ስልኩንስ ለምን ቸኩሎ ዘጋ? አነጋገሩም ጥድፊያና ችኮላ የተቀላቀለው ነበር። 'ምን ሆኖ ይሆን?' ናትናኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ክፉ ታሰበው። 'አደጋ ደርሶበት ይሆን? ድምፁም ትክክል አይደለም-ጎረነነ።'

"ማነው? ምን ሆንክ?" አለች ሲቻኮል ስታየው ርብቃ ከተኛችበት ተነስታ አልጋው መሃል ቁጭ እያለች።

"ደህና ነኝ። አብርሃም ነው።" ቀልጠፍ ብሎ ልብሱን ይለባብስ ጀመር።
"እና የት ልትሄድ ነው በሌሊት?" ከላይዋ ላይ ብርድ ልብሱን ገፋ ተነሳች።

"ሆቴል ዲ አፍሪክ ነው ያለኝ። ትንሽ ችግር ሳይገጥመው አይቀርም። እንጃ አነጋገሩ ትክክል አይደለም።" ናትናኤል ፈጠን ብሎ ሱሪውን አጠለቀ። ሸሚዙን እስኪለብስ መቆየት አልፈለገም። ድፍን አንገት ያለውን ወፍራም ሹራቡን አጠለቀና ፀጉራም ካፖርቱን ከቁም ሳጥን ውስጥ ጎትቶ አወጣው።

"ምን ሆንክ አለ?" አለች ርብቃ ግራ ተጋብታ።

"ዛሬ ጠዋት አግኝቼው ነበር ለአንድ ጉዳይ። ለምን እንደፈለገኝ ግን አልነገረኝም። ዝም ብሎ 'ና' ነው ያለኝ።" ናትናኤል የሚለው ሲጠፋው ትከሻውን ሰበቀና ተወው። ከራስጌ የመኪናውን ቁልፍ አነሳና አልጋውን ዞሮ

እቅፍ አድርጎ ግንባሯ ላይ ሳማት:: "ተኚ:: አልቆይም:: እሺ ... በሩን ከውጭ ቆልፌ በሰር እወረውረዋለሁ::" እየተቻኮለ ወጣ:: ዘግቶት የሄደው በር ላይ አፍጥጣ ቀረች::

አሳንሰሩ እስኪመጣ መጠበቅ አልፈለገም:: አስር ደቂቃ ነው ያለው አብርሃም:: ሁለት ሁለቱን ሁለት ሁለቱን እየዘለለ በፎቁ ቁልቁል ተንደረደረ::

"ምነው ደህና?" አሉት የማታው ዘበኛ ወፍራም የሌሊት ካፖርታቸውን እንደደረቡ ከተኮፈሱበት እጥር ላይ እየተነሱ::

"ሠላም ነው::" ፈጠን ብሎ መኪናው ውስጥ ገባ::

መኪናውን አስነስቶ ከግቢው ወጣ:: መንገዱ ጭር ብሏል:: ብንብን የሚለው ካፊያ የመኪናውን የፊት መስታወት በጥቃቅን ነጠብጣቦች ሸፈነው:: የዝናብ መጥረጊያውን ተጫነና ፍጥነቱን ጨመረ:: ብሔራዊ ቴአትር አጠገብ ሲደርስ ዝናቡ ሃይል ጨምሮ የመኪናውን ጣሪያ ያቀልጠው ጀመር:: ያለ እረፍት ውልብ- ውልብ የሚለው የዝናብ መጥረጊያ ትንፋሽ ያጠረው መሰለ:: ሰዓቱን ተመለከተ:: አራት ሊሞላ ጥቂት ደቂቃዎች ቀርተዋል:: ዘግይቷል:: ፍጥነቱን ጨመረ:: ሆንጋ ተራ ያለው የመንገድ መብራት ቦግ ብሏል:: ቀዩ የትራፊክ መብራት ከመሬቱ ላይ ሲያርፍ በዝናቡ የተዘፈቀው አስፋልት የእሳት ጎርፍ የፈሰሰበት ይመስል ደም ይመስላል:: ናትናኤል ከጎንና ከጎን የሚመጣ መኪና እንዳለ ተመለከተ:: መስቀልያው መንገድ ንፁህ ነው ... አማን ነው:: ቤንዚን መስጫው ላይ ቆመበት:: መኪናው ቀዩን የትራፊክ መብራት አልፋ ተሽቀነጠረች:: ሜክሲኮ አደባባይ እንደደረሰ ወደቀኝ ታጠፈና ጎኑን ሰጥቶ ወደቆመው ሆቴል ተጣደፈ::

መንገድ ዳር ከተገተረው ሆቴል አፋፍ ሲደርስ ጥግ ይዞ ቆመ:: ሞተሩን አጠፋና መብራቱን ቀንሶ ትንሹን መብራት እንዳበራ ተጠባበቀ::

እልሁ ቢወጣለትም ዝናቡ አሁንም ሳግ ይተናነቀዋል:: የዝናብ መጥረጊያው በዝግታ እላይ እታች ይላል:: የፊት መስተዋቱ በገባ ትንፋሹ በጉም ተሸፍኗል:: እጁን ሰድዶ ወለወለው:: ዙሪያውን ተመለከተ:: የሆቴሉ ደንበኞች ያቆሟቸው ጥቂት መኪናዎች ከፎቁ ስር በተርታ ተኮልኩለዋል:: መንገዱ ጭር ብሏል:: ከመንገዱ ባሻገር ጥጉን ይዛ አንድ ሲትሮይን ቆማለች:: አብርሃም የለም...

"አሉ - ቀጥል::" አለ የአረብ ገጽታ ያለው ከሲትሮይኗ መሪ ኋላ የተቀመጠው ሰው በፈረንሳይኛ:: "አስታውስ፤ ጊዜ አትውሰድ፤ መስኮቱን አንኳኳ:: ዝቅ እንዳደረገ አንድ ብቻ ክትትለት:: መኪናውን እዙሬ እጠብቅሃለሁ::"



አጠገቡ የተቀመጠው ጥቁር ሰው ጭንቅላቱን በስምምነት ነቀነቀ:: ከደረበው ካፖርት የጎን ኪስ ውስጥ ሽጉጥ አወጣና በግራ እጁ ይዞት የነበረውን ቱቦ የመሰለ የድምጽ ማፈኛ ገጠመለት:: በአውራ ጣቱ የሽጉጡን መዶሻ ወደኋላ መልሶ የሲትሮይኗን በር ከፍቶ ወጣ::

ዝናቡ ይሁን ወይ አለቅጥ የረዘመው ቁመቱ ሰውየው ከትከሻው ጎበጥ ያለ ነው:: በቀኙ የያዘውን ሽጉጥ በካፖርቱ የጎን ኪስ ውስጥ ሸጉጦ መንገዱን ተሻግሮ አነስተኛ መብራቷን እንዳበራች ወደቆመችው 131 ፊያት አመራ::

ዝናቡ ይወርዳል:: የዝናብ መጥረጊው ሳይሰለች ከወዲያ ወዲህ ይንቀገቀገል:: ናትናኤል የመኪናውን ትንሽ መብራት ሳያጠፋ አይኖቹን በሰፊው ከፍቶ የሆቴሉን በር ይመለከታል:: ዝናቡ ብን ብን ይላል:: አብርሃም የለም::

ድንገት የመኪናው መስኮት ሲንኳኳ ተሰማው:: ናትናኤል ፊቱን መለስ አድርጎ ተመለከተ:: በዝናቡ ነጠብጣብ በተሸፈነው መስኮት ውስጥ የታየው ግን የተሰባበረና የተወለጋገደ ምስል ነበር፤ ቢሆንም የሰው ቅርጽ መሆኑ ይለያል:: 'አብርሃም?' ናትናኤል እጁን ሰድዶ መስኮቱን ዝቅ አደረገ::

የዝናብ ካፖርት ደርቦ ብንብን በሚለው ዝናብ ውስጥ የቆመው ሰው አብርሃም አለመሆኑን ወዲያው ተረዳ:: ደነገጠ:: ስህተቱ ትዝ አለው፤ ያጠፋው ጥፋት ፊቱ ላይ ድቅን አለበት::

"እቤት...?" አለ የሚከተለው እየታወቀው::

"መንጃ ፈቃድ::" አለው ትራፊክ ፖሊሱ ሠላምታ ከሰጠው በኋላ:: የሆንጋ ተራን የትራፊክ መብራት ጥሶ ሲያልፍ ነበር ጥግ ይዞ የነበረ ሞተረኛ ትራፊክ ፖሊስ ሞተር ብስክሌቱን አስነስቶ በዝናብ ውስጥ የተከታተለው::

ናትናኤል ደረቱን ዳበሰ:: ሹራብ ድፍን ሹራብ:: መንጃ ፈቃዱስ? ኮቱ ኪስ ውስጥ? እቤት! የሚከተለው ጭቅጭቅ ሲታሰበው ጭንቅላቱን ይፈልጠው ጀመር::

"ይቅርታ ወንድም ችግር ገጥሞኝ..." የሚለው ጠፋው ናትናኤል::

"መንጃ ፈቃድ ጌታዬ::" ፈርጠም አለ ትራፊክ ፖሊሱ::

ናትናኤል መኪናው ውስጥ ተኮፍሶ መደራደሩ እንደማያዛልቀው ሲረዳ ቀልጠፍ ብሎ በሩን ከፈተና ከመኪናው ወረደ:: ትራፊክ ፖሊሱ ወደኋላው አፈግፍጎ በዝምታ ይመለከተው ጀመር::

"ወንድም... ችግር አጋጥሞኝ ድንገት ከቤት ቸኩዬ ነው የወጣሁት .... መብራቱንም የጣስኩት ለዚሀ ነው:: ይቅርታ አድርግልኝ::" ወደጎን ሽፈፍ ሽፈፍ እያለ የሚዘንበው ዝናብ ፊት ፊቱን አለው::

"በመጀመሪያ መንጃ ፈቃድዎን ጌታዬ::'"
"እሱን ነውኮ የምልህ:: እየሀ ቸኩዬ ስወጣ..."
"መንጃ ፈቃድ የሎትም? " በጨለማው ውስጥ ትራፊክ ፖሊሱ ፈገግ ያለ መሰለው::
"አለኝ - አለኝ:: እቤት እረስቼው ስለወጣሁ ነው::" ናትናኤል በራሱ ተናደደ::

"እሺ ጌታዬ .... ወደ ጣቢያ ሄደን ብንነጋገር ይሻላል::"
"ቆይ - ቆይ እንደሱ አይደለም ረጋ በል እንጅ::"
"ይቅርታ ጌታዬ ጊዜ ባናጠፋ ይሻላል:: ዝናብ ውስጥ ነው ያለነው::"
"መጀመሪያ የምልህን ስማኝ::" አለ ናትናኤል ሳይታወቀው ንዴት የገዛ ህሊናውን እየሰለበው::

እዚህ ድረስ መጥቶ አብርሃምን ሳያገኝ ሊሄድ አይችልም! በፍጹም አብርሃም አንድ አይነት ችግር ገጥሞት እንደሆነስ?

"እየው... ምን መሰለህ..." ጠጋ አለ ናትናኤል ወደትራፊክ ፖሊሱ:: የሚበጀው መለማመጥ ነው፤ ረጋ ብሎ ማባበል፤ ክንዱን ያዝ አድርጎ እሽሩሩ ማለት::

"በሀግ አምላክ!" አለ የትራፊክ ፖሊሱ ናትናኤል ሲጠጋው ወደኋላው አፈግፍጎ እጁን ወገቡ ላይ ወዳንጠለጠለው መሣሪያ እየሰደደ:: " ቀጥል ማለት ቀጥል ነው"

ናትናኤል መኪናው ውስጥ ገብቶ ሞተሩን አስነሳና ወደ መንገድ ገባ:: ሮጥ ብሎ የሞተር ብስክሌቱ ላይ ጉብ ያለው የትራፊክ ፖሊስ ፍጥነት ሰጠት አድርጎ ከጎን ከጎኑ እየሄደ ያናግረው ጀመር::

"ቀስ እያልክ አሽከርክር... እ... እዚሁ ነው የምንሄደው - እምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ::"

ናትናኤል የመኪናውን መስኮት ዘጋበት::



ከፖሊስ ጣቢያው ደጃፍ እንደደረሱ ናትናኤል ከአጥር ውጭ መኪናውን አቁሞ ሲወርድ ትራፊክ ፖሊሱ ቁልፉን ተረከበው::

"ውስጥ እንግባ::" አለ ትራፊክ ፖሊሱ በቅንድቡ ወደ ጣቢያው መግቢያ እያመለከተ::

ናትናኤል ፊት ፊት እየቀደመ ተከታትለው ወደ ጣቢያው አመሩ::

"መብራት ሲጥስ ተከታትዬ አስቆምኩት:: መንጃ ፈቃድም የለው::" አለ ትራፊክ ፖሊሱ ከጠባቡ ጠረጴዛ ኋላ ለተቀመጠ ተረኛ መኮንን የናትናኤልን የመኪና ቁልፍ እያቀበለው::
"መታወቂያ::" አለ ተረኛ መኮንኑ ፊቱን ወደናትናኤል መልሶ በተቀመጠበት አንጋጦ እየገመገመው::

" አልያዝኩም::"
ተረኛ መኮንኑና ትራፊክ ፖሊሱ ተያዩ:: ሁኔታው እንዳላማራቸው ግልጽ ነበር::

"መንጃ ፈቃድ የለህም! መታወቂያም የለህም:: ይህ ሁሉ አንሶህ ወንጀል ትፈጽማለህ::" ተረኛ መኮንኑ ፊቱን ወደ ናትናኤል መልሶ አፈጠጠበት::

"ምን ወንጀል ፈጸምኩ ደግሞ? " ናትናኤል ተገረመ::

"ጥሰኸው የሄድከው መብራትኮ የዳንስ ቤት አምፑል አይደለም::" አለ ትራፊክ ፖሊሱ በተራው እየተገረመ::

ናትናኤል በራሱ ጥፋት ብግን አለ::
"ምንም ወረቀት የለህም ማለት ነው?" ተረኛ መኮንኑ ጠየቀው::
"የምን ወረቀት?" ናትናኤል ከዚህ በኋላ የፈለገው ቢመጣ ግድ ያለው አይመስልም::

"አንድ ሰውኮ ማንነቱን የሚገልጽ ወረቀት ሊይዝ ይገባዋል:: እንደው እንደ እንሰሳ አንመላለስም::" ተረኛ መኮንኑ ቆጣ አለ::

"ተናገርኩኮ.... ከቤት ስወጣ ችግር አጋጥሞኝ ተጣድፌ ስለነበር የመታወቂያ ወረቀቶቼን ሁሉ ኮቴ ውስጥ ነው ትቼ የወጣሁት፤ መብራቱንም የጣስኩት ለዚህ ነው::" በስጨት አለ ናትናኤል::

"አሃ ቁጣም! አለ እንዴ!?" አለ ተረኛ መኮንኑ ደስ የማይል ፈገግታ እያሳየ። ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ውስጥ የሚያስገባ ጠባብ በር ከፈተና "አስር አለቃ!" ብሎ ተጣራ።

ረጅም ደንደሳም ፖሊስ!- አሥር አለቃ።

ናትናኤል ከውስጠኛው ክፍል ብቅ ያለውን ሰው ሲመለከት ወኔው ከዳው፤ ተስፋ ቆረጠ። ከዚህ በኋላ ተከራክሮም ሆነ አግባብቶ ከገባበት ወጥመድ እንደማይወጣ ተገነዘበ።

"እሽ ወንድም፤ ስም።" ቆፍጠንጠን አለ ተረኛ መኮንኑ አውሬ የሚመስለውን የአሥር አለቃውን ከጎኑ አቁሞ።

"ናትናኤል ግርማ።"

"አድራሻ?"

ናትናኤል በተቻለው መጠን ንዴቱንና ብስጭቱን ዋጥ አድርጎ ለተጠየቀው ሁሉ መልስ ሰጠ።

"ጥሩ እንግዲህ... መኪናዋ የተሰረቀች አለመሆኗ ከተረጋገጠ በኋላ የመታወቂያ ወረቀቶችህንና የመንጃ ፈቃድህን እይተን በህጉ መሠረት ላጠፋኸው ጥፋት እንከስሃለን። እስከዚያ ድረስ ግን ማረፊያ ቤት መቆየት ይኖርብሃል።"

ናትናኤል አልተከራከረም። ክርክር ለውጥ አያመጣም። አስር አለቃውን ተከትሎ በጠባቧ በር አልፎ ወደ ውስጥ ገባ። ከፊት ለፊቱ ለማዳ እንስሳ እንዳስከተለ ገበሬ ዘና ብሎ የሚራመደውን ደንደሳም ፖሊስ ሲመለከት ዘገነነው። እንደ ወንጀለኛ ከፍርግርግ በር ጀርባ ሊዘጋበት ሲጣደፍ ሲያይ በሰው በሰው አለው። ከተራ ቀማኞች ማጅራት መቺዎች መንጋ ሊደባልቁት? ጨክነው?!

አስር አለቃው ከአንድ በር እንደደረሰ ቆም ብሎ ወገቡ ላይ በሰንሰለት ከተንጠለጠሉ ቁልፎች አንደኛውን በበሩ ቀዳዳ ውስጥ ሰደደና በሩን ከፈተ። ወዲያው ፊቱን ወደ ናትናኤል መልሶ በቀኝ እጁ በያዘው አጭር ዱላ የገዛ ጭኑን ይተመትም ገባ። ቋንቋው 'ትገባለህ ወይስ እንፈታተሽ?' መሆኑ ሲገባው ናትናኤል ጊዜ ሳያጠፋ በተከፈተው በር ሹልክ ብሎ ገባ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጨለማው ክፍል ባዶ መሆኑን ከመተሳሰፊያው በሚመጣው ብርሀን ሲመለከት ነፍሱ መለስ አለችለት። ወዲያው አስር አለቃው በሩን ዘግቶ ከውጭ ሲቆልፍበት ድቅድቅ ጨለማ ዋጠው።

ለጥቂት ደቂቃዎች በጨለማው ውስጥ እንደቆመ ቀየ። 'አብርሃም በዚያ ሰዓት ምን ፈልጎ ይሆን የደወለው?' ርብቃ ትዝ አለችው። ታስባለች፤ እንደወጣ ጥፍት ሲልባት ያለጥርጥር "እንዱጋ ተደፍቶ ቀረ" ነው



የምትለው። በረጅሙ ተነፈሰ ናትናኤል በጨለማው ውስጥ ማጅራቱን እያሻሸ።

ምን ያህል እንደቆየ ትዝ አይለውም። 'ዝ... ዝ' የሚለው የማያቋርጥ የትንኝ ድምጽ ጆሮው ላይ አዜመበት። ድንገት የክፍሉ መብራት በግ አለ። መብራቱን ያበሩት ከውጭ እንደሆነ ገባው። 'በጊዜ ጥግህን ያዝ' ነው ነገሩ ብሎ አሰበ።

በጠባቧ ክፍል ውስጥ ለአይን የሚስብ ምንም ነገር አይታይም። ከወዲያ ጥግ ከበሩ ትይዩ በሥነሥርዓት የተነጠፈ ጠባብ አልጋ አለ። ይኸው ነው። ናትናኤል ጊዜ ሳያጠፋ ወደፊት ተራምዶ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠና ጭንቅላቱን ሁለት መዳፎቹ መሃል ቀብሮ ያስብ ጀመር። ብዙ አልቆየም እንደፈራው የክፍሉ መብራት ጠፋ። ናትናኤልን ግን ከሃሳቡ አልቀሰቀሰውም።

አንድ ነገር አግኝቶ መሆን አለበት አብርሃም የደወለለት። ከቻለ ሊረዳው ቃል ገብቶለት ነበር። ቀን ምሳ በልተው አብርሃም "በዘጠኝ ሰዓት ከጓደኛዬ ጋር ኢትዮጵያ ሆቴል ቀጠሮ አለኝ..." ስላለው እዚያው ካደረሰው በኋላ ፍንጭ ካገኘ ሊደውልለት ተስማምተው ነበር።

"አብርሃም ለማለት የፈለግኸው ገብቶኛል.... ሁኔታው ውስብስብና አደገኛም ነው... ግን በማቀርበው ሪፖርት ላይ ነገሩን አደባብሼ ማለፉን አልፈልግም... ገባህ? .... ስለዚህ የሚጠቅመኝ አዲስ ሃሳብ ካገኘህ ደውልልኝ ... እ?" ነበር ያለው ናትናኤል መኪናውን ኢትዮጵያ ሆቴል በራፍ ላይ አቁሞ ከመለያየታቸው በፊት።

"ምን ችገረኝ ናትናኤል.... እንቆቅልሹን ብፈታውኮ እኔም ደስ ባለኝ ነበር። ግን ደግሞ ራሴን ለአደጋ ማጋለጥ አልፈልግም... ደግሞ ፈጠነም ዘገየ አባት መሆኛዬ ደርሷል.... " ፈገግ አለ አብርሃም። "ልጄ ደግሞ እርግጠኛ ነኝ አባት ይፈልጋል።"

"ውለታ መላሽ ያድርገኝ።" ናትናኤል እጁን ዘረጋለት ተጨባበጡ።

"እ.... በነገራችን ላይ ከተገናኘን አይቀር ለምን አልነግርህም... እንዳልኩህ ጥቅምት ላይ ማግባቴ ነው» አለ አብርሃም ፈገግ ብሎ ጺሙን በኩራት እየላገ። «ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ሚዜዬ አንድትሆን ብጠይቅህስ?"

"ቸኩልኩኝ!" ናትናኤል ስሜቱን መደበቅ አልሆነለትም።

"አብሮ ማደግ ቀላል ነገር አይደለም።" የጓደኛውን ትከሻ ቸብ አድርጎ አብርሃም ከመኪናው ወረደ። "ቻው ናቲ! እደውልልሃለሁ ለማንኛውም።"

'ደወለ:: ግን ምን ፈልጎ ደወለ? ምን ሊነግረው ደወለ? ምን አግኝቶ ደወለ?' ናትናኤል በመቆያ ቤቱ አልጋ ላይ ቁጭ ብሎ ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ ክንዶቹን ጉልበቶቹ ላይ ቸክሎ ለጥያቄው መልስ ፈለገ:: 'ለምን ደወለ?'...

- 8 -

ስልኩ ሲያንቃጭል ጋለል ካለችበት ፎቴ ላይ በርግጋ ተነሳች:: በመጨረሻ... ሸለብ አድርጓት ነበር::

ሌሊቱን ቁጭ ብላ ነበር ያደረቻው:: ማታ እንደሄደ 'ቶሎ ይመለሳል' ብላ ስላሰበች ተመልሳ አልጋ ውስጥ ገብታ ተኛች:: ብንን ስትልና ሰዓቷን ስትመለከት ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከአስር ነበር:: ዞር ብላ ከጎኗ ተኝቶ እንደሆነ በጨለማው ውስጥ አልጋውን ዳሰሰችው:: አልተመለሰም:: መብራቱን አብርታ ድጋሚ ሰዓቷን ተመለከተች:: ልክ ነች:: ከሶስት ሰዓት በላይ ሆኖታል ከሄደ:: ቅንድቦቿን አጠጋግታ ለማሰብ ሞከረች:: እስካሁን እንዴት ይቆያል፤ ችግር አጋጥሞት ይሆን አብርሃም? ታዲያ ችግር ቢያጋጥመውስ እንዴት ደውሎ እንዲህ ነው አይላትም... ርብቃ አልጋው መሃል ቁጭ ብላ ታወጣ ታወርድ ጀመር:: 'እሱ እራሱስ እንደዚያ ተቻኩሎ ሲሄድ አደጋ ገጥሞት እንደሆነስ? ገብሬልዬ!' ሆዷ ውስጥ ያለው ልጅ የተሳወሰ መሰላት:: ዳበስ አደረገችው ሳይታወቃት:: ስጋት ይጠረጥራት ጀመር:: ግንኮ ከዚህ ቀኝታ ቢደውልምኮ አትሰማውም:: እስካሁንስ ደውሎ አቅቶት እንደሆነስ?'

ፈጠን ብላ ብርድ ልብሱን ከላይዋ ላይ ገፋ ከአልጋው ተነሳች:: ፒጃማዋ ላይ የጠዋት ልብሷን ደረበችና ወደ ሳሎን ገባች:: ከስልኩ አጠገብ ፎቴ ላይ ተቀመጠችና አይኖቿን ከፊት ለፊት ካለው የናትናኤል ፎቶግራፍ ላይ አሳረፈቻቸው::

'ምን ሆኖ ይሆን? እንዴት አይደውልም? ሰው ያስባልም አይል?' ሰዓቷን ተመለከተች ሰባት ከሃያ::

ጊዜው እየተሸረሸረ ሌሊቱ እየተናደ በሄደ ቁጥር የርብቃም ሆድ እየተከፋ ሄደ:: ሁለቴ መታጠቢያ ቤት ደርሳ ተመለሰች:: 'እውነት በጤናው ይሆን?' ሰዓቷን ተመለከተች - ዘጠኝ ከሩብ:: ክፉው ታሰባት:: '"ቀስ ብለህ ንዳ" ሲሉት አይሰማ! በዛ ዝናብ ሲሮጥ... ገብሬልዬ!' ሰዓቷን ተመለከተች ዘጠኝ ከሃያ::



ሌሊቱ እየሸሸ ንጋቱ እየቀረበ ሄደ ናትናኤል አልተመለሰም፤ አልደወለም::

ስልኩ መልሶ አምባረቀባት:: ፈራችው:: ሶስተኛ ጊዜ እሪ! አለ ፈጠን ብላ አነሳችው -

"ሃሎ"

"ሃሎ ... ርብቃ...?"

"ናቲ! ደህና ነህ?" አለች ድምፁን ስትሰማ::

"ደህና ነኝ ርብቃ::"

"ትንሽ አታስብም... ሰው ያስባል ብለህ!" አቋረጠችው:: የአነር ንዴት ጉሮሮዋ ውስጥ ተማገደ:: የአፎይታና የመረጋጋት ስሜት ሰውነቷን ሲወረው ሳይታወቃት አይኖቿ በእንባ ተሞሉ::

"ርብቃ ስሚኝ... ችግር አጋጥሞኝ ነው:: ቆይ ርብቃ ስሚኝ..." አለ ድጋሚ ልታቋርጠው ስትል ተሽቀዳድሞ:: «ርብቃ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነኝ::»

"ፖሊስ ጣቢያ?!" ጮሀ አቋረጠችው:: የሰማችውን ማመን አልቻለችም:: "'ታስሬአለሁ' ነው የምትለኝ?!" ደነገጠች:: ፖሊስ ጣቢያ? ፖሊስ... ሌባ... ለአንድ አፍታ የእሷን ናትናኤል የፊጢኝ አስረው ፀጉሩን ላጭተው እየገፈተሩ ከወረበሎች ታዛ ሲደባልቁት ታያት::

"ርብቃ እባክሽ ረጋ ብለሽ አዳምጪኝ:: ማታ መንጃ ፈቃድ ረስቼ ስለወጣሁ ነው እዚሁ ያሳደሩኝ:: ይልቅ መታወቂያዬንና የመንጃ ፈቃዴን ይዘሽልኝ ነይ:: የመኪናዋን ሲብሬም እዚያው ታገኚዋለሽ:: ታውቂዋሽ አይደል አምስተኛን?"

"ማንን?"

"አምስተኛን?"

"አምስተኛ!" ግራ ገባት ርብቃ::

"አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ!" ናትናኤል ትዕግስቱ እልቅ አለበት::

"የት ነው? አላውቀውም ናቲ"

"እይው... ሜክሲኮ አደባባይጋ ከደረስሽ በኋላ..."

ርብቃ ከየት ወዴት ልብሷን እንደቀያየረች ትዝ አይላትም:: 'ውሸቱን ነው! ሰው መንጃ ፈቃድ ረሳህ ተብሎ እስር ቤት አይገባም! ውሸቱን ነው:: አንድ ነገር አለ::' ሆዷ ተንጓጓባት:: መታጠቢያ ቤት... ቶሎ... ቶሎ.... ቀሚስ... በጭንቅላቷ... ጫማዎቿ ውስጥ ዘላ ገባች... ቶሎ.... ቦርሳዋን ይዛ ወጣች:: የአፓርትመንቱን በር ከውጭ ስትቆልፍ፡ የረሳችው ትዝ አላት - መንጃ ፈቃድ! መታወቂያ! የናቲ! በሩን ከፍታ ገባች:: ወደ መኝታ ቤት ሮጣ የራስጌ ኮመዲኖ ፈተሸች:: የለም::

መሳቢ.ውያን ስባ አየች:: የለም:: ቆም ብላ አሰበች:: የት ነው አስቀምጦ የሄደው? አሃ! ቁም ሣጥኑ! ራመድ ብላ ቁም ሳጥኑን ከፈተች:: የላይኛው መደርደሪያ... የመሃለኛው... የታች - የለም:: ርብቃ ግራ ገባት:: መኝታ ቤ መሃል ቆማ ቀረች:: ዙሪያውን ተመለከተች:: የት ነው ያስቀመጠው? ኮቱ አነሳቸው:: 'አ-ና... ና!'

የገንዘብ ቦርሳውን አወጣች:: ከፈተችው:: ሳንቲሞች ተዘረገፉ ቅጭልጭል እያሉ በየስርቻው ተበተኑ:: መታወቂያ ወረቀት? አዎ የመን ፈቃድ? አዎ:: ሮጣ ወጣች - መንገዱ ጭር እንዳለ ነው::

ታክሲ ተሳፍራ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ደረሰች::

"ምንድንነው?" አላት በር ላይ የቆመው ፖሊስ እጆቹን ከኪሱ ሳያወጣ::

"ስልክ ደውለው ጠርተውኝ ነው:: ልግባ?"

"ማንን ነው የፈለግሽው?"

"ሰው:: እዚህ ያደረ::" አለች ርብቃ 'እስረኛ' ማለቱ ሲቀፋት::

"እስረኛ ነው?"

"እ... " 'ናቴ እግዜር ይይልህ!'

"ታዲያ እንደሱ አትይም... ግቢ::" አለ ጭንቅላቱን ወደጎን መታ አድርጎ::

ጠባቧ ክፍል ውስጥ ወንበር ላይ ተቀምጦ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያነባል:: ወደ ክፍሉ ስትገባ ሲያያት ከተቀመጠበት ተነሳ::

"ርብቃ::" አለ ግራ ክንዷን ያዝ አድርጎ::

"ደህና ነህ?! " በጤና ቆሞ ሲያዋራት አይኖቿን ማመን አቃታት::

"ደህና ነኝ - - ደህና ነኝ::" አለ ፈጠን ብሎ መደናገጧን ሲያይ:: "ምንም ችግር የለም::"

ከጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠው ተረኛ መኮንን ቀና ብሎ ተራ በተራ ይመለከታቸዋል::

"አመጣሽው?"

"ምኑን?" ቀና ብላ ግራ በገባው ፊት አይን አይኑን አየችው::

"መንጃ ፈቃዴን ነዋ!"

"አ...አዎ::" አለች ቦርሳዋን በፍጥነት እየከፈተች:: ከውስጥ የገንዘብ ቦርሳውን አውጥታ ሰጠችው::



"ይኸው" አለ ናትናኤል የመንጃ ፈቃዱን፣ ሊብሬውንና መታወቂያ ወረቀቱን ከቦርሳው ውስጥ አውጥቶ ከተረኛ መኮንኑ ፊት ጠረጴዛው ላይ እየከመረ::

ተረኛ መኮንኑ የመታወቂያ ወረቀቶቹን ተራ በተራ ከተመለከታቸው በኋላ ከመሳቢያው ውስጥ ትራፊክ ፖሊሱ ትቶለት የሄደውን የመጥሪያ ወረቀት አውጥቶ የመታወቂያ ወረቀቱን ከሊብሬና መንጃ ፈቃዱ ጋር አቀበለው::

"በሆነው እንደተከፋህ ይገባኛል:: ግን እኛም ምርጫ ስለሌለን ነው:: አየህ... ሌባውንና ጨዋውን መለየት ያስቸገረበት ጊዜ ነው:: በዚህ ሰዓት ያለመታወቂያ፣ ያለመንጃ ፈቃድ መብራት እየጣስክ ስትከንፍ ደግሞ መጠርጠር ይገባናል:: ለማንኛውም አዝናለሁ በአጋጣሚው::"

'ድንቅ ዲስኩር' አለ ናትናኤል በልቡ መታወቂያ ወረቀቶቹን እየተቀበለ::

"ይህን ይዘህ ያው ትራፊክ ጽህፈት ቤት ቅረብ::" አለ ተረኛ መኮንኑ የመጥሪያ ወረቀቱን እያቀበለው::

ምልስ አልመለሰም ናትናኤል:: ጥፋቱ ሁሉ የእርሱ የራሱ መሆኑ ግልጽ ብሎ ቢታየውም ቅጥ ያጣ ንዴቱን መሸፈን አልተቻለውም:: የርብቃን ክንድ ያዝ አድርጎ ከጣቢያው ወጣ:: ከውጭ ያደረችው 131 ፊያት መኪናውን ሲያይ ዘመዱ መሰለችው::

መኪና ውስጥ እንደገቡ ርብቃ ሆራ አፈጠጠችበት-ቀንዷን አሹላ "አትዋሸኝ! ናትናኤል ምን አድርገህ ነው የታሰርከው?" ድንገት በንዴት እየተንቀጠቀጠች ገጠመችው::

የመጥሪያ ወረቀቱን ዘረጋላትና የመኪናውን ሞተር አስነሳ::

"ናትናኤል እውነቱን ንገረኝ::" ጎፈሯ ቆመ::

"ርብቃ በቃ ይኸው ነው:: መብራት ጣስኩ:: ትራፊክ ፖሊሱ ተከታትሎ ያዘኝ፣ መንጃ ፈቃድ ጠየቀኝ:: የለኝም:: ጣቢያ ወሰደኝ:: መታወቂያ ወረቀት ጠየቁኝ:: አልያዝኩም:: አንድ ክፍል አስገብተው ዘጉብኝ::"

"አውሬዎች!"

"ጥፋቱ በሙሉ የኔ ነው ርብቃ ፣ መኪናዋን ስርቄም ሊሆን ይችል ነበር::"

“ሰውና ሌባ መለየት አይችሉም?” ሙኾቸበት።
ናትናኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ሳቀ።

“ርብቃ ሌባምኮ ሰው ነው!ረከስ እንጅ።”
“እነሱስ እሺ! ያ ብሽቅ ለምንድነው በሌሊት የጠራህ?”
“ማ?”
“አብርሃም ነዋ!”
“አብርሃም...”
ናትናኤል ለአንድ አፍታ ዝም አለ። አብርሃም ለምንድነው በሌሊት የጠራው...?

“ለምን አቆምክ?” አለች ርብቃ ናትናኤል መኪናውን ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ስር ሲያቆም።

“መጣሁ ስልክ ደውዬ።” ተጨማሪ ጥያቄ ለመጠየቅ ጊዜ ሳይሰጣት የመኪናውን በር ከፍቶ ወረደ።

'አብርሃም ለምን ደወለ? ለምን ነበር አፍሪካ ሆቴል ድረስ በዛ በሌሊት እንዲመጣ የነገረው?' ናትናኤል ወደ ቀዩ የህዝብ ስልክ አመራ።

የስልኩን እጀታ አንስቶ ጆሮው ላይ ደገነው ...ቲ...ቲ...ቲ የአብርሃምን ቁጥር ደወለ...ተይዟል... ደግሞ ሞከረ...ቲ...ቲ...

“ሃሎ”
“ሃሎ እባኮት አብርሃም ይኖር ይሆን...”
“እ...የለም።” አለው የሴት ድምፅ።
“ስራ ነው የሄደው?”
“እ...ይ” አመነታችበት።
“ባክሽ ካለ ናትናኤል በይልኝ ...እ...”
“እ...ይ...እ... አደጋ ደርሶባቸዋል ብለው ደውለው እትዬ አሁን ወጡ ወደ ሃኪም ቤት።”
“የት? ማ?” ናትናኤል በጦር እንደተወጋ አይነት ደነገጠ።
“እትዬ።”
“ማነው አደጋ የደረሰበት...ምሥራቅ ነች?”
“ጋሼ።”
“አብርሃም?”
“አዎ።”
“የት ነው ያለው? ማለቴ...” ተማታበት።
“ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መሰለኝ ያሉት።”



ናትናኤል ስልኩን ዘግቶ እየሮጠ ወደ መኪናው ተመለሰ።
“ምን ሆንክ?” አለች ርብቃ ሁኔታውን ስታይ ተደናግጣ።
“አደጋ አጋጥሞት ነው። እኔኮ ማታውኑ ተሰምቶኛል።” አለ የመኪናውን በር ዘግቶ ሞተሩን እያንጫረረ።

“ማነው? አብርሃም ነው?”
“አዎ።” አለ የመኪናውን ጎማ አንሳጦ መንገድ ውስጥ እየገባ።
“ቀስ በል ናትናኤል...እንጋጫለን።” አለች ርብቃ በቀኝ እጇ የመኪናውን ኪስ ወጥራ ይዛ።

'አብርሃም በውድቅት ለምን ጠራው? አደጋ ደርሶበት? አደጋ ደርሶበት ቢሆን ያኔውኑ ይነግረው ነበር። አይደለም። አደጋ ደርሶበት ሊሆን አይችልም። እርግጥ ድምፁ ትክክል አልነበረም አለቅጥ ጎርንኖ ነበር። ቢሆንም አደጋ የጋጠመው ሰው ዓይነት አልነበረም። አደጋ ሊሆን አይችልም። ከደወለለት በኋላ መሆን አለበት አደጋው የደረሰው። ግን...'ናትናኤል ቅንድቦቹን እየቋጠረ እየፈታ ከራሱ ጋር ተከራከረ።

ከሆስፒታሉ የውጭ በር እንደደረሱ ናትናኤል የመኪናውን በር ከፍቶ ከመውረዱ በፊት ፊቱን ወደ ርብቃ መለሰና “እዚሁ ጠብቂኝ።” አላት። እየተቻኮለ ደፋ ደፋ እያለ ወደ ሆስፒታሉ በር አመራ።

“ወዴት ነው?” በተጀባበነው ጋቢ ላይ ወፍራም ካኪ ካፖርት የደረበው የሆስፒታሉ ዘበኛ ጠየቀው።

“ወንድሜ አደጋ ደርሶበት በስልክ ተጠርቼ ነው።”

በድንጋጤ አመድ የመሰለውን የናትናኤልን ገጽታ ሲመለከት የሆስፒታሉ በረኛ በሩን ከፈተና አስገባው። ራመድ ራመድ እያለ ወደ ሆስፒታሉ ህንፃ አመራ። ከፊት ለፊቱ የምትመጣ ነርስ አጠገብ ሲደርስ ቆም አለ “ባክሽ የኔ እህት አደጋ የደረሰበት ሰው ነበር። በስልክ ተጠርቼ ነው። የት አገኘዋለሁ?”
“ያውልህ ቀጥታ ሄድና...ያ በረንዳ ይታይሃል...በዚያ በኩል ግባ።”

ቀጠለ - ደፋ ደፋ እያለ። ነርሷ ያመለከተችው በር ጋ ሲደርስ ወደ ውስጥ ገባ። ባዶ መተላለፊያ። ወደፊት ቀጠለ። ከጠረጴዛ ኋላ የተቀመጠች ሌላ ነርስ ሲመለከት እጥፍ ብሎ ወደእሷው አመራ።

“ሠላም ...እባክሽ አደጋ የደረሰበት ሰው...”
“ማን ይባላል?” አለች አቋርጣው።
“አብርሃም አያሌው...አብርሃም አያሌው።”

"እ... ያውልህ:: ቀጥታ ሂድና ወደ ግራ ታጠፍ:: በዚያ ጋ ሰውየው በወጣበት በር በኩል::"

ቀጠለ - ደፋ ደፋ እያለ:: ነርሷ ያመለከተችውን በር ከፍቶ ሲገባ በመጀመሪያ የተመለከተው የአብርሃምን እጮኛ ነበር:: ምሥራቅ ስታየው ከተቀመጠችበት ዘላ ተነሳች::

"ያውና!" አለች ሊይዟት የሚታገሉትን አባቷን መንጭቃ ወደ ናትናኤል እየቀረበች:: "ምንድነው?! ምንድነው ንገሩ! " ጮኸችበት:: "ማነው? ማነው እንዲህ ያደረገው?!" ፊቷ በእንባ ረስርሷል፤ ፀጉሯ ተንጨባሯል፤ ሰውነቷ ይቋጠራል ይፈታል::

ናትናኤል ከገባበት በር ሳይርቅ በድንጋጤ ደንዝዞ ቆመ:: የሚለው፣ የሚናገረው፣ የሚያደርገው ተማታበት:: አባቷ ከኋላዋ ተከትለው መጥተው ክንዷን ይዘው እየታገሉ፣ እየተጓተቱ መልሰው ከነበረችበት ወንበር ላይ አስቀመጧትና ጭንቅላቷን ትከሻቸው ላይ አስደግፈው ጉንጮቿን ጭንቅላቷን እየደባበሱ ማባበላቸውን ቀጠሉ::

ናትናኤል ግራ ተጋብቶ ቀፍረው እንደቀበሩት አጣና መተሳሰፊያው መሃል ተገትሮ ቀረ:: በክፍሉ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ በእሱ ላይ ያፈጠጡ መሰለው:: ሁሉም የአብርሃምን እጮኛ ተከትለው የመጡ መሆናቸውን ተረዳ::

"ማነው እንዲህ ያደረገው? አብራችሁ ነበራችሁ?"

ናትናኤል ዞር ብሎ ተመለከተ:: ጠና ያሉ ሰው ናቸው:: ጺማቸውና ከጆሮዎቻቸው በላይ ያለው ቡፍ ያለ ቀሪ ፀጉር ነጥቷል::

"ምንድነው?... ምንድነው የሆነው አብርሃም? " አለ ናትናኤል መልሰው እሱኑ ሲጠይቁት ግራ ገብቶት::

"አንተ አይደለህም እንዴ ጓደኛየው...?" አሉ ሰውየው ለአንድ አፍታ ዞር ብለው ምሥራቅን አየት አድርገው ድጋሚ ፊታቸውን ወደ ናትናኤል እየመለሱ:: "...ከጓደኛው ጋር ጠዋት እንደወጣ ነው እንዲህ የሆነው' ነው'ኮ ያሉችን:: ትላንት ማታ በሁለት ሰዓት ተኩል ነው፤ ፖሊሶች ያገኙት ካዛንችስ::"

"ማ...እኔ...? እሱ ነው'ኮ ደውሎ የጠራኝ"

ድንገት ብልጭ አለለት... 'ካዛንቺስ!ትላንት ለሶስት ሩብ ጉዳይ ስልክ ደውሎ የጠራው የአብርሃም ድምፅ አልነበረም...የ ጎርናና ድምፅ የአብርሃም



አልነበረም!... 'ናትናኤል አፉ ደረቀበት... አብርሃም ያለው፣ የነገረው ታወሰው- 'ናትናኤል በእሳት እየተጫወትን ነው::-'

"ምንድነው ያደረጉት?" አለ ናትናኤል አጠገቡ የቆሙትን ሰው ክንድ ጨምድዶ::

"በጥይት ነው የተመታው::" አሉ ሰውየው በደከመ ድምፅ::

"ጎድተውታል? " ናትናኤል ሰውነቱ ተንቀጠቀጠበት::

"የዚች ልጅ አምላክ ይጠብቀው እንጅ እሱስ እንዳይሆን ነው::" አሉ ሰውየው በረጅሙ ተንፍሰው::

"የት ነው ያለው?" ናትናኤል መላ ሰውነቱ ጨው መርጨት የጀመረ ይመስል ተቃጠለ ሆዱ አፉ፤ መላ ሰውነቱ...

"ከዚህኛው ክፍል ነው አሉን:: እንጃ... " አሉ ሰውየው ናትናኤልን በቆመበት ትተውት ሁለት እጆቻቸውን ከኋላ ከጀርባቸው ላይ አጣምረው አንገታቸውን ደፍተው እየተንጎራደዱ::

ናትናኤል ሰውየው ወዳመለከቱት በር አመራ:: ከበሩ ከመድረሱ በፊት ከውስጥ አንድ ነርስ በሩን ከፍታ ወጣች::

"የኔ እህት ... " ጠጋ ብሎ ክንዷን ያዛት:: "በጣም ተጎድቷል? ተስፋ አለው?"

ነርሷ ቀና ብላ አየችው፤ መልስ ግን አልመለሰችለትም:: አይኖቿ የሚሉትን፣ የሚናገሩትን ሲያይ ሰውነቱ ተርበተበተበት:: "ባክሽ ሃኪሙን ማየት እፈልጋለሁ:: ቶሎ በይልኝ::"

ነርሷ ተመልሳ ወደ ክፍሉ ገባች:: ብዙ ሳትቆይ ሃኪሙን ይዛ ተመለሰች::

"ዶክተር:: ተስፋ አለው?" በሚንቀጠቀጥ እጁ የሃኪሙን ክንድ ለቀም አደረገው::

"እስቺጋሪ ነው ለመናገር::" አለ እጠር ብሎ መለጥ ያለው ቀጭን ሃኪም ከሥራው ላይ ያስጠራውን ሰው ምንነት ለመገመት እየሞከረ::

"ላየው እፈልጋለሁ::"

ሃኪሙ የሰማውን ማመን የቻለ አይመስልም::

"ምኑን ታየዋለህ? ህክምና እየተደረገለት እኮ ነው::"

"ዶክተር..." ናትናኤል ድንገት ራሱን የገዛ መሰለ። "የምናገረውን፤ የምጠይቀውን ነገር አስቸጋሪነት በደንብ እረዳዋለሁ። ግን እንዲህ ያደረጉትን ሰዎች ማንነት የማረጋግጠው ሳገኘው ነው።"

"ይቅርታ የኔ ወንድም የኔ ኃላፊነት ሰውየውን ከሞት ማትረፍ ነው። የአጥፊዎቹ መያዝና አለመያዝ አያሳስበኝም።"

"እሱን ግን ያሳስበዋል!" አለ ናትናኤል ጣቱን በተዘጋው በር ላይ ቀስሮ። አብርሃምን ከሞት ታተርፋትም አታተርፋትም ይሆናል። በዚህች ደቂቃ ሊናገራት የሚፈልጋት ነገር አለች። ያንን ካልሰማሁ ከሱ በፊት ሌሎች በከንቱ እንደታረዱ ከሱም በኋላ ሌሎች ይታረዳሉ።"

"ልታነጋግረው አትችልም። ማለቴ ሊመልስልህ አይችልም።"

"አይኑን ማየት ይበቃኛል።"

ሃኪሙ ትክ ብሎ ተመለከተው። ከራሱ ጋር ክርክር የገጠመ መሰለ።

"ዶክተር... ደቂቃዎች እየጠፉን ነው። እነዚህ ደቂቃዎች ከሁላችን ለእሱ ይበልጥ ብርቅ ናቸው።"ናትናኤል የጨበጠውን የሃኪሙን ክንድ ይበልጥ ጨምድዶ ያዘው።

"ከግማሽ ደቂቃ በላይ አልፈቅድልህም። በዓይን ብቻ ነው የምታነጋግረው። ሊመልስልህ መሞከር የለበትም።" አለ ሃኪሙ። በሩን ከፍቶ ወደ ውስጥ አስገባው።

በጀርባው ተንጋሏል። ተስፋ ቆርጠው የመጨረሻዎቹን ደቂቃዎች አንድ በአንድ በትግዕሥት የሚሸኙ የሚመስሉት ዓይኖቹ ነጩ ኮርኒስ ላይ ተተክለዋል። ከራስጌው ከተንጠለጠሉት አራት ጠርሙሶች የሚነሱት ቀጫጭን ላስቲክ ቱቦዎች በክንዱና በጆሮ ግንዱ ላይ ከተሰገሰጉት መርፌዎች ጋር ተያይዘዋል። ድምፅ የለም በስተቀኝ የቆመ አንድ መሣሪያ ብቻ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት "እህ...እህ" የሚል፤ የሚያቃስት ይመስላል።

የአብርሃም ዓይኖች ናትናኤልን ሲያዩ ድንገት ነፍስ የዘሩ መሰሉ። ናትናኤል ጓደኛውን ቁልቁል ተመለከተው።

"እነሱ ናቸው?" አለ ናትናኤል እንባውን እየታገለ ጥያቄ ሳይሆን ተራ ዓረፍተ ነገር በመሰለ አነጋገር። ትክ ብለው የሚመለከቱት የጓደኛው የአብርሃም ዓይኖች 'አዎ' ያሉት መሰለው። ናትናኤል ጉሮሮው በምሬት ሲወጠር ተሰማው። "አብርሃም እኔንም እስኪገድሉኝ አልተዋቸውም።" አለ ናትናኤል አይኖቹን የሞላው እንባ የሚያየውን ሁሉ እየሰባበረበት እያወላገደበት። አብርሃም ፈገግ ያለ መሰለው። ድንገት ከተንጋለለበት



ለመነሳት ያሰበ ይመስል ከደረቱ ለጠጥ አለና መልሶ ተወጠ። አፉን ከፈተ። በጭንቀትና በስቃይ ተነፈሰ። "ካልቨርትን አግኝ...ካልቨርትን" አለ አብርሃም በለሆሳስ።

ናትናኤል ክንዱን ሲያዝ ተሰማው።

"በቃ።" አለው ሃኪሙ ክንዱን ይዞ።

"ቆይ... ትንሽ!... " አለ ናትናኤል ፊቱን ወደ ሃኪሙ መልሶ "እንዶ..."

"በቃ።" አለ ሃኪሙ ናትናኤል ሁኔታውን እንዳልተረዳ ሲመለከት ሁለት ክንዶቹን ያዝ አድርጎ። "በቃ አርፏል።"

ናትናኤል ፊቱን መንጭቆ ወደ ጓደኛው መለሰው። አብርሃም ፊት ላይ ምንም ለውጥ አይታይም። አሁንም ያየዋል። 'ሊሆን አይችልም!አልሞተም!'

ከአልጋው በስተግራ ቆማ የነበረች ነርስ የአብርሃምን አይኖች በመዳፏ መለስ ስታደርጋቸው እንደተከደኑ ቀሩ።

ሃኪሙ የናትናኤልን ክንድ ያዝ አድርጎ ከክፍሉ አወጣው።

ናትናኤል በሆስፒታሉ መተላለፊያ ያጋጠመው በደንብ ትዝ አይለውም። ብቻ በዚያ የነበሩ ሁሉ ያለቅሱ ይራበሹ እንደነበር ያስታውሳል። ግን ምን ጊዜም የማይረሳው በሩቁ እንደ ህልም የተሰማው ድምፅ አለ። የአብርሃም እጮኛ ምሥራቅ ሁለት እጆቿን ጭኖቿ ውስጥ ከትታ እንደ ህፃን ልጅ ጉብጥ ብላ እየተንሰቀሰቀች ያወጣችው ድምፅ... "አንተ ነህ የገደልከው! አንተ ነህ ገዳዩ! አንተ ነህ! አንተ!...አንተ!"

* * *

"አትነሳ... መጣሁ ቡና ይዤልህ።" ተነስታ ወጣች ርብቃ።

ናትናኤል ሃሳቡ እየተሰባሰበለት ሲመጣ የሆነው ሁሉ ድጋሚ እየመጣ ፊቱ ላይ ይመላለስ ጀመር። 'ወይኔ! ወይኔ አብርሃም! ግን ለምን? ለምን? ለምን ገደሉት? ምን አደረጋቸውና ገደሉት? እርሱ ነበር የእባቡን ጭራ የረገጠ። አብርሃም ለምን ተነደፈ? እሱ እንዴት ዳነ? እሱን እንዴት ተውት? ለምን ተውት?' በሃኪም ቤቱ ደረቅ አልጋ ላይ በጀርባው ተንጋሎ ያየው ጓደኛው በዓይነ ህሊናው አፈጠጠበት። ትክ ብለው ሽቅብ የተመለከቱት የአብርሃም ዓይኖች መጥተው ድቅን አሉበት። 'ናትናኤል አላልኩህም? በእሳት እየተጫወትን ነው አላልኩህም? የምመክርህ ነገር ቢኖር ይህን ነገር ማነፍነፍህን ትተህ በሠላም ስራህን እንድትሰራ ነው። እንደ እሳት እራት መጥፊያህን ስታሳድድ ዝም ማለት አልችልም! ናቲ

ራሴን ለአደጋ ማጋለጥ አልፈልግም... አባት መሆኛዬ ደርሷል... ልጁ አባት ይፈልጋል... ናቲ ለጥቅምት ሚዜዬ እንድትሆን ብጠይቅህስ ... ካልቨርትን አግኝ... ካልቨርትን... ካልቨርትን...ካልቨርትን

አይኖቹን እየሞላ ከላይ ከላዩ እየዋለለ የሚተንጎደጎደው እንባው አላቆምልህ አለው። ሌላ አስጠሊታ ድምፅ ጆሮው ላይ አንቃጨለበት

'...አንተ ነህ የገደልከው! አንተ ነህ ገዳዩ!አንተ ነህ!አንተ!...'

የአብርሃም አሙኛ ሁኔታ ታወሰው። እንደ እብድ በግራና በቀኝ ክንድና ክንዷን ይዘዋት ያ ውብ ፊቷ ተንጨባሮ እንደ ህልም ታየው። ጎንበስ ብላ ስትንሰቀሰቅ ፊቱ ላይ መጣችበት። ዓይኖቹን ጨመቃቸው።

'... አንተ ነህ! አንተ! አንተ!'

ናትናኤል ከቆመበት አልተንቀሳቀሰም። በሆስፒታሉ መተላለፊያ ፍዝዝ ብሎ እንደቆመ ቆየ። ከሆስፒታሉ የወጣው ዘግይቶ ነበር። ድንገት እራሱን በረጅሙ መተላለፊያ ብቻውን ቆሞ አገኘው። ከኋላው በር ሲከፈት ተሰማው። ፊቱን መለሰ። ሁለት ነርሶች ከፊትና ከኋላ ሆነው በተሽከርካሪ አልጋ ላይ የተንጋለለውን የኀደኛውን በድን እየጎተቱ ወጡ። ከጫፍ እስከ ጫፍ ነጭ ስስ ጨርቅ አልብሰውታል። በመተላለፊያው እየገፉ ይዘውት ሄዱ። በቆመበት ለመጨረሻ ጊዜ አብርሃምን ተሰናበተው። 'ናቲ ለጥቅምት ሚዜዬ እንድትሆን ብጠይቅህስ?'

አጥወለወለው። ቶሎ ብሎ ነጩን የሆስፒታል ግድግዳ ደገፍ አለና ቆመ። በቀስታ እየተራመደ ከሆስፒታሉ ህንፃ ወጣ። ከአጥሩ በር ሲደርስ የሆስፒታሉ ዘበኛ ለአንድ አፍታ ፊቱን ከተመለከተ በኋላ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በሩን ከፈተለት። ከአጥር ግቢው ወጣ። መንገዱን ሲሻገር ሲል ድጋሚ የሚያየው ሁሉ ብዥ አለበት። ቶሎ ብሎ መንገድ ጥግ ይዛ የቆመች ነጭ ሲትሮይን ላይ ደገፍ አለ። መኪናውን የት ነበር ያቆማት? እሩቅ ትሆን? አ...አይደለችም። 'ካልቨርትን አግኝ... ካልቨርትን...'

ከዚያ በኋላ የሆነው ጭጋግ ሆኖ ነው የሚታየው። ብቻ ርብቃ ደግፋ መኪናው ውስጥ ስታስገባው እንደ ህልም ትዝ ይለዋል።

"ቀና ብለህ ብትቀመጥ አይሻልህም?"

ትራሱን ከጀርባው አስገባችለት። አልጋው ላይ ተቀምጣ እፍ እፍ እያለች ማንኪያውን ወደ አፉ አስጠጋችለት። በደመነፍስ አፉን ከፈተ-ሾርባ። አፉ ውስጥ ቀፈፈው። ወይኔ አብርሃም! "በቃኝ"። አላት ማንኪያ የያዘውን እጇን በእጁ እየገፋ።

"ናቲ ምን መሆንህ ነው?...ራስህን ተቆጣጠረው እንጂ?"

"በቃኝ አልኩሽ በቃኝ።"



"እሺ በኋላ ራትህን ትበላለህ፤ ይሄን ጠጣ አሁን።"

ቀመሰው። ጠተት። አፉ ላይ ተንቀዋለለበት። ቢሆንም ሊያስቸግራት አልፈለገም። መልሶ ፉት አለው።

"በቃ ናትዬ። ጨክን ማለት ነው ያለብህ። ናትናኤል... አንተ ተጽናንተህ ቤተሰቦቹን ማፅናናት ነው ያለብህ።" አለች ርብቃ ትራሱን ከጀርባ እያስተካከለችለት።

ቤተሰቦቹ!

'...አንተ ነህ ገዳዩ!... አንተ ነህ!... አንተ!... አንተ!...'

ጠተት የያዘውን ብርጭቆ አቀበላትና በሁለት እጆቹ ጆሮዎቹን ጥርቅም አድርጎ ያዛቸው።

-9-

የበሩ ደወል ሲጮህ ከተኛበት በርግጎ ተነሳ። ከአልጋው ላይ የተበታተኑትን እርቃናቸውን ያሉ የሴቶች ፎቶግራፎች የያዙ መጽሄቶችን ሰብስብ አድርጎ ቁምሳጥኑን ከፈተና ወደ ውስጥ ወረወራቸው። የጠዋት ልብሱንና ጫማውን አጠለቀና ነጥብ 22 ብሬታ ሽጉጡን ከራስጌ አንስቶ ከመኝታ ቤቱ ወጣ። የበሩ ደወል ድጋሚ ሲያንባርቅ ሰዓቱን ተመለከተ። ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከሀያ።

ሽጉጡን በጠዋት ልብሱ የግራ ኪስ ውስጥ እንደከተተ የበሩን ሰንሰለት ሳይነቅል በሩን በቀጭኑ ከፍቶ ተመለከተ።

"አሃሮን!" በሩን ዘጋና ሰንሰለቱን ነቅሎ ቁልፉን ከፍቶ በሩን በረገደው። "ምን ሆነሃል?" አለ አመድ የመሰለውን የአሃሮንን ፊት ሲመለከት መንገድ ለቅቆ እያስገባው።

"አሁንም ተቀደምን።" አለ አሃሮን በብስጭት ፋረልን አልፎ ሄዶ በአንደኛው የሳሎን ሶፋ ላይ ዘፍ እያለ።

"ምንድነው ነገሩ?" ፋረል በሩን ቆልፎ ባለበት ፊቱን መልሶ አሃሮን ላይ አፈጠጠ።

"ገደሉት"

"ማንን?"

"አብርሃምን"

ፋረል በዝምታ ከአሃሮን ፊት ለፊት ተቀመጠና በግራ ኪሱ የያዛትን ብሬታ አውጥቶ መሃል ጠረጴዛ ላይ ወርወር አደረጋት።

"ጥፋቱ የኛ ነው። ሰውየው ስለ ካልቨርት የሚያውቀው ነገር እንዳለ ጠርጥሬአለሁ... እንዳልከው ብንመለምለው ኖሮ..."

"እንዳትመለምለው የገፋፋሁህ በበቂ ምክንያት ነው።" አለ አሃሮን እራሱን በመከላከል ዓይነት። «ለዛውም ሰውየውን እንዲህ በቀላል ልትመለምለው የምትችል አይመስለኝም።»

"እሱ ችግር አይፈጥርም ነበር። ወኪል አመላመል ስማር አስተማሪዎቹ በንቁ አይኖች እንድከታተል የነገሩኝን እያንዳንዱን ነጥብ የሚያሟላ ሰው ነበር። አንደኛ ከፍተኛ የባንክ ዕዳ አለበት" አለ ፋረል ጣቶቹን ሁሉ ጨብጦ የአውራ ጣቱን ቀስሮ "ሁለተኛ" አለ አመልካች ጣቱን አወጣና "ለአለቆቹ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳለው እዚያው ካለ ወኪሉ ተረድቻለሁ። ብቻ ያ ሁሉ ዋጋ የለውም አሁን" አለ ድንገት እጁን አወናጭፎ።

"አሁን ዋናው ጥያቄ ለምን ገደሉት የሚለው ይመስለኛል።" አሃሮን በረጅሙ ተነፈሰ።

"ለዚህ ምንም ጥርጥር የለኝም። ሰውየው አንድ የደረሰበት ምስጢር አለ። ወይ ሁላችን የምንፈልገውን ካልቨርት ይዞት የተሰወረውን ምሥጢር ያውቃል። አለበለዚያም የካልቨርትን አድራሻ ደርሶበታል።"

"ጥሩ" አለ አሃሮን ፋረልን ወደሚፈልገው መስመር እየመራ። "ግን እስካሁን ለምን ሳያስወግዱት ቆዩ...ትላንት ማታ ምን አዲስ ነጥብ ተገኘ?"

"ያንን ለመናገር ይከብዳል" አለ ፋረል። በብስጭት ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ መጠጥ መደርደሪያው እየሄደ። በጠዋት ለመጠጣትና ላለመጠጣት ጭንቅላቱ እርስ በርሱ ሲጋጭበት ለአንድ አፍታ ቆም አለና ፊቱን ወደ አሃሮን መለሰ። «አሃሮን አገናለሁ...ግን አሁን ያሰኘኝ ቁጭ ብሎ ማልቀስ ነው። አንደ ብትወጣልኝ ያንን ነበር የማደርገው። ሰዎቹ ጤነኛ አይመስሉኝም። እያንዳንዱን ፍንጭ ያለርህራሄ የሚገድሉ ከሆነ..."

"ብስጭቱን ለጊዜው እናቆየውና ወደ ፍሬነገሩ እንመለስ። ትላንት ምን አዲስ ነገር ስላገኙ ይመስልሃል አብርሃምን የገደሉት?" አለ አሃሮን ረጋ ባለ መንፈስ።

"አላውቅም።" አለ ፋረል ያቀመቀመ ጉንጩን እየፈተገ መጥቶ በወንበሩ ላይ እየተቀመጠ።



"ሮበርት... እኔ ግን ቀን ከተገናኘው ሰው ጋር በተያያዘ ምክንያት ይመስለኛል ለሞት የበቃው። ምናልባት አብርሃም ለውጭ ጉዳዩ ሰው የሰጠው መረጃ ይኖራል። አለበለዚያም እሱ ራሱ ከሰውየው ያገኘው ወደ ወጥመድ የከተተው ምስጢር አለ። ያም ሆኑ ይህ የሁለቱ መገናኘት ለጊዜው ልንገልፀው ያልቻልነው ሚዛን አናግቷል።"

"እሺ ልክ ነህ እንበል።" አለ ፋረል እግሮቹን አጣምሮ ወደኋላ እየተለጠጠ።

"ለዚህ ሚዛን መናጋት ምክንያት የሆነው የሁለቱ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ ከሆነ ይህን ማግኘት የምንችለው ከማን ነው ትላለህ?"
"ከውጭ ጉዳዩ ሰው።"

"ጥሩ። ግን ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ሁኔታውን ስትመለከት ለአብርሃም ሞት ምክንያቱ የሁለቱ ግንኙነት የጋራ ምሥጢራቸው ከሆነ የውጭ ጉዳዩ ሰው ለምን አልተገደለም?"

"ምን ለማለት ነው የፈለከው?" አለ ፋረል ቀንድቦቹን አኮሳትሮ። "የውጭ ጉዳዩ ሰው አብርሃም ምን ያህል እንደሚያውቅ ለመመርመር የተላከ ወጥመድ ነው ለማለት ነው?"
"ሊሆን አይችልም?"

"አይመስለኝም።" አለ ፋረል በእርግጠኝነት "አንደኛ የውጭ ጉዳዩ ሰው የመረጃ ሰው ቢሆን አብርሃም ጋ ደውሎ በግልጽ አያወራም። ሁለተኛ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ከመኮንኑ ጋር ያደረገው ንግግር ሰውየው ምንም እንደማያውቅ የሚያሳይ ነው።"

"በጣም ግሩም" አለ አሃሮን ፈገግ ብሎ "የፈለግሁት ይህን ነው። ሮበርት አሁን አንተ የተናገርከውንና እኔ ያቀረብኩትን ሃሣብ በአንድ ላይ ስመውሰድ ከፈለግን የውጭ ጉዳዩ ሰው ወይ ፍፁም አሳሳች የሆነ አደገኛ የመረጃ ሰው ነው፤ አለበለዚያም ፍፁም ምንም የማያውቅ አደገኛ ደደብ ነው። ከሚለው ድምዳሜ እንደርሳለን።"

"እና?" አለ ፋረል የአሃሮን አቅጣጫ አልገለጥልህ ሲለው።

"እናማ... አንድ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ እስከሆንን ድረስ ወይ አውቆ የያዘውን አለበለዚያም ሳያውቅ በየዋህነት እጁ የገባውን ከፍተኛ ምሥጢር እጃችን ማስገባት እንችላለን።"

"ምንድነው ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን ያለብን?" አለ ፋሬል አሃሮንን አትኩሮ እየተመለከተ።

"አፍኖ ማስቃየት።" አለ አሃሮን በጨበጠው ቡጢ ጉልበቱን ደልቆ።

"የፈጣሪ ያለህ! በኔ በኩል የዚህ አይነት ሥራ ሊሰሩ የሚችሉ የመስክ ሰዎች ለጊዜው የሉኝም።" አለ ፋረል የቀኝ እጁን አንስቶ። የስሁብትም ለማለት እንደፈለገ ሁሉ። "ከዛም በላይ ለንደን እጄን እንዳረጥብ ለጊዜው ፈቃደኛ አይደለም።"

"ሁሉን ለኔ ተወው" አለ አሃሮን ተነስቶ እየቆመ። "ካንተ የምፈልገው ነገር በዚህ ሰውዬ ዙሪያ ያሉ ሰዎችን ሁሉ ስልክ እንድትጠልፍልኝ ነው። ለጥቂት ቀናት መግቢያና መውጫውን መከተል እፈልጋለሁ...ከዚያ ልክ አገባዋለሁ።"

"ለስልኩ ችግር የለም።" አለ ፋረል። "ያንን በጥቂት ሰዓታት እፈጽመዋለሁ።"

"በበኩሌ በዙሪያው ያሉ የሚቀርቡትን ሰዎች በቋሚ ክትትል አሸፍናቸዋለሁ።" አለ አሃሮን ለመሄድ እየተነሳ። "እመነኝ ይሄ ሰው ወደ ካልቨርት የሚያደርሰን ትኬት ነው።"

-10-

ናትናኤል በማግስቱ ጠዋት ከተኛበት ጠንክሮ ቢነሳም አብርሃም ቤተሰቦች ጋ ሄዶ ለማጽናናት አልደፈረም። 'ደፍሮ ቢሄድስ ምን ብለው ይቀበሉት ይሆን? ገዳዩ ማን ሆነና?'

ርብቃን ላለማስከፋት ሲል ያቀረበችለትን ቁርስ በዝምታ ተመገበ።

"ናትናኤል... ግን ዛሬ ለምን እቤት አትውልም?እኔም አለቃዬን አስፈቅጄ እመለሳለሁ። አልቆይምኮ" አለችው።

አልመለሰላትም። እንዳቀረቀረ ራሱን ነቀነቀ- "አይሆንም" ለማለት።

"ናትናኤል ደህና አይደለህምኮ።"

"ርብቃ ሥራ ብገባ ነው የሚሻለኝ። እዚህ ከዋልኩ የባሰ ነው። አንቺም ግቢተሽ ስሪ፤ ትላንት ቀረሽ። ዛሬ ደግሞ..."

ቢሮዋ አድርሷት ሲመለስ ርብቃ እጁን ያዘ አድርጋ አይን አይኑን አየችው-



"ናቲዬ አደራ ረጋ በል። ቢሮህ እደውልልሃለሁ።" እጁን ይዛ አስጠነቀቀችው። ጭንቅላቱን በእሺታ ነቀነቀላት። ጉንጩን ስማው ከመኪናው ወረደች።

ቢሮው ደርሶ ወደ ውስጥ ሲገባ ፀሃፊው ከመቀመጫዋ ተነስታ ተቀበለችው።...

"እንደምን አደርክ፤ በደህና ነው የጠፋኸው?" አለች ፈገግ ብላ።

"እንደምን አደርሽ ሳምራዊት። ደህና ነኝ ትንሽ ..." የቢሮውን በር ከፍቶ ገብቶ ከወንበሩ ላይ ከተቀመጠ በኋላ በባዶው አየር ላይ አፈጠጠ። የሆነው ሁሉ በቅዠት ዓለም የተደረገ ይመስል ተምታታበት።

ቃል ገብቷል። ቃሉን አያጥፍም። "እኔንም እስኪገድሉኝ አልተዋ ቸውም።" ብሎታል። ቃሉን አያጥፍም። ወይ እነሱ ይቀድሙታል። ወይ እሱ ይቀድማቸዋል። ግን አይተዋቸውም። በፍጹም አይተዋቸውም!የታች ከንፈሩን በጥርሱ ቀርጥፎ ያዘው።

ሁኔታውን በሙሉ አንድ በአንድ ለአለቃው ይነግራቸዋል። እርግጠኛ ነው በሚችሉት ሁሉ አብረውት እንደሚቆሙ እርግጠኛ ነው። ካስፈለገም መሰማራት ያለበት ሰው ሁሉ ተሰማርቶ በገቡበት ጉራንጉር ያሳድናቸዋል። ከዚህ በኋላ ምንም መሸፋፈን የለም። ማንም ከመንገዱ አይመልሰውም። ማንም ከእጁ አያድናቸውም! በጨበጠው ቡጢ ውስጥ ጥፍሮቹ የገዛ መዳፉን ሰርስረው የገቡ መሰለው። የቢሮው በር ሲከፈት ቀና አለ። ሳምራዊት ነበረች።

"እነዚህ ጠዋት የመጡ ሪፖርቶች ናቸው። ትላንት የመጡትን ወረቀቶች እዚህ ጋ አድርጌልሃለሁ። እ... ትላንት በጣም ፈልገውህ ነበር።" አለች ፀሐፊው ወረቀቶቹን ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠችለት። ቢሮ እንደገባ እንዲመጣ ብለው ነበር።

"ገብተዋል አሁን?" ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ ጠየቃት።
"አዎ።" ጭንቅላቷን ወዘወዘችለት።
የቢሮውን በር ከፍታ ከመውጣቷ በፊት መለስ አለችና-
"ትላንት ምን አጋጠመህ?ችግር አለ እንዴ? " አለች።
"ምንም ችግር የለም" አላት በአጭሩ ለመገላገል።
"ቡና ይምጣልህ? ቁርስም አልበላህ እንደሆን።"
ናትናኤል ጭንቅላቱን ነቀነቀ "አያስፈልግም" ለማለት።
ሳምራዊት ለአፍታ ትክ ብላ ተመልክታው በሩን በቀስታ ዘግታ ወጣች።

አሁኑኑ ሄዶ እያንዳንዱን ነገር እያፍረጠረጠ ያስረዳቸዋል። አብርሃም የነገረውን ምሥጢር ሁሉ ገልጾ ይነግራቸዋል። ለነዛ ነፍሰ በላዎች

ጊዜ ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ በፍፁም!ከመቀመጫው ተነስቶ ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን ይዞ ከቢሮው ወጣ፡፡

"እንደምን አደርሽ፡፡" አላት የአለቃውን ፀሐፊ ወደቢሮዋ ሲገባ፡፡

"ውይ!ናትናኤል እንደምን አደርክ... ምነው ጠፋህ፡፡ በደህና ነው?" ጥፍሯን ትሞርድበት የነበረውን ሞረድ ጣል አድርጋ ጨበጠችው፡፡

"ፈልገውኝ ነበር መሰለኝ ትላንት፡፡"

"በጣም፡፡ አስሬ ይሆናል 'ያንን ልጅ ጥሪልኝ' ያሉት፡፡ በደህና ነው ግን የቀረኸው?" የጥፍሯን ሞረድ እያነሳች ጠየቀችው፡፡

"ትንሽ ችግር ገጥሞኝ ነው፡፡ ሰው አለ ወይስ ልግባ?"

"ግባ-ግባ፡፡" አለች ቅንድቦቿን ሰማይ ሰቅላ በቀኝ በያዘችው የጥፍር ሞረድ ወደ ቢሮአቸው በር እያመላከተችው፡፡

ናትናኤል የአለቃውን ቢሮ መዝጊያ አንኳኩቶ ገባ፡፡ ቢሮአቸው ከወትሮው ይበልጥ በፒፓቸው ጭስ ታፍኗል፡፡ አለቃው ጀርባቸውን ለበሩ ሰጥተው ውጭ ውጭውን እያዩ ቆመዋል፡፡ በሩን ዘግቶ ወደ ውስጥ ሲዘልቅም ጀርባቸውን ሰጥተውት ከቆሙበት አልተነቃነቁም፡፡

ናትናኤል ጉሮሮውን ሲያፀዳዳ ድንገት ዞር ብለው ተመለከቱት፡፡

"ናትናኤል!... የት ጠፋህ? አጥብቄ ፈልጌህ ነበር፡፡" አሉ ለአንዳፍታ ፒፓቸውን ከአፋቸው አላቀው፡፡ ራመድ ራመድ አሉና ወደ ወንበራቸው ተመልሰው ቀቀመጡ፡፡ "ቁጭ በል! ቁጭ በል!" ሁኔታቸው ከወትሮው የተለየ ሆነበት-አለቀጥ ተጣደፉበት፡፡ "እ...ምን ላይ እየሰራህ ነው? ማለቴ የተለየ የያዝከው ጉዳይ..."

ናትናኤል የጥያቄቸው እንግዳ መሆን ብቻ ሳይሆን የድምፃቸው መርገብገብና የሰውነታቸው መቁነጥነጥ አስገረመው፡፡ እረፍት ያጡ ይመስላሉ! ቢሆንም አጋጣሚው አሁን እንደሆነ ገመተ፡፡ ነገሩን ዘርዝሮ ሊያስረዳቸው የሚገባው አሁን ነው፡፡ ጊዜ ማጥፋት የለበትም! እነዛ ነፍሰ አጥፊዎች እስኪሰወሩ ጊዜ መስጠት የለበትም...

"ባለፈው ሰሞን የአፍሪካ ኤምባሲዎች ባደረጉት እንቅስቃሴ ላይ ነው የምሰራው ያለሁ...እ... የላይቤርያው አታሼ..."

"ተወው- ተወው» አሉት አቋርጠው፡፡ ናትናኤል ግራ ተጋብቶ በዝምታ ይመለከታቸው ጀመር፡፡ አለቃው እንዳቀረቀሩ በጠረጴዛቸው ላይ የተቆለለውን ወረቀት እያመሰ ቀጠሉ፡፡ «ተወው ናትናኤል...እሱን ለጊዜው



ተወውና ቀደም ብለህ ጀምረኸው የነበረውን በምዕራብ አፍሪካ ለሚገኙ ኤምባሲዎቻችን የምንልካቸውን ሰዎች..."

"ይህኛው አስቸኳይ መስሎ ስለታየ ነበርክ እዚህኛው ላይ ያተኮርኩት፡፡" ነድድ ብሎት አቋረጣቸው፡፡

"አዎ... ነበር... ነበር ግን አሁን አስቸኳይ አይመስለኝም...እየህ ጉዳዩን ፖሊሶች እየተከታተሉት ነው፡፡ በሥራቸው ጣልቃ እንድንገባ አይፈልጉም፡፡"

"ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን አስቸኳይ ነው፡፡» በወንበሩ ላይ ወደ ፊት አገዝምሞ ድጋሚ አቋረጣቸው..«የሰው ነፍስ እየጠፋ ነው፡፡" ለድምፁ አስፈሪ ቃና ለመስጠት ሞከረ፡፡

ለአንድ አፍታ ካቀረቀሩበት ቀና ብለው ተመለከቱት፡፡ በዓይን ንግግር የጀመሩ መሰሉ፡፡ ዓይኖቹን ሳይሰብር ፊት ለፊት ተመለከታቸው፡፡ "እ? የምን የሰው ነፍስ መጥፋት? ማ? እከ ማ?" ብለው እስኪጠይቁት በናፍቆት ተጠባበቀ፡፡

"ያ የእኛ ሥራ አይደለም፡፡ የፖሊስ ነው... የምልህን አድምጥ ናትናኤል፡፡""አሉት ቀዝቀዝ ብለው፡፡

"በመጀመሪያ ያድምጡኝ፡፡ ያኔ...."

"ናትናኤል" ድጋሚ አቋረጡት፡፡ "ናትናኤል... በዚህ ጉዳይ ውስጥ ድጋሚ እጅህን እንድትከት አልፈልግም፡፡" አለቃው ከተቀመጡበት ተነስተው ቆሙ፡፡ 'ከቢሮዬ ውጣልኝ' ማለታቸው እንደሆነ ተረዳ፡፡ "እንደ አለቃ ሳይሆን እንደ አባት ሆኜ ነው የምመክርህ፡፡" ድምጻቸውን አረጋዊ ለዛ አላብሰው ሊያግባቡት ሞከሩ፡፡

"ቆይ ላስረዳዎት፡፡ ሁኔታውንኮ አልተረዱትም፡፡ ነገሩ ሌላ ነው፡፡" አለናትናኤል ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ ሽቅብ እየተመለከታቸው፡፡ "ጓደኛዬ..."

"ምንም የምታስረዳኝ ነገር የለም፡፡ አርፈህ ሥራህን ስራ፡፡" የጀመረውን ሳይጨርስ አቋርጠው በቆሙበት እጃቸውን ዘረጉለት፡፡

"አርፌህ ሥራህን ሥራ አብርሃም!" ናትናኤል ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመ፡፡ ዓይኖቹ የማያዩት፣ ጆሮዎቹ የማይሰሙት፣ ሁሉም ህልም መሰለው፡፡

ናትናኤል ለአብርሃም 'የኔ አለቃ የሚገፋፉኝ ፍሬ ያለው ነገር ይገኘ እንድመለስ ነው' ያለው ትዝ አለው።

አብርሃም '... እንግዳው አለቃህም እንዳንተ አይናቸው ተሸብቧል... 'ብሎት ነበር።

'የአለቃው ዓይን ተገለጠ ማለት ነው? እሱ የማያየውን ምሥጢር መመልከት ጀመሩ ማለት ነው? የእሱ አይን መቼም አይገለጥ። እንዲገለጥም አይሻ! የተዳፈነው፣ ያበቃው የእሱ ጓደኛ ነው። አብርሃም ነው።'

ናትናኤል ትክ ብሎ አለቃውን ተመለከታቸው። አይናቸውን ሰበሩ። በጎንና በጎን ያንጠለጠሏቸው ክንዶቻቸው የእርሳቸው የራሳቸው እንዳልሆኑ ሁሉ ረዘሙበት፣ ተንዘላዘሉበት። እንደገና ቀና ብለው ሲያዩት አይኖቻቸው ውስጥ የሚጋልበውን ያልተገራ ሌጣ ፍርሃት ተመለከተ። አዘነላቸው። ተፀየፋቸው።

ግድ የለም። ብቻውን ወደ ጨለማው ይወጣል። ያለረዳት ብቻውን አድኖ ይይዛቸዋል። ቀድሞውንም አለቃውን ተማመኖ አልተነሳም። ቃል ገብቷል ለአብርሃም -'አልተዋቸውም' ብሎታል። ሞት? ግድ የለውም። አብርሃም እንኳን ልጁን ትቶ ሄዷል። እሱ አንድ ነው። ብቻውን ነው። ቢቀርም ቢሄድም ማንንም አይጎዳም።ርብቃ? አዎ። ግን ቢጤዋን አታጣም። ቃል ገብቷል። ከአሁን ወዲያ አይመለስም። ህግ ፊት እስኪያቀርባቸው፣ በገመድ ተንጠልጥለው ዥው ዥው ሲሉ እስኪያይ አያርፍም።

"የእሙት ፈቃዱን አሁን መውሰድ እችላለሁ?" አላቸው አለቃውን።

አልተናገሩም። ጭንቅላታቸውን በ'አዎንታ' ነቀነቁለት። የዘረጉለትን እጃቸውን ሳይጨብጥ ፊቱን መለሰ። የቢሮአቸውን መዝጊያ ከፍቶ ከመውጣቱ በፊት የበሩን እጀታ እንደጨበጠ ዞር ብሎ አይኖቹን አጥብቦ ተመለከታቸው።

"ዓርብ እለት አንድ መላምት ላይ እንድደርስ ጠይቀውኝ ነበር። የጠየቁኝ መላምት ላይ ደርሻለሁ...አዲስ አበባ ውስጥ አንድ አውሬ ገብቷል።" አላቸው።

ለአንድ አፍታ አገጫቸው የተንጠለጠለ መሰለው። የቢሮአቸውን በር ዘግቶ ወደ ቢሮው አመራ።

ወደ ቢሮው ተመልሶ በጠረጴዛው ላይ የነበረውን ወረቀት ሁሉ እየሰበሰበ በመሳቢያው ውስጥ ያጭቅ ጀመር። ብዕሮች፣ ወረቀቶች፣ መሰፊያዎች፣ የፋይል ትሬዎች... አንድ በአንድ እየተነሱ ከታችኛው መሳቢያ ውስጥ ታጎሩ። ጠረጴዛው እራቁቱን ሲቀር ከወንበሩ ላይ ተቀመጠና ሁለት



መዳፎቹን በባዶው ጠረጴዛ ላይ ጫናቸው። 'ካልበርትን አግኝ... ካልበርትን...' የአብርሃም ድምፅ ደጋግሞ ተሰማው።

ሙሉ ሃሳቡን አሰባስቦ አንድ ቦታ ማዋል አለበት... ባለው ኃይሉ ፈጥኖ ማሰብ አለበት። ብቻውን ነው። ጠላቶቹ የዋዛ አይደሉም። አብርሃም እንዳለው እንደ እሳት እራት ወደፍሙ እየተሽቀዳደመ ነው... መቃጠል የለበትም... መንደድ የለበትም...መጋየት የለበትም...ሁልጊዜ መቅደም አለበት... ሁሉጊዜ ከፊት መገኘት አለበት... መበለጥ አይችልም... ሁልጊዜ መብለጥ አለበት። አለዛ እንደ አብርሃም ያበቃል... አለዛ ያቃማል...ሁሉም ነገር ያከትማል። ማክተሙን አይፈራም። ግን እሳቱን ማጥፋት አለበት። የንፁሃንን ነፍስ እየቀጠፈ በመሃላቸው የሚመላለሰውን አውሬ አጥምዶ መያዝ አለበት። ከየት ነው መጀመር ያለበት? ለፖሊስ ማስታወቅ? አዎ ፖሊስ ጋ ሂዶ ጉዳቸውን ማፍረጥረጥ፣ የስውር ክትትል ዘርግቶ አንድ በአንድ ማስለቀም። ግን...

የአብርሃም አደራ ታወሰው- "ካልበርትን አግኝ... ካልበርትን..."

ናትናኤል መሳቢያውን ስቦ ነጭ ወረቀት አወጣ። ከደረት ኪሱ ውስጥ ብዕር። ነጩ ወረቀት ላይ ሃሳቡን ያሰፍር ጀመር።

አንድ፡ በአፍሪካ ኤምባሲዎች የሚሰሩ ወታደራዊ አታሼዎች ወደየአገሮቻቸው እየተጠሩ ሄዱ ማለት...የየአገሮቻቸው መንግስታት ሊገልፁላቸው፣ ሊያሳውቋቸው፣ ሊያስጠነቅቋቸው የሚገባ ሁኔታ ተፈጠረ።

ሁለት፡ አንዳንድ አታሼዎች ሲመለሱ የተቀሩት በሌሎች ተተኩ ማለት... ገሚሶቹ ለተመደቡበት ሃላፊነት ብቁ ሆነው በመገኘታቸው ሲመለሱ፣ የተቀሩት ለሃላፊነቱ ተስማሚ በማይሆኑ በሌሎች ተተኩ።

ሶስት፡ ለሥራው ብቁ ተብለው ከተመለሱ አታሼዎች መካከል በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁለት ተገድለው ሲገኙ አንድ የገባበት ጠፋ ማለት... የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለታቸው አለበለዚያም ብቃት ስለጎደላቸው በአውሬው ተበሉ... ሁለት ተወገዱ፣አንድ ተሰወረ።

አራት፡ ሁኔታውን መከታተሉና ማጣራቱ ተገቢ ቢሆንም የኢትዮጵያ መንግሥት አካላትም ሆኑ ሌሎች የአፍሪካ መንግሥታት ነገሩን መሸፋፈንን መረጡ ማለት... የአፍሪካ መንግሥታት እንዳይወጣ የሚሹት ምሥጢር ተፈጠረ አለዚያም በዙሪያቸው የተተበተበው የአውሬው መረብ መነቃነቅ ከለከላቸው።

አምስት፡ አንዳንዶቹ የጠፋውን የላይቤርያ አታሼ ለማግኘት በግል ያደረጉት ጥረት አደጋ ላይ ጣላቸው ማለት... የላይቤርያው አታሼ አድራሻ እንዳይገኝ የሚሹ ወገኖች ምሥጢሩ እንዳይጋለጥ ሲሉ ነፍስ እስከማጥፋት ይደፍራሉ።

ናትናኤል ድንገት አንድ ጥያቄ ተደነቀረበት። 'አብርሃም ብቻ አልነበረም የሳይቤርያውን አታሼ አድራሻ ያነፈነፈ። እንዳውም በተቃራኒው ነገር ቆስቋሹ እርሱ ራሱ ነበር። ታዲያ ለምን አብርሃምን ገደሉት... እሱንስ ለምን ተውት?'

ፖሊሶች አብርሃምን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ቆስሎ አገኙት። እሱጋ ስልክ የተደወለለት ወዲያውኑ ነው... በዚያ ሌሊት በስልክ የጠራው አብርሃም አልነበረም። አብርሃምን የገደለ ጎርናና ድምፅ ነበር እሱንም የጠራው። አብርሃምን ከገደሉ በኋላ እሱን በስልክ ጠርተውታል። ታዲያ እንዴት ሳይገድሉት ቀሩ? ጠርተውት አልቀረም ሄዷል። በተባለው ቦታ መኪናውን አቁሞ አነስተኛ መብራቱን እንዳበራ ጠብቋቸዋል። ታዲያ እንዴት... ?

"ትራፊክ ፖሊስ!" አለ ናትናኤል ጮሆ። መልሱ ድንገት ብልጭ አለለት። 'ትራፊክ ፖሊስ አደናቀፋቸው?' እንዳቀዱት ሳይገድሉት በፊት የትራፊክ ፖሊሱ ደርሶ አጨናገፋቸው? ትራፊክ ፖሊሱ ባይዘውስ ኖሮ... ትራፊክ ፖሊሱ ባይደርስ ኖሮ... ናትናኤል ዘገነነው። ለአንድ አፍታ በሃኪም ቤቱ የብረት አልጋ ላይ ተንጋሎ ያየው የአብርሃም ፊት እፊቱ ላይ ድቅን አለበት። ይሄኔ እሱም ሞቶ ነበር ማለት ነው? ግን ለምን? ያማ ግልጽ ነው። ከአብርሃም ጋር የተገናኘበትን ጉዳይ ተረድተውታል ማለት ነው። ግን እንዴት? አብርሃምን በስልክ አነጋሮታል። ስልክ ጥሩምባ ነው... ሁሉም ይሰማዋል። በአንድ ምሽት ሁለቱንም ሊገድሏቸው ነበር ማለት ነው። በአጋጣሚ ነው የመለጣቸው? እና አሁንስ? ምንድነው የሚጠብቀው? ምንድነው ዕድሉ? ናትናኤል እያንዳንዱ ነገር እየተገለጠለት ሲመጣ ስጋቱ ጥፍር አውጥቶ ይቧጥጠው ጀመር።

'የሳይቤርያውን አታሼ አድራሻ እንደማነፈንፍ ሲያውቁ ሊገድሉኝ በስልክ ጠሩኝ! ናትናኤል ከወረቀቱ ላይ ቀና አለ።' አዎ ቀዳዳው ያለው እዚህ ነው። አንድ ድክመት አላቸው። እንቅልፍ የነሳቸውና የሚያቁነጠንጣቸው ቁስል አለ። አብርሃም እንዳለው ሰውየው በገዛ ፈቃዱ ተሸሽጓል። በእጃቸው ያልገባላቸው ቁልፍ እርሱ ነው። ይዘውት ቢሆን ኖሮ ገድለው ወይም ሰውረውት ይረጋጉ ነበር። ነገር ግን ሊያገኙት አልቻሉም - የሳይቤርያውን አታሼ! ቁልፉን። ይህ ማለት ደግሞ እነርሱ ሳያገኙት በፊት የሳይቤርያውን አታሼ እጁ ያገባ ወገን ጉዱን ያፍረጠርጠዋል። ምሥጢሩን ያዝረበርበዋል ማለት ነው። ያ ነው ቁልፉ? አብርሃም በመጨረሻ 'ካልቨርትን አግኝ' ያለው ለዚህ ነው! ፖሊስ ጋ መሄድ የለበትም። ቁልፉ ያለው እዚያ አይደለም። ቁልፉን! የሳይቤርያውን አታሼ ብቻውን ማግኘት አለበት። ግን እንዴት? አብርሃም ስለ ሳይቤርያው አታሼ የነገረውን ለማስታወስ ሞከረ።

መረጃ....የውስኪ ጠርሙስ...ሾፌር...ቤላ መጠጥ ቤት... የእሥራኤል ፓስፖርት የያዘች ሴት... ሞሳድ... ኤም.አይ.ስድስት... ካዛንቺስ... ወዳጁ



ቤት... የሴት ልብስ ለብሶ... ተሰወረ... ከአብርሃም የሰማው ሁሉ በቅዕበቱ ትዝ አለው።

ናትናኤል አይኖቹን ጨፍኖ አሰበ። 'የሳይቤርያው አታሼ በማንም እጅ ውስጥ አይደለም ማለት ነው። ከአገሩ መንግሥት መሸሹ ግልፅ ስለሆነበት እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ተሸሽጎ ተቀምጧል። እንዲያ ባይሆን በዲፕሎማቲክ መብቱ መጠቀም ይችል ነበር። እንግዲያው ሲያገለግላቸው የቆዩት የእንግሊዝ ወይንም የእሥራኤል ስለላ ድርጅቶች ለምን በሽፋን አላወጡትም? ምናልባት ከነርሱም ጋር ያልተጣጣሙበት ነጥብ ይኖራል። ስለዚህ ከነሱም መሰወሩ አስፈላጊ ሆነ።እንግዲህ ግልፅ ፍሊጋ እንዳይደረግበት የሚከላከልለት ማነው? የአገሩ መንግሥት? ሊሆን አይችልም። የኢትዮጵያ መንግሥት? ይህም አይሆንም። የእንግሊዝና የእሥራኤል ተጽዕኖ? አይመስልም። እንግዲያው ማን?'

'ማንም ሆነ ማን ይህ ወገን የሳይቤርያው አታሼ ይዞት የተሸሸገውን ጉድ ደብዛ ለማጥፋት ሲል ነፍስ ከማጥፋትና ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ከማስፈራራት የማይመለስ ነው! ብዙ አይኖች ይኖሩታል! ብዙ ጆሮዎች ይኖሩታል! ረጅም እጅ አለው! ጥፍሮቹ ሹል ናቸው! ጥርሶቹ ስል ናቸው! አስቀያሚ አውሬ...'

ናትናኤል የጨፈናቸውን አይኖቹን ገልጦ ባዶው አየር ላይ አፈጠጠ። 'እንዴት አድርጎ ነው ከዚህ አውሬ መሸሽ የሚችለው? አውሬው እንዴ ሊበላው ሞክሯል። ድጋሚ ሊሞክርም ይችላል። የመጀመሪያውን በአጋጣሚ አምልጧል። ሁለተኛውንስ እንዴት ማምለጥ ይችላል? አውሬው ሁሉን ያያል! ሁሉን ይሰማል! ግን ደግሞ የሳይቤርያውን አታሼ ከጥርሱ ሊያገባው አልቻለም። ለምን? የሳይቤርያው አታሼ ስለተሰወረ።' ደጋግሞ አሰበ።

'እንግያዲው እሱም እንደሳይቤርያው አታሼ ድንገት መሰወር ነዋ' በጠራራ ፀሐይ ተንኖ መጥፋት። ያ ነው መድሃኒቱ። አለበለዚያ.... ' የአብርሃም ፊት መጣበት። ዘገነነው።

የውጭ ስልክ ጮኸ። አነሳው።
"ሃሎ።"
"ሃሎ - ናቲ?"
"ሃይ ርብቃ" ናትናኤል ፊቱ ላይ የወረዛውን ቀዝቃዛ ላብ በመዳፉ አበስ አደረገው።
"እንዴት ነህ? ደህና ነህ?"
"በጣም።"
"ከሥራ እንደወጣህ መጥተህ ውሰደኝ። አንተጋ ነው የማድረው።"

## -11-

"ጥሩ" አለ ብርጋዴር ጄነራሉ ለበርካታ ደቂቃዎች ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ለማርቆስ አንድ ዕድል ለመስጠት ወስኖ:: "ሁለት ቀን እሰጥሃለሁ:: በዚህ ጊዜ ውስጥ የሰውየውን ንፁህነት ማረጋገጥ የምትችል ከሆነ..." የጀመረውን ዓረፍተ ነገር ሳይጨርስ አቋረጠ::

"እመነኝ:: ናትናኤል ምንም አያውቅም:: እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን በወኪሌ እየተከታተልኩት ነው:: ከአብርሃም ሊያገኝ ይችላል ብለን ስለፈራነው መረጃም በዝርዝር አጣራለሁ:: ከዛሬ ማታ አያልፍም::" አለ ማርቆስ:: ለጊዜውም ቢሆን በናትናኤል ላይ የተላለፈውን የሞት ውሳኔ ለማዘግየት በመቻሉ እየተደሰተ::

"የአብርሃም ቤተሰቦች ጉዳይስ?"

"አዎ" አለ ማርቆስ ፈጠን ብሎ "እንዳልኩህ ወደ ፖሊስ ሄደው አብርሃም የሞተው ከናትናኤል ጋር እንደወጣ መሆኑንና ናትናኤልንም ስለሚጠረጥሩ ተይዞ እንዲመረመርላቸው ፖሊስን እየገፋፉ ነው:: ቢሆንም አብርሃምን የገደለችው ሴት ለመሆኗ ምሥክሮች አዘጋጅተን ፖሊሶችን በፈለግነው መስመር እየመራናቸው ነው::"

"ጥሩ :: ግን አሁንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት አንድ ውሳኔ ላይ እስከምንደርስ ድረስ ናትናኤል በምሥክርነትም ሆነ በሌላ መልኩ ከጠበቆች ወይም ከፖሊስ ከማንኛውም ወገን ጋር ግንኙነት አድርጎ ስለ አብርሃም የሚያውቀውን መናገር የለበትም:: ያንን መጠበቅ ያንተ ሃላፊነት ነው::" አለ አለቅየው አመልካች ጣቱን በማርቆስ ላይ ቀስሮ::

"ሁሉን ለእኔ ተወው:: እያንዳንዱን ነገር ጨርሼ ጠረጴዛህ ላይ ታገኘዋለህ:: ከዚህ ወዲያ ቀንም ሌሊትም አይኔን ከእርሱ አልነቅልም" አለ ማርቆስ::

"መልካም ዕድል::"

ማርቆስ ከአለቃው ቢሮ ወጥቶ ፒታርን አስከትሎ ወደ እራሱ ቢሮ ገባና በሩን ዘጋ::

"ቁጭ በል ፒተር" አለ ቀልጠፍ ብሎ ወንበሩ ላይ እየተቀመጠ::

"ተግባባን?" አለ ዝርዝር ትዕዛዝ ለፒተር ካዥጎደጎደለት በኋላ "አሁኑኑ ከክትትል ክፍል አንድ ሰው ይዘህ ሂድ:: ለአንዲት ደቂቃ እንኳን



ከአይንህ እንዲርቅ እንዳትፈቅድለት::" እያንዳንዱን ነጥብ ዘርዝሮ ካስተላለፈ በኋላ ኮቱን ከወንበሩ ላይ አንሳና ፒተርን ትቶ እየተቻኮለ ወደ በሩ አመራ:: "ዝርዝር ሪፖርቱን ማታ እዚያ እፈልገዋለሁ::" አለ አመልካች ጣቱን በገዛ የቢሮ ጠረጴዛው ላይ ቀስሮ::

መኪናው ውስጥ ገብቶ ከግቢው ወጣ:: ወደ ወኪሉ ቢሮ ሲሄድ በእርካታ መንፈስ ነበር:: መጥፋት የሌለበት የአንድ ሰው ነፈስ እንዳዳነ ተሰማው:: መኪናውን ከወኪሉ መሥሪያ ቤት አጥር ውጪ አቁሞ በእግሩ ወደ ውስጥ ገባ:: ወደ ዋናው ህንፃ በሚያስገባው በር አልፎ በስተቀኝ ያለውን የህዝብ ስልክ አነሳና ወደ ቢሮዋ ደወለ::

"ሃሎ" አለው የሴት ድምፅ::

"ከአክራ ነበር::" አለ ማርቆስ በተለመደው የመክፈቻ ምልክት::

"አውሮፕላኑ በስንት ሰዓት ይገባል?" አለ ያው የሴት ድምፅ መልሶ::

"አሁን" አለ ማርቆስ ወዲያውኑ ወደ መገናኛው ቦታ እንድትሄድ ምልክት እየሰጣት::

ቀልጠፍ ብሎ ስልኩን ዘጋና ወደ መገናኛው ቦታ ተጣደፈ:: በአንድ መተላለፊያ ፊት ለፊት ወደተሰሩት የሴቶችና የወንዶች የመታጠቢያ ቤቶች በሚያስገባው በር ገባና በስተግራ ከተደረደሩት የመታጠቢያ ሳህኖች ወደ አንዱ አምርቶ ቧንቧውን ከፍቶ እጆቹን ይታጠብ ጀመር::

በጠባቧ መተላለፊያ የነበረ አንድ ሌላ ሰው እንደወጣ ማርቆስ ቀልጠፍ ብሎ መደዳ ከተደረደሩት የሴት መጸዳጃ ክፍሎች የአንዱን በር ከፍቶ ገባና በሩን ከውስጥ ቀረቀረው:: ጆሮውን አቅንቶ መጠባበቅ ያዘ::

በስተቀኝ ያለው የመጸዳጃ ክፍል በር ሲከፈትና ከውስጥ ሲቀረቀር ተሰማው::

'ቃ - ቃቃ - ቃ - ቃቃ -' ሁለቱን የመጸዳጃ ክፍሎች የሚለየውን ስስ የእንጨት ግድግዳ በሳንቲም እያንቋቋች እንዲቀጥል ምልክት ሰጠችው::

"ቆንጆዎቹ" አለ አፉን ዘወትር ወደሚጠቀሙባት ቀዳዳ አስጠግቶ::

"ቀጥል" አለው የሴተ ድምፅ::

"ቢሮው ገብቷል?" አላት::

"አዎ" አለው ያው የሴት ድምጽ

"ትላንት አልገባም ብለሽኝ ነበር::"

"ዛሬ ገብቷል::"

"እስካሁን ከአብርሃም ጋር ስላደረገው ግንኙነት ያገኘሽው አለ?"

"ምንም ላገኝ አልቻልኩም:: ላነጋግረው ሞክሬ ነበር... ግን..."

"ግን ምን?"

"ሊያነጋግረኝ ፈቃደኛ አይመስልም::"

"ጥሩ... በተቻለሽ ከአብርሃም ምን እንዳገኘ ለማግኘት ሞክሪ::"

"እሺ እሞክራለሁ::"

"ሁለተኛ" አለ ማርቆስ ጠበቅ አድርጎ «ከአሁን በኋላ በየሳምንቱ የምታቀርቢውን ሪፖርት በቀን በቀን እፈልጋለሁ::

"እሺ::"

«ጨርሻለሁ::» አለ ማርቆስ::

ከጎኑ ያለው ክፍል ተከፍቶ ሲዘጋ ተሰማው:: ለጥቂት ደቂቃዎች ባለበት ቆየና አካባቢው ጭር ማለቱን በበሩ ቀዳዳ ካረጋገጠ በኋላ ቀልጠፍ ብሎ በሩን ከፍቶ ወጣ::

## -12-

የቀኑ የሥራ ሰዓት እስኪገባደድ አልጠበቀም:: ከአሁን ወዲያ እንደሌሎች በሰዓት አይመራም:: ተባራሪ ነው - ድኩላ፤ ታዳኝ ነው ጅግራ:: መሮጥ... መሸሽ መሸሽ... መብረር መብረር::

ለምሳም ከቢሮው አልወጣም:: እዛው ቢሮው ውስጥ ቁጭ እንዳለ ማድረግ ያለበትን አንድ በአንድ፤ ደቂቃ በደቂቃ አሰላስለው መልሶ መላልሶ አብላላው፤ አኘከው:: 'አ! አ! መፍራት የለም'! ጊዜ የለውም ለመፍራት... መቁረጥ አለበት... ግን ደግሞ መሮጥ መሸሽ... መሽሎክሎክ የላይቤርያውን አታሼ ማግኘት ቀልፉን...'

"የት ጠፋሽ? ብፈልግሽ የለሽም" አለ ፀሐፊውን የቢሮውን በር ዘግቶ እየወጣ::

"ወደ መታጠቢያ ቤት ሄጄ ነው::" አለች ፀሐፊው ቀና ሳትል::

"ሰው ከፈለገኝ አሁን ወጣ አለ በይ:: እመለሳለሁ፤ መዝገብ ቤት ነኝ:" አላት ከቢሮው ወጥቶ ቢሮዋን በረጃጅም እርምጃዎች እየተሻገረ:: ሳምራዊት ከጀርባ ትክ ብላ ተመለከተችው::

"በስልክ የሚፈልግህ ሰው አለ:: አሁን ደውለው ሳገናኝህ ስል ስልኩ ተቋረጠብኝ:: መልሰው ይደውሉ ይሆናል::" አለች ሳምራዊት እጇን በስልኩ እጀታ ላይ እንደጫነች::



"ማነኝ አሉ?"

"እ...ይ ዝም ብለው 'አለ ወይ' አሉኝና አዎ ማን ልበል' ስል ስልኩ ተቋረጠ::

"ምህረተአብ ይሆናል::" አለ ናትናኤል ሰዓቱን እየተመለከተ::

ምህረተአብ በሰሜን አፍሪካ ክፍል ውስጥ የሚሰራ የሥራ ባልደረባው ነው::

«አይ የውጭ ስልክ ነው'ኮ፤ ደግሞ የምህረተአብን ድምፅ አውቀዋለሁ:: ይሄ በጣም ጎርናና ነው::»

በጣም ጎርናና!... ጎርናና ድምፅ!... አውሬው!... አዳኙ!

ለምን ደወለ? ምን ሊለው ደወለ? መኖሩን ለማረጋገጥ! አዎ መኖሩን አረጋገጠ:: ስልኩ ተቋረጠ:: አ! አ! ስልኩን ዘጋው - አውሬው:: ናትናኤል ሌሊት ከእንቅልፉ ባንኖ ተነስቶ ራሱን በጨለማ ክፍል ውስጥ እንዳገኘ ህፃን ዙሪያው አስፈሪ ሆነበት:: ወደ እሱም እየመጣ ነው!

"ከአንድ ሰዓት በኋላ ደውል በይው - መልሶ ከደወለ::"

"ትመለሳለህ አይደል... የት መሄድህ ነው?" አለች ፀሐፊው ድንገት ብድግ ብላ:: «አንድ የማነጋግርህ ነገር ነበር:: ማታም ቢሆን ከሥራ በኋላ ትመለሳለህ?»

"እንጃ አዎ -አዎ መዝገብ ቤት ነኝ'ኮ::" ፈጠን ብሎ ከቢሮዋ ወጣ:: በተመላለፈው መሀል ቆም ብሎ አሰበ:: እየተከታተሉት ነው! ምራቁ እልም አለ:: ወደ መዝገብ ቤት ለመሄድ ሃሳብ አልነበረውም፤ አልሄደም:: አለቅጥ መደናገጡ እራሱን አበሳጨው:: 'መጠንቀቅ ብቻ ነው ያለበት:: መጠንቀቅ!'

ሳይጣደፍ ረጋ ባለ ሁኔታ በፎቁ የጓሮ በር ወጣ:: ተርታውን ተደርድረው የቆሙ መኪናዎች ተመለከተ:: ቀና ሲል ፀሐፊው በመስኮት ቁልቁል ስትመለከተው አየ:: ፈገግ አለና እጁን አወዛወዘላት:: እንዳየች ስታውቅ መጋረጃውን ለቅቃ ወደኋላ ተመለሰች::

"ጋሼ ዋለልኝ እንደምን ዋሉ::" ወደ መሥሪያ ቤቱ ነባር ሾፌር አመራ::

"እንደምን ዋልክልኝ ጌታዬ!" ሥራ ፈትተው ከተቀመጡበት አነስተኛ የጭነት መኪና ውስጥ ወጥተው ሁላምታ ሰጡት - ጋሼ ዋለልኝ::

"ሁኑ - ሁኑ፡፡ ደህና ዋሉ?" አሏቸው ተጠግቶ የዘረጉትን እጃቸውን እየጨበጣቸው፡፡

"ደህና - ደህና የኔ ልጅ፡፡" አሉ ጋሼ ዋለልኝ ያወለቁትን የጨርቅ ቆብ መልሰው ሽበት የሸፈነው ጭንቅላታቸው ላይ ጣል እያደረጉ፡፡

"እባኮት እዚህ ኤይድ ባንክ ደረስ ብለን እንምጣ፡፡ ለሥራ ነው፡፡" አላቸው ዘና ብሎ፡፡

"እሄ ስምሪት ሳይፈቅድማ..." የተለመደውን ንትርክ ጀመሩ፡፡
"ነግሬዋለሁ - ነግሬዋለሁ፡፡ ሥራ ስለያዘ ነው እንጂ እሱም አብሮኝ ሂያጅ ነበር፡፡ ያሬድ አይደል... ነግሬዋለሁ፡፡"

"ግን አደራ..." አሉ ጋሼ ዋለለኝ እያወላወሉ፡፡
"ስነግሮት! ይልቅ ቶሎ ደርሰን እንመለስ፡፡ እዚህ ነውኮ፡፡" አዋከባቸው፡፡
"ከነገርከውማ ምን ገዶኝ! ቢሆንም አደራ፡፡ ጭቅጭቁ ነው እኔን የሰለቸኝ፡፡" እያጉረመረሙ ወደ መኪናቸው ገቡ፡፡

ናትናኤል ፈጠን ብሎ ሸራ ከለበሰችው አነስተኛ የጭነት መኪና ጀርባ ዞረና ሸራውን ገለጥ አድርጎ ከእቃ መጫኛው ላይ ዘሎ ወጣ፡፡ ሸራውን አስተካክሎ ዘጋው፡፡ ወንበሩ ላይ ፎቀቅ አለና ከጀርባቸው ያለውን መስኮት አንኳኳላቸው፡፡

"እንሂድ ጋሽ ዋለልኝ፡፡"

"ከዚያ ከኋላ ምን ትሰራለህ እዚህ ቦታ እያለ?" አሉ ጋሽ ዋለልኝ ከጎናቸው ከጋቢናው ያለውን ወንበር በእጃቸው ቸብ አድርገው፤ አንገታቸውን ጠምዝዘው እየተመለከቱት፡፡

"ይሂዱ - ይሂዱ፡፡ ይዘን የምንመጣው ዕቃ ስላለ ነው፡፡ እሱን ለመደገፍ በኋላም ቢሆን እዚሁ መምጣቴ አይቀርም ብዬ ነው፡፡" አላቸው ድምፁን ለማርገብ እየሞከረ፡፡

"እንዳልክ!" ጋሽ ዋለልኝ 'ምን ቸገረኝ' ለማለት እንደፈለጉ ዓይነት ትከሻቸውን ነቅነቅ አደረጉና የመኪናቸውን ሞተር አስነስተው ከፊት ለፊታቸው የተገተረውን ፎቅ በስተግራ ዞረው ወደ ግቢው በር አመሩ፡፡

ከጭነቷ መኪና ጀርባ የተሸፈነውን ሸራ ገለጥ አድርጎ በቀጭኑ ተመለከተ፡፡ ብርማ ቀለም ያላት 131 ፊያት መኪናው ከህንፃው ፊት ከተደረደሩት የሠራተኞች መኪናዎች መሀል ቆማለች፡፡ ተሰናበታት፡፡



"ኤይድ ባንክ ነው ያልከኝ?" ጋሽ ዋለልኝ ጮኸው ጠየቁት፡፡
"አዎ - አዎ፡፡" አለ ናትናኤል ሸራውን በቀጭኑ ከፈት አድርጎ እንደያዘ ፊቱን ወደ ጋሽ ዋለልኝ መለስ አድርጎ፡፡ ወዲያው በር በቀጭኑ ከፍቶ በያዘው ሸራ አሾልኮ ከጀርባ ያለውን ሁሉ ያጠና ጀመር፡፡

"የመረጃው መሥሪያ ቤት አባል ከሆንክ ጀምሮ የምሄድበትን ብቻ ሳይሆን የመጣሁበትንም መንገድ ማየት ተምሬአለሁ..." ትዝ አለው አብርሃም ያለው፡፡

ከኋላ የተከተለሁ መኪና የለም፡፡ እሱ የተሳፈረበት የጭነት መኪና ከመሥሪያ ቤቱ ግቢ ስትወጣ አንድ ቀይ ፎርድ መኪና ወደ ግቢ ገባች፡፡ ዙሪያውን ተመለከተ፡፡ ወዲያ ማዶ ሁለት ሰዎች የስልክ እንጨት ተደግፈው ያወራሉ፤ ሁለት ሴቶች ቁልቁለቱን ይወርዳሉ፤ አንድ ሎተሪ ሻጭ ችላ ብለውት ዳተቱን የሚወጡትን አዛውንት እየወተወተ ከጎን ከጎናቸው ይሮጣል፤ ወዲያ ማዶ መናፈሻው ውስጥ አንድ ነጭ ሲትሮይን ቆማለች...

ናትናኤል ሸራውን በቀጭኑ ከፍቶ እንደያዘ ትንፋሹን በረጅሙ ለቀቀው፡፡ 'የታል አውሬው? አውሬው የለም? ሀሳም ነው?' ዋናው ነገር ከመሥሪያ ቤቱ መውጣቱን አውሬው አያውቅም፡፡ አልተከተለውም፡፡ ናትናኤል በአሸናፊነት ስሜት ፈገግ አለ፤ አይኖቹን ግን ከመኪናው ጀርባ ካለው መንገድ ላይ አልነቀለም፡፡

ጋሽ ዋለልኝ ወደግራ ታጥፈው ወደ እርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ አመሩ፡፡ መኪናዋ ከባንኩ በር ፊት ለፊት እንደቆመች ናትናኤል ሸራውን ገልጦ ዱብ አለ፡፡

"መጣሁ እዚሁ ይጠብቁኝ፡፡" አላቸው ወደ ጋሽ ዋለልኝ ራመድ ብሎ፡፡
ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ ሽማግሌው - "እሺ" ለማለት፡፡

ናትናኤል በባንኩ የፊተኛ በር ገባ ብሎ ደቂቃም ሳይጠፋ ወዲያው ወደ ውጭ ከሚወጡ የባንኩ ደንበኞች ጋር ተደባልቆ ከባንኩ ወጣ፡፡ ከጠባቧ መንገድ አልፎ ከዋናው መንገድ ገባ፡፡ ጋሹ ዋለልኝ ወደ ባንኩ ሲገባ አይተውት ይሆናል፡፡ ሲወጣ ግን እንዳላጤኑት እርግጠኛ ነበር፡፡ በተቀመጡበት መኪና ውስጥ እንዳሉ ፍዝዝ ብለዋል ሽማግሌው፡፡

"ታክሲ! ካዛንቺስ፡፡"

የታክሲውን በር ከፍቶ ገባ፡፡ ካዛንቺስ ከመድረሱ በፊት ሂሳቡን ከፍሎ ከታክሲው ወረደ፡፡ ወደ አንድ ኪዎስክ ጠጋ ብሎ "ባክህ ባርኔጣ

አለ?" ብሎ ለጣፋ ባርኔጣ ገዝቶ ጭንቅላቱ ላይ ደፋት። መንገዱን ተሻግሮ ከካዛንቺስ የሚመጣ ታክሲ አስቁሞ 'መርካቶ' ብሎ ተሳፈረ።

በመጣበት መንገድ ሲመለስ ባንኩ ጋ ሲደርስ ጋሽ ዋለልኝን በአይኑ ፈለጋቸው። እዚያው መኪናቸው ውስጥ ተቀምጠው ከፊት ለፊታቸው ባለው አየር ላይ አፍጥጠው አገኛቸው። አለፋቸው። የተሳፈረበት ታክሲ ከላይኛው ቤተመንግሥት ወደ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የሚያመራውን አውራ ጎዳና አቋርጦ ወደ ፍልውሃ አቅጣጫ ሲያመራ ለአንድ አፍታ በስተቀኙ የሚገኘውን የመሥሪያ ቤቱን ዳገፍ እስከ ግንባሩ ከደፋው ባርኔጣው ስር በሚንከባለሉ አይኖቹ አሰሰው። እዚያና እዚያ ጥቂት ሰዎች ይታያሉ። ከመሥሪያ ቤቱ ግቢ አንድ ጥቁር መርሰዲስ መኪና ወጣ። መናፈሻው ውስጥ የቆመችው ነጭ ሲትሮይን አሁንም እዛው ነች። አለፈ።

ኢትዮጵያ ሆቴል ጋ ከመድረሱ በፊት 'መርካቶ' ብሎ የተሳፈረበትን ታክሲ አስቁሞ ወረደ።

"የፖስታ ከረጢት አለህ? አንድ ስጠኝ።" መንገድ ዳር ተቀምጦ ከረሜላና ማስቲካ ከሚሸጥ ልጅ ላይ የፖስታ ከረጢት ገዛና የዋናው ፖስታ ቤትን የታችኛ በር ደረጃዎች በሩጫ ወጣቸው። በአዳራሹ ውስጥ ከረጃጅሞቹ መስኮቶች ጥግ ከተደረደሩት የመፃፊያ ጠረጴዛዎች ወደ አንደኛው ሄዶ ከደረት ኪሱ ውስጥ ወረቀትና እስክሪኙቶ አውጥቶ መፃፍ ያዘ

*ርብቃ ብዙ ማለት እፈልግ ነበር።*
*ግን ጊዜ የለኝም። ርብቃ እቤት*
*ሄደሽ የመሃከለኛውን ቁምሳጥን*
*ስትከፍቺ ስምንት መቶ ብር የያዘ*
*ካኪ የፖስታ ከረጢት ታገኛለሽ።*
*ከራስጌ ደግሞ ሂያ ሰላሳ ብር*
*ታገኛለሽ። ያገኘሽውን ይዘሽ ዛሬ*
*ማታ በአንድ ሰዓት አምባሳደር*
*ትያትር ፎቅ በግራ በኩል ግቢ።*
*ልክ ሁለት ሰዓት ሲሆን ተነስተሽ*
*ወደ መፀዳጃው ክፍል ግቢ። እዚያ*
*ታገኘኛለሽ።*

*ያንቺው ናትናኤል*
*አንብበሽ ስትጨርሺ ይሄን ወረቀት አቃጥይው እሺ!*

ወረቀቱን አጣጥፎ የፖስታ ከረጢት ውስጥ ከከተተው በኋላ የአፓርትመንቱን በርና የመኝታ ቤቱን ቁም ሳጥን ቁልፍ አብሮ በፖስታ ከረጢቱ ውስጥ ጨመራቸውና ወደ ፖስታ ሳጥኑ አመራ። የፖስታ



ሳጥኑን ከፍቶ በቀኙ የያዘውን ከረጢት ከውስጥ ከትቶ መዝጊያውን መለስ አድርጎ ተወው።

የፖስታ ቤቱን ሰፊ አዳራሽ ተሻግሮ በተርታ ከተደረደሩት ቢጫ የሕዝብ ስልኮች መሃል አንዱን አንስቶ መደወል ያዘ።

"ሃሎ... ምህረት ነሽ? እንደምንድነሽ? አወቅሽኝ? ናትናኤል ነኝ..."
"ሃይ ናትናኤል! እንደምንድነህ"
"አለን... አለን ደህና ነሽ?"
"ደህና እንዴት አስታወስከኝ ባክህ...!"

ምህረት የርብቃ የመሥሪያ ቤት ጓደኛ ነች። ቀደም ብሎ ሁለቱም አንድ ቢሮ ውስጥ ይሰሩ ስለነበር ርብቃን ፈልጎ ሲደውል አልፎ አልፎ ምህረት ስልኩን ስለምታነሳ አዘውትረው በስልክ ተገናኝተዋል። በአካልም ሁለት ሶስቴ ተያይተዋል።

"ምህረት እባክሽ ርብቃን ፈልጌአት ነበር። ላስቸግርሽ ትጠሪልኝ?"
"እዚህኮ አይደለችም። ቆይ ስልኩን ላዙርልህ ወደ እሷ ቢሮ። አትዝጋው።" አለች ምህረት ተሳስቶ የደወለ መስሏት።

"ቆይ! ቆይ!" አለ ናትናኤል ፈጠን ብሎ። "ተይው! ስልኩን አታዙሪው። አንቺ ጋ ብትጠሪልኝ እሷኑ።"

ምህረት ግራ ገባት። 'እሷ ቢሮ ደውሎ ከሌላ ቢሮ ሰው ጥሪልኝ ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ቀጥታ ርብቃጋ አልደወለም? አይ ወንድ! የሰበቡ ብዛት! እሷ ድሮውኑ ጠርጥራለች እንደፈለጋት፤ወየው! ግን ርብቃ ምን ትላታለች ብታወጣው?።'

"እሺ መጣሁ ጠርቻት።" አለችው ሳቋን አፍና፤ እስክሪኙቶዋን ጠረጴዛ ላይ ጣል አድርጋ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ እየተነሳች።

ናትናኤል የስልኩን እጀታ ጆሮ ግንዱ ላይ እንደለጠፈ ዞር ዞር ብሎ አካባቢውን ፈተሸ። በርካታ ሰዎች በአዳራሹ ውስጥ ይተላለፋሉ። ናትናኤል እያንዳንዱን ተላላፊ በጥንቃቄ ለማጥናት ሞከረ፤ በሩቁ ጥግ ይዞ የሚመለከተው፤ የሚከታተለው ሰው ፈለገ። ቢሆንም በእሱ ላይ የተለየ አትኩሮት ያለው ሰው ሊያገኝ አልቻለም። ድንገት አንድ ረዘም ደልደል ያለ ሰው መጥቶ ከጎኑ ያለውን የሕዝብ ስልክ አነሳ። ናትናኤል አይኖቹን የጎድን ሰውየው ላይ ተከላቸው። ሰውየው ቡኒ ኮትና ሱሪ ለብሶ በነጭ ሸሚዙ ላይ ጠቆር ያለ ክራባት አስሯል። ሰውየው ስልክ መደወል ጀመረ።

"ሃሎ"

"ሃሎ... ርብቃ?" አፉን በመዳፉ ሸፍኖ መናገር ጀመረ።

"ነኝ። ናቲ ነህ?"

"አዎ ርብቃ ስሚኝ ስሚኝ..." ልታቋርጠው ስትል ተሽቀዳድሞ። "ርብቃ በጥንቃቄ ስሚኝ..."

"እየሰማሁህ ነውኮ፤ ደህና ነህ ግን?" አለች ማስጠንቀቂያው ሲበዛባት ስጋት ገብቷት።

"ደህና ነኝ ርብቃ... ትንሽ ችግር ስለገጠመኝ ነው የደወልኩልሽ ርብቃ። አሁን ላገኝሽ አልችልም። የፖስታ ሳጥን ቁጥሬን ታውቂዋለሽ? ተይ! ተይ! አትናገሪው።" አለ ርብቃ ቁጥሩን መጥራት ስትጀምር ተሽቀዳድሞ። "ታውቂዋለሽ አይደል? ጥሩ... ርብቃ የምልሽን ብቻ አድርጊ። ጥያቄ አትጠይቂኝ። ገባሽ አም። የፖስታ ሳጥኔ ውስጥ መልዕክት ትቼልሻለሁ። አሁኑኑ ሄደሽ ወረቀቱን አውጥተሽ አንብቢው። ወረቀቱ ላይ የተጻፈውን አድርጊ። ገባሽ?"

"ቁልፉኮ አንተጋ ነው።"

"ሳጥኑን አልቆለፍኩትም። መዝጊያውን መለስ አድርጌ ነው የተውኩት። ወረቀቱን ካነበብሽ በኋላ እዛው በክብሪት አቃጥይው በፍጹም ይዘሽው እትሂጅ። እደራ!"

"ምንድነው ነገሩ?" አለች ድብብቆሹ የተንዛዛባት ርብቃ።

"የምልሽን ብቻ አድርጊ፤ ጥያቄ አትጠይቂኝ! ገባሽ?"

"ገባኝ - ገባኝ።"

ናትናኤል ስልኩን ዘግቶ ወደ አዳራሹ መውጫ አመራ። የፖስታ ቤቱን ደረጃዎች በፍጥነት እየተራመደ ወረደ። ራሱን መቀየር ይኖርበታል። ለዚያ ደግሞ ገንዘብ ያስፈልገዋል። በኪሱ የያዘው ገንዘብ ደግሞ በቂ አይሆንም። የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ በሁለት አውራ ጣቶቹ በርግዶ ተመለከተው። ሶስት የአስር፤ ሁለት የአምስት፤ ሶስት የአንድ ብር ኖቶች - አርባ ሶስት ብር።

ባንክ ያለውን ማውጣት ቢችል ጥሩ ነበር። ግን ከአሁን ወዲያ ወደዚያ መሄድ አደገኛ ነው። ርብቃ በምታመጣለትና ከቤት ባስቀመጠው ስምንት መቶ ብሩ ሁሉንም ማቻቻል ይኖርበታል።

መንገድ ላይ አንድ ጥቁር የፀሐይ መነጽር ገዝቶ ሰካ። ብዙም ሳይሄድ ወደ አንድ የልብስ ሱቅ ገባና የአንገት ልብስ ጠየቀ።



ባለሱቋ ሁለት አማራጭ አምጥታ ፊቱ ዘረጋችለት።

"ስንት ስንት ናቸው?"

"ይህኛው አስራ ስድስት ይሄኛው አስራ ሁለት።" በያዘችው እስክሪኝቶ እየጠቆመች።

ግራጫ መልክ ያለውን የአስራ ሁለት ብሩን የአንገት ልብስ ገዝቶ አንገቱ ላይ ጠምጥሞት ወጣ። ገንዘብ መቆጠብ ይኖርበታል። ሰዓቱን ተመለከተ። ለአሥራ አንድ ሰዓት አስር ጉዳይ። ከርብቃ ጋር የያዘው ቀጠሮ እስኪደርስ ከሁለት ሰዓት በላይ አለው። ማደሪያውን ማዘጋጀት አለበት - በጊዜ። ግን የት ነው መልህቁን መጣል ያለበት? ባህር ውስጥ። አዲስ አበባ ውስጥ ባህር የለም?... አለ! አለ! - መርካቶ።

መርካቶ ባህር ነው። መርካቶ ገብቶ ባህር እንደገባች ትንሽ አሳ መሰወር አያስቸግርም። ከክፍለሃገር አውቶቡስ መሳፈሪያ ሲደርስ ከታክሲው ወርዶ በእግሩ ከዋናው መንገድ ተገንጥሎ ወደ ሠፈር በሚያስገባ ጠባብ መንገድ ገባ። እዚህ አካባቢ ትናንሽ ምግብ ቤቶች፤ ሆቴሎችና መጠጥ ቤቶች እንዳሉ ያስታውሳል። በአካባቢው ችምችም ብለው የተደረደሩትን ቤቶች ነጣጥሎ መመልከቱ ያስቸግራል። እዚህም ቤት እዚያም ቤት... እዚህም በር እዚያም በር... እዚህም መስኮት እዚያም መስኮት... እዚህም ሴት እዚያም ሴት። 'አሰለፈች ምግብ ቤት'... 'ጥሩ ምግብ ይገኛል'... 'ብርሃኔ ግሮሰሪ'... 'አበበች ሆቴል'... ዘው ብሎ ገባና ጥግ ካለ ወንበር ላይ ተቀመጠ።

ቤቷ ትንሽ ነች፤ ክፍሏ ጨለማ። አይኖቹ ላይ የሰካውን የፀሃይ መነፅር አውልቆ ኪሱ ከተተው። አይኖቹ ቀስበቀስ የክፍሉን ጨለማ ሲላመዱት ዙሪያውን ይቃኝ ጀመር።

ከወዲያ ጥግ ከበሩ ትይዩ የመጠጥ ጠርሙሶች የተደረደሩበት መደርደሪያ ግድግዳውን ታክኮ ቆሟል። ከጣሪያው ሊደርስ ትንሽ የቀረው ባልኮኒ ስር በተደረደሩት ጥቂት ረጃጅም ወንበሮች ላይ የሆቴሏ ጎረምሳ ደንበኞች ተፈናጠው ቢራ ይጠጣሉ። በጠባቧ ክፍል ውስጥ ትንንሽቹን ጠረጴዛዎች እየከበቡ በተኮለኮሉት ወንበሮች ላይ በርካታ ጠጪዎች ምርጫቸውን እየተጎነጩ ያወካሉ። ናትናኤልን ነገሬ ያለው አልነበረም። መርካቶ ባህር ነው...

የሆቴሉ ባለቤት ከባልኮኒው ጆርባ በረጅም ወንበር ላይ ፊጥ ብለው ውር ውር የሚሉትን አሻሻጮቻቸውን ይታዘባሉ።

"ምን ልታዘዝ።" አለችው ከፊት ለፊቱ ያለውን የሲጋራ መተርኮሻ እንስታ ጠረጴዛውን ወልወል ካደረገች በኋላ መተርኮሻውን ከቦታው እየመለሰች። ጎንበስ ስትል ትላልቅ ጡቶቿ ከሰፊው የቀሚሷ አንገትዬ ይደርሱና እኔ ልቅደም፣ እኔ ልቅደም ትንቅንቅ ይይዛሉ።

"ሻይ" አላት ቀና ብሎ አይኗት መልሶ እያቀረቀረ።

"ትኩስ ነገር የለም።" በበሩ ውጭ ውጭውን እያየች።

"እሺ. ለስላሳ።" አላት ቀና ብሎ እይቷት። ለስቅጥ የወረደው የቀሚሷ እንገትዬ ቅድ ኮረብታ ጡቶቿን ለአገሩ ያስጎበኛል።

"ለስላሳም የለም።" አለች በረጅሙ ተንፍሳ። "አልኮል ነው ያለው - ቢራ።" እራቁት ጡቶቿ ላይ ግራ እጇን ጣል አደረገችው።

"አልጋ አለ?"

"ምንድነ?" አለች ግራ እጇን ከጡቶቿ ሳታነሳ ቅንድቦቿን አጠጋግታ ኮስተር ለማለት እየሞከረች። ለአንድ አፍታ ሳቅ ያፈናት መሰለች።

"አልጋ" መልሶ ጠየቃት።
"ይልቅ ምን ልታዘዠ" አንገቷን እስክስ! ዳሌዋን ነቅነቅ አድርጋ።
"አልጋ አለ ወይ ነውኮ ያልኩሽ።"

"እም አለ። አሁን ምን ልታዘዝ።" አለች ጡቶቿ ላይ ጭናው በነበረው እጇ አፏን ሸፍና እፍራምነቷን ለማሳየት እየጣረች።

ረከስ ያለውን መምረጥ አለበት። ገንዘብ መቆጠብ አለበት።
"እሺ ቢራ አምጭልኝ... እና አልጋም ያዢልኝ።» የአስር ብር ኖት አውጥቶ ሰጣት።
"አሥራ ስምንት ነው የሚመጣው።" አለች የአስር ብር ኖቱን እንደያዘች ከለችበት ሳትነቃነቅ።
"አልጋው?" አለ ደንግጦ።
"አልጋው ሶስት እኔ አስራ አምስት። ባንድነት አስራ ስምንት አንመጣም?" አለች እየተሽኮረመመች።
"አልጋ ብቻነውኮ ያዥልኝ ያልኩሽ።"
"ባዶ አልጋ?" ኮስተር ብላ ቁልቁል ተመለከተችው... ፊቷ ላይ የነበረው ፈገግታ ሁሉ እልም ብሎ።

"አዎ። እና ቢራውን አምጪልኝ። ሳንቺም ተጋበዥ..." በተቻለው መጠን በዙሪያው ካሉ ሰዎች ጋር መሻረክ እንዳለበት ተሰማው። ከአሁኑ ማስከፋትና ማስኮረፍ ከጀመረ ድምሩ ጥሩ አይመጣም። "የማታውን ደግሞ እያየን እያየን።" አላት ፈገግ ብሎ።

ከንፈሯን ላስ አይኖቿን እርግብግብ አድርጋለት አስር ብሩን ይዛ ሄደች።



ሰዓቱን ተመለከተ። ለአስራ ሁለት ሄዶ ጉዳይ። በቂ ጊዜ አለው።
ከሆቴሉ በአስራ ሁለት ከሩብ/ ቢወጣ ከአንድ ሰዓት በፊት አምባሳደር ትያትር ይደርሳል - ርብቃጋ።

"ይኸው።" አለችው ለረጅም ጊዜ እንደሚተዋወቁ ሁሉ ፊቷን በፈገግታ አስውባ። ያዘለውንና የጋበዛትን ሁለት የቢራ ጠርሙሶች ከነብርጭቆዎቻቸው ጠረጴዛው ላይ ካስቀመጠች በኋላ አራት ብር መልስ አቀብላው ወንበር ስባ ከፊት ለፊቱ ተቀመጠች።

ቀና ብሎ አያት። ፈገግ አለችለት - የጎድን እይታው። ቢራ ስለጋበዛት ብቻ መጥታ አጠገቡ መቀመጧን ሲረዳ የሚላት ጠፋው። ብቻውን መሆን ነበር የፈለገው - ብቻውን ሆኖ ማሰብ። ምን ሰበብ ሰጥቶ ሊያስነሳት እንደሚችል ሲያስብ ዘዴው ጠፋው።

"ማነው ስምሽ።" ድላድል የሆነ መሰለው በገዛ ጥያቄው።
"ዘውዲቱ።" አለችው የታች ከንፈሮቿን ምጥጥ አድርጋ መልሳ ፈገግ እያለችለት።
"ተጫወቺ።"
"እሺ።" አለች ከፊት ለፊቷ የተቀመጠውን የቢራ ጠርሙስ አንስታ በአንድ ትንፋሽ ግማሽ እያደረሰችው።
ናትናኤል ድጋሚ 'ተጫወች' ላለማለት ወሰነ።
"በዛ እንዴ?" ጭንቅላቷን ጋደል አድርጋ ተሽኮረመመችለት።
"ምኑ?"
"ሂሣቡ።"
"የምኑ ሂሣብ?"
"አሥራ አምስቱ ነዋ!"
"አ - ይ" የሚመልስላት ሲማታበት አፍጥጦ ተመለከታት።

"ከፈለግህ እቤት እንሄድና የአልጋ አትከፍልም። እራትም ችግር የለም፤ አሥራ ሁለት ብር።" አለች ለአንድ አፍታ የቤቱን ባለቤት ገልመጥ ብላ ተመልክታ።

"የት ቤት ነው የምንሄደው?"
"እኔጋ።"
"እዚህ አይደለም እንዴ የምትሰሪው?"
"እዚህ እሻሽጣለሁ። ግን የራሴ ቤትም አለኝ።"
"የት ነው ቤትሽ?"
"ቅርብ ነው።" አለች ጭንቅላቷን እሷ ብቻ ወደምታውቀው ወደቤቷ አቅጣጫ መታ አድርጋ።
"እስቲ ለማንኛውም ማታ እንነጋገርበታለን።"

ከፊቷ የተቀመጠውን የቢራ ጠርሙስ አንስታ ሸክሙን ገላገለችው።

"ለራስሽ አንድ ጨምሪ። ማታ እንገናኛለን።" አላት ሶስት ብር ሰጥቷት ከተቀመጠበት እየተነሳ።

ከመውጣቱ በፊት ሮጥ ብላ መጥታ ሳንቲም መልሶች ዘረጋችለት።

"ያዢው።"

"ትመለሳለህ?" ለዛ ባለው ድምፅ።

"እንዴ አዎ። አልጋ ይገር!"

"ልጠብቅህ?"

"እ..." አለ 'አዎም' 'አይም' ሳይል በደፈናው።

ውጪውን ከጠበቀው በላይ ጨልሞ አገኘው። ሰዓቱ ገና አስራ ሁለት ሰዓት ከአስር ቢሆንም ምድር ላይ እንደ አከንባሎ የተደፋው የሐምሌ ደመና ዙሪያውን እኩለ ለሊት ሊያስመስለው ከጅሎታል። በሁለት ታክሲ አቋራርጦ አምባሳደር ትያትር ሲደርስ ለአንድ ሰዓት ሃያ ጉዳይ ሊል ትንሽ ነበር የቀረው።

ወደ ትያትር ቤቱ ደጃፍ አልተጠጋም። ራቅ ብሎ ታክሲ ከሚጠብቁ ሰዎች መሃል ተደባልቆ አከባቢውን በጥንቃቄ ይቃኝ ጀመር።

ብዙም ሳይቆይ አይኑ አንድ ከዚህ በፊት ያየውና የሚያውቀው ነገር ላይ አረፈ- ነጭ ሲትሮይን። ጭንቅላቱ በፍጥነት ወደኋላ ማጠንጠን ጀመረ። ይህችን ሴትሮይን ከዚህ በፊት አይቷታል። አዎ። ዛሬ ከመሥሪያ ቤቱ ተደብቆ ሲወጣ መናፈሻ ውስጥ ነበረች። ድንገት ሌላ ትዝታ ብልጭ አለለት። ሃኪም ቤት-አብርሃም! ከሃኪም ቤቱ ሲወጣ ያዞረው ጊዜ የተደገፋት መኪና ነጭ ሲትሮይን። አፉ ደረቀበት። የተረሳው የተዘነጋው ሁሉ አንድ በአንድ እየተሰበሰበ ቦታ ቦታውን ያዘ፤ መልክ መልኩን ጨበጠ።

ሲትሮይኗ ጥግ ይዛ ቆመች። ከፊት በተሳፋሪ በኩል ያለው በር ተከፍቶ አንድ ሰው ወረደ። ረጅም ነው። ከርዝማኔው የተነሳ ይመስላል ከትከሻው ጎበጥ ያለ ነው። ሰውየው ቀልጠፍ ባሉ እርምጃዎች ወደ ቲያትር ቤቱ ደጃፍ አመራና ከደረጃዎቹ ስር እንደደረሰ ድንገት ቆም ብሎ ከሰው ለመከለል ለመደበቅ እንደፈለገ ሁሉ ፊቱን ወደ ባቡር መንገዱ መለሰ። ጥቁር ነው። ቁመቱ ብቻ ሳይሆን ትከሻውም አገር ነው። ከደረበው ጥቁር ግራጫ የዝናብ ካፖርት ስር ጠቆር ያለ ሰማያዊ ሙሉ ልብስ ለብሶ ጥቁር ቀጭን ክራባት አስሯል።

ናትናኤል አይኖቹን በሰውየው ዙሪያ አንከባለላቸው። .... ርብቃ!

ከትኬት መቁረጫው መስኮት ፊት ከቆመው ወጣት ጀርባ ርብቃ ቆማለች። ናትናኤል ያያት ከጀርባዋ ቢሆንም እሷ መሆኗን ለመለየት አልተቸገረም። ከፊቷ የቆመው ወጣት ትኬት አስቆርጦ ወደ ውስጥ ሲገባ



ርብቃ በቦታው ተተካች። ቦርሳዋን ከፍታ ገንዘብ ካወጣች በኋላ ጎንበስ ብላ በመስተዋት ጀርባ ለተቀመጠችው ትኬት ቆራጭ አቀበለቻት።

ናትናኤል ለአፍታ ፊቱን ወደ ነጯ ሲትሮይን መለሰ። ራቅ ብላ ከቲያትር ቤቱ ደጃፍ በግማሽ ክብ ቅርፅ ከተደረደሩት መኪናዎች በስተግራ ጥግ ቦታ ይዛለች።

ከመሪው ኋላ የተቀመጠው ሰው የአረብ ገጽታ ያለው ነው። ጊዜው ቢመሽም ሰውየው ኢትዮጵያዊ አለመሆኑን ለመረዳት አልተቸገረም። ናትናኤል ፊቱን ወደ ትኬት መቁረጫው ሳጥን መለሰ። ርብቃ ትኬቱን ተቀብላ ወደ ውስጥ ስትገባ ለአንድ አፍታ ጀርባዋን ተመለከተ። ወዲያው ፊቱን ወደ መንገዱ መልሶ ቆሞ የነበረው ረጅም ሰው ቀልጠፍ ብሎ ወደ ትኬት መቁረጫው መስኮት ቀርቦ ገንዘብ ሊያወጣ እጁን ደረት ኪሱ ውስጥ ከተተ።

ናትናኤል ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ገባው። 'ሰውየው ርብቃን እየተከታተለ ነው። ምናልባት ከእሱ ጋር ቀጠሮ እንደያዘች ደርሰውበታል። ግን እንዴት? ያነጋገራት በቢሮዋ ስልክ አልነበረም። የመሥሪያ ቤቷን ስልኮች በሙሉ ጠልፈዋል ለማለት ደግሞ... ታዲያ እንዴት?'

ለደቂቃዎች በቆመበት ሲያሰላስል ቆየ። ሰውየው ገንዘብ አውጥቶ በክቧ ቀዳዳ ውስጥ ለትኬት ቆራጯ ሲያቀብላት በምትኩ ትኬቱን አስያዘችው። 'ሰውየው ሊገባ ነው! ርብቃን ተከትሎ መግባቱ ነው!'

ናትናኤል በደመነፍስ መንገዱን ተሻግሮ ወደ ትያትር ቤቱ ሮጠ። የአንገት ልብሱን ከፍ አድርጎ አፉን ጭምር ሸፍኖ ወደ ትያትር ቤቱ ደረጃዎች እየቀረበ መጣ። ረጅሙ ሰው ትኬቱን ለበረኛው አሳይቶ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ናትናኤል ቀልጠፍ ብሎ ወደ ትኬት መቁረጫው መስኮት ተጠግቶ የአስር ብር ኖት አወጣና ከውስጥ ለተቀመጠችው ትኬት ቆራጭ አቀበላት።

ትኬት ቆራጯ ብሩን ተቀብላው የመስተዋት ሳጥኗን ከውጭ በኩል ተደግፎ ከቆመ የትያትር ቤቱ በረኛ ጋር ቀልድ ትመላለስ ጀመር። ረጋ ባለ ሁኔታ አስር ብሩን ከታ አንድ ብጫ ትኬት ቆረጠችና ለናትናኤል አቀበለ ችው። ከዚያ በኋላ ከሚያቃልዳት የሥራ ባልደረባዋ ጋር አንድ ሁለት እየተመላለሰች መልሱን ትቆጥር ጀመር።

ናትናኤል አይኖቹን ወደ ውስጥ ልኮ ተመለከተ። ረጅሙ ሰው በስተግራ ታጥፎ ወደ ፎቅ ወደሚወስዱት ደረጃዎች ሲያመራ ተመለከ ተው። ሊያመልጠው ነው! ቀድሞት በጨለማው አዳራሽ ውስጥ ቦታ ከያዘ ሊከታተለው እንደማይችል ሲገነዘብ ናትናኤለ ሥጋት ወረረው።

"የኔ እመቤት ቶሎ በይልኝ።" አላት ትኬት ቆራጯን።

ቀና ብላ ገረመመችው፡፡ የቆጠረቻቸውን አንዳንድ ብሮች የጣቷን ጫፍ ላስ አድርጋ ድጋሚ ትቆጥራቸው ጀመር፡፡ ሰውየው ወደፎቅ የሚያመሩትን ደረጃዎች መውጣት ጀመረ፡፡ ናትናኤል ዞር ብሎ ትኬት ቆራጯን ተመለከታት፡፡ ብሩን ትቶ ሲሄድ አሰበ፡፡ አ! አ! የሰዎችን አይን መሳብ የለበትም፡፡

"እባክሽ..." አለ እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ፡፡

"ምን አስቸኮለህ? ፊልሙ'ኮ አልተጀመረም፡፡" አለችው እየተቆናጠረች ትኬት ቆራጯ፡፡ መልሱን አቀበለችው፡፡

ናትናኤል ፈጠን ብሎ ትኬቱን አሳይቶ ረጅሙን ሰው ከጀርባው ተከትሎ ወደ ቲያትር ቤቱ ገባ፡፡ ከፊት ለፊቱ ደረጃዎቹን የሚወጣው ረጅም ሰው መጋረጃውን ገልጣ የገባችውን ርብቃን እየተከተለ ሁለት ሁለቱን ደረጃ እያለፈ ከቀዩ መጋረጃ ደረሰ፡፡ ተከተለው፡፡

ሰውየው መጋረጃውን ገልጦ አንደገባ ናትናኤል ጊዜ ሳይፈጅ ወደ አዳራሹ ዘው አለ፡፡

ለአይን በሚደዘው ደብዛዛ ብርሃን የተጥለቀለቀው አዳራሽ ጢቅ ብሎ ባይሞላም ፊልሙን ለመመልከት የገባው ሰው ጥቂት አልነበረም፡፡ ፊልሙ ገና አልተጀመረም፡፡ በመሃሪያ ብቻ የተቀነባበረው ለስላሳ ሙዚቃ በለሆሳስ ሽው እያለ ይንፍሳል፡፡

ረጅሙ ሰው ርብቃ የተቀመጠችበትን ቦታ አንዴ ብቻ ገልመጥ ብሎ ከተመለከተ በኋላ ቀጥታ ወደፊት መራመድ ሲጀመር ናትናኤል ወደቀኝ እጥፍ ብሎ ወደ መፀዳጃ ቤት በሚያመሩት ደረጃዎች ወደላይ ወጣ፡፡ ርብቃ የት እንደተቀመጠች ቢመለከትም አይታው እንዳትመጣ ስለሰጋ ፊቱን አቀርቅሮ የአንገት ልብሱን ከፍ አድርጎ ተጀቡኖ ወደፊት ቀጠለ፡፡ ወደ መጸዳጃ ቤቱ ከሚያስገባው በር አጠገብ ካለ ወንበር ሲደርስ ወንበሩን መለሰና ተቀመጠ፡፡ ከተቀመጠበት ቦታ ሆኖ የርብቃን እንቅስቃሴ መከታተል እንደሚችል ካረጋገጠ በኋላ በአንገቱ ዙሪያ የጠመጠመውን ጨርቅ ወደ አፍንጫው ከፍ አደረገና ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ሸርተት ብሎ ጉልበቶቹን ከፊቱ ካለው ወንበር ላይ አስደግፎ ተከለለ፡፡

ወዲያው ከፊት ለፊት ካለ ወንበር ላይ ያስደገፋቸውን ጉልበቶቹን አሳቆ በአዳራሹ ቁልቁል ተመለከተ፡፡ ረጅሙ ሰው በተደረደሩት ወንበሮች መሃል ለመሃል በሚያልፈው ጠባብ መተላለፊያ በስተግራ ርብቃ ከተቀመጠችበት ወንበር ሁለት ረድፍ ፈንጠር ብሎ ከጀርባዋ ተቀምጧል፡፡



ናትናኤል ጉልበቶቹን ወደ ግራ ዞር አድርጎ እንደገና ተመለከተ፡፡ ርብቃ ጀርባዋን ለጥታው ከፊት ለፊት ካለው ነጭ አቡጀዲ ላይ አፍጥጣለች፡፡ ሰዓቱን ተመለከተ - ለአንድ አምስት ጉዳይ፡፡

ሳይታወቀው ጣቶቹን አፉ ውስጥ በተራ እየከተተ ጥፍሮቹን በጥርሱ ይመገርልጣቸው ጀመር፡፡ የአብርሃም ድምፅ አቃጨለበት፡፡

'.... እንደ እሳት እራት... አላስፈራራህም! የሚያስፈራራስ ራስህ ፈቅደህ የገባህበት ዓለም...' ይላል ድምፁ፡፡

'አይፈራም! ትንሽም አይፈራም!'

ድንገት የአዳራሹ መብራት ቦግ - እልም - ቦግ እልም አለ፡፡ ማስጠንቀቂያ፡፡ ፕሮግራሙ ሊጀመር ጥቂት ደቂቃዎች ቀሩ፡፡ ናትናኤል ሰዓቱን ተመለከተ- አንድ ሰዓት ከሁለት ደቂቃ፡፡ የአንደኛውን እጁን ጥፍር ጨርሶ ወደ ሌላው ተጋባ፡፡

'አይፈራም! በፍጹም!'

ድንገት በአዳራሹ ውስጥ የነበረው ደብዛዛ ብርሃን ውድም አለና ከፊት ለፊት ያለው አቡጀዲ በሰማያዊና በቀይ ብርሃን ተጥለቀለቀ፡፡

... 4...3...2...1...0.... መብረቅ... ሰማዩን እየበዳደሰ፤ እየሰነጣጠቀ እምሽክሽክ አደረገው፡፡ ከአድማስ አድማስ የሚጠራራው የሚያስገመግመው ነጎድጓድ አዳራሹን አንቀጠቀጠው፡፡

ናትናኤል ፊቱን መልሶ ተመለከተ፡፡ በሩቅ በጨለማው ውስጥ ይታዩታል፡፡ የሁለቱም ቅርጽ ቁልጭ ብሎ ይታየዋል፡፡ በጨለማው ውስጥ ደቅቆና ጠቆር ብሎ፡፡ አፉ ውስጥ ያለውን ጥፍር ተፋና ሰዓቱን ወደ አይኑ አስጠግቶ ተመለከተ - አንድ ከአምስት፡፡

ሃምሳ አምስት ደቂቃዎች መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ልክ በሁለት ሰዓት ላይ ነው ወደ መጸዳጃው ክፍል ግቢ ያላት፡፡ ግን ደግሞ አውሬው ተከትሏት ሊገባ ይችላል፡፡

አጥፍቷል! ግን እንዴት ይጠርጥር? እሷንም እንደሚከታተሏት በምን ይወቅ? በፊት እንዳቀደው ቀደም ብሎ ወደ መጸዳጃው ቤት ገብቶ ቢጠብቃትስ? እህ! አውሬው ተከትሏት ቢመጣስ? ቢመጣስ ምን ሊያደርገው ይችላል? መቼም ተኩሶ ሊገድለው አይደፍርም፡፡ የተኩስ ድምፅ እንዳይሰማበት ይፈራል፡፡ ግን ባይገድለውም ጭራውን እንዳይዙ ፈቀደላቸው ማለት ነው፡፡ መሆን የለበትም! በጭራሽ መታየት የለበትም፡፡

ምንም ፍንጭ ሊሰጣቸው አይገባም:: ታዲያ እንዴት አድርጎ ነው ርብቃን ሊያገኛትና ገንዘቡን ሊቀበላት የሚችለው?

ቢቀርበት ይሻላል:: ትቶ ቢወጣ ይሻላል:: ከዛስ? ኪሱ ባለቸው ሰላሳ ብር እስከ መቼ ተሰውሮ ሊቆይ? የግድ ርብቃ የያዘችውን ገንዘብ እጁ ማስገባት አለበት:: እሷንም መሰናበት አለበት:: መቼም ሁሉን ዘርዝሮ ሊነግራት ባይችልም ጫፉን ሊያስይዛት ይገባል:: ከመሬት ተነስቶ ብን ብሎ አይጠፋ! ግን ምንድነው የሚላት? «እየቃዠሁ ነው» ብትለውስ?

ሰዓቱን ተመለከተ:: አንድ ከሃያ አምስት:: ሰላሳ አምስት ደቂቃዎች ቀሩት...

ድንገት በቲያትር ቤቱ አዳራሽ ውስጥ ተኩስ አስተጋባ:: ደገመ:: የሴት ጩኸት - እሪታ:: ደገመ:: ሌላ ጥይት አፏጨ:: የሥቃይ ድምጽ ጣር:: ናትናኤል አይኖቹን አፈጠጠ:: ከፊት ለፊቱ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ በደም የተበከለ ጭንቅላቷን በሁለት እጆቿ ግጥም አድርጋ ይዛ ወደፊት ስትንከባለል ስትደፋ ተመለከታት:: ቶሎ ብሎ አይኖቹን በአዳራሹ ከምት ታየው የፊልም ተዋናይ ላይ አነሳና ዞር ብሎ በጨለማው ውስጥ ጠቆር ብሎ የሚታየውን የርብቃን ማጅራት ተመለከተ:: ተዝናንታ ተቀምጣ ፊልሙን ትመለከታለች::

ሳይታወቀው ሆዱ ተላወሰበት:: ምን ማድረጉ ነው? ለምን በዚህ ነገር ውስጥ ርብቃን ከተታት? እነዚህ ነፍሰ ገዳዮችኮ እሱን ሲያጡ ወደ እርሷ ሊዞሩ ይችላሉ:: አጥፍቷል! አደገኛ ስህተት ነው የፈጸመው:: እሱ ወደ የገባበት ዓለም ነው:: እሷ በምን ዕዳዋ?

የዛሬን ብቻ! ከዛ በኋላ አጠገቧም አይደርስ:: እሷ የምታውቀው ነገር እንደሌለ ሊረዱ ይገባል:: ለአንድ አፍታ የእሱ ርብቃም እንደ አብርሃም በጀርባዋ ተንጋላ አይኖቿ ፈጠው ሞትን ሲጠባበቁ ታዩት:: ሰውነቱን ነዘረው:: ሁለተኛ አጠገቧ አይደርስም!

ሰዓቱን ተመለከተ:: ለሁለት አስር ጉዳይ:: አስር ደቂቃ::

ጣሪያው ላይ ጥፍር ፈሰገ፤ አጣ:: የከንፈሩን ጫፍ ይቀነጣጥብ ጀመር:: ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ርብቃ በጸፈላት መሠረት ተነስታ ወደ መጸዳጃ ቤት ትገባለች:: ያን ጊዜ ምን ማድረግ አለበት? ተከትሏት መግባት? ሰውየው ተከትሏት ቢመጣስ? ባለበት ተቀምጦ መቆየት? ሳያገኛትና ሳያነጋግራት ገንዘቡን ሳይቀበላት መሄድ? የገዛ ልቡ ደረቱን ሲደልቀው ፍርሃት እንደ ውርጭ ሲያንጠረጥረው እራሱን ታዘበ:: ምንድን ነበር ያሰው አብርሃምን? "አልተዋቸውም እኔንም እስኪገድሉኝ አልተዋቸውም" ታዲያ አሁን ፍርሃትን ምን አመጣው? አፍ መድረቅንና እጅ ማላብን ምን አመጣው? ናትናኤል እራሱን ጠላው፤ ተፀየፈው::



ድንገት በጨለማው አዳራሽ ውስጥ እንቅስቃሴ ታየው:: ዞር ብሎ አይኖቹን በሰፊው ከፍቶ በጨለማው ውስጥአፈጠጠ::ርብቃ! ከተቀመጠችበት ተነስታ ከጀርባ የተቀመጠውን ተመልካች እንዳትከልል ጎንበስ ብላ ወደጎን እየተራመደች ወደ መተላለፊያው ወጣች::ናትናኤል ሰዓቱን ተመለከተ - ሁለት:: ዞር ብሎ ከጀርባዋ የተቀመጠውን ሰው ተመለከተው:: ሰውየው ከቦታው አልተንቀሳቀሰም:: ርብቃ ወደ መተላለፊያው ደረሰችና ወደ መጸዳጃ ቤት የሚወስዱት ደረጃዎች በጨለማው ውስጥ እንዳያደናቅፏት በቀኝ እጇ ግድግዳውን እየዳበሰች ደረጃውን መውጣት ጀመረች::

መጸዳጃው ቤት በር አጠገብ ካለ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ ናትናኤል እየቀረበችው ስትመጣ በጭለማው ውስጥ ተመለከታት:: ዞር ብሎ በሰውየው አቅጣጫ ተመለከተ:: ከቦታው አልተነቃነቀም::ርብቃ ደረጃዎቹን ጨርሳ በስተግራው ያለውን የመፀዳጃ ቤቱን መዝጊያ ከፍታ ስትገባ ከውስጥ ከመጸዳጃ ቤቱ የወጣው ነጭ የፍሎረሰንት ብርሃን ለአንድ አፍታ ቀልቀል በአዳራሹ ውልብ አለ::

አፍጥጦ እየው::አውሬው ፊቱን ወደ ኋላ ጠምዝዞ በአይኑ ይከታተላታል:: የመፀዳጃው ቤት መዝጊያ ተመልሶ ሲዘጋ አስፈሪ ፊቱን የአዳራሹ ድቅድቅ ጨለማ ዋጠው::

ናትናኤል ሳይታወቀው አፍኖ የያዘውን ትንፋሹን ለቀቀው:: አሁን ቶነስቶ መግባት አለበት:: አለበለዚያ ርብቃ ግራ ትጋባለች:: ሲቀርባት፤ ስታጣው እንደ አብርሃም አደጋ ደርሶበታል ብላ ልትሰጋ ትችላለች:: ወደ ውስጥ ሲገባ አውሬው ተከትሎት ቢመጣስ? ለምን ከበሩ ኋላ ጠብቆ ማጅራቱን ብሎ ከመሬት አይጠቀልለውም? ቡጢ ጨበጠ ናትናኤል:: ሲመታው ባይወድቅለትስ? ማጅራቱን ሲለው ተንገዳግዶ ቢቆምስ? ፊቱን መልሶ ቢያፈጥስ?ሸሚጡን ላጥ አድርጎ አነጣጥሮ ጭንቅላቱን ቢፈረክሰውስ? ናትናኤል የጨበጠውን ቡጢ ለቅቆ በተቀመጠበት ወንበር ላይ ተመቻቸ::

ሰዓቱን ተመለከተ:: ሁለት ከአምስት:: የት ጠፋች? እየጠበቀችው መሆን አለበት:: ርብቃ እንዴት አድርጌ ልምጣ? ተነሳ ሰውየው፤ አውሬው ተነሳ! ጎንበስ ብሎ ወደ ጎን እየተንፏቀቀ ወደ መተላለፊያው ወጣና ወደ መጸዳጃው ቤት የሚያመሩትን ደረጃዎች አንድ በአንድ በጥንቃቄ እየቆጠረ ተጠጋ::

የት ነው የሚሄደው? ርብቃ ውስጥ ነበረች መዘግየቷ ጥርጣሬ ውስጥ ከቶት መሆን አለበት ተከትሏት ሊገባ የወሰነው::

ሰውየው ደረጃዎቹን እየወጣ እየቀረበ ሲመጣ ያ ግዙፍ አካሉ በጨለማው ውስጥ እየረዘመና እየተመዘዘ ሲመጣ ናትናኤል የእንገት ልብሱን እስከ አፍንጫው ድረስ ከፍ አድርጎ ይዞ ሰውነቱን በተቻለው አሳንሶ ወንበሩ ላይ ተሸማቆ ተቀመጠ::

ሰውየው የመፀዳጃ ቤቱን በር ወደ ውስጥ ገፍቶ ሲገባ ነጩ ብርሃን ድ.ንግማ. በአዳራሹ ውልብ አለና መልሶ ድርግም አለ፡፡ ብዙም ሳይዘገይ በሩ ድ.ንግማ. ተከፈተ፡፡ ናትናኤል በቀስታ ፊቱን ወደ ግራ መለስ አድርጎ የጎድን ቁልቁል ተመለከተ፡፡ ከመፀዳጃው ክፍል የወጣው ሰው በሩን ዘግቶ ወደፊት ተራመደ፡፡ 'ጫማውን! ጫማውን!' በደረጃዎቹ ጥግ በበሩት ትናንሽ መንገድ ማሳያ ቀያይ መብራቶች ተመለከተ... እግር... ጫማ... የሴት ጫማ... ርብቃ!.... 'አሁን!'

"ርብቃ!" አንሾካሾከ ናትናኤል፡፡ ፈጠን ብሎ ወደግራ አዝምሞ ቀኝ ክንዷን ጨመደደና ወደራሱ ጎተታት፡፡ "እኔ ነኝ ርብቃ" አለ ደግሞ በሹክ ሹክታ፡፡ "ናትናኤል ነኝ" ክንዷን እንደያዘ በእግሮቹ ላይ አሻግሮ በስተቀኙ አስቀመጣት፡፡ እንደ እቃ ተጎተተችለት፡፡ ወዲያው ነፍሷን ስታውቅ በጨለማው ውስጥ አፈጠጠችበት፡፡

"ምንድነው ነገሩ? ምን ሆነሀል? "

"ሽ - -ሽ! ዝም በይ፡፡"

በስተግራው ያለው በር ተከፈተ፡፡ ለአንድ አፍታ ነጩ ብርሃን በአዳራሹ ቁልቁል ተወራጨና መልሶ እልም አለ፡፡ ዙሪያው ጨለማ ለበሰ፡፡ ከመፀዳጃ ቤት የወጣው ሰው ሁለት እርምጃዎች ወደፊት እንደተራመደ ድንገት ቆም አለ፡፡ ለአፍታ የተደነጋገረው መሰለ፡፡

ሰውየው ርብቃን በቦታዋ ሲያጣት እንደተደናገጠ ናትናኤል ተረዳ፡፡ ወዲያው ሰውየው ፈጠን ብሎ ደረጃዎቹን ወርዶ ቀዩን መጋረጃ ገልጦ ከአዳራሹ ወጣ፡፡

"ምንድነው ነገሩ ናትናኤል?" ትከሻውን ጨምድዳ ጠየቀችው፡፡

"ቀስ ብለሽ ተናገሪ!" ግራ እጇን በሁለት መዳፎቹ መሃል ከቶ አሻሸው፡፡ "አመጣሽልኝ ያልኩሽን ገንዘብ?"

"አዎ... ግን ምንድነው የሆንከው?"

"ርብቃ ነገሩን ከመነሻው ሳስረዳሽ አልችልም፡፡ ጊዜውም የለኝ፡፡ ደግሞ ነገሩን ማወቅሽም ጥቅም የለውም፤ ጉዳት እንጅ፡፡"

"ለምንድነው የምትደብቀኝ ናትና..."

"ቆይ - -ቆይ" አቋረጣት ክንዷን ያዝ አድርጎ፡፡ «እነግርሻለሁኮ፡፡ ባጭሩ እነግርሻለሁ፡፡ ርብቃ በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ኤምባሲዎች የሚሰሩ ሁለት የውጭ ዜጎች ባለፈው ሳምንት ተገድለው ተገኙ! አንዱ ደግሞ ተሰወረ፡፡ አብርሃምጋ የሄድኩት ስለዚሁ ጉዳይ የሚያውቀው ነገር እንዳለ እንዲነግረኝ ነበር፡፡ ብቻ ምን ልበልሽ... ባጭሩ የተሰወረውን ሰው አድራሻ እንደምንፈልግ ሲያውቁ እኔንም አብርሃምንም ሊያጠፉን ተነሱ፡፡ አብርሃምን ገደሉት፡፡ እኔ የዛን ማታ ትራፊክ ይዞኝ አመለጥኩ፡፡ ርብቃ ያን ማታ አብርሃም አልነበረም ደውሎ የጠራኝ፤ ሊያጠምዱኝ ነበር፡፡



ባጭሩ አሁን እኔንም አይተውኝም፡፡ ለጊዜው መሸሸግ አለብኝ፡፡ አለበለዚያ ባላሰብኩት ሰዓት የአብርሃም ዕጣ ነው የሚጠብቀኝ፡፡"

"ማናቸው እነሱ?"

"አላውቅም፡፡"

"እንዴት አታውቅም! ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ እያልከኝ፡፡"

"እውነቱን ነው ርብቃ አላውቅም፡፡ ብቻ አብርሃምን ከሱም በፊት ሌሎችን እንደገደሉ አውቃለሁ፡፡ ካገኙኝ ተራው የኔ ነው፡፡"

"ገብሬልዬ! ምንድነው የምታወራው? አንተን ምን ከተተህ እዚህ ውስጥ መጀመሪያ ነገር?" በሆዷ የደበቀችውን ማውጣት አለባት፤ ሁሉን!

"ርብቃ..."

"ለምንድነው ለፖሊስ የማትናገረው... ? ለፖሊስ ተናግሮ ማስያዝ ነው እንጅ ለምንድነው የምትሸሸገው? አንተ ገዐህ አስከሆንክ ድረስ?" ልታረጋጋው ይገባል፡፡ ጊዜ... ጊዜ ያስፈልጋታል፡፡ ከዛ በኋላ ምሥጢር ብላ የያዘችውን ትነግረዋለች፡፡

"ፖሊስ ዋጋ የለውም፡፡ ፖሊስ እንደማይመልሳቸው እርግጠኛ ነኝ፡፡" ናትናኤል የስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ሁኔታ ታወሰው፡፡

"ለምን አይመልሳቸውም!... ደፍረው ፖሊስ ጣቢያ አይመጡ!" አባብላው ይዛው ቤቷ መሄድ አለባት! ጥሏት መጥፋት የለበትም... ፍጹም!

"ርብቃ እመኚኝ... ምንም አጥር አይመልሳቸውም፡፡" ናትናኤል ርብቃን ሊያሳምንበት የሚችልበት ዘዴ ሲጠፋው ትንፋሹ አጠረው፡፡ አላማው ሽሽትና ነፍሱን ማዳን ብቻ እንዳልሆነ... ማሳደድም የላይቤርያውን አታሼ ማግኘት፤ አውሬውን ማጥመድ የአብርሃምን ደም መበቀል መሆኑን በነገራት ትረዳለት ይሆን? 'የት አባታቸው በርታ!' ትለው ይሆን ወይስ 'ተው ይቅርብህ፤ ይገድሉሃል' እያለች የሳሳች ልቡን በፍርሃት ትነጣት ይሆን? "ርብቃ ለትንሽ ቀናት ነው የምሸሸገው፡፡ እመኚኝ! እንደሚያዙ እርግጠኛ ነኝ! ካለሁበት ቦታም ቢሆን እደውልልሽና እንነጋገራለን በስልክ፤ በስልክ በጓደኛሽ በኩል፤ ምህረት ቢሮ፡፡"

"የዚህን ያህል አደገኛ ከሆኑ ለምን እኔጋ አድረህ ነገ ጠዋት ነገሩን ሁሉ ዘርዝረህ ለፖሊስ አታሳውቅም?"

ሳቅ አለ ናትናኤል። "አንቺ ጋ መሆን አልችልም። በቀላሉ ያገኙኛል።" እንደሚከታተሏት ማወቅ የለባትም ትሸበራለች። አሰበ።

" የኔን ቤት የት ያውቁታል? እየው..."

"ርብቃ እባክሽ የምልሽን ተቀበይኝ! ሌላ የምቆይበት ቦታ አስ አታስቢ።"

"እንዴት ነው የማላስበው በሠላም አገር እንዲህ ስትሆን? የት ነው የምትቆየው ለመሆኑ? ቆይ ገገ ቢሮ ልደውልልህና...."

ናትናኤል ከዚያ የተናገረችውን አላዳመጣትም። ቀዩ መጋረጃ ተንቃንቀ ተገለጠ - አውሬው!

"የታለ ያመጣሽው ገንዘብ?" በጨለማው ውስጥ ዞር በሹክሹክታ ጠየቃት።

በፍጥነት ቦርሰዋን ከፍታ አንድ ፖስታ አቀበለችውና ሌላ የተጠቀለለ ገንዘብ ሰጠችው።

"ምንድነው ይሄ?"

"እቤት ያለውን ገንዘብ ሁሉ አምጪ ስትለኝ ካስቀመጥከው ስምንት መቶ ብር በላይ እንደምትፈልግ ስለገባኝ እቤት ያስቀመጥኩት አንድ ሽህ አምስት መቶ ብር ነበር፤ ይገርው መጣሁ።"

ትላልቅ አይኖቿ በጨለማው ውስጥ በቅዱሳተ ቅዱሳት መሃል የተለኮሱ ጧፎች መሰሉት። ጠጋ ብሎ በተራ ሳማቸው። ቀና ብሎ በመጋረጃው አቅጣጫ ተመለከተ። ሰውየው መጋረጃውን ገልጦ ወደ ውስጥ ገባ።

"ናት..."

"ቻው ርብቃ።" አለ ልታቅፈው ስትጀምር፤ ልታናገረው ስትጀምር፤ ድምጿ መስለል ሲጀምር ፈጠን ብሎ ኮስተር አለና። "አታስቢ እሺ? ጥሩ ቦታ ነው የምቆየው።"

"እኮ መቼ ትመጣ...?" እንባ ሲተናነቃት ድምጿ ከመሃል ከዳት።

"ስችል እኔ ራሴ አገኝሻለሁ።" እንደገና ጠጋ ብሎ ሳማት። በጨለማው ውስጥ ያጋጠመውን በስስት ላሰው... ጉንጮቿን ... ቅንድቧን... አይኗን... አፏን። "እወድሻለሁ ርብቃ" አይኖቿን የሳመበት አፉ ጨው ጨው አለው። "ርብቃ አታልቅሺ፤ እባክሽ አታስጨንቂኝ።" ትከሻዎቿን ይዞ ነቀነቃት። ዞር ብሎ ወደ መጋረጃው ተመለከተ።



ሰውየው ግራ ተጋብቷል። ይከተላት የነበረችው ሴት እዚያው አዳራሽ ውስጥ ቦታ ትቀይር ወይ ወደ ምድር ቤት ትሂድ እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም። ከትያትር ቤቱ አለመውጣቷን ከዘበኞቹ አረጋግጧል። እንግዲያው የት ነች? ወደ መጀመሪያው የወንበሮች ረድፍ ጠጋ ብሎ ጫፍ ላይ አንድ ወንበር መልሶ ተቀመጠ።

"ከጠፋህብኝ ግን ሄጄ ለፖሊስ ነው የምናገረው!" ትከሻውን ያዛ።

"ያኔ ሞቴን ታፋጥኝልኛለሽ።"

"ናትናኤል!" ግራ ገባት ርብቃ 'ጉዱን ብትነግረው ይሻል ይሆን? ያረገዘችውን... በሆዷ የያዘችውን... ወይስ...'

"ነገርኩሽ እኔ እራሴ እመጣለሁ። ቻው።" ናትናኤል የያዘውን የርብቃን ክንድ ጨብጥ አድርጎ ለቀቀና ከወገቡ ጎብደድ ብሎ በጨለማው ውስጥ አግድም በስተቀኝ ተራመደ። ከበባቡ መተላለፊያ አሁንም ጎንበስ እንዳለ በስተቀኝ በኩል ወዳለው የአዳራሽ በር አመራ። ከመውጫው ደርሶ መጋረጃውን ገልጦ ከወጣ በኋላ ከውጭ በኩል መጋረጃውን በቀጭኑ ገለጥ አድርጎ ከጀርባው የተከተለው ሰው አለመኖሩን አረጋገጠ። በጨለማው ውስጥ አውሬውን ለመለየት ባይችልም በአዳራሹ ውስጥ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ መጋረጃውን ለቅቆ ጠባቦቹን ደረጃዎች በጥድፊያ ወርዶ በአንገት ልብሱ ግማሽ ፊቱን ሸፍኖ ከትያትር ቤቱ ወጣ።

መንገዱን ተሻግሮ ወደ ታክሲ ተራ ሲያመራ ወደ ቀኝ ገልመጥ ብሎ ተመለከተ። ነጯ ሲትሮይን በቦታዋ ቆማለች።

ሁለት እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ጨመረና ታክሲ ከሚጠብቁ ሰዎች መሃል ገብቶ ተቀላቀለ።

'ሊነግረኝ አልፈለገም እንጅ የፈራሁት ደርሷል። ከዛ ከጓደኛው ጋር ያደረገው ነገር አለ። ገብሬልዬ!'

ከቲያትር ቤቱ የወጣችው ፊልሙ ሳያበቃ ናትናኤል እንደሄደ ነበር። ፒያሳ ወደሚገኘው አፓርታማዋ የሚወስዳትን ታክሲ ለመያዝ መንገዱን ተሻግራ ቆመች። ጭንቅላቷ ውስጥ ተራውን ሳይጠብቅ የሚግተለተለው መጥፎ ሃሳብ አብሰከሰካት። ፍዝዝ ብላ እንደቆመች ሁለት ታክሲዎች አለፏት።

"ታክሲ! ፒያሳ!" ሶስተኛ ከማለፉ በፊት ጮሃ ተጣራች፤ አልሰማትም።

ናትናኤል ክንዷን ጨበጥ አድርጎ ተሰናብቷት ሲሄድ ያዥው ያዥው ነበር ያላት። ንገሪው ሁሉን ዘርግፊለት፤ ዘርግፊለት ነበር ያሰኛት። አዎ ሊጠላት ይችላል፤ ሊቆጣ ይችላል፤ ቢሆንም ሳያውቅ መሄዱ አንገበገባት። ብትነግረው ይሻል ነበር። እሱን ለማጥመድ፤ መረብ ውስጥ ለመክተት፤ ለመጉዳት ብላ እንዳሳደረገችው አስተዛዝና ብትነግረው ይቅርታ ያደርግላት ነበር። ምን ማድረግ እንዳለባቸው አብረው ዕቅድ ያወጡ ነበር። ዘገየች!

"ታክሲ! ፒያሳ!" አራተኛው ታክሲ ጥሏት ሳይሄድ ጮሃ ተጣራች።

ባለታክሲው ገልመጥ እያለ እየተመለከታት ሲያመነታ ቆየና እራቅ ብሎ አቆመላት። ሮጥ ብላ የኋላውን በር ከፍታ ገባች።

"ፒያሳ?" አላት ባለታክሲው ፊቱን ወደኋላ መልሶ ለማረጋገጥ።

"አዎ።" አለችው ርብቃ ጭንቅላቷን በ 'አዎንታ' እየወዘወዘች።

"ከኋላሽ መጥቶ ሲቆለልኮ ልትገቢ መስሎኝ ነው ያለፍኩሽ።" አላት ባለታክሲው ፈገግ ብሎ በኋላ መመልከቻው መስታወት እየተመለከታት።

"እ?" አለች ምን እንደሚያወራ አልገባ ሲላት

"ሲትሮይኑን ነው የምልሽ ሃ! ሃ! " ባለታክሲው ሲስቅ ሞኝ ይመስላል።

"ሲትሮይን?"

"አላየሽውም እንዴ? ከኋላሽኮ አንገርቦ ነበር። በእንጀራሽ እንዳልገባ ነበርኮ መጀመሪያ ስታስቆሚኝ ያለፍኩሽ።" ያንኑ የሞኝ ሳቁን መረቀላት።

የሚያወራው ስላልገባት ዝም አለችው።

"ሃ! ሃ! ተስፋ አልቆረጠም ሰውዬሽ። ያውልሽ ይከተለኛል። ብጫ መብራት። ሃ! ሃ!" አላት ባለታክሲው በኋላ መመልከቻው ከጀርባ የሚከተለውን ሲትሮይን እየተመለከተ።



ርብቃ ጭንቅላቷን ጠምዝዛ ከጀርባዋ የሚከተላትን መኪና ተመለከተች። ወደ ጎን ሞለል ሞለል ያሉት ብጫ የፊት መብራቶች የሲትሮይን አይን መሆናቸው በሩቁ ያስታውቃል።

"ቆጨሽ እንዴ? " አለ ባለታክሲው ፈገግ ብሎ።

"ምኑ?"

"እኔ ታክሲ ውስጥ መግባትሽ ነዋ። አጠፋሁ ወ - -ይ ለማለት ነው ሃ! ሃ! ሃ!"

ቸካት፤ ዝም አለችው።

"ትንሽ ብትታገሺ በነፃ ፒያሳ የሚያደርስሽ ታገኚ ነበር ለማለት ነው። ሌላ ሌላውን ብንተወው እንኳን እ?"

የባለታክሲው ጨዋታ አልጥምሽ ሲላት ፊቷን ወደውጭ መልሳ መመልከት ያዘች።

"አ! አ! ጠንካራ ነው ሰውዬሽ!" አላት ባለታክሲው የቸርችል ጎዳናን ወጥተው ወደ ፒያሳ ሲታጠፉ።

"እ? "

"ሰውዬ...ሽ ጠንካራ ነው አልኩ።" አለ እየተቁነጠነጠ። "አሁንም ተከትሎናል። ቆራጥ ነው እንቺዬ!"

ርብቃ ወደኋላ ዞራ ተመለከተች። እነዛው ሞላላ ብጫ መብራቶች አፈጠጡባት።

"ታውቂዋለሽ እንዴ?."

አልመለሰችለትም።

"ከዚህ ነው የምታጠፊው" አላት ሲኒማ ኢትዮጵያ ጋ ሲደርሱ። "መልካም ሌሊት! ሃ! ሃ! ሃ!" ሂሳቡን ከፍላ ዞር ስትል በጅል ሳቁ ተሰናበታት።

ርብቃ ወደቀኝ ታጥፋ ቁልቁል ወደ አፓርታማዋ አመራች። የአፓርታማዋን አጥር ግቢ በር አልፋ ከገባች በኋላ አንደኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኘው ክፍሏ ከመውጣቷ በፊት ምድር ቤት ካለችው ትንሽ ግሮሰሪ ገባች።

"እንደምን አመሻችሁ።" አለች ርብቃ የግሮሰሪዋን ባለቤትና የልጅ ልጃቸውን ስታይ።

"እንደምን ዋልሽልኝ የኔ ልጅ።" አሉ አሮጊቷ የግሮሰሪ ባለቤት ደንበኛቸውን ሲያዩ በተቀመጡበት እየተሻሹ።

"እስቲ የቢራ ሶሚ ስጪኝ እንትናዬ።" አለች ርብቃ ወጣቷን ልጅ።

"ርብቅዬ ደህና ነሽ? " አሏት እሮጊቷ ባለግሮሰሪ። መልስ ሲያጡ ቀጠሉ፡ "እኔንስ አሞኝ ሰነበተ ባክሽ። ክረምቱ ክፉቶም ይሁን እኔ እየጠነከርኩ መጥቼ! እንጃ ብቻ" እሮጊቷ ብቻቸውን ሳቁ። "ምነው ዛሬ በእግርሽ?" አሉ አሮጊቷ ለወትሮው በመኪና እቤቷ ድረስ አድርሷት ከግሮሰሪያቸውም ምናምን ገዛዝቶ የሚሄደውን ወጣት ከአጠገቧ ሲያጡት ፈገግ ብለው እያይዋት።

"አይ-ደህና ነው! ዘመድጋ አምሽቼ ነው።" አለች ርብቃ ቋንቋቸው ሲገባት። ወጣቷ ልጅ የተጠየቀችውን ሎሚ እንዳቀበለቻት ሂሳቡን ከቦርሳዋ አውጥታ ክፍላ "ደህና እደሩ።" ብላቸው ወጣች።

ከግሮሰሪው ወጥታ ወደ ፎቁ በር ዞር ስትል አየቻት። ሲትሮይኗ። ከአፓርታማው ግቢ ውጪ መብራቶቿን አጥፍታ ቆማለች! ከአፓርታማው ግቢ ውጪ መብራቶቿን አጥፍታ ቆማለች! ርብቃ ችላ ብላው ወደ ፎቁ ገባች። የአፓርታማዋን አሰልቺ ደረጃዎች ወጥታ አንደኛ ፎቅ ላይ የሚገኘውን የክፍሏን በር ከፍታ ልትገባ ስትል የማጠበስ ስጋ ሽታ አወዳት፡፡ሆዷ ተላወሰባት። ቶሎ ብላ በሩን ከፍታ ገባችና አንድ ሎሚ አውጥታ አፍንጫዋ ስር ያዘችው። ይህን ሰሞን ሆዷ አለቅጥ እየተረበሸ አስቸግሯታል። የአፓርታማውን በር ከውስጥ ቆልፋ የሳሎኑን መብራት ሳታበራ የመኝታ ቤቷን በር ከፍታ ገባች። መብራቱን ካበራች በኋላ ቦርሳዋን ጥግ ካለ ወንበር ላይ ወርወር አድርጋ ወደ ጠባቧ መታጠቢያ ቤቷ ገባች።

ፊቷን በቀዝቃዛ ውሃ ከታጠበች በኋላ በፎጣ አደራርቃ ወደ መኝታ ቤቷ ተመለሰች። መኝታ ቤቷ መካከለኛ ስፋት ያለው ነው። በአንድ ወገን መሃል ለመሃል አልጋዋ ተዘርግቷል! በስተቀኝ ቦርሳዋን ጣል ያደረገችበት ረጅም መደገፊያ ያለው አረንጓዴ ወንበር ተሰይሟል። ከአልጋዋ ፊት ለፊት ማታ ማታ አምሽታ ስትሰራ የምትቀመጥበት ወንበርና ጠረጴዛው ጥግ ይዘዋል። ጠረጴዛው ሰፋ ያለ ቢሆንም የተሸከማቸው በርካታ መጽሐፎችና ወረቀቶች ጠባብ አስመስለውታል። ከጠረጴዛው በስተግራ ግድግዳውን ታክኮ የቆመው የመጽሐፍ መደርደሪያ ውስጥ ደግሞ በተለይ በአፍሪካ ደራሲዎች የተደረሱ በርካታ መጽሐፎች ተገጥግጠዋል።

ከበሩ በስተቀኝ ወዳለው ቁምሳጥን ሄደች ብላ ከታችኛው መሣቢያ ውስጥ የሌሊት ልብሷን አወጣችና አልጋዋ ላይ ጣል አደረገችው። እንደወትሮዋ ግን የለበሰችውን ልብስ አንድ በአንድ ማውለቅ ያዘች። በተስላቸ ሁኔታ ያወለቀቻቸውን ልብሶች ከቁምሣጥኑ አልሰቀለቻቸውም። ብጫውን የሌሊት ልብስ እያወለቀች ወንበሩ ላይ ተራ በተራ ጣለቻቸው። ብጫውን የሌሊት ልብስ አጠለቀችውና ከጠረጴዛዋ ፊት ለፊት ተቀመጠች።

ማንበብም ሆነ መጻፍ አላሰኛትም። ለአንድ አፍታ ጠረጴዛው ላይ በተከመረው ወረቀት ላይ አፈጠጠችበት። ልትከላከለው ብትሞክርም እየሮጠ ግጥሥም የሚልባት የናትናኤል ነገር ጮሂ ጮሂ አሰኛት-



አሁን ምን ይባላል? በገዛ እጇ!ከዛሬ ነገ ስትል! ስትርበተበት እሷው ባጠመደችው እንዲህ ዓይነት ነገር ውስጥ ገባና አረፈው። የኋ ናትናኤል ሀ!የልጇ አባት!ቀኝ እጇን ወደ ሆዷ ልካ ዳሰሰችው። ግን ምንድነው ያላት ናትናኤል? "ከኤምባሲ የጠፋ ሰው ስንፈልግ... አብርሃምን ገደሉት እኔንም እይተውኝም..." ምን ማለት ነው? እውነቱን እንደሆነስ? ግን ምኑ ነው እውነት የሚመስለው? ግራ የገባው ነገር ነውኮ። ሊነግራት አልፈለገም እንጂ ነገሩ ሌላ መሆን አለበት። ደግሞስ እሱ ንፁህ እስከሆነና ጥፋት እስካላጠፋ ለምን ሊገሉት ይነሳሉ? ለምንድነው ነገሩን ሁሉ ዘርዝሮ ሊነግራት ያልፈለገው? አንድ የሆነ ነገር አለ።' ሆዷ ውስጥ ያለው ሽል የተፈራገጠ መሰላት። እንባዋ አሰፌሰፈ! ሆዷ ተገለባበጠባት! ጉንጮቿን እየገመሰ የሚወርደውን እንባ ችላ አለችው።

ለምን ያህል ሰዓት እንደቆየች አታውቅም። በመጨረሻ ከተቀመጠችበት ተነስታ መታጠቢያ ቤት ገብታ በእንባ የራሰውን ፊቷን በቀዝቃዛ ውሃ ደጋግማ ታጠበችው! የጋለ ሰውነቷን አቀዘቀዘችው። ሁለት የእንቅልፍ እንክብሎች ከዋጠች በኋላ የመታጠቢያ ቤቱን በር ዘግታ ወደ አልጋዋ አመራች። አልጋዋ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ወፍራሙን መጋረጃ ለመጋረድ ወደ መስኮቱ ስትጠጋ በስሱ መጋረጃ ውስጥ ድጋሚ ተመለከተቻት።

ነጯ ሲትሮይን እዚያው በቆመችበት አለች።

ርብቃ ወፍራሙን መጋረጃ ጋርዳ አልጋዋ ውስጥ ገባችና በራስጌዋ የተቀመጠውን የፎቶግራፍ ምስል አንስታ ትክ ብላ ተመለከተችው-

"ናቲ ያደረከትን ብነግርህ ይቅርታ ታደርግልኝ ይሆን? ናቲ የዘረጋሁብህን ወጥመድ ብነግርህ ትምረኝ ይሆን? ናቲ እርግገርልሃለሁ።" እንባዋ አይኖቿ ጠርዝ ላይ አሰፈሰፈ!ተንቀዋለለ - ተወችው። ፈሰሰ። "ናቲ ልጅህ ይራገጣል።"

11

## “እያንዳንዱ ትውልድ ሃላፊነቱን ሊገነዘብ ይገባል፤ ሊፈጽመው አልያም ሊከዳው::”

ፍራንዝ ፋኖን

-14-

“ፕ!ደህና አድርጎ ረገጠን አይደል!” አለች ዘውዲቱ የሚያናፋው ውሽንፍር አንድ ክፍል ቤቷ ከመግባቱ በፊት ተሽቀዳድማ በሩን እየዘጋች:: «የበደ ክረምት:: አሁንስ መግቢያና መውጫያም ጠፋው መሰለኝ::» በስብሶ አላይዋ ላይ የተጣበቀ ቀሚሷን የእባብ ቆዳ እንደሆነ ሁሉ ቁልቁል በጥያፌ ተመለከተችው::

“ሃይለኛ ዝናብ ነው:: አይደል?» አላት ፊቱን ያበሰበሰውን ውሃ በመዳፉ እየሞዠቀ::

“ምን ትጠይቀኛለህ... በቁመትህ ሙሉ እያዝረበረብከው::” ራመድ ብላ የፊት መመልከቻ መስታወቱ ከላይ እስከታች የተተረተረ ቁምሳጥኗን ከፈተችው:: “ምን ታየኛለህ !አውልቀው እንጅ ኮትህን:: በስብሰሃል'ኮ:: እስኪደርቅ ነው እንጂ የምትጠብቀው?” ከውስጥ ደረቅ ልብስ እያወጣች::

“የት ጋ ላድርገው?” አለ በዝናቡ ውሃ የበሰበሰውን ኮቱን አውልቆ በሁለት ጣቶቹ አንቀርናፎ ይዞ::

ክፍሏ ጠባብ ነች:: አንድ ታጣፊ አልጋ ጥግ ይዛለች:: በስተግርጌ እንደከመዲኖ የሚያገለግል የእንጨት ወንበር ቆሟል:: ባንድ ጠርዙ ላይ የቆመችው ሻማ እንጥፍጣፊ ወርዶ አንድ እግሩን አልብሶታል:: መሃል ላይ አንድ ትንሽ የዳንቴል ጨርቅ ተነጥፋበታለች:: በጨርቋ ላይ አንድ የሸቶ ብልቃጥና የጥፍር ቀለሞች ተደርድረዋል:: ከበሩ ትይዩ... ከመስኮቱ በስተቀኝ በተደራረቡ የሸክላ ጡቦች ላይ ተደግፎ የቆመው መስታወቱ የተሰነጠቀ ቁም ሳጥን ተገትሯል:: ሌጣዋን ብው የምትለው አንድ አምፖል ክፍሉ ጠብታል::

“በሩ ላይ ሚስማር አለልህ... አንጠልጥለው::” አለች ጫማዎቿን እያወለቀች:: “ወይኔ ደሄ ብሽቅ ሶል ድጋሚ ለቀቀ::”

“ምን አልሽኝ?”



“ተወው እዚሁ ነው:: ያዝ ፀጉርህን አድርቀው:: ሸሚዝህንም አውልቀው እንጂ” ሽንጉርጉር ሰፊ ፎጣ ወረወረችለት:: በውሃ የራሰ ወይን ጠጅ ቀሚሷን በጭንቅላቷ አወለቀችውና ራስኬ የቆመው ወንበር ድጋፍ ላይ ዘርጋ አድርጋ አሰጣችው:: ለነገ ይደርቃል::

አይኖቹ ሳይፈልግ ከጅርባ ከወገቧ በታች ካለው ሞላ ያለ ሰውነት ላይ አረፈ:: ነጩ ስስ የውስጥ ልብሷም አልተረፈ፤ ብስብስ ብሏል:: ገላዋ ላይ እንደሙጫ ተጣብቆ ያረፈበትን ገላ ቅርጽ ይዞ ለሰው እይን ይዳርጋል:: የጡት መያዣ አላደረገችም::

መሬት የወደቀውን ፎጣ አነሳና ሸሚዙን ማውለቅ ጀመረ:: የፎጣው ቀለም ብጫ ቢሆንም የተሸከመው እድፍ ቡራቡሬ አስመስሎታል፤ ቀፈፈው::

“አዳርቀው እንጅ- ዋ!በኋላ ብርድ እንዳያደርቅህ::” አልጋዋ ጫፍ ላይ ቁጭ አለችና ነጩን የውስጥ ልብስ በጭንቅላቷ አወለቀችው:: አረንጓዴ ነጠብጣቦች ያሉት ነጭ የውስጥ ሱሪ አጥልቃለች:: “ስትጨርስ ፎጣውን ወርውርልኝ::” አለችው ጀርባዋን ሰጥታው እንደተቀመጠች::

ፎጣውን ወረወረላት::
ከተቀመጠችበት ተነስታ ገላዋን በፎጣው ታደራርቅ ጀመር::
“ምን ቆመህ ታየኛለህ... ሱሪህን አውልቅና አልጋ ውስጥ ግባ እንጅ:: መብራቱንም አጥፋው::”

ከቆመበት ሳይንቃነቅ ቁልቁል ተመለከታት:: ርብቃ ታወሰችው:: ንጽህናዋ ጨዋነቷ... 'የፈጣሪ ያለህ! ከሸርሙጣ ጋር!' መብራቱን ሳያጠፋ ሱሪውንም ሳያወልቅ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ:: 'ምንድን ነበር የጠበቀው? ሁለት አልጋ? የፈጣሪ ያለህ! ከሸርሙጣ ጋር? ራሱን ማመሳሰል አለበት? ባይመሳሰል ይቅር! ሌላው ይቅር በሽታው::' ተጨነቀ::

ከአምባሳደር ትያትር እንደወጣ ታክሲ ተራ ሄዶ ቢገተርም ታክሲ አግኝቶ አውቶቡስ መሳፈሪያ ሲደርስ ሶስት ሰዓት አልፎ ነበር::

አልጋ ወደያዘበት ሆቴል የሚያጣፈው ቀጭን ኮረኮንች መንገድ ባይጠፋውም ቀን አቧራ ቅሞ ያየው ሰፈር በቀይ፣ በሰማያዊና በወይን ጠጅ አምፖሎች ወዝቶ፤ተብረቅርቆ ተጥለቅልቆ ሲጠብቀው አንዱን ሆቴል ከሌላው፤ ይህኛውን ቡና ቤት ከዚያኛው መለየት፣አቃተው:: ሁለት መጠጥ ቤቶች ገብቶ ከሞከረ በኋላ ፈልጎ እንደማያገኘው ሲረዳ ሥጋት ገባው::

“እባክህ ወንድም 'አበበች ሆቴል' እዚህ አካባቢ መሰሎኝ ነበር::” አለው በምሽቱ ከሚተራመሰው ጠጪ መሃል አንዱን አስቁሞ::

"አበበች? ያውልህ።" ብሎት አለፈ ሰውየው።
ከጀርባው ነበር ቤቱ። ዞሮ ገባ።

ግም! ግም! የሚለው ሙዚቃ ጠባቧን ክፍል ይነዝራታል። ቀን ያየውን ባልኮኒና መደርደሪያ ሲያይ ቤቱ የገባ ይመስል ሰውነቱ ዘና ሲል ተሰማው።

መቀመጫ ቦታ ይፈልግ ጀመር።ክፍሏ በጠጪዎች ተጨናንቃለች። መሃል ላይ ዳንሰኞች ይጋፋሉ...ይጓተታሉ። ወለሉ ከስር ይርገበገባል። መቀመጫ ቦታ ሲያጣ ወደ ባልኮኒው ጠጋ አለና ትከሻውን ሰያፍ አስገብቶ ክርኑን ባልኮኒው ላይ ተከለ።

"ምነው ጠፋህ?"

ፊቱን መልሶ ተመለከተ። ቀን ያየት ልጅ ነበረች። በቀኝ እጇ ሁለት የኮኛክ መለኪያዎች የተቀመጡበት ትሪ ይዛለች።

"ጠፋሁ እንዴ?" አለ ፈገግ ለማለት እየሞከረ።
"በ- -ጣም" ፈገግታ አስጎነጨችው። "ምን ልታዘዝ? ለምን እዚያጋ አትሆንም?" አለችው ድንገት ባዶ የተለቀቀ ቦታ እያመለከተችው።

ባልኮኒውን ተሰናብቶ ወዳመለከተችው ቦታ ሄዶ ተቀመጠ። ቦታው ማዕዘን ላይ ስለሆነ ተስማምቶታል። እዚያ ባልኮኒ ላይ ተንጠልጥሎ ግራ ነበር የገባው። በሕይወቱ መጠጥ ቤት ገብቶ መጠጥ የጠጣበት ጊዜ በቁጥር ነው። አንዴ ወይም ሁለቴ?...እንጃ እሱም። መጠጥ ቤት ሲገባ መድረክ ላይ እንደወጣ ተዋናይ ሰዎች ሁሉ እሱን የሚያዩ ነው የሚመስለው።

"ምን ይምጣልህ?" መጠጥ የፈሰሰበትን ጠረጴዛ እየወለወለች ጠየቀችው።

"ኮኛክ።" አላት ዙሪያው ያሉ አንድ ሁለት ጠረጴዛዎችን ካጠና በኋላ።
"ለኔስ?" ፈገግ ብላ ቁልቁል ተመለከተችው።

"አዎ - - አዎ ላንቺም።" ለራሱ ብቻ ማዘዙ ጥፋት ይመስል አሳፈረው። ወገቧን እየወዘወዘች ሄደች። ቀን በጣም ወፍራም ሆና ነበር የታየችው። እንጃ ምናልባት ለብሳው የነበረው ሰፊ ቀሚስ ይሆናል... ምናልባት ደግሞ መብራቱ ይሆናል... አሁን ደግሞ መካከለኛ ደልዳላ ሴት ትመስላለች። የተደበቀ ውበት ይኖራት ይሆን? ረጅም ነች!ሰውነቷም ሞላ ያለ ነው፤ አዎ ...



ያዘዛትን ኮኛክ በሁለት መለኪያዎች ይዛ ስትመለስ ሳይታወቀው አይኖቹ የሚውረገረግ ወገቧ ላይ አረፉ። ዕድሜዋም ቀን እንደገመተው አይደለችም... ቢበዛ ሃያ ሰባት አለዛም ሃያ ስምንት። ሲመለከታት ሞቅ ያላት ትመስላለች።

"እ- -ሺ." አለች መለኪያዎቹን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ ከፊት ለፊት ባለው ወንበር ላይ እየተቀመጠች "ስትቆይ ጊዜኮ ቀረህ ብዬ ነበር።"

"እ?" አለ የሙዚቃው ጩኸት ያለችውን አላሰማህ ቢለው።
"ቀረህ ብዬ ነበ- -ር።"
"እመጣለሁ ብዬሽ?"
"ምን ይታወቃል የምታጋጥምህ ቆንጆ። አዲስ አበባችን አትታመንም።" ተሽኮረመመች- የተጠና የተሸመደደ መሽኮርመም።
"ክፍል ይገኝ እንደሆነ እቀራለሁ፤ ባይሆን ያገኘኋትን ቆንጆ ይገፍላችሁ ከተፍ እላለሁ እንጂ።"

"አ! በነገራችን ላይ አልጋህ ተይዟል።"
"ተይዟል?" ምን ማለቷ እንደሆነ ሊገባው አልቻለም።
"ስትቆይ ጊዜ ቀረ ብለው እምቤቲቱ አከራዩት።" አለች 'አዝናለሁ' ከሚል አመለካከት ጋር።

"እንዴት?! ክፍሌ ሄደ?!" ፊቱ ሁሉ በንዴት ተለዋወጠ።
"አትቆጣ እንጂ። እኔጋ ታድራለህ ችግር የለም።"
"መጀመሪያ ነገር የያዝኩትን ክፍል ለምን..." የጀመረውን ሳይጨርስ ሰዓቱን ተመለከተ "ሌላ ክፍል የለም?"

"አ! አመሸህኮ አንተም... አሁን የት ይገኛል ብለህ ነው።" አለች ተስፋ በሚያስቆርጥ ድምፅ።

"ሌላ ቦታስ ብሞክር?" ለመነሳት እንዳሰበ ሁሉ ከተቀመጠበት ጎብደድ ብሎ ምክር ይጠይቅ ጀመር።

"አትልፋ።" ፈገግ ብላ አቋረጠችው። "በዚህ ሰዓት የትም አታገኝም። ማጅራት መቺውም አሰፍስፏል፤ ነገርኩህኮ ከፈለግህ እኔጋ ታድራለህ አልኩህ። የአልጋ አትከፍልም።" ተሽኮረመመች።

"ሄደን እንየው እንግዳው።" አለ ናትናኤል ግራ ሲገባው።
"ምኑን?" በተራዋ ግራ የገባት መሰለች።
"ቤትሽን ነዋ።"

“ምኑን ታየዋለህ? ቤት-ቤት፤ አልጋ-አልጋ!” ግራ በተጋባ ገጽ ቅንድቦቿን ግንባሯ ላይ አጠጋግታ ደርድራ ተመለከተችው።

“ድገሚኝ” አለ መለኪያውን አንስቶ ኮኛኩን ጭልጥ አደረገና።

ከመነሳቷ በፊት የራሷን መለኪያ ከእሱው ጋር አመሳሰለችው። የኮኛክ ጠርሙስ አምጥታ መለኪያዎቻቸውን ከሞላች በኋላ ጠርሙሱን ይዛ ተመለሰች። ሄድ መለስ ስትል ሞቅታዋ እየባሰባት እንደሄደ ለናትናኤል ታውቆታል።

“መጫወት ትፈልጋለህ?” አለችው ዳንስ አይሉት ግፊያ የያዙትን በመጠጥ ቤቷ መሃል ወለል ላይ የሚተራመሱትን ሰዎች ሲመለከት ስታይ።

“እ-እ” አለ ጭንቅላቱን ነቅንቆ።
ሳቅ አለች።
“ምነው ሳቅሽ?”
“አንድ ነገር ልንገርህ? በጣም የተለየህ ነህ። ለምን እዚህ እንደመጣህ ሊገባኝ አልቻለም።”
“እንዴት?”
“አየህ... ስራዬ ከብዙ ወንዶች ጋር ያገናኘኛል። ወንዶች ደግሞ እንደ ወረቀት ናችሁ። ፊቱን፣ አነጋገሩን፣ አካሄዱን ሌላም ሌላም አይቼ ስለአንድ ወንድ ብዙ መናገር እችላለሁ። አንተ ግን...” የታች ከንፈሯን ምጥጥ አደረገችና ዝም አለች።

“እኔ ግን ምን?”
“አንተ ግን... እንጃ ብቻ...” ጀምራ ተወችው።
“ግድ የለም ተናገሪ።” አለ ሳቅ ብሎ መለኪያውን አንስቶ ፉት አለለት።

“ምን ልበልህ... አንተና የመጣህበት ቦታ አልተጣጣማችሁም። ምናልባት ራሳቸውን ለመርሳት ከሚጥሩት ውስጥ ትሆናለህ።”

“እንዴት ናቸው እነሱ?” አላት ሳቅ ብሎ።

“እንዴት ልበልህ... ወይ ከሚስቱ ወይ ከአለቃው ይጣላና አለዚያም ከግዜሩ ይኳረፍና እልሁን ሊወጣ ሲባልግ ፕሮግራም አውጥቶ ይመጣል። ታዲያ እዚህ ከመጣ በኋላ የሚያየው ሁሉ ሌላ ዓለም ይሆንበትና... እንዴት ልበልህ... ፍዝዝ ይላል።”

“ፊዝዝኩ እንዴ? ”



“አለ አይደል።” ፈገግ አለች።
“ጥሩ ጭንቅላት ያለሽ ትመስያለሽ ካነጋገርሽ።”

“ሀ! ሀ! ሀ!” ከት ብላ ሳቀችበት። “አትገረም። ሥራዬ ስለሆነ ነው። እህ...የፈለገው ዓይነት ጭንትላት ይኑርህ ስለግብርና ከገበሬው በላይ ልታውቅ አትችልም። ስለወንዶች ምንነት ማወቅ ከፈለክ ደግሞ ሸርሙጥ። ... ያኔ ከለበሰው ንፁህ ሱፍና የፀዳ ክራባት በታች ወንድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትረዳለህ።”

“ለወንዶች ያንን ያህል ፍቅር ያለሽ አትመስይም።”

“ወንድ የምታፈቅር ሸርሙጣ የለችም። ሸርሙጣ ነኝ። ግን ደግሞ ወንድ ልጅ አለኝ። ተግባባን? የምወደው ትንሽ ወንድ ልጅ። የስምንት ዓመት ልጅ። እንደኔ አስቀያሚ ሆኖ እንዲያድግ አልፈልግም። ስለዚህ አስተምረዋለሁ፤ ስለምወደው። ግን ዋጋ የለውም።” እጆቿን ተስፋ በመቁረጥ ስሜት አወናጨፈቻቸው። “እሱም ሲያድግ ይሸረሙጣል።”

“ምን ማለትሽ ነው?... ከተማረና ራሱን ከቻለኮ ... ደግሞ ወንድ ልጅ ቡና ቤት ከፍቶ...?”

“ሂ! ሂ! ቡና ቤት ከፍቶ አይሸረሙጥም... ልክ ነህ። ግን አንተነትህ ነው ቁም ነገሩ።ቢሮም ተቀምጦ ይሸረሙጣል። ልንገርህ... ባለፈው ጊዜ ይሄንኑ አንድ ልጄን ትምህርት ቤት ላስመዘግብ ሄጄኩልህና ቦታ የለም ስላሉኝ ርዕሰ መምህሩን ላነጋግር ገባሁልህ። ምን አለኝ መሰለህ...የልጁ አስተማሪ፤ ለዛውም አያት የሚያክል ዳውላ- “የት ላግኝሽ?” “ለምን?” “ሻይ ልጋብዝሽ” ብቻ ስንቱን ላውራልህ። ካስተማሪው ጋር ሸርሙጬለት ልጄ ቦታ የለም በተባለበት ትምህርት ቤት ውስጥ ቦታ አግኝቶ ገባ። እናቱም ሸርሙጣ አስተማሪውም ሸርሙጣ። ቡና ቤት ከፍቶ መጠጥ ቸርችሮ ገንዘብ ተቀብሎህ አልጋ ውስጥ አብሮህ የምትገባ ብቻ መሰለችህ ሸርሙጣ? ቢሮ ተቀምጦ ጉቦ የሚጠባበቅም ሸርሙጣ ነው፤ ችሎታ ሳይሆን ዳሌና ሽንጥ፤ ባትና ጡት እያየ ጉዳይ የሚፈጽምም ሸርሙጣ ነው። ሁሉም። ብቻ የሚያበሳጨኝ ሸርሙጬ ሸርሙጣ መቀለቡ ነው።”

“የምን ሸርሙጣ ነው ደግሞ የምትቀልቢው?”
“ልጄን ነዋ።” መለኪያዋን አንስታ ተጎነጨችለት።
“ተይ እንደዛ አትበይ። የሚያድግ ልጅ የሚደርስበት አይታወቅም።”

“ትላንት እኛም የምናድግ ልጆች ነበርን። የትላንት አበባዎች የዛሬ ሸርሙጦች”አለች መለኪያዋን እየጋባች። “ልጨምር? ” አለች እየሳቀች።

"ጨምሪ::" ደጋግሞ ጠጣ ናትናኤል:: እሷም ደጋገመች፡

ከቡና ቤቱ ሲወጡ አምስት ሰዓት አልፎ ነበር:: ሰማዩ ምጥ ይዞት ይጨነቃል... ንፋሱ ማርያም ማርያም ይላል:: ተያይዘው ለመሄድ ተነሱ::

"ይሄ ዝናብ እንዳይቀድመን ፈጠን ፈጠን በል::" አለችው በኮረኮንቹ መንገድ ወደ ውስጥ እየገባች ወደቤቷ እየወሰደችው::

ብዙም ሳይሄዱ ዱብ ዱብ ያደርገው ጀመር::

"ሩቅ ነው እንዴ ቤትሽ?" አለ በጨቀየው ኮረኮንች መንገድ እየተወላከፈ እየተከተላት::

"ቅርብ ነው:: ደርሰናል::"
"ዝናቡኮ ሊዘንብ ነው::" አለ ከጎን ከጎኗ እያለ::
"ጥሩ ነው:: ያጸዳናል::" አለች እየሳቀች::
'ቅርብ ነው' ያለችው ቤቷ ሲደርሱ በዝናቡ ረስርሰው ነበር::

"ልብስህን አውልቅና ግባ እንጂ::" አለች ሰውነቷን ያደረቀችበትን ፎጣ ቁምሣጥን ውስጥ ወርውራ ብርድልብሱን እየገለጠችለት::

"ለምንድነው ግን የያዝኩትን ክፍል ለሌላ የሰጣችሁብኝ?"

"አሁን ምን ጎደለብኝ ልትል ነው?" አንሶላው ላይ ቁጭ ብላ፤ የውስጥ ሱሪዋን አውልቃ አልጋ ውስጥ ስትገባ አይኖቹን ፊት ለፊት ካለው ግድግዳ ጋር ጠፈራቸው::

"አይ ለነገሩ ነው:: ከከፈልኩ በኋላ ለምን...?"
"ስትቆይ ጊዜ ትቀራለህ ብለው ስድስት ብር ለማግኘት ነበር ያሰቡት እመቤቲቱ"
"እንዴት?"
"አንተ አንደ ከፍለህ ሄደሃል:: ስለዚህ ክፍሉን ለሌላ ቢያከራዩትና አንተ እንዳመሸህ ብትቀር ኖሮ ስድስት ብር ቤት ገባ ማለት ነበር:: ከመጣህም ያው ሶስት ብርህ ይመለስልሃል:: የደንቡ ሶስት ብር ግን አይታጣም:: ገባህ? "

"ስድስት ብር ልታገኚ ነበራ ያሰብሽው::"
"እኔ አይደለሁም:: የቤቱ እመቤት ናቸው:: ይልቅ ግባ አልጋ ውስጥ::" አለች በጀርባዋ ተንጋላ ሽቅብ እያየችው::



"መቼም ተመልሼ ስመጣ ሳትናደዱ አትቀሩም" አለ እንደ ማልጎምጎም::

"እኔ በበኩሌ አልተናደድኩም::"
"ለምን?"
"እዛው ክፍል ይዘህ ብናድር ኖሮ የማገኘውን አሥራ አምስት ብር ከመቤቲቱ ጋር ለሁለት ነበር የምካፈለው:: ያ ደግሞ ሰባት ከሃምሳ ነው አይደል? ከዛ ላይ ሃምሳ ሳንቲም ያንሰላ ይነሳለታል:: ሰባት ቀረ ማለት አይደል? እዚህ ይዤህ ከመጣሁ ግን አስራ ሁለቱ ቤት ገባች ማለት ነው:: ተግባባን?»

"እ"
"በል ግባ አልጋ ውስጥ:: ወሬ አበዛህ፤ ጋዜጠኛ ነህ መሰለኝ::" አለች ብርድ ልብሱን እየገለጠችለት::

"እይው ዘውዲቱ... ካንቺ ጋር ለመተኛት ብዬ አይደለም የመጣሁት::" ሰውነቱ ያልወደደውን ድርጊት መፈጸም አልፈለገም::

"ታዲያ ምን ልትፈጥር ነው?" ተገርማ ጠየቀችው::
"ማደሪያ ቦታ ስለፈለኩኝ ብቻ ነው::" አለ እንዳትቆጣ በለዘብታ::
"እንዴት?" ግራ ተጋባች::
"ምን መሰለሽ... በቃ የማድርበት ቦታ ስለሌለ ነው የመጣሁት::"
"እና? ያ ከዘውዲቱ ጋር እንዳትተኛ ይከለክልሃል? ተነጋግረን መሰለኝ የመጣነው!"
"እሰጥሻለሁ - - እሰጥሻለሁ:: አሥራ ሁለት ብሩን እሰጥሻለሁ::" የተቆጣች ሲመስለው ፈጠን ብሎ አባበላት::

"ለምንድነው የምትሰጠኝ እብረኸኝ ካልተኛህ?" ቀና ብላ አልጋዋ ላይ ተቀመጠች:: "ለማኝኮ አይደለሁም::" እነዛ ትላልቅ ጡቶቿ አፈጠጡበት:: "መጀመሪያ ለምን መጣህ አሁንስ?"

"ነገርኩሽኮ:: ስለመሸና አልጋ ስለማላገኝ:: አልጋዬን ለሌላ ሰው ባትሰጡብኝኮ ..."
"አሁንስ መች አልጋ አገኘህ? ወይስ ተነስቼ ግድግዳው ጋ ልቁምልህና ገብተህ ትተኛ? ማሙሽዬ::"

"ተነሽ አላልኩምኮ:: ደህና ነኝ:: ተመችቶኛል:: ባይሆን ለሰሞኑ በዋጋ ከተስማማን ቤቱን ታከራይኛለሽ::"

"እና አሁን እሱጋ ተከፍለህ ልታድር ማለት?" ሳቅ አፈናት። "ወይኔ ልጅት ስንት ዓይነት አለ ባካችሁ! ታቃለህ ባለፈው ወር አንዱ አብሮኝ እዚህ ድረስ መጥቶ አልጋ ቢነካው ጡቶቼ መሃል ገብቶ ሲያለቅስብኝ አደረ። ዛሬ ደግሞ ጌታው እግሬ ላይ ቀቀምጦ ሊያድር ነው።" ሳቋን ቀጠለች።

አብሯት ሳቀ።

"ብል የውስጥ ልብስ ከዛ ውስጥ አቀብለኝና ገብተህ ተኛ።አልነካህም።" አለች ሳቋን ሳታቋርጥ።

ናትናኤል የመኝታው ጉዳይ ጭንቀቱ ጋብ እያለለት ሄዷል። ከቁምሳጥኗ ውስጥ ሰማያዊ የውስጥ ልብስ አቀበላት። ብርድ ልብሱን ገልጣ የውስጥ ልብሷን በጭንቅላቷ ስታጠልቅ አይኖቹን ከራቁት ገላዋ ላይ ቶሎ አነሳቸው።

"እማምላክን አንተ ድንግል ነህ። በል መብራቱን አጥፋውና ና።" አለች ሳቋን ማቆም አቅቷት እየተንፈቀፈቀች።

መብራቱን አጥፍቶ አልጋ ውስጥ ሲገባና በጀርባው ሲተኛ ጠባብ ታጣፊ አልጋ ሳይፈልጉ ገላ ለገላ ስታነካካቸው ናትናኤል ተሸማቀቀ። ለምን እንደሆነ ባይረዳውም ልውነቱ ብርድ እንደገባው ሁሉ ሲቀዘቅዝ ተሰማው።ጎረምሳም ሆኖ ሞክሮት አያውቅ። ጓደኞቹ በየቡና ቤቱ ስለፈጸሙት ጀብዱ ሲያወሩ በጥያፌ ነበር የሚያዳምጣቸው። ቱፍ! ሰው እንዴት እንደዚያ ያለ ዕቃ በገንዘብ ይከራያል? ቱፍ! በንጽህና የተጠበቀና በነፃ የሚታደል አያለ! ቱፍ!

"አይዞህ አልባላም። ታውቃለህ...? ስለእናንተ ስለወንዶች መጽሐፍ ብፅፍ ሃብታም ነበር የምሆነው።" አለች ዘውዲቱ በጨለማው ውስጥ አግድም እየተመለከተችው።

"እንዴት?"

"አሃ! ስንቱን ዓይነት መሰለህ የማየው። ቀዩ፤ጥቁሩ፤ ተሳዳቢው፤አልቃሻው፤ ተደባዳቢው፤ሞልቃቃው። ያውልህ የቁም ሳጥኔን መስተዋት እንዲህ ያደረገልኝ እንዲያ ዓይነቱ ነው - - ጠርሙስ ሲወረውር ብቻ ወንድ የሚመስለው ህ! ዛሬ ደግሞ እቤቱ ድረስ ተከትሎኝ መጥቶ አልጋ አይነካኝም የሚል መጣ።በነገራችን ላይ ቀዩ ጥቁሩ ስል አስታወሰኝ። የአፍሪካ መሪዎች ለስኔ አልነበር እንዴ የሚሰበሰቡት?"



"ለመስከረም ተዛውሯል።" አላት ጨለማው ላይ አፍጥጦ። "ምነው ጠየቅሽኝ?" ጠየቃት። ለምን እንደጠየቀችው ማብሰልሰሉን ግን ወዲያው ተያየዘው።

"ንግድ ይጠፋል! እነሱ ሲመጡ። በል ደህና እደር።" አለችው በደረቷ እየተገለበጠች። "እናፍ... እነዚህ ትንኞች ደግሞ ዛሬ ተነስቶባቸዋል። ... ሸርሙጦች።"

-15-

ከምድር በታች ተቆፍሮ በተገነባውና ግድግዳና ጣሪያው ለፈንጂ ጥቃት እንዳይፈታ በብረት ወራጅና ማገር ተጠናክሮ በሲሚንቶ ደንድኖ በተሰራው በዋና ማዘገር ውስጥ ያለው መስኮት የለሽ የስብሰባ ክፍል በቁጣ ተሞልቷል። በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁለት ሰው ሰራሽ የአየር መሳቢያዎች አየር እየሳቡ ሲያስገቡ የሚያሰሙት- 'ስ...ስ' የሚል ቀጭን ድምፅ ለአንድ አፍታ ክፍሉን በዋጠው ፀጥታ ውስጥ ጎልቶ ወጣ።

የምሥራቅ አፍሪካ ቡድኑ-ለ የፀጥታ ክፍል ዘጠኝ ባለሥልጣናት በክፍሉ መሃል ለመሃል በተዘረጋው ጥቁር ሰፊ ጠረጴዛ ዙሪያ ከተደረደሩት አሥራ ስምንት ወንበሮች ግማሹን ይዘዋል። በትክክል ከየት እንደሚወጣ የማይታየው ክፍሉን የሞላው ብርሃን በእያንዳንዱ ባለሥልጣን ፊት ላይ የተጋገረውን ቁጣና የተንጠለጠለውን ጭንቀት ያሳጣል።

"ቀድሞውንም ያሰጋኝ ይኸው ነበር።" አለ ኬንያዊው ገርክ ዊልያም የአጥቂ ስለላ ኃላፊ ጥርሶቹን እንደገጠመ በጠረጴዛው ዙሪያ የተደረደሩትን የሥራ ባልደረቦቹን እየገረመመ።

"አሁንምኮ..." ኮሎኔል ማርቆስ ሁኔታውን ለማስረዳት ጀመረ።

"ይቅርታ!" አለ ገርክ ዊልያም አቋርጦት "ኮሎኔል የተሰጠህን ሃላፊነት በሥርዓት ለመወጣት እንዳቃተህ የተረዳሁ ይመስለኛል።"

"ለማለት የፈለኩት..."

"ስህተት ፈጽመሃል!" የኬንያው ሰው ድጋሚ አቋረጠው። የተሰማውን ንዴትና ጥላቻ ለመደበቅ ሳይሞክር፤ ደም የጎረሱ አይኖቹን ኮለኔል ማርቆስ ላይ ደግኖ "ይህን ስህተት ደግሞ በአፋጣኝ ልታርም ትችላለህ የሚል እምነት ፈጽሞ የለኝም።" አለ።

"ጥፋቱ የኔ ነው።" አለ ብርጋድየር ጀነራሉ ረጋ ባለ ድምፅ መሃል ገብቶ ሁኔታውን ለማብረድ እየሞከረ።

ማርቆስ ለአንድ አፍታ ባለሥልጣናቱን ተመለከተ። የሰዎቹ ብስጭትና ቁጣ የእርሱ የራሱ ማመንታት ውጤት መሆኑን ሲገነዘብና በእያንዳንዳቸው ገጽ ላይ የተሳለውን ጥላቻና ጥያቄ ሲያጤን አንገቱን ደፋ።

"በቅድሚያ ሰውየው እንዲወገድ ከተወሰነ በኋላ በጎን ውሳኔውን መቀየሩ በራሱ ግራ የሚያጋባ ይመስለኛል?" አለ የክትትል ሃላፊ የሆነው አንድ አይናው የሞርኮ ሰው በተሰባበረ እንግሊዝኛ። ያደረገውን ጥቁር መነጽር በአፍንጫው ላይ ወደላይ ገፋ አደረገና ቀጠለ... "ያም ስህተት ከተፈጸመ በኋላ" አለ አንድ አይኑን ከጀነራሉ ላይ አንስቶ በኮሎኔል ማርቆስ ላይ ተክሎ "የግድያ ውሳኔውን በክትትል ለመቀየር ከተፈለገ ክትትሉን ሊያደርግ የሚገባው የእኔ ክፍል መሆን ሲገባው ክትትሉን ሌሎች በፈቃዳቸው አድርገውት አሁን በመጨረሻ ሰውየው ከተሰወረ በኋላ ይህን ሪፖርት ማቅረብ ለእኔ ፍጹም አሳፋሪ ሆኖ ነው የማገኘው።"

"የግድያውን ውሳኔ ያዘገየሁትና ለጊዜው ክትትል ለመዘርጋት የወሰንኩት እኔው ነኝ። እዚህ ላይ ጥፋት መሆኑን እቀበላለሁ። ሆኖም..." አለ ብርጋዴር ጀነራሉ በተረጋጋ መንፈስ "ይህንን ውሳኔ የወሰንኩት በጊዜው የውጭ ጉዳዩ ሰው ያገኘ ቃህል አስቢ የሆነ መረጃ በእጁ አሳገባም የሚለው ግምት ስላየለና አስፈላጊ ያልሆነ ግድያ እንዳንፈጽም በሚል ነበር። ይህን ስል..."

"ይቅርታ አድርግልኝ እዚህ ላይ" አለ በተደጋጋሚ በመሃል እያቋረጠ የሚገባው ገርክ ዊልያም እልሁን መቆጣጠር እያቃተው "...በተደጋጋሚ አስፈላጊ ያልሆነ ግድያ እየተባለ የሚነሳው ነጥብ ለኔ ፍጹም ልቀበለው የምችል አይደለም። ፍራንዝ ፋነን እንዳለው በቅኝ ግዛት ሠንሠለት ለገባ ነፍስ ብቸኛ አማራጭ መንገዱ ሃይል ነው-እሳት! ጫካን ስትመነጥር ሰደድ ስትለቅበት በጥሻ ውስጥ ስለምትገኝ የጽጌረዳ ግንድ ልትጨነቅ አትችልም። እሳቱን ለኩሰው! ሰደዱን ልቀቀው! ይንደድ። ዱሩን ይብላው። የፈለግኸውን ሜዳ ታገኛለህ! በቃ! " አለ ከፊቱ ያለውን ጠረጴዛ በቡጢ መትቶ።

"ደህና። አሁን ጥፋቱን መላልሰን መላልሰን ብናነሳው ዋጋ ያለው አይመስለኝም።" አለ በፀጥታው ክፍል ሁለተኛ ሰው የሆነው ሩዋንዳዊው አንድሬ አማሪ "አሁን ልንመክርበት የሚገባ ነጥብ ስለሚቀጥለው እርምጃ ይመስለኛል።"



"ወኪልህ ምን የምታውቀው ነገር አለ ስለሰውየው መሰወር?" አለ አዲስ አበባ ከገባ ገና ሁለተኛ ወሩን የያዘው የግብጽ የመረጃ ሰው አይኖቹን ባሻገር በተቀመጠው ማርቆስ ላይ ተክሎ።

"እ... ለጊዜው ምንም ፍንጭ ለማግኘት አልቻለችም። 'እመለሳለሁ' ብሏት ነው ድንገት የተሰወረው።" ማርቆስ ራሱን ጠላ።

"እስካሁን ምን እርምጃ ወስደሃል?" አለ ያው ግብፃዊ መኮንን መልሶ።

"ከአዲስ አበባ መውጫ በሮችን በክትትል ሰዎች ሽፍነን እየተጠባበቅን ነው። ምናልባት ለመውጣት ከሞከረ በሚል በየአውሮኘላንና በባቡር ጣቢያዎችም በየአቅጣጫው የፎቶግራፍ ምስሎቹን በትነናል።"

ውይይቱ በተከታታይ ለሦስት ሰዓት ቢቆይም ባለሥልጣናቱ ከክፍሉ ሲወጡ ፍጹም ይቅርታ እንዳላደረጉለት ኮሎኔል ማርቆስ ከፊታቸው ላይ ከሚነበበው ቁጣ ተረዳው። ብርጋዴር ጀነራሉ ቀድሞ ከክፍሉ ሲወጣ "ቢሮዬ እፈልግሃለሁ።" ስላለው የተቀሩት ወጥተው እስኪያበቁ በተጠንቀቅ ጠበቀና ከክፍሉ ወጥቶ ወደ አለቃው ቢሮ አመራ።

"ቁጭ በል" አለው ጀነራሉ ከመደርደሪያው ላይ የውስኪ ጠርሙስ አንስቶ በሁለት ብርጭቆዎች ቀድቶ አንዱን እያቀበለው። "ጠጣው ይጠቅምሃል።" አለ ፈገግ ብሎ ማርቆስ በተቀመጠበት ቁልቁል እየተመለከተው።

"ጥፋቱ የኔ ነው።" አለ ማርቆስ ግንባሩን እያሻሸ።
"ዋናው ነገር ከዚህ መማር ያለብንን በአንክሮ ማስተዋል ነው።"
ማርቆስ ምንም ሳይናገር ያጋባውን የውስኪ ብርጭቆ ከጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ቀና አለ።

"ማርቆስ፤ በአሁኑ ሰዓት ናትናኤል እራሱን የት እንደደበቀ የሚያውቅ ሰው ካለ ጋዜጠኛዋ ትመስለኛለች።" አለ አለቅየው አይኖቹን አጥብቦ።

"የምታውቅ አይመስለኝም።" አለ ማርቆስ እራሱን በመዳፉ ላይ አስደግፎ።

"ታውቃለች! እርግጠኛ ነኝ ማታ ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኘው ከእርሷ ጋር ነው። ማወቅ አለባት።" አለ ጀኔራሉ ድንገት ትዕግሥቱ

እንዳለቀበት ሁሉ በስጨት ብሎ። "አስታውስ ካልቨርትን ከአይናችን ስር የሰወረችው ያች ሽርሙጣ ነች... ማርቆስ ሴቶችን ፍጹም አትመን!"

"እሺ ...ግን... ምን ማድረግ እንችላለን?"

"መርምራት!" አለ አለቅየው ግልፍ ብሎት "ይዘህ መርምራት!"

"ካላወቀችስ?"

"ታውቃለች! ይቺን ያህል አልጠራጠርም።" አለ ጀነራሉ የሁለት ጣቶቹን ጥፍር እያፋጨ።

"ለመናገር ፈቃደኛ ባትሆንስ?"

ድንገድ የአለቅየው አይኖች በቁጣ ፈጠጡ። ወደፊት ጠረጴዛው ላይ ተደፋና አይኖቹን ማርቆስ ላይ አፈጠጠ-

"ሁለት እግሮቿን ይዘህ ሁለት ቦታ ሰንጥቃት። ያን ጊዜ ፈቃደኛ ትሆናለች።"

ማርቆስ ተነስቶ ከክፍሉ ወጣ።

## -16-

ወር!

ከዚህ በላይ ምን ያህል ታግሳ መቆየት እንዳለባት ለራሷም አልገባሽ ነው ያላት። 'ታገሺ' ይሏታል አሁንም 'ታገሺ ይገኛል' ይሏታል። መቼ ነው የሚገኘው? እስከ መቼ ነው የምትታገሰው?

ለስሙ ጠዋት ከመኝታዋ ተነስታ መብላት አይበለው ቁርሷን ቀማምሳ ወደ ቢሮዋ ትሄዳለች። ስራ መስራት ካቆመች ግን ሰንበታለች። የግብር ደውጣ ከየጋዜጣውና መጽሄቱ የሰበሰበችው ቅራቅንቦ ትላንት ማታ በሬዲዮ ፕሮግራሟ ሲተላለፍ ለራሷ እስከዘገንናት ድረስ መነሻና መድረሻ የሌለው እና ቢሉት ቡን የሚል ፍሩሽካ ነበር።

የቀኑ የሥራ ሰዓት ሊገባደድ ሰላሳ ደቂቃዎች ቢቀሩትም ቢሮዋ ውስጥ ተጎልታ መቆየቷን ትርጉም ስታጣበት ከተቀመጠችበት ተነስታ የቢሮዋን በር ከውጭ ቆልፋ በጠባቡ መተላለፊያ ወደ ጓደኛዋ ወደ ምህረት ቢሮ አመራች።

"ሀይ ርብቃ።" አለች ምህረት ከፊት ለፊቷ ከተቆለለው ወረቀት መሃል ቀና ብላ።

"አልደወለም?"

ምህረት በዝምታ ራሷን ነቀነቀች...'አልደወለም'



ምህረት ከተቀመጠችበት ተነስታ ጠረጴዛዋን ዞራ ወደ ርብቃ ሄደችና በሁለት እጆቿ የጓደኛዋን ሁለት ክንዶች ግጥም አድርጋ አይን አይኗን ትመለከታት ጀመር-

"ርብቃ ለምን አትነግሪኝም ምንድነው የሆናችሁት? ሳንቺም'ኮ የሚቀልሽ ብትናገሪው ነው።"

"ምህረት ነገርኩሽኮ...ልነግርሽ የምችለው ነገር አይደለም።"

"እና ብቻሽን ብታኝኪው ነው የሚሻለው?" ክንዶቿን እንደያዘች ነቀነቀቻት።

ርብቃ ክንዶቿን አስለቀቀችና ጥግ ካለ ፎቴ ወንበር ላይ ወደቀች።

'ሰው እንዴት ብን ብሎ ይጠፋል?' ካንዴም ሁለት፣ ሦስት፣አራቴ ቤቱ ሄዳ ሞክራለች። መሥሪያ ቤቱ ብትደውልም ፀሃፊው ከአለቃው ፈቃድ እንደተቀበለ ነው የነገረቻት። ያን ያህል የማይቀርቡት ጓደኞቹጋ ሁሉ እየደወለች ናትናኤል ብትልም ልታገኘው ቀርቶ ፍንጭ እንኳን ልታገኝ አልቻለችም።

'በጤናው አይደለም። አንድ ነገር አድርገውታል።' ርብቃ በሃሳብ ተዋጠች። 'ግን ምን አደረጉና?'

"ግን ብቻሽን እንዲህ ከምትሆኚ ብትናገሪውና ቢወጣልሽ ጥሩ ነበር። ወይ መፍትሄው ቀላል ይሆን ይሆናል። ሰው'ኮ ችግሩን አውጥቶ ሲያማክር" ምህረት ጓደኛዋ ጎን ተቀምጣ በተቻላት ወተወተች።

'በጤናው ቢሆን እንዴት እንዲህ የገባበት ይጠፋል? እደውላለሁ ብሎ እንዴት እንዲህ ድምፁ ይጠፋል? ለትንሽ ቀን ነው ብሎ እንዴት በወጣበት ይቀራል?ዋሽቷታል። እሷ መጀመሪያውኑ ሆዷ ፈርቷል፣ ያኔውኑ ጠርጥራለች። አንድ ነገር ፈጽሟል። እና ምን ሊሆን ነው ታዲያ? አገር ጥሎ ሊጠፋ?' ርብቃ ድንገት ሰውነቷ ተሸማቀቀባት። 'ነብሬልዬ! አገር ጥሎ ቢጠፋስ? ለዚህ ይሆን እንዴ ያንን ገንዘብ የያዘው? ወይኔ በነገረችው ኖሮ ሁሉንም። እሱን ለመጉዳት አስባ እንዳልሆነ ግልጽ አድርጋ በነገረችው፣ባስጠነቀቀችው ኖሮ'

"ይልቅ በኋላ ራስሽን ከምትጎጂ ነግረሽኝ አብረን እንመካከር። ደግሞ ምንም ቢሆን እህቱ ነኝ። ካጠፋም እቆጣዋለሁ። አንቺም ከሆንሽ ያጠፋሽው እግሩ ላይ ወድቄ እለምነዋለሁ።መቼም ሊላው ቢቀር ለዚህ አላንስም።"

'ትቶኝ ሄዷል ማለት ነው። መቼም በአገር እያለ ጨክኖ ወር ሙሉ ዝም አይለኝም። ሄዷል።ጠፍቷል። ጨክኖ ከነልጁ ትቶኝ ሄዷል። ግን ለምን አታለለኝ? እኔስ አላታለልኩትም? አላጠመድኩትም? ግን ቢሆንስ

ለልጁ እንኳን እንዴት አይራራም? መች ነገርኩትና?! የእኔው የራሴ ነው ጥፋቱ፡፡ እንዳረገዝኩ እንኳን ሳላውቀምኩ፡፡ ልጅ እንዳለው እንኳን ልነገርኩትምኩ፡፡'

"አረ በናትሽ! ወይኔ እማዬ! ርብቃ ምን መሆንሽ ነው? እታልቅሽ እንጂ፡፡ ርብቅዬ ምን መሆንሽ ነው? ቀይ እንጅ ... የት ነው የምትሄጅው? ርብቃ! ራስሽን ነውኮ የምትጎጅው፡፡ እይው ፊትሽን ምን እንዳስመሰልሽው፡፡ በቃ- -በቃ ርብቃ - -ቀይ ቁጭ በይና እናውራ፡፡ የት ነው የምትሄጅው ቀይ!"

"ልቀቂኝ!"
"አልለቅሽም ርብቃ!"
"ልቀቂኝ ማለት ልቀቂኝ ነው፡፡" አለች ርብቃ መሃረብ በያዘችበት ቀኝ እጇ ግራ ክንዷን ለማስለቀቅ እየታገለች፡፡

"ርብቃ እሳመምሽኝ እጄን!"
"ልቀቂኝ፡፡"
"አልለቅሽም ንገሪኝ፡፡"
"ምንድነው የምነግርሽ?"

"ርብቃ ረጋ በይ፡፡ ጓደኛሽ ነኝኮ፡፡ ደግሞ ይሄ በሁላችንም ላይ የሚደርስ ነው፡፡ ያ ከፍታና እንዲያ ያደረገኝ ጊዜ አንቺ አልነበርሽም 'ደግሞ ለወንድ' ስትይኝ የነበርሽው? ርብቃ አይዞሽ እሱ ቢቀር ሌላ ይመጣል፡፡"

"አልፈልግም ሌላ፡፡ ምህረት ልቀቂኝ፡፡"

"እርጉዝ ነሽ፡፡ አይደል? ለዚህ ነው አይደል?" በድንነት የያዘቻቸውን የርብቃን እጆች ለቀቀቻቸው፡፡

ለአንድ አፍታ ርብቃ አደብ የገዛች መሰለች፡፡
"እንዴት አወቅሽ?"

"እኔምኮ ሴት ነኝ- ርብቃ፡፡ ደግሞ በደንብ ነው የምታስታውቂው፡፡ አንቺ መደበቅ ስለፈለግሽ ሁሉም ያላወቀ ለመምሰል እየሞከረ ነው እንጅ በደንብ ነው የምታስታውቂው፡፡ባይገርምሽ እመቤትም እንደ ቀልድ አድርጋ አንስታብኝ ነበር፤ችላ አልኳት፡፡"

"ይሄን ያህል አስታውቃለሁ ማለት ነው?"
"ርብቃ ላንቺ እንደሆነ እንጃ ይሄ በግልጽ የሚታይ ነውኮ፡፡"
"ግን ገና ነኝኮ ማለቴ ገና ስድስተኛ ወር...?"



"ርብቃ ስድስት ወር ማነሱ ነው? ቁመት ስላለሽ ነው እንጅ ይሄኔ... ብቻ ዋናው ነገር የሚያሳስብሽ ነገር የለም፡፡ ምናልባት የመጀመሪያሽ ስለሆነ ይሆናል፡፡ የወንዶችን ፀባይ እስካሁን ካልተረዳሽው ደግሞ በጣም የዋህ ነሽ ማለት ነው፡፡ ገደል ይግባ፡፡ ይሂድ፡፡ ይልቅ ጊዜው ሳይሄድ ማለቴ ሰው እንዳያውቅ ከፈለግሽ ዘመድጋ ራቅ ብለሽ መውለድ ነው፡፡ አየሽ... ቀደም ብትይ ያለችግር ያወጡልሽ ነበር፡፡ አሁን ግን ጠነከረ፡፡"

"ምህረት እንደሱ አይደለም፡፡ አልገባሽም፡፡"

"ርብቃ ለማስወጣት እንዳትሞክሪ፡፡ አደገኛ ነው በዚህ ጊዜ፡፡ ልጁ ይወለድና የሚያሳድጉ ሰዎች አይጠፉም፡፡ ብቻ ሁሉን ለኔ ተይው፡፡ የምትቆይበት ቦታ ከሆነም ችግሩ እህቴጋ ባህር ዳር ትሄጃለሽ እንጂ ለማስወጣት እንዳትሞክሪ፡፡ ሄለን የወባ መከላከያ ወስዳ ምን እንደሆነች ታስታውሺ የለ? ለዛውም የሦስት ወር፡፡"

"አልፈልግም - አልፈልግም፡፡"

"ርብቃ ብቻ አጉል ነገር እንዳትሞክሪ፡፡ ከአሁን ወዲያ በምንም አታወጪውም፡፡ ሕይወትሽን ከማጥፋት በቀር የምትጨምሪው ነገር የለም፡፡"

"ምህረት ተይኝ፤ ሕይወቴንም አልፈልገውም፡፡"
"ርብቃ አበድሽ እንዴ!"
"አዎ!"
ርብቃ ከጓደኛዋ ቢሮ ወጥታ በጠባቡ መተላለፊያ ተሻግራ ወደ ውጭ ስትወጣ ጭንቅላቷ እንደ ወፍጮ ከበዳት፡፡ አይኖቿ የማታዋን ፀሃይ ጨረር መቋቋም ሲያቅታቸው ጨፈነቻቸውና ለአፍታ ቆም አለች፡፡'ለማነው ሃጢያቷን መናዘዝ የምትችለው?'

ሰውነቷ እንደተረጋጋላት ከግቢው ወጥታ ታክሲ ይዛ ወደ አፖርታማዋ አመራች፡፡ የአፖርታማዋን የአጥር በር አልፋ ወደ ዋናው የሕንፃ መዝጊያ ስትደርስ - -

"እንደምን ዋልሽ ርብቅዬ!" ሲሏት ሰማች፡፡ ቀና አለች፡፡
ምድር ቤት፤ ባለግሮሰሪዋ እሟጊት ነበሩ፡፡
"እንደምን ዋሉ፡፡" አለቻቸው በተቻላት ፈገግ ለማለት እየሞከረች፤ እንዳይከፉ፡፡
"ትኩስ እንቁላል - አለኝ ርብቅዬ፤ አትፈልጊም?" አሏት ጮክ ብለው፡፡

"ነገ::" ብላቸው ደረጃዎቹን መውጣት ጀመረች:: አሁን ምንም አላሰኛትም:: የአንደኛውን ደርብ ደረጃዎች ጨረሳ ወደ ክፍሏ እጥፍ ስትል በአንደኛ ፎቅ ላይ ያሉ ተከራዮች በጋራ ምግብ ከሚያበስሉባቸው ክፍሎች ከአንደኛው የመጣ የምግብ ሽታ አወዳት:: ሆዷ ተገለባበጠባት:: ምሳ አልበላችም፤ ቁርስም እንደነገሩ ነበር የቀማመሰችው:: የተሰማት ግን የረሃብ ስሜት አልነበረም:: እንደው እርብሽ አለባት - ሆዷ::

ወደ ክፍሏ ገባችና በሩን ቶሎ ዘጋችው ቦርሳዋን ከአንደኛው ፎቴ ላይ ጣል አደረገችና ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች:: እንደምንም አልጋዋ ደርሳ ዘፍ አለችበት:: ጭንቅላቷን ይወቃት፤ ያበራያት፤ ያነፍሳት ጀመር:: ያ ብሽቅ ራስ ምታት ሊጀምራት ነው:: ማጅራቷን ጭምድድ አድርጎ ሲይዛት ተሰማት:: ኮሜዲኖዋን ከፈተችና መድሃኒቶች ከምታስቀምጥበት ካርቶን ውስጥ አስፕሮ አውጥታ ያለ ውሃ በምራቋ አባብላ ዋጠችው:: ውጭው እየጨለመ ቢመጣም በአልጋዋ ላይ እንደተንጋለለች ቆየች::

'ወይ ናትናኤል! ሳይነግራት ሲሄድ ሆዱ እንዴት እሺ አለው? ጠርጥሯት ይሆን እንዴ? የስራችውን ተንኮል ደርሶበት የተበተበችውን መረብ ተረድቶ ጠልቷት ይሆን እንዴ? የእሱን ልጅ ተሸክማ እንደቀረች ባወቀ! የራሷ ጥፋት ነው:: ትዉልደዋለች:: ዲቃላ! የናትናኤል ዲቃላ! ሆዷን ዳበሰችው ምነው ሁሉን ቀድማ በነገረችው ኖሮ:: ለምን አልጠረጠረችም? ገንዘብ እንድታመጣለት ሲጨይቃት ለምን አልገባትም? ጥሏት አገር ትቶ እንደሚጠፋ ለምን አልገመተችም? ግድ የለም::' የእልህ እንባ አይኖቿን እየለበለበ ሲወርድ የታች ከንፈሯን ነክሳ ያዘችው::

'ብትነግረው ኖሮ ትቷት አይሄድም ነበር:: ይቅርታ ብትጠይቀው ለምን እንዲያ እንዳደረገች ከመጀመሪያው ዘርዝራ ብትነግረውና እንዳይፈራ አረጋግታ ብታስረዳው ኖሮ እዚህ ውስጥ ባልገባም ነበር:: ጥፋቱ የራሷ ነው:: ሌላው ቢቀር ሳረገዘችው ልጁ ሲል ይምራት ነበር::'

ጭንቅላቷ ፍርስ ልበል አላት:: ሌላ አስፕሮ መውሰድ አሰበች:: ግን በባዶ ሆዷ አሁንም አሁንም አስፕሮ ሊጎዳው ይችላል ልጇን:: ኤጭ! ደግሞ ለዲቃላ! ከተንጋለለችበት ቀና አለችና ከጎኗ ያለውን ኮመዲኖ ከፍታ የመድሃኒት ካርቶኑን ጎተተችው:: ካርቶኑ ከእጇ አምልጦ ወደቀ:: ከውስጥ የነበረው የመድሃኒት ቁልል ወለሉ ላይ ተዘረገፈ - - ብጫና ቀይ- ቫይናክ፤ ምሥር -የወሊድ መከላከያ፤ ነጫጭ እንክብሎች-የወባ መከላከያ...

ድንገት የጓደኛዋ የምህረት ምክር ታወሳት -

"ለማስወጣት እንዳትሞክሪ... ሄለን የወባ መከላከያ ወስዳ ምን እንደሆነች ታስታውሽ የለ...?"



'ገደል ይግባ! ሁሉም ነገር ገደል ይግባ! መኖርም አትፈልግ! ደግሞ ለዲቃላ!' ከተበተኑት መድሃኒቶች መሃል ለይታ አነሳችው የወባ መከላከያ መድሃኒት... 'አደገኛ ነው'... ግድ የላትም! ለምኑ? ለናትናኤል ዲቃላ?! ሰባት ነጫጭ እንክብሎች... ዲቃላ... ዞር ብላ ወደ ጠረጴዛዋ ሄደች... የናቷ... አንድ ብርጭቆ አንስታ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባችና ግማሽ ድረስ ውሃ ሞልታው ተመለሰች... የናትናኤል ዲቃላ ... ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና በግራ መዳፏ ውስጥ የጨበጠቻቸውን እፍኝ ሙሉ እንክብሎች ውሃ በያዘው ብርጭቆ ውስጥ ጨመረቻቸው '...ይሟሙ... ይፍረሱ... ከዛ ትጠጣዋለች... ከዚያ በኋላ ለቅሶ የለም... መቃጠል፤ መንደድ፤ መንገብገብ የለም::'

ለአንድ አፍታ በስሱ መጋረጃዋ ውስጥ የምሽቷ ጨረቃ ታየቻት:: ግማሽ ጨረቃ፤ ጎደሎ ጨረቃ ግን ብሩህ ጨረቃ:: ወደ መስኮቷ ጠጋ አለችና መጋረጃውን ወደጎን ሰብስብ አድርጋ ተመለከተች:: ብቸኛ ጨረቃ... ሰባራ ጨረቃ... ዲቃላ...

ድንገት አይኗ ወደጎን ተወናጨፈ:: ከሆስቴሉ አጥር ውጭ ተመለከተች:: እንባ የሞላቸውን አይኖቿን በእጇ ሞገቀቻቸውና ድጋሚ ተመለከተች:: እነዛው የምታውቃቸው ሞለል ያሉ ብጫ መብራቶች:: ጥር ባለው መንገድ መኪናዋ ቀልቀል መጥታ ከአፖርታማው በር ልትደርስ ትንሽ ሲቀራት ጥግ ይዛ ቆመች:: መብራቶቿ ሲጠፉ የጎን በሩ ተከፈተና አንድ ሰው ወረደ:: በጨረቃዋ ብርሃን ውስጥ ረጅም ቁመናው ታየት:: የመኝታ ቤቷ መብራት ስላልበራ ከውጭ እንደማትታይ በመገመት ባለችበት ቆማ ቀረች::

ከመኪናዋ የወረደው ሰው ወደ አፖርታማው የአጥር በር ተጠጋና ከሽማግሌው በረኛ ጋር ያወራ ጀመር:: ምንድነው የሚፈልገው? ደግሞ ቤቷ ድረስ ለምን መጣ? ሰውየው የሚጨቃጨቅ ይመስላል:: ከዘበኛው ጋር 'ልግባ' 'አትገባም' ይመስላል::

ወዲያው ሽማግሌው ዘበኛ በሩን ከፍተው ወጡና ከረጅሙ ሰውዬ ጋር ተከታትለው ወደ መኪናዋ አመሩ:: መኪናዋጋ እንደደረሱ ሰውየው ወደኋላ ቀረት አለና ከጀርባ ሽማግሌውን ዘበኛ ማጅራታቸውን ቢላቸው ደቃቃው ሽማግሌ በያዙት ረጅም ዱላ ላይ ተንሸራተው ከመሬቱ ላይ ተዘረጉ::

ርብቃ በድንጋጤ ደርቃ ቀረች:: እጆቿን አፏ ላይ ጭና በጎደሎዋ ጨረቃ ስስ ብርሃን በሚታየት ደብዛዛ ትርዒት ላይ አይኖቿን አፈጠጠች::

ሰውየው በፍጥነት ፊቱን መልሶ ወደ አፖርታማው የአጥር በር ሮጥ አለ:: የብረቱን በር ገፋ አድርጎ ገባ:: ለአንድ አፍታ ቆም ያለ መሰላት:: ወዲያው ፈጠን ብሎ ወደ አፖርታማው የፊት በር አመራ::

'ምንድነው የሚፈልገው?' ጭንቅላቷ 'ገው! ገው! አለባት፤ አቅለሸለሻት፤ ሊያዞራት ፈለገ። ጠረጴዛውን ደገፍ ብላ ቆመች። የእግር ኮቴ ድምጽ የሰማች መሰላት። የበር ድምጽ ተሰማት። የሚከፈት የበር ድምፅ 'በሯን ... የክፍሏን የፊት መዝጊያ አልቆለፈችውም እንዴ?' ከሆዷ ያለው ሽቀብ ይተናነቃት ጀመር። የመኝታ ቤቷ በር እጀታ ወደታች ሲዘም... በሩ... በቀጭኑ ሲ...ጥጥ ሲል ተሰማት። አይኖቿን አፍጥጣ በሩ ላይ ተከለችው። 'ቆልፈው የለም እንዴ በሯን? ታዲያ... እንዴት ተከፈተ... በሩ?'

-17-

"እና ደግሞ ጭራ"
"የምን ጭራ? "
"ጭራ ነዋ፤ የዝንብ ማባረሪያ ጭራ።"
"ደግሞ ጭራ ምን ይሰራልሃል?"
"ነገርኩሽኮ፤ ቄስ መምሰል ነው የምፈልገው።"

ወር ሆነው ዘውዲቱ ቤት ዘግቶ ከተቀመጠ። ድንገት ሲሰወር ደብዛው ሲጠፋ አውሬው እየገነሬ በየስርቻው እንደሚያነፈንፍ ገምቷል። ቢሆንም አንድ ቦታ አድብቶ ጊዜ እስከወሰደ ድረስ መልሰው ጭራውን ለመያዝ ይቸገራሉ። በዛ ጊዜ ውስጥ እሱም ራሱን ለመቀየር ጊዜ ያገኛል።

ከዘውዲቱ ጋር በሂሳብ ተስማምተው እዛው ሰነበተ። አብሯት የሚያድር ደንበኛ ያገኘች ሌሊት እፎይ ብሎ እንዴ በጀርባው እንዴ በደረቱ እየተገላበጠ ደልቶት እየተኛ... ያልቀናት ሌሊት ደግሞ የማታ ማታ እየተጎተተች መጥታ በዛችው ጠባብ ታጣፊ አልጋ ላይ እየተጋፉ ወር አለፈ፤ እንደምንም።

ጉና ቤቷን በተከራየ በአራተኛው ቀን ነበር አኳኋኑ ስላስቸል ብሏት የጠየቀችው። የጠበቀው ጥያቄ ነበር፤ መምጣቱ አላስደነገጠውም፤ አላስበረገገውም። ተዘጋጅቷል፤ ምን እንደሚመልስላት ያውቅ ነበር።

"ጺምህን ለምን አትላጨውም? ደግሞ ለምን ወጣ አትልም? ከጠዋት ጀምረህ እስከ ማታ በር ዘግተህ ምንድነው? የጤና ነው?" አለችው ጠዋት ከደንበኛ ጋር አድራ አረፋፍዳ ስትመጣ ከቤት ስታገኘው።

"እም።" አላት ነገሩን በአጭሩ ለመቅጨት።



"ምን ማለት ነው 'እም?'" አለች የምታብጥረውን ፀጉሯን ለቃ ቁልቁል በተቀመጠበት እየተመለከተችው።

"አዎ ነዋ።" አለ ደበልጥ ገፍታ እስኪትመጣ ወጥሬ እስኪትይበው።

ሁኔታው እንዳላማረት በግልጽ ታስታውቃለች። ቀሚሷን በጭንቅላቷ አውልቃ አልጋው ላይ ወርወር አደረገችውና ከፊት ለፊቷ ያለውን ቁም ሳጥን ከፈተች።

"እየው ወንድም" አለች ከቁም ሳጥኑ ውስጥ የተሰቀለ ልብስ ማውረዷን ሳታቋርጥ ፊቷን ወደሱ መልሳ። «እየው ወንድም ብሬ እስካልተቋረጠ ድረስ ዓመትም ተዘግተህ ብትቆይ ግድ የለኝም። ግን ደግሞ ችግር አልፈልግም። ከፖሊስ ነው የተደበቅከው አይደል?"

"ምን ማለትሽ ነው? እንዴት ከፖሊስ?"ደነገጠ።

"ተው ባክህ... " አለች ከቁመሳጥኗ ያወረደችውን ቀሚስ እየጠለቀች። "አሁን ማን ይሙት ዓለም በቃኝ ብለህ እኔ ጎጆ ውስጥ ሱባዔ የገባኸው ለነፍስህ ነው?"

የሚለው ጠፍቶት ዝም ብሎ ተመለከታት።
"ሰርቀህ ነው፤ አይደል? ሰርቀህ ነው የተደበቅኸው?"
"አይደለም... አይደለም።" አለ ፈጠን ብሎ። ለፖሊስ እንዳታሳጣው ሰጋ።

"ታዲያ ምንድነው? ወይስ ፍቅር ያዘህ ከኔ!" አለች ድንገት ስቃ። "እየው እኔ ግድ የለኝም። ሌባ ቀርቶ የፈለከውን መሆን ትችላለህ። ግን ልምከርህ። ከፖሊስ ከሆነ የተደበቅኸው እዚህ ተከተህ አታመልጣቸውም። አንድ ቀን ወጣ ያልክ ቀን ጋማህን ያብቱሃል። ራቅ ብለህ ሂድ። ድሬድዋ ወይ ጅማ፤ እንደገንዘቡ እንደሰረቅኸው ገንዘብ ብዛት።"

"ሰርቄ አይደለም ዘውዲቱ።" ከተቀመጠበት አልጋ ላይ ተነስቶ በጠባቧ ክፍል ጉርደድ ማለት ያዘ።

"ታዲያ እኔ ቤት ውስጥ እናትህን ቀብረሃል? " አይኖቿ አብረው እየተንጎራደዱ ወገቧን ይዛ ጠየቀችው።

ጊዜው እንደሚደርስ ቀድሞውኑም ገብቶታል። እንደምትጠይቀው ወጥራ እንደመትይዘው ገብቶታል።የሚያሳምን ምክንያት መስጠት

እንዳለበትም ተረድቷል:: አለበለዚያ ለሳምንታት ቤቷ ውስጥ ተደብቆ ሊቆይ አይችልም:: በአጭሩ 'የቤትሽን ኪራይ እስካቋረጥኩ ድረስ...አያገባሽም::' ብሎ ዝም ሊያሰኛት ይችላል:: ግን ደግሞ ልትፈራ ትችላለች! ወንጀል ፈጽሞ ከቤቷ የተሸሸገ ሊመስላት ይችላል:: "ውጣ!" ብትለውስ? ፖሊስ ይዛ ከተፍ ብትልስ?ለዚህ ነው ቀደም ብሎ የሚላትን ያዘጋጀው:: ሊያስደነግጣት አይገባም:: ግን ደግሞ ልታዝንለት ይገባል:: ችግሩን ተረድታ ልትረዳው ፈቃደኛ መሆን አለባት:: ቀስ ብሎ ማግባባት አለበት::

"ምን መሰለሽ ዘውድዬ... " አለ ቀረብ ብሎ ግራ ክንዷን ያዝ አደረገና:: "ግን አደራ..."

"አ...ይ ይሄን ያህል የሚያስጨንቅህ ከሆነ አትንገረኝ:: ምን መሰለህ ከብዬ... በሠላም መኖር ስለምፈልግ ብቻ ነው:: ገላዬን ሸጬ የኖርኩት አንሶኝ 'ተባበርሽ...ምንትስዬ ተብዬ ዘብጥያ መውረድ አልፈለግም:: ይገባሃል አይደል?ልጅ አለኝ:: የምወደው የምቀልበው ወንድ ልጅ::ነገ የሚሸረሙጥ..." ፈገግ አለች::

ልታስከፋው እንዳልፈለገች ከሁኔታዋ ያስታውቃል::ባለፉት ቀናቶች ሳይታወቃቸው በመሃላቸው የመግባባት ስሜት ተፈጥሯል::ስሙን ስትጠይቀው 'ከበደ' ብሎ እንደዋሻት ብትረዳም አላስጨነቀችውም፤ ሲቃ ተወችው::ተከትለዋት እቤቷ ድረስ መጥተው ተጨማልቀው አጨማልቀዋት ሳንቲም ወርውረውላት እንደሚሄዱ ደንበኞቿ እንዳልሆነ ግን ተረድታዋለች:: የመጀመሪያው ማታ 'አብሬሽ አልተኛም' ሲላት ለይስሙላ ነበር የመሰላት:: ኢጋጥመዋታላ! የጓዛ ገንዘባቸውን ከፍለው መጥተው ተለማመጡን የሚሉ፤ ካላንቀለጳጳሳችሁን የሚሉ፤ "ያው የገዛችሁት ዕቃ" ሲባሉ የሚግደረደሩ::

ያን ቀን ማታ 'በል የውስጥ ልብሴን አቀብለኝ' ብላው ያለችውን አቀብሏት መብራቱን አጥፍቶ ከጎኗ አልጋው ውስጥ ሲገባ ይዘግይ እንጂ ያው እንደ አውሬ ወንድሞቹ የማታ የማታ ዘሎ እንደሚያንቃት አልተጠራጠረችም ነበር:: አልጋው ውስጥ ገብቶ በጀርባው ተኝቶ አንጋለውት እንደሄዱ ህፃን ጣሪያ ጣሪያውን ሲመለከት በጨለማው ውስጥ ስታየው ደነቃት፣ ቢሆንም አላመነችውም:: 'ዘግይቶ ሊጎትር ነው' ብላ ደህና እደር አለችውና በደረቷ ተገልብጣ ተኛች:: እንቅልፍ ሊወስዳት ግን አልቻለም:: ሰውነቷ አላርፍልሽ አላት:: 'ከአሁን አሁን ዘሎ...' እያለች አላይ እታች የሚለውን ትንፋሹን ተከተለችው::

እንቅልፍ እንዳልወሰደው እርግጠኛ ነበረች:: እንዳሰበችው ሃሳቡን ሳይቀይር ዘገየባት:: 'ቢያነቃቃውና በጊዜ ብገላገል' ብላ በእንቅልፍ ልቧ እንዳለች ሁሉ ተወራጨችና በብርድ ልብሱ ውስጥ ክንዷን ሰድዳ አንድ እጇን ጭኑ ላይ ጣል አደረገችው:: ተፈታተነችው:: ሲሸማቀቅ ተሰማት:: እጅን ሰድዶ እጇን ከላዩ ላይ አነሳና በቀስታ እራቅ አድርጎ አስቀመጠው::



በእንቅልፍ ልቧ ያለች ሳይመስለው አልቀረም:: 'ጃውሳው! በጉ!' ተረጋጋች:: ሳታውቀው ድብን ያለ እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ አለ::

በተከተሉት ቀናት ሳትጠይቀው ቀድሞ የተስማሙበትን የወር የቤት ኪራይ ሂሳብ ሰጣት:: ከዛ በተረፈ ከሆቴል እንድታመጣለት ገንዘብ እየሰጣት እራሱን ብቻ ሳይሆን እሷንም እየቀለበ ተቀመጠ:: 'ተገኝቶ ነው?':: ግን ደግሞ ከቤት ብቅ አለማለቱ የተደበቀ ሰው አስመስሎታል:: 'አንድ ክፍል ቤቷ ውስጥ ዘግቶ መቀመጥ ምን ማለት ነው? ታዲያ ይሄን ዝም ብሎ ማለፍ ይቻላል? እህእ ነገ አንዱ መርቶበት ቢያስይዘው አብራ መውረዷ አይደለም? የተካፈለች አብራ የገመጠች ይመስል ሆ!

"ልክ ነሽ! ልክ ነሽ! ይገባኛልኮ:: ግን ሠርቄ አይደለም::" አላት የያዛቸውን ክንዶቿን ለቆ አልጋው ላይ እየተቀመጠ::

"እሺ, ምንድነው ታድያ?"

"እይው ምን መሰለሽ..." ያጠነጠነውን ይተረትር ጀመር:: አራት ቀን ሙሉ ብቻውን በሚሆን ሰዓት እየተንጎራደደ ያጠናውን የተለማመደውን ዲስኩር ጀመረ::

"በምስራበት መሥሪያ ቤት ውስጥ ረዳት የሂሣብ ክፍል ኃላፊ ሆኜ ነው የማገለግለው:: ዘውድዬ እኔ ትዳር ያለኝ ሰው ነኝ፤ የሁለት ልጆች አባት ነኝ:: ነገር አልሻም፤ በሠላም ስርቼ ከቤቴ መግባት ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር ያገኘሁትን ተቋድሼ ማደር ነው የምሻ:: ምን መሰለሽ..." ትክ ብለው ቁልቁል የሚያዩት አይኖቿ ሰርስረውት ገቡ:: ግንባሩን የምታነብ መሰለው:: ሁለት እጆቹን አንስቶ ለአንድ አፍታ ፊቱን በመዳፎቹ ውስጥ ደበቀው:: «ዘውድዬ እመኚኝ እኔ አምስት ሳንቲም አልነካሁም:: ፈጣሪ ምሥክሬ ነው ሰባራ ሳንቲም አላነሳሁም:: ግን በመሥሪያ ቤታችን በርካታ ገንዘብ ጎድሎ ተገኘ:: ነገሩ እንደተገለጸ የመሥሪያ ቤታችን የሂሣብ ሹም የኔ አለቃ የገባበት ጠፋ:: ዘውድዬ ገንዘቡን ያጠፋው እርሱው ነው:: አውቀዋለኋ ንፅህናዬን:: ከእኔና ከእሱ ሌላ ደግሞ ማንም ገንዘቡን ሊያጠፋ አይችልም:: አለቃዬ በተሰወረ በሶስተኛው ቀን እኔን ይዘው ሊመረምሩኝ እንዳሰቡ የሰማ ሰው ሹክ አለኝ:: ምርጫ ባጣ ለጊዜው ብዬ ተሰወርኩ::"

"ተሳስተሃልኮ!" አለች ዘውዲቱ ራመድ ብላ መጥታ ከጎኑ አልጋው ላይ እየተቀመጠች:: "ስትጠፋኮ አንተ ያደረከው... ማለቴ ገንዘቡን ያጠፋህ ነው የሚያስመስልብህ::"

"ምን ላድርግ ዘውድዬ?!" እንዳመነችው ገባው:: ልቡ ተረጋጋ:: ይበልጥ በቅራቅንበው ሊያስምጣት ተዘጋጀ:: "ቢይዙኝስ? ቢያንገላቱኝስ? ቢያስሩኝስ? ዘውድዬ ያላጠፋሁትን ገንዘብ 'ውሰድ' ቢሉኝ ምን ሊውጠኝ ነው? ህፃናት ልጆቼ ምን ሊውጣቸው ነው? ስውየው መያዙ አይቀርም

ዘውድዬ:: እውነቱ ይገለፃል:: ያኔ እወጣለሁ:: እኔ እራሴ ሄጄ እጄን በፈቃዴ እሰጣለሁ:: እውነቱ ይገለፃል:: ሌባው ሳይያዝ ግን እጄን መያዝ የለባቸውም::"

"ሰውየው እንደሚያዝ በምን አወቅህ?"

"ዘውድዬ ተደብቀን እስከመቼ እንኖራለን? እንዳችን እንያዛለን ያማ አይቀርም:: ዋናው ነገር ቀድሞ ማን ይያዛል ነው:: አየሽ ቀድመው እሱን ከያዙት አመለጥኩ ማለት ነው:: ንጽህናዬን የሚያውቅ ፈጣሪ ረዳኝ ማለት ነው:: እንዲያ እንዲሆን ደግሞ ዱካዬን ማጥፋት አለብኝ:: ለጊዜው መሰወር አለብኝ:: ለዚህ ነው የማስቸግርሽ! ዘውዲቱ እመኚኝ ብድርሽን እከፍላለሁ:: ነገ ቤተሰብ ነን! ወንድምሽ ነኝ! ባለቤቴም እህትሽ ነች...እ?" አይን አይኗን እያየ አስተዛዝኖ አታለላት::

"የሰረቀውም ያልሰረቀውም እኩል የሚባረርባት ዓለም!" ለራሷ ነበር የተናገረችው ዘውዲቱ::

ተረጋጋ:: አምናዋለች! ያለጥርጥር አምናዋለች! የተረተረላትን ቱባ ውሸት ምንም ሳታስቀር ውጣለታለች:: ተረጋጋ::

ከዚያ ቀን ወዲያ ብዙም አላስቸገረችው:: በቀን ሶስቴ ምግቡን ከሆቴል እየገዛች ታመጣለች:: በተረፈ ታጽናናዋለች:: ፊዘዝ ያለ ሲመስላት "አይዞህ አታስብ ተጫወት" ትለዋለች:: እልፍ ተርፉ ቤቷን ተከራይቶ በገባ በሳምንቱ-

"ግን ቤተሰብህኮ በጣም ነው የሚረበሸው:: ከፈለክ መልዕክት ላድርስልህ" አለችው::

"አ! አ! ዘውድዬ ይሄማ አይሆንም:: ዋዛ አድርገሻቸዋል ፖሊሶችን:: ይሄኔ ቤቴ ዙሪያው ይጠበቃል:: ስትገቢ ካዩሽ ከኋላ ተከትለውሽ ነው የሚመጡት::" አላት::

"ግድ የለም:: ስልክ ደውዬ ባለቤትህን አንድ ቦታ እቀጥራታለሁ::"

"አይ ዘውድዬ! የምን ስልክ አመጣሽብኝ:: አሁን በእኔ አቅም ልጆቼን ቀልቤ ተርፎኝ ስልክ ቤቴ ገባ?" ያዘነ መሰለ::

"በቃ... በቃ አትበሳጭ:: እኔኮ ባለቤትህ ትጨነቃለች ብዬ ነው::"

"ግድ የለም ዘውድዬ... ባይሆን ራሴን ቀያይሬ ከአንድ ከሳምንት በኋላ ወጥቼ ሁኔታውን ሁሉ ለሳልዬ እመለሳለሁ::" አላት ለመጪው ውሸት እያዘጋጃት::



ከቤቷ በገባ በወሩ ነበር ወደ ውጭ ሊወጣ እንደተዘጋጀ የነገራት::

"ጺምህም አድጓል... ማንም አያውቅህም:: ግን ለማንኛውም ጠንቀቅ በል::"

"በጣም እንጂ ዘውዲቱ! በጣም አየሽ የጺሜ ማደግ በቂ አይደለም! ሁለመናዬ መቀየር አለበት::"

"ታዲያ ምን ልትፈጥር ነው? ጡቱን አላበድርህ! እሱንም ብሰጥህ ሻይ ሊጋብዙ ያስቆሙሃል::" አለች እየሳቀች::

"ዘውዲቱ አይደለም! ጡትሽን አይደለም:: የምትገዥልኝ ዕቃዎች አሉ::"
"የምን ዕቃ?"

"ጥምጥም! የቄስ ጥምጥም.... እ... ጋቢ..... ደግሞ ከዘራ! ጫፉ ላይ መስቀል ያለው ምርኩዝ... አወቅሽው አይደል?"

"ምን ልትሆን ነው?"
"ቄስ መስዬ ልወጣ ነው ያሰብኩት::"
"አንተ ጉደኛ ነህ!" አለች ዘውዲቱ በተገረመ ፊት አፍጥጣ እየተመለከተችው::
"እና ደግሞ.... ጭራ::"
"የምን ጭራ?"
"ጭራ ነዋ! የዝንብ ማባረሪያ ጭራ ቄሶች የሚይዙት::"
"ደግሞ እሱ ምን ይሰራልሃል?"
"ነገርኩሽኮ ቄስ መምሰል ነው የምፈልገው አልኩሽ:: ደግሞም ፊቴን እሸፍንበታለሁ::"

"እና ደግሞ ሌላስ? ምን ቀረህ?" ሳቋን ማፈን አቃታት ዘውዲቱ "ሀ! ሀ! ሀ! የታቦት ገርንጥላስ? ሂ! ሂ! ሂ! ጽናጽልስ? ከበሮስ? ሀ! ሀ! ሀ! ሀ!" ጭንቅላቷን ወደኋላ ጥላ በሳቅ ፍርስ አለች::

"ዘውዲቱ አታሹፊ! ላስቱክ ቦት ጫማም ግዢልኝ:: መንነደኛ እንድመስል:: ከገጠር የመጣሁ እንድመስል::" የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ይበቃታል ያለውን ገንዘብ ሰጣት::

ያን ማታ ከስራ ስትመለስ ያላትን የጠየቃትን ሁሉ አንድም ሳታስቀር ገዝታ አመጣችለት:: በሩን ከፍቶ ሲያስገባት የተሸከመችውን ሁሉ አልጋ ላይ ዘረገፈችውና በረጅሙ ተነፈሰች...

"እሺ አባ ደህና አመሹ" አለችው እየሳቀች::

"ታዲያስ ዘውድዬ::" አለ ጉንጮቿን በጣቶቹ ቆንጠር አድርጎ:: ፈጠን አለና አልጋው ላይ ያስቀመጠችለትን በጋዜጣ ወረቀት የተጠቀለሉ ዕቃዎች ተራ በተራ የተጠቀለሉበትን ወረቀት እየቀደደ ይመለከታቸው ጀመር::

"ሳሳ ያለ ጋቢ አትገገርም ነበር? ይሄን ተሸክሜ..."

"ሌሊት ቆመው ሲያስቀድሱስ ብርዱስ?" አለች እየሳቀችበት፤ አልጋ ውስጥ ልትገባ እየተዘጋጀች::

"አንቺኮ ታሾፊያለሽ:: ፐ! ከዘራው ይልቅ ምርጥ ነው::"

"ምርጥ ምርጡን ለአባ::"

"ጥምጥም ነው ይሄ አይደል?" አላት ነጭ ሸማ አንጠልጥሎ::

"እንደተገልጋዩ ነው... መቀነትም ይሆናል::" አለችው::

"ደግሞ ይሄ ምንድነው?" አላት የእንጨት መስቀል አንከርፎ ይዞ::

"መስቀል ይሉታል:: ድሮ... ድሮ እየሱስ የሚባል ሰውዬ ነበር..."

"ማን አልሽ?"

"ክርስቶስ ማለቴ ነው!"

"ዘውዲቱ! በናትሽ አትጫወቺብኝ:: አቋረጣት::"

"ምን አሾፋለሁ... መስቀል የማይዝ ቄስ አይተህ ታውቃለህ? አንዷ አሮጊት ሮጠው መጥተው 'አባ አሳልሙኝ' ቢሉህ ምን ልትል ነው 'ዘውዲቱ አልገዛችልኝም' ልትል ነው?"

መስቀሉን እንደያዘ ሣቅ ይተናነቀው ጀመር:: ትክክል ነች:: ዋናውን መማሪያ ነው የረሳው:: የቄሱን - መስቀሉን::

"ዘውዲቱ ያንቺ ጭንቅላትኮ ያለቦታው ነው::" አለ ሳይታወቀው::

"እንዴት? የት መሆን ይገባው ነበር... ጭኖቼ መሃል?" አለች ልብሷን ለማወላለቅ እየተዘጋጀች::

"እንደሱ ማለቴ አይደለም:: ለማለት የፈለኩት... እ... እ..." አለ ግራ ሲገባው እየሳቀ::



"አባ አይቀድሱብኝ:: ይልቅ መስቀሉን ወዲያ ያስቀምጡና ልብሶን አወላልቀው አቅፈውኝ ይደሩ::" አለች የለበሰችውን አበሻ ቀሚስ እያወለቀች::

ያወለቀችውን ቀሚስ ከቁም ሳጥኗ ስቀላ ተመለሰች:: ከሰውነቷ ጋር የተለጠፈ የሚመስለውንና ያፈጠጠ ጡቷን ወጥሮ የያዘውን ነጭ ልስልስ የውስጥ ልብሷን በጭንቅላቷ በኩል እያታገለች ሳበችው:: መካከለኛ የፓፓያ ቅርጽ ያላቸው ጡቶቿ ውስጥ ልብሱ ሚገርቅ አድርጓቸው ሲያልፉ ናትናኤል ዓይን ላይ እንደ ጎማ ደጋግመው ነጠሩበት:: ያልተሟሸ ሸክላ የመሰለው ደረቷና እንብርቷ አካባቢ የሚታየው ቅርጿ ገና ሳይነኩት ከሩቅ የሚለሰልስ ነው:: የዳሌዋ ሚዛን በአግባቡ አበጥ ብሎ የሽንጧን አወራረድ ደርገዝ ይጠብቃል:: ናትናኤል ባለፉት ቀናት እየተላመዳት በመምጣቱ ዓይናፋርነቱን ከላዩ ላይ ጥሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ቂስነቱን ረስቶ ትክ ብሎ ተመለከታት:: አይኖቹን በሰውነቷ ላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ አሮጣቸው:: ዞር ብል ይሉኝታ... ሀሲና በማስተዋል እየታዘዘ በውበት አድናቆት ይርካ...ተፈጥሮ ትደነቅ... ከእግዚአብሄር በታች ቅርጽ ቢመለክ ምን ያስገርማል! ...የሴት ልጅ ቅርጽ፤ የጃኔረዳ አበባ ቅርጽ፤ የግራር ዛፍ ቅርጽ፤ የወንዝ ዳር አለት፤ የነስር አሞራ፤ የእንስሳ፤የሜዳ አህያ... የዘውዲቱ.... እህህ!

"ምነው አባ ቄሱ ትክር ብለው አዩኝ?" ስትለው ከሄደበት ሃገር ተመለሰ::

"አይ... ገዛም ብዬ እንደው... አለ አይደል..." የሚመልስላት ጠፋው:: ትንሽ ደንገጥ እንደማለት ቢልም አይታውን ከላይዋ ላይ አልነቀል አለ::

ዘውዲቱ እየተውረገረገች ወደ ቁም ሳጥኗ ተጠግታ እጇን ወደ ውስጥ ሰድዳ የተሰበረ የፊት መስታወት ስታወጣ በጀርባና በትከሻዋ የደሳሳዋን ትንሽ ክፍል የታመቀ አየር የምትቀዝፈው መሰለች:: የዳሌዋ ሚዛናዊ እንቅስቃሴ ለመጥ ካለው ቀጭን ወገቧ ጋር ሙዚቃዊ ስልት ፈጥሮ በውስጥ ሱሪ ብቻ የተሸፈነውን መቀመጫዋን ጎልቶ እንዲወጣ አድርጎታል:: ናትናኤል ሰውነቱ ሲሟሟቅ ተሰማው:: ይሄ ነው ብሎ የማይለው አንዳች ስሜት ሁለመናውን ይወረውና ይወጣጥረው ጀመር::

"እንዳቅማችን እኛም መስተዋት አለን... የተሰበረም ቢሆን የፒያሳም ባይሆን ቅባትም..." አለችና ከአልጋዋ ትራስጌ የቅባት ቆርቆሮና ቢልቃጥ አወጣችና አልጋው ላይ እግሯን አነባብራ ተቀምጣ ትቀባባ ጀመር::

"ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል ሲሉ አልሰማሽም? አይዞሽ" አላት ግርንቡዷ ላይ እንደተቀመጠ ዓይኖቹን በተነባበሩት እግሮቿ ላይ ተክሎ የባቶቿን ዘና ያለ ማራኪ አወራረድ እያደነቀ።

"እስስ እውነትክን ነው... አትመልከቺ ሱፍ አትዩ መኪና እኛም እንገዛለን ዕድሉ ሲቃና ብሎ የለ ዘፋኙ" አለች በአርጌ ማበጠሪያ ሁኑሯን እየሞገርቀች።

ናትናኤል ሳያስበው አንድ የሚጸጸተው ነገር ድንገት ተናገረ። "ቆንጆ ነሽ" አላት ትንፋሹ እየተናነቀው። የአድናቆት ቃል ምን ይጎዳል?

"ቆንጆ ነኝ? ቆንጆ ነኝ? አለችና መስተዋቱን አልጋዋ ላይ ውርውር አድርጋ

"የቂስ ቆንጆስ አንተ..." ብላ ድኩላ እንደሚያጠምድ ነብር ዘላ ተጠመጠመችበት። ጭኖቿን ጉልበቱ ላይ አጋድማ እያገላበጠች ታሻሸው ጀመር።

"ልቀቂኝ" አለ ሲገፈትራት እየተፍጨረጨረ።
"አሁን ገና ተያዝክ አይደል..." እያለች በሳቅ ትንከተከት ጀመር፤ ያሞጠሞጡ ጡቶቿን በደረቱ ላይ እንደ ደንገላሳ እያንከባለለች -

"እንዲህ ነች ዘውዲቱ! ቆንጆ ነሽ እያልክ ደሞ ልትገፈትረኝ።" እጆቿን ሊያስለቅቃት ሞከረ።
"እልለቅህ ዛሬ ብር አምባርህን ሳልሰብረው! ...ሙከራዋን ወደ ቀልድ ለወጠች እየተፍነከነከች።
"ዞር በይ ዘውዲቱ" በመጨረሻ ተሳከለት። ሲገፈትራት እጇን አሳልፉ ለቀቀችውና አልጋዋ ውስጥ ኀብታ እያስካካች ትንፈቀፈቅ ጀመር። ሙከራዋን በኋልዮሽ አስተሳሰቢ ቀልድ አድርጋ እንዳየችው ለናትናኤል ታውቆታል።

ናትናኤል ሁለመናው እንደጋለ ነው። አልቦታል። የልቡ አመታት ጨምሯል። ቀዝቃዛ ነላዋ ለቆት የሄደ አልመሰል እስኪለው ድረስ ተቅበጠበጠ፤ ተቁነጠነጠ። ሱሪው መጠጣጠሩን አሁን ነው ያወቀው። ሠይጣን የሚባለው ለካ ይሄ ነው... አዳምና ሄዋን ወይስ ሄዋንና አዳም.... አዳም ለካ ደካማ ነው... ኢምንት... የሴት ትንፋሽ በሙቀት ኀረት በቅጽበት ጉድ የሚያደርገው... የሴት ልጅ ገላ ሲነካውና የሴት ልጅ ጣት ሲዳስሰው ስሜቱ እንደ በረዶ ቀልጦ በሴኮንዶች ምርኮኛ የሚያደርገው... ይገርማል... ለካ ሰው ወዶ አይደለም አይገቡበት አዘቅት የሚወርደው... በጨለማ ዋሻ ውስጥ የሚሰምጠው... ለጥቂት እኮ ነበር። ለዓላማው የተነሳሳ መሆኑና በአስተዳደጉ ባይተዋር የሆነበትን ሽርሙጥናን መጥላቱ እንጂ ጉድ ሆኖ



ነበር። ለማናቸውም ግን ፈተና ነው ዛሬ ያሳለፈው። ዘውዲቱም አይበገሬነቱ እንደገባት ግልጽ ነው....

"እረ ና ተኛ ባክህ...እኔ እንቅልፌ መጣ... መስታወቷን ደሞ እቦታዋ አኑርልኝ። ጎሽ የኔ ቡት ጠባቂ... የኔ ዘበኛ" አለችው አየዘጋች።

"ጭኔ ሳትገባ ታቅፈኛለህ እሺ? በገብርኤል!" አለች ቀጠለችና
"በሚገባ እንጅ። ወንድም እህቱን አቅፎ አይተኛም ያለው ማነው?" አላት ፈገግ ብሎ።

ያንን ሌሊት አቅፏት አደረ።

* * *

ዘውዲቱ ያላትን ሁሉ በገዛችለት በማግስቱ ቦት ጫማውን አጥልቆ ጋቢውን አጣፍቶ ለብሶ ጥምጥሙን ጠምጥሞ፤ መስቀሉን ጎያው ከቶ ጺሙን አጎፍሮ በምርኩዙ መሬቱን እየተነከሰ ጭራውን በተን መለስ እያደረገ ጭንቀትና ፍርሃት እያንጠረጠሩት ወጣ።

"ያመሻሉ እንዴ?" አለችው የቤቷን ተለዋጭ ቁልፍ እየሰጠችው።
"አይመስለኝም።" አላት የተንዘላዘለ ጋቢውን ወደ ትክሻው ሽቅብ እየሰበሰበ።

"ተጠንቀቅ... እ ... እቤትህ ድረስ ባትሄድ ጥሩ ነው። ባይሆን ባለቤትህ ከቤት የምትወጣበትን መንገድ ፈልግ።"

"አታስቢ" ብሏት ወጣ።

በጠባቧ ኮረኮንች መንገድ አልፎ ከዋናው የመኪና መንገድ ብቅ እንዳለ ፍርሃት ፍርሃት አለው። ሰው ሁሉ እሱን እሱን የሚያይ የሚመረምር መሰለው። ታክሲ ተሳፍሮ ወደፒያሳ ገሰገሰ። ሂሣቡን ከፍሎ ከታክሲ ከወረደ በኋላ በመሃል ፒያሳ ሲያልፍ የገዛ ምስሉን በረጃጅሞቹ የሱቅ መስታወቶች ውስጥ ሲመለከት ለራሱም ማመን አቃተው፤ምንም ቄስ አልመሰልህ አለው። የሚያውቁት ቢያገኙት...'ፈጣሪዬ!' አለ ከራሱ ጋር። አንድ ነገር ደግሞ ይጎለዋል። ከውጭ የሚታየው አለባበሱ ቅስናው ሕጋዊ መሆን አለበት። ሕጋዊ የመታወቂያ ወረቀት ያስፈልገዋል። ምን ማድረግ እንዳለበት ለሳምንታት አውጥቶ አውርዶ በዝርዝር አቅዶታል። ጊዜ አላጠፋም መንገዱን ተሻግሮ ከአንድ ፎቶግራፍ ማንሻ ቤት ገባ።

"እንደምን ዋልሽልኝ የኔ ልጅ::" አሏት ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጣ ትናንሽ ፎቶግራፎች በመቀስ የምትከረክም ቤት ሲገቡ::

"አቤት እንደምን ዋሉ::" አለች ልጅቷ ከተቀመጠችበት ተነስታ ቄሱ ከጉያቸው ያወጡትን መስቀል እየተሳለመች::

"እባክሽ ፎቶ ልነሳ ብዬ... አሁን ይደርስልኝ ይሆን?" አሏት አስተዛዝኖ::

"አዬ... አሁን እንኳን አይደርስሎትም:: ነገ በዚሁ ሰዓት ቢመጡ አዘጋጅተን እንጠብቆታለን::"

"አይ! አይ! ነገ በዚህ ሰዓትማ ደብረሊባኖስ አቀበቱ ላይ ነኝ:: አሁን አልኩሽዪ:: እባክሽ የእኔ ልጅ ሳስቸግርሽ:: መንገደኛ ሁኜ ነው::" ለሳምንታት ያጠናውን ቃለ ምልልስ እንዳመጣጡ እያስተካከለ ያወርደው ጀመር ቄሱ:: ቀዝቃዛ ፍርሃት ነፍስ ዘርቶ በጀርባው ተንቆረቆረ::

"እስቲ ይቆዩ አንዴ:: አስራት! አስራት!" እያለች ወደ ጓዳ ገባች ልጅቷ:: ብዙም ሳትቆይ ረዘም ጠቆር ያለ ጺማም ወጣት ተከትሏት መጣ::

"እንደምን አለህልኝ የእኔ ልጅ::" አሉ ቄሱ የተዝረከረከ ጋቢያቸውን ወደትከሻቸው ሰብስበው የእንጨት መስቀላቸውን ወደፊት እየገፉ::

"እንደምን አደሩ::" አላቸው ወጣቱ ጢጋ ብሎ የዘረጉለትን መስቀል እየተሳለመ::

"ተቸግሬ አስቸገርኳችሁ... ፎቶ ብታደርሱልኝ ብዬ ነበር እባክህ... አሁን ከሰዓት ሂያጅ ነኝ ወደ ደብረሊባኖስ... ፎቶ አስፈልጎኝ ነበር መታወቂያዬ ጠፍቶብኝ::" ቄሱ ጺማቸውን እየዳሰሱ አስተዛዝነው ጠየቁት::

"አሁን እንኳን ብዙ ነበረብኝ...ብቻ እስቲ ይግቡ::" አለ ወጣቱ ከጀርባ ያለውን ቀይ መጋረጃ እየገለጠ::

"ተባረክ ልጄ..... ብሩክ ሁን::"

በርጩማው ላይ ተቀምጠው ቄሱ አንገታቸውን ቀና አደረጉ:: ከግራና ከቀኝ የቆሙት ቡጢ የሚያካክሉ የመብራት አምፖሎች የሚፈነጥቁት ብርሃን ከፊታቸው ላይ ካለው ወዝ ሲያርፍ ቄሱ አብለጨለጩ::



"ቀና... ቀና ይበሉ አባት... ወደ ጎን...እ...እ... እም... እዚህ ... እዚህጋ ይመልከቱ... አ...አ...ም...በቃ::" አላቸው መብራቶቹን እያጠፋ::

"ተባረክ:: እንጀራህ ከፍ ይበል::" አሉ ቄሱ ከበርጩማው ላይ እየወረዱ:: ተንዘላዝሎ መሬት የደረሰውን ጋቢያቸውን መልሰው አጣፍተው ቀዩን መጋረጃ ሰብሰብ አድርገው ወጡ::

"ከደህ ልጠብቅ መሰል::" አሉ ቄሱ ወንበር ላይ ቁጭ እያሉ::
"አዎ:: ቁጭ በሉ! ቁጭ በሉ::" አለቻቸው ወጣቷ ሴት::
"ተባረኪ የኔ ልጅ...ተባረኪ::"

ከግማሽ ሰዓት በኋላ በትንሽ የወረቀት ከረጢት ውስጥ ስድስት ፎቶግራፎች ይዘው ከፎቶግራፉ ቤት ወጡ! ቀና ቀና እየተነፈሱ ቄሱ::

ፎቶግራፍ ብቻውን በቂ አይደለም:: ወረቀቱ ያስፈልጋል:: መታወቂያ ወረቀት! የማንም ይሁን ብቻ መታወቂያ ወረቀት:: አንድ ስርዓት አስከባሪ አስቁሞ 'አባ መታወቂያ' ቢለው ሳይፈራ ሳይቸር ደረቱን ገልብጦ ጋቢውን ገልቦ መኻረጥ ሊያደርገው የሚችለው መታወቂያ ወረቀት ያስፈልገዋል:: ከየት እንደሚያገኘውም ያውቃል:: የመታወቂያ ወረቀቶች እንደዋዛ ጠረጴዛ ላይ ጣል የሚደረጉባቸው ቦታዎች የት የት እንዳሉ ያስታውሳል:: ባለፉት ሳምንታት ቀን በሃሳብ ተጠፍሮ እየተንጎራደደ ሌሊት በቅዠት ተወጥሮ እየተወራጨ የተዘጋጀበትን ዕቅድ ተራ በተራ ይፈጽመው ጀመር::

ከመንገድ ማጥ ካሉ ሱቅ የፖስታ ከረጢትና ወረቀት ገዝቶ ወረቀቱን አጣጥፎ ፖስታው ውስጥ ከቶ ፖስታውን አሽጎውና ወደ ዋናው ፖስታ ቤት አመራ::

ረጅም ምርኩዙን በብብቱ ይዞ በፖስታ ቤቱ የላይ በር ገባ:: የፖስታ ሳጥኖች የተደረደሩበትን መተላለፊያ አልፎ ከዋናው አዳራሽ ዘው አለ:: መደዳውን ከተገጠገጡት መስታወት መስኮቶች ጀርባ የፖስታ ቤቱ ሠራተኞች በየወንበሮቻቸው ላይ ተደርድረው ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ::

ወደ ቀኝ ገልመጥ አለና ወደ አንደኛው የደብዳቤ መጻፊያ ጠረጴዛ ተጠግቶ ጠረጴዛው ላይ አቀረቀረ::አልፎ አልፎ ቀና እያለ ከፊት ለፊቱ በስተግራ ጥግ ያለውን መስታወት ይመለከት ጀመር:: ልቡ አለቅጥ ተጣደፈበት:: በሀሳቡ ሺህ ጊዜ ያመላለሰው ዕቅድ ሊዘበራረቅበት ዳዳው::

ከመስኮቱ በታች ያለውን ጠረጴዛ ተመለከተ:: ሁለት ይሁኑ ሦስት ብቻ የመታወቂያ ወረቀቶች ይታዩታል:: ካቀረቀረበት ቀና አለና በእጁ የያዘው የታሸገ የፖስታ ከረጢት ወደፊት አንከርፍፎ ወደ መስኮቱ ተጠጋ:: የደረቀ ከንፈሩን በደረቅ ምላሱ በረሸው::

ከፊት ለፊቱ አንድ ሰው ቀደም ብሎ ደረሰና ከመስታወቱ ጀርባ ለተቀመጠችው ወጣት ሴት ሠላምታ ከሰጣት በኋላ አንድ ትንሽ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ አቀበላት።

ልጅቷ ወረቀቷን ተቀብላ ካነበበቻት በኋላ ከተቀመጠችበት ተነስታ ከጀርባ ወዳለ የቁም ሳጥን ሄደች። የእንጨት ሳጥኑን ከፍታ አንዱ አንዱን እንደ ሌላውን ስታነሳ ከቆየች በኋላ አንድ በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ ዕቃ ይዛ ተመለሰች።

"ዶክተር ዓለሙ ገዛኸኝ?" አለች ወረቀት ያቀበላትን ሰው ቀና ብላ ተመልክታ።

"አዎ...ነኝ"

"መታወቂያ።"

ሰውየው ቀልጠፍ ብሎ የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ከውስጥ የመታወቂያ ወረቀቱን መዘዝና አቀበላት። ልጅቷ መታወቂያ ወረቀቱን ተቀብላ የተጻፈውን ስምና ፎቶግራፍ ከተመለከተችና ትክክል መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ በካኪ ወረቀት የተጠቀለለውን ዕቃ ለሰውየው አቀበለችውና-

"ይክፈሉት። አለች"

ሰውየው ከውጭ አገር የተላከለትን በካኪ ወረቀት የተጠቀለለ ዕቃ ያለጥንቃቄ ወረቀቱን ከላይ ቀዳዶ አንስቶ ተመለከተው የተደራረቡ አራት የሲዲዩ ክሮች ነበሩ።

"ካንሰር አድርገውት ይመስሉ። መታወቂያዎ እዚህ ይቆያል። በዚህ ቀጥታ ይሂዱና ወደቀኝ እጥፍ ሲሉ..." ልጅቷ ሰውየውን አመላከተችው።

ሰውየው የተላኩለትን አራት ክሮች ሰብስቦ ይዞ ከአዳራሹ ወጣ።

"የኔ ልጅ" አሉ ቀረብ ብለው ቆመው የነበሩ ነጭ ጥምጥም የጠመጠሙ ቄስ። "እዚህ ላይ የሚጣፈውን ትጥፊልኝ... አላውቅበት ብዬ። እንዳላዘረው ሰጋሁ።" የያዙትን የታሸገ ፖስታ ወደ ልጅቷ ፊት አስጠጉት። ሲናገሩ ድምጻቸው ይንቀጠቀጣል። ወረቀቱን ሲያቀብሏት ምርኩዛቸው እምልጧቸው ወደቀ።

"ምንድነው የፈለጉት?" አለች ልጅቷ ቄሱ ሲደነጋገሩባት ግራ ተጋብታ።

"የኔ ልጅ ይህን ቦስጣ ልልከው ፈልጌ ነበር። ታዲያ ከይህና ከይህ የሚጣፈውን እንዳላበላሽ ሰጋሁ።" አሉ ቄሱ ያሸጉትን ፖስታ እያገላበጡ። "እምን ከምን እንደሚሰፍር አላውቅበት ብዬ... ትጥፊልኝ።" ለሳምንታት የሸመደዱትን ተረተሩላት።

"የሚልኩለትን ሰው አድራሻ ያውቁታል?" አለች ልጅቷ ፖስታውን ልትቀበል እጇን እየዘረጋች።

"እንዴታ!ቄስ ገብረክርስቶስ ጋ"
"አይደለም... አይደለም... ማለቴ ሙሉ አድራሻውን" አለች ልጅቷ ፈገግ ብላ።

"እነግርሻለሁ። ብቻ አንቺ ከሥፍራ ከስፍራው ጣፊልኝ።"
ልጅቷ ወረቀቱን ከተቀበለቻቸው በኋላ ወረቀቱ ላይ አቀርቅራ የሚነግሯትን ለመፃፍ ትጠባበቅ ጀመር።

"ቄስ ገበዝ ገብረክርስቶስ በይማ።"

ልጅቷ በፖስታ ከረጢቱ ጀርባ ላይ ቄሱ ያሏትን ማስፈር ጀመረች። ቄሱ ጠጋ ብለው በጠረጴዛው ላይ ተደራርበው የተቀመጡትን የመታወቂያ ወረቀቶች ሰበሰብ ሰበሰብ አደረጓቸው።

"እንዲያ... ደብረሊባኖስ ገዳም... በይ... አዎ...ደ...ብ...ረ..." ቄሱ ከጠረጴዛው ላይ የሰበሰቧቸውን አራት መታወቂያዎች አጋብሰው ከጋቢያቸው ስር ከኪሳቸው ውስጥ ጨመሯቸው። "ሸዋ... በይበት... እንዲያ ተባረኪ!" አሉ ድምጻቸው እየተንቀጠቀጠ።

"የእርሶስ አድራሻ? " አለች ልጅቷ ቀና ብላ እየተመለከተቻቸው።
"እኔማ ምን አድራሻ አለኝ? መንገደኛም አደለሁ?" አሏት ቄሱ ፖስታቸውን ተቀብለው ለመሄድ እየተጣደፉ።
"ቢሆንም ስሞትን እንኳን ልጻፈው።"
"ልክ! ልክ! ቄስ ዘነበ... ዘነበ ወልደሰማያት በይልኝ። እንዲያ ዘነበ።" አሉ ድግንት የተቻኮሉት ቄስ።

የፈለጉትን አድራሻ በታሸገው ፖስታ ላይ ጽፋ እንደጨረሰች ቄሱ መርቀዋት ፈጠን ብለው ከፖስታ ቤቱ አዳራሽ ወጡ። ገልመጥ አላሉም። መንገዱን ተሻግረው ታክሲ ውስጥ ገብተው ወደ ክፍለሃገር አውቶብስ መሳፈሪያ ሲያመሩ ነበር ምርኩዛቸውን ረስተው መምጣታቸው የታወሳቸው። ክው አሉ። ለመመለስ ግን አልደፈሩም።

ናትናኤል የገጠር አውቶቡስ መሳፈሪያ ደርሶ እንደወረደ ወደ ተከራየው ወደ ዘውዲቱ ቤት አልሄደም:: ወደ አንድ ሱቅ ገባና ስልክ ጠይቆ ርብቃ መሥሪያ ቤት ደወለ::

"ሃሎ- ምህረት?"

"ናትናኤል!" አለች ምህረት ገና ድምፁን ስትለየው::

"እንደምንድነሽ ምህረት ደህና ነሽ?"

"አንተ! ምን እንዲህ አጠፋህ? በጤናህ ነው?"

"አለሁ- አለሁ:: ምህረት እባክሽ ርብቃን ትጠሪልኝ..."

"የለችም:: ለመሆኑ አዲስ አበባ ነው ያለኸው?"

"ስራ አልገባችም?" አለ ጥያቄዋን ችላ ብሎ::

"አዎ ከትላንት ጀምራ አልገባችም:: ቤቷ ደውዬ ነበር የሚያነሳ የለም:: ደጋግሜ ሞክሬ ነበር::"

ናትናኤል ምህረትን ተሰናብቶ ስልኩን ዘግቶ ወደ ዘውዲቱ ቤት መንገድ ጀመረ:: ሃሳብ ገባው:: አሟት ይሆን? እንዴት ሁለት ቀን በተከታታይ ከሥራ ትቀራለች... በጤና ብትሆን? ቤቷ ሲደውል አሰበና ፈራ:: ስልኳ ተጠልፎ እንደሆንስ... ድጋሚ አደጋ ላይ ሊጥላት አይገባም:: ቆየይቶ ሰሞኑን እዚያው ምህረት ቢሮ ደውሎ ቢያነጋግራት ይሻላል::

ናትናኤል ዘውዲቱ ቤት ሲደርስ በሩ እንደተቆለፈ ነበር:: ዘውዲቱ የለችም ማለት ነው:: የሰጠችውን ተለዋጭ ቁልፍ አውጥቶ በሩን ከፍቶ ገባና ከውስጥ ቆለፈው:: ዕዲያው ጋቢውን ወርውሮ ጥምጥሙን አውልቆ ጥሎ ከኪሱ ውስጥ ከፖስታ ቤት የሰረቃቸውን አራት የመታወቂያ ወረቀቶች አውጥና ተራ በተራ እየከፈተ አነበባቸው::

ሻለቃ ብርሃኑ ገብረማርያም- አቶ ጀማል አብዱልከሪም-ዶክተር አለሙ ገዛኸኝ-ሲስተር ሠናይት አሸኔ:: ሀሳብ ገባው::የትኛውን ሊያቀስ እንደሚችል ግራ ገባው::

ምርጫ አልነበረውም::ዶክተር አለሙ ገዛኸኝ የሚለውን መታወቂያ ነጥሎ አንስቶ በጥንቃቄ ፎቶግራፉን ነቀለና ቀን ከተነሳቸው ፎቶግራፎች መሃል አንዱን ተካበት:: ወዲያው ቶሎ ብሎ ከመሬት አንስቶት ወደ ቤት ገባና ጭቃውን በጨርቅ ያፀዳ ጀመር:: የመታወቂያ ወረቀቱን በጥንቃቄ ጠራረገው፤ አፀዳው::እንደ በፊቱ ንፁህ ባይሆንም...መቼስ...'አለሙ ገዛኸኝ የሚለው ይነበባል::ያንን ነበር የሚፈልገው:: 'ዶክተር' የሚለው አስፈላጊ አልነበረም:: ለተቀሩት መታወቂያዎች ደግሞ ሰሞኑን ሌሎች ፎቶግራፎች ይነሳሳቸዋል::



## -18-

በሩ...የመኝታ ቤቷ በር ወደ ውስጥ ሲገፋ ጠረጴዛውን ደገፍ እንዳለች ቀረች::በሩ ተከፍቶ የሰው ቅርጽ ታየት:: ሰውየው ወደ ውስጥ ገብቶ በሩን ዘጋው:: ከጆርባው ባለው መስኮት የሚገባው ስስ የጨረቃ ብርሃን ቀጠን ረዘም ካለው ሰውነቱ ላይ ሲያርፍ ሰው ሳይሆን ህይወት ያለው ጥላ መሰላት:: ግራ ጉንጩን ከላይ እስከታች የነመሰው አስጠሊታ ጠባሳ የአካሉ አንድ ክፍል እንዳልሆነ ሁሉ በጨረቃዋ ብርሃን ውስጥ ጎልቶ ታየት:: አተኩራ ትናንሽ አይኖቹን ተመለከተቻቸው:: ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ጀመር:: ሆዷ ውስጥ ያለው ሽል የተላወሰ መሰላት::ሊያስመልሳት እንደፈለገ ሁሉ አንጀቷ ሲመናተል፤ ለራሱ ነፍስ የዘራ ይመስል ሲቋጠር ሲፈታ... ሳይታወቃት ወደፊት ዘላ ጉብ አለችበት::

"ገደላችሁት! ገደላችሁት አይደል? አታለላችሁኝ!"

አውቃ አስባ ሳይሆን ከውስጥ የሚነዳትና የሚጋልባት ዛር እንዳለ ሁሉ ዘላ ሆኑሩን ጨመደደችው:: ፊቱን በጥፍሮቿ ገባችበት::

"ርብቃ!" ጥፍሮቿን አሹላ አይኖቹን ልትጎጉጠው ስታሻቅብ ባለ በሌለ ሃይሉ እራሱን እየተከላከለ ጮኸ:: "ርብቃ! አልገደልነውም! ማንም አልደረሰበትም... እሱን ለመግደልም አላሰብንም... ርብቃ አዳምጪኝ!" ሁለት እጆቿን ወደኋላ ጠምዝዞ ደረቷን ደረቱ ላይ ለጥፎ አንገቷን በቀኝ እጁ ግጥም አድርጎ ይዞ ጮኸባት::

"ውሸታም! ውሸታም! አታላችሁኛል፤ ገድላችሁታል...ተፋ!" ፊቱን በምራቅ አለበሰችው::

"አልሞተም!አለ:: ስላመለጠን ነው ወደ አንቺ የመጣነው:: ርብቃ ረጋ በይ!"

ለአንድ አፍታ ረጋ ያለች መሰለች::ቀና እንዳለች ቁና ቁና እየተነፈሰች አፈጠጠችበት:: ድንገት እጆቹን መንጭቃ ከእቅፉ ወጣች:: ከፊቱ ተጋርጣ አይኖቿን አጉረጠረጠችበት::

"ልትገድሉት ነበር የጠራችሁት፤ ጓደኛውን እንደገደላችሁት እሱንም ልትገድሉት ነበር:: አትዋሽ! አሁን ደግሞ ወር ሙሉ እናገኘዋለን ታገሽ ስትለኝ ቆይተህ አመለጠን ትለኛለህ!"

"ርብቃ እመኚኝ:: እሱን የመግደል ሃሳብ አልነበረንም:: አስፈላጊም አልነበረም:: ምንም አያውቅም:: በድንግዝግዝ ጨረቃ ብቻውን እንደሚሮጥ

እብድ ነው፡፡" አለ ሰውየው ከኪሱ ውስጥ መሃረብ አውጥቶ ፊቱ ላይ የተዝረበረበውን ምሬቅ እየጠረገ፡፡

"ጓደኛውን አልገደላችሁትም? አትዋሽ!"

"ገድለነዋል፡፡ አስፈላጊም ነበር መሞቱ፡፡ ምሥጢሩን ከሞላ ጎደል ደርሶበታል፡፡ በማንኛውም ሰዓት ሊያወጣው ይችል ነበር፡፡ አደገኛ ሰው ነበር፡፡"

"እሱን የገደላችሁት ሌሊት ናትናኤልን ጠርታችሁታል፡፡ ልትገድሉት ነበር፡፡ አትዋሽ!" ከሥሯ ያለውን ወለል በእግሯ ደቃችው፡፡

"ርብቃ እመኚኝ፡፡ የዛን ቀን ጓደኛው አደገኛ የሆነ እርምጃ ወሰደ፡፡ ገደልነው፡፡ ምንም ምርጫ አልነበረም... እርግጥ በጥድፊያ ውስጥ ነበርን፡፡ የዛን ማታ ሁለቱም እንዲገደሉ ነበር የተላለፈው ትዕዛዝ፡፡ እንደአጋጣሚ ያንቺ ሰውዬ አመለጠ... ትራፊክ ፖሊስ ይሆት፡፡ በማግስቱ ግን ሁኔታው ሲረጋጋ የሞቱ ትዕዛዝ ተነስቶ የሃያ አራት ሰዓት ክትትል እንዲደረግበት ነበር የተወሰነው፡፡"

"...ሰዎቻችን መሥሪያ ቤቱ ሲገባ አይተውታል፡፡ ግን ከሰዓት በኋላ እንደደወለልሽና አምባሳደር ቲያትር ውስጥ በስውር ሊያገኝሽ እንደሚፈልግ ባሳወቅሽን ጊዜ ሰዎች ተመድበው ትያትር ቤቱ ድረስ ተከታትለውሽ ነበር፡፡ ግን አንቺ ራስሽ ከመታጠቢያ ቤት ከወጣሽ በኋላ እንደተሰወርሽበት ነበር ሪፖርት ያደረገው፡፡ ከዛ በኋላ ልናገኘው አልቻልንም፡፡"

"ብታገኙት ምን ልታደርጉት? ልታርዱት፤ ልትገድሉት?"
"ረጋ በይ፡፡ ማንም ሊገድለው የሚፈልግ የለም፡፡"

"ታዲያ ለምን ፈለጋችሁት?" ፊቷን አስግጋ ቀረበችው፡፡ "ተናገር!ምን ልታደርጉት ፈለጋችሁት? ሁሉን ዘርዝረህ ንገረኝ... ናትናኤል ከመጥፋቱ በፊት አንድ የተሰወረ ዲፕሎማት እንደሚፈልግ ነግሮኛል፡፡ ምን ማለት ነው? ማነው እሱ?"

"ነገርኩሽ!ለሞት የሚያደርስው ነገር የለም፤ በቃ፡፡ ምንም አያውቅም! የተሰባበሩ ጥቃቅን ጥያቄዎች ይዞ ነው ከወዲያ ወዲህ የሚሮጠው፡፡ እርግጥ ጓደኛው ስለተገደለ ፈርቶ ይሆናል... ግን ባጭሩ እሱን መግደል አስፈላጊ አይደለም፡፡ በቁጥጥር ስር ልናቆየው ነው የምንፈልገው... እስከጊዜው፡፡ ከዚህ ውጪ ዝርዝር ነገሮችን ልነግርሽ አልችልም፡፡ አንቺም ታውቂያለሽ፤እያንዳንዳችን ማወቅ የሚገባን እንደየደረጃችንና እንደአስፈላጊነቱ ማወቅ የሚገባንን ብቻ ነው፡፡"



"ልታስሩት!...የፈጥኝ አስራችሁ እየገረፋችሁ እያንገላታችሁ ልትገድሉት!" አይኖቿን አጥብባ በጥላቻ ተመለከተችው፡፡ "ለዚህ ነው የፈለጋችሁት እንግዳው!"

"ዓላማ አለን! አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ሌሎችን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የገዛ ሕይወታችንን አሳልፈን ልንሰጥለት የተዘጋጀንለት ዓላማ አለን!"

"ዓላማ ቢስ ናችሁ! አታላችሁኛል ! ሁላችን ተታለናል፡፡ ምንም ቁንጅና የለንም፡፡ ቀንጆዎች አይደላችሁም! ነፍሰ ገዳዮች ናችሁ!"

"ቀንጆ ማለት ደካማ ማለት አይደለም... ቀንጆ ማለት አቅም የለሽ ማለት አይደለም... ራሱን የማይከላከል ቁንጅና የቀትር ሀሃይ ሲወጣ ይረግፋል...ቀንጆዎች ነን... ጠንካሮችም ነን፡፡"

"በምን ተለዩችሁ ከቀድሞዎቹ?...በምን ተለዩችሁ ከከዱተኞቹ?... ሥልጣን ላይ ከተሰገሰጉት እሾሆች በምን ቀለዩችሁ? እናንተም እንደነሱ ትኮስኩሳላችሁ፤ እናንተም እንደነሱ ትናደፋላችሁ፤ እናንተም እንደነሱ እሾህ ናችሁ! ምኑ ላይ ነው ቁንጅናችሁ?"

"ቁልቋልም ጽጌረዳም እሾህ አላቸው...ሁለቱም ይናደፋሉ... ጽጌረዳ ግን ቀንጆ ነው... ጽጌረዳዎች ነን... ጥቁር ጽጌረዳዎች... ጠላቶቻችንን ... ሊቀጥፉን የሚመጡትን እንደ ጽጌረዳ እንናደፋለን... ለሚያደንቁን ግን ውብ ነን... ለሚያሸቱን ጥዑም ነን፡፡"

ፊቷን መልሳ አልጋዋ ላይ ቁጭ አለች፡፡

"ቀንጆ ማለት ደካማ ማለት አይደለም...ራሱን የማይከላከል ቁንጅና..." የሚለው የማርቆስ ንግግር ጆሮዋ ላይ ደወለባት፡፡ እነዚህ ምን ቀንጆዎች ናቸው?...በግድያ የሚያምኑ በእፊና የሰለጡኑ የቀትር ጅቦች!ምናቸው ይታመናል? የሁላም ሀሮች!...ጥላቻዋ ገኖ ይታያት ጀመር፡፡ መቼ ነበር... አዎ ሶስና ለልደት የጋበዘቻቸው ዕለት... ናትናኤልንና እሷን... "የአፍሪካ ጥያቄ የፖለቲካ ጥያቄ ነው፤ የአፍሪካ ነፃነት የሚገኘው በተዋህዶ እንቅስቃሴ አፍሪካ አንድ ስትሆን ነው" ባለችው ጊዜ ናትናኤል ምን ነበር ያላት?ለማስታወስ ሞከረች፡፡ "በአገሮች መካከል ኢኮኖሚያዊ ትብብርና ጥንካሬ መቅደም አለበት፡፡ የፖለቲካው ውህደት ከዚያ በኋላ ነው የሚመጣው... ለአፍሪካ እድገት ቅንጅት ያለው እንቅስቃሴ መኖር አስፈላጊም ቢሆን ሂደቱ ዲሞክራሲያዊ መሆን አለበት፡፡ በዕቅድ የሚመራ ዲሞክራሲ በትምህርትና በልምድ ሲዳብር ይገባል..." ሲል ናትናኤል የተናገራት ትዝ

አሳት፡፡ ርብቃ አንዳች አዲስ ነገር በህሊናዋ ጓዳ ውልብ አለባት፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ናትናኤል ዲሞክራሲያዊ ህብረት ሲል ምን ማለቱ ነበር? አዎን ግልጽ ነው... እነዚህ ራሳቸውን "ቀንጆ" ያሉት ሰዎች የሚከተሉት መስመር ይሄ አይደለም፡፡ "እነሱ የሚያምኑት በኃይል ነው፡፡ ዲሞክራሲ ማለት ለነሱ ዝም ብሎ ለአፍሪካ መቆርቆር ነው... አፍሪካ አንድ ትሁን ሲሉ በኃይል እንጠቀም ማለታቸው መሆኑ በእኩይ ተግባራቸው ይታያል...አይሆንም አይሆንም ... ልክ አይደሉም... ወይ ናትናኤል...ናቲ... ናቲ... ልክ ነህ... ናቲ..." በእጆቿ ራሷን ቀብራ በሃሳብ ጭልጥ ካለችበት ስትመለስ የግንዛቤዋ የቀስ በቀስ ሂደት መከሰት ስሜቷን ነካው፡፡ ጩሂ ጩሂ አሰኛት፡፡

"ረጋ ብለሽ አዳምጪኝ... እንዳልኩሽ ልንጎዳው አንፈልግም... ግን ደግሞ በደመነፍስ ያለዕውቀት ጥፋት ለማድረስ ሲሯሯጥ ዝም ብለን ልንመለከተው አይገባም... የያዝነውን ዓላማ ስላልተረዳ ብቻ ወላታችን ሆኗል..."

"አስሬ ይሆናል የነገርኳችሁ...በየሳምንቱ በምጽፈው ሪፖርት ላይ... 'ይመልመል... ብቁ ነው ይመልመል' ብያችኋለሁ!"

"ርብቃ ያንን አላውቅም... ውሳኔ የሚሰጡ ሌሎች ናቸው... ዋናው ነገር አሁን ባለማወቅ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል...ንገሪኝ...የት ነው ያለው?"

"አላውቅም! እየፈለግነው ነው የምትለኝ ውሸት ነበር ማለት ነው?እየደወልኩ ጠፋ ስልህ አላመንከኝም ማለት ነው!"

"ውሸትሽን ነው፡፡"
"አላውቅም አልኩህ አላውቅም! ...ውሸቱን አይደለም፡፡"

"አስታውሺ...ከናትናኤል ጋር ያገናኘሽ የእኛ ዓላማ ነው፡፡ አንቺ ግን አላማሽን ረስተሽ ለስጋ ፍላጎትሽ ተሸነፍሽ..." አይኖቹን አሳንሶ በንቀት ቁልቁል ተመለከታት፡፡ "የት ነው ያለው...ንገሪኝ፡፡"

"ዓላማችሁ ነፍስ መቅጠፍ መሆኑን ባውቅ ኖሮ! አላማችሁ ሕይወት ማጨለም መሆኑን ባውቅ ኖሮ አላማዬ ብዬ አልይዘውም ነበር፡፡"

"ምንድን ነበር የጠበቅሽው? ፌሽታ? ጭፈራ?...አትሞኚ... ከግባችን ለመድረስ የግድ ደም መፍሰስ ካለበት ይፈሳል...ምርጫ የለንም፡፡" አጠገቧ አልጋዋ ላይ ተቀምጦ ትከሻዋን በሁለት እጆቹ ይዞ ትክ ብሎ ተመለከታት "...አስታውሽ የጋናው ነቢይ ያለውን፡፡ ... ደህንነታችን አንድነታችን ነው... ከዚያ ውጪ ደህንነት የለንም፡፡ በዚህ ሰዓት ከዓላማሽ ማፈግፈግ አትችይም... ክህደት ነው፡፡"



ቀና ብላ አትኩራ ተመለከተችው፡፡

"...እመኚኝ... አንጎዳውም... ጊዜው ደርሷል... ያኔ ነፃ ይሆናል፡፡ ለትንሽ ጊዜ አንድ ቦታ ሰውረን እናስቀምጠዋለን... ምንም አናደርገውም... የት ነው ያለው?"

"ነገርኩህኮ እኔ ራሴ የት እንዳለ አላውቅም፡፡"
"እደውልልሻለሁ ማለቱን አስታውቀሽ ነበር፡፡"
"አዎ፡፡ ብሎኝ ነበር... ግን አልደወለልኝም፡፡"
"ለምን? እንዴት አልደወለም? ምሥጢሩን አውጥተሻል ማለት ነው፡፡"
"ባወጣሁት በነገርኩት ደስ ባለኝ ነበር!" አለችው በጥላቻ እየተመለከተችው፡፡

"እርጉዝ ነሽ? " ድንገት ጠየቃት፡፡ ቃናው ጥያቄ ሳይሆን ትዝብት መሰላት፡፡

ደነገጠች፡፡ 'እንዴት ደረሱበት?'
"ያ የግል ጉዳዬ ነው፡፡" አለች በትቻላት ድፍረቷን አሰባስባ አፍጥጣ እየተመለከተችው፡፡

"የመጨረሻ ዕድል እሰጥሻለሁ፡፡የት ነው ያለው?"
"አላውቅም!"

ድንገት ከትከሻው እንደ ወስፈንጠር ተለጠጠባት፡፡ ከአልጋው ላይ ተፈናጥሮ ተነሳ፡፡ጥርሱን ሲነክስ ጉንጩ ላይ የተጋደመው ጠባሳ በጨረቃዋ ብርሃን ጎልቶ ወጣ፡፡ ራመድ ብሎ ወደ መስኮቱ ሄደና መጋረጃውን ሰብሰብ አድርጎ ከአፓርታማው አጥር ውጭ ወደቆመችው ሲትሮይን ቁልቁል ተመለከተ፡፡ ወዲያው ከግራ የደረት ኪሱ የቅርብ ርቀት መገናኛ ሬዲዮ አውጥቶ ተጫነው-

"ቀንጆዎቹ...ቀንጆዎቹ... ዜሮ አራት... መቀጠል ትችላለህ፡፡" ፊቱን መልሶ በጨለማው ውስጥ አፍጥጦ ተመለከታት፡፡
"ከዳተኛ ነሽ...ባንዳ..." አለ ቅዝቅዝ ብሎ፡፡

ከተቀመጠችበት ሳትንቀሳቀስ በፍርሃት ተመለከተችው፡፡

"...ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ከዚች ክፍል መውጣት አትችይም...ሰውዬሽን...አታስቢ እናገኘዋለን፡፡ እንዳገኘነው እናስወግደዋለን፡፡" ወደ መኝታ ቤቷ በር ራመድ ብሎ በሩን ከውስጥ ቀረቀረው፡፡

"ምን ልታደርጉኝ ነው? እኔንም ልትገድሉኝ አሰባችሁ እንዴ?" አለችው ፍርሃቷን ለመሸፈን እየታገለች::

"አስፈላጊ አይደለም:: አንቺም ታውቂዋለሽ:: አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ መግደል ብቻ ሳይሆን በደስታ የገዛ ሕይወታችንን እንሰዋለን::ከአሁን ወዲያ በዓለም ላይ ማንም አይመልሰንም! ማንም አይቋቋመንም! ተንቀን፤ ተጠልተን፤ ተዋርደን፤ ለባርነት መለያ ሆነን ኖረናል:: ተግዘናል፤ ተሸጠናል፤ ተለውጠናል:: አሁን ግን ያበቃል:: ደህንነታችንን፤ ለይስሙላ ያልሆነ እውነተኛ ነፃነታችንን በአንድነታችን እናገኘዋለን...ቅርብ ነው ጊዜው..."

ወንበር ስቦ ተቀመጠ::

አልጋዋ ላይ እንደተቀመጠች በጨለማው ውስጥ አፈጠጠችበት:: ያለፈው ሁሉ እንደቅዠት እየተዘበራረቀና እየተደራረበ መጣባት...

* * *

ሶስና ነበረች የመለመለቻት...አንድ በአንድ ቀልጭ ብሎ ይታወሳታል... ጓደኛዋ ሶስና ነበረች የመለመለቻት::

ርብቃ ሶስናን የምታውቃት በዩኒቨርስቲ ዓመቶቿ ነው:: ሁለቱም የቋንቋ ተማሪዎች ነበሩ:: ከትምህርት ዓለም ተሰናብተው ወደ ሥራ ዓለም ሲሸጋገሩ ሶስና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ርብቃ ደግሞ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሥራ ያዙ::

የሥራ ቦታቸው መለያየት ሊለያያቸው የሚችል ቢሆንም አልተራራቁም:: ቢያንስ በሣምንት አንዴ እየተገናኙ አብረው ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር:: በመጨረሻም የለያያቸው ሶስና በአንደኛ ፀሃፊ የሥራ መደብ ካይሮ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ መሄዷ ነበር::

ባለፈው ዓመት መጨረሻ ገደማ ላይ ነበር:: ከሥራ ሰዓት በኋላ ዘወትር እንደሚያደርጉት ቀጠሮ ተሰጣጥተው ተገናኝተው ሲጫወቱ አመሹ:: ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ሶስና ድንገት ተነስታ ቀጠሮ እንዳላት ስትነግራት ርብቃ አዲስ ነገር ሆነባት::

"በዚህ ሰዓት?" አለች መምሸቱን ተመልክታ::
"አዎ ርብቅዬ... ማታ ማታ ነው የምንገናኘው::"
"ማነው ባክሽ?" አለች ርብቃ እየተሽከረመመች::



"አ! ወንድ መስሎሽ ነው እንዴ ... አይደለም... ጓደኞቼ ናቸው::"
"እኔ የማላውቃቸው ጓደኞች! ሂ! ሂ! ሂ!" ርብቃ ሳቀች ጓደኛዋ የደበቀቻት ምሥጢር እንዳለ በማመን::

"ርብቃ ሙች... እንዳሰብሽው አይደለም:: ምን መሰለሽ... በእርግጥ አታውቂያቸውም:: እኔም ቅርብ ጊዜ ነው የተዋወቅኋቸው... እና ... አልፎ አልፎ ተገናኝተን በተለያዩ አርዕስቶች ላይ እንነጋገራለን::"

"ምን ልትፈጥሩ?" አለች ርብቃ ጓደኛዋ የምትለው መላቅጡ ሲጠፋት::

"የተሻለ ዓለም!" አለች ሶስና ጓደኛዋ ትኩር ብላ እየተመለከተቻት "... ምን መሰለሽ ..." አለች የርብቃን መደናገር ስታይ:: "በአንድ ርዕስ ላይ ስትከራከሪ የተለያዩ ሃሳቦችን ታገኚያለሽ:: ጭንቅላትሽ ይሰፋል አስተሳሰብሽም ይዳብራል::"

"እና ለመከራከር ተቀጣጥራችሁ ትገናኛላችሁ ማለት ነው?"

"አዎ:: አንድ ርዕስ እንመርጥና እንዘጋጅበታለን:: ለምሳሌ...ስነጽሁፍ ...ወይ...ኋላቀርነት... ወይ... አፍሪካ... በቃ አንድ ርዕስ... ከዛ በርዕሱ ላይ እያንዳንዳችን እንዘጋጅና ተገናኝተን የሰበሰብነውን እንለዋወጣለን፤ እንከራከራለን::"

"ጥሩ ነው ሃሳቡ::" አለች ርብቃ ቦርሳዋን እያነሳች:: "በይ ከሄድሽ ቶሎ እንሂድ:: እንዳይመሽብሽ::"

"ለምን አብረን አንሄድም?"
"የት?!" አለች ርብቃ ጓደኛዋ ላይ አፍጥጣ::
"እሁን ያልኩሽ ቦታ ነዋ::"
"አበድሽ እንዴ? ደግሞ እኔ ምንድነኝ? አንቺኮ ጓደኞችሽ ስለሆኑ..."

"አይደለም- አይደለም:: ባይገርምሽ አብዛኛዎቻችን የተዋወቅነው እዛው ነው:: እየሽ እያንዳንዱ አባል ብስሉ አለው የሚለውን ሰው መጋበዝ ይችላል::እና ተጋባዡ አንድ ፕሮግራም ይካፈልና ከጣመው አባል ይሆናል::"

"ሌላ ጊዜ::" አለች ርብቃ የጓደኛዋን ክንድ ይዛ ከነበሩበት ቡና ቤት እየወጡ::

"ለምን? ነይና እይው:: ምንም መናገር አያስፈልግሽም:: ዝም ብለሽ ተቀምጠሽ እኛ ስንወያይ ታዳምጫለሽ:: እንዳልኩሽ ፕሮግራሙ የሚጠቅምሽ ከመሰለሽ... እያየሽ ትቀጥያለሽ:: ማን ያውቃል... ብዙ ነገር ታስተምሪን ይሆናል:: ጋዜጠኛ መሆንሽን ሲያውቁማ ወጥረው ነው የሚይዙሽ::" ሶስና ገፋፋቻት::

"ጋዜጠኛ ለፍላፊ ነው ለማለት ነው... ብሽቅ!" አለች ርብቃ ጓደኛዋ የወትሮውን ብሽሽቅ የጀመረች መስሏት::

"አይደለም... አየሽ ... ጋዜጠኞች በተለያዩ አርዕስቶች ላይ ስለምትሰሩ ከተራው ሰው የተሻለና ሰፋ ያለ እውቀት ይኖራችኋል:: ይህ ደግሞ የሚያከራክር አይደለም:: የኛ ጋዜጠኞች ደግሞ ዋዛዎች አይደላችሁም...::"

"እ...እ"

"ሙች - ሙች ከምሬ ነው:: ሌላውን ብንተወው እንኳን... ለየግላችሁ ያላችሁ ዕውቀት የሚናቅ አይመስለኝም:: ብቻ አስቲ ነይና እይው::"

"ኧረ በናትሽ ሳይጠሩኝ ሰተት ብዬ ቤታቸው ስሄድ ምን ይሉኛል?"

"በደስታ ነው የሚፈነድቁት... ርብቃ ሙች! አዲስ ሰው በመጣ ጊዜ ምን ያህል እንደምንደሰት ብታውቂ... አዲስ አስተያየት! አዲስ አመለካከት ማለት ነው!"

"ግን ታመሹ እንደሆነ?"

"ምንም ችግር የለም:: መኪና የሚይዙ ስላሉ ሁላችንን በየቤታችን የሚጥሉን እነሱ ናቸው:: እሱ አያሳስብሽ...እሺ በቃ እንሂድ... እሺ?" ውጥር አድርጋ ያዘቻት::

"ግን... እንጃ..." እያለች ነበር ርብቃ ለመሄድ የተስማማችው::

ታክሲ ተሳፍረው በንፋስ ስልክ መስመር ወደ ጎተራ አቅጣጫ አመሩ:: መሃል ላይ ሶስና "እዚህጋ ይበቃናል::" ብላ ታክሲውን አስቁማ ሲወርዱ ሊጨልም ዳድቶት ነበር:: አንድ ሰዓት ከአሥር::

"አርፍደናል!ከአንድ ሰዓት በፊት መገኘት ነበረብን::" አለች ሶስና ከዋናው መንገድ በስተግራ ተገንጥሎ ሽቅብ ወደሚወጣ መንገድ እያመራች::



ጎን ለጎን እየተራመዱ በዝምታ ቀጠሉ:: ከአንድ ግራጫ ቀለም ከተቀባ የብረት በር አጠገብ ሲደርሱ ሶስና ጠጋ ብላ መጥሪያውን ተጫነችው::

አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላት ትንሽ የስርቆሽ በር ተከፈተችና አንድ ሰው አጮልቆ ተመለከታቸው:: ሶስና ምንም ሳትናገር ጠጋ ብላ ፊቷን አሳየችው:: የስርቆሿ በር ተዘጋችና ዋናው የብረት በር ተከፈተላቸው:: ገቡ::

ርብቃ ከማታውቀው ቤት ሳትጠራ በመምጣቷ እፍረት ቢሰማትም ውስጥ ገብታ ጉዷን እስክታየው ቸኮለች:: ከፊት ለፊት ያለው ቤት ትልቅ ሳይሆን ቀልበጭ ብሎ በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ይመስላል:: ምናልባት በቅርብ ጊዜ የተሰራ ስለሆነም ሊሆን ይችላል:: ከፊት ለፊት የሚታዩት ሁለት መስኮቶች ተዘግተዋል!በግቢው ውስጥ ከጥግ እስከጥግ እንደምንጣፍ የተነጠፈው አስፋልት መሐል የሚታይ የእትክልት ዘር የለም:: ቤቱ ሕይወት ያለበት አይመስልም::

የገዛ ቤቷ እንደሆነ ሁሉ ሶስና "ነይ:: አይዞሽ አትፍሪ..." እያለች የዋናውን ቤት የፊት በር ከፍታ ገቡ:: ከውስጥ የተቀበላቸው ጨለማ ነበር:: በጠባቧ መተላለፊያ ውስጥ ባለው ደብዘዝ ያለ ብርሃን ሦስት የተዘጉ በሮች ይታያሉ:: ስልክ የተቀመጠበት ትንሽ ጠረጴዛና ወንበር ጥግ ይዘዋል:: በተረፈ ምንም የለም:: ድንገት የታፈነ የሚመስል ድምፅ በስተቀኝ በኩል ካለው በር ጆርባ መጣ:: ሰዎች የሚነጋገሩ ይመስላል - በለሆሳስ::

"ነይ እንጂ..." አለች ሶስና በስተቀኝ ወዳለው በር እያመራች:: ርብቃ ከተል አለቻት::

ከውስጥ የተቀበላቸው ክፍል ከመተላለፊያው የተሻለ ብርሃን ያለበት ቢሆንም እዚያም ያለው ጨለማ ለአይን የሚከብድ ነበር:: እራቅ ካለ ማዕዘን የቆመው ባለ ረጅም ቋሚ መብራት ድብዝዝ ያለ ብርሃን ይተፋል:: ከቋሚ መብራቱ ቀይ ጨርቅ የሚፈሰው ብርሃን ቤቱን ፍም አስመስሎታል::

"ይቅርታ ስላረፈድን:: እንደምን ዋላችሁ::" አለች ሶስና በደፈናው::

በሳሎን ክፍሉ ውስጥ ሰዎች ተቀምጠዋል:: ወዲያ ማዶ የተዳፈነው ቀይ ብርሃን አጠቃላይ ቁመናቸውን እንጅ ገፃቸውን ጥርት አድርጎ አያሳይም::

"ዛሬ አዲስ እንግዳ ይዤ ነው የመጣሁት::" አለች ሶስና የርብቃን እጅ ይዛ ወደ ሳሎኑ እየተጠጋች::

ማናቸውም ድምፅ አላሰሙም:: በተቀመጡበት ጭንቅላታቸውን እያንቃነቁ ስምምነታቸውን ሲገልፁ ርብቃ በጨለማ ውስጥ ሸንጎ የተቀመጡ አማልክት መሰሏት::

ሶስና ከማናቸውም ጋር አላስተዋወቀቻትም::የርብቃንም ስም አልተናገረችም:: አንድ ፎቴ ላይ እንድትቀመጥ ካመለከተቻት በኋላ ከወደጥግ ካለ ጠረጴዛ ላይ ወደ ተቀመጠች አነስተኛ ማቀዝቀዣ ሄዳ ከፈተቻት:: ለአንድ አፍታ ከማቀዝቀዣዋ ውስጥ የወጣው ብርሃን በሳሎን ክፍሉ ውስጥ ሲናኝ ርብቃ ከፊት ለፊቷ የተቀመጡትን ሦስት ሰዎች ተመለከተቻቸው... ሁለቱ ወንዶች ሲሆኑ በስተቀኝ ዳር ያለችው ሴት ነች... በስተግራዋ የተቀመጡትን ሰዎች ግን ለመመልከት አልቻለችም:: የማቀዝቀዣዋ ብርሃን ከጀርባቸው ነበር::

ወዲያው ሶስና ማቀዝቀዣዋን ስትዘጋ ክፍሉ በቀድሞው ጨለማ ውስጥ ሰመጠ:: ሶስና ከማቀዝቀዣዋ ውስጥ ያወጣቻቸውን ሁለት የኮካኮላ ጠርሙሶች ይዛ ከጠረጴዛው ላይ ከተደረደሩት ብርጭቆዎች መሃል ሁለቱን አንስታ ይዛ ተመለሰችና ርብቃ ጎን ተቀመጠች::ጠርሙሶቹን ከፍታ ከቀዳች በኋላ ቀና አለች::

"ይቅርታ...አቋረጥናችሁ...?"

"ችግር የለም:: ገና ስንጀምር ነው የደረሳችሁት::" አለ ፊት ለፊት የተቀመጠው ሰው:: ድምፁ ረጋ ለዘብ ያለ ነው:: ወዲያው በስተግራ ወደተቀመጠው ሰው ዞር አለና... "እሺ ቀጥል::" አለ::

"እዎ... እና ...እንዳልኩት ሁላችንም ባርያዎች ነን..." አለ በስተግራ የተቀመጠው ሰው በጨረፍታ የተኮለኮሉትን ሁሉ በተራ እየተመለከተ "ባርያ!" አለ ድጋሚ ጮክ ብሎ:: "የካሊፎርኒያው ነጭ የስነልቦና ሊቅ አርዘር ጆንሰን እንዳለው በዝቅተኛ የአእምሮ የዕድገት ደረጃ ላይ በሰውና በዝንጀሮ መሃል የምንገኝ ፍጡሮች ነን እኛ አፍሪካውያን:: ይህንን ባንቀበል ደግሞ ተጨማሪ ድንቁርና ይሆንብናል:: ማለቴ - ባርነታችንን:: እዚህ ላይ ባርያ ስል ማስተዋል የጎደለው በራሱ ሊቆም የማይችል አሳፋሪ ዝርክርክ ተቀጥላ ፍጡር ማለቴ እንጅ ምናልባት እንዳንዶቻችሁ እንደምታስቡት ጥቁርና ለንቦጫም ማለቴ አይደለም:: በፍጹም! እስቲ አዲስ የመጣችውን ልጅ አንድ እንቆቅልሽ ልጠይቃት..." አለ ሰውየው ድንገት ወደ ርብቃ ፊቱን መልሶ:: "አስቢው! ይታይሽ! የገዛ ክርሱን ሊሞላበት ከውጭ የሚጠብቅ፣ የገዛ ገላውን ሊሸፍንበት ከውጭ የሚጠብቅ፣ በባዕድ ዳንኪራ እየረገጠ እርስ በርሱ የሚናከስ ዝንጀሮ ማነው? ንገሪኝ! ለሰዛ አገር ስጪኝ!" ጮኸባት::

ርብቃ ተማታባት::

"አለቀ!" አለ አለመናገሯ ስምምነት እንደሆነ ሁሉ:: "አፍሪካዊ ነው - ባርያ!"

ለአንድ አፍታ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ነገሠ::



"እንቆቅልሹ ለእኔ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ 'አፍሪካዊ' ሳይሆን ኋላቀር ህዝብ እለው ነበር መልሱን::" አለ በስተግራ ከተቀመጡት ሰዎች ሁለተኛው:: "በዓለማችን ላይ ኋላቀር የሆነን ህዝቦች ደግሞ እኛ አፍሪካውያን ብቻ ነን ለማለት ያስቸግራል::"

ደቂቃዎች እየተሽቀዳደሙ በነጎዱ ቁጥር ክርክሩ እየጦፈ የተናጋሪዎች እልህ እየጋመ ሲመጣ ርብቃ በገዛዎ ታ አንድም ሳይቀራት ተከታተለቻቸው:: ዝግጅቱ አልቆ ሲበተኑ ሶስና አብረው እንዲያድሩ ስለጠየቀቻት ከተሰብሳቢዎቹ መሃል አንደኛው ሁለቱንም በመኪናው ሶስና ቤት ድረስ አድርሷቸው ተሰናብቷቸው ተመለሰ::

ሶስና የቤቷን በር ከፍታ እስኪገቡ አልተነጋገሩም ነበር::

"ሶስና...ግን ያ ሰውዬኮ እውነቱን ነው:: መጀመሪያ ሲናገር በጣም ነበር ያበሸቀኝ:: ማለቱ... 'ባርያ ነን' ሲል:: ግን በኋላ ባሰበው የጨፈነኝ አጉል ኩራት መሆኑ ገባኝ::" አለች ርብቃ ወደ ውስጥ እንደገቡ::

"እንዴት?" አለቻት ሶስና ትኩር ብላ እያጠናቻት::

"አስቢው እስቲ:: እውነቱንኮ ነው:: ባርያ ማለትኮ ልዩ ፍጡር ማለት አይደለም:: የራሱን መብት ማስጠበቅ የማይችል ማለት ነው:: እስቲ የትኛው አፍሪካዊ አገር ነው በሁለት እግሮቹ ቆሜአለሁብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገር? ታዲያ በሁለት እግሩ መቆም ያልቻለ ህፃን ሲሰጡት ከመቀበል ሲከለክሉት ከመነጫነጭ አልፎ በየት አገር ነው መብቱን የሚያስጠብቅ? አንቺ እማምላክን ዛሬም ባርያዎች ነን!" የተናገረችው ለራሷ የቀፈፋት ይመስል ርብቃ እጇን አፏ ላይ ጫነችው::

ከዛን ቀን ጀምሮ በየሳምንቱ ሁለት ሁለት ቀን እዚያው ቤት እየተመላለሰች ለአራት ወራት ዝግጅቱን ስትካፈል ቆየች:: መረቡ እንደ ሸረሪት ድር ከተበተባት አጥማጆቿ እንዳቀዱት አፍሪካዊነቷ ነፍስ ዘርቶ እንደ ሽል ሆዷ ውስጥ መገለባበጥና መራገጥ ከጀመረ በኋላ ነበር ሁኔታው የተገለፀላት::

ለአራት ወራት አብረዋት ተቀምጠው ሲከራከሩና ሲፋተጉ የነበሩ ሁሉ ይሰሩት የነበረው ቲያትር መሆኑን የተገነዘበችው እጅግ ዘግይታ ነበር:: ሁሉም የያዙት አቋም አንድ ነበር::ወክለው የሚከራከሩት ወግነው የሚፋተጉት ግን የእሷኑ ህሊና ግራና ቀኝ ነበር:: ሳታውቀው ሳትገነዘበው መረባቸው ውስጥ ገባች:: አይኖቿ በሩላት:: እሷም እንደ አጥማጆቿ ሌሎች አይናቸው ያልበራላቸውና አይናቸው የሞጨሞጨ አስቀያሚዎች ሲመጡ -

"ባርያ! ባርያዎች ነን!" እያለች እልህ ዘራች፤ቁጭት አበቀለች፤ አፍሪካዊነት አጨደች፤ቆንጆዎች አመረተች።

ስብሰባውን መካፈል በጀመረች በሰባተኛው ወር ነበር በህቡዕ ድርጅቱ ውስጥ በአፍሪካዊነቷ ልታገለግል በሙሉ ልብ ቃል የገባችው። መጀመሪያ ቀን በተሰበሰበችባት ጨለማ ክፍል ውስጥ...

በክፍሉ ውስጥ የእሷው ብጤ አዲስ ተጠማቂዎች ተሰብስበዋል - ስምንት። ሌሎች የማታውቃቸው እንግዶችም በሥነሥርዓቱ ላይ ተገኝተው ነበር። ክፍሉ ውስጥ በአጠቃላይ ያለው ሰው ሃያ ይደርሳል። አብዛኞቹ በእርሷ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ መሃል ፎቴው ላይ ቦታ የተሰቀቀላቸው አራት ሰዎች ግን በዕድሜ የገፉ ነበሩ።

ሰዎቹ የተገኙት ዝግጅቱን ለመምራትና አዲስ አባላቱን ለመቀበል ነበር። ርብቃ በደብዛዛዋ ብርሃን ውስጥ ተመለከተቻቸው። ሦስቱን ሰዎች በፍጹም አታውቃቸውም... በግራ በኩል ጥግ ላይ የተቀመጡትን አንደኛውን ሰው ግን ለይታ ስማቸውን ባትጠራም ከዚህ በፊት መልካቸውን ማየቷ ትዝ ይላታል። ቢሆንም የት እንደሆነ ልታስታውስ አልቻለችም።

ዝግጅቱ እንደተጀመረ ከአራቱ አዛውንት አንደኛው ንግግር አደረጉ።

"ከሰላሳ ዓመታት በፊት በ1963 አዲስ አበባ ላይ ከየአትጣጫው የተሰበሰቡ የጥቂት ነፃ አፍሪካ አገሮች መሪዎች ስብሰባ ላይ ተገኝቼ ነበር። ያኔ እኔም እንደ እናንተ ገና ትኩስ ጎልማሳ ነበርኩ።" አሉ ከተቀሩት ሦስት አዛውንት በዕድሜ ላቅ ያሉ የሚመስሉት የመሃለኛው። ደብዛዛው ቀይ ብርሃን በትልምና በደረጃ በተከፋፈለው ፊታቸው ላይ ሲያርፍ የቀለጠ ነሃስ አስመስሏቸዋል። ቀዩ ብርሃን ሲነካው ዝገት የሚመስለውን ሽበት የበዛበት ፀጉራቸውን ...እንደ ጧፍ የሚንቀለቀለውን አይናቸውን በእምቢተኝነት ቀጥና ቀና ያለ ትከሻቸውን ስትመለከት ርብቃ ሃውልት መሰሏት፤ቅርስ።

"ያኔ..." ቀጠሉ ፊታቸው የሃዘን ፈገግታ ለብሶ።"ያኔ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የተስፋ ጸዳል ይንቀለቀል ነበር...ያኔ ...ጠንካራ አፍሪካን ገንብተን ከሌላው የሰው ዘር ጋር ትከሻ ለትከሻ ልንቆም እርግጠኞች ነበርን። ከሰላሳ ዓመታት በፊት...ድሮ። በስብሰባው ላይ የአፍሪካ አባት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተናገሩት ምን ጊዜም ከአእምሮዬ አይጠፋም። 'አንድነታችን ከጊዜ ጋር የምንቀዳጀው ነው። በቀን ተቀን በምናደርገው እንቅስቃሴ... ጠንካራ መሠረት ከጣልን... ግንበኛውና መሣሪያው ከሰጠ... ጠንካራ ቤት እንገነባለን።' ነበር ያሉት። ሰላሳ አመታት አለፉ። ያ ቤት አሁንም አልቆመም። ይብሱን የተጣለው መሠረት ይሰነጣጠቅ ጀመር፤ የግንበኛው አላዋቂነት ይሆን ወይስ ግንበኞች በዙ? ልባም ሠራተኛ ጠፋ? ወይስ በጣሽ ቀጣዩ ሂያጅ መጪው ፈላጭ ቆራጩ በረከተ?"



የክፍሉ ፀጥታ ከመቃብር ከበደ።

"በዛን ወቅት መንገዱን አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ነበር።" ሰውየው ቀጠሉ... "የአፍሪካው ልጅ፤ የጋናው ነብይ ንክሩማ... 'ዋ! ነበር ያለው ዋ! ከፊታችን የተጋረጠውን የአፍሪካ ችግር ተባብረን በአንድነት ከመጋፈጥ ወደኋላ ብንልና ተበታትነን ብንቆም በድጋሚ በሌላ የቅኝ ግዛት ስር ወድቀን ለከፋ ምሬትና ሰቆቃ መከተል መሣሪያ እስክንሆን ድረስ እርስ በርሳችን ስንነካካተልና ስንበጫጨቅ እንቆያለን።' ነበር ያለው።"

"ተሳስቶ ኖሯል ያ ሰው? ተሳስቶ ኖሯል ያ ነብይ?"

ሽማግሌው መልስ ይፈልጉ ይመስል በክፍሏ ውስጥ የተሰበሰቡትን ሁሉ በተራ ተመለከቷቸው። ተጠባበቁ። መልስ አላገኙም።

"ዛሬ ምን እያደረግን ይሆን?!ያ ሰው እንዳለው እርስ በርሳችን እየተገናተልን አይደለም? ዛሬ ምን እያደረግን ይሆን? እርስ በርሳችን እየተበጫጨቅን አይደለም? ያኔ ከዋሜ ንክሩማን ተቃውመው የቆሙ የሪጅናል ውህደት አቀንቃኞች የጥንቃቄና የእርጋታ መከኮሳት የት ገቡ? ዛሬ ምን ይላሉ? ምነው ድምፃቸው ጠፋ? በከፋ የቅኝ ግዛት ስር፤ በረሃብና በድንቁርና ስር በእንብርክ የሚድኸው የዛሬው የአፍሪካ ህዝብ 'ተጠየቁ' ቢላቸው 'ያ ሰው ተሳስቶ ነበርን?' ቢላቸው ምን ይሆን መልሳቸው?"

አዛውንቱ ለአፍታ አቀርቅረው ቆዩ። መልሰው ቀና ሲሉ ፊታቸው እልህና ቁጭት ለብሶ ነበር።

"ለወቀሳ ጊዜ የለንም፤ለቁጭት ጊዜ የለንም፤ለምሬት ጊዜ የለንም፤ሰላሳ ዓመት አምጠናል። እንወልዳለን ቆንጆ ቆንጆ ልጆች። ዛሬ እዚህ የተሰበሰባችሁ ሁሉ አዋላጆች ናችሁ። አዲስ የመጣችሁትን እንኳን ጨለማው ተገፈፈላችሁ እላለሁ። በተረፈ ከፊት የምንጋፈጠውን ሁሉ በሙሉ ልብ ልትቋቋሙት ቃል ትገባላችሁ።"

ርብቃ የገባችው ቃል ምን ያህል አስፈሪና ጥልቅ እንደሆነ እየሰረፀባት የመጣው ጊዜ ከሄደ በኋላ ነበር።

"ብዙ አወራሁ" አሉ ሽማግሌው ዝግጅቱ አልቆ ሲሄዱ ሲነሱ "ስለአፍሪካችን ሲነሳ ብዙ ዝም ማለት ይቀናኛል። እኔ ብቻ ሳልሆን እኩዮቼ ሁሉ በዕድሜያችን ያየነው ልሳን የሚያደርቅ ነው። ዛሬ ግን ሃላፊነቴን መወጣት ነበረብኝ። ብዙ አወራሁ። ይበቃል።"

ተነሱ።

በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ተነስተው ቆሙ:: ሰውየው በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በተራ ጨብጠው ሲያበቁ አብረዋቸው ከመጡት በዕድሜ ከሚቀርቧቸው ሰዎች ጋር ተከታትለው ወደ በሩ አመሩ:: ከክፍሉ ከመውጣታቸው በፊት ቆም አሉና በክፍሉ ውስጥ ሰብሰብ ብለው በአክብሮት የሚመለከቷቸው ወጣቶች ላይ አተኮሩ...

"ተጠንቀቁ!" አሉ አዛውንቱ ፈገግ ብለው:: "እዚህ ያወራነውን ጮክ ብላችሁ አታውሩ:: አፍሪካችን ተኝታለች:: እንዳትባንን::"

ርብቃ ወዲያው የተሰጣት ትዕዛዝ ወይም ኃላፊነት አልነበረም:: "ጊዜው ሲደርስ ...ስትፈለጊ ትጠሪያለሽ::" ተብላ ቆየች:: ቢሆንም በወር አንዴ እሷ የምትገኝበት ሀቡዕ ህዋስ በሚያደርገው ስብሰባ ላይ እየተገኘች ስለአፍሪካ ሁለገብ ችግር የሚደረጉትን ውይይቶች ስትካፈል ቆየች::

ከሁለት ወር በኋላ ነበር የመጀመሪያው ትዕዛዝ በምሥጢር የተላለፈላት:: በሬድዮ "የአፍሪካ ምጣኔ ሃብት" በሚል ርዕስ ሣምንታዊ ፕሮግራም እንድታዘጋጅ ተነገራት:: በመጀመሪያ ሃሳቡን ለአለቃዋ እንዴት እንደምታቀርብ ቸግሯት ነበር:: ነገር ግን በማግስቱ አለቃዋ እራሳቸው አቢሮአቸው ድረስ አስጠርተዋት ማክሰኞ ማታ የሚቀርበው የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ስለሚቋረጥ በምትኩ ሊቀርቡ የሚችሉ ፕሮግራሞች ሰብስቢና እንነጋገርባቸዋለን::" አሏት::

ደነገጠች:: ነገሩ ገባት:: አባል የሆነችበት ህቡዕ ድርጅት ምን ያህል ውስጥ ለውስጥ ስር የሰደደ እንደሆነ ተገነዘበች::

"እ ... የአፍሪካ ምጣኔ ሃብት ... ላይ..." አለች ሳታውቀው::

"ግሩም!" አሉ አለቃዋ ፈገግ ብለው ከመቀመጫው እየተነሱ እየጨበጧት:: "በርቺ:: ማንኛውም ችግር ቢገጥምሽ ቀጥታ እኔጋ ነይ:: አይዞሽ::"

ከአለቃዋ ቢሮ ስትወጣ ጉልበቶቿ እየተብረከረኩ ነበር:: ሃላፊነቱ ከወፍጮ ከብዶ ታያት::

*ሁለተኛው ትዕዛዝ ከሁለት ወራት በኋላ ተከተለ::*
*"እና ምንድነው ማለት ነው የማደርገው?"*

"ባጭሩ በፈለግሽው መንገድ ... በእህትነትም ሆነ በሌላ ታጠምጅዋለሽ...እንዳልኩሽ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በአፍሪካ ጉዳይ ቢሮ ውስጥ ሁለተኛውን ወንበር የያዘ ሰው ነው::እያንዳንዱን ነገር ለማግኘት



እንፈልጋለን::በተቻለሽ አለቢው... አ...ቢቱ ይዟቸው የሚመጡ ወረቀቶችን አጥኚ:: ያገኘሽውን ሁሉ:: ከዚህ በተረፈ...በየጊዜው ተጨማሪ መመሪያ ይተላለፍልሻል::" የህቡዕ ህዋሷ መሪ ነበር - ማርቆስ::

"እንዴት ነው ሰውየውን የማገኘው? ማለቴ ..."

"የሚቀጥለው ቅዳሜ ሶስና 'የልደት በዓሌ ነው' ብላ ትጠራሻለች ... ግብዣው ላይ ትገኛለሽ ... አብረው ስለሚሰሩ እሱንም ትጠራዋለች:: ታስተዋውቅሻለች:: ከዚያ በኋላ እኔና አንቺ እየተረዳዳን እንቀጥላለን::" ትከሻዋን ቸብ አድርጎ ተነሳ "በነገራችን ላይ የሰውዬሽ የምሥጢር ስም 'ዱርዬው' ነው:: ገባሽ? 'ዱርዬው' " አለ ማርቆስ በጠባሳ የተገመሰ ፊቱን በቀኙ ፈቱግ አድርጎ "ተግባባን?"
"ገባኝ::"

እንደተባለችው ሶስና በልደት በአሏ ላይ አስተዋወቀቻቸው:: ናትናኤልን "ዱርየው"ን የህዋሷ መሪ ማርቆስ እንዳላት መረቧን ዘርግታ ፍቅረኛዋ አደረገችው:: ሰርስራ ሕይወቱ ውስጥ ገባች:: ምስጢሯን ነግራው 'ምሥጢርህን' አለችው:: ያገኘችውን ሁሉ አሳልፋ ሰጠች:: ጊዜ ሲሄድ እሷው የዘረጋችው መረብ እሷኑ ተበተባት፤ አደናቀፋት፤ ወደደችው:: ሆኖም ሳታቋርጥ ለቡድኑ መረጃዎችን ስታቀብል ቆየች:: ይህ ብዙም አላሳሰባትም:: ምክንያቱም ናትናኤል ለአፍሪካ የነበረው ግለት ከማናቸውም የደበዘዘ አልነበረም:: ስለዚህም ነበር ለህዋሷ መሪ በሳምንት አንዴ በምታቀርበው ዘገባ ላይ 'ዱርዬው' በህቡዕ ድርጅቱ ውስጥ ቢመለመል ጉዳት እንደማያስከትል ደጋግማ ያመለከተችው:: ለምን እንደፈሩት ባይገባትም ምክሯን ሊጠቀሙበት አልወደዱም:: ቢሆንም እንደዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ ይገባሉ ብላ ጠርጥራም አታውቅ:: 'ናትናኤልን እንደ ወንጀለኛ ማሳደድ! መጀመሪያ ነገር ነፍስ ማጥፋትንስ ምን አመጣው? ጓደኛየውንስ ለምን ገደሉት? ፈጣሪዬ የት ገብቶ ይሆን የተሰወረው? እውነት ቢያገኙት አይጎዱትም ይሆን? እንዴት ልታምናቸው ትችላለች? ቢገድሉትስ? ቢቀር ይሻላል:: እንዲያይዙት ብትረዳቸውና አይኖቿ ስር አንድ ነገር ቢያደርጉትስ? ገብሬልዬ! ግን ደግሞ ራሳቸው ፈልገው ቢያገኙትስ?' ዘገነናት:: ዘገነናት ያለፈው ትዝታ ሁሉ መጣባት::

እና ቀና ብላ ተመለከተቻው በሩ አጠገብ ካለ ወንበር ላይ ተቀምጦ እያከታተለ በላይ በላዩ ሲጋራ የሚያጨሰውን ሰው:: በትዝብት መልሶ ተመለከታት:: 'ባንዳ!' ያላት መሰላት ድጋሚ::

"ማርቆስ" አለችው አይኖቿ ላይ እንባዋ አቆርዝዞ፤ "ማርቆስ ግን ምን አደረጋችሁ? ናትናኤልኮ ምንም አያውቅም:: ማርቆስ እውነቱን ነው፤ ምንም አያውቅም:: እመነኝ አብረን ብዙ ሰርተናል:: እውቅሃለሁ ታውቀኛለህ:: አልዋሽህም:: ምንም አያውቅም ናትናኤል::"

“ነገርኩሽኮ፡፡ ምንም እንደማያውቅ እኛም ደርሰንበታል፡፡ ግን ሊደርስበት ወደማይገባ ቁልፍ እያነፈነፈ እየተጠጋ ነው፡፡ሊያገኘው ይችላል፡፡ ሰውዬሽ ቀላል ሰው አይደለም፡፡ ምሥጢሩን ካገኘ ደግሞ ዕቅዱ ሁሉ እጁ ገባ ማለት ነው፡፡ያ ደግሞ ለእኔና ለአንቺ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ለአፍሪካ...ውድቀት ነው ብጥብጥ ነው...ሁከት ነው፡፡ማንም ይቅርታ አያደርግልንም፡፡አንድ በአንድ በየአገሩ እየታደንን በየአገሩ እየተመነጠርን እንንጠለጠላለን” ሲጋራውን ምጥጥ አድርጎ ከተቀመጠበት ተነሳና መተርኮሻው ላይ ደፈጠጠው፡፡ “ያ ከመሆኑ በፊት እጃችን መግባት አለበት፡፡ አፍሪካ በደም ከመዘፈቋ በፊት፤ በሺህ የሚቆጠሩ ንፁህ ልጆቿ ከመታረዳቸው በፊት ናትናኤል መያዝ አለበት፡፡”

“ይመልመል ስላችሁ ቢመለመል ይህ ሁሉ አይመጣም ነበር፡፡ ናትናኤል የአፍሪካን ችግር ከማንኛችንም እኩል የተረዳ ሰው ነው፡፡ በራሳችሁ ጥፋት...በገዛ ራሳችሁ ዳተኝነት ዛሬ በማያውቀው ምሥጢር ታሳድዱታላችሁ፡፡ ያኔ ቢመለመል ኖሮ ... እንዳልኳችሁ ቢመለመል ኖሮ...”

“ርብቃ ንገረኝ ካልሽ እነግርሻለሁ፡፡ናትናኤል ያልተመለመለበት ምክንያት አለው -ወኔ ቢስ ነው፡፡ፈሪ ነው ማለቴ አይደለም፡፡ ያንን አሳውቅም፡፡ግን ስልብ ነው፤ለስልሷል ቦቅቡቋል፤ በነጮች ቅራቅንቦ ላሽቋል፡፡ ርብቃ እመኚኝ! በርካታ የናትናኤል ብጤ የተማሩ አፍሪካውያን የአፍሪካን ችግር ሳይረዱት ስለቀሩ አይምሰልሽ ዋጋ ቢስ የሚሆኑት፡፡ የራሳቸው ሚዛን ስለሌላቸው በነጮች መስፈሪያ በነጮች ሚዛን ስለታወሩ ነው...

“ጆሞ ኬንያታ እንዳለው ከዘመናት በፊት ነጮች ክርስትናን እየሰበኩና ስለሰማያዊው መንግሥት እያወሱ 'የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ' እያሉ በግራ ወንጌል አንግበው በቀኝ ጠመንጃ ጨብጠው ገቡ፡፡ 'የምድሩን ተውት'አሉ፡፡ 'ዋናው የሰማዩ ነው' አሉ፡፡ 'ቀኙን ሲያጉኗችሁ ግራውን ስጡ' አሉ፡፡ አመንናቸው፤ተንበርክከን ጭንቅላታችንን ደፋን፡፡ አልፍተውን አላሽቀውን ሲጨርሱ በተርታ አሰልፈው ለባርነት ሸጡን፤ ለዘመናት እንደ በግና ፍየል ጥጃና ግመል ወይፈንና ግመል ላትና ሻኛችንን ደንደስና ፍርምባችንን እያማረጡ ሸጡን፤ ሸመቱን፡፡

“ዛሬ ደግሞ የተገላቢጦሽ ስለዲሞክራሲና ስለሰው ልጅ መብት ሊሰብኩልን ተነሱ፡፡ ያለፈው ሁሉ ተረሳና የሰሩን ሁሉ ተዘንጋና ስለበጎውና ስለትክክለኛው መንገድ ሰባኪዎቹ ዛሬም እነሱው ሆኑ፡፡ ቃል ኪዳናቸውን ሰብረው ወንጌልን በሰበኩበት አፋቸው ገቢያ አውጥተው በዋጋ እንዳልተከራከሩብን ዛሬ ድጋሚ ቅዱስ መስለው 'ረከሳችሁ' አሉን፤ 'የሰው መብት አፍሪካ ውስጥ ተረገጠ' አሉ፡፡ 'አፍሪካ ውስጥ ዲሞክራሲ ድምጥማጡ ጠፋ' አሉ፡፡ እነ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል የዛሬዎቹ ሚሽነሪዎች ሆኑ፡፡ በግራ ዲሞክራሲን በቀኝ ብድርና ዕርዳታ አንግበው ድጋሚ መጡ፤



'የዲሞክራሲን መንገድ አዘጋጁ ጎዳናውንም አቅኑ' አሉ፡፡ 'ኢኮኖሚውን ተውት፤ ተደጋግፎና ተረዳድቶ ስለመስራቱ፤ ስለማደጉና ስለመበልፀጉ አትጨነቁ' አሉ፤ 'ስለኋላቀርነታችሁ አትመራመሩ' አሉ፤ 'መጀመሪያ ዲሞክራሲ' አሉ 'መጀመሪያ የሰው ልጅ መብት'፤ 'መጀመሪያ የራስን ዕድል በራስ መወሰን' አሉ...

“የሚያሳዝነው ግን የእኛ ድጋሚ መታለል ነው፤” ድጋሚ እየተንበረከክን ድጋሚ ጭንቅላታችንን እየደፋን መሆናችን ነው፡፡

“ቴዎድሮስ ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ያለውን ታስታውሻለሽ- 'በመጀመሪያ የሃይማኖት ሰባኪዎችን ትልካላችሁ፡፡ ቀጥሎ እነሱን የሚጠብቅ ቆንሲል፡፡ ቆንሲሉን ለመጠበቅ ደግሞ ወታደሮቻችሁን፡፡ በመጨረሻ አገራችንን ትወስዳላችሁ' ነበር ያለው፡፡ ርብቃ የዛሬም ስልታቸው የተለየ አይምሰልሽ፡፡ ዲሞክራሲን ይሰብኩናል፡፡ ቀጥሎ እሱኑ ማጠናከሪያ ብድርና ዕርዳታ ያጎርፉልናል፡፡ ብድርና እርዳታውን ውጤታማ ለማድረግ ተብሎ ደግሞ በኢኮኖሚያችን ገብተው መሪ ቀያሽ፤ ደጋፊ አማካሪ፤ፈላጭ ቆራጭ ይሆናሉ፡፡ በመጨረሻ አድቅቀውን አላቁጠውን ሲያበቁ ተረጅ ተደጋፊ ለማኝ ተመፅዋች ያደርጉናል፡፡እምቢ ካልንና ተንኮል ሸራቸውን ቀድመን ካወቅንባቸው እርስ በርስ በዘርና በሃይማኖት እያጎናተሉና እያስታጠቁ እያራገቡ ያጨፋጭፉናል፤ ሳንወድ በግድ ያንበረክኩናል፤አንገታችንን ያስደፉናል፡፡ ሃቅና ሀሰቱን አማተው አገለባብጠው እኛኑ እራሳችንን ያስወቅሱናል፤ ሳናውቅ ሳንጠረጥር ነጭ አምላኪ ያደርጉናል፡፡ የነሱ ጨቋኝነት ወደ ጎን ተብሎ እኛኑ 'ጨቋኝና ተጨቋኝ' ብለው ይለያዩናል፡፡

“አፍሪካውያን ለሁለተኛ ጊዜ በነጮች ተበልጠናል፡፡ ለዘመኑ ሃይማኖት ለዲሞክራሲ ለዘመኑ ሚሽነሪዎች-ለነጭ ጋዜጠኞች ተበልጠናል፡፡ ለዘመኑ የኢኮኖሚ ጠረኞች- ለአይ.ኤም.ኤፍ.፤ ለዓለም ባንክና ለሌሎቹ ተንበርክከናል፤ አንገታችንን ደፍተናል፡፡ ዳግማዊ ሞት ሞተናል፤ ዳግማዊ ትንሳኤ ያሻናል፡፡

“ሬሳው - የሚሸትና የሚከረፋው ሬሳው - ያልተማረውና ያላወቀው ምስኪን አፍሪካዊ አይምሰልሽ፡፡ በተማርነውና አወቅን ሰለጠንን ባልነው ይብሳል 'ድሮም ጥቁር...' 'ድሮም አፍሪካ...' ብሎ ነገር በሚጀምረው አወቅሁ ባይ ስልጡን አፍሪካዊ ይብሳል፡፡ ሳንጠረጥር ሳናውቅ ሳንሰማ ሰልበውናል፡፡”

“ለዚህ ነው ናትናኤል ሊመለመል አይችልም ያልኩሽ፡፡ ወኔ የለውም ስልብ ነው ያልኩሽ፡፡ አብሮን ሊሰለፍ የሚችል ለዘመኑ ሃይማኖት ያልተንበረከከ፤ አንገቱን ያልደፋ ኩሩ አፍሪካዊ ብቻ ነው፡፡ 'መጀመሪያ አፍሪካ፤መጀመሪያ የተባበረች አንድ አፍሪካ፤ መከፈል ያለበት ሁሉ ይከፈል ግን አንድ አፍሪካ' የሚል መሆን አለበት፡፡ ተግባባን?” ማርቆስ ውስጥ

ያመቀውን ሁሉ የተነፈሰና የቀለለው ይመስል ተመቻችቶ ተቀምጦ ሲጋራ ፍለጋ ኪሱ ገባ።"

"አልገባኝም..." አለች ርብቃ አፍጥጣ እየተመለከተችው "ምን ላይ ነው የናትናኤል ወኔ ቢስነት ታዲያ? ዲሞክራሲ ምን ላይ ነው ችግር የፈጠረው? ዲሞክራሲ በአፍሪካ መስፈን ምን ላይ ነው ጉዳት የሚሆነው፤ የዘመኑ ሃይማኖት እያልክ የምትኮንነው?"

"እየሽ አንቺም ሳታውቂው መተብተብሽን? ርብቃ... ከዘመናት በፊት ነጮች ለአፍሪካውያን የሰበኩት ክርስትና አጥፊና ጎጅ ሆኖ ይመስልሻል የማታ ማታ ለባርነት የተዳረግነ? አይደለም። ክርስትና ሃሉትና ማወናበጃ፣ ክርስትና ማታለያ ሆኖ አልነበረም። እውነቱ ግን ነጮች ክርስትናን፣ ወንጌልን መሣሪያ አድርገው፣ መሸፋፈኛ አድርገው ሊያዘናጉን መቻላቸው ነው። ወንጌልን እንሰብክ ብለው ጉብተው ውስጥ ገመናችንን ሊሰልሉ፣ ሊያውቁ፣ ሊያጠኑንና ሊሲያዩን በመቻላቸው ነው፤ ቀበሮ ሲሆኑ በግ መስለው በመምጣታቸው ነበር። ርብቃ ዛሬም ዲሞክራሲ ማታለያ አጥፊና ጎጅ ሆኖ አይደለም። ምሥጢሩ ግን በዲሞክራሲ ሰበብ እርስ በርሳችን እየለያዩ እያቧጨቁ ማፋጀታቸው ነው። ለያይተው በታትነው አዳክመው ድጋሚ ሊሸጡን ሊሸምቱን መነሳታቸው ነው። ከዘመናት በፊት ክርስትናን እንደተጠቀሙበት ዛሬ ዲሞክራሲን ማንሳታቸው ነው።"

"እና ምን ማድረግ አለብን?"

"'መጀመሪያ አፍሪካ' ማለት አለብን። 'መጀመሪያ አንድነታችን' ማለት አለብን። ያ ብቻ ነው ጥንካሬያችን። ያ ብቻ ነው ብርታታችን። ያን ጊዜ ... አፍሪካ አንድ ስትሆን እንደዛሬው የሃምሳ አገሮች ሹክሹክታ ሳይሆን የአንድ አፍሪካ ድምፅ ያስገመግማል። ያን ጊዜ ዓለም ያዳምጠናል። ያን ጊዜ ብርታታችንን ይገነዘቡታል። አፍሪካችን ገና የምትለማ ነች - ይህን ገንቡ ያንን አፍርሱ ስላሉን ሳይሆን የሚበጀንን እንገነባለን የማይጠቅመንን እናፈርሳለን፤ አፍሪካችን ሰፊ ገበያ ነች - ይህን በዚህ ሽጡ ስላሉን ሳይሆን በሚያዋጣን እንሸጣለን፤ ይህን በዚያ ግዙ ስላሉን ሳይሆን በሚስማማን እንሸምታለን። አፍሪካ ድንግል ናት፤ ጥሬ ሃብት የእኛ ነው፤ ከፋን ቢሉ እናበላልጣቸዋለን፤ አቃረን ቢሉ እናማርጣቸዋለን።

"ያን ጊዜ ዛሬ የተሳለቁብን ዛሬ የተዘባበቱብን የገላችንን ቀለም አይተው 'እድፍ'፤ ኋላቀርነታችንን ገላምጠው 'ዝንጀሮ' ያሉን ሁሉ ወዳጅነታችንን ይመኙታል፤ ወንድማማችነቱን ያከብሩታል። 'አይ' ቢሉ 'አሻፈረኝ' ቢሉ ሊገፉትና ሊገድቡት የማይደፍሩት ጎርፍ ሊዝቁት ሊጨርሱት የማይሞክሩት የባህር አሸዋ ጥቁር ሕዝብ ከፊታቸው እንደተጋረጠ ይገነዘባሉ... ያኔ ነው ዲሞክራሲ ! ያኔ ነው የሰው ልጅ መብት



... ያኔ ነው የራስን ዕድል መወሰን... ርብቃ ያ ጊዜ መጥቶ እልሄንና ቁጭቴን እንድወጣ ነው ፈጣሪን የምለምነው ... ያ ነው ጸሎቴ።"

-19-

ታክሲው ውስጥ የሚጮኸው ሙዚቃ ጭንቅላቱን በጠበጠው። ማታ እንቅልፍ አልወስድህ ብሎት ሲጨነቅ ነበር ያደረው።

"ምንድነው የሆንከው? ለምን አትነግረኝም?" አለች ዘውዲቱ ከሆቴል ገዝታ ካመጣችው ምግብ እያጎረሰችው። "ምስኪን አሁንስ ሚስትህ ናፈቀችህ መሰለኝ።"

ያጎረሰችውን እያላመጠ ዝም አላት። ወሬ አላሰኘውም። ምግቡም እንዳያስከፋት ብሎ ነው እንጅ ቢቀርበት በወደደ።

እራት በልተው ተጣጥበው መብራቱን አጥፍተው አልጋ ላይ ከወጡ በኋላ ናትናኤል በጀርባው እንደተንጋለለ አይኖቹን ጣሪያው ላይ ተክሎ ቀረ።

'ምን ሆና ይሆን? እንዴት ሁለት ቀን ሙሉ ስራ ሳትገባ ትቀራለች... በጤናዋ ባትሆን ነው እንጅ። ደግሞ ምህረት 'እቤቷ ደወዬ የሚያነሳ አጣሁ' ማለቷ ምን ማለቷ ነው? ቤቷን ዘግታ የት ትሄዳለች? ምናልባት አሚት ወላጆቿጋ ሄዳ ይሆን እንዴ? የወላጆቿን ቤት ደግሞ አያውቀውም፤ ጉለሌ እንደሆኑ ነግራዋለች። ግን በደፈናው ጉለሌ ተብሎ አይኬድ። ቤቷ ሄዶ ይሞክር ይሆን?'

ሌሊቱን ሲጨነቅ አደረ። አሁን ደግሞ ታክሲው ውስጥ ያለው ሙዚቃ አይሉት ጩኸት...

"ሲጋራ ፋብሪካ ነው ያሉኝ?" አለው ባለታክሲው።

"እ? አዎ የኔ ልጅ። ከዚህ ይበቃኛል።" ናትናኤል የታክሲውን በር ከፍቶ ወረደ።

"አባ! ገንዘቡስ?!" ባለታክሲው የመኪናውን ጥሩንባ ተጭኖ ጮኸ።

"ይቅርታ! ይቅርታ!" አለ ናትናኤል ከሄደበት ተመልሶ ኪጋቢው ስር ከደረት ኪሱ ገንዘብ እያወጣ "ይቅርታ የኔ ልጅ። ሃሳብ ገብቶኝ ተዘንግቶኝ ነው።" ገንዘቡን ለባለታክሲው አቀበለው።

ዘውዲቱ የገዛችለት ሳስቲክ ቦት ጫማ መንገደኛ ቢያስመስለውም እላይ ከፊቱ እግሩን ከርክሮት ክፉኛ አቁስሎታል። በተራመደ ቁጥር የጫማው ክፈፍ ቁስሉን ሲነካበትና ሲፈትግበት ይለበልበዋል።

ከመንገዱ ባሻገር የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ህንፃ ብቻውን ተገትሯል ... ሥራ ፈት። ናትናኤል ይህንን ፎቅ ሲመለከት ምንም ትርጉም አይሰጠውም ... በፎቁ ቅርፅ ውስጥ መልዕክት ካለ 'አንድ' የሚል መሆን አለበት ... ቀጥ ያለ ፎቅ ... አንድ።

ናትናኤል አይኖቹን ከፎቁ ላይ ነቅሎ ሃሳቡን አሰባሰበ። ለጥያቄው መፍትሄ የሚያገኝለት ካልቨርትን ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ ከተረዳ ቆይቷል። ካልቨርትን አግኝቶ የአውሬውን ማንነት ይፋ እስካላወጣ ድረስ የተደበቀውንና የተሸሸገውን ምሥጢር እስካላዘረከረከው ድረስ አንድ ቀን ከአንዱ ጥግ ነው የሚደፋት።አብርሃምን እንደደፋት።

ይህ ከመሆኑ በፊት ካልቨርትን ማግኘት አለበት። ግን ካልቨርትን ለማግኘት ከየት 'ሀ' ብሎ እንደሚጀምር እንቆቅልሽ ሆነበት።

'መረጃ... የውስኪ ጠርሙስ... ሾፌር ... ቤላ
መጠጥ ቤት... ሴት ... ሞሳድ ... ኤም. አይ.
ስድስት...ካዛንቺስ ወዳጁ ቤት... የሴት ልብስ
ለብሶ ... ተሰወረ።'

ቁልፉ የግድ እዚህ ውስጥ መሆን አለበት... መፍትሄው እዚህ ውስጥ ከሌለ ካልቨርትን ሊያገኘው አይችልም። ምክንያቱም እሱ የሚያውቀው ይህን ብቻ ነው - አብርሃም የነገረውን።

ያለጥርጥር ካልቨርት እንዲሰወር የካዛንቺሷ ወዳጁ ረድታዋለች። በመጨረሻ የታየው ከእሷ ቤት ሲወጣ ነው። ምናልባት የት እንደሚገኝም ታውቅ ይሆናል። በተቻለው መንገድ ሴትየዋን ማግኘት አለበት። ካልቨርትን ሊረዳው እንደሚፈልግ ሊያሳምናት ይገባል። ትጠረጥረው ይሆናል። ግን ሊያሳምናት ከቻለና ካልቨርት ያለበትን ቦታ ከነገረችው ድብብቆሹ አበቃ ማለት ነው። ያን ጊዜ ያለጥርጥር አውሬውን መረቡ ውስጥ ይከተዋል።

ካልቨርት የሚያውቀው ነገር እንደሌለስ? ማወቅ አለበት! ምንም የማያውቅ ከሆነ ለምን ተሸሸገ? ያውቃል። ለሕይወቱ የሚያሰጋው ምሥጢር ይዟል። ያንን ምስጢር ማግኘት አለበት። ካልቨርትን ለማግኘት ደግሞ መጀመሪያ የካዛንቺሷን ሴት አግኝቶ ማሳመን፣ ማግባባት ማሸነፍ። እሷ ብቻ ናት ዕድሉ።



ግን አውሬው ለምን ሴትየዋን አቆያት? ያለጥርጥር ወደ ካልቨርት የምትመራ መንገድ ናት። ይህንን ደግሞ አውሬው ሳያውቀው የሚቀር አይደለም። ታዲያ ለምን አሰነበታት? ለምን አስገድዶም ቢሆን የካልቨርትን አድራሻ አላወጣጣትም? ወይም ለማንኛውም ወገን ምሥጢሩን የካልቨርትን አድራሻ እንዳትጠቁም ለምን እንደ አብርሃም አላስወገዳትም?

ምናልባት ሴትየዋ ራሷ ወጥመድ እንደሆነችስ? የካልቨርትን አድራሻ የሚያነፈንፍ አይጥ ወደ ካዛንቺስ እንዲመጣና ከወጥመድ እንዲገባ የተንጠለጠለች የሥጋ ቁራጭ እንደሆነችስ? ካዛንቺስ ከመድረሱ አንገቱን ቆርጠው ቢጥሉትስ?' ናትናኤል ሰጋ። አብርሃም ያለው ትዝ አለው-

"... ሁለቱን የክትትል ሰዎች ባሰማራን በሶስተኛው ቀን አንደኛው ሰዎችን በስለት ታርዶ እዛው ካዛንቺስ ቱቦ ውስጥ ተጥሎ ተገኘ..."

'ሀ! "እዛው ካዛንቺስ" - 'ወጥመድ'

'ያለጥርጥር ካዛንቺስ ወጥመድ ተጠምዶለታል። ቢሆንም ምርጫ የለውም። ወደ ካልቨርት ሊቀርብ የሚችለው የካዛንቺሷን ሴት ሲያገኝ ብቻ ነው። የግድ ካዛንቺስ መሄድ አለበት።'

'ካዛንቺስ። ካዛንቺስ ምኑጋ? ካዛንቺስ ስንት አውራ መንገዶች አሉ?... ካዛንቺስ ስንት መጠጥ ቤቶች አሉ? የትኛዋ ናት የካልቨርት ወዳጅ? "የፈጣሪ ያለህ!"' የካዛንቺስ ስፋቱና የቀሚስ ለባሹ ብዛት ታየው።'

'ሌላ ጥያቄ! እንዴት ሊያገኛት ይችላል? ማን ሊመራው ይችላል? አብርሃም ምንድነው ያለው...?'

"...የቅብብሎሹን ሠንሠለት መስበር ነው...
ካልቨርት የሰረቀውን መረጃ...በውስኪ ጠርሙ
ሶች...በሾፌርነት ለሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ያቀ
ብላል...ሹፌሩ ቤላ መጠጥ ቤት ላላት..."

'ሹፌሩ ...ሹፌሩ ቤላ መጠጥ ቤት ያላትን ሴት ያውቃታል ማለት ነው። የካዛንቺሷንስ? ሊያውቃት ይችላል? ምናልባት ካልቨርት የሚቀርበው ከሆነ ሊያውቃት ይችላል። ያለው ምርጫ ሾፌሩ ነው። ሾፌሩን አግኝቶ የካዛንቺሷን ሴት አድራሻ እንዲሰጠው መጠየቅ።'

"... ሾፌሩ የኛ ሰው ነው... በእሱ በኩል ነው
መረጃውን የምናገኘው..." ነበር ያለው
አብርሃም።

'ሌላ ወጥመድ:: ሾፌሩም አደገኛ ነው:: "ካዛንቺስ ያለችውን የካልቨርትን ወዳጅ ሆቴል አሳየኝ::" ሲለው መቼም መጠራጠሩ አይቀርም:: "እሺ ና" ብሎ ገመድ በአንገቱ ቢያስገባለትስ? መሬት ለመሬት እያንሸተተና እየጎተተ ቢያስይዘውስ? እርግጥ ያለው ምርጫ ወደ ካዛንቺሷ እመቤት የሚደርሰው ብቸኛ መንገድ የሳይቤርያው ኤምባሲ ሾፌር ብቻ ነው:: ለይቶ የሚያውቀው አድራሻ የእርሱን ብቻ ነዋ! ቢሆንም ሰውየውን በአካል መገናኘት የለበትም::አንድ ዘዴ መፍጠር አለበት::' ናትናኤል ለበርካታ ቀናቶች ሲያወጣ ሲያወርድ መልስ ሲሻለት የቆየውጥያቄ ይህ ነበር::መልሱን አግኝቷል:: አቅዶ ወጥኖ ጨርሷል:: ትከሻው ላይ አሳርፍልህ ያለውን ጋቢ እያስተካከለ ከመንገድ ወዳለ ትንሽ ቁርስ ቤት ገባ::

"የኔ ልጅ እባክሽ ስልክ ታስደውይኝ...እከፍላለሁ::ችግር አጋጥሞኝ ነው- ልጅ ታማብኝ::" አላቸው እናቱ የሚሆኑትን የቁርስ ቤቷን ባለቤት ጠጋ ብሎ:: ያቀደውን ደረጃ በደረጃ ይፈጽም ጀመር::

ሴትየዋ ስልክ ማስደወሉን ባይወዱትም ከቁስ ጋር! ከእግዚአብሄር ሰው ጋር ክፉ መነጋገሩን አልፈለጉትም:: ከባልኮኒው ስር አንድ ሰማያዊ ስልክ አውጥተው ቁሉ ፊት ቆለሉትና "ያው" ብለው ፊታቸውን አዙረው ሄዱ:: ደረታቸው ላይ የተቆለለው የጡት ተራራ የዘውዲቱን ጋራ ያስንቃል::

ናትናኤል ሴትየዋ ዞር እንዳሉለት የስልኩን መነጋገሪያ አንስቶ በመጀመሪያ ወደ ማዞሪያ ደውሎ የሳይቤርያ ኤምባሲን የስልክ ቁጥር ከጠየቀና ካገኘ በኋላ ወደ ኤምባሲው ደወለ:: 'በሳይቤርያው ኤምባሲ ውስጥ ከአንድ በላይ ሾፌር ሊኖር ይችላል:: የትኛውን አቅርቡልኝ ሊል ነው? ብቻ ማናቸውም ቢሆኑ የካልቨርት ስም ሲጠራ ከትክክለኛው ሰው ጋር ያገናኙት ይሆናል:: ያለው ምርጫ መሞከር ብቻ ነው:: አብርሃም -"ሾፌር" ነው አለው እንጂ በስም ለይቶ አልነገረውም:: 'ወይኔ! አብርሃም በኖረ ኖሮ አብረው ስንት ነገር በሰሩ...በሳምንታት ሳይሆን በቀናት ውስጥ እጃቸው ውስጥ ባስገቡት ነበር ካልቨርትን...'

"ሃሎ... ሳይቤርያ ኤምባሲ" አለ ቀጭን የሴት ድምፅ::

"ሃሎ... የእኔ እመቤት እባክሽ ከእናንተ ዘንድ መኪና የሚሾፍር ልጅ ነበረ... ዘመድ ከአገር ቤት መልዕክት አስይዞ ከእደራ ጋር ቢልከኝ ነው...ባክሽ አስጠሪልኝ::"

"ማንን ነው የሚፈልጉት?ስሙ ማነው?"

"ሹፌር ...የኔ ልጅ ...ሹፌር ነው::"

"ስሙን ይንገሩኝ::" መንጨቅጨቅ አደረገችው::



"የኔ ልጅ ተዘነጋኝ ... ከአገር ቤት..."

"ስዩምን ነው?" አለች ልጅቷ በስጨት ባለ ድምፅ አቋርጣው::

"አዎ ... አዎ የኔ ልጅ እሱን ነው::" ምርጫ አልነበረውም::

"አንድ ጊዜ ይጠብቁ::"

ግንባሩ ላይ ቸፈፍ ያለውን ላቡን ጠረገና ተዘጋጀ:: አሁን እንደቂስ ሳይሆን እንደ ወታደር ማውራት አለበት:: ፈጣንና ቁርጥ ያለ መልክት:: እንዳቀደው ለቀናት የተለማመደውን ዲስኩር ሊያወርደው ተዘጋጀ::

"አቤት::" አለ በአፍንጫው የሚናገር የሚመስል ሰው::

"ሃሎ ... ስማኝ ስዩም:: ተጠንቀቀህ አዳምጠኝ::" አለ ናትናኤል ቆፍጠን ባለ ድምፅ:: "ካልቨርት ነው የላከኝ... ትሰማኛለህ?" ናትናኤል ለአንድ አፍታ ከወዲያ ያለው ሰው የሚያሰማው ድምፅ እንዳለ ተጠባበቀ::

"እየሰማሁ ነው::" አለ ሰውየው ፈጠን ብሎ::

'ሹፌሩ መሆን አለበት! ሌላ ሰው ቢሆን በፍጥነት ከሁኔታው ጋር ራሱን ለማዛመድ ይቸገር ነበር::' ናትናኤል ደስ አለው::

"ስዩም ... አሁኑኑ ከኤምባሲው ወጥተህ ከሲጋራ ፋብሪካ በላይ ካለች ትንሽ የቁርስ ቤት ድረስ እንድትመጣ:: ቢጫ ቀለም የተቀባች የቁርስ ቤት ነች ... ኮትህን አውልቀህ በትከሻህ ላይ አንጠልጥለው:: ከአሥር ደቂቃ በላይ አልጠብቅህም::"

ናትናኤል ስልኩን ሰውየው ጆሮ ላይ ጠረቀመውና የቁርስ ቤቷን የስልክ ቁጥር አንብቦ በጭንቅላቱ ይዞ ወደ ባለቤቲቱ ዞረ::

"ተባረኪ የኔ ልጅ:: እንጀራሽ ከፍ ይበል:: የአያት የቅድመ አያቶችሽን ስም የምታስጠሪ ያርግሽ::" ምርቃቱን አጎርጎረጎደው:: ወዲያው ጋቢውን እየገለበ "ስንት ነው ሂሣቡ ... የኔ ልጅ የደወልኩበት?" እያለ ይፍተለተል ጀመር::

"ግድየለም አባቴ ምርቃቶ ይበልጣል::" አሉ ሴትየዋ ከምርቃቱ እንዲጨምር የፈለጉ ይመስል::

"ተባረኪ:: ቤትሽ አይጎደል:: ልጅሽን ባሪ ቀባሪ ያድርግሽ..." ከምርቃቱ ሳያሳንስ ጋቢውን አስተካክሎ ከቁርስ ቤቷ ወጣና በፍጥነት መንገዱን ተሻግሮ ከሌላ ቡና ቤት በረንዳ ላይ ቆም ብሎ ይጠባበቅ ጀመር::

ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀጭን አጭር ሰው መንገዱን ተሻግሮ ወደ ቢጫዋ ቁርስ ቤት ሲጣደፍ ተመለከተ፡፡ኮቱን ትከሻው ላይ አንጠልጥሎታል፡፡ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽህፈት ቤት ፊት ለፊት ካለው የላይ ቡርዩ አውቶቡስ እስከ ቁርስ ቤቷ ለመድረስ ብዙ ባያስኬድም ወደፊት ደፋ - ደፋ የሚለው ሰው ረዥም መንገድ የተጓዘ ይመስላል፡፡ ሰውየው ከቁርስ ቤቷ እንደደረሰ ወደውስጥ ከመግባቱ በፊት ቆም ብሎ ዙሪያውን ተገላምጦ ተመለከተ፡፡ ወዲያው ዘው ብሎ ወደ ውስጥ ገባ፡፡

ሰውየው ወደ ውስጥ ሲገባ ናትናኤል ፈጠን ብሎ ከጥግ ወዳለ የህዝብ ስልክ አመራና አንብቦ በጭንቅላቱ የያዘውን የቢጫዋን ቁርስ ቤት ቁጥር ደወለ፡፡

"አ...ቤት፡፡" አለ የሴት ወይዘሮ ድምፅ፡፡
ያ ከምር ጡታቸው መጥቶ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት -ናትናኤል፡፡

"እንደምን ዋሉ...ደህና ኖት?!" ሴትየዋ መልስ ከመስጠታቸው በፊት አጣደፋቸው "ገብረየሱስ ነኝ...እንደምን ኖት?!" አለ እንደሚያውቃቸው ተገዝናንቶ፡፡ "እባኮት ከስዩም ጋር ቀጠሮ ነበረን እርሶ ቤት ... እንዴ ያገናኙኝ...ስዩም ይበሉልኝ...እቤትዎ ውስጥ ነው ያለው...ደህና ኖት ግን እርስዎ...በሉ ስዩምን ያገናኙኝ..." በላይ በላይ አጣደፋቸው፡፡

"የማን ስዩም?" አሉ ሴትየዋ ፋታ ሲያገኙ፡፡

"እንዴ!... ረሱን እንዴ? እቤትዎ በልተን ጠጥተን? አይ የርሶ ነገር! ይበሉ ስዩም ይበሉልኝ፡፡ አይ የርሶ ነገር! ደንበኞችንም ይረሱ ጀመር?" አጣደፋቸው፡፡

"ኧረ ንሽቴ! የምን መርሳት አመጣህብኝ፡፡!" አሉ ሴትየዋ ድፍረት አሰባስበው፡፡ "ደሞ እናንተን ደንበኞቼን ልርሳ? ሄ! ሄ! ሄ! ገና ሳላረጅ ምነው ባክህ! ደህና ነህ ግን አንተ ጠፋህሳ?"

ሴትየዋ ሲጣሩ "ስዩም የሚባል! ስልክ!" ሲሉ በስልኩ ውስጥ ተሰማው፡፡ ነፍሱ መለስ አለችለት፡፡ ስልኩን ጆሮው ላይ እንዳይጠረቅምበት ሰግቶ ነበር፡፡
"ሀሎ..." አለው ያው ነፍናፋ ድምፅ፡፡
"ስዩም?" ናትናኤል ቆፍጠን ባለ ድምፅ ጠየቀ፡፡
"ነኝ...የት...?"



"ዝም ብለህ አዳምጠኝ፡፡ቁርስ ቤቷ ውስጥ ያጠብቀኛል ብለህ አስበህ ከሆነ ሞኝ ነህ፡፡ መልዕክቱን ብቻ አስጥሀለሁ፡፡ ትስማማለህ?" አለ ናትናኤል ጥድፊያ በተቀላቀለው ድምፅ፡፡

"አዎ -አዎ፡፡ ቀጥል፡፡"

"ጥሩ... እንዳልከህ ካልቨርት ለአንተ የማደርስለትን መልዕክትና በርከት ያለ ገንዘብ ሰጥቶኛል፡፡ መልእክቱን ከመስጠቴ በፊት ግን አንተነትህን ማረጋገጥ አለብኝ፡፡"

"ነኝ...ነኝ ግድ የለም፡፡ ስዩም ነኝ፡፡"

"ዝም ብለህ አዳምጠኝ! ስምጠይቅህ ጥያቄ ብቻ አጫጭር መልስ ነው የምፈልገው፡፡" አለ ናትናኤል ሰውየውን ይበልጥ ለማደናገር ቱግ ብሎ፡፡ "ካልቨርት በየትኛው ጣቱ ላይ ነው ቀለበት የሚያደርገው?" ያዘጋጃትን ማስመሰያ ጥያቄ አስቀደመ፡፡ 'በአውራ ጣቱ ላይ' ቢለውም ግድ አልነበረውም፡፡ ነገር ግን ወደ ዋናዎቹ ጥያቄዎች ከመግባቱ በፊት የሰውየውን ጭንቅላት ማሟሸት አለበት፡፡
"ቀለበት አያደርግም ካልቨርት፡፡" አለ ሰውየው በሚያስደንቅ ፍጥነት፡፡

"ጥሩ፡፡ አሁንም ፈጣን መልስ እፈልጋለሁ፡፡ ተጠንቀቅ ብትሳሳት ወይ ብትጠራጠር፡፡ ብትዘገይ ስልኩን ዘግቼ ነው የምሄደው፡፡ የምፈልገው ትክክለኛውን ስዩም ነው፡፡ የያዝኩትን በርካታ ገንዘብ ላልሆነ ሰው ማስታቀፍ አልፈልግም፡፡ አድምጥ፡፡ የካዛንቺሷ ሴት ስም ማነው?" ናትናኤል በጭንቀት ትንፋሹን ያዘ፡፡

"የምሥራች ይልማ!" አለ ሰውየው ሌላ ሰው እንዳይቀድመው የፈራ ይመስል በጥድፊያ፡፡
"የስልክ ቁጥሯስ?" አከታትሎ ጠየቀው፡፡
"ትዝ አይለኝም፡፡?"
"እንግዳው ስዩም አይደለህም፡፡ደህና ዋል፡፡"
"ቆይ! ቆይ!" አለ ነፍናፋው ድምፅ በጭንቀት ተወጥሮ፡፡ "ቆይ ስልኩን እንዳትዘጋው፡፡ ማስታወሻዬን ልይ... ቆይ... አንዴ... እ...እ... እዎ ...ይኸው..."

ናትናኤል ስልኩን በጆሮውና በትከሻው መሃል ይዞ ሰውየው የነገረውን የስልክ ቁጥር በወረቀት ላይ ይጽፍ ጀመር፡፡ ድንገት ከላይ ከሜክሲኮ አደባባይ አቅጣጫ አንድ ነጭ ፎርድ መኪና በከፍተኛ ፍጥነት መጥታ ከቢጫዋ ቁርስ ቤት በር ላይ ቆመች፡፡ ወዲያው ከውስጥ የነበሩ

ሁለት ሰዎች በሮቻቸውን እየከፈቱ ወረዱ። ሁለቱም የመኪናዋን በሮች ለመቆለፍ እንኳን ሳይሞክሩ እየተጣደፉ ወደ ቁርስ ቤቱ አመሩ። ጥቋቁር ኮትና ሱሪ ለብሰው የከታቸውን ቁልፎች ቆልፈዋቸዋል። ናትናኤል ፈጣን ግባው። ተሎ ዘይ መቀየስ እንዳለበት ተረዳ።

"ጥሩ።" አለ ድምፁን ሳይቀይር ረጋ ባለ መንፈስ። "ስዩም ያለሁት ናዝሬት ነው። ነገ ከጠዋቱ ልክ በአራት ሰዓት ናዝሬት ከቴሌመኒኬሽን ሕንፃ ፊት ለፊት 'ግራር ሆቴል' የሚል ቤት አለ እዛ እጠብቅሃለሁ። ነጭ ኮትና ጥቁር መነጽር አደርጋለሁ። ፒፓ አጨሳለሁ። አደራ ያወራነውን በምስጢር ያዘው።" ናትናኤል ስልኩን ዘግቶ እራት ብሎ ይጠባበቅ ጀመር።

ወዲያው ከቢጫዋ ቁርስ ቤት የላይቤርያው ኤምባሲ ሾፌር ሁለቱን ሰዎች አስከትሎ ብቅ አለ። ሦስቱም ተከታትለው ወደ መኪናዋ ገቡ። መኪናዋ ግን አልተንቀሳቀሰችም። ከኋላ የተቀመጠው የላይቤርያው ኤምባሲ ሾፌር እጆቹን እያወናጨፈ ሲያወራ ሁለቱ ሰዎች ፊታቸውን ወደኋላ መልሰው ሲያዳምጡት ቆዩ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ስዩም ከመኪናዋ ወርዶ ለብቻው መንገዱን ተሻግሮ ወደ መሥሪያ ቤቱ አቅጣጫ ሲያመራ ነጯ ፎርድ ተጠምዝዛ ሽቅብ በሜክሲኮ አደባባይ አቅጣጫ ተፈተለከች።

ፈገግ አለ ናትናኤል። "ነገ ናዝሬት እንገናኛ" አለ ከራሱ ጋር። ወዲያው ከኪሱ ከቷት የነበረችውን ወረቀት አውጥቶ አነበባት። ካዛንቺስ... የምሥራች ይልማ... የፈለገው ይህን ነበር - ስሟንና የስልክ ቁጥሯን። የፈለገውን ሁሉ አግኝቷል።

የላይቤርያው ሾፌር ያለጥርጥር ለበላይ አለቆቹ አስታውቋል! ለአብርሃም አለቆች። ቢሆንም ለጊዜው አትኩሮታቸው ናዝሬት ከተማ ውስጥ ስለሚሆን እዛው ነው የሚሄዱት። የአውሬውም ጆሮ በአካባቢው ካለ የአውሬውም አይን ናዝሬት ላይ ነው የሚያፈጥ። ሁሉም ናዝሬት ነው የሚንጋጉት። አሁን ነው ጊዜው። አሁን ነው መንቃነቅ ያለበት።

"ሃሎ።" የህዝብ ስልኩ ውስጥ ሳንቲም ጨምሮ ደወለ።

"ሃ...ሎው" ሙልቅቅ ያለ የሴት ድምፅ ጆሮው ውስጥ ገርረር አለበት።

"እ... የምሥራች ይልማ ሆቴል ነው... እባኮት..."

"አዎ ነው። ማንን ላቅርብሎት?" ሙልቅቅቅ አለችበት።

"እንደምንዋልሽ የኔ እመቤት። እ... ከባህር ዳር ነበር የመጣሁት። ባልንጀራዬ መስተንግዷችሁን አድንቆ እናንተጋ እንዳርፍ የስልክ ቁጥራችሁን ሰጥቶኝ ነበር። እ... ለባለቤቲቱም ደብዳቤ ይገፎ ነበር። ግን ቤታችሁን ላገኘው አልቻልኩም። ባክሽ..."



"እይውሎት..." አቋረጠችው። "ሞቢል ነዳጅ ማደያው ጋ አይደል ካዛንቺስ?" የልጅቷ ድምፅ ሲወርድ እንደ ተልባ ነው። "ያውቁታል...? በቃ በሱጋ ቀጥታ ሲሄዱ እንደዚህ በስተቀኝ ወደ ላይ ወደግራ የሚታጠፍ መንገድ አለ... እ-ዎ! እሱን ትተው በስተቀኝ ትንሽ እንደሄዱ በትልቁ 'የምሥራች ሆቴል' የሚል ማስታወቂያ አለ። አጥሩ ሮዝ ቀለም የተቀባ..." አቅጣጫውን ከነምልክቱ ጥርት አድርጋ ነገረችው።

ናትናኤል ወዲያውኑ ታክሲ ተሳፍሮ ወደ ካዛንቺስ በረረ። እዚያ ሲደርስ ምን እንደሚያደርግ ግን ለራሱም ግልፅ አልሆነለትም። በሁለት ታክሲ አሳብሮ የምሥራች ሆቴልን ደጃፍ አለፍ እንዳለ የታክሲውን ሂሣብ ከፍሎ ወረደና ጋቢውን ትከሻው ላይ ቆልሎ ዘውዲቱ የገዛችለትን አዲሱን ምርኩዙን እያስቀደመ እሱ እየተከተለ ከመንገድ ባሻገር ያለውን ሆቴል እያጠና አለፈ። እራቅ ብሎ ከሄደ በኋላ ከአንድ የአውቶቡስ ፌርማታ ከለላ አድርጎ ተቀምጦ በትዕግሥት ለብርካታ ደቂቃዎች አካባቢውን ሲያጠና ቆየ።

መደዳውን የተለያዩ ቡና ቤቶችና ሆቴሎች ተሰልፈዋል። የተሳሰ የተቀባባና በንፅህና የተያዘው ግን የካልቨርት ወዳጅ ሆቴል ነው። ለዚህ ጥርጥር የለውም። በደንብ የተጠበቀ ግቢ እስከሆነ ድረስ ደግሞ በሮቹ የማይሰበሩ መስኮቶቹ የማይፈለቀቁ አጥሩ የማይዘለል ማለት ነው። ሰው ሳያየው ወደ ግቢው ለመግባት አስቸጋሪ ነው። ከሆቴሉ በስተግራ አጥሩን ታክኮ ወደ ውስጥ ወደ ሠፈር የሚያስገባ ጠበብ ያለ ሌላ መንገድ አለ።

ናትናኤል በተቻለው መጠን ወደ ሆቴሉ ሳይጠጋ ዙሪያውን የሚገኘውን ሁሉ በጭንቅላቱ ውስጥ ለመመዝገብ ሞከረ።ወጥመድ አዘጋጅተው በአንገቱ ሊያስገቡ ቢሞክሩ ቢያንስ ወዴት መሮጥ መብረር እንዳለበት ማወቅ አለበት። ያንን መፈጸም የሚችለው ደግሞ በትድሚያ አካባቢውን ሲረዳው ሲያውቀው መውጫ መግቢያው ከሰውነቱ ጋር ሲዋሀድ ብቻ ነው። ከተቀመ ጠበት የአውቶቡስ ፌርማታ ተነስቶ ወደ ሆቴሉሳይጠጋ ዙሪያውን በአይኑ እያሰሰ ጉራንጉሩን ሁሉ አጠና።በመጨረሻ ታክሲ ተሳፍሮ ወደ ዘውዲቱ ቤት ተመለሰ።

'ማታ ሲጨልም ሰው ወደ ቤቱ ሲገባ አይጦች ከጎሬአቸው ሲወጡ ጅቦች ሲያስካኩ ይመለሳል። መጀመሪያ እረፍት፤ ወደ ቤት ወደ ዘውዲቱ ጎሬ...ምሳ መብላት፤መተኛት፤መተኛት...ማረፍ...ጭንቅላቱን ንፁህ ማድረግ።'

ናትናኤል ከቤት ሲደርስ ዘውዲቱ አልነበረችም።ቢሆንም አልተከፋም። ልብሱን አወላልቆ አልጋ ውስጥ ገብቶ ጥቅልል አለ።እንቅልፍ እንደሚወስደው ግን እርግጠኛ አልነበረም።እርግጥ ከአሁን ወዲያ የሚያስበው የሚያስላስለው የሚተበትበው ነገር የለም...ድርጊት ነው መልሱ። የካልቨርትን ወዳጅ ማግኘት የካልቨርትን አድራሻ እንድትነግረው ማሳመን... ካልቨርትን ማግኘት!

ትከሻው ሲነቀነቅና አይኖቹን ሲገልጥ ነበር ሃይለኛ እንቅልፍ ወስዶት እንደነበር የተገነዘበው።

"ዛሬ እንቅልፍ ምሳ ሆነ እንዴ? በራብ ገደልከኝኮ አንተን ስጠብቅ።" አለች ዘውዲቱ አጠገቡ ቆማ ቁልቁል በተጋደመበት እየተመለከተችው።

"እ... " ዓይኖቹን በመዳፉ እያሻሸ ተነስቶ አልጋው ላይ ተቀመጠና ሰዓቱን ተመለከተ። አስር ከአስር። "...ለምን አትበይም ነበር አንቺ? እኔ'ኮ ደክሞኝ..." ተነፋነፈ እንቅልፍ ባጎረነነው ድምፅ።

"ምን ብቻዬን እበላለሁ...አሁንማ የሌለብኝን መጥፎ ፀባይ ከሰው ጋር መብላት ለምጄ ብቻዬን ስሆን ስራ ይመስለኝ ጀምሯል።" አለች እየሳቀች። "በል ተነስና ፊትህን ታጠብ። ይህን ያበጠ ፊትህን ጋሽ ወጋየሁ ቢያዩ መርፌ ካልወጋሁህ ነበር የሚሉ።"

"ማናቸው ጋሽ ወጋየሁ?" አለ ከተኛበት እየተነሳ።

"የሰፈራችን ደንቅ ሃኪም ... ማነው? ... አምጣልኝ... እ... ስሙ ጠፋኝ...ብቻ ከአንድ ትልቅ ሆስፒታል ድሬሰር ናቸው። እኛ ሠፈር ውስጥ ደግሞ ዶቶር! የማያድኑት የበሽታ ዓይነት የለም።"

"ድራሹ ነው የሚያጠፉት በይኝ።" አለ እየሳቀ ከአልጋው እየወረደ።

"ለዛውም በአንድ መርፌ ነዋ!" እየሳቀች። "የውሸት ሃኪም ይሉሃል እሳቸው ናቸው። ብቻ ምን አለፋህ... ቁርጠትም ይሁን ውጋት ወለምታም ይሁን ስብራት የፈረደበት ያ ቂጥ ነው የሚጠቀጠቅ... ሂ! ሂ! ሂ! ሂ! ... ደግሞ አንዴ ቀሚስ ገልበው ከገቡ አቤት አቀያየታቸው!ሄደው ጥና...ት! መርፌ የሚወጉህ ሳይሆን መርፌ የሚሰሩ ነው የሚመስል።"

"ታዲያ ለምን እሳቸው ጋ ትሄጃለሽ?"
"እህ... ሲያመኝስ?"
"የውሸት ሃኪም ናቸው እያልሽ?... ቢሳሳቱ'ኮ ሊጎዱሽ ይችላሉ"

"ተው ባክህ...የውሸት ያልሆነ ምን አለ? እስቲ ንገረኝ።ማነው 'ይህን አላውቅም፤ ይህ ከአቅሜ በላይ ነው ' ብሎ ወንበሩን ለሌላ የሚለቅ?' ሊጎዱሽ ይችላሉ ' ይለኛል። ተጎድቼ ያለቀልኝ ሽርሙጣ ምኑ ይጎዳል? የሰፈር ሃኪሞች ብቻ ናቸው እንዴ ያለዕውቀታቸው፤ ያለችሎታቸው የሰው ቂጥ የሚዘግኑ? ተው ባክህ በባዶ ሆድ አታናግረኝ። ይልቅ ፊትህን ታጠብና



እንብላበት።" ከሆቴል ገዝታ ያመጣችውን ምግብ ትሪ ላይ መገልበጥ ጀመረች።

ናትናኤል የቤቷን በር ከፍቶ ወጣና ደጃፍ ላይ ባለው የቧንቧ ውሃ ከወገቡ በላይ ይለቃለቅ ጀመር። ወደፊት እንዳጎነበሰ ቀዝቃዛው ውሃ ጮረር እያለ በትከሻው በማጅራቱ አድርጎ ጭንቅላቱን ሲያርሰው ሰውነቱን ጭፍግግ አድርጎ ይዞት የነበረው እንቅልፍ ድራሹ ጠፋ። ታጥቦ ሲጨርስ ሰውነቱን እንደ ውሻ አርገፍግፎ ወደቤት ገባ።

ገላውን ሊያደርቅበት አስቦ የዘውዲቱን ቆሻሻ ፎጣ ከወንበሩ ላይ አነሳና ቢቀፈው መልሶ አስቀመጠው። በእርጥብ ገላው ላይ ሸሚዙን እያደረገ ፊቱን ወደ ዘውዲቱ መለሰ።

"ዘውዲቱ ይህ ፎጣ ቢታጠብ'ኮ ጥሩ ነበር።"
"ከዚያስ? ሲያልቅ ትገዛልኛለህ? "
"ምን ይጨርሰዋል? "
"ሳሙና ነዋ! እሲድ መሆኑ ቀረ እንዴ? ደሞስ ለምን ብዬ አጥበዋለሁ? ታጥቤ ፀድቼ አይደል እንዴ ሰውነቴን የማደርቅበት?"

"ታዲያ ይሄ ቆሻሻ ከየት መጣ?" አለ ያስቀመጠውን ፎጣ አንስቶ ከፊት ለፊቱ ዘርግቶ ይዞ።

"እና ምን ሳድርግህ የኛ ቀብራራ! የዘውዲቱ ቤት ቆሸሸብህ?" ድንገት ቱግ አለች።

"ዘውድዬ ..." አለ ደንገጥ ብሎ። ሂድ ከቤቴ ውጣ የምትለው መሰለው። "እንደዛ ማለቴ ሳይሆን... ላንቺ ብዬ ነው... ለጤናሽ ጥሩ አይደለም... አየሽ..."

"ባክህ በጤና ጥበቃ ቅራቅንቦ አትወጥረኝ። ትበላ እንደሆን ቶሎ ብለህ ብላ።" አለች ትሪው ላይ ካለው እንጀራ ቆረስ አድርጋ ከወጡ ላይ ጣል እያደረገች። "ከቆሻሻ ጋር መኖር ለምጃለሁ። ፎጣዬ ብቻ መሰለህ ቆሻሻ? ሀ! ሕይወቴም ቆሻሻ ነው፤ ህሊናዬም ቆሻሻ ነው። የሳሙና አረፋ የሚያፀዳኝ ይመስልሃል? ወይስ ሳሙናና ውሃ መጥላቴ ለዚህ ሕይወት ዳረገኝ? ተወኝ ባክህ። ብፀዳ ባልፀዳ... ግን ለምንድነው እየጎተጎትክ የማልፈልገውን የምታናግረኝ?" ልትጎርስ የጠቀለለችውን እንጀራ ጣል አደረገችው ትሪው ላይ።

* * *

ናትናኤል ከታክሲው ሲወርድ ምሽቱ ገፍቶ ነበር::የመንገድ መብራቶች አይኖቻቸውን በግ አድርገው ከፍተው ቁልቁል አፍጥጠዋል:: የመሸባቸው መንገደኞች ወደየቤቶቻቸው ይጣደፋሉ::የመሸላቸው ደግሞ ከየጎሬአቸው እየወጡ በየመጠጥ ቤቱ ደጃፍ ያንገፈግባሉ::ፍሙ ተያይዟል:: ከየመጠጥ ቤቱ ደጃፍ ከየጎጇቸው መዝጊያ ተከልክለው አሳፊ አግዳሚን የሚያሽከረምሙት ሴቶች ያርገበግቡታል፤ እፍ...እፍ ይሉታል:: ጭሱ ይግተለተላል:: ካዛንቺስ ትርክክ ብላለች::

የታክሲውን በር ዘጋና ለአንድ አፍታ ቆም ብሎ ዙሪያውን ቃኘ:: ክንፎቿን አራገበችና ኩ... ኩሉ! አለች ካዛንቺስ... ነጋላት...

"ጋሼ ጫማ ልጥረግ?"

ጭንቅላቱን ነቅንቆ ወደፊት ቀጠለ:: ጫማው ተጠርጓል:: የቄስ ልብሱን አውልቆ፣ የገዛ ራሱን ኮትና ሱሪ አድርጎ፣ ከራባቱን አስሮ የድሮው ናትናኤል ሆኗል:: የተለየ ነገር ቢኖር ያጎፈረ ጺሙ፤ የደፋው የእስላም ነጭ ቆብና በኪሱ የያዘው 'አቶ አብዱልከሪም' የሚለው የመታወቂያ ወረቀት ነው::

በመኪና መንገድ ጥግ በእርጋታ እየተራመደ ወደሆቴሉ ተጠጋ:: በራፉ ላይ ጥቂት መኪናዎች ቆመዋል:: አንገቱን አቀርቅሮ በፍጥነት እየተራመደ ቆርቆሮውን የግቢ በር ገፋ አደረገና ወደ ግቢው ገባ::

-20-

ከመንገዱ ባሻገር በቆመችው ቢ.ኤም. ደብሊው ውስጥ ተቀምጠው ሲጠባበቁት የቆዩት ሁለት ሰዎች ታያዩ::

"እኔ ቀድሞውንም አውቀአለሁ::" አለ አህሮን ፊቱን ከጎኑ ወደተቀመጠችው የመስክ ሠራተኛው መልሶ:: "እንዳልገደሉት እርግጠኛ ነበርኩ::"

"እኔ ገድለውታል ብዬ ነበር የገመትኩት» አለች ሴቲቱ::"ወር ሙሉ የት ገባ ትላለህ?"

"በብዙ እንደአንቺ ነበር ግምቴ:: ግን አየሽ ቢገደል ኖሮ አሬሳውን አይሸሽጉትም ነበር:: እንደሌሎቹ ሟቾች በየቱቦው ወይ በየመጠጥ ቤቱ ደጃፍ ነበር የሚጥሉት:: አውቆ ነው የተሰወረው::"



"ለምን ለመሰወር ወሰነ?"

"ይህማ ግልጽ ነው:: አብርሃምን ሲገድሉት እሱም ዒላማ ውስጥ እንደሚገባ ጠርጥሮ መሆን አለበት::"

"ታዲያ አሁን ለምን መጣ... እራሱንኮ ለጥቃት እያመቻቸ ነው::"

"እም:: ግን እስከመቼ ሊደበቅ ይችላል? ዋናው ተፈላጊ ካልቨርት ቢያዝም ባይያዝም ይህኛው ሟች መሆኑን ተገንዝቦታል:: ያለው አማራጭ እርሱ እራሱ ካልቨርትን እጁ ማስገባት ነው:: ያን ጊዜ ብቻ ነው መደራደር የሚችለው::"

"ወር ሙሉ ግራ አጋብቶን በመጨረሻ!" አለች ሴቲቱ::

"እኔ የፈራሁት እኛ ጭራውን ከመያዛችን በፊት ብቻውን የካልቨርትን አድራሻ ያገኛል ብዬ ነበር::"

"ልክ ነህ::ግን እዚህ ድረስ የመጣው የካልቨርትን አድራሻ ባያገኝ ነው::"

"ከዚህ በኋላ በተቻለን ከአይናችን መሰወር የለበትም:: ከኋላ እስከተከተልነው ድረስ ወደ ካልቨርት እንደሚያደርሰን እርግጠኛ ነኝ::"

"ግን እንዴት ሊደርስባት ቻለ?" አለች ከጎኑ የተቀመጠችው ሴት::

"ዛሬ ቀን ደውሎ ነበር:: ድምፁን ቀይሮ ከመንገድ እንደገባ መንገደኛ መስሎ ነው የሆቴሉን አድራሻ የጠየቀውና የተረዳው:: አየሽ ሮበርት ምናልባት ካልቨርት በስልክ ከሴትየዋ ጋር ሊገናኝ ይችላል ብሎ ስለጠረጠረ የሆቴሏንና የቤቷን ስልኮች በወኪሉ አስጠልፎ እያንዳንዱን ጥሪ በጥንቃቄ ይመረምራል:: እሱ ድምጹን በማጎርነን ብቻ ሊያሳስት የሚችል መስሎት ነበር:: እርግጥ የሰው ጆሮን ማታለል ትችያለሽ::የዘመኑን ኤሌክትሮኒክስ ግን በፍጹም:: የድምፁን ቅጅ አግኝቶ ምርመራ እንደጀመረ ነው ሮበርት ድምፁ የእርሱ መሆኑን ከሌሎ ቅጅዎች ጋር አመሳክሮ የደረሰበት::"

"ገባኝ:: ግን እየጠየቅሁህ የነበረው ሴትየዋ ከካልቨርት ጋር ግንኙነት እንዳላት እንዴት እንዳወቀ ነበር::"

"እሱን አላውቅም:: ግን የኢትዮጵያ ሀረ ስለላ ሰዎች ደርሰውበት ስለነበር ያ ሟቹ ጓደኛው ከመገደሉ በፊት ነግሮት ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ በትክክለኛው መስመር ላይ እየተጓዘ ነው::"

"ነው:: ግን አንዴ ሆቴሉ ውስጥ ከገባላቸው በኋላ ምን እንደሚያደርጉት ታውቃለህ:: ካሮት ያየች ጥንቸል ነው የሆነው:: ዘው ብሎ ጆንያቸው ውስጥ መግባቱን አላወቀም::"

"በተቻለሽ መጠን ልትሸፍኚው ሞክሪ። መሞት የለበትም። ካልበርትን የሚያገኝ ሰው ካለ ይህ ሰው ነው።" አለ ሰውየው አይኖቹን አጥብቦ።

"ምን ማድረግ እንዳለብሽ ታውቂያለሽ አይደለም? ማለቴ... ሴትየዋን..." አላት ቀጠለና።

"አንድ በአንድ።" አለች ሴቲቱ ከመኪናዋ ኪስ ውስጥ ትንሽ ሽጉጥ አውጥታ በሰፊ ቀሚሷ የጎን ኪስ ውስጥ እየሸጎጠችው። 'አንድ በአንድ።'

"ምናልባት ከወራት በላይ ላንከራተተን ጥያቄ መልስ ታገኚለት ይሆናል።" አለ ሰውየው ሳቅ ብሎ። "መልሱን ካገኘሽ ምን እንደሚሆን ታውቂያለሽ?"

ሴቲቱ በጥያቄ መልክ ተመለከተችው

"በሚቀጥለው አውሮፕላን ወደ ቴልአቪቭ።" አለ ፈገግታውን አሙቆ።

"ጅቦች! እንዴ አታላችሁኛል። አይበቃም?" አለች የመኪናውን በር ከፍታ እየወረደች።

-21-

ናትናኤል የቆርቆሮውን የአጥር በር ገፋ አድርጎ ሲገባ ያጋጠመው ሰፊ ግቢ ነበር። በግራና በቀኝ አያሌ መኪኖች ተደርድረዋል። ከሆቴሉ ህንፃ ውስጥ ገብተው መስተናገድ ያልፈለጉ ደንበኞች ያማራቸውን እዚያው ከየመኪናዎቻቸው ውስጥ እዘው ይጋበዛሉ። ፍጥነቱን ሳይቀንስ ወደፊት በሆቴሉ ዋና በር አቅጣጫ ገሰገሰ።

ግቢው በጨለማ ቢዋጥም ከፊት ለፊት የሆቴሉ አዳራሽ ብርሃን እውጭ በረንዳው ላይ የምሽቱን አየር እየተነፈሱ የሚጋበዙ እንግዶችን ያሳያል።

በዋናው በር መግባት አደገኛ ነው። ያለጥርጥር እሱን የሚጠብቅ ድንገት የሚወነጨፍ ወጥመድ ሊኖር ይችላል።

ወደቀኝ እጥፍ ብሎ በሆቴል ቤቱ በስተቀኝ ወደጓሮ ዞረ።



ጭስ። እዚያና እዚህ ተፍ ተፍ የሚሉ የወጥ ቤት ሴቶች። ማናቸውም ቀና ብለው አላዩትም። በጨለማው ውስጥ ዘና ብሎ ከኋለኛው በር ደጃፍ ወጣ ብላ ወደቆመች ሴት ጠጋ አለ።

"ታዲያስ!" አላት እንደቤተኛ ተዝናንቶ።

"አለን!" አለች በጨለማው ውስጥ ፊቱን ለማየት እየሞከረች።

"የምሥራችን ምን ነካት ዛሬ?" አለ ጎንበስ ብሎ የእግር ሹራቡን ሳብ ሳብ እያደረገ ፊቱን እንዳታየው። ጨለማው ፊቱን እንደሚከልልለት ቢረዳም መንፈሱ አልረጋጋልህ አለው።

"እንዴት ምን ሆኑ?" አለች ሴትየዋ የእመቤቷ ስም ሲነሳ።

"አላየኋትም።" አለ ፊቱን ወደ ማዕድ ማዘጋጃው ቤት መልሶ።

"እረ አሉ። ከዋናው ቤት ናቸው'ኮ።"

"ከዋናው አዳራሽ?" አለ ለጥቂት ሴኮንዶች ፊቱን መለስ አድርጎ አይቷት ወዲያው ዞር ብሎ እየተንጠራራ። ሴትየዋ የምታውቀው ሰው የዘነጋችው ደንበኛ ይሆናል ብላ እንድትጠራጠር አለቀጥ እየተዝናናባት። "ዋናው አዳራሽማ ገብቼ ነበር። የለችም። ክፍል ጨርሳችኋል እንዴ?" አላት አከታትሎ።

"አልጨረስንም። ልያዝሎት?" አለችው።

"አዎ።" ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ሰጣት።

ሴትየዋ ወደ ውስጥ ስትገባ እያፏጨ እየተንጎራደደ ጠበቃት። ከወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡትን ብቅ ጥልቅ እያሉ እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱትን ሴቶች እየተመለከተ ቆየ።

"አዛሉ! ሁለት ጥብስ አንድ ክትፎ ሶስት ፍርፍር ቶሎ በይ!" አለች አንድ ሴት ከጀርባው ካለ መስኮት ብቅ ብላ። "ዓለም! ዓለምነሽ! ለሦስት ቁጥር ሰዎች አምቦ ውሃ ውሰጂላቸው እንጂ!" ወደ ውስጥ የገባችው ሴት መልሳ በዛው መስኮት ብቅ ብላ ተጣራች።

"መጣሁ - መጣሁ! እዚህም'ኮ ስራ ነው። ጭቅጭቅ!" ዓለምነሽ እያልጎመጎመች ከማዕድ ቤቱ ወጥታ የአምቦ ውሃ ጨብጣ ወደ ዋናው ቤት ሮጠች።

"ይኸው... ሰባት ቁጥርን ያዝኩሎት።" አለችው ቁልፉንና መልስ ገንዘብ የያዘችበትን እጇን ወደፊት ዘርግታ።

ቁልፉን ብቻ ተቀብሎ "ተይው" አላት መልሱን ልትሰጠው ስትከጅል።

"እግዜር ይስጥልኝ።" አለች በጨለማው ውስጥ ፈገግታ ደርባ።

"ምስር ከአዲስ ደንበኞች ጋር ነች መሰለኝ? እኛን ረሳችንሳ።" አለ የተከራየውን ክፍል ቁልፍ ሌባ ጣቱ ላይ እያሽከረከረ።

"አይ...ከነጋሼ ኪዳኔ ጋር ናቸው...ጓዳ።"

"ኪዳኔ የኛ?" አላት በጭፍን።

"አዎ።" አለችው። ቤተኛ ነው ብላ እንደደመደመች ግልጽ ሆነለት።

"አይ እነሱስ ከሆኑ ችግር የለም። እንዴ ሰው ይፈልግሻል በያት።ክፍሌ ውስጥ ነኝ።" ለመመለስ ጊዜ ሳይሰጣት ፊቱን መልሶ መደዳ ወደተሰሩት የመኝታ ቤቶች አመራ...4...5...6...7 ቁልፉን ከቶ በሩን ከፈተና ወደ ውስጥ ገባ። በሩን ከዘጋው በኋላ መብራቱን አበራው።

የክፍሉን አብዛኛ ቦታ የያዘው ቀይ ጨርቅ የለበሰ አንድ ሰፊ አልጋ በሁለት ኮመዲኖዎችና ቁምሳጥን ታጅቦ መሃል ላይ ተንጋሏል። አነስተኛ የፊት መታጠቢያ ሳህን ከነፊት መስታወቱ በስተቀኝ ይታያል። ከክፍሉ ጀርባ ከአልጋው ራስጌ አንድ የተዘጋ የእንጨት መስኮት አለ። ናትናኤል ክፍሉን ካጠና በኋላ ወደፊት ራመድ አለና በኮርኒሱ መሃል የተንጠለጠለችውን አምፖል አላላት። ጨለማ።

አልጋው ላይ ተቀምጦ መጠባበቅ ያዘ። ልቡ እየተነሳ ሲፈርጥ ደረቱን ሲነርተው እራሱን አሳፈረው።ለሳምንታት አንድ በአንድ ሲያስኬደው የቆየው ዕቅድ ቀላል ሆኖ እንዳልታየው ሁሉ ሰዓቱ ሲደርስ በላብ ይዘፈቅ ጀመር። '...ምንድነው የሚላት? ካልቨርት ያላትን ነው መድገም ያለበት። የካልቨርት ቢጤ ምስኪን ተባራሪ ነው መሆን ያለበት። ያኔ ነው ካልቨርትን ባየችበት አይኗ ልታየው የምትችለው። ባታምነውስ? ብትጮኽስ? ኡ! ኡ! ብትልስ? ወይ አባብላ የተስማማች መስላ ብታስይዘውስ? እንዴ ክፍሉ ውስጥ ከገባች በኋላ መውጣት የለባትም። መጀመሪያ መውጣት ያለበት እሱ ነው። ግን ብትጮህ ምን ያደርጋታል? አፏን አፍኖ ይዞ ማስፈራራት? አጥፍቷል። ጩቤ ቢይዝ ጥሩ ነበር።' ቀደም ብሎ ያላሰበው ያልጠረጠረው ሁኔታ ሲከሰትለት ደንገጥ አለ። ለጥቂት ደቂቃዎች አሰላሰለና ድንገት አፈፍ ብሎ ተነስቶ በሩን ከፍቶ ወደ ማዕድ ቤት ሮጥ ብሎ ሄደ።

"አዛሉ! ዓለምነሽ! ማናችሁ... ምነው ዛሬ ችላ አላችሁን!" ጭንቅላቱን በማዕድ ቤቱ ጠባብ መስኮት ገባ አድርጎ ተጣራ። ከውስጥ የክፍሉ ብርሃን ሴቶቹን ቁልጭ አድርጎ ቢያሳየውም ከውጭ የቆመው የእርሱ ፊት ግን በጨለማው ውስጥ እንደተዋጠ ነበር።

"አቤት...ምንድነው?" አለች አዛለች ትሁን ዓለምነሽ ያልለየት ሴት በግራዋ መጥበሻ በቀኟ ሳህን እንደያዘች ፊቷን ወደ እርሱ መልሳ።

"ስንቱ ነው የምንልክባችሁ? ቢላ! ቢላ! ቢላ! በይ አሁን አንድ ስጪኝ!" አለ እጁን ዘርግቶ እያራገበ።



ዞር ብላ ከጠረጴዛው ላይ የተቀመጠ የገበታ ቢላ አንስታ አቀበለ ችው።ቢላውን ከተቀበላት በኋላ ፊቱን መልሶ እየተጣደፈ ወደ ተከራየው ክፍል ሲመለስ ከጀርባው ድምጽ ተሰማው። የክፍሉን በር ከፍቶ እንደያዘ ዞር ብሎ ተመለከተ።

"ማን ነው? ብለዋል አትዬ...ማን ልበላቸው ስሞትን?" አለች የላኩት ልጅ ስሙን ባለማስታወሷ እያፈረች።

"ይሻላል? ሀ! ሀ! ሀ! ሀ!" ልጅቷ ላይ አንባረቀባት። "ብላ ብላ ደግሞ 'ማነው' ትለኝ ጀመር? እንደምትያት ... 'መታወቂያ ወረቀቱን ብልክ አይሻልም ወይ?'ብሏል በያት" ጊዜ ሳይሰጣት ወደ ክፍሉ ገባ። "ማነሽ...ደሞ ሻማና ክብሪት ይዘሽልኝ ተመለሽ፡ አምፖላችሁ ተቃጥሏል። እንደው ነውኮ እዚህ የምንመጣ። የናንተ አስተናጋጅነት ድሮ ቀረ።" በሩን ዘጋው።

አለቅጥ መዝናናቱ ልጅቷን ግራ እንደሚያጋባትና እመቤቷ በቅርብ የሚያውቁት ሰው ነው ብላ እንድታስብ እንደሚያደርጋት ገብቶታል። ክፍሉ ውስጥ ከገባ በኋላ ቢላ የጨበጠ ቀኝ እጁን ኪሱ ውስጥ ከትቶ አልጋው ላይ ተቀመጠና ጨለማው ላይ አፈጠጠ።

ቢላውን የጨበጠበት እጁ በላብ ሲጠመቅ አውጥቶ ሱሪው ላይ ሞዠቀው። መፍራት የለበትም በፍፁም! አሳዳጆቹ ፍርሀት የሚገባቸው፤ ርህራሄ የሚውጣቸው አይደሉም። አንገቱን እርደው ቱቦ ውስጥ ሊጥሉት የተዘጋጁ ናቸው። ፍርሀት አይበጀውም። ፍርሀት አያዋጣውም።

ምንድነው የሚላት? ሊያስፈራራት አይገባም። እሱም እንደ ካልቨርት ተባራሪ መሆኑን ነው ሊያሳምናት የሚገባው። ያን ጊዜ ነው የምታምነው፤ ካልቨርትን ባየችበት አይኗ የምታየው። እንቢ ካለች ግን በራሷ ቢላዋ ያባብላታል።

ያለበት ክፍል በር ወደ ውስጥ ተከፈተ።

"እንዴ! ምነው ጨለማ ውስጥ ?!" ለሴት ጎርነን ያለ ድምፅ።

"አምፖልሽ ተቃጥሏል ምስርዬ። ሻማ በያት ልጅቷን።" አለ ናትናኤል በጭለማ ውስጥ እንደተቀመጠ ተዝናንቶ። ልቡ ትቹህ ልብረር-ልብረር አለው።

"ማነህ?" አለ ያው ጎርነን ያለ የሴት ድምፅ ጥርጣሬ የገባው በሚመስል ቃና።

"እስቲ ሻማው ይምጣና እንተያያለን።" ቢላውን ጨምቆ ያዘው። ክፍሉ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ሻማውን መለኮስ የለባትም! ማን መሆኑን መለየት የለባትም! አትለየውማ! አታውቀውማ!

"ማነሽ ... ብርክቲ ... እስቲ ከአንደኛው ክፍል አንድ አምፖል አምጪ።" ከበር የቆመችው ሴት የካልቨርት ወዳጅ ያለበትን ክፍል መዝጊያ ከፊት አድርጋ እንደቆመች ስትናገር ተሰማው።

"ይኸው ሻማ አምጥቻለሁ።" አለ የሌላ ሴት ድምፅ።

"በይ አምጪው ሻማውን። ሂጂና ከአንዱ ባዶ ክፍል ደህና አምፖል አውልቀሽ አምጪ።" አለች ከበር የቆመችው ሴት።

"ይሁን - ይሁን፤ ሻማ ካለ ይበቃል።" አለ ናትናኤል ጮክ ብሎ።

ከበር የነበረችው ሴት የያዘችውን በር ገፋ አድርጋ ወደ ውስጥ ገባችና የክብሪቱን ሳጥን ከፍታ ክብሪት ማውጣት ጀመረች።

"ክበሩ ዞር በይ! ንፋሱ ያጠፋብሻል።" አለና ድንገት ብድግ ብሎ ከጀርባዋ ያለውን መዝጊያ ዘጋው። ቆለፈው። "አምጪው" ብሎ ሻማውንና ክብሪቱን ከእጇ ቀማት።

"እንዴ! ቆይ ልለኩሰው እንጂ!" ሴትየዋ በጨለማው ውስጥ ግራ ተጋብታ ቆመች።

ናትናኤል ተንጠራርቶ እጁን አወናጨፈና በክፍሉ መሃል የተንጠለጠለችውን ሲገባ ያላላትን አምፖል ሲያገኝ መልሶ አጠበቃት።

ክፍሉ በብርሃን ተሞላ።

ድንገት በብርሃን በተጥለቀለቀው ክፍል ውስጥ ለሴኮንዶች አይኖቻቸውን እያጨናበሱ ተፋጠጡ። ከጠበቃት በላይ ወጣት ነች። ከሰላሳ አትበልጥም። ለሴት በጣም ረጅም ነች። ከታች እስከላይ ሙልጭ ብሎ የወጣው ቀይ ገላዋ ደህና እንደተያዘ ጮኾ ይናገራል።

"ማነህ?" አፈጠጠች።

"አታውቂኝም አላውቅሽም። የምረዳሽ የምትረጂኝ ነገር ስላለ ብቻ ነው እንቺጋ የመጣሁት።" አለ ጀርባውን ለበሩ ሰጥቶ እንደቆመ ፊት ለፊት እየተመለከታት።



"ምንድነው የምረዳህ?" አንድ እርምጃ ወደ ኋላ አፈገፈገች።

"አትፍሪ፤ እንቺን የሚያሰጋሽ ነገር የለም። ስሚኝ..." ካልቨርት ያላትን ነው መድገም ያለበት... ካልቨርት ያላትን! "ስሚኝ..." አለ ድጋሚ ምራቁን ውጦ።"ሲገድሉኝ የሚያባርሩኝ ሰዎች አሉ። መሸሸግ አለብኝ፤ ከኋላዬ እንደ አብድ ውሻ የሚያሯሩጡኝ ሰዎች አሉ። መደበቅ አለብኝ፤ መሸሽ አለብኝ። ግን ደግሞ መሸሽ ብቻ በቂ አይደለም። አንድ ቀን እያንዳንዳችንን ከያለንበት ከየተደበቅንበት ፈልፍለው ያወጡናል። እየረዱ በየስርቻው ይጥሉናል።" ለአንድ አፍታ ትክ ብሎ ተመለከታት። "ይህ ከመሆኑ በፊት ልናቆማቸው ይገባል። ልንገታቸው ይገባል። ልንገታቸው የምንችለው ደግሞ እኛ ተባራሪዎቹ በአንድነት ስንጋፈጣቸው ብቻ ነው። በየአቅጣጫው ተበታትነን በመደበቅ አይደለም።" ንግግሩን አቋርጦ በዝምታ ተመለከታት። ፍርሃት ፊቷን አስምጦታል። ቢሆንም የተናገረው ሁሉ እንቆቅልሽ እንዳልሆነባት ግልፅ ነበር። ፊቷ ላይ የሚያንገበግበው ፍርሃት እንጂ መደናገር አልነበረም።

"እና... እኔ ምንድነው የምረዳህ?"

"ከካልቨርት ጋር ሆኜ እነዚህን አውሬዎች ልጋፈጣቸው ነው የምፈልገው። ከካልቨርት ጋር ብታገናኝኝ..."

"ካልቨርት የት እንዳለ አላውቅም።" አቋረጠችው። ሮጣ ከክፍሉ ልትወጣ እንዳሰበች ሁሉ ከጀርባው ያለውን በር አሻግራ ተመለከተች።

"ትክክል ነሽ። መደበቅሽ ትክክል ነው። ምክንያቱም የሚያሳድዱን አውሬዎች እኛን አጃቸው ለማስገባት የማይፈጥሩት ዘዴ የማይሞክሩት መንገድ የለም። ግን እመኚኝ። እኔም እንደ ካልቨርት ተባራሪ ነኝ። እኔም እንደ ካልቨርት ታዳኝ ነኝ። እርጂኝ። ራስሽንም ካልቨርትንም ልረዳ እችላለሁ። ልናቆማቸው እንችላለን፤ልንገታቸው እንችላለን። ግን ካልቨርትን ማግኘት አለብኝ። ብቻዬን ወደጨለማው መውጣት አልችልም። ረዳት እፈልጋለሁ። ካልቨርትን እፈልጋለሁ"

"ነገርኩህ። ስለካልቨርት የማውቀው ነገር የለም።"

ያለበት ክፍል በር ድንገት ተንኳኳ።

"ማነው?" አለ ናትናኤል ፊቱን ወደ መዝጊያው መልሶ።

መልስ የለም። በሩ ድጋሚ ተንኳኳ። ናትናኤል ደነገጠ። በግዛ እጁ እንደ አይጥ ሮጦ ወጥመዳቸው ውስጥ እንደገባላቸው ተረዳ። ዞር ብሎ የካልቨርትን ወዳጅ ተመለከታት።

"እዚህም አሉ?" አላት በደፈናው። ምን ለማለት እንደፈለገ ግን ለራሱም ግልፅ አልነበረም።

ለአንድ አፍታ ከተማማች በኋላ በአምንቷ ጭንቅላቷን ነቀነቀችለት።

ሰውነቱ ሲግል ተሰማው። ልቡ ያንን ደረቱን ይነርተው ጀመር። አፉ ክው ብሎ ደረቀ። ወደ በሩ ተጠጋ።

"ማነው?" አለ ድንገት ፍርሃቱን ከድምፁ ላይ ለመደምሰስ እየጣረ።

"አምሃ'ሉን አምጥቻለሁ" አለ የሴት ድምፅ።

ሰውነቱ ሲረጋጋ ውሃ እንደፈሰሰበት ሁሉ ከላይ እስከታች ሰውነቱን ቀዘቀዘው።

"ተይው... ሳልቶ ነበር አምሃ'ሉ፤ አጥብቄዋለሁ።" አላት ወደ በሩ ጠጋ ብሎ።

ፊቱን መልሶ ቆመ። ግንባሩ ላይ ችፍፍ ያለውን ቀዝቃዛ ላብ በክንዱ ሞገርቀው። ትክ ብላ የምትመለከተውን የካልቨርትን ወዳጅ አይኖች ሲያይ ፍርሃቱን ከፊቱ ላይ እንዳነበበችው ተረዳ። 'ምናልባት በካልቨርት ፊት ላይ ያነበበችው ፍርሃት ታውሷት ይሆናል።' ብሎ አሰበ።

"ለምንድነው የሚያባርሩህ?" አለችው። እርጋታዋ አስደነቀው።

"ካልቨርት አልነገረሽም?" አላት አልፏት ሄዶ አልጋው ጫፍ ላይ እየተቀመጠ።

"አልነገረኝም። ሊነግረኝ የሚችለው ነገር እንዳልሆነ ስላስረዳኝ አስጨንቀ አልጠየኩትም።"

"ትክክል ነው ያደረገው። ቢነግርሽም ዋጋ አይኖረውም።" አለ ምሥጢሩን እንደሚያውቅ ሁሉ አይኖቹን በባዶው ግድግዳ ላይ ተክሎ።

"ለምንድነው ለፖሊስ የማታስታውቀት?" ለመጀመሪያ ጊዜ ድምጿ ውስጥ ጭንቀት አቃጨለ። "እስከመቼ ተደብቃችሁ ትኖራላችሁ?"

"ከፖሊስ በላይ ናቸው።"

"ነግሮኛል። ይህንንና ሌላም ነግሮኛል የሴፍ። ግን ቢሆንም ሕይወታችሁን ሁሉ በድብብቆሽ ልታሳልፉት አትችሉም!"

"ትክክል ነሽ። እኔም የምለው ይሄን ነው። ተባራሪዎች እኔና ካልቨርት ብቻ አይደለንም። ሌሎችም አሉ። ግን እስከመቼ ተደብቀን



እንዘልቃለን? ለዚህ ነው የሚመጣውን ሁሉ ተጋፍጠን መቆም አለብን የምለው። ምናልባት ጥቂቶቻችን ሕይወታችንን እናጣ ይሆናል። ግን ይህ ምንም አይደለም። የተቀሩት ንፁህ አየር ተንፍሰው ይኖራሉ።"

"ታዲያ ለምን...?"

"ለዚህ ነው።" አቋረጣት። "ለዚህ ነው ካልቨርትን የምፈልገው፤ ሌሎቹንም እየዞርኩ የምፈልገው። ጥቂቶቹን አግኝቻቸዋለሁ አብዛኞቹ ግን አብረውኝ ሊቆሙ ፈቃደኛ አይደሉም። እንደ ቱሃን መሽሽትን እንደ አይጥ መሽሎክሎክን ነው የመረጡት።" ለጥቂት ሴኮንዶች ዝም አለ።

ዓይኖቿን ሳትሰብር ትክ ብላ ተመለከተችው። ለአንድ አፍታ ፊቷ ላይ ሃዘኔታ ያነበበ መሰለው።

"ካልቨርት የት ነው ያለው? እርጂኝ።" ድምፁን ለስለስ አድርጎ ጠየቃት።

ድንገት ከየት መጣ ሳይለው ጥርጣሬ ፊቷን ሸፈነው።

"አላውቅም።"

ተስፋ እንደቆረጠ ሁሉ ትንፋሹን በረጅሙ ለቅቶ ወደ ወለሉ አቀረቀረ።

"እየው።" መጥታ አጠገቡ አልጋው ላይ ተቀመጠች። "ምናልባት እውነትህን ሊሆን ይችላል። ግን የሴፍ ሊረዱት የሚፈልጉ ወገኖች እንደሌሉና አድራሻውን ለማንም መናገር እንደሌለብኝ አስጠንቅቆኛል።"

"እውነቱን ነው። ማንም ሊረዳው የሚፈልግ ሰው የለም። እኔም እራሴ ካልቨርትን ለመርዳት ስል አይደለም ከሞቀ ቤቴ በሌሊት የወጣሁት። ትሰሚኛለሽ? ! ለነፍሴ፣ ለግል ሕይወቴ ፈርቼ ነው። ግን የኔ፤ የካልቨርትና የሌሎቹም ሕይወት የሚተርፈው ከተደበቅንበት ወጥተን አሳዳጆቻችንን ስንገታቸው ብቻ ነው። እንደ ሰጎን ጭንቅላታችንን አሸዋ ውስጥ ቀብረን ስለቆምን አይደለም። እመኚኝ ያገኙናል። እመኚኝ። አንድ በአንድ እየረዱ ይጥሉናል። ካልቨርት የት ነው ያለው?"

"ጥሩ ... ጊዜ ስጠኝ... በመጀመሪያ እሱ ምን እንደሚል መልዕክት ልኬ ማወቅ አለብኝ። ስምህ ማነው? ማን ልበለው?" አለች ክንዱን ያዝ አድርጋ ትክ ብላ እየተመለከተችው።

"ጊዜ የለኝም! ጊዜ የለኝም! ከኋላዬ እያሳደዱ የሚሮጡት ተከታዮች የሚፈልጉት ነፍሴን ነው! ተረዳሽኝ! ነው ይገባሻል?! አንቺ ከካልቨርት

ጋር እስክትመካከሪ ልጠብቅ አልችልም!" በንዴት ተንቀጠቀጠ።

"ይቅርታ፤ ምንም ላደርግልህ አልችልም። " ከተቀመጠችበት ተነሳች።

"ይቅርታ አትጠይቂኝ። የእኔን ነፍስ ብቻ አይደለም ስጋት ላይ የጣልሽው፤ የካልበርትንም ነው። አመኚኝ ያገኙታል። የጊዜ ጉዳይ ነው፤ያገኙታል። ዓይንሽ ፊት አርደው ይጥሉታል። ይህ ከመሆኑ በፊት አርጂው! የት ነው ያለው ካልበርት?" ከተቀመጠበት ተነሳ። ቢላው! ቢላው! ልምምጥ ካልገባት የራሷ ቢላዋ ጠልቆት ይገባል። ቢላውን ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ ያዘው።

አይኖቿ ቢላው ላይ ሲያርፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊቷ ገረጣ።

"ምን ልታደርግ ነው?"

"ምን የማደርግ ይመስልሻል? ጓደኞቼ እንዴት እንደተገደሉ ልተርክልሽ? ከሞቀ ቤቴ ወጥቼ እንደቀረሁ ላዋይሽ? የገዛ ፊቴን እንደ እስስት እየቀያየርኩ እንዳበደ ውሻ እንዴት እንደምሮጥና እንደምክለፈለፍ ላውጋሽ?" ቢላውን እንደያዘ ተጠጋት።

"አትነካኝም!" አለች የማይታይ ክለላ እንዳላት ሁሉ ከቆመችበት ሳትንቀሳቀስ። "ጫፌን ብትነካኝ ዮሴፍ ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ"

"ካልበርት እንደ እኔ ተባራሪ ሚዳቆ ነው። ምን ሊያደርግ ይችላል?" ቢላውን ወደፊት ገፋ አድርጎ ተጠጋት።

"ያወጣዋል!" ጮኸችበት። "ምሥጢራችሁን ሁሉ ያወጣዋል። ደግሞ ነግሬችኋል። አትነኩኝም!" ፍርሃትና ጥርጣሬ ድምጿን ይነዝረው፣ እንደ በገና ክር ያርገበግበው ጀመር።

"እኔ ምን የምፈልግ ይመስልሻል ታዲያ? ያንን ነውኮ የምፈልገው፤ ምሥጢሩ መውጣቱን ነውኮ የምፈልገው! ገባሽ?!" አምባረቀባት። "ካልበርት የጠፋው የተሸሸገው የኔን ምሥጢር ይዞ አይደለም። ምሥጢሩን ቢያወጣው በሃሳም እቤቴ እመለሳለሁ።" ቢላውን እንደያዘ ቀረባት። ሊይዛት ግራ እጁን ሲሰድ በድንጋጤ ወደኋላ ስታፈገፍግ ቀይ የአልጋ ልብስ በለበሰው አልጋ ላይ ወደቀች። ለአንድ አፍታ ጮኸች።

በሩ ተንኳኳ።

ናትናኤል ፊቱን መለስ አድርጎ አዳመጠ። ድጋሚ ተንኳኳ። ናትናኤል ግራ እጇን ለቀም አድርጎ ድምፅ እንዳታሰማ ቢላውን አንገቷ ስር ሸጉጦ በምልክት አስፈራራት።



"ማነው? በይ።" አላት ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ።

"ማነው?" አለች የምሥራች በሚንቀጠቀጥ ድምጿ።

መልስ የለም። በሩ ተንኳኳ።

"ማነው?" አለች የምሥራች ጮክ ብላ። ድምጿ ፍርሃቷንና ጭንቀቷን በከፍሉ ውስጥ አስተጋባው።

መልስ የለም። በሩ ተንኳኳ።

ናትናኤል ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ ሹክ አላት።

"ቆይ መጣሁ... እንዴ ጠብቂኝ!" አለች የምሥራች ጮክ ብላ።

ናትናኤል ዘሎ አልጋው ላይ ወጣና ከራስጌ ያለውን መስኮት በቀስታ ከፈተው። ጨለማ። አሁንም ገፋ አድርጎ ጭንቅላቱን ብቅ አደረገና ተመለከተ። ጭር ያለ ጓሮ። ዞር አለና የምሥራችን ክንድ አፈፍ አድርጎ "ዝለይ" አላት በሹክሹክታ።

"የት ነው የምዘለው?" በፍርሃት የረዘመ ፊቷን ቀና አድርጋ አፈጠጠችበት።

"ለማድረግ የማልፈልገውን ነገር እንዳደርግ አታስገድጂኝ።" አለ የያዘውን ቢላ ጫፍ ወደ እምብርቷ አስጠግቶ። "ጥያቄ አልፈልግም፤ ዝለይ።"

እሷ በመጀመሪያ፤ እሱ ተከትሏት በመስኮቱ ዘለው ወጡ።

"የት ነው የምትወስደኝ?" በግራው ክንዷን ይዞ እየጎተተ በቀኝ በያዘው ቢላ ወገቧን እየነካካ እየገፋት፤ ሲያዋክባት እረ በይ - እረ በይ አላት። ነገር ግን አፏን ብትከፍት በቀኝ የያዘውን ረጅም ቢላ ሽንጧ ላይ እንደሚሰካው ሲሰማት ዝም ማለቱን መረጠች።

"ዝም ብለሽ ነይ፤ ፀአጥሩ ላይ እንዘላለን።" አላት በቢላው ጫፍ ወገቧን እየነካካ ወደ ጓሮው የቆርቆሮ አጥር እየገፋት።

"አልችልም!" አለች ድንገት መጋኛ እንደመታት ድርቅ ብላ ቆማ።

"ጥሩ... እኔ ከመዝለሌ በፊት ቢላሽን ሆድሽ ውስጥ አጨምርልሻለሁ።" ፊቱን ወደፊቷ አስጠግቶ በጥርሶቹ መሃል ተናገራት።

"አልችልም ነው'ኮ የምልህ! እንዴት ነው በአጥሩ የምዘለው?" አለች በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች በልመና ድምፅ። "የስርቆሽ በር አለ፤ በዚያ አስወጣሃለሁ። እኔን ተወኝ። አልናገርም።"

"የታለ የስርቆሹ በር?" ናትናኤል አብርሃም የነገረው ትዝ አለው '...ካዛንቺስ ከወዳጁ ቤት የሴት ልብስ ለብሶ ድሪያ ተከናንቦ በስርቆሽ በር ሲወጣ አየው...' "የታል" አላት ደግሞ።

ሳትናገር ወደ ግራ እጥፍ ብላ ዙሪያውን በቆርቆሮ ከታጠረው ግቢ በአንደኛው መዓዘን ከጓሮ ወዳለች ትንሽ በር ወሰደችው።

"ልቀቀኝ!" ይዟት ከግቢው ሲወጣ ሲል ክንዷን ለማስለቀቅ እየታገለች ሙኸች።

የቢላውን ጫፍ ትከሻዋ ላይ ተከለና የለበሰችውን ቀሚስ በጡቶቿ መሃል ቁልቁል ቀረደደው። በድንጋጤ በድን ሆነች።

"ድጋሚ ድምፅሽን አሰሚና ይህን ቢላ ዓይንሽ ውስጥ እጨምረዋለሁ። ተጠንቀቂ። እርቂ ከመሄዴ በፊት አልለቅሽም። ካሁን በኋላ እንዳትታገይኝ!" በጭለማው ውስጥ አፈጠጠባት።

ድንገት ከጀርባቸው የሰው ዱካ ተሰማቸው።

ክንዷን እንደያዘ በስርቆሽ በሩ ወጣና እየጎተታት ቀን ባጠናት ከዋናው መንገድ ተገንጥላ ወደ ሠፈር ውስጥ በምትገባው ቁልቁለት ተንደረደረ።

መንገዱ ጭር ብሏል። በግራና በቀኝ የተደረደሩት ትናንሽ መሸታ ቤቶች በሮቻቸውን ገርበብ ገርበብ እንዳደረጉ ደንበኞቻቸውን ያስተናግዳሉ። ክንዷን እንደያዛት ሮጠ።

ከጀርባቸው የቆርቆሮ ኳኳታ ተሰማ።

"ቁም!"

ወደ ግራ እጥፍ ብሎ በኮረኮንች መንገድ ወደ ውስጥ ገባ። ያደረገችው ረጅም ጫማ ቢያስቸግራትም እየተወለካከፈች አብራው ሮጠች። ከግቢው ከወጡ በኋላ ለራሱም ግልፅ ባልሆነለት ሁኔታ የተለየ ስጋት የያዛት ይመስል፤ እሷም እንደሱው ተባራሪ እንደሆነች ሁሉ አብራው ተጣደፈች።



ከሩቅ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በርሜሎች ሲመለከት ክንዷን ይዞ ወደዚያው ጎተታት።አካባቢውን ባለበሰው የቆሻሻ ክምር ላይ ተሻግረው ከበርሜሎቹ ጀርባ ዞረው ሸብረክ ሸብረክ አሉ።በስተግራ ራቅ ብሎ መደዳውን ከተኮለኮሉት የመሸታ ቤቶች የሚወጣው ደብዛዛ ብርሃን አካባቢውን በድቅድቁ ጨለማ ከመዋጥ አድኖታል። ወዲያ ማዶ አንድ የጭነት መኪና ሸራውን ተከናንቦ ጥግ ይዞ ቆሟል። በስተቀኝ የውሾች ጥል በጨለማው ውስጥ አስተጋባ። ድምፃቸውን አጥፍተው ተጠባበቁ።

ናትናኤል ቀና ሲል በጨለማው ውስጥ አንድ ነገር ውልብ ሲል ተመለከተ። ዓይኖቹን በሰፊው ከፍቶ በጨለማው ላይ አፈጠጠ። ድምፅ ተሰማው... እየቀረበች ስትመጣ ሲለያት በእርጂታ ትንፋሹን ለቀቀ። ሀካራም ሴት ነበረች። እንደመንገዳገድ ትልና ወደፊት ትራመዳለች። ትንሽ ታንጎራጉርና ደግሞ ወደፊት ትራመዳለች። ብዙም ሳይቆይ ከሰካራሟ ጀርባ የሌሎች ሰዎች ሩጫ ተሰማ። ናትናኤል ከበርሜሎቹ ጀርባ ሳይወጣ ጭንቅላቱን ብቻ አቅንቶ ተመለከተ።

ሦስት ሰዎች እየተራረረጡ በኮረኮንቹ መንገድ መጡ። በኮረኮንቷ መንገድ ላይ እየተወለካከፉ ሲሮጡ ናትናኤል አዳኞቹ እንደሆኑ ገባው። ሰካራሟ ሴትጋ እንደደረሱ ከሦስቱ አንደኛው የያዘውን ባትሪ መለስ አድርጎ ፊቷ ላይ በግ አደረገባት።

"ትዝታ እ... እባላለሁ።" አለች ሰካራሟ አይኖቿን ከባትሪው ብርሃን በክንዷ ከልላ "ሀ! ሀ! ሀ! ከፈለግህ ደሞ እቤት እንሂድና።"

ባትሪውን ያበራባት ሰው ትቷት ከጓደኞቹ ጋር ወደፊት ቀጠለ። ሦስቱ ሰዎች ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎቹ ሲደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ቆም አሉና ተነጋገሩ። ወዲያው ሁለቱ በስተቀኝ ታጥፈው በጨለማው ውስጥ ሲሰወሩ ባትሪ የያዘው ሰው በበርሜሎቹ አቅጣጫ አመራ።

ናትናኤል አብራው የተደበቀችውን የካልሽርትን ወዳጅ ጠረጠራት። ብትጮህስ? ብትጣራና ብታሲዘውስ? እዚሁ ቆሻሻ መጣያ በርሜል ስር ደፍተውት ሊሄዱ አይደል? ፊጠን ብሎ ቀኝ እጁን በትከሻዋ አሳልፎ አፏን አፈናትና በግራ እጁ የያዘውን የቢላ ጫፍ አንገቷ ስር ሸጎጠው።

"ትንፍሽ እንዳትይ... ፊቱን ከማዞሩ በፊት ይሄ ቢላ ማጅራትሽ ነው የሚደርሰው።" አላት ዓይኖቹን በበርሜሎቹ አቅጣጫ በሮጠው ሰው ላይ ተክሎ።

ሳትነቃነቅ አይኖቿን ብቻ አቅንታ በጭንቀት ተመለከተችው። አንገቷ ስር የተሸጎጠው የቢላ ስለት ለስላሳ ቆዳዋን እንደ ምላጭ ሲሰነጥቀው ተሰማት።

ሰውየው ወደ በርሜሎቹ እየተጠጋ በመጣ ቁጥር በደመነፍስ ያወቀና የተረዳ ይመስል ፍጥነቱን ቀንሶ የባትሪውን ብርሃን እንደ ነብር ጅራት ከወዲያ ወዲህ እያላጋ ዙሪያውን እየፈተሸ በዝግታ ይራመድ ጀመር:: እየቀረባቸው ሲመጣ ናትናኤል በበርሜሎቹ አናት ላይ ተመለከተው:: በግራው ባትሪውን እንደጨበጠ በስተቀኝ የኮት ኪሱ ውስጥ የጨመረውን እጁን ሲመለከት ሰውየው መሣሪያ እንደያዘ ናትናኤል ተረዳ:: በየምሥራች አፍ ላይ የጫነውን የቀኝ እጁን ጠበቅ አደረገና በግራው የያዘውን ቢላ ከአንገቷ ስር አውጥቶ ይዞ ተዘጋጀ:: ተጠባበቀ:: ከበርሜሎቹ ዙሪያ የፈሰሰው ቆሻሻ ላይ ሲረግጥ የአዳኙ ኮቴ ኮሽታ ተሰማው:: ሲጠጋውና ሲቀርበው ሲደርስበት ተወርውሮ ቢላውን ሊሰካበት ተዘጋጀ:: ሰውየው ድንገት ቆም አለ:: ያመነታ መሰለ... ባትሪውን ዞር አድርጎ በበርሜሎቹ ላይ አበራ:: የባትሪውን ብርሃን በዙሪያው አወናጨፈው:: ወዲያው ፊቱን መልሶ በኮረኮንቹ መንገድ ወደፊት ቀጠለ::

ሰውየው ከራቀ ወዲያ ነበር ናትናኤል ለመተንፈስ የደፈረው:: የምሥራችን አፍ ለቀቀና ቁና አደረጋት::

"አይዞሽ አትፍሪ፣ ልጎዳሽ አልፈልግም:: እመኚኝ:: ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ነው የምትፈልጊው?" አለ ትከሻዋን በሁለት እጆቹ ይዞ እየነቀነቀ:: "በይ ተነሺ... ሳንቻኮል በእርጋታ እየተራመድን ወደ ዋናው መንገድ እንወጣለን:: ለመሮጥ ወይ ለመጮህ ብትሞክሪ ግን ምርጫ አይኖረኝም::"

"አልሮጥም::" አለች ፊቷን መልሳ በፍርሃት እየተመለከተችው::

ናትናኤል የምሥራችን ክንድ እንዳያዘ ቁጢጥ ካለበት ብድግ ሲል እንቅስቃሴ ታየው:: ተመልሶ ሽብረክ አለና እንዳጎነበሰ አሻግሮ ተመለከተ:: እየተንገዳገደች ቆም ራመድ እንደገና ቆም እያለች በኮረኮንቹ መንገድ ተመልሳ ትመጣለች- ሰካራሟ::

"ተነሺ..." አለ ናትናኤል የምሥራችን ክንድ እየጎተተ:: "ሰካራሟ ነች::"

ከተደበቁበት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በርሜሎች ስር ወጥተው ፈጠን ብለው በዋናው መንገድ አቅጣጫ አመሩ::

"ታዲያስ!" አለቻቸው ከፊት ለፊታቸው እየተወለካከፈች፣ እየተንገዳገደች የምትመጣው ሰካራም::"እስቲ ወንድም ብር ግፋ::" አለችው ናትናኤልን ስትመለከት እጇን ወደፊት ዘርግታ::



"ዞር በይ!" አለ ናትናኤል አልፏት ለመሄድ እየሞከረ:: ድንገት በዘረጋችው መዳፏ ውስጥ የጨበጠችውን ሲመለከት ግን መላ አካላቱን ደነዘዘው:: የምሥራች ከፊቷ የተደቀነውን ስታይ እንዳትጮህ የፈራች ይመስል የገዛ አፏን በገዛ መዳፏ ግጥም አድርጋ ዘጋችው::

"የማይሆን ነገር አትሞክር::" አለች ሰካራሟ የያዘችውን ሽጉጥ ወደ ሆዱ ገፋ አድርጋ:: "ተነቃንቀ...እዘረግፍሃለሁ::" ድንገት ፊቷን ወደ የምሥራች መለሰችው:: "አንድ ዕድል እሰጥሻለሁ፣ ካልቨርት የት ነው?" የሽጉጧን አፈሙዝ መለስ አድርጋ የምሥራች ላይ ደቀነችው:: "ነገሪኝ ጊዜ አትውሰጂ!"

"እኔ አላውቅም::"

በእጁ የጨበጠው የምሥራች ክንድ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው::

"ተኩሼ ሳልቀረድድሽ ንገሪኝ:: ካልቨርት የት ነው?" ሴትየዋ አፏን ሳትከፍት በጥርሶቿ መሃል ተናገረች::

"አላውቅምኮ::" የምሥራች ድምፅ እንደወና ትንፋሽ ሳሳ::ፍርሃት ያንቀጠቅጣት ጀመር::

ሴትየዋ አላመነታችም:: ወደኋላ ጥቂት እርምጃዎች አፈገፈገች:: ናትናኤል ያልጠበቀው ድምፅ 'ቡፍ!' አለ:: የምሥራች እጁ ላይ ተልፈሰፈሰችበት... ለቀቃት...፣ ዝልፍልፍ ብላ በስተቀኙ ተዘረጋች:: ከፊት ለፊቱ ሽጉጧን ደግናበት ከቆመችው ሴት ጋር ተፋጠጠ:: ትንፋሹን ይዞ ጠበቃት:: አእምሮው እርስበርሱ ተጣላበት:: ሊፈነዳ ያሰበ ይመስል ማጅራቱ ሲወጠር ተሰማው:: ዘሎ ይነቃት? ወይስ መጨረሻውን በቆመበት ይቀበል? ድንገት ፊገግ ያለች መሰለው... ፈገግ አለች ሴትየዋ:: ከኋላው የሩጫ ድምፅ ተሰማው:: ከፊት ለፊቱ ቆማ የነበረችው ሴት በፍጥነት የሽጉጧን አፈሙዝ ወደ መሬት መለሰችና ከትከሻው ላይ አሻግራ በጨለማው ላይ አፈጠጠች-

"ሩጥ!" አለችው በሹክሹክታ ወደጎን ትታው የሩጫው ድምፅ ወደመጣበት እየተራመደች:: "ተዋትና ሩጥ!" አለችው ድጋሚ ፊቷን መልሳ:: የምሥራችን እየጎተተ ወደ ጥግ ሲሸሽግ ስታየው:: "እሷን ተውና ሩጥ!"

ናትናኤል ሳይመልስላት የምሥራችን በብብቶቿ ውስጥ ገብቶ እየጎተታት ወደ ጥግ ሸሸግ አለ:: መሬቱ ላይ ተንበርክኮ የምሥራችን ጭንቅላት ቀና አደረገና ትንፋሿን አዳመጠ:: አለች::

"የምሥራች... የምሥራች..." ድምፁን ቀንሶ ተጣራ::

አይኖቿን በትግል ገልጣ ተመለከተችው... እየሞተች ነው... እየቀዘቀዘች ነው... እያበቃች ነው... ሊያድናት እንደማይችል ተረዳ::

"የምስራች... ንገሪኝ... ካልቨርት የት ነው ... ንገሪኝ! ሁላችንን ሳይጨርሰን በፊት ንገሪኝ!"

"ካል...ቨርት ...ዮ..ሴፍ..." ከጉሮሮዋ የሚወጣው ድምፅ ሻከረበት::

"አዎ ዮሴፍ... ዮሴፍ ካልቨርት የት ነው ያለው?"

ከወዲያ የሚሰማው የሩጫ ድምፅ እየቀረበው መጣ... አንድ ሴት ስታንጎራጉር ይሰማል... በጨለማው ውስጥ...

"ዮ...ሴፍ..." የምሥራች ድምፅ በጭንቀት እየተበጣጠሰ ተንጠባጠበ::

"አዎ ...አዎ የት ነው?"

የሩጫው ድምፅ ቀረበ:: ናትናኤል ጭንቅላቱን መልሶ ከጀርባው ተመለከተ:: ሰካራሟ መሀል ኮረኮንቹ ላይ እየተንገዳገደች ወደፊት ራመድ ትልና እንደገና ቆም ብላ ታንጎራጉራለች...

"ንገሪኝ የምሥራች... ካልቨርት የት ነው?"

"ዮሴፍ... እ... እማዬጋ" አየር ለመሳብ ስትታገል ደረቷ ሽቅብ ተሰቀለ::

"የት ... የት?"

"እ..እማዬጋ ...ድሬ...ዳዋ..." የጀመረችውን ከመጨረሷ በፊት ሰውነቷ ተዝለፍልፎ ክንዱ ላይ ወደቀች:: ናትናኤል ቀና ሊያደርጋት ሞከረ:: አብቅታለች:: ሰውነቱ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነበት:: ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ለመሮጥ ተዘጋጀ:: ከወዲያ እየሮጠ የሚመጣው ሰው ሰካራሟጋ ሲደርስ በጨለማው ውስጥ ታየው:: አዳኙ ወደ ሴትየዋ እንደደረሰ በግራው የያዘውን ባትሪ ፊቷ ላይ ቦግ አደረገውና ወዲያው ወደጎን ገፍተር አድርጓት አለፈ... ከመቅፅበት ባትሪውን ወደጎን መለስ አድርጎ ናትናኤል ላይ ሲተክለው ናትናኤል ቁጢጥ ካለበት መነሳት ተሳነው::

አዳኙ ቀኝ እጁን ከኪሱ መንጭቆ አውጥቶ ሽጉጡን ደግኖ ይዞ ተጠጋው::

"አገኘሁህ!" አለ ወደ ውጭ ተንፍሶ:: ወዲያው ከናትናኤል ጎን የተዘረጋውን የምሥራችን ሰውነት ሲመለከት አይኖቹ ከየጉድጓዶቻቸው ወጡ:: "ገደልካት?!" አለ የሚያየውን ማመን አቅቶት አፉን በድንጋጤ ከፍቶ::

"እኔ አይደለሁም! እኔ አይደለሁም!" አለ ናትናኤል ጭንቅላቱን በጭንቀት እየርገፈገፈ::

ሰውየው በጥላቻ ቁልቁል ተመለከተው:: "ከሃዲ! ያንተ ዓይነቶቹ ውሾች ናቸው ለባርነት የዳረጉን! ዝርክርክ!" ሽጉጡን አንስቶ አነጣጠረበት::



ናትናኤል ጉሮሮው እንደኮረት ሲወጠርበት ልሳኑ ሲከዳው... ሁለት እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ አውለበለባቸው:: 'አርፌህ በሠላም ኑር...እንደ እሳት እራት ወደ ፍሙ... ተጠንቀቅ...'የሽጉጡን አፈሙዝ ተመለከተው... እንደ አጋንንት ከፊቱ ተደቅኖ ሲያየው ሰውነቱ ፈሰሰ... አይኖቹን ጨፈናቸው... ርብቃ! ...'ቡፍ!' ሲተኮስ ተሰማው:: የትጋ እንደተመታ አልታወቀውም:: እላዩ ላይ ወደቀበት:: ዓይኖቹን ገልጦ ግራ ተጋባ:: አዳኙ እላዩ ላይ ተዘርግፎበታል:: ዓይኖቹ ከየጎሬአቸው ወጥተው ተንልጉለዋል:: በጭንቅ የገጠመው ጥርሱና ከጉሮሮው የሚወጣው ሲር ሲር የሚለው ድምፅ... ባንድ ወገን ከአፉ ቡልቅ ብሎ የወጣ ደም ደረቱ ላይ ሲረጭ... ናትናኤል ሰውየውን ከላዩ ገፍትሮ አገለለው:: ቁጢጥ ባለበት ጥይት የበሳውን ገላውን አዳመጠ:: የለም:: ከተቀመጠበት ተነሳ::

ራቅ ብላ በቀኟ ያንጠለጠለችውን የሽጉጥ አፈሙዝ ወደ መሬቱ መልሳ ቆማለች:: ፈገግ አለችለት:: ጀርባውን ለግድግዳው እንደሰጠ ተመለከታት::

"ሩጥ::" አለችው ፈገግ ብላ::

ሮጠ::

ሮጠ ናትናኤል:: በኮረኮንቹ አድርጎ ቁልቁል በመጣበት ቀጭን መንገድ ሽቅብ በረረ:: ከኋላው የተከተለው አጋንንት እንዳለ ሁሉ በጨለማው ውስጥ እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ በነነ:: በአካባቢው ድምፅ አልነበረም:: ጠባቧን የኮረኮንች መንገድ ጨርሶ ከመውጣቱ በፊት ብቻ ከጀርባው ሳቅ አጀበው:: የሴት ሳቅ-የሰካራም ሳቅ-

"ሃ! ሃ! ሃ! ...ሂ!ሂ!ሂ! ሂ!"

-22-

በጥፊ ጆሮ ግንዷን አናጋው::

ለጥቂት ደቂቃዎች ያለችበት ጠፋት፤ዙሪያዋ ጨለማ ለበሰ:: እዛው አፓርትመንት ክፍሏ ውስጥ እጆቿንና እግሮቿን ከአልጋዋ ጋር በአንሶላ ጨርቅ ጥፍር አድርገው አስረው እንዳትጮህ አፏ ውስጥ ጨርቅ ጎስጉሰው ለጉመው አጋድመዋታል::

"ንገሪኝ!" አለ ድጋሚ ሊያጣፋት እየተንጠራራ "የት ነው ያለው? ትነግሪኛለሽ አትነግሪኝም?"

“የምስራች... ንገሪኝ... ካልቨርት የት ነው ... ንገሪኝ! ሁላችንን ሳይጨርሱን በፊት ንገሪኝ!”

“ካል...ቨርት ...ዮ..ሴፍ...” ከጉሮሮዋ የሚወጣው ድምፅ ሻከረበት።

“አዎ ዮሴፍ... ዮሴፍ ካልቨርት የት ነው ያለው?”

ከወዲያ የሚሰማው የሩጫ ድምፅ እየቀረበው መጣ... አንድ ሴት ስታንጎራጉር ይሰማል... በጨለማው ውስጥ...

“ዮ...ሴፍ...” የምሥራች ድምፅ በጭንቀት እየተበጣጠሰ ተንጠባጠበ።

“አዎ ...አዎ የት ነው?”

የሩጫው ድምፅ ቀረበ። ናትናኤል ጭንቅላቱን መልሶ ከጀርባው ተመለከተ። ሰካራሟ መሀል ኮሪኮንቹ ላይ እየተንገዳገደች ወደፊት ራመድ ትልና እንደገና ቆም ብላ ታንጎራጉራለች...

“ንገሪኝ የምሥራች... ካልቨርት የት ነው?”

“ዮሴፍ... እ... እማዬ.ጋ” አየር ለመሳብ ስትታገል ደረቷ ሽቅብ ተሰቀለ።

“የት ... የት?”

“እ..እማዬጋ ..ድሬ...ዳዋ...” የጀመረችውን ከመጨረሷ በፊት ሰውነቷ ተዝለፍልፎ ክንዱ ላይ ወደቀች። ናትናኤል ቀና ሲያደርጋት ሞከረ። አብቅታለች። ሰውነቱ ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነበት። ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ለመሮጥ ተዘጋጀ። ከወዲያ እየሮጠ የሚመጣው ሰው ሰካራሟጋ ሲደርስ በጨለማው ውስጥ ታየው። አዳኙ ወደ ሴትየዋ እንደደረሰ በግራው የያዘውን ባትሪ ፊቷ ላይ ቦግ አደረገውና ወዲያው ወደጎን ገፍተር አድርጓት አለፈ.... ከመቅፅበት ባትሪውን ወደጎን መለስ አድርጎ ናትናኤል ላይ ሲተክለው ናትናኤል ቁጢጥ ካለበት መነሳት ተሳነው።

አዳኙ ቀኝ እጁን ከኪሱ መንጭቆ አውጥቶ ሽጉጡን ደግኖ ይዞ ተጠጋው።

“አገኘሁህ!” አለ ወደ ውጭ ተነፍሶ። ወዲያው ከናትናኤል ጎን የተዘረጋውን የምሥራችን ሰውነት ሲመለከት አይኖቹ ከየጉድጓዶቻቸው ወጡ። “ገደልካት?!” አለ የሚያየውን ማመን አቅቶት አፉን በድንጋጤ ከፍቶ።

“እኔ አይደለሁም! እኔ አይደለሁም!” አለ ናትናኤል ጭንቅላቱን በጭንቀት እየርገፈገፈ።

ሰውየው በጥላቻ ቁልቁል ተመለከተው። “ከሃዲ! ያንተ ዓይነቶቹ ውሾች ናቸው ለባርነት የዳረጉን! ዝርክርክ!” ሽጉጡን አንስቶ አነጣጠረበት።



ናትናኤል ጉሮሮው እንደኮረት ሲወጠርበት ልሳኑ ሲከዳው... ሁለት እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ አውለበለባቸው። 'እርፈህ በሠላም ኑር...እንደ እሳት እራት ወደ ፍሙ... ተጠንቀቅ...'የሽጉጡን አፈሙዝ ተመለከተው... እንደ አጋንንት ከፊቱ ተደቅኖ ሲያየው ሰውነቱ ፈሰሰ... አይኖቹን ጨፈናቸው... ርብቃ! ...'ቡፍ!' ሲተኮስ ተሰማው። የትጋ እንደተመታ አልታወቀውም። እላዩ ላይ ወደቀበት። ዓይኖቹን ገልጦ ግራ ተጋባ። አዳኙ እላዩ ላይ ተዘርግፎበታል። ዓይኖቹ ከየጎሬአቸው ወጥተው ተጎልጉለዋል። በጭንቅ የገጠመው ጥርሱና ከጉሮሮው የሚወጣው ሲር ሲር የሚለው ድምፅ... ባንድ ወገን ከአፉ ቡልቅ ብሎ የወጣ ደም ደረቱ ላይ ሲረጭ... ናትናኤል ሰውየውን ከላዩ ገፍትሮ አገለለው። ቁጢጥ ባለበት ጥይት የበሳውን ገላውን አዳመጠ። የለም። ከተቀመጠበት ተነሳ።

ራቅ ብላ በቀኟ ያንጠለጠለችውን የሽጉጥ አፈሙዝ ወደ መሬቱ መልሳ ቆማለች። ፈገግ አለችለት። ጀርባውን ለግድግዳው እንደሰጠ ተመለከታት።

“ሩጥ።” አለችው ፈገግ ብላ።

ሮጠ።

ሮጠ ናትናኤል። በኮረኮንቹ አድርጎ ቁልቁል በመጣበት ቀጭን መንገድ ሽቅብ በረረ። ከኋላው የተከተለው አጋንንት እንዳለ ሁሉ በጨለማው ውስጥ እጆቹን ወደፊት ዘርግቶ በነነ። በአካባቢው ድምፅ አልነበረም። ጠባቧን የኮረኮንች መንገድ ጨርሶ ከመውጣቱ በፊት ብቻ ከጀርባው ሳቅ አጀበው። የሴት ሳቅ-የሰካራም ሳቅ-

“ሃ! ሃ! ሃ! ...ሃ!ሂ!ሂ! ሂ!”

## -22-

በጥፊ ጆሮ ግንዷን አናጋው።

ለጥቂት ደቂቃዎች ያለችበት ጠፋት፤ዙሪያዋ ጨለማ ለበሰ። እዛው አፓርትመንት ክፍሏ ውስጥ እጆቿንና እግሮቿን ከአልጋዋ ጋር በእንሶላ ጨርቅ ጥፍር አድርገው አስረው እንዳትጮህ አፏ ውስጥ ጨርቅ ጎስጉሰው ለጉመው አጋድመዋታል።

“ንገሪኝ!” አለ ድጋሚ ሲያጣፋት እየተንጠራራ “የት ነው ያለው? ትነግሪኛለሽ አትነግሪኝም?”

ጭንቅላቷን በጭንቀት አርገፈገፈችው፡፡ ከተሰነመው አፏ ጀርባ ጉሮሮዋ - "የት እንዳለ አላውቅም፡፡ እውነቴን ነው!" አለች፡፡ ድምፅ ግን አላወጣችም፡፡

ውልብ አለባት ድጋሚ፡፡ ጆሮዋ ላይ ሌላ ጥፊ ደወለ፡፡
"ንገሪኝ!"

ዱላው እየጨመረ በመጣ ቁጥር እልኂና ቁጣዋ 'እንዴት ተደፈርኩ' ባይነቷ እንደጪው እየሟሙ ለማይታክተው እንባዋ አስረከበዋታል፡፡ ፀጉሯ ሲጨመደድ ተሰማት፡፡

"ንገሪኝ! የት ነው ያለው?"
ድጋሚ በጥፊ አይኖቿን ከደናቸው፡፡
"ንገሪኝ!"

ተከትሎ ምን እንደተናገረ አልሰማችውም፡፡ ጆሮዋ ላይ የሚደውለ ውን ስቃይ ተከትሎ ዙሪያዋ ፅልመት ተከናነበ፡፡ አይኖቿን ድጋሚ ስትገል ጣቸው ሰውነቷን ክፉኛ ቀዘቀዛት፡፡ለሶስተኛ ጊዜ ውሃ አፍስሰውባታል፡፡ አልጋዋ በየደቂቃው ህሊናዋን በሳተች ቁጥር በሚቸለስባት ቀዝቃዛ ውሃ ረስርሷል፡፡ የለበሰችው ስስ ቀሚስ አላይዋ ላይ ተጣብቋል፡፡

ዓይኖቿን ገርበብ አድርጋ ተመለከተቻቸው፡፡ ሶስቱም በአልጋዋ ዙሪያ ቆመው ቁልቁል ይመለከቷታል፡፡ ሁለቱን አታቃቸውም፡፡ ሶስተኛው ግን ያው የህዋሷ መሪ ማርቆስ ነበር፡፡ በጠባሳ የተገመሰ ፊቱን ቁልቁል አንዘርቦ ይመለከታታል፡፡ ደጉን የተወያየችው የገዛ ጓደኛዋ አልመስልሽ አላት፡፡ አይኖቿን ጭምቅ አድርጋ ጨፈነቻቸው፡፡ በተንጋለለችበት እንባዋ የገዛ አይኖቿን እንደጪው እየለበለበ ፈሰሰ፡፡

"ከሃዲ!" አለ በስተግራዋ የቆመው ሌሊቱን ሲጠፈጥፋት ያደረው ሰው - ድንገት ፊቱን መልሶ የመኝታ ክፍሏን በር ከፍቶ እየወጣ፡፡

በክፍሉ ውስጥ የቀሩት ሁለት ሰዎች ለጥቂት ደቂቃዎች ያለ እንቅስቃሴ ቁልቁል ሲመለከቷት ቆዩ፡፡ ወዲያው ማርቆስ ጠጋ ብሎ አፏ የተሰነመበትን ጨርቅ መፍታት ጀመረ፡፡ ሸቅብ ፊቱን ስትመለከተው ከዓመት በላይ የምታውቀው አብራው የቀለደችና የሳቀች ያው የድሮው የህዋሷ መሪ ማርቆስ መሆኑን ማመን አቃታት፡፡

"ምን ማድረግህ ነው?" አለ ከበስተግርጌ የቆመው ጺማም ሰውዬ- ማርቆስ አፏ የተሰነመበትን ጨርቅ ሲፈታላት ሲያይ እየተቁነጠነጠ፡፡

ማርቆስ ለሰውየው መልስ ሳይሰጠው አፏን ሞልቶ ተርፎ የነበረውን ቡትቶ ጨርቅ ጎትቶ አወጣላት፡፡ ተበርግዶ የቆየ መንጋጋዋ የራሷ



መንጋጋ እንዳልሆነ ሁሉ አልገጥምልሽ አላት፡፡ ደርቆ የቆየ ጉሮሮዋ የገዛ ምራቋን አልውጥልሽ አላት፡፡ እንባዋ ብቻ ጉንጮቿን እየተለተለ መውረዱን ቀጠለ፡፡

"ርብቃ ...ለምን ለእኛም ለራስሽም አስቸጋሪ ትሆኛለሽ?" ማርቆስ ቁልቁል እየተመለከተ ተማፀናት፡፡ "ርብቃ ልለምንሽ... የት እንዳለ ንገሪንና ይህ ሁሉ ያብቃ፡፡" ተለማመጣት፡፡

ለምን አይገባቸውም?! ናትናኤል የት እንደለ አላውቅም ስትላቸው ለምን አያምኗትም?! እንዴት አድርጋ ነው እውነቱን እውነት ነው የምትላቸው?

"የት እንዳለ አላውቅም፡፡" ልትል ፈለገችና ጉሮሮዋ አልታዘዝሽ አላት፡፡ በጀርባዋ በተንጋለለችበት ጭንቅላቷን ነቀነቀች፡፡

"ርብቃ ጊዜ በወሰድሽ ቁጥር ሁኔታው ለራስሽ እየከፋ ነው የሚሄደው፡፡ የምትጋፈጫቸው ሰዎች ትዕግሥታቸው ያለቀና ቁጣቸው ወደ ዕልህ የተቀየረ ራሳቸውን መቆጣጠር የማይችሉ ናቸው፡፡ ርብቃ እነዚህ ሰዎች ሊያደርጉት የሚገፋፉትን ደግሞ ማንም አይወደውም፡፡ አንቺ ሴት ነሽ፡፡ እነዚህን ሰዎች የሚቋቋም የመንፈስ ጠንካራነት የለሽም፡፡ በቀላሉ እንደቀርከሃ ሊሰባብሩሽ ይችላሉ፡፡ በቀላሉ! እባክሽን... ንገሪኝ፡፡ ናትናኤል የት ነው?" የሌሊት ሁኔታዋን መቋቋም አቅቶት ሲቁነጠነጥ ያደረው ማርቆስ የባሰ ከመምጣቱ በፊት ሊያሳምናት ታገለ፡፡

"እ...አላውቅም፡፡" አለችው እንባዋን እያስተናገደች፡፡
"ጥሩ፡፡ መስሪያ ቤትሽ ደውሎ ሲያጣሽና ስራ ከገባሽ ውለሽ ማደርሽን ሲረዳ እንዴት እዚህ አልደወለም?"
"ፈርቶ ይሆናል... እኔ ምን አውቃለሁ፡፡" እውነተኛነቷን ይገልፅላት ይመስል ድምጿን አለሰለሰችው፡፡

"ምን? ማንን ነው የሚፈራው?"
"እናንተን፡፡" አለች በለቅሶ መሃል፡፡

"አየሽ! ይህ ማለት አንቺ ከእኛ ጋር ግንኙነት እንዳለሽ አውቋል ወይም በፊትም ያውቅ ነበር ማለት ነው፡፡ ይህን ሊያውቅ የሚችለው ደግሞ አንቺ..."

"አልነገርኩትም!" አለች እቅጣጫውን ስትረዳ አቋርጣው፡፡ "እኔ አልነገርኩትም፡፡እኔ በእርሱ ላይ መረጃ ስሰበስብ መቆየቴንም ጭራሽ አያውቅም፡፡ ግን እዚህ ቢመጣ ልታገኙት እንደምትችሉ ጠርጥሮ ይሆናል፡፡"

"ለምን ድጋሚ መሥሪያ ቤትሽ ስልክ አልደወለም? ባለፈው ጊዜ ሲደውል ጓደኛሽ ቢሮ ክገባሽ ውለሽ ማደርሽን እንድትነግረው አድርገናል:: እዚህ መደወል ወይ መምጣት ነበረበት:: አልመጣም፤አልደወለም:: መሥሪያ ቤትሽም መልሶ አልደወለም:: ለምን?"

"አላውቅም::" አለች በማስተዛዘን::

"ውሸት! አውቂል... ሁሉንም ተረድቶታል:: ለዚህ ነው ሊገናኝሽ ያልሞከረው:: ባያውቅ ኖሮ..."

"ውሸቱን አይደለም!" አቋረጠችው "እመኑኝ ናትናኤል ምንም የማያውቀው ነገር የለም ናት..."

"ያውቃል! ያውቃል! ምንም የማያውቅ ሰው በጭካኔ የሁለት ሰው ነፍስ አጥፍቶ አይሰወርም:: ትሰሚኛለሽ? የፈጸመው ወንጀል ምንም የማያውቅ ሰው የሚፈጽመው አይደለም!" ትከሻዋን በሁለት እጆቹ ይዞ ነቀነቃት::

"ናትናኤል ሰው አይገድልም...ውሸት ነው::" ለራሷ ነበር የተናገረችው::

"ርብቃ... ልምዶችን ያውቁታል:: ለይተው ስላወቁትም ነው የተከተሉት:: ይገባሻል? የካልቨርትን አድራሻ ከሴትየዋ ማግኘት ስላልቻለ ምናልባትም አድራሻውን አስገድዶ ካውጣጣት በኋላ ነው ደረቷን በጥይት የበሳው፤ ገድሏት የሄደው:: አስታውሽ እሷን ብቻ አይደለም ያጠፋው፤ የኛንም ሰው ነው:: ርብቃ... አባብ ነው ሰውዬሽ:: ሁላችንንም አታሎናል:: ምንም የማያውቅ የዋህ መስሎ አታሎናል:: አንቺንም አታሎሻል:: አብረን ልናቆመው ይገባናል:: ንገሪኝ፤ የት ነው የተሸሸገው?"

"አላውቀውም አልኩህኮ::"
ገፁ በንዴት ተኮማተረ::

"ርብቃ..." አይኖቹን አጥብቦ ተመለከታት:: "በአንድ ወቅት ከጎናችን መቆምሽን አንዘነጋውም፤ ያ የሩቅ ትዝታ አይደለም፤ ግን ደግሞ መረባችን በከዳተኞች ምላጭ ሲበጣጠስና ውጥናችን በባንዳዎች ራስ ወዳድነት እርቃኑን ወጥቶ እያንዳንዳችን ለስደትና ለሞት ስንዳረግ በዝምታ መመልከት አንችልም:: ይህ እንዳይሆን ደግሞ የምንጠላውንም ነገር ቢሆን ለማድረግ እንገደዳለን:: ርብቃ ትሰሚኛለሽ? መንፈስሽ መከላሸት ካለበት እናከላሽዋለን፤ ሰውነትሽ መዋረድ ካለበት እናዋርደዋለን፤ ህሊናሽ መጨቅየት ካለበት እናጨቅየዋለን... የማታ ማታ የጠየቅንሽን ሁሉ ታወጪዋለሽ:: ይህ ከመሆኑ



በፊት አስተውዪ:: ናትናኤል አታሎሻል! የሲጋ ፍላጎትሽን ተጠቅሞ ምስጢራችንን ከቀዳ በኋላ አጋልጦሽ ተሰውሯል:: የት ነው ያለው? ናትናኤል የት ነው?"

"አላውቅምኮ" እንባዋ ገና ድሮ በቀደደው ቦይ ይንቆረቆር ጀመር::

የመኝታ ቤቷ በር ተከፍቶ ሦስት ሰዎች ተከታትለው ገቡ:: ሁለቱን አይታቸው አታውቅም:: አንደኛው ግን ከትላንት ጀምሮ ሲቀጠቅጣት የቆየ ነው:: ከፊት ቀደም ያለው ሰው በእድሜ ጠና ያለ ይመስላል:: ወደፊት ራመድ ብሎ ወደ አልጋዋ ግርጌ ከተጠጋ በኋላ በክፍሉ ውስጥ ለተሰበሰቡት ሰዎች እንዲፈቷት ምልክት ሰጣቸውና ከማርቆስ ጋር በሹክሹክታ ይነጋገር ጀመር::

ተከትለውት የገቡት ሰዎች ፈጠን ብለው እጆቿንና እግሮቿን ፈተው ለሁለት ብብትና ብብቷ ውስጥ ገብተው ከአልጋው ላይ አነሷትና ጥግ ወዳለ ወንበር ተሸክመው ወሰዷት:: እግሮቿ በገዛ ክብደቷ ስር እንደ ሰንበሌጥ ተልፈሰፈሱባት:: ወንበሩ ላይ ካስቀመጧት በኋላ ከአልጋዋ ግርጌ የቆመው ሰው ወንበር ስቦ ከፊት ለፊቷ ተቀመጠ:: ዕድሜው ገፋ ያለ መሆኑን ከጆሮ ግንዶቹና ራሱ ላይ ጣልጣል ያደረገበት ሽበት ያሳጣል:: የለበሰው ሙሉ ልብስ፣ ያጠለቀው ጫማና የጺሙ አከረካከም... የጠገበ ነጋዴ አስመስሎታል::

በውሃ የበሰበሰውን ልብሷን ሲመለከት አይኖቹን ከላይዋ ላይ ሳይነሳ "ልብስ ደርቡላት::" አለ::ቀልጠፍ ባለ ሁኔታ ከቁም ሳጥኗ ውስጥ አውጥተው ቢጋቢ ጠቀለሏት::

"በዚህ አይነት ሁኔታ መገናኘታችን በእውነት ያሳዝነኛል::" በተቀመጠበት ወደፊት ዘመም ብሎ ተናገራት::"ድርሻሽን በሚያኮራ ሁኔታ ስትወጪ ቆይተሻል:: እያንዳንዳችን በተለያዩ ምክንያቶች ለስህተት እንዳረጋለን:: ይህ ቢያሳዝንም ሊያስቀጣን አይገባም::"ወደፊት ጎንበስ ብሎ ጉልበቶቿን እየተመተመ አበረታታት::"የሥራ ድርሻዬን መናገሬ ከደንቡ ውጪ ቢሆንም ሁኔታው የሚጠይቀው በመሆኑ አልደብቅሽም:: በንቅናቄው ውስጥ የመረጃ ክፍል በምሥራቅ አፍሪካ የምድብ-ለ መሪ ነኝ:: ብርጋድየር ጄኔራል አብይ ሰናይ እባላለሁ::ምን አይነት አስጊ ሁኔታ ላይ እንዳለን ላስረዳሽ አልሞክርም:: ምክንያቱም በሚገባ ትረጂዋለሽ:: ስለሁኔታው ገለፃ እንደተደረገልሽ ተነግሮኛል:: አልደግመውም:: እንድትረጂኝ ነው የምጠይቅሽ...ቆይ! ቆይ!" አለ ሰውየው ርብቃ ልታቋርጠው ስትል ቀኝ እጁን ወደፊት ዘርግቶ:: "አስጨርሺኝ:: እንደተነገረሽ ናትናኤል የካልቨርትን ወዳጅ ገድሏታል:: ስለካልቨርት ማንነት በቂ እውቀት እንዳለሽም ነግረውኛል:: ስለዚህ ካልቨርት ስለወዳጁ መገደል ፍንጭ ከደረሰው እርሱ ራሱ እንደዛተው ምሥጢራችንን በቀጥታ ለውጪ የስለላ ድርጅቶች አለበለዚያም ለጋዜጠኞች ነው አሳልፎ

የሚሰጠው። ይህ ምን እንደሚያስከትል ከእኔ እኩል ትረጅዋለሽ። እርግጥ የሴትየዋን እሬሳ ለጊዜው ሰውረነዋል።በቤቷም ውስጥ ያሉ ሴቶች ስለሁኔታው እንዳይረዱና እንዳያወሩ የሚቻለው ሁሉ እየተደረገ ነው። ነገር ግን አሁንም እንድ እጃችን ያልገባ ውል አለ።ናትናኤል የሴትየዋ ግድያ በእኛ እንደተፈጸመ አድርጎ ለካልቨርት ሊያስተላልፍ ከቻለ ወይንም የካልቨ ርትን አድራሻ ደርሶበት ከተገናኘውና ምሥጢሩን ከተረዳ ውጤቱ ለሁላ ችንም ጥፋት ነው። እመኚኝ በአሁኗ ሰዓት ናትናኤል ከካልቨርት የበለጠ አደገኛ ነው፤ ሊያጠፋን ይችላል። እጅግ አደገኛ ሰው ነው።"

"እኔኮ..." አለች ርብቃ እንባዋ በዓይኗ ሲሞላ ልትውጠው እየታገለች።

"ይገባኛል... ይገባኛል... ስለሁኔታሽ ተነግሮኛል።" አለ ሰውየው ለአንድ አፍታ ዓይኖቹን ወደ ሆዷ ዝቅ አድርጎ። «እርግጥ ስህተት ቢሆንም አንዴ ተፈጽሟል። ያረገዝሽው ልጅ የእርሱ ነው። ለዚህም ነው ሕይወቱን ለአደጋ አሳልፈሽ መስጠቱ የከበደሽ፤ ይገባኛል። ወደእዚህ የመጣሁት መሃል ላይ የምንስማማበትን መስመር ለመፍጠር ነው። አንቺ የት እንዳለ ትነግሪኛለሽ። እለበለዚያም አጥምጄ እንድይዘው ትረጂኛለሽ። እኔ ደግሞ በሕይወቱም ላይ ሆነ በአካሉ ማንኛውም ዓይነት አደጋ እንደማይደርስበት ቃል እገባልሻሁ። እጃችን እንደገባ እዚህ እናመጣዋለን ወይም አንቺን እርሱን ወደምናቆይበት ስፍራ እንወስድሻለን። ለጊዜው ብቻ በቁጥጥር ስር እናቆየዋለን። ዕቅዳችንን ከውጤት ልናደርስ የቀረን አጭር ጊዜ ነው። ከስድስት ቀን በኋላ አደገኛነቱ ያክትማል። ሁለታችሁም ነፃ ናችሁ፤ ቃል እገባልሻለሁ። ትስማሚያለሽ?" ጎንበስ ብሎ ጉልበቷን በወዳጅነት ስሜት ያዝ አደረገው።

"የት እንደተደበቀ አላውቅም...የት ብዬ ልናገር?"

"ግድ የለም... ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ዘጠኝ ሰዓት ላይ መሥሪያ ቤትሽ ጓደኛሽጋ ደውሎ ነበር። ስላንቺ ማሰቡንም ነግሯታል። ትንሽ መታመምሽንና ቤትሽ ስልክ ደውሎ ቢያነጋግርሽ እንደሚሻል እንድትነግረው አድርገናል። በማንኛውም ሰዓት እዚህ ሊደውል ይችላል። በሚደውልበት ሰዓት በጠና መታመምሽንና እንዲያይሽ መፈለግሽን አስተዛዝነሽ ትነግሪዋለሽ። በተቻለ መጠን ወጥመዳችን ውስጥ እንዲገባ ታባብዪዋለሽ።" ክንዷን ያዝ አድርጎ ተናገረ።

ርብቃ በረጅሙ ተነፈሰች። ጭንቅላቷ እርስ በእርሱ ይጨቃጨቅ ይከራከር ጀመር... 'ይገድሉታል፤ እውነት ከሆነ «ሰው ገደለ» ያሉት እውነት ከሆነ አይተውትም... ሊያጠልሉት ነው... ሊያግባቡት ነው... መስማማት የለብትም...'እምቢ ብትል የሚከተላትን ስታስብ አይኖቿ በእንባ ተዘፈቁ። 'ያስቃይዋታል...ይደበድቧታል... ያንገላቷታል...'



"ጊዜ የለንም... በማንኛውም ደቂቃ ሊደውል ይችላል። እመኚኝ... እጁ እንዳገባ እርጂኝ፤ ቃሌን እጠብቃለሁ።"

"አልችልም።" አለችው እንባዋ በጉንጮቿ እየወረደ።

"ቃሌን ማንም ሊሽረው አይችልም! እመኚኝ። የምነግርሽ እውነት ነው። አንዲት ፀጉሩ ከላዩ አትወድቅም።"

"አላምንም ... ሁላችሁንም አላምንም። ጓደኛውን ገድላችሁታል። አይደለም? እሱንም አትተውትም።" ድምጿ በጭንቅ ቃተተ።

"ከቃሌ በላይ ልሰጥሽ የምችለው ማስተማመኛ የለኝም...ቃሌ ደግሞ እውነት ነው።"

"አላምንም! ውሸት ነው! ውሸት ነው! ውሸት ነው!..." እንዳትሸነፍ የፈራች ይመስል አይኖቿን ጨፍና ጭንቅላቷን ቀኝና ግራ አላጋችው።

"ስለምንሽ ካልረዳሽኝ አስገድጄሽ የምፈልገውን እንድትፈጽሚ ማድረግ እችላለሁ።" ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁ ውስጥ የነበረ ልስላሴ ሲቆረፍድ ተሰማት።

"አልችልም! ልትገድሉኝ ትችላላችሁ።አይኔ እያየ ሰሞቱ አልጠራውም... ግደለኝ!" ሰውነቷን ነዘራት።

"አልገድልሽም። ያ ፍጹም ስህተት ነው።" አለ ሰውየው ከተቀመጠበት በእርጋታ እየተነሳ።

ከጀርባው ለቆሙት ሰዎች ምልክት ከሰጣቸው በኋላ በእርጋታ ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ውጭ ውጪውን ይመለከት ጀመር። ከወንበሯ ላይ ለሁለት ተሸክመው አንስተው አልጋዋ ላይ አጋደሟት። በፍጥነት አፏን ፈልቅቀው ቡትቶ ጨርቅ ጠቅጥቀው ለጎሟት።አንዴ ብቻ "ማርቆስ!" አለች በጭንቀት...ያ የምታውቀው የሚያውቃት የህዋሷ መረ ያግዛት፣ ያድናት ይመስል። ከቆመበት አልተንቃነቀም።በጭንቅ የሚውጠው ምራቅ ማንቁርቷን እላይ እታች ሲያመላልሰው የተጨነቀላት፣ ያዘነላት መሰላት። ተስፋ አደረገች። ትክ ብሎ ሲመለከታት አይኖቹ እንባ ያቀረዘዙ መሰላት። ተስፋ አደረገች። ማርቆስ ግን ከአልጋዋ በስተቀኝ ፈንጠር ብሎ እንደቆመ ቀረ። አፏ ሲለጎም ልሳኗ ሲከዳት በአይኖችዋ ተማፀነችው። ዓይኖቹን ከአይኖቿ ነቅሎ ትንፋሹን እላይ እታች እየመላለስ ቆሞ ቀረ። ተስፋ ቆረጠች። ለማይቀረው ዱላና ስቃይ ተዘጋጅታ ተጋደመች። ተጠባበቀች... አልጋዋ ላይ ያጋደሟት ሰዎች እጆቿን ግራና ቀኝ ከአልጋው ጠርዝ ጋር ጠፍረው ካሰሩት በኋላ የለበሰችውን በውሃ የበሰበሰ ስስ ቀሚስ ከላይዋ ላይ እንደ ወረቀት እየቀዳደዱ ያነሱት ጀመር። ድንገት ሲትነቷ ግንፍሏት ወጣ።

እግሮቿን እያፈራገጠች ወገቧን እየሰበቀች ቀሚሷን እላይዋ ላይ ለማስቀረት ታገለች... ቀሚሷን ግን አላተረፈችውም:: እግሮቿን ግራና ቀኝ በርግደው ከአልጋው ጠርዞች ጋር ጠፈሯቸው...

የቀሰማትን ህፍረት፣ የተሰማትን ውርደት ያጥብላት ይመስል እንባዋ ያለማቋረጥ በዓይኗ ጎንና ጎን ተንዠቀዠቀ:: ሃሞቷ ሆዷ ውስጥ የፈሰሰ ይመስል ሰውነቷ በመራራ ተሞላ::ግራና ቀኝ ተበርግደው የታሰሩ እግሮቿን ከታሰሩበት ገመድ ጋር እያፋተገች ሰውነቷን፣ ሴትነቷን፣ ለመሸፈን፣ ለመደበቅ፣ ለመሸሸግ ታገለች:: ገመዶቹ ግን አልተሸነፉላትም...

"ስልክ በሚደውል ሰዓት በጠና መታመምሽን እስተዛዝነሽ ትነግሪዋ ለሽ..." ፊቱን ሳይመልስ በመስኮቱ ውጭ ውጭውን እየተመለከተ በእርጋታ ተናገራት:: መጥቶ እንዲያይሽም ትገፋፊዋለሽ::የመረጥሽውን መንገድ ተጠቀሚ-ተለማመጪው፤ለምኚው፤አልቅሺ:: መምጣት አለበት::ያንን ብቻ አስታውሺ:: ይህ ደግሞ የእኔ ብቻ ሳይሆን የአንቺም ፍላጎት ነው:: ምክንያቱም ሳይመጣ ቢቀር ለሚቀጥሉት በርካታ ቀናት መጥፎ ነገር ታያለሽ:: እመኚኝ:: ከዚያ በኋላ ቀሪ ሕይወት ቢኖርሽ እንኳን ልትኖሪው ፈቃደኛ አትሆኚም::" ፊቱን መልሶ ቆመና ትክ ብሎ ተመለከታት:: ወዲያው ከአልጋዋ በስተቀኝ ከቆሙት ሁለት ሰዎች ለአንደኛው ምልክት ሰጠው::

በስተቀኟ የቆመው ሰው ከደረበው ጥቁር ቆዳ ጃኬት የውስጥ ኪስ ውስጥ እስክሪብቶ የምትመስል ዕቃ አውጥቶ በአንደኛው ጫፉ በኩል ክንድ እስክታክል ድረስ መዘዛት::ከቀኝ ኪሱ ውስጥ አነስተኛ የሲጋራ መለኮሻ አውጥቶ ከለኮሰው በኋላ የመዘዛትን ቀጭን ሽቦ ጫፍ በእሳቱ ላይ አሳረፋት:: ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ቀጭኗ ሽቦ በቁመቷ ሙሉ ከጫፍ እስከጫፍ ግላ ፍም መሰለች::ጠጣር ብረት መሆኗ ቀርቶ ፈሳሽ እሳት እስክትመስል ድረስ ተንቀለቀለች:: በዙሪያዋ ቀይ ብርሃን እስኪያንገበግብ ጋመች::

ሰውየው ቀጭኗ ሽቦ ፍም መምሰሏን ሲመለከት የሲጋራ መለኮሻውን አጥፍቶ የጋለችውን ሽቦ ወደፊት ይዞ ወደ እግሮቿ መሃል ቀረበ:: ጉልበቶቿ መሃል ገባ::

ተወራጨች:: ከፋመችው ሽቦ ለመሸሽ በተቻላት ሰውነቷን ከአልጋው ጋር አጣበቀችው:: ሽቦዋ ግን በቀስታ በጭንና ጭኖቿ መሃል ወደ ሰውነቷ እየቀረበቻት መጣች... ጭንቅላቷን አርገፈገፈችው...ቃተተች...

"እመኚኝ የምናደርገውን አትወጂውም...ወይስ ይህንንም ውሸት ነው ትያለሽ? ቃሉን እስካልፈጸምሽ ድረስ የሚከተለውን አትወጂውም::" ጆሮዋውን ለመስኮቱ እንደሰጠ አሻግሮ ተመለከታት::



በፍርሃት ተርበተበተች:: በእርጋታ እየተራመደ ወደ አልጋዋ ተጠጋ:: ቀኝ እጁን እራቁት ትከሻዋ ላይ ጭኖ እንደ ህፃን ልጅ በሃዘኔታ ቁልቁል ተመለከታት::

"ባልኩሽ ሃሳብ ትስማሚያለሽ፣ ሲደውል ረጋ ብለሽ ታነጋግሪዋለሽ:: መፍራት የለብትም፣ ቢሆንም በመጠኑ መደንገጥ አለበት:: መታመምሽንና ሊያይሽ እንደምትፈልጊ አስተዛዝነሽ ታስረጂዋለሽ፣ ታባብይዋለሽ::"

ሰውነቷን ሳታነቃንቅ ዓይኖቿን ብቻ በፍርሃት እያቁለጨለጨች ሽቅብ ተመለከተችው::

ወደፊት ጎንበስ ብሎ ከማጅራቷ የተቋጠረውን ጨርቅ ፈትቶ አፏ ውስጥ የተጎሰጎሰውን ቡትቶ አወጣላት::

"አይዞሽ ጥርጣሬ አይግባሽ:: ልንጎዳሽ አንሻም:: ዛሬም ነገም ባልንጀሮችሽ ነን:: ለአንድ ዓላማ የቆምን ነን:: ያንን ሠይጣን... ያንን ነፍሰ ገዳይ ብቻ እጄ አግቢልኝ::"

"ሠይጣን አንተ ነህ!" ድንገት ዛር ፈለቀባት:: "ነፍሰ ገዳይ አንተ ነህ! እኳን እጅህ ላገባልህ እጠገቡ አትደርስም - ቱፍ! " አፏ ውስጥ በተጠራቀመው መራራ ምራቅ ፊቱን ሸፈነችው:: በጥፊ ሲያግላት ያለችበት ተዘበራረቀባት:: እግሮቿ መሃል ሲገቡ ተሰማት:: ሽቦዋ! ሽቦዋ::!

-23-

ናትናኤል ጊዜ ሳያጠፋ ታክሲ ተሣፍሮ ወደ ለገሃር ሄደ::

ደጋግሞ ደውሎ ነበር ስልኩ የተነሳለት::ቀደም ብሎ መሥሪያ ቤቷ ጓደኛዋ ምህረትጋ ደውሎ ርብቃን አቅርቢልኝ ሲላት አሁንም ወደ ስራ ገበታዋ አለመመለሷን ስትነግረው አለቅጥ ተጨነቀ፤ከራሱ ጋር ክርክር ገጠመ:: እንደታመመችና ቤቷ ደውሎ ከቻለም ሄዶ ቢያያት እንደሚሻል ምህረት ስትነግረው መንፈሱ ሸፈተበት:: ልቡ ላይ እንደጦር የተሸነቀረበት ግን ሌላ ነበር-

"በጣም አሟታል እንዴ?" አላት ምህረትን ቅንድቦቹን አጠጋግቶ:: "ምንድነው በሽታዋ... ማለቴ..."

"እንዴት ነው ነገሩ...አላወቅህም ማለት ነው? ወይስ...ናትናኤል ርብቃኮ እርጉዝ ነች::"

ድንገት እንደመሸ ሁሉ ጭልምልም አለበት፤ጭንቅላቱ እንደ ድንጋይ ከበደው፤ ማጅራቱን ጨምድዶ ያዘው:: አንድ ቃል ብቻ ይደጋግም ጀመር - "ፈጣሪዬ! ፈጣሪዬ! ፈጣሪዬ! " ስልኩን ከዘጋ በኋላ በቆመበት ተገትሮ ቀረ:: እንደህፃን ልጅ ቁጭ ብሎ ማልቀስ ፈለገ:: "ርብቃ ... ርብቃ!" ራሱን መቆጣጠር ተሳነው - "ገደል ይግባ!" ሁሉ ነገር ገደል ይግባ!" የሚንቀጠቀጥ እጁን ኪሱ ከቶ ከአንድ ቡና ቤት ገብቶ ተቀመጠ:: ለሰዓታት ከራሱ ጋር ተወራጨ:: በመጨረሻ ከቡና ቤቱ ወጥቶ የህዝብ ስልክ ይፈልግ ጀመር::

ስልኩ ቢጠራም የሚያነሳው ሰው አልነበረም:: በሚንቀጠቀጥ ቀኝ እጁ የስልኩን እጀታ ጨምድዶ ይዞ ተጠባበቀ:: 'ርብቃኮ እርጉዝ ነች' ስልኩ ይጠራል፤ የሚያነሳ የለም:: 'ቀጥታ እቤቷ ድረስ ብሄድስ?'- አሰበ:: 'መሄድ የለብኝም:: እሷንም ቢሆን ለባሰ አደጋ ማጋለጥ ነው የሚሆነው::' ደጋግሞ ደውሎ ነበር ስልኩ የተነሳለት-

"ሀሎ" አለ ስልኩ እንደተነሳ ቀድሞ:: ድምፅ ተጠባበቀ:: ግን ምንም አልነበረም:: መልሶ "ሀሎ" አለ የሚንቀጠቀጥ ድምፁን ለማረጋጋት እየታገለ::

"ናቲ...ና...ናቲ..." ድምጿን ከመቅጽበት ለየው:: ቢሆንም በጣም የደከመ ድምጽ ነበር::

"ርብቃ! ደህና ነሽ...?"

"ናቲ...ናቲ... አቃጠሉኝ...ና..."

"ናትናኤል ነኝ ርብቃ... ጮክ በይ አይሰማኝም:: ርብቃ መሥሪያ ቤትሽ ደውዬ ነበር:: ርብቃ... እ?... አይሰማም::" ድምጿ እየደከመበት ሄደ::

ሌላ ሰው ስልኩን እንደተቀበላት ተረዳ::

"ሀሎ::" አለ ለስለስ ያለ የወንድ ድምፅ::

"ሀሎ... እባኮት ርብቃን ነበር::"

"ማን ልበል?"

"ሀሎ...እባኮት ርብቃን ያቅርቡልኝ::" ናትናኤል ረጋ ብሎ ጠየቀ::

"ይቅርታ:: ትንሽ አሟታል:: ስልክ መቅረብ አትችልም:: የምነግርልዎት መልዕክት ካለ..."

"እ...ሷኑ ለማነጋገር ስለምፈልግ ነበር::" ናትናኤል ጠንከር አለ::

"ይቅርታ... ስትነጋገር ስለሚደክማት ነው:: መልዕክት ካሎት ልንገርሎት:: ታናሽ ወንድሟ ነኝ... ብስራት ነኝ::"



ናትናኤል ለማስታወስ ሞከረ:: ቤተሰቦቿን ብዙም አልቀረባቸውም፤ ቢሆንም ከብስራት ጋር ከአንድ ሁለት ሦስት ጊዜ ተገናኝተዋል:: ብስራት ገና ሃያ ዓመት ያልሞላው ወጣት ወንድሟ ነው::

"እንደምንዋልክ ብስራት:: ናትናኤል ነኝ፤ ታስታውሰኛለህ? የርብቃ...እ..."

"አዎ - አዎ አስታውስሃለሁ:: እንደምንድነህ? ደህና ነህ? ምነው ጠፋህ? ርብቃ በጣም አስባለች:: ለምን ብቅ አትልም?"

"እ..." ናትናኤል አመነታ:: "ምን መሰለህ ብስራት... መምጣት እንኳን አልችልም:: ግን እሷ እንዴት ነች?"

"አሟታል... በጣም ነው የታመመችው:: ሐኪም ቤት እየመላለስናት ነው::"

"ምን አሉ ሐኪሞቹ? ማለቴ ምንድነው?" ናትናኤል በልቡ የሚንቀዋለለውን ለመጠየቅ ጭንቅ አለው::

"አላወቁላትም:: ግን ምግብ አይበላላትም፤ቢትበላም አይረጋላትም:: ሰውነቷ ላይ ግን ችግር የለባትም:: 'ጭንቀት ነው' ነው የሚሉት ሐኪሞች:: ምን እንደሚያስጨንቃት ግን ሊገባን አልቻለም:: በጣም ደክማለች:: ናትናኤል መጥተህ ብታያት ጥሩ ነበር:: በእንቅልፍ ልቧ ሁሉ ስምህን ትጠራለች፤ ከቀን ወደቀን እየባሰባት ነው::"

ናትናኤል በረጅሙ ተነፈሰ:: እጁን ግንባሩ ላይ ጫነ:: ከራሱ ጋር ክርክር ገጠመ:: 'የፈለገው ይምጣ ሄዶ ያያታል:: መቼም በቤቷ አካባቢ ሊያገኙብኝ ይችሉ ይሆናል:: ግን ምርጫ የለውም:: ሹልክ ብሎ ገብቶ ሹልክ ብሎ ይወጣል' ወሰነ::

"ብስራት መደወሌን ለማንም አትናገር ዛሬ ማታ መጥቼ አያታለሁ እሺ? ልክ ከምሽቱ አስራ ሁለት ተኩል ሲሆን ውጭ በሩጋ ጠብቀኝ"

ናትናኤል ስልኩን ከዘጋ በኋላ በግራው ያንጠለጠለውን ትንሽ የሸራ ሻንጣ ይዞ እዚያው ለገሃር አቅራቢያ ወዳለ አነስተኛ ቡና ቤት ተመልሶ ገባ:: ጥግ ወዳለ ወንበር ሄዶ ስውነቱን ለማርገብ፣ ለማረጋጋት በዝምታ ተቀመጠ:: በግራሰና በዘይት የተጨማለቀ ሰማያዊ ቱታ ለብሷል:: ጭንቅላቱ ላይ ያጠለቀው ዙሪያው እንደጠወለገ ቅጠል የተልፈሰፈሰው ባርኔጣ በግንባሩ ላይ አዝምሞ ፊቱን ሸፍኖታል:: ከደረት ኪሱ ሲጋራ አውጥቶ

ከሚንቀጠቀጥ እጁ ጋር እየታገለ ከለኮሳት በኋላ ክብሪቱን እያጠፋ ሲጋራዋን ምጥጥ አደረጋት። "ርብቃ... ርብቃ... ምነው አጠንብሽ መሆን ብችል!"

"ምን ልታዘዝ፡" አለችው ስሚያዊ ሽርጥ ወገቧ ላይ ሸብ ያደረገች አስተናጋጅ የለበሰውን ቆሻሻ ቱታ ሰታይ ድምጿን ቀፍጠን አድርጋ።

"ቡና፡" አላት ቀና ብሎ አይቷት የዋጠውን የሲጋራ ጭስ በረጅሙ እየለቀቀ።

"ሂሣብ በቅድሚያ ነው የሚከፈለው።" አለች ሁለት እጆቿን በጎንና ጎን የሽርጥ ኪሶች ውስጥ እየወሸቀች።

ከቀኝ ኪሱ ውስጥ ሣንቲሞች አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ በተን አደረገላት። ሃሳቡ ግን ሌላ ቦታ ነበር። ርብቃ ለምን ደበቀችው? ወይስ ወሬ ገና ነው ማለት ነው!ሊሆን አይችልም። ደብቃው ነው። ግን ለምን... ለምን?

የሚወደው ገጿ መጥቶ ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። 'ርብቃ'ኮ እርጉዝ ነች' የምህረት ድምፅ አቃጨለበት፤ 'አሚታል... ምግብ አይበላላትም ... ስትበላም አይረጋላትም... "ጭንቀት ነው" ነው የሚሉት ሐኪሞቹ...' የብስራት ድምፅ ደወለበት...

"አምላኬ ምን ዓይነት ጉድ ውስጥ ነው የከተትከኝ" አለ አምላኩ ከፊት ለፊቱ ባለ ወንበር ላይ የተቀመጠ ይመስል ፊት ለፊት አፍጥጦ።

ምንድነው ሊያደርግ የሚችለው? ቀጥ ብሎ ፖሊስጋ ሄዶ እጁን መስጠት። ቢገሉትስ? ይግደሉት። ከዚህ በላይ ስቃይ መሸከም አይችልም! ግን ለፖሊሶችስ ምን ሆንኩ ብሎ እጁን ይሰጣል? ሁሉን ነዋ!... የሆነውን ሁሉ ዘርዝሮ ማውጣት ነዋ! ግን ማን ያዳምጠዋል? ማን ያምነዋል? ፍጹም! ፖሊስ ወጥመድ ነው! እጁን መስጠት ማለት ሞቱን ማፋጠን ማለት ነው። ለማን ይበጃል መሞቱ? ለርብቃ? ለልጁ? የአብርሃም መሞት ማንን ጠቀመ? መረጋጋት ነው ያለበት። ካሁን ወዲያ ወደኋላ ማለት አይችልም! መረጋጋት ነው ያለበት።

ከቁጥጥር ውጭ በሚንቀጠቀጥ ቀኝ እጁ የያዛትን ያለቀች ሲጋራ ለመጨረሻ ጊዜ መጠጣትና ከፊት ለፊቱ ጠረጴዛ ላይ በተቀመጠው የሲጋራ መተርኮሻ ውስጥ ደፈጠጣት። 'መረጋጋት... መረጋጋት ነው ያለበት...'

የቡና ቤቱ አስተናጋጅ ያዘዛትን ቡና አምጥታ እፊቱ ደነቀረችለት። አንስቶ ፉት አለው። ስኳር አልነበረውም። ክፉኛ መረረው። ቢሆንም ስኳር አልጠየቃትም። ድጋሚ ፉት አለው። ትኩስ ቡና በጉሮሮው አልፎ በሆዱ ሲተራመስ ስንዝር በስንዝር ተከታተለው። ሆዱ ጩርርር...ር ሲል



ተሰማው። ትላንት ምሳ የበላ ነው። ቢሆንም ምግብ አላሰኘውም። ከቡናው ድጋሚ ፉት አለለት። ሰውነቱን ማዝናናት አለበት፤ ማረጋጋት አለበት። በተቀመጠበት ወንበር ላይ በደኋላ ጋለል ብሎ ዓይኖቹን ጨፈናቸው። ቀኝ እጁ ከደረት ኪሱ ገብቶ ሲጋራና ክብሪት ይዞ ተመለሰ። ርብቃ ለምን ደበቀችው? በቃ በቃ... ስለርብቃ ማሰብ የለበትም። አለበለዚያ ያብዳል፤ አለበለዚያ አእምሮውን ይስታል። አእምሮውን ወደኋላ አጠንጥኖ የደረሰበትን ያጋጠመውን ድጋሚ መረመረው...

ከትላንት ወዲያ ማታ ዓይኑ ስር ከተፈጸመው ግድያ በኋላ ሰውነቱን አረጋግቶ መቆየት አልቻለም። አንዴ እንደቆሰለች ሚዳቋ ቀጠል በተንከሻከሸና ወፍ በበረረች ቁጥር መበርገግ ብቻ ሆነ።

"ሩጥ!" ስትለው አሁንም ጥርት ብሎ ይሰማዋል። "ሩጥ!" እንዴት እንደ ሮጠ ትዝ አይለውም። ወደ ዋናው የመኪና መንገድ ከገባም በኋላ ሩጫውን አልገታም ነበር። በመጨረሻ ፍርሃቱ ታግሶለት ሳይሆን ልቡ ልፍረስ ሲለው... አፉ ደም ደም ሲለው፤ ድካም ጉሮሮውን ይዞ ሲፈጠርቀው ሲጀምር፤ ጥጋት ይዞ ቆመና ቁና ቁና እየተነፈሰ አይኖቹን በጨለማው ውስጥ በመጣበት አቅጣጫ አፈጠጣቸው።

ሊያፍነው ቢሞክርም ከሚጨስ ሳንባው እየተጣደፈ በአፍ በአፍንጫው የሚሽቀዳደም የገዛ ትንፋሹ ድምፅ አሰጋው። ከወዲያ ማዶ ትንፋሹን ሰምተው እንዳይመጡ የፈራ ይመስል እጁን አፉ ላይ ጭኖ ቆመ።

ድምፅ የለም። ዘግይቶ ነበር እርቆ መሄዱንና በዙሪያውም ማንም እንደሌለ የተረዳው፤ ነፍሱ መለስ ያለችለት። ሲፈራ ሲቸር ከተደበቀበት ጥጋት እየተገላመጠ ወጥቶ በመኪና መንገዱ ጥግ ጥግ እየተራመደ ራቅ ብለው ወደሚታዩ የመሸታ ቤቶች አመራ። በዚያ ሰዓት ርቆ ለመሄድ መሞከር እንደሌለበት ተረድቷል። እዚሁ አፍንጫቸው ስር ነው መደበቅ ያለብኝ ብሎ አሰበ። አይጠረጥሩኝም። እዚሁ ይቆያል ብለው አይገምቱም። አለበለዚያ ርቄ ለመሄድ ከሞከርኩ ወዲህ ወዲያ ስል ያገኙኛል። ቶሎ አንድ ቦታ ይዤ መርጋት አለብኝ! እመሃላቸው ቢሆንም ማድፈጥ መቻል አለብኝ።

ትዝ ይለዋል... "እባክሽ የእኔ እህት አልጋ አለ?" አላት ወደ አንድ አነስተኛ ሆቴል ገባ ብሎ።

ሴትየዋ መልስ ሳትሰጠው አይኖቿን አፍጥጣ መላ ሰውነቱን ትመለከተው ጀመር። ጎንበስ ብሎ የገዛ ሰውነቱን ሲመለከት በረገገ። ከፊት ለፊት ነጭ ሸሚዙ እጆቹ፣ ክንዱ ሁሉ በደም ተበክሏል። ሰራሱ እስኪያስደነግጠው ድረስ ክፉኛ በደም ተጨማልቋል።

"እ - - -እ ሰዎች ተደባድበው ስገላግል ነው። እ...አልጋ አላችሁ?"

መልስ ሳትሰጠው ጭንቅላቷን ብቻ ነቀነቀችበት። ፊቷ ላይ የሚንቀዋለለውን ያልተቆነጠጠ ፍርሃት ሲመለከት ተስፋ ቆረጠ… ሌሊቱን ቆሞ ቢያድር አልጋ እንደማታከራየው ገባው። ለእርዳታ ሳትጮኽ 'እ! እ!' ብላ ሳታስይዘው ቶሎ ብሎ ወጣና በፍጥነት በጨለማው ውስጥ ተሰወረ።

ድጋሚ ሌላ ሆቴል ከመግባቱ በፊት የኮቱን ቁልፍ ግጥም አድርጎ ቆልፎ፣ ኮሌታውን ቀልብሶ እጆቹን ከሱሪው ኪስ ውስጥ ወሸቃቸው። ወደ ሆቴሉ ሲገባ የፊተኛው አዳራሽ ባዶ ነበር። ደንበኞች ወጥተው የአዳራሹን መስኮቶች የምትዘጋጋ አስተናጋጅ ተመለከተ።ፈገግታ አስቀደመና አልጋ ጠየቃት።

"ስድስት ብር።" አለች ስታየው ኮስተርተር ብላ መስኮቶቹን መዘጋጋቷን ሳታቋርጥ።

በደም የተጨማለቁ እጆቹን ከሱሪው ኪስ ውስጥ እንዴት እንደሚያወጣ ግራ ተጋባ። በአዳራሹ ውስጥ ያለው ብርሃን ደብዛዛ ቢሆንም እጆቹ የተነከሩበትን ደም ብትመለከት ልጅቱ የሚሰማት ስሜት አልጋ እንደሚያስከለክለው እርግጠኛ ነበር።

"መጀመሪያ ክፍሉን ልየው።" አላት በተቻለው ራሱን ለመግዛት እየጣረ።

'ተከተዪኝ' ለማለት ጭንቅላቷን መታ አደረገችና ፊቷን መልሳ ወደ ጓዳ ገባች። ተከተላት። ከሚከራየው ክፍል ሲደርሱ በሩን ከፍታ፣ መብራቱን አብርታ ፈቀቅ አለችለት። ወደ ክፍሉ ገባና ቀልጠፍ ብሎ መብራቱን አጠፋው። ወዲያው የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ከመተላለፊያ በሚመጣው ስስ ብርሃን የአስር ብር ኖት አውጥቶ ሰጣት።

"መልሱን ያዥው ... እ… መታጠቢያ ቤት ይኖራል?"

"የለም!" አለች ከአስር ብሩ የሚመለሰው አራት ብር የእርሷ መሆኑን ስታውቅ ፈገግ ብላ።

መታጠቢያ ቤት ገብቶ በደም የተበከለ ልብሱንና ሰውነቱን አጣጥቦ ወደተከራየው ክፍል ተመለሰ። አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ አይኖቹን ከደነ። እንቅልፍ ግን አልጎበኘውም። ሰውነቱ ሊረጋጋለት አልቻለም።

'ምንድነው ነገሩ?' የተዘበራረቀበትን ሁኔታ ትርጉም ሊሰጠው ተጣጣረ። 'ሴትዮዋ ከየት መጣች? ስካራሟ ማነች? ያለጥርጥር የካልቨርትን አድራሻ ትፈልጋለች። ለዚህም ነው የምሥራችን የገደለቻት። ግን እሱን ለምን ተወችው? መተው ብቻ ሳይሆን ሕይወቱን ለማትረፍ የሌላ ሰው



ሕይወት ለምን አጠፋች? እሷ ማነች? በአውሬው ውስጥ ለውስጥ አለመግባባትና መከፋፈል አለ ማለት ነው? አንደኛው ወገን ሊያጠፋው ሲፈልግ የተቀረው ወገን ሞቱን አይሻም ማለት ነው? ግን ለምን? የእርሱ መኖር ማንን ይጠቅማል? እንዴት? የምሥራች መሞትስ ምን ይጨምራል? ሴትየዋ ማነች? ሰውየውስ? ሰውየው በምሥራች ሞት ለምን ተደናገጠ? እርሱንስ ለምን ሊገለው ሞከረ? ሴትየዋ ከጀርባው ባትቀድመው ጨርሶት ነበርኮ!'

'የምሥራችን ሳይሆን የእርሱን መጥፋትና መሞት የሚሻ ወገን አለ ማለት ነው። ያለ ጥርጥር ይህኛው ወገን ነው አብርሃምን የገደለው። ግን እነማን ናቸው? ምንድነው የሚፈልጉት? ግልፅ ነው። ሁሉም የሚፈልጉት ካልቨርትን ነው። የካልቨርትን አድራሻ የምታውቅ የምሥራች ብቻ ነበረች። ሊያስፈራሯት ቢላውን ሲያወጣባት ምንድን ነበር ያለችው የምሥራች?'

"አትነካኝም! ጫፌን ብትነኩኝ ዮሴፍ ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ! ያወጣዋል… ምሥጢራችሁን ያወጣዋል!"

'አዎ…እንደጠረጠረው ካልቨርት ይዞት የተሸሸገው ምሥጢር አለ። አውሬው የምሥጢሩን መጠበቅ ለማረጋገጥ ሲል ካልቨርትን እጁ ማስገባት ቢፈልግም የምሥራችን ለመተናኮል ያልደፈረው ካልቨርት ምሥጢሩን በይፋ በማውጣት እንዳይበቀለው በመፍራት መሆን አለበት። አውሬው የካልቨርት አባራሪ ይምሰል እንጂ አስረኛውም ነው። ምክንያቱም ካልቨርት የአውሬውን ምሥጢር በመዳፉ አድርጓል። የአብርሃም አደራ ታወሰው «ካልቨርትን አግኝ… ካልቨርትን» አብርሃም ትክክል ነው። ቁልፉ ያለው ከዚያ ነው። ካልቨርት የያዘውን ምሥጢር በጁ ያገባ ሁሉ የአውሬውን አፍንጫ መሰነግ ይችላል። ግን ምንድነው ምሥጢሩ? የት ነው ካልቨርት…? የምሥራች ነበረች አድራሻውን የምታውቅ። ሞታለች። ሌላ ማን አለ? እርሱ ራሱ ! ነግራዋለች። አዎ… የካልቨርትን አድራሻ ነግራዋለች። እሱ ብቻ ነው የካልቨርትን አድራሻ የሚያውቅ-'

"እ…እማዬጋ…ድሬዳዋ።"

'እማዬጋ… ድሬዳዋ… የት ናቸው እማዬ? እናቷ? ድሬዳዋ… ድሬዳዋ የት?'

ናትናኤል በተከራየው የሆቴል ክፍል ውስጥ በጀርባው አልጋው ላይ እንደተንጋለለ ዓይኖቹን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ ቀረ።

'በድሬዳዋ እየተዘዋወረ "የምሥራች እናት" እያለ አይፈልግ! ስማቸውን እንኳን አያውቅም። የምሥራች ይልማ። እርግጥ የምሥራችን አባት ስም ያውቃል - አቶ ይልማ… አስር አለቃ ይልማ… ቄስ ይልማ… ፊጣሪ ይወቅ! አባቷን ካገኘ ግን እናቷን አገኘ ማለት ነው። አብረው አይኖሩ እንደሆንስ? ቢሆንም የእናቷን አድራሻ ሳያውቁ አይቀሩም። ግን አባቷንስ

ቢሆን... "አቶ ይልማ" እያለ በድሬዳዋ ከተማ ቢዞር አባቷን እንዴት ማግኘት ይችላል? የአባታቸውን ስም ቢያውቅ ጥሩ ነበር። ያንን እንኳን ማግኘት ይችላል። እ... ተመልሶ ወደ ሆቴሏ ሄዶ የንግድ ፈቃዷ ላይ ማንበብ ይችላል። የአባቷና የአያቷ ስም ይኖራል። ግን ከአሁን ወዲያ ወደዚያ አቅራቢያ መሄድ በገዛ እጅ መንጠልጠል ነው። ሰው ቢልክስ? ማንን? አንዱን የሆፈር ስራፈት ጎረምሳ አምስት ብር ቢያሳየው ሄዶ ያነብለታል። በዚህ አደገኛ ሰዓት የላከው ወጣት የንግድ ፈቃዷን ተጠግቶ ፊደል ሲቆጥር "ምንድነው የምትሰራው?" ብለው ቢይዙትስ? "ምራ" ቢሉትስ? አስከትሏቸው ከተፍ ቢልስ? አ! አ! አ! አይሆንም። ሌላ ምርጫ መኖር አለበት። የንግድ ፈቃድ... ግብር... አገር ውስጥ ገቢ... አዎ እዚያም የአያቷ ስም ይኖራል። ግን አገር ውስጥ ገቢ የሚያውቀውና ፋይሏን አውጥቶ የሚያይለት ወይ የሚያሳየው የለውም። ሄዶ ፋይሏን ቢጠይቅ ደግሞ ጥርጣሬ መፍጠር ነው። "ለምን ፈለግኸው? ምንድነህ አንተ?" ቢሉት ምን ሊመልስ? አ! አ! አይሆንም። ሌላ ምርጫ ... ሌላ ... መፍጠን አለበት! መቅደም አለበት! ቶሎ ወደ ድሬዳዋ... ቶሎ ወደ ካልቨርት... ቶሎ ወደ ምሥጢሩ... ቶሎ ቶሎ! የአባቷ ሙሉ ስም ማነው? ይልማ... ይልማ ማን?

ናትናኤል ለጥያቄው መልስ ሲያገኝ ይበልጥ ተበሳጨ። ለዚህ ቀላል ጥያቄ፣ ለዚህ ቀላል መልስ ይህን ያህል ከተቸገረ እንግዲያው ማስተዋል ቀንሷል ማለት ነው። ከሚገባው በላይ ተወናብዷል ማለት ነው። ፈርቷል ማለት ነው።

እራሱን ገሰጸው።

ረጋ ማለት አለበት። አለበለዚያ በማይረባ ስህተት እራሱን አጋልጦ ይሰጣል።

ስሟን እስካወቀ! የስልክ ቁጥሯን እስካወቀ! የአባቷንና የአያቷን ስም ከማንኛውም የስልክ ደብተር ላይ በቀላሉ ያገኘዋል።

ሌሊቱን በሙሉ በሃሳብ ሲታመስ ሳያሸልበው ፀሐይ ሥፍራዋን ተረከበች።

ናትናኤል ከአልጋው ተነስቶ ማታ አለቅልቆና በእርጥብ መሃረብ ጠራርጎ ከግርጌካለ ወንበር ላይ ያስጣቸውን ሸሚዙንና ኮቱን አንስቶ ለባበሰና ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ። በተቻለው መጠን ረጋ ብሎ ተጣጥቦ ያለፈውን ሌሊት አሻራ ሙልጭ አድርጎ ካፀዳ በኋላ ወደ ሆቴሉ አዳራሽ ብቅ አለ።

ጥግ ላይ ተቀምጦ ሁለት ስኒ ቡና ጠጣና ፈጠን ብሎ ከሆቴሉ ወጣ። ሌሊቱን ያለእንቅልፍ ቢያሳልፈውም የድካም ስሜት አልተሰማውም። ምናልባት ድንጋጤው ይሆናል፤ ምናልባት ፍርሃት፤ ምናልባት ሥጋት።



ደሙ በሰውነቱ ውስጥ ሲሽቀዳደምና ሲራወጥ ለራሱ ይሰማዋል። መፍጠንና መሮጥ አለበት!

ታክሲ ተሳፈረና ወደ መርካቶ ሸሸ።

መርካቶ ባህር ነው - ውቅያኖስ! መርካቶ ጫካ ነው - ደን። መርካቶ ቤቱ ነው- 'የዘውድዬ'።

መሀል መርካቶ ከታክሲ እንደወረደ ወደ አንድ ቡና ቤት ገባ። ገንዘብ ተቀባይዋን ተጠግቶ ሠላምታ ከሰጣት በኋላ የስልክ ማውጫ ጠየቃት።

"ጩኒ ቁልፍ።" አለች ረጅም ወንበር ላይ የተቀመጠችው ወጣት ሴት ወደኋላ ዞራ።

በእድሜ የሚመጣጠናት ወንድ ልጅ በቀጭን ሰንሰለት ውስጥ የተሰገሰጉ አስር የሚሆኑ ቁልፎች አቀበላት። ከቁልፎቹ ውስጥ አንዷን መርጣ አወጣችና አጠገቧ ያለ መሳቢያ ስባ የስልኩን ደብተር አውጥታ አቀበለችው።

"እግዜር ይስጥልኝ" አላት ማውጫውን ተቀብሏት እየከፈተው።

'የምሥራች ይልማ' መጀመሪያ የምሥራችን ስም ፈለገ። በርካታ የምሥራች ይልማዎች የተደረደሩበትን ገፅ እንዳገኘ የስልክ ቁጥሯን ፈለገው። ቁጥሩን እንዳገኘ ወደኋላ ተመልሶ በትይዩ የተፃፈውን የምሥራችን ስም እስከ አያቷ ስም አነበበው -'የምሥራች ይልማ ገዛኸኝ'።

"አቶ ይልማ ገዛኸኝ" ድጋሚ የስልክ ማውጫውን እየገለባበጠ ይፈልግ ጀመር...

አቶ ይልማ ገዛኸኝ... ይ... ይ... ይ... ይልማ አዳሙ... ይልማ ብሩቱ ... ይልማ ገብረማርያም...ይልማ ገዛኸኝ!

የስልክ ቁጥሩን በወረቀት ላይ ገለበጠና የቡና ቤቱን ገንዘብ ተቀባይ አመስግኖ ወጣ። እዚያው አካባቢ የሕዝብ ስልክ ፈልጎ አቶ ይልማ ገዛኸኝ መኖሪያ ቤት ደወለ።

"አ..ቤት" አለው ቀጠን ያለ የሴት ድምፅ።
"እባኮት አቶ ይልማን ነበር"
"ሥራ ናቸው" አለች ሴትየዋ በተሰላቸ ድምፅ።
"እባኮት ችግር ገጥሞኝ ነው የሥራ ቦታቸውን ስልክ ቢሰጡኝ።"

"የሱቁን ነው?"
"አዎ ... ላገኛቸው የምችልበትን ቦታ።"

ነገረችው። ቀልጠፍ ብሎ ቁጥሩን ጻፍ ጻፍ አደረገና አመስግኗት ስልኩን ዘጋ። ወዲያው የሰጠችውን ቁጥር ደወለ።

"ሃሎ" አለ ውፍረት የደፈነው፣ ሲጋ የዘጋው፣ እርስ በእርሱ የሚተሻሽ ድምፅ።
"እባኮት አቶ ይልማ ይኖራሉ?"
"ነኝ። ማን ልበል?"
"እንደምን ዋሉ። የምሥራች ነበረች የላከችኝ..." ናትናኤል የሰውየውን ስሜት ለማጥናት ለአንድ አፍታ ዝም አለ።

"ማን አሉኝ?" አሉ ሰውየው መልሰው።
"የምሥራች... የምሥራች ይልማ።"
"ከየት ነው? ማንኛ ነው የሚፈልጉት?" ሰውየው ግራ የተጋቡ መሰሉ።
"የምሥራች... የምሥራች የእርሶ ልጅ።"
"የማን ልጅ?" ሰውየው ይበልጥ ተደነጋገራቸው።
"ካዛንቺስ ሆቴል ያላት የእርሶ ልጅ።የምሥራች ይልማ...ባለሆቴሏ።"
"የምን ሆቴል ነው የሚሉኝ?"
ይቅርታ ጠይቋቸው ስልኩን ዘጋ።

ሌላ ይልማ ገዛኸኝ በአዲስ አበባ ስልክ ማውጫ ደብተር ውስጥ የተመዘገበ የለም። ያለው አማራጭ ወደ ድሬዳዋ መጓዝ ብቻ ነው። ድሬዳዋን አያውቃትም። እዚያም ሄዶ መቸገሩ የማይቀር ነው። ግን የተሻለ ምርጫ የለም።

መፍጠን አለበት። ምንም ጠባብ ቢሆን በተከፈተለት በር ሁሉ መሮጥ አለበት። ወደ ካልቨርት መጠጋት አለበት።

ዝግጅቱን ለማጠናቀቅ ወደ ባቡር ጣቢያ ሄዶ በማግስቱ ምሽት ላይ ወደ ድሬዳዋ በሚሄድ ባቡር ላይ የሁለተኛ ማዕረግ ትኬት ከቆረጠ በኋላ አውቶቡስ ተራ ወደ ዘውዲቱ ቤት ወደ ጎሬው በረረ።

ምሳውን ከዘውዲቱ ጋር ከበላ በኋላ ከሰዓት ወደ ገበያ ወጣ። መርካቶ የዘመን መለወጫ በዓልን- መስከረም አንድን - ለመቀበል በሚዘገጃጅ ገበያተኛ ተጣባለች።



ወደ ድሬዳዋ ሲሄድ ሲለብስ ያሰበውን ጀለቢያና ሸርጥ ነጠላ ጫማ እንዲሁም አንድ አነስተኛ የሸራ ሻንጣ ገዛ። አዲስ አበባ እስካለ ድረስ ደግሞ አጥልቆት የሚዘዋወረውን ውራጅ የጋራዥ ቱታና ራቱን ጥሩ አድርጋ የምትሸፍንለት አንድ የተልፈሰፈሰች ባርኔጣ ጨመረ።መንገድ ላይ ከአንድ ጋራዥ ገባ ብሎ ለዘበኛው ሁለት ብር ሰጠና በትንሽ ቆርቆሮ የተቃጠለ ዘይት ይዞ ወደ ጎሬው ሲመለስ ከአንድ ሱቅ ገብቶ አንድ ጥሩ ሸቶና የቤት ነጠላ ጫማ ሸመተ። ከዘውዲቱ ቤት ሲደርስ ባይመሽም ቀኑ ገፍቶ ነበር። ልብሱን አወላልቆ ዘውዲቱ አልጋ ውስጥ ገብቶ ጥቅልል አለ። የዘውዲቱን ቤት ተከራይቶ ከገባ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘውዲቱ አብራት የሚያድር ደንበኛ አጥታ እንድትመጣ ተመኘ።

ያን ሌሊት ዘውዲቱ ቀንቷት ደንበኛ አገኘች፤አልተመለሰችም። አልጋዋ ላይ ብቻውን ሲገላበጥ ሲያቃዠው አደረ።አንዱን ቅዠት ሳያገባድድ ሌላ ቅዠት እያቋረጠው ያባረረው ውሻ ሳይዘው ጭልጥ ካለ ገደል እየገባ... ከገደሉ ወለል ደርሶ አናቱ እንደ እንቁላል ሳይፈርጥ አየር ላይ ጭልፊቶች ገላውን እየገመጡ አይኖቹን እየጓጎጡ ሲወራጭ አደረ።

ጠዋት በሩ ሲከፈት በርግጎ ሲነሳ ጭንቅላቱን በፋስ ሲወቅረው ተሰማው -እራስ ምታት ነፍስ ዘርቶ።

"እንደምን አደርክ?" አለችው ዘውዲቱ ወደ ውስጥ ገብታ በሩን እየዘጋች። "እስካሁን አልተነሳህም? ሁለት ሰዓት አልፏልኮ።" የያዘችውን የላስቲክ ከረጢት ወንበር ላይ ጣል አድርጋ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለችና ኩንታል ስትሸከም እንዳደረች "ኡፍ......ፍ!" አለች። "እንዴ ለምን እራትህን ሳትበላ አደርክ?" አለች ሳይከፈት ያደረውን የምግብ ሳህን ከራስጌ ስታይ ዞራ እየተመለከተችው።

"አላየሁትም ነበር።" አላት ናትናኤል እራቁት ደረቱን እያከከ ዞሮ ከራስጌ የተቀመጠውን ሳህን እየተመለከተ።

"እና ጾምህን አደርክ ማለት ነው? ደግሞ ከትላንት ወዲያ የት ነበር ያደርከው?" ጥያቄ አከታተለችበት።

ሳይመልስላት ከአልጋው ተነስቶ ከወገቡ በላይ ለመለቃለቅ በሩን ከፍቶ ወጣ። ሰውነቱን ተለቃልቆ ሲመለስ ዘውዲቱ ከራስጌ ያደረውን ሳህን ከፍታ በግራ እጇ ይዛ እየተንጎራደደች በላይ በላዩ ስትጎርስ አገኛት።

"ቡዳ የሆነ ሰውዬ...ራቱን ሳያበላኝ ቤቱ ወስዶ እንደቅሪላ ሲያለፋኝ አደረ።" አለች እየሳቀች። "ሳጉርስህ?"
ራሱን ነቀነቀ። ናትናኤል ምግብ አላሰኘውም።
"ምን ሆነሃል? ቤት ደህና አይደሉም እንዴ?"

"ደህና ናቸው እነሱ..." የጀመረውን እንጠልጥሎ ተወው::
"ታዲያ ምን ሆነሃል?"
"ሰውየው ተያዘ::"

"የቱ ሰውዬ?" መንጎራደዷን አቁማ በተቀመጠበት ቁልቁል ተመለከተችው::
"አሊቃዬ:: የመሥሪያ ቤታችንን ገንዘብ ያጠፋው::"

"አትለኝም!" የያዘችውን የምግብ ሳህን ከራስጌ አስቀምጣ በወጥ የተጨማለቀ እጇን አንከርፋ አልጋው ላይ ከጎኑ ተቀመጠችና አይን አይኑን ትመለከተው ጀመር:: "ውሸትክን ነው!"

ናትናኤል ከዘውዲቱ የሚለይበት ሰዓት እንደደረሰ የተገነዘበው ከአንድ ቀን በፊት ነበር:: የምሥራች "እማዬጋ... ድሬዳዋ" ካለችው ወዲያ:: ዘውዲቱን ሲሰናበታት ደግሞ ምክንያት መስጠት አለበት:: ቢሆንም ችግሩ ሁሉ እንደተፈታ አድርጎ መቅረብ የለበትም:: መጪው አይታወቅም:: ማን ያውቃል... ተመልሶ ወደ አዲስ አበባ መምጣትና መሸሸግ ያስፈልገው ይሆናል:: ያን ጊዜ የት ይገባል? ዞሮ መግቢያው መሸሸጊያው ነች-ዘውዲቱ::

"አዎ ተያዘ ዘውድዬ... እየተመረመረ ነው አሉ:: ግን ገና ነው፤ ያመነ አይመስለኝም::"

"እ..ሺ!" አለች ለተጨማሪ ወሬ ጓጉታ ድዷ ውስጥ የገባ ምግብ በምላሷ እየጠረገች::

"ግን መጥፎ ወሬ ሰማሁ..."
"ምንን?" ቅንድቦቿን አጠጋጋቻቸው::
"ፖሊሶች አዲስ አበባ ውስጥ መደበቄን ደርሰውበታል አሉ:: ያየኝ ሰው ሳይመራብኝ አልቀረም::"
"ገብርኤልን!..." ደነገጠች:: "እንዴት አወቅህ?"
"በየዘመዶቼና በየጓደኞቼ ቤት እየዞሩ ሲያጠያይቁ ነው አሉ የሰነበቱት::" አላት ሃሳብ እንደገባው ሁሉ አይኖቹን ቡዝዝ አድርጎ ለምጻም ግድግዳዋ ላይ ተክሎ::

"አይዞህ:: እዚህ ሊያገኙህ አይችሉም፤ ከቤት አለመውጣት ነው... ድምፅህን ካጠፋህ..." ልታረጋጋው ጀመረች::

"አይ ዘውድዬ... እኔም ተደገፍ ለአንቺም መዘዝ ከምሆን ከአዲስ አበባ ብወጣ ይሻላል:: እማዬጋ ልሄድ ነው ያሰብኩት::"



"የት ናቸው እናትህ?"
"ደብረብርሃን::"

ከሰዓት በኋላ ጆለቢያውን ነጠላ ጫማውን ሌሎቹንም እቃዎቹን በሽራው ቦርሳ ውስጥ ቀርቅቦ፤ በተቃጠለ ጥቁር ዘይት የተጨማለቀ ቴታውን አጥልቆ፤ ልፍስፍስ ባርኔጣውን አድርጎ ተሰናበታት::

"ልክ አይደለህም:: ይሄን ያህል ጊዜ አብረን ቆይተን... ዘመን መለወጫ ሁለት ቀን ሲቀረው ትተኸኝ ትሄዳለህ? በፍጹም ልክ አይደለህም:: ምናለበት ሁለት ቀን ቆይተህ እንቁጣጣሽን አብረን ብናሳልፍ" ተለማመጠችው::

"አይሆንም ዘውድዬ:: ከደረሱብኝ መጥፎ ነው::" አለ ጊዜ ማጥፋት እንደማይገባው ለራሱ እየመከረ:: "ዘውድዬ ይሄን ለአንቺ ነው የገዛሁት::" አላት ሹራቡንና ነጠላ ጫማውን እየሰጣት:: "ብድር መመለሴ አይደለም፤ ብድርሽን የምመልሰው ጥሩ ቀን ሲመጣ ነው:: ይሄን ለዘመን መለወጫ ነው የገዛሁልሽ::"

የዘውዲቱ ዓይኖች በእንባ ተሞሉ:: ለስላሳነት ሲያይባት የመጀመሪያ ጊዜው ነበር:: ሁሌ ተናጋሪ ሁሌ ግድ የለሽ ነበረች ዘውዲቱ:: አይኖቿ ውስጥ ያቆረዘዘውን እንባ ሲመለከት እሷም ለስላሳ፣ እሷም ሙቅ እንደሆነች ተረዳ:: ዘላ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበት::

ከዘውዲቱ ቤት ሲወጣ ዘጠኝ ሰዓት አልሞላም ነበር:: ወደ ድሬዳዋ የሚጓዘው ባቡር ምሽት ላይ ይነሳል:: ወደ ድሬዳዋ ከመሄዱ በፊት ግን ርብቃ መሥሪያ ቤት ለመደወል ወሰነ::

ርብቃ መሥሪያ ቤት ሲደውል ምህረትን ሲያገኝ ግን ያልጠበቀው ዱብ ዕዳ ጭንቅላቱን መታው -የሱ ርብቃ አርግዛለች...የሱ ርብቃ ልጁን በሆዷ ተሸክማ ብቻዋን ትጨነቃለች... የሱ ርብቃ...'

ናትናኤል ወደኋላ ጋደል ካለበት ወንበር ላይ ቀና አለና ተቀመጠ:: ሰዓቱን ተመለከተ:: አስራ አንድ ተኩል ሊል ነው:: የርብቃን ወንድም በአስራ ሁለት ተኩል ነው የቀጠረው:: አንድ ሰዓት አለው ማለት ነው::

ከተቀመጠበት ተነስቶ ከቡና ቤቱ ወጣ:: ሰማዩ ላይ ያዘበዘበው እርጉዝ ደመና ሌሊቱን ሀይለኛ ዝናብ ሊጥል እንዳሰበ ያስታውቃል:: ለነሃር ታክሲ ይዞ በቸርችል ጎዳና ሽቅብ ወደ ፒያሳ - ወደ ርብቃ አፓርታማ አመራ::
'መጠንቀቅ አለበት:: በቤቷ አካባቢ የሚያንኮብቡ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ::ሲገባና ሲወጣ መታየት የለበትም:: አለበለዚያ እርጦ ከእጃቸው

እንደገባላቸው ነው የሚቆጠር:: መጠንቀቅ አለበት::/ ቀጥታ ወደ ክፍሏ ማምራት የለበትም:: መሰለል... ዙሪያውን ማጥናትና መጠንቀቅ... አለበለዚያ ለሷም ተጨማሪ ችግር ነው የሚፈጥርባት'

ርብቃ አፓርትመንት ከመድረሱ በፊት እራቅ ብሎ ከታክሲ ወረደና የሸራ ሻንጣውን ትከሻው ላይ አንግቦ ጭንቅላቱ ላይ የደፋትን የጨርቅ ቆብ ወደ ታች ወደ ግንባሩ እየጎተተ በመንገዱ ቀልቀል በእርጋታ ወረደ:: ሰዓቱ ገና ቢሆንም ከዳር እስከ ዳር ያንገርበበው ጥቁር ደመና አካባቢውን የመሸ አስመስሎታል:: ሰዓቱን ተመለከተ:: በአንድ ሰዓት አካባቢ ባቡር ጣቢያ መገኘት ይኖርበታል::

ሃምሳ ደቂቃዎች አሉት... ብዙ መቆየት የለበትም - ርብቃ ጋ:: ቶሎ አይቷት መውጣት አለበት:: መጨከን አለበት... መጨከን... መጨከን::

-24-

እንደ ድንጋይ ከተጫናት ሰመመን ውስጥ ቀስ በቀስ እየወጣች ስትመጣ... እላይዋ ላይ ተጭኖ የያዛት ድቅድቅ ጨለማ እንደ ጭስ እየሳሳ እየበነነ ለቋት ሲጠፋ በመጀመሪያ የተቀበላት በእግሮቿ መሃል የሚንዝራት የደነዘዘ ስቃይ ነበር:: ቀስ በቀስ ጭንቅላቷ እየጠራ ቢመጣም አይኖቿን ለመክፈት አልደፈረችም:: ሌላ ዱላ፣ ሌላ ስቃይ ሌላ የጋለ ሽቦ የሚችል አካል አልነበራትም:: በክፍሉ ውስጥ ብቻዋን ትሁን አትሁን እርግጠኛ አልነበረችም:: አይኖቿን ለመክፈት ግን አልደፈረችም::

እጆቿ ግራና ቀኝ ተወጥረው ከታሰሩበት ተፈተው በድን እንደሆኑ ሁሉ በግራና በቀኝ ተዘርረዋል:: በተኛችበት ልብስ ደርበውላታል:: እግሮቿ ግን አሁንም ግራና ቀኝ ሁለት ቦታ ተወጥረው እንደታሰሩ ናቸው:: ቁስሏን ለማዳመጥ ሞከረች:: በጭኖቿ መሃል የሚሰማትን ስቃይ ለማዳመጥ ዝም አለች - የተዳፈነ... የደነዘዘ... የደበዘዘ ስቃይ:: ግራ ክንዷ ላይ ህመም ተሰማት:: ለመነቃነቅ ግን አልደፈረችም:: በአይነ ህሊናዋ ሁኔታውን ለመቅረፅ ሞከረች:: መቼ ነበር በጋለ ሽቦ ጭኖቿ መሃል ስውነቷን ያቃጠሏት? ዛሬ? ትላንት? ዛሬ ምንድነው? ቀን ነው ሌሊት? ሰዓታትና ቀናት ትርጉም ካጡባት ቆይተዋል::

ድምፅ የሰማች መሰላት:: ዓይኖቿን እንደከደነች ጆሮዎቿን አስልታ ተጠባበቀች:: የበር ድምፅ ተሰማት... የሚከፈት በር የሚያሰማው ድምፅ...

"አልተነሳችም::" አለ አንድ ድምፅ በሹክሹክታ::



"ኮሎኔል" አለ አንድ ድምፅ በሹክሹክታ "ዙሪያውን አጥረነዋል:: በርም ላይ አንድ ሰው አቁመን እየተጠባበቅን ነው::"

"መጣሁ" ሲል ተሰማት ማርቆስ::

ሁለት የእግር ኮቴዎች በግራና በቀኟ ተሰሚት...በስተቀኝ አንድ መዳፍ ግንባሯ ላይ አረፈ::

"ከነቃች የመርፌ ማደንዘዣውን ስጣት:: ስቃይ ሊኖርባት ይችላል::" የማርቆስ ድምፅ ነበር::

"ካስቸገረችኝስ... ልምታት?" አለ በስተግራዋ የቆመ ሌላ ሰው::

"ረጋ ብለህ አባብለህ ውጋት:: ለምን ትመታታለህ? ደግሞ አታስቸግርህም... ከተወራጨችብህ ግን ግሉኮሱን ንቀልላት::" አለ እጁን ግንባሯ ላይ የጫነው ማርቆስ በጣቶቹ ፀጉሯን ወደኋላ እያበጠረ:: "ጠዋት እቀየርልሃለሁ::"

ኮቱ ተሰማት:: ተከታትለው ሲወጡ ሰማች:: በሩ ሲዘጋ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሲነግስ ስትፈራ ስትቸር አይኖቿን ገለጠቻቸው::መኝታ ክፍሏ ውስጥ ብቻዋን አስተኝተዋታል:: በቢጫው የብርድ ልብሷ ከአንገቷ እስከ እግሯ ጫፍ ድረስ ሸፍነዋታል:: በተንጋለለችበት ዙሪያዋን ተመለከተች:: ግራ ክንዷ ላይ የሚሰማት ህመም ከራስጌዋ ከተንጠለጠለው የግሉኮስ ከረጢት ጋር የተያያዘው መርፌ ክንዷን ጠልቆ የገባበት ላይ መሆኑን ተረዳች:: የክፍሉ መጋረጃ ተዘግቷል:: በጥግና ጥግ የታየው ሰማይ ጨልሟል... መሽቷል:: ለመነቃነቅ ስትሞክር ግራና ቀኝ የታሰሩት እግሮቿ መሃል የተዳፈነው ስቃይ እንደ ጦር ወጋት:: ከስሱ የብርድ ልብስ በታች ያለው እራቁት ሰውነቷ ተንሰፈሰፈ::

ድምፅ ተሰማት- የመኝታ ቤቷ በር ተከፈተ:: ቶሎ ዓይኖቿን ጨፈነቻቸው:: እንደነቃች ማወቅ የለባቸውም:: ዝም ብላ መተኛት ነው ያለባት:: መረበሽ የለባትም! አለበለዚያ ይመቷታል:: ዝም ብላ መተኛት:: በሩ ሲዘጋ ተሰማት! የእግር ኮቴ እየቀረባት መጣ... አንድ በላብ የረጠበ እጅ እራቁት ትከሻዋ ላይ ሲያርፍ ተሰማት... ትንፋሹ... እላይ እታች የሚል ትንፋሽ... እላይዋ ላይ የነበረው ስስ የብርድልብስ ተገፈፈ... መረበሽ የለባትም... መንቃቷን ማወቅ የለባቸውም... አለበለዚያ ድጋሚ ያሰቃይዋታል... ትከሻዋ ላይ ያረፈው በላብ የራሰ መዳፍ ወደታች ወደ ደረቷ ተንሸራተተ... አልተንቀሳቀሰችም... ጡቶቿ ሲዳሰሱ ተሰማት... እላይ እታች የሚል ትንፋሽ... ፍርሃት ወረራ... ግራ ክንዷ ላይ የተሰካውን መርፌ አስሮ የያዘው ፕላስተር ተላጠ... ክንዷ ላይ የተሰካው መርፌ ተነቀለ... መንቃቷን ማወቅ የለባቸውም... አለበለዚያ ይመቷታል... እላይ

እታች የሚለው ትንፋሽ ቀረባት:: ብርድ ልብሷ ወደታች ተጎተተ... ፍርሃቷ እየጨመረ መጣ... እላይ እታች የሚለው ትንፋሽ ወደ አንገቷ ስር ሲጠጋ ተሰማት... ብርድ ልብሱ ከላይዋ ላይ ተንሸራቶ ወደ መሬት ወደቀ:: ራሷን መቆጣጠር አቃታት... አይኖቿን ገለጠቻቸው::

ጺማሙ ሰውዬ ነበር:: እላይዋ ላይ እንዳንገርበበ ድንገት አይኖቿን ስትገልጥ ደንገጥ አለ:: ወዲያው ... ፈገግ አለላት... የሸሚዙን ቁልፎች መፍታት ጀመረ... ፈገግ አለላት ድጋሚ... ሸሚዙን ከላዩ ላይ ወርውሮ ተጠጋት... እጆቹን ጡቶቿ ላይ ጫናቸው... ድንገት ተወራጨች:: ሙቅ... እርጥብ እጆቹን ከላይዋ ላይ ገፍትራ ተሸማቀቀች... ፈገግ አለላት:: አልጋዋ ላይ የተንጋለለውን እራቁት ገላዋን ከላይ እስከታች በተራቡ አይኖቹ ዳሰሰው:: ምራቁን ሲውጥ... ትልቅ ማንቁርቱ እላይ እታች ሲመላለስ... በፍርሃት ተንቀጠቀጠች:: ድንገት ዘሎ አፏን በመዳፉ አፈናት... ታገለችው... እጆቿን እያፈራረቀች እንደብረት የደደሩ ሁለት ክንዶቹን ደበደበቻቸው ... ቢጠብቻቸው... ያለብዙ ችግር አፏ ውስጥ ጨርቅ ነስንሶ ለጎማት...

ትንፋስ-ትንፋስ እያለ ቁልቁል ተመለከታት:: አይኖቹ የሚያርፉበት ቦታ ያጡ ይመስላል:: መላ ሰውነቷ ላይ ተንቀዠቀዠ...

ሱሪውን ማውለቅ ጀመረ... በተንጋለለችበት... በምሬት... ጭንቅላቷን አወራጨችው... እንባዋ ደረሰላት...

-25-

"ቢሮው ትዕግስቱ አልቋል::" አለ ከቴልአቪቭ የገባው ይሁዳ አሚ የብርቱካን ጭማቂውን ተጎንጭቶ ብርጭቆውን ካስቀመጠ በኋላ ረጅም ጺሙን እየዳሰሰ::

የአዲስ አበባ ሂልተን ሆቴልን የመዋኛ ስፍራ በስተቀኛቸው አድርገው ተቀምጠዋል:: በርካታ እንግዶች በመዋኛ ልብሶቻቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ:: የተቀሩት በደረትና በጀርባቸው እየተገላበጡ ጭል ጭል የምትለውን ለስላሳ የጸጉሜ ፀሐይ ይሻማሉ::

ይሁዳ አሚ በሆቴሉ ውስጥ ከያዘው የመኝታ ክፍል ወጥቶ ከቀጠሮአቸው ስፍራ የደረሰው ልክ በሰዓቱ ነበር:: ከቀጠሮው ሰዓት ቀደም ብሎ የደረሰው አሃሮን የእንግዳውን ፀባይ ስለሚያውቅ የብርቱካን ጭማቂ አዝዞ ከፊት ለፊቱ አስቀምጦ ይጠባበቅ ጀመር:: አሚ የሌሊት ልብሱን ሳይቀይር በላዩ ላይ ወፍራም የጠዋት ልብሱን ደርቦ ወገቡ ላይ ቀበቶውን ሸብ አድርጎ ከጥጥ የተሰራ ወፍራም የእግር ሹራብና የቤት ነጠላ ጫማ



እንዳደረገ ወደ መዋኛው ስፍራ የሚወስደውን ደረጃ በእርጋታ ወርዶ ወደ አሃሮን አመራ::

"እንኳን ደህና መጣህ::" አለ አሃሮን ተነስቶ እንደቆመ የአሚን እጅ ጠበቅ አድርጎ እየጨበጠ::

"እንኳን ደህና ጠበቅኸኝ::" አለ አሚ ነጫጭ ውብ ጥርሶቹን ለአንድ አፍታ ብልጭ አድርጎ የግደኛውን እጅ እየወዘወዘ::

አሚ "ኪዶን" በሚል ስያሜ በሚታወቀው የሞሳድ ገዳይና አፋኝ ክፍል ውስጥ ለአስራ ሰባት ዓመታት የሰራና 'አትግደል' እና 'አትዋሽ' ከሚሉት ከሙሴ ትዕዛዛት በስተቀር በተቀሩት በስምንቱ ትዕዛዛት ላይ ፌዝ የማያውቅ ጥብቅ ሃይማኖተኛ አይሁዳዊ ነው:: በሌሊት ልብሱ ላይ የደረበው ወፍራም የጠዋት ልብስና ቡፍ ካለ ጥጥ መሳይ የቤት ጫማው ጋር ሲያዩት ጺማሙ ሰው በቤት ውስጥ ተቀምጦ የሳጠራ ዘንቢሎችን ሲሰራ የሚውል የዋህ ገበሬ ይመስላል::

"የብርቱካን ጭማቂ::" አለ አሚ ፈገግ ብሎ ከጎኑ የቆመውን የሆቴሉን አስተናጋጅ እየተመለከተ::

የአልኮል መጠጥ ፍጹም የማይቀምስና የአሳማ ስጋ አፉ የማይገባ ጥብቅ ሃይማኖተኛ የሆነው አሚ በመስከረም 5 1972 በሙኒክ ሃያኛው ኦሎምፒክ ዝግጅት ላይ የብላክ ሴፕቴምበር ቡድን የእሥራኤል ስፖርተኞችን ሰፈር በመውረር አስራ አንድ ተጨዋቾችን ከገደለ በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትር ጎልዳሜይርን የብቀላ ትዕዛዝ ዳር ለማድረስ ሞሳድ ኦፕሬሽኑን እንዲመራለት የመረጠው ከፍተኛ ችሎታ ያለው የመረጃ ሰው ነው:: ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት የተቀበለው አሚ በአንድ ወቅት በያሲር አራፋት 'ፋታህ' ድርጅት ውስጥ የስለላ ኃላፊ የነበረውንና በኋላም ሞሳድ የሙኒኩ ሽብር ጠንሳሽ ነው ያለውን ዩሱፍ ናደር ወይም አቡ ዩሴፍንና በቀጥታ የሙኒኩን እልቂት አቀናጅቷል ብሎ የጠረጠረውን ዓሊ ሃሰን ሳሌም ወይም ሞሳዶች በሰጡት የቅጽል ስም 'ቀዩን ልዑል' ጨምሮ ከሰላሳ አምስት በላይ የሚሆኑ ቀንደኛ ሽብርተኞችን በኪዶን አፈሙዞችና ፈንጂዎች በያሉበት ሲለቅማቸው የገዛ እለቆቹ ሳይቀሩ በመደነቅ ራሳቸውን ነቀነቁ:: በጥቅምት 1972 በሮም የፒ.ኤል.ኦ ተወካይ በነበረው አብዱልዋይል ዝበይተር ግድያ የተጀመረው የሞሳድ የአሸባሪዎች አደን በምሥራቅና በምዕራብ አውሮፓ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ ለወራት ሽብር ሲነዛ ቆየ::

ከዚያ ሽብር ወዲያ አሚ በሞሳድ ውስጥ እንደሚከበር ሁሉ በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙ ሽብርተኛ ቡድኖች ተጠላ::

"ቢሮው ትዕግሥቱ አልቋል::" አለ አሚ የቀረበለትን የብርቱካን ጭማቂ እያነሳ::

"ባለኝ ሃይል ሁሉ እየተንቀሳቀሁ ነው::" አለ አሃሮን አሚን ለመምሰል ቀደም ብሎ ያዘዘውን የብርቱካን ጭማቂ ገፋ እያደረገ::

"ወንድሜ" አለ አሚ ጺሙን ወደታች እየላገ "ከአሁን በኋላ በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ለመሰብሰብ የምናደርገው ጥረት ብቻውን መልስ እንደማይሆን ቢሮው አምኗል::"

"ይሁዳ" አለ አሃሮን ፈገግ ብሎ "አንተ እንደምትመጣና እንድቀበልህ መልዕክት ሲደርሰኝ ምን እንደሚከተል መገመት አላስቸገረኝም::" አለ አሃሮን በምሳድ ገዳይና አፋኝ ቡድን አባል የሆነውን ሰው እየተመለከተ::

"ጥሩ ገምተሃል እንግዳው::" አለ አሚ ፈገግ ብሎ "ለማንኛውም ዝርዝር ዕቅዱን እሰጥሃለሁ:: መኝታ ቤቴ ሻንጣዬ ውስጥ አለ:: ለጊዜው ዋና ነጥቡን ከፈለግህ በአጭሩ ላስረዳህ እችላለሁ::"

"ቀጥል::" አለ አሃሮን በወንበሩ ላይ እየተመቻቸ::

"አሃሮን" አሚ ለአንድ አፍታ ዞር ዞር ብሎ አካባቢውን ካጠና በኋላ ቀጠለ "ባለፉት ሁለት ሳምንታት በአፍሪካ አደገኛ የጦር መሣሪዎች ሲንቀሳቀሱ ሰንብተዋል:: መነሻው በእርግጠኝነት ከዚህ ነው ማለት ባይቻልም ወይ ከጆሃንስበርግ አለዛም ከካይሮ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ::"

"አደገኛ የጦር መሣሪያ ስትል?" አለ አሃሮን ድምፁን ቀንሶ

"እጃችን የገቡት ማስረጃዎች ጥቂት ፎቶግራፎችና ግማሽ በግማሽ የተቃጠለ ጥራዝ ነው:: እነዚህ ማስረጃዎች እንዴት እንደተገኙ ግን ለእኔ ግልጽ አይደለም:: የሆነው ሆኖ ወደተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የተጓጓዙት መሣሪያዎች በርካታና ዓይነታቸውም የተለያየ ቢሆንም አስገራሚ ሆኖ የተገኘው ግን በስሪቱ የሶቭየት ህብረት ከሆነው የስትሬላ ሚሳይል ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ከትከሻ ላይ የሚወነጨፍ ሚሳይል ነው" አለ አሚ::

"ምኑ ላይ ነው አስገራሚነቱ?" አለ አሃሮን::

"ጥራዙ ውስጥ ያሉ ያልተሟሉ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ እነዚህ ሚሳይሎች የኒውክሊየር አረር የሚገጠምላቸው ናቸው:: ይህ ምን



ማለት እንደሆነ ይገባሃል::" አለ አሚ:: ለመጀመሪያ ጊዜ በጥልቀት ተንፍሶ በዝምታ የሚያዳምጠውን አሃሮንን እየተመለከተ ቀጠለ:: "አስፈሪው ነጥብ ግን የአፍሪካ አገሮች አደገኛ የጦር መሣሪያዎችን መቀባበላቸው አይደለም:: ዋናው ነጥብ ከእነዚህ መሣሪያዎች ውስጥ የተወሰኑት ከአፍሪካ ውጪ ወደአልታወቁ ሥፍራዎች ተወስደዋል የሚል የመረጃ ፍንጭ መገኘቱ ነው:: ይህ ደግሞ የኒውክሊየር አረር የተገጠመላቸውና ከሰው ትከሻ ላይ ሊወነጨፉ የሚችሉ ሚሳይሎችን በአጥፍተህ ጥፋ የሽብር ፈጠራ ጥቅም ላይ ሊያውላቸው የደፈረ አንድ ወገን አለ ማለት ነው:: ውጤቱን አንተ እራስህ ልታሰላው ትችላለህ::"

"በገዛ ደጃፍህ ቆመህ ዓለም ስትጠፋ ታያለህ ማለት ነው::" አለ አሃሮን የኒውክሊየር ሽብር ፈጠራ ምን ገጽታ ሊኖረው እንደሚችል ለማሰብ እየሞከረ::

"ምናልባት እያንዳንዱ የአውሮፓ የአሜሪካና የእስያ ታላላቅ ከተማ በኒውክሊየር አረሮች ይመታል:: አስጠሊታው ጉዳይ ግን ማንኛውም መንግሥት በየትኛውም አገር ወይም ቡድን ላይ የምላሽ ጥቃት መሰንዘር እንዳለበት ሊያውቅ አይችልም:: ምክንያቱም ጥቃቱ የሚፈጸመው እዚያው ከውስጥ ሰርገው በሚገቡ ያበዱ ሽብርተኞች ይሆናል::"

"የፈጣሪ ያለህ! ታዲያ ያንተ እዚህ መምጣት..." አሃሮን የጀመረውን ጥያቄ ሳይጨርስ በመሃል አቋረጠ::

"አሃሮን" አለ አሚ አይኖቹን ከመዋኛው ሥፍራ ዙሪያ ብሚሯሯጡ ህፃናት ላይ ተክሎ "እኔ ወደእዚህ የመጣሁት የዚህ ሁሉ ምሥጢር ጭንቅላት አዲስ አበባ ውስጥ ስለሆነ ነው:: እነዚህ አደገኛ መሣሪያዎች ከአንዱ የአፍሪካ አገር ወደሌላው እንዲጓጓዙ የተሰጠው ትዕዛዝ በትክክል በማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ቢያዳግተንም ትዕዛዙን ያስተላለፈው አካል እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ለመገኘቱ እርግጠኛ ሆነናል::"

"ይህ ነገር ፍጹም ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን ያስፈራል::" አለ አሃሮን የተሰማውን መደናገጥ ለመደበቅ ሳይሞክር::

"ትክክል ነህ:: ቁልአቢብም ከተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ የደረሰ ይመስለኛል::"

"እና የሚቀጥለው ምንድነው ... ምንድነው መፍትሄው...?

"እኔና አንተ ቀድመን አዲስ አበባ ውስጥ እሳት እናቀጣጥላለን::" አለ አሚ::

"አልገባኝም::"

"አሃሮን ከሚቀጥሉት ቀናት ጀምረን በጭፍን በእጃችን የገባውን ማንኛውንም ከፍተኛ ወታደራዊ ባለሥልጣንና የአፍሪካ ዲፕሎማት እንገድላለን፤ እናፍናለን:: ይህ በተለያዩ የአፍሪካ ከተማዎች በአንድ ሰዓት ይጀመራል:: ኦፕሬሽኑን የሚመራው ሌላ ሥራ አቁመው እዚህ ላይ ብቻ ሃያ አራት ሰዓት በሚሰሩ የበላይ ባለሥልጣናት የተደራጀ ቡድን ከቴልአቪብ ነው:: እኔ የአዲስ አበባውን ሽብር ልመራ ነው የመጣሁት:: ረዳቶቼ በሚቀጥሉት አራት ቀናት ገብተው ይጠናቀቃሉ::"

"ጭፍን ሽብር ወዴት ያደርሰናል?"

"እየሁ... ለጠራት ብንታገልም ወደ ምስጢሩ ሰብረን ማለፍ አልቻልንም:: ይህ የሚያሳየው ደግሞ ምሥጢሩ የሚጠበቀው እጅግ ከፍተኛ የድርጅት ብቃት ባለው አካል መሆኑን ነው:: ስለዚህ እኛ በጭፍን የምናካሂደው ሽብር በዚህ ድርጅት ሥንሥለት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል:: ሆኖም ዋናው ጥቃት ይህ አይደለም:: ዋንኛ ዓላማችን በድርጅቱና በመላው አፍሪካ ውስጥ ሽብር መንዛትና የእርስ በርስ አለመተማመንን መዝራት ከዚያም ተከትሎ በሚመጣው መፍረክረክና ግርግር ወደ ምሥጢሩ የሚያደርሰንን ቀዳዳ መፈለግ ነው:: እየሁ ግድያውንና አፈናውን የምናካሂደው እኛ መሆናችንን እስካልደረሱበት የድርጅቱ አባላት የእራሳቸውን አንድነት መጠራጠርና እርስ በእርስ መፈራራት ይጀምራሉ::"

"እና እርስ በእርስ ቢፈራሩስ?"

"በአጭር ጊዜ ውስጥ ድርጅቱ አፈናውንና ግድያውን እስካልተቆጣጠረው ድረስ እያንዳንዱ አባል የገዛ እራሱን ነፍስ ለማዳን ሽሽትና ማፈንገጥ ውስጥ ይገባል፤ክህደት ይከተላል::"

"ጥሩ:: ግን የኔ ድርሻ ምንድነው?" አለ አሃሮን::

"እርዱን እኔ አካሂዳለሁ:: አንተ በግርግሩ ውስጥ ወደ ምሥጢሩ የሚያመራውን ቀዳዳ ትፈልጋለህ::"

"መቼ ነው የሚጀመረው ያንተ እርድ?" አለ አሃሮን ፈገግ ብሎ::

"ከሦስት ቀናት በኋላ::"

"ጥሩ" አለ አሃሮን በረጅሙ ተንፍሶ:: ትንሽ ካመነታ በኋላ ቀጠለ "ግን ምናልባት ከዚያ በፊት ምሥጢሩን አገኘዋለሁ የሚል ግምት አለኝ::"

"እንዴት?" አለ አሚ ለመጀመሪያ ጊዜ እርጋታው እየጠፋ::

"አሚ" አለ አሃሮን ግንባሩን አሻሸና "ምሥጢሩን በእርግጥ ያውቃል ብለን የምንገምተው አንድ የአፍሪካ ዲፕሎማት አለ:: ለጊዜው ተሰውሮብናል:: ቢሆንም ይህን ዲፕሎማት እያደነ ያለ አንድ ኢትዮጵያዊ



አድራሻውን አግኝቶታል የሚል ጥርጣሬ አለኝ:: ይህን ኢትዮጵያዊ ስከታተል ቆይቼ በመጨረሻው ጭራውን ይዠለሁ::"

"ይህን 'ኢትዮጵያዊ' የምትለውን አፍንክዋል ማለት ነው?"

"አላፈንኩትም:: ከጀርባ እየተከታተልኩኝ ነው:: ወደምፈልገው ዲፕሎማት እንደሚመራኝ እርግጠኛ ነኝ:: ትላንት ማታ ይኸው ሰው ራሱን ቀያይሮ በሃሰት ስም ወደ ድሬዳዋ ከተማ ለመሄድ የባቡር ትኬት ሲያስቆርጥ ልጆቼ አገኙት::"

"እሺ::" አለ አሚ አይኖቹን አጥብቦ ተጨማሪ ለመስማት እየተጠባበቀ::

"ባቡሩ ዛሬ ማታ ይነሳል:: ልጆቼን እንዲከተሉትና የሳይቤርያውን ዲፕሎማት ፈልገው እንዲያፍኑ አዘጋጅቻቸዋለሁ::"

"በቂ ሃይል አለህ?"

"ከበቂ በላይ::" አለ አሃሮን በመተማመን:: "ስምንት ሰዎችን የያዘ ቡድን ከኢትዮጵያዊው ጋር በአንድ ባቡር ለመሄድ ዝግጅቱን ጨርሷል::"

"ከዚህ ሁሉ በኋላ የፈለከውን ዲፕሎማት ሳታገኘው ብትቀርስ?"

"ያንተ እርድ ይቀጥላል" አለ አሃሮን ፈገግ ብሎ::

## -26-

አፓርትመንቷ ጋ ከመድረሱ በፊት ወደ ግራ እጥፍ ብሎ ከአንድ ትንሽ ሻይ ቤት ገባና ከበሩ አጠገብ ካለ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሻይ አዘዘ:: ጥንቃቄ ያስፈልጋል - እርጋታ:: ባሻገር የሚታየው የአፓርትመንቱ ቅጥር ግቢ አለቅጥ ጭር ብሏል:: የወትሮው ግርግር፤ወጪና ገቢ አይታይም:: ከአፓርትመንቱ ስር መኪናዎች በስርአት ተደርድረው ቆመዋል:: ለወትሮው ሲሯሯጡ የሚታዩ ሲጫወቱ የሚገኙ የአፓርትመንቱ ነዋሪዎች ልጆች በግቢው አይታዩም::በር ላይ ብቻ እኛው የድሮው ሽማግሌ ዘበኛ አፈርማ ካፖርታቸውን ደርበው ከዘበኛዋ ቤት ደጃፍ ላይ ቁጭ ብለው ያንጎላጃሉ::

ይህ ነው ብሎ ምክንያት ባይሰጠውም ፍርሃት ገባው:: ፀጥታ ተራ ነገር አይደለም:: እንዲህ ዓይነቱ ሙሉ ፀጥታ አደጋ ከመድረሱ በፊት የሚያንዣብብ ማዘናጊያና አደጋው ከደረሰ በኋላ ድንጋጤን ደርቦ

የሚንጠለጠል ግግርት ነው:: ጥፍሩን መቆረጣጠም ጀመረ:: ጭንቅላቱ ግራና ቀኝ ቆሞ ይሟገት ጀመር::

ሰዓቱን ተመለከተ:: አሥራ ሁለት ከሃያ::

'ገዛም ብዬ ነው'ኮ ... ይልቅ ቶሎ ገብቼ አይቻት ብወጣ ይሻላል...ግንበአካባቢው የአውሬው አይን ቢኖርስ... ስገባ ቢያየኝስ?ወዲያው ቢከቡኝስ ታዲያ እስከመቼ እዚህ ተቀምጬ እቆያለሁ?! ስልክ ደውዬ ወንድሟን «ውጣ» ብለውስ ከአፓርትመንቱ እራቅ እንዲል ነግሬው ባነጋግረውስ ምን ዋጋ አለው? ገብቼ ካላየኋትማ ለምንስ መጣሁ? ብገባ ይሻላል... አዎ አይቻት ቶሎ እወጣለሁ... በአካባቢው ካሉ ግን ያለጥርጥር እንደ ጅግራ ነው ክንፌን ብለው የሚጥሉኝ...ምን ዘዴ መፍጠር ይሻላል?'

- ጭንቅላቱን አፋጨው:: አካባቢው እየጨለመ መጣ:: የመንገድ መብራቶች በግ በግ ቢሉም ደቂቃዎች በሄዱ ቁጥር ይበልጥ የሚደምቀውን ጨለማ መታገል ማሸነፍ መግፈፍ እየቃታቸው መጡ:: ናትናኤል ያለበትን ክፍል ቃኘው:: ትንሺ የሻይ ቤት ንጽህና የሌላት ናት:: በውስጧ የተሰበሰቡትም ሰዎች እሷው እንዳጠለቀው በዘይት የተጨማለቀ የጋራዥ ቱታ ቆሻሻ ልብስ የለበሱ ግዙትተኛ ኑሮ የሚገፉ፤ የሚጎትቱ እንደሆኑ ያስታውቃሉ:: ሰዓቱን ድጋሚ ተመለከተ:: አስራ ሁለት ተኩል:: በተቀመጠበት እንዳለ አሻግሮ የአፓርትመቱን መግቢያ በር ቃኘው:: በሩቅ በድንግዝግዝ አንድ ሰው ይታየዋል:: የበሩን አንድ ወገን መቃን ተደግፎ ቆሟል ሰውየው:: ናትናኤል አትኩሮ ተመለከተው፤ ካፖርት ለብሶ አንገትዬውን ቀልብሶ የቆመውን ሰው ግን ሊለየው አልቻለም::

'ብስራት ይሆን? መሆን አለበት::' አሰበ::

ተነስቶ ወደ አፓርትመንቱ መሄድ ግን ፈራ:: ድጋሚ ዞር አለና እሱ ከተቀመጠበት ስፍራ ፊንጠር ብሎ ሁለት ክንዶቹን ጠረጴዛ ላይ ተክሎ ጉንጮቹን በሁለት መዳፎቹ ደግፎ የተቀመጠ ጎረምሳ ላይ አተኮረ:: አንድ ዘዴ መጣለት:: ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ወጣቱ ተጠጋ::

"ሰላም...ልቀመጥ?" አለ ከወጣቱ ጠረጴዛ ዙሪያ ከተደረደሩት ሦስት ወንበሮች አንዱን ያዝ አድርጎ::

ወጣቱ ጉንጮቹን ከሁለት መዳፎቹ ውስጥ ሳያወጣ አይኖቹን ብቻ አቅንቶ ተመለከተው::

"ተቀመጥ::" አለ ወጣቱ ግድ እንደሌለው ለማሳየት ትከሻውን ከፍ ዝቅ አድርጎ::



"አንድ የምትሰራልኝ ስራ ነበር:: በቂ ገንዘብ እከፍልሃለሁ::" አለ ናትናኤል ከኪሱ ቦርሳውን አውጥቶ ሁለት የአስር ብር ኖቶች እየመዘዘ::

ከፊት ለፊቱ የተቀመጠው ወጣት ቀዩዮቹን ኖቶች ሲመለከት ጉንጮቹን ለቀቅ አደረገና ቀና አለ:: የደረበው ረጅም አሮጌ ኮት አንገትዬው ነትቧል፤ ከውስጥ ሸሚዙ በሽቷል::

"ትስማማለህ?"

"ምንድነው የምሰራልህ? የሚደበደብ ሰው ከሆነ እርሳው::" አለ ወጣቱ አገጩ ላይ ችፍርግ ብሎ የበቀለውን የቆሸሸ ጺም እያከከ::

"አይደለም::" አለ ናትናኤል ወደፊት ጠጋ ብሎ "እየው ያ ፎቅ ይታይሃል? በሩ ላይ የቆመው ሰውዬ ይታይሃል?"

ወጣቱ በአምንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

"...ቀጥ ብለህ ወደ ሰውየው ትሄድና አጠገቡ ልትደርስ ጥቂት እርምጃዎች ሲቀርህ 'ናትናኤል ይፈልግሃል' ተከተለኝ' በለውና ድንገት ፊትህን መልሰህ እየሮጥክ ከግቢው ወጥተህ ትመጣለህ::"

"እናስ... ከዛ በኋላስ?"

"በቃ::"

"እንዴት በቃ? " አለ ወጣቱ ፊቱ ጥርጣሬ ለብሶ:: "እዛች ደርሼ ስለተመለስኩ ነው ይህን የምትሰጠኝ?" ወጣቱ ዓይኖቹን በሁለቱ የአስር ብር ኖቶች ላይ አነጣጠራቸው::

"አዎ::"

"ምንም ሳልሰራ?"

"አዎ::"

"አትቀልድ:: ነገር አለው::" አለ ጎረምሳው ወደ አንድ ወገን እየሳቀ::

"ምንም ነገር የለውም::"

ወጣቱ አይኖቹን አጥብቦ ናትናኤልን ሊያጠናው ሞከረ::

"ለምን እራስህ አትሄድም?"

"ትፈልጋለህ አትፈልግም?" አለ ናትናኤል ሁለቱን የአስር ብር ኖቶች ወደፊት እየገፋ::

ወጣቱ ከራሱ ጋር ክርክር የገጠመ መሰለ:: ናትናኤል ድንገት ትቶት ሲነሳ ፈጠን ብሎ አብሮት ተነሳ::

"እሺ አምጣ፡፡ ፀጥ ብዬ ገብቼ ናትናኤል ይጠራሃል ብዬው ፀጥ ብዬ መውጣት ነው... አይደል?"

"እየሮጥክ ነው የምትወጣው፤ ፀጥ ብለህ አይደለም፡፡ ልክ ከሰውየው እንደምትሸሽ ዓይነት እየሮጥክ፡፡" ናትናኤል ቆፍጠን አለ ሃያ ብር የያዘውን ቀኝ እጁን ወደኋላ ሰብስቦ፡፡

"እሺ አምጣ... እሮጣለሁ፡፡" አለ ወጣቱ እጁን ወደ ብሩ ዘርግቶ፡፡

"ደርሰህ ስትመለስ... መሮጥህን ካየሁ በኋላ፡፡" ናትናኤል ፈርጠም አለ፡፡

"እሺ ግማሹን ስጠኝ፡፡"

"ደርሰህ ስትመለስ ሙሉው ያንተ ነው፡፡"

ወጣቱ ከሻይ ቤቷ ወጥቶ ወደ አፓርትመንቱ ሲያመራ ናትናኤል ተከትሎት ወጣና የመኪና መንገዱን ተሻግሮ ከለላ ይዞ የሚሆነውን ይከታተል ጀመር፡፡

የሚጠባበቁት ሰዎች ካሉ ወደ አፓርትመንቱ ሲገባ ሊይዙት ወጥመድ ያጠመዱ ካሉ ወጥመዳቸው በወጣቱ ላይ እንደሚወነጨፍ እርግጠኛ ነበር፡፡

ወጣቱ የአፓርትመንቱን የአጥር ግቢ በር አልፎ ሲገባ ሽማግሌው ዘበኛ ከእንቅልፋቸው አልነቁም፡፡ ወጣቱ እጆቹን የኮት ኪሶቹ ውስጥ ከትቶ በእርጋታ አፓርትመንቱ በር ላይ ወደቆመው ሰው አመራ፡፡ ሰውዬውጋ ለመድረስ የሦስት እርምጃዎች ሲቀሩት ድንገት ቆም አለና ናትናኤል እንዳዘዘው መልዕክቱን ተንፍሶ ፊቱን መልሶ ሮጥ ከማለቱ ግራና ቀኝ ቆመው የነበሩ መኪናዎች በሮች እየተበረገዱ አራት ሰዎች ዱብ ዱብ አሉ፡፡ ናትናኤል አይኖቹን አፍጥጦ ቀረ፡፡ በሁኔታው የተደናገጠው ወጣት ለማምለጥ ቢሞክርም ከአጥር ግቢው በር ከመድረሱ በፊት ይዘው አፍስፍስ አድርገው ከአንደኛዋ መኪና ውስጥ ከተቱት፡፡

ለደቂቃዎች ናትናኤል ካለበት ሳይንቀሳቀስ ተጠባበቀ፡፡ ወዲያው የመኪናዋ በር ተከፈተና በሁለት በኩል የወጣቱን ክንዶች የጨመደዱ ሁለት ሰዎችና ሌሎች ተጨማሪ ሦስት ሰዎች ወደ አፓርትመንቱ ግቢ በር ይጣደፉ ጀመር፡፡ ከአፓርትመንቱ ግቢ ሲወጡ ናትናኤል ወደ ኋላ አፈገፈገና ጥሩ ከለላ ይዞ በሩቁ በአይኑ ይከተላቸው ጀመር፡፡

አምስቱ ሰዎች ወጣቱን ከበው ወደ ሻይ ቤቷ ተጣደፉ፡፡ ከሻይ ቤቷ ደጃፍ እንደደረሱ ሁለቱ ልጁን አስቀድመው ከተል ብለው ሲገቡ ሁለቱ በሻይ ቤቷ ጓሮ ዞሩ፡፡ የተቀረው አምስተኛው ከፊት ለፊት ጀርባውን ግድግዳው ላይ ለጥፎ ቀኝ እጁን ከኮቱ ስር ብብቱ ስር ከቶ ቆመ፡፡



ናትናኤል ሰውየው ከኮቱ ስር የጨበጠው ምን እንደሆነ ሲረዳ አብርሃም ታወሰው፡፡ ሻይ ቤቷ ውስጥ የገቡት ሰዎች ከውስጥ ሲያጡት ወጥተው አካባቢውን ሊያስሱ እንደሚችሉ ሲረዳ ፈጠን ብሎ ከተደበቀበት ወጣና ሽቅብ በሩጫ ተፈተለከ፡፡ ታክሲ ተራ ደርሶ 'ሰንሃር' ብሎ ታክሲው ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ ሁሉ ሁለት ሦስቴ እየተገላመጠ ተመለከተ፡፡ ከጀርባው የተከተለው ሰው ግን አልነበረም፡፡ ወደኋላ መመለስ አይችልም፡፡ 'ካሁን በኋላ ያለው ምርጫ መጨከን ብቻ ነው፡፡ መቁረጥ፡፡ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለርብቃም አደገኛ ነው... አውቀዋል! ስልኳን ጠልፈውታል ማለት ነው! ለዚህ ነው በሯ ላይ ተዘጋጅተው የጠበቁት፡፡ ቢሄድኮ ኖሮ ባይጠረጥርና እሱ ራሱ ሄዶ ቢሆን ኖሮኮ...'

ናትናኤል ሰውነቱን ሁሉ ዘገነነው፡፡ የአብርሃም ዓይኖች ታወሱት... የየምሥራች እሬሳ ተደቀነበት፡፡ አማተበ፡፡ 'ምንም ምርጫ የለውም፡፡ መቼም ርብቃ ታዝናለች... ግን ሁኔታውን እንዴት ሊያስረዳት ይችላል? «ቤትሽን ከበው ይጠብቁኛል» አይላት ነገር ለእሷም አደገኛ ነው፡፡ ስለነገሩ የምታውቀው የሚያስመስልባት፡፡ ለጊዜው ትቀየመው፡፡ አንድ ቀን ያስረዳታል፡፡ ከስር ከመሰረቱ ይተርክላታል፤ ታምነዋለች፤ እርግጠኛ ነው ታምነዋለች፡፡'

የተሳፈረበት ታክሲ ባቡር ጣቢያ ደርሶ ከታክሲው ሲወርድ ዙሪያው ጨለማ ለብሶ ነበር፡፡ ሳያመነታ ወደ አንድ ቡና ቤት አመራና መታጠቢያ ቤት ጠይቆ ገባ፡፡

ቀልጠፍ ብሎ በዘይትና በአቧራ የተጨማለቀ ቱታውን ከላዩ ላይ አውልቆ፤ እጆቹን ተጣጥቦ፤ ከጨርቅ ቦርሳው ስር የተደፈጠጠ ፀጉሩን አበጣጥሮ ሲጨርስ የገዛ ልብሱን ለበሰና ከሸራ ሻንጣው ውስጥ ትቶ በሸሚዙ ላይ ነጭ ጃለቢያውን አጠለቀ፡፡ መደረቢያውን በአንገቱ አጠለቀና በለፈስፋሳ የጨርቅ ቆቡ ፋንታ ሽርጡን ጠምዝዞ አድርጎ ጭንቅላቱ ላይ ጠመጠመው፡፡ ያደረገውን የቆዳ ጫማ በነጠላ ጫማ ቀየረው፡፡ በሻንጣው ይዞት ሲዞር ከዋለው በእንሰት ቅጠል ከተጠቀለለው ጠውላጋ የጫት ቅጠል አንድ ዘለላ መዝዞ ጥቂት ቅጠሎች ቀነጣጠበና በመዳፉ አድቦልቡሎ ከአፉ ጨመረው፡፡ ያወለቀውን ቱታ እዛው መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ትቶ ሻንጣውን በቀኝ ትከሻው አንጠልጥሎ ዙርባ ጫቱን በግራ ብብቱ ሸጉጦ ከቡና ቤቱ ወጣ፡፡ በኪሱ ያለው መታወቂያ ነጭ ሸሚዝ ለብሶ፤ የእስላም ቆብ ደፍቶ የተነሳው ፎቶግራፉ የተለጠፈበት ነው፡፡ 'ጀማል አብዱልከሪም' ይላል ስሙ፡፡'

ወደ ባቡር ጣቢያው ሲያመራ አድቦልቡሎ አፉ ውስጥ የከተተው ጫት በምራቁ እየራሰ ጣዕም ማፍለቅ ሲጀምር እሬት የጎረሰ መሰለው፡፡ ምራቁን እንትፍ አለና የተጨማደደ ፊቱን ለማፍታታት እየታገለ ጉንጩን ቡጠ. አሳክሎ ሰልፍ ከያዘው ባቡር ተሳፋሪ ኋላ ስፍራውን ያዘ፡፡

ሸኘው፣ ተንገፍ፣ ህፃኑ፣ ሽማግሌው፣ ሴባው፣ ነጋዴው፣ ዘንቢሉ፣ ሻንጣው፣ ትከሻው፣ ዳሌው እርስ በርሱ ይጋፋል። በባቡር ሄዶ ስለማያውቅ ይሆናል ዙሪያውን ተለማምዶ የግድ የለሽነት ገፅታ ለመላበስ ተቸገረ። በገፉት ቁጥር ገድገድ እያለ፣ እግሩ ስር በገቡ ቁጥር እየተደናቀፈ፣ ትኬቱን አሳይቶ ከባቡሩ ገብቶ ቦታውን ያዘ። ከጀርባው ተከትለውት ከገቡት ሰዎች መሃል ዓይኖቹ በአንድ ሴት ላይ አረፉ። ሴትዮዋ አጠገቧ ካለ ጎልማሳ ጋር እየተጫወተች አልፋ ከጀርባው በሁለተኛው ረድፍ ተቀመጠች። ለአንድ አፍታ ዞር ብሎ ተመለከታት። 'ፊቷን ያውቀዋል... ግራ ግንባሯ ላይ ያለውን የሽታ ምልክት ከዚህ በፊት አይቶታል። ማናት? ድንገት ሴትየዋ ዞር ስትል ዓይን ለዓይን ተጋጩ። ደንገጥ ብላ ዓይኖቿን ሰበረች። ናትናኤል ግራ ገባው። 'ማናት? ያውቃታል...ማናት?'

ባቡሩ ጡሩምባውን አምባረቀው። ከአንድ ሰዓት ተኩል ቆይታ በኋላ ባቡሩ ተንቀሳቀሰ። ናትናኤል ከጀርባው የተቀመጠችው ሴት ማንነት ከነከነው።

ባቡሩ ከጣቢያው ተነስቶ የአዲስ አበባን መሃል ሰንጥቆ ውልቅ ሲል ከቤቶች በርና መስኮት የሚወጣ ብርሃን ታየው። በምሽቱ ቀዝቃዛ አየር የሚሯሯጡ ህፃናት...በየመንገዱ ነፋስ የሚቀበሉ ወጣቶች... ቆመው የሚያወጉ አዛውንት...። ባቡሩ ጥሩምባውን አሰማ... ቱ...! ...ቱ! ቱ! መኪናዎች በሰልፍ ቆመውባቡሩን ሲያሳልፉ የጎተራ መንገድ ውልብ አለበት። ችምችም ያሉ ቤቶች... ከባቡሩ ጎንጎን የሚሮጡ ህፃናት እጃቸውን እውለበለቡለት።ፈገግ አለ።የስልክ እንጨት...ሜዳ...ሜዳ...ባዶ ሜዳ...ጨለማ...

ሆዱ ባባበት... ሊያቅለሸልሸው ፈለገ። ለመጀመሪያ ጊዜ አፉ ውስጥ ያለውን የጫት ጭማቂ ዋጥ አደረገና ፊቱን ኮሶ አስመሰለ። አእምሮው አላርፍ ሲለው ድጋሚ ፊቱን ጠምዘዝ አድርጎ ከጀርባ ያለችውን ሴት ተመለከታት። ድጋሚ ዓይን ለዓይን ሲጋጩ አሁንም ቀድማ ዓይኖቿን ሰበረች። 'መስሎኝ ነው ወይስ አውቃታለሁ'-ፊቱን መልሶ ተቀመጠ። ባቡሩ ናዝሬት ከመድረሱ በፊት አዲስ አበባ ላይ ካንዣበበው ጥቁር ደመና ስር አፈትልኮ ሲወጣ አካባቢው በጨረቃዋ ብርሃን ወገግ አለ። ናትናኤል በሩቁ ተራሮቹና ኮረብታዎቹ... ጣት ጣት የሚያካክሉት ዛፎች ውልብ ውልብ እያሉ ወደ መጡበት ሲጣደፉ ድሮ ህፃን ሆኖ አባቱ ያሉት ትዝ አለውና ፈገግ አለ...

አንድ ጊዜ ድሮ በደብረዘይት መንገድ ሲሄዱ ነው። እናቱና አባቱ ከፊት እሱ ደግሞ ከኋላ ተቀምጦ ነበር። ከተቀመጠበት ድንገት ተነስቶ ከፊት ከተቀመጡት እናትና አባቱ ትከሻ መሃል ገባ አለና "አባዬ ዛፉ መሬቱ ሁሉም ወዲያ ሄዱልህ!" አለ ወደ ጀርባው እየመለከተ ሌሎች ያላዩት ጉድ ያገኘ መስሎት አደጋ ከመድረሱ በፊት ለማስጠንቀቅ።



"ሀ! ሀ! ሀ!" ሳቁበት አባቱ የመኪናውን መሪ በግራ እጃቸው እንደያዙ ፊታቸውን መለስ አድርገው በቀኝ እጃቸው ጉንጩን ቆንጠር ቆንጠር እያደረጉ። "አይ ናትናኤል... እኛ ወደ ደብረዘይት ስንሄድ ደብረዘይት ወደኛ መንገድ ጀምሯል አትለኝም? ሀ! ሀ! ሀ!" እናቱም ተደርበው ሳቁበት።

"ያዝ።" የሚል ድምፅ ሰምቶ ከሃሳቡ ነቃ።

ናትናኤል ፊቱን መልሶ ተመለከተ። ከጎኑ ባቡሩ ውስጥ የተሳፈረችው ወጣት ሴት በእፍኗ ዳቦ ቆሎ ዘግና ዘረጋችለት። ቀይ ነች። የእንቁላል ቅርጽ ያለው ፊቷ... ጎላ ጎላ ያሉ አይኖቿ... ጎረድ ያለው አፍንጫዋ... ትናንሽ ከናፍሯ የህፃን ገጽታ ሰጥተዋታል። የአደሬ ያባህል ልብስ ለብሳለች። ሳቅ ስትል ከላይ በስተቀኝ የወርቅ ጥርሷ ብልጭ አለለት።

"ያዝ ...ዳቦ ቆሎ።" አለችው እጇን ወደፊት ሰደድ አድርጋ። ድምጿ ለሴትም ቢሆን ቀጠን ያለ ነው።
"አላህ ይስጥልኝ።" አላት እየተቀበላት።
"የት ነው የምትሄደው?"
"ድሬዳዋ።"
"እኔም እዚያው ነኝ። ከዚያ ነው የምትኖረው?"
"እ...እመላለሳለሁ..ነጋዴ ነኝ።"
"ኮንትሮባንድ?" አለች የተናገረችው ሥራ ህጋዊ የዕለት ተዕለት ተግባር እንደሆነ ሁሉ ተዝናንታ።
"አይ...ሱቅ አለኝ። ለሱቁ ነው።"
"አትለኝም!"
"ወላሂ።"
የወርቅ ጥርሷን ብልጭ አደረገችለት።
"የሐረር ልጅ ነህ?"
"ወሎ።"
"አትለኝም! እናቴ ወሎዬ ነች።" የወርቅ ጥርስ። "የአገሬ ልጅ ነህ ለካ!"

ፈገግ አለ ናትናኤል። ከያዘችው የዳቦ ቆሎ ጭማሪ ዘግና አስታቀፈችው።

"ይጣፍጣል።" አላት አይኑን ጨፍኖ፤ አፉ ውስጥ የነበረውን የጫት ቅጠል እንዳለ ከዋጠ በኋላ በምትኩ ዳቦ ቆሎ እየቃመበት።

"ይኸውልህ ጥሎብኝ ባለሙያ ነኝ።" ተሽኮረመመችለት።
"በቃ እህቴን ታስተምሪልኛለሽ።" ሳቀ።

"የት? አዲስ አበባ ነች ድሬ?"
"ደሴ ናት።?"
"ሚስትህን አይሻልም? ሰርታ እንድታበላህ?"
"አይ ሚስትስ ገና እያፈላለግሁኝ ነው።" አለ ፈገግ ብሎ።
"አሄሄ... !"
"ወላ...ሂ!"

"እንግዳው እንደኛህን ባለሞያዋን አፈላልገህ ብታገባ አይሻልም?" የወርቅ ጥርስ። "ሲቲና እባላለሁ።"

"ናት...አ... ጀማል... ጀማል አብዱልከሪም።"

ፈገግ አለችለት ድጋሚ።

የሌሊቱን አብዛኛውን ክፍል ከሲቲና ጋር ሲጫወት አሳለፈው። ቀልዷ ለዛዋ በተለይ ሴታሴትነቷ አለቅጥ ሳበው።

አሰቦትን እንዳለፉ ሲቲና ደከመኝ ትንሽ ልረፍ ብላ ድሪ ነጠላዋን ፊቷ ላይ ጣል አድርጋ ትከሻው ላይ ደገፍ አለች። የተቀረውን ጉዞ አለፍ አለፍ እያለ ፊቱን እየመለሰ በስሱ ድሪ ነጠላ ውስጥ አልፎ የተከደኑ አይኖቿንና ጥቅጥቅ ያሉ ረገፍረፍም ሽፋሽፍቶቿን እየተመለከተ በዝምታ ጉዞውን ቀጠለ።

ናትናኤል እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገው ነበር ድንገት ከጎኑ ያልጠበቀው ንቅናቄ የተሰማው።

-27-

በሰሃጩ አጨማለቃት።ራቁት ገላውን እራቁት ገላዋ ላይ እንደቁንቡርስ አንደባለለው፤ መላ ፊቷን በሚርገበገብ ከንፈሩና በምላሱ አልኮሰኮሰው፤ እጆቿንና እግሮቿን ከአልጋው ጠርዞች ጋር እንደተጠፈሩ አፍዋ በቡትቶ ታጭቆ እንደተጎሰጎሰ በተንጋለለችበት ጥያፌዋን፤ ምሬቷን ሰውነቷን እያወራጨች አሳየችው።

ግድ አልነበረውም...

በከርዳዳ ጺም የተሸፈነ ፊቱን ከፊቷ ላይ አንስቶ እስረኛው ምርኮኛው በሆነው ከስሩ በተንጋለለት ገላዋ ላይ አንቀዋለለው፤ አይን አዋጅ ሆነበት። ...በደመነፍስ ይዳብሳት ጀመር። 'በል...በል' የሚለውን ግፊት፤



'ሂድ...ሂድ' የሚለውን ስካር 'ሩጥ...ሩጥ' የሚለውን እብደት፤ ጥድፊያ እምቆ መቆየቱ ጣፋጭ የስቃይ ስሜት ፈጠረለት። ከረሜላውን ከአፉ ከትቶ ከረሽሽሞ ጎረዳድሞ ከመዋጡ በፊት፤ የጎረሰውን ከረሜላ እየመላለሰ በመዳፉ ላይ እየተፋ በስስት በስቃይ ስሜት እያየ በስቃዩ በሰቀቀኑ እንደሚደሰት ህፃን የንኀለትን የተንቀዋለለትን ገላዋን ከስሩ አጋድሞ ተስቃየ- ለራቁት ገላዋ ሳሳለት።

ጺማም ፊቱን ወደ ደረቷ አስጠግቶ በጡቶቿ መሃል ወደቀ። ሳይጎረድማት መጠጣት፤ ሳይከረሽማት ላሳት፤ መልሶ ከአፉ አውጥቶ ተመለከታት። አውሬ ሆነች። ጥላቻዋ እየጨመረ... ምሬቷ እየከረረ... እልኂ እየጋመ በመጣ ቁጥር የልቡ ምት እየጨመረና ትንፋሹ እየተፋጀ መላ ሰውነቱ በላብ እሙለጨለጨ... ፊቱን ከጡቶቿ መሃል አውጥቶ ቁልቁል አዘገመ...

ወገቧን ሰብቃ ሰደበችው፤ ሽንጧን እያላጋች ረገመችው፤ ጭኖቿን እየማታች ተፋችው...

ደስታው ወሰን አጣ...

ጎንበስ ብሎ የሚወራጭ አካሏን በሰሃጩ በራሱ ከንፈሮቹ ተረከበው። እንደ እንፋሎት የሚጋረፍ ትንፋሹ ለስላሳ ቆዳዋን ፈጃት ለበለባት። ሀሊናቸውን መሳት የጀመሩ ደዳራ ጣቶቹ የሴት አካልዋን በጭካኔ አፍረጠረጡት።

በሩ ተበረገደ።

በጉልበቶቿ መሃል እንደተንበረከከ በድንጋጤ ፊቱን ወደጀርባው መነጨቀው። የተመለከተውን አልወደደውም። በር ላይ በድን ይመስል የተገተረው ሰው የሚያየውን ትርዒት ለመረዳት ጊዜ ፈጀበት። የሚመለ ከተው እየተገለጸለት ሲሄድ በእልህ ይንቀጠቀጥ ጀመር።

"ጠርጥሬሃለሁ! አንተ ውሻ... ጠርጥሬሃለሁ!" አለ ማርቆስ በሩን ለቅቆ ወደ ክፍሉ ከመግባቱ በፊት ከኮቱ ስር ሽጉጡን ላጥ አድርጎ አቀባብሎ እላይዋ ላይ በተከመረባት ሰው ላይ እየደገነ። "እንዳትንቀሳቀስ... ከዚያ አልጋ ላይ ለመውረድ ሞክርና እንደ ውሻ እገድልሃለሁ!" አለ ማርቆስ ሽጉጡን እንደደገነ ወደ ስልኩ እያመራ። "ትንሽ ተንቀሳቅስና ምክንያት ስጠኝ - ግንድህን አጋድምሃለሁ!" በቀኝ የያዘውን ሬድዮ ወደ አፉ አስጠግቶ ተናገረ። "ሃሎ... ቆንጆዎቹ... ቡድን ለ... አስቸኳይ ነው... ዜሮ አራት..." ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለ። "ቁጥር አንድ ጋር አገናኙኝ።" የሬዲዮ መገናኛውን በግራው እንደጨበጠ በቀኙ የያዘውን ሽጉጥ እላይዋ ላይ በተከመረው ሰው ላይ ደግኖ ተጠባበቀ። "ሃሎ ...ዜሮ አራት... በፍጥነት እፈልግሃለሁ... እዚሁ

ድረስ... ሌላ ሰው አይደለም አንተ ራስህ ተገኝተህ መመልከት አለብህ::" አነጋግሮ ሲያበቃ ስልኩን ዘግቶ ሽጉጡን ወደፊት አስቀድሞ ወደ አልጋው ተጠጋ::

"ጉድህን እናየዋለን!" አለ ማርቆስ ጺማሙን ሰውዬ በጥላቻ እየተመለከተ::

"ይቅርታ አድርግልኝ ማርቆስ:: ሌላው ይቅር ልብሴን ልልበስ::" አለ ሰውየው በጭኖቿ መሃል እራቁቱን እንደተንበረከከ በልምምጥ ፊት ማርቆስን እየተመለከተው::

"ከማነው ሃጢያታችንን የምንሸሽገው? ለዓመታት አንዳችን የአንዳችንን ሃጢያት እንዳናይ... የገዛ ሃጢያታችን እንዳይታይ ፊታችንን ስንመላለስ ቆይተናል:: ከአሁን ወዲያ ግን ገበናችን መገለጥ አለበት:: ከኃጢያታችን እራቁታችንን መተያየት አለብን:: እውነት ተሸፋፍና ተጀቧቡና አትኖርም:: እራቁቷን ነው የምታምር::" በዕልህ ተንቀጠቀጠ:: "እራቁቷን!"

"ማርቆስ ልብህ ይራራ... ሁላችን እንሳሳታለን... ማረኝ:"

"ማነው ለዱር እውሬ... ለተናካሽ እውሬ የሚራራ? ቀሚሷን ገልበው እርቃኗን እንጋለው ለሚያረክሷት፣ ጭኖቿን በርግደው ሴትነቷን አጋልጠው ለባዕድ ለሚሸጧት፣ አፍሪካ ርህራሄ አይኖራትም:: ምህረት ምንድነው? በየዋህነቷ ለቸረቸራችሁ፣ በልበገርነቷ ለሸረሞጣችሁ፣ በድንግልናዋ ላቃጠራችሁ ምህረት ምንድነው? አፍሪካ መቼ ነው ቀሚሷን ዝቅ የምታደርግ፣ ጭኖቿን የምትሰበስብ፣ እፍረቷን የምትሸፍን? እናንተ ስትጠረጉ ብቻ ነው! ምህረት አያሻም! ራቁታችንን መተያየት አለብን!"

የክፍሉ በር ከጀርባው ሲበረገድ ከላይዋ ላይ እራቁቱን የተንበረከከው ጺማም ሰው ዓይኖቹን ጨፈነ::





የቢሮውን በር በርግዶ ሲገባ ብርጋድየር ጄኔራሉ ከጠረጴዛው ጀርባ እንደተቀመጠ አፍጥጦ ተመለከተው::

"ያገኘነው!" አለ ማርቆስ ትንፍስ ትንፍስ እያለ::

"ናትናኤልን?" አለ ጄኔራሉ የሰማውን ለማረጋገጥ::

"አዎ::" አለ ማርቆስ ጭንቅላቱን ነቅንቆ ፀጉሩን እየደባበሰ:: "ቢታምኑኝም ባታምኑኝም እራሴን እስከምጠላ ተስፋ ቆርጬ ነበር::"

"እንዴት ያገኘከው? ማለቴ የት?" አለ ጄኔራሉ ማርቆስን ተቀመጥ ሳይለው በቆመበት እንዳፈጠጠበት::

"ባቡር ላይ::" አለ ማርቆስ ወደፊት ተራምዶ ወንበር ላይ እየተቀመጠ:: "ዛሬ ማታ ወደ ድሬዳዋ ለመሄድ ባቡር ላይ ሲሳፈር እዛው የመደቡኳቸው ሁለት ሠራተኞቼ አይተውት አብረውት ተሳፍረዋል::"

"ወደ ድሬዳዋ ተሳፍሯል-ነው የምትለኝ? ያገኙት ያልከኝ መስሎኝ ነበርኮ::" አለ ጄኔራሉ ፊቱን አኮሳትሮ "መከታተሉ ምንድነው ትርጉሙ ለምን ቀጥታ አላስወገድከውም?"

"አታስብ... ከአዲስ አበባ እስከ ድሬዳዋ ያሉትን ጣቢያዎች በሙሉ በሰዎቻችን ሸፍኛቸዋለሁ::"

"ባቡሩ ሳይነሳ ለምን አልያዝከውም?"

"ጄኔራል ሰውየው ትኬት ሲቆርጥ ሰዎቻችን አላዩትም:: ምናልባት በሌላ ሰው አስቆርጦም ሊሆን ይችላል:: ድንገት ባቡር ላይ ሲሳፈር ያዩ ሠራተኞቼ ምርጫ ስላልነበራቸው ስልክ ደውለው ሲያስታውቁኝ ባቡር ጣቢያ ውስጥ አስጠጋጅ ሃይል ስላልነበረ ተከትለውት እንዲሳፈሩ አዘዝኳቸው::"

"ታዲያ ምንን ነው ያዘኩት የምትለኝ?"

"ከዚህ ወዲያ ሊያመልጥ አይችልም:: በየትኛውም ጣቢያ ቢወርድ ከማንም ጋር ከመገናኘቱ በፊት እንዲያስወግዱት ትዕዛዝ አስተላልፌአለሁ::" አለ ማርቆስ በፍጹም እርጋታ:: "በየጣቢያው የሚጠባበቁት ሰዎች አሉ::"

"አንተ ራስህ ለምን ድሬዳዋ በረህ አትጠብቀውም? የምልህ ይህ ሰው አደገኛ ነው:: ጄኔራሉ ተረበሸ... "አንተ ራስህ ቀድመህ ብትጠብቀው እመርጣለሁ::"

"አንድ ሄሊኮፕተር አዘጋጅቼ እየተጠባበቅሁ ነው... ቀጥታ ወደ ድሬዳዋ እንዳልበር ምናልባት በመሃል ሊወርድ ስለሚችል ባቡሩ እያንዳንዱን ጣቢያ ሲያልፍ ከየጣቢያው ያሉ ሰዎች የሬድዮ መልዕክት እያስተላለፉልኝ እየጠበቅሁ ነው::"

"የት ነው ያለው አሁን?" አለ ጀኔራሉ በጉጉት::
"ባቡሩ ናዝሬትን ማለፉን እንዳረጋገጥኩ ነው ወደአንተ የመጣሁት::" አለ ማርቆስ::

"ማርቆስ!" አለ ጀኔራሉ ፊቱ በጭንቀት ተወርሮ:: "ይህ አካሄድህ አላማረኝም... እንበልና ይህ ሰው በሁለት ጣቢያዎች መሃል ከባቡሩ ቢዘል ምን ልታደርግ ነው? ከቦታው ላይ ምን ያህል ዘግይተህ እንደምትደርስ አታውቅም?"

"አብረውት የተሳፈሩት ሰዎች የነፍስ ወከፍ መሳሪያ የታጠቁ ናቸው::"

"የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ይታጠቁ እንጂ ለዚህ ሥራ የሰለጠኑና የተዘጋጁ አይመስሉኝም... ተራ የክትትል አባላት ናቸው... አይደለም?" አለ ጀኔራሉ ጠረጴዛውን በቡጢ ደልቆ::

"እርግጥ የክትትል ሠራተኞች ናቸው ግን..."

"ማርቆስ! ማርቆስ! ምን እየሰራህ ነው?" አለ ጀኔራሉ ተነስቶ እየቆመ "ጊዜ አታጥፋ:: አሁን ቀጥታ ሰዎችህን ይዘህ ያንን ባቡር በሄሊኮፕተር እንድትከተለው እፈልጋለሁ::" አለ የቀኝ እጁን አመልካች ጣት ባቡሩ የሄደበትን አቅጣጫ እንደተረዳ ሁሉ አየር ላይ ቀስሮ:: "ወይ ብቁ የሆነ ቡድን እራስህ አዘጋጅተህ ላክ::"

"ጀኔራል..." አለ ማርቆስ ፈጠን ብሎ ተነስቶ የአለቃውን ጭንቀት ለማርገብ እየሞከረ:: "ረጋ በል:: እንደምይዘው ቅንጣት ጥርጣሬ ሊገባህ አይገባም:: ለማንኛውም አሁኑኑ ከዚህ አንድ ቡድን እልካለሁ::"

"ጥሩ ጥሩ... ሂድ" አለ ጀኔራሉ ሰዓቱን እየተመለከተ "በስንት ነው የተነሳው?"

"ከምሽቱ በአንድ ከሃያ ነው የተነሳው ... አሁን አምስት ከሩብ ነው::"



"ማርቆስ... እባክህ ተጠንቀቅ:: ይሄ ሰው ፍጹም አደገኛ እየሆነ ነው የመጣው... ምናልባት ከምሥራች የካልቨርትን አድራሻ ደርሶበት ከሆነ ወደ ድሬዳዋ የተሳፈረው:: ትንሽ ስህተት ምን እንደምታስከትል ታውቃለህ::"

"እሬሳውን ወደዚህ ማምጣት ያስፈልጋል?"

"የፈጣሪ ያለህ! እሬሳውን ብትፈልግ አንገትህ ላይ አስረኸው ዞር:: ግደለው! ከባቡሩ እንደወረደ ግደለው:: ግደለው በቃ!"

የቢሮው በር ሲዘጋ ጀኔራሉ በባዶው ክፍል ውስጥ እንደቆመ በረጅሙ ተንፈሰና ከክፍሉ የወጣው ኮሎኔል ያዳምጠው ይመስል «ማርቆስ - ማርቆስ ቶሎ በል!» አለ በጭንቀት::

-29-

የረር ጎታ ሲቃረቡ ነበር ሲቲና ከእንቅልፏ የተነሳችው::

"ለምን አትተኛም ነበር? ቀንክ ይደክምሃል» አለችው:: እንቅልፍ ያሳበጣቸውን ጉንጮቿን እያሻሸች::

"ተመችቶሽ ተኛሽ?" አላት ፈገግ ብሎ::
"አመሰግናለሁ:: የሚመች ትከሻ አለህ::" አለች እየሳቀች:: ጎንበስ ብላ ከሻንጣዋ ውስጥ ሎሚ አወጣችና አንድ ለእሱ አንድ ለራሷ ወሰደች:: "ሎሚ ያነቃቃል፤ ታውቃለህ?" አለች የያዘችውን ሎሚ እየመጠጠች::

ድሬዳዋ ለካሬ ደርሰው ከባቡሩ ሲወርዱ ናትናኤል ተደነጋገረው:: የባቡር ጣቢያው በሰው ተጨናንቋል:: አንድ እርምጃ ለመራመድ ሁለት ሦስት ሰዎች መገፍተር አለባቸው:: ሰው ከየት ወደየት እንደሚሄድ መለየት ያስቸግራል:: ብቻ ባለበት ይተራመሳል፤ ይገፋፋል፤ ይተሻሸል:: ከጎኑ ተቀምጣ የነበረችው ሴት አብሯት ከተቀመጠው ተሳፋሪ ጋር እያወራች ስትወርድ ዞሮ ተመለከታት:: አብሯት ካለው ሰው ጋር ታውራ እንጂ አይኖቿ ከእርሱ ጋር ነበሩ:: እርግጠኛ ነው... ከዚህ ቀደም አይቷታል::

"የት ነው የምታርፈው?" አለችው ሲቲና ቀድማ ከባቡሩ እየወረደች::
"እ... አልወሰንኩም::" አላት ከጎርባው ተቀምጣ የነበረችውን ሴት ማንነት ለማስታወስ እየጣረ:: እርግጠኛ ነው... መልኳን ያውቀዋል ግን ራቀበት::

"ማለቴ ዘመድጋ ነው... ወይስ ሆቴል?" አለችው ሲቲና::ድንገት ብልጭ ሲልለት ድጋሚ ፊቱን ወደ ሴትየዋ አዙሮ ተመለከታት:: የአብርሃም ሠራተኛ! ዞሮ ተመለከታት:: ሳያውቀው ዓይን ለዓይን ተጋጩ:: ቀድማው ፊቷን መለሰች:: ሴትየዋ ቀድሞ ካላየቻው ሁለት ሰዎች ጋር ስታወራ ተመለከተ::

"እ...ምን አልሽኝ? አይ... ሆቴል ነው የማርፈው ለጊዜው::" አለ ፊቱን ወደ ሲቲና መልሶ::

"ከፈለግህ እኔጋ ማረፍ ትችላለህ::ባዶ ቤት ነው ያለሁት::"
"እ... " አለ አሁንም ፊቱን መልሶ የአብርሃምን ሠራተኛ ባየበት አቅጣጫ ተመለከተ:: ዓይኑን የምትሸሽ መሰለው:: አብረዋት የነበሩት ሦስት ሰዎች በአጠገቧ የሉም:: ሴትየዋ ብቻዋን ጥግ ይዛ ቆማለች::

«ማለቴ... ለሁለት ለሦስት ቀን ችግር የለም ማለቴ ነው::» ከጎን ከጎኑ እየሄደች አንገቷን አቀርቅራ ተናገረችው ሲቲና::

ከሰው ግፊያ ወጣ ብለው ወደዳር ላይ የያዟቸውን ሻንጣዎች ከመሬት ላይ አሳርፎ ቀና ሲል ባሻገር ተመለከታት:: ሴትየዋ አሁንም ታየዋለች:: 'ምናልባት የት እንደምታውቀኝ ጠፍቷት ይሆናል::' ብሎ አሰበ::

"እስቸግርሽ እንደሆነ..." አለ ፊቱን ወደ ሲቲና መልሶ::
"በፍጹም::" አለች ፊቷ በሃፍረት እየቀላ::

"እ... " ናትናኤል አመነታ:: ሆቴል አለመያዙ ከዓይን የሚያድነው ብቻ ሳይሆን ገንዘብም የሚቆጥብለት ነው:: ግን ይቺን ልጅ ተከትሎ ከቤቷ ሄዶ ምን እንደሚከተል ለማወቅ አስቸጋሪ ይሆናል:: መቼም ምሳና እራት ሊያበላት ወይ ለነፍሷ ብላ እንዳላስጠጋችው ግልጽ ነው:: ግን ቢሆንስ እንዴት ድንገት ልታቀርበው ፈለገች? "ምን መሰለሽ..." አለ ግብዣዋን እምቢ የሚልበት ዘዴ ጠፍቶት አቧራ ያበላሸውን ነጭ ጀለቢያውን እያራገፈ::

"አስቸግራታለሁ ብለህ አስበህ ከሆነ ምንም ችግር የለም:: ባዶ ቤት ነው ከፍቼ የምገባው:: ወላሂ አልኩህ::"

"እስቲ እየሄድን እናውራ::" አለ ናትናኤል የሰው ትፍግፍግ ማለትና የአየሩ ሙቀት ትንፋሽ ቢያሳጥረው::

ጎንበስ ብሎ ሻንጣውን ሲያነሳ ከጎኑ ቆማ የነበረችው ሲቲና ገፍትራ ከመሬት ደባለቀችው:: መሬት ላይ ሁለቱ ተንከባሎ ቀና ሲል ነበር ነገሩ



ጭንቅላቱን የመታው - ከጀርባው ቆመው የነበሩ አንድ አዛውንት በደም የተጨማለቀ ሆዳቸውን ይዘው ወደ መሬት ሲያዘቅጡ አይኖቹን አፍጥጦ ተመለከታቸው:: 'እሪ!' አለች ከጎናቸው የነበረች ወጣት ሴት:: ከወደቀበት ለመነሳት ሲጣደፍ ሲቲና ሽብረክ ብላ ከተከናነበችው ድሪያ ስር ሽጉጥ መዠረጥ ስታደርግ አየ:: ተቀደመች:: የያዘችው ሽጉጥ ከእጇ ውስጥ ተፈናጥሮ ሲወረወር እሷ ደረቷን አፍና ወደ ኋላዋ ወደቀች... ዙሪያውን ረብሻ ሆነ... ጩኸት... ሩጫ... እሪታ... ተኩስ እሪታ ዙሪያውን አደባለቀው... ናትናኤል ከአንገቱ ቀና አደረገት...

«ሩ...ጥ! ተከትለውሃል... ሩጥ!» አለችው በግራ እጇ በደም የተዘፈቀውን ደረቷን አፍና እንደያዘች ሲር ሲር ከሚለው ትንፋሿ እየቆጠበች «ሩጥ!»

ቀና ሲል አየው:: የጨበጠውን ሽጉጥ ከትከሻው በላይ ይዞ ከራቱ የሚጋረጡትን ሰዎች አንዱ ወዲህ አንዱ ወዲያ እየገፋ እየገፈታተረ ወደእሱ እየቀረበ ሲመጣ በሚተራመሰው ሕዝብ መሃል በሩቁ አየው ከአብርሃም ሠራተኛ ጋር የነበረውን አንድ ሰውዬ! እንደ ጥንቸል ተፈናጥሮ ከሚደነባበረው ከሚራበሸው ሕዝብ መሃል እየተሹለከለከ በትርምሱ ውስጥ ሰመጠ... 'የአብርሃም ሠራተኛ! የፈጣሪ ያለህ! የአብርሃም ሠራተኛ!' ከራሱ ጋር እየነበነበ ሮጠ:: ከጀርባው የተኩስ እሩምታ አጀበው::

ወዴት እንደሚሮጥ... የት እንደሚደርስ ግድ አልነበረውም:: ብቻ ሮጠ:: እራቅ እንዳለ በሩቁ እንዳይለዩት ጭንቅላቱ ላይ የጠመጠመውን ሽርጡን አውልቆ በእጁ ያዘው:: ትንሽ ከራቀ በኋላ ደግሞ ወደ ጥግ ዞር አለና ጀለቢያውን አውልቆ ወርውሮ ከወገቡ በታች ሽርጡን አጥልቆ ከላይ ነጭ ሸሚዙን እንዳደረገ ከራሱ ጋር እያንተመተመ ሮጠ:: 'የአብርሃም ሠራተኛ! እንዴት ሊከተሉት ቻሉ? ወደ ድሬዳዋ መምጣቱንስ እንዴት አወቁ? ሲቲና ባትገፈትረውኮ ... ወደፊቱ ሲወድቅ ባይስቱትኮ...' በደም የተጨማለቀ ሆዳቸውን ይዘው ያዘቀጡት ሽማግሌ ታዩት:: 'የፈጣሪ ያለህ! ገለውት ነበርኮ የአብርሃም ሠራተኛ! ወይኔ አብርሃም! ለካ ሳያውቀው!'

ሲቲናስ ማነች? 'ሩጥ...ተከትለውሃል...ሩጥ' የምስራችን የገደለቻት ሴት ምንድን ነበር ያለችው? 'ሩጥ!' ሲቲና ማነች? የፈጣሪ ያለህ! ሁሉ ነገር ተወሳሰበበት:: ማሰቡን አቁሞ ሩጫውን ቀጠለ::

-30-

ያለበት ቤት የት እንደሆነ ለመረዳት አልቻለም:: በስተግራው መደዳውን የተሰሩ ቤቶች ማስታወቂያዎቻቸውን በየበሮዎቻቸው ላይ እንዳንጠለጠሉ ተደርድረዋል:: ፎቶግራፍ ቤት...የልብስ ስፌ...ሰዓት ማደሻ...በስተቀኝ ደግሞ በረንዳው ላይ የሳጠራ ወንበሮች የተደረደሩበት በሀረግ የተሸፈነ በረንዳ ያለው ቡና ቤት ይታያል -ድሬዳዋ::

ወደ ቡና ቤቱ ተጠጋና አካባቢውን ለማጥናት ሞከረ:: የፊተኛው ክፍል ሰፊ ቢሆንም ጨለምለም ያለ ነው:: ፊጠን አለና ወደ ውስጥ ገባ:: በትናንሽ ጠረጴዛዎች ዙሪያ የተኮለኮሉ ትናንሽ የብረት ወንበሮች ፊንጠር ፊንጠር ብለው ከብ ከብ ሰርተዋል:: ቢጋዝ የተወለወለው የሲሚንቶ ወለል ቢያብለጨልጭም ሽታው ይከብዳል:: ቁርስ የሚያደርጉ የቡና ቤቱ ደንበኞች በየወንበሮቻቸው ተቀምጠው ያዘዙትን ይስተናገዳሉ::

ባዶ ጠረጴዛ ፈለገና ወንበር ስቦ ተቀመጠ::

"ምን ልታዘዝ?" በስተቀኝ የተንዘላዘለ ፀጉሯን ማጅ ላይ እየጠመጠመች እየፈጠች ጠየቀችው::

"ሻይ::" አላት ቶሎ ለመገላገል:: ፊቷን መልሳ ሄደች:: ናትናኤል ከራሱ ጋር ምክክር ቀጠለ::

"ጊዜ የለውም:: መፍጠን አለበት:: አለበለዚያ ያገኙታል በማያውቀው ከተማ ውስጥ ተደብቆ መቆየት ዘበት ነው:: ግን እንዴት ተከተሉት? ከርብቃ ቤት አምልጦ ሲሮጥ ተከትለውት ነበር ማለት ነው? መሆን አለበት:: የአብርሃምስ የቤት ሠራተኛ እዚህ ምን አመጣት? ወይኔ! አብርሃምን ትከታተለው ነበር ማለት ነው! አሁን ደግሞ...

የቡና ቤቱ አስተናጋጅ ያዘዘውን ሻይ አምጥታ ፊቱ አስቀመጠችለት::

"እባክሽ የእኔ እመቤት የስልክ ቁጥር ማውጫ ደብተር ይኖራችኋል?" አላት::

"ይቅርታ የለንም:: ለምን ማዘረያ አይጠይቁም?"

ጥሩ ሃሳብ!

"ስልክ አገኝ ይሆን?" አላት ሽቅብ እየተመለከታት::

በአገጯ ስልኩ ያለበትን አመለከተችው:: ከዋናው በር ጀርባ ግድግዳው ላይ ወደተንጠለጠለው የሕዝብ ስልክ አመራ::



"ሃሎ...የኔ እህት ባክሽ...አቶ ይልማ ገዛኸኝ...ይልማ...አዎ" ማዘረያ ደውሎ ጠየቀ::

"አንድ ጊዜ..." አለችው በስልኩ መስመር ላይ ያለችው የቴሌኮሙኒኬሽን ሠራተኛ::

የስልክ ቁጥሩን ነገረችው:: ቀልጠፍ ብሎ ወረቀትና እስክሪብቶ ፍለጋ ደረቱን ዳበሰ...በርሳው! ሽንጣው! በድንጋጤ ደርቆ ቀረ... ሰቃውን ሁሉ ከሽንጣው ጋር ከዛቡር ማቢያው ትቶ መሮጡ ሲታወቀው መብረቅ እንደመታው ዛፍ አፈር መሰለ::

"አቤት? ስንት አልሽኝ?" ድንጋጤውን አፍኖ ያዘ ድጋሚ ጠየቃት::

ቁጥሩን ደገመችለት:: የነገረችውን ቁጥር በቃሉ ይዞ ወደ ጠረጴዛው ተመለሰ:: ፊቱ አመድ የነሰነሰበት ይመስል ነጣ:: ሽንጣው ውስጥ ያስቀመጠው ገንዘብ ሁሉ ጠፍቶ መቅረቱ ሰቀቀን ለቀቀበት:: ቶሎ እስና ከሸሚዙ የደረት ኪስ ገብቶ ከዚያ ያገኛቸውን ጥቂት ዝርዝር ብሮች ቆጠራቸው:: አስራ ሶስት የአንድ ብር ኖቶች:: ድጋሚ ከሱሪ ኪሱ ገብቶ ጥቂት ሳንቲም... ጭልምልም አለበት:: ከስምንት መቶ ብር በላይ የሚሆን በፖስታ ከረጢት ውስጥ አድርጎ ከሽንጣው ስር ማስቀመጡን ሲያስታውስ... ሽንጣው ውስጥ አጣጥፎ ከከተተው ኮቱ ውስጥ ስልሳ ብር ማስቀመጡ ሲታሰበው... ያንን ሁሉ በግርግሩ ውስጥ ከዛቡር ማቢያው ትቶ አስራ ሦስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም ይዞ መብረሩን ሲያስብ ልቡን አመመው::

አስራ ሦስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም!አለቀ::

ድንገት ተነሳና ወደ ስልኩ ሄደ:: የስልኩን እጀታ አንስቶ ካለችው ገንዘብ ላይ ሃያ ሳንቲም ቀንሶ የሕዝብ ስልኩ ውስጥ ጨመረና በቃሉ የያዘውን የአቶ ይልማ ገዛኸኝን ስልክ ቁጥር ደወለ:: ካልሾርትን ማግኘት አለበት! በአስራ ሦስት ብር ከሁለት ቀናት በላይ መቆየት አይችልም:: ለዛውም ካልያዙት ነው:: በማያውቀው ከተማ ሲንቀዋለል ከነፍሱን ይዘው እየገፈተሩ ቱቦ ስር ጥለው ጭንቅላቱን ካልነደሉለት ነው:: አሥራ ሦስት ብር! የፈጣሪ ያለህ! በግንባሩ ላይ ምንጭ እንደፈለቀ ሁሉ የሚንቆረቆር ላቡን በክንዱ ላይ ሞገርት አደፈና የስልኩን መነጋገሪያ ጆሮ ግንዱ ላይ ለጥፎ ተጠባበቀ::

"ይልማ ጋራዥ::" አለው የሴት ድምፅ::

"ሃሎ...እባኮት አቶ ይልማን ነበር::" ፈጣሪውን ይማፀን ገባ::

"ማን ልበል?"

"አቶ ይልማ...ይልማ ገዛኸኝ::"

"ከየት ነው?" አለች ሴትየዋ በመገረም ቃና::

"ከዚህ ነው - ከድሬዳዋ ... እባክት እንዴ ቢያገናኙኝ::" ልቡ ተንጠለጠለ::

"ይቅርታ ተሳስተዋል::" አለች ሴትየዋ ለመናገር ያልፈለገችው ነገር እንዳለ ሁሉ እያቅማማች::

"ቆይ! ቆይ!" አለ ስልኩን እንዳትዘጋበት ተሸቀዳድሞ:: የስልክ ቁጥሩን በእርጋታ እየጠራ ትክክል መሆኑን ጠየቃት::

"ቁጥሩ ትክክል ነው:: ግን..." አቅማማችበት::
"አቶ ይልማ የሉም?" ጭንቀቱ በጭንቀት ተወጠረ::
"እንደዛ የሚባል ሰው የለም::" ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችበት::

ሊሆን አይችልም! ነገሩ ሁሉ ተደበላለቀበት:: የስልኩን መነጋገሪያ ከቦታው መልሶ ወደ ወንበሩ ተመለሰ:: አለቀ:: ካልቨርትን ለማግኘት የነበረው ተስፋ ከእጅ ያመለጠ እንቁላል ሆነበት:: 'ህ!...' አስራ ሶስት ብር ይዞ ሸሽት ታየው:: አስራ ሶስት ብር ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ እንኳን በቂ አይደለም:: 'ምንም ምርጫ የለውም! መስረቅ ካለበት ይሰርቃል! ማጅራት መምታት_ ካለበት ይመታል!ግን አዲስ አበባ አይመለስም! ካልቨርትያለው እዚህ ነው:: የምሥራች ነግራዋለች:: ካልቨርት ድሬዳዋ ነው! ካልቨርት አፍንጫው ስር ነው!' ጠረጴዛውን በቡጢ ደወለው::

በቡና ቤቱ አዳራሽ የተቀመጡ ሰዎች ጠረጴዛውን ሲጠልዘው ሲሰሙ ቀና ቀና እያሉ እየተገላመጡ ያዩት ጀመር::በገዛ ድርጊቱ ተደናገጠ:: ጥንቃቄ!... መረጋጋት! መረጋጋት! ሻዩን አንስቶ ፉት አለው:: ቀዝቅዟል:: አልተወውም:: በእርጋታ ደጋግሞ ፉት እያለ ጨረሰው:: ቢደግም አይጠላም ነበር:: ኪሱ ውስጥ ያለውን ገንዘብ ሲያስታውሰው ተወው::

በተቀመጠበት ዓይኖቹን በዘዝ አድርጎ አእምሮውን ለማሰራት ሞከረ '...ካልቨርት የት ነው?- «እማዬጋ...ድሬዳዋ»...እማዬ...የአቶ ይልማ ገዛኸኝ ባለቤት... አቶ ይልማ ገዛኸኝ ... ይልማ ... ይልማ... ምንድን ነበር ያለችው ስልኩን ያነሳችው ሴት ... ይልማ... ምን? ...ይልማ ጋራዥ... ጋራዥ...'

የቡና ቤቱን አስተናጋጅ ጠቀሳት:: መጣች::

"እባክሽ የኔ ቆንጆ 'ይልማ ጋራዥ' የሚባል ታውቂያለሽ ድሬዳዋ ውስጥ?" የአንድ ጋራዥ ስም ጠርቶ ውለዱ ሲል እራሱን አስገረመው::

"ይልማ...ይልማ...እንትንጋ ነው... ማነው? ...ብቻ ...ከአሸዋ ሜዳ ከድልድዩ ሳይደርሱ ወዲህ ከባንኩ ትንሽ አለፍ እንዳሉ..." የማያውቀውን ከተማ ትተርክለት ጀመር::



"እይው..." አለ ድምፁን አለዝቦ አቋርጧት:: "ለድሬዳዋ አዲስ ስለሆንኩ ነው::"

"የሚያሳይዎት ልጅ ልጥራሎት? ቅርብ ነው::" አለች::
"ጥሩ... ጥሩ::" ጭንቀቱን እየወዘወዘ መስማማቱን ገለፀላት::

ጋራዡን ከሚያሳየው ልጅ ጋር ካገናኘችው በኋላ በደረቅ ምሥጋና ተሰናብቷት ከልጁ ጋር ተፈተለከ:: ጉርሻ ቢሰጥት ደስ ባለው ነበር... ግን...::

"ይልማ ጋራዥ ነው አይደል? ነ" ይለዋል ከፊት ለፊቱ ቱስ ቱስ የሚለው ህፃን ልጅ:: ዕድሜው ከአስር አመት አይበልጥም:: ያደረጋት የላስቲክ ነጠላ ጫማ ተበጣጥሳለች:: በተራመደ ቁጥር ወደ ኋላ ልትቀር ታስባለች:: ልጁ ግን ትቷት ሊሄድ ፈቃደኛ አይመስልም:: በእግሮቹ ጣቶች ቆንጠጥ አድርጎ ይዞ ወደፊት ይጎትታታል:: ትንሽ ይሄድና "...ይልማ ጋራዥ ነው አይደል? ነ" ይለዋል::

ናትናኤል ላቡ በጀርባው እየተንቆረቆረ ከልጁ ኋላኋላ ይጣደፋል::

"ያው! ይሄ ነው ይልማ ጋራዥ:: ሜካኒኮቹን ልጥራሎት?" አለ ልጁ ተስፋ ቆደረገውን ጉርሻ በሆዱ ይዞ መስተንግዶውን እያጧጧፈ::

"አይ ተወው::" አለ ናትናኤል ከኪሱ አስር ሳንቲም አውጥቶ ለልጁ እየዘረጋለት::

"አቦ ይጨምሩ! ከለገሃሬ ድረስ አምጥተውኝ" አለ ልጁ አስር ሳንቲሟን ሲያይ ፊቱ በቅያሜ ተንጠልጥሎ::

"ሌላ ጊዜ እሰጥሃለሁ::" አለ ናትናኤል አስር ሳንቲሟን ገፋ አድርጎ::
"አስር አልወስድም!" አለ ልጁ በብስጭት::

ናትናኤል አልተግደረደረም::ሳንቲሟን ኪሱ ከቶ ወደ ጋራዡ በር ተጣደፈ::ልጁ ከጀርባው እናቱን ተሳድቦ ሲሮጥ ሰማው:: ግድ አልነበረ ውም:: የጋራዡ ግቢ ሰፋት ያለው ቢሆንም ከውስጥ የተሰገሰጉት በርካታ መኪናዎች ጠባብ አስመስለውታል:: ደማቅ ሰማያዊ ቱታ የለበሱ የጋራዡ ሠራተኞች ኮፈናቸው በተበረገደ መኪናዎች ዙሪያ ተፍ ተፍ ይላሉ::

"የት ነው?" አሉት ከበሩ ጥግ በተደራረቡ ድንጋዮች ላይ የተቀመ ጡት ሽበት የሸፈናቸው ዘበኛ ከተቀመጡበት ወገባቸውን ይዘው እየተነሱ:: የከንፈሮቻቸውን ጥግና ጥግ በጎረሱት ጫት አረንጓዴ ሆኗል::

"እንደምን ዋሉ...አቶ ይልማን ነበር::" አሳቸው ጠጋ ብሎ::

ሰውየው ግራ በመጋባት መልክ ትክ ብለው ተመለከቱት:: መልስ አልሰጡትም ብቻ እብድ እንደሆነ ሁሉ አፍጥጠው አዩት::

"እ...» ቀጠለ:: "ልጃቸው ከአዲስ አበባ ልካኝ ነው:: ይኖሩ ይሆን?"

"አቶ አደፍርስ ማለትህ ነው?" አሉ ሽማግሌው የፀሃይዋን ጨረር በመዳፋቸው ከልለው::

"አዎ... አቶ ይልማን ነው::"
ሰውየው ጤነኛ እንዳልሆነ ሁሉ ትክ ብለው እያዩት ጭንቅላታቸውን ነቀነቁበት::

"የአቶ ይልማ ጋራዥ አይደል እንዴ ይሄ?" አለ ናትናኤል ተስፋው እየተሟጠጠ::

"ክፉው ሞት ሳይወስዳቸው በፊት- አዎ::" አሉት ሰውየው ተመል ሰው በተደራረቡት ድንጋዮችላይ እየተቀመጡ::

"ምን አሉኝ?" አለ ደንገጥ ብሎ::
"የኔ ወንድም...አቶ ይልማ ከሞቱ መጪው ህዳር ሁለተኛ ዓመታ ቸው ነው::" አሉት ሽማግሌው ከጎናቸው በኮኮላ ጠርሙስ ካስቀመጡት ውሃ እየተጎነጩ::

ናትናኤል ለጥቂት ደቂቃዎች ፈዞ ቆየ:: -

"እባኮት ባለቤታቸው የሚኖሩበትን ያውቁ ይሆን?"

ሽማግሌው ችላ ብለውት በዝምታ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁበት:: ወሬው የጣማቸው አይመስልም::

"እባኮት ስለባለቤታቸው የሚያውቅ ሰው ካለ ላስቸግርዎት..." ናትናኤል የሽማግሌውን ፊት ሲመለከት ቶሎ ኪሱ ገባና ሁለት ብር መዞ ተመለሰ::

"እስቲ ግባና ባለቤትየውን አነጋግር:: ወንድም ናቸው::" አሉት ሽማግሌው ዘበኛ ሁለት ብራቸውን ኪሳቸው እየጨመሩ::

"የማን ወንድም? "
"የአቶ ይልማ ወንድም::'አቶ አደፍርስ' ብለህ ጠይቅ::"



ናትናኤል ሽማግሌውን አመስግኖ ወደ ውስጥ ገባ::

"ይቅርታ ወንድም አቶ አደፍርስን ፈልጌ ነበር::" አንዱን የጋራዥ ሠራተኛ አስቀድሞ ጠየቀው::

"እኛውልህ::" አለው በዘይት የተጨማለቀ እጁን ዘርግቶ እያመለከተው::

ናትናኤል ወደ ሰውየው አመራ ተጠግቶ በአክብሮት ሠላምታ ሰጣቸው:: በጣም አጭርና ሆዳቸው ወደፊት የገፋ ናቸው:: ሙልጭ ካለው መላጣቸው ጎንና ጎን ከጆሮዎቻቸው በላይ ቡፍ ቡፍ ያሉ ጥቂት የሚቆጠሩ የፀጉር ብናኞች ይታያሉ:: የጋራዥ ባለቤት ሳይሆን የሆቴል ወጥቤት ኃላፊ ነው የሚመስሉት::

"እንደምን ዋሉ:: እባኮት ላስቸግርዎት:: ከአዲስ አበባ ነው የመጣሁት::"

"አላህ ይስጥህ -አላህ ይስጥህ!" በሚያስገመግም ድምፅ ጮሁና እጃቸውን እያወናጨፉ ፊታቸውን አዞሩበት::

"አይደለም ጌታዬ:: ለእርዳታ አይደለም:: መልዕክት ይገባ ነው የመጣሁት::"

"የምን መልዕክት?" በዚያው ሃይለኛ ድምፃቸው ጠየቁት ፊታቸውን ከስክሰው::

"የምሥራች ነበረች የላከችኝ እናቷጋ::ጃፋ የሰጠችኝ አድራሻ ጠፋብኝና የአባቷን ስም አውቀው ስለነበረ ማዞሪያ ስጠይቅ የእርስዎን አድራሻ ሰጡኝ::"

"አንተ ግም! ያችን መኪና ፍታት አላልኩም? ጥሩ አውደልድል ሳምንት ይድረስና ከጎንህ ታገኘዋለህ! " ሰውየው ተቆጥተው ሲጮሁ የጋራዡ ሠራተኞች ሁሉ ጭልፊት እንዳዩ ጫጩቶች በየስርቻው አንገታቸውን ይቀብራሉ:: "የማነች የምሥራች?" አሉት ድንገት በቁጣ የተለዋወጠ ፊታቸውን ወደ ናትናኤል መልሰው::

"የአቶ ይልማ ልጅ...የምሥራች ይልማ::"
ለመጀመሪያ ጊዜ ሰውየው ረጋ ብለው አትኩረው ተመለከቱት::
"ምንድነው ደግሞ እኔጋ የምትልክህ?"
"እናቷጋ ነው የላከችኝ:: የእናቷን አድራሻ ያውቁት እንደሆነ..." ረጋ ብሎ የሚፈልገውን አስረዳቸው:: ተስፋ ታየው::

"የየትኛዋ ልጅ መሆኗን አውቄ?" አሉ ሰውየው ለወንድማቸው ቤተሰብ ያላቸውን ጥላቻ ሳይደብቁ።

"ካዛንቺስ ሆቴል አላት።"

"አሀ፦ ሽርሙጣዋ ነች?" አሉ ሰውየው ጥላቻ በተቀላቀለበት ድምፅ። "የእናቷን አድራሻ አልከኝ እ...ደቻሳ ነው። ፈልገው። ታገኘዋለህ።" አሉ ሰውየው የሚቆጡት ሠራተኛ በአይናቸው እያፈላለጉ።

"የት አሉኝ?" ናትናኤል ሰውነቱ በእፎይታ ስሜት ሲወረር ተሰማው።

"ደቻሳ አልኩህ።" በቆመበት ትተውት ሄዱ።

"የት ነው ደቻሳ? ይቅርታ የኔ ጌታ... ለድሬዳዋ አዲስ ስለሆንኩ ነው።" አለ ናትናኤል ከኋላ እየተከተላቸው በልመና ቃና።

ሰውየው ቆም ብለው ከላይ እስከ ታች ገመገሙት። የለበሰውን ሸርጥ ሲያዩ የድሬ ሰው ነው ብለው ማሰባቸውን ተረዳ።

"ታዲያ አሁን ስራዬን ትቼ ካንተ ጋር ልንከራተት?" አሉ ሰውየው ጥለውት ወደ ሠራተኞቻቸው እያመሩ።

"አይደለም ጌታዬ። የሚያመላክተኝ ሰው ቢሰጡኝ...የሰው አደራ ስለሆነብኝ ነው።" አለ ከኋላ ከኋላ እየተከተላቸው።

"ይቅርታ ወንድም። እዚህ ስራ የፈታ ሰው የለም። ደቻሳ ነው አልኩህ ጠያይቅ፤ ታገኘዋለህ። ተው! ተው! እሱን አክስጅን አትነካኩ ብያለሁ! ግም! የወር ደሞዝህ ይገዛው መስሎሃል!" ሰውየው አንድ ሠራተኛቸው ላይ እያንባረቁ ቆሙ። ሲቆጡ ወፋፍራም ጉንጮቻቸው በርበሬ ይመስሉና በርጫቸው ከትንፋሻቸው ጋር ሽቅብ ቁልቁል ይናጣል።

"የናትየውን ስም ይነግሩኛል?" ቀስ ብሎ ጠየቃቸው።

"ምንድነው የምትለኝ? ስም? ብዙነሽ ነው መሰለኝ።"

'ብዙነሽ...ደቻሳ... ደቻሳ የት ነው? መንደር ነው? ሠፈር? ከተማ ነው? አገር?'

"ከተማውን የማያውቅ ሰው ባመጣ በምልክት ይነግሩልኛል? እባኮትን ተቸግሬ ነው ይርዱኝ።" እንዳይቆጡ አለሳልሶ ያዛቸው።

ሰውየው በተሰላቸ መልክ በረጅሙ ተነፈሱና ቆም ብለው አስተዋሉት።



"ተክላይ!" ተጣሩ። "ና ወዲህ!"

የጠሩት ወጣት እጁን ያጨማለቀውን የሞተር ዘይት በቡትቶ ጨርቅ ላይ እየጠራረገ መጣ።

"እየው... የዩሱፍን ሱቅ ታውቀው የለ? በቃ ከዚያ ስትደርስ በኪምስኩ ፊት ለፊት እጥፍ የሚል ኮረኮንች መንገድ አለልህ። እዛ አድርሰውና ቶሎ ተመለስ። ደሞ ሄደህ ጥፍት በልና እንተያያለን። የቮልሷ ጋስኬት ዛሬ ተቀይሮ አይለቅና ከቅዳሜ በኋላ እዚህ አትውልም። ግም! ሂድ አሁን!" ሰውየው ሳይታወቃቸው ተቆጥተው ይንቀጠቀጡ ጀመር።

ናትናኤል ሰውየውን ደጋግሞ አመስግኖ ተክላይን ተከትሎ ወጣ። መንገዱ ላይ ብዙ ሰው አይታይም። የጠዋቷ ፀሃይ ለዓይን ታጥበረብራለች። መንገድ ላይ ከተክላይ ጋር አልተነጋገሩም። ከተላከበት ቦታ አድርሶት ለመመለስ የቸኮለ የሚመስለው ወጣት በፍጥነት ሲራመድ እሱም ከጎን ከጎኑ ተጣደፈ። ከቦታው ሲደርሱ «በእዚህ ነው።» አለው ተክላይ ወደ አንድ ኮረኮንች መንገድ እየመለከተው። ወዲያው መልስ ሳይጠብቅ ፊቱን መልሶ በመጣበት መንገድ በሩጫ ተመለሰ።

በኮረኮንቹ መንገድ ገባ።

"እንደምንዋለ...እባኮት... የወይዘሮ ብዙነሽን ቤት ፈልጌ ነበር።" ከደጃፋቸው ቁጭ ብለው ስፌት የሚሰፉ ሴት ተጠግቶ ጠየቀ።

- "ያውልህ... በዚህ ቁልቁል ውረድ፤ደርሰሃል።" ሴትየዋ ፊታቸውን ከፀሃይዋ ጨረር ጋርደው ሽቅብ እየተመለከቱት አቅጣጫውን አመለከቱት።

ኮረኮንች መንገዷ ጠባብ ሆና በግራና በቀኝ ቅጥልጥል ቤቶች እጅ ለእጅ ተያይዘው ተደርድረዋል። እየተወላከፈ ወደፊት ቀጠለ። ትንሽ እንደሄደ ከፊት ለፊቱ እየሮጠ የሚመጣ ትንሽ ልጅ አስቆመና ጠየቀው። ልጁ ትንሽ አመልካች ጣቱን ቀስሮ "ያው!" አለው።

ስስ ሰማያዊ ቀለሟ ረግፎ እዚህና እዚያ የተመላለጠች ትንሽ የጭቃ ቤት ነች። ከዋና በሯ በስተግራ ያለው የእንጨት መስኮት ጥርቅም ተደርጎ ተዘግቷል። ገርበብ ካለው ቀይ ቀለም ከተቀባው የፊት ለፊቱ በር ጀርባ ሕይወትያለ አይመስልም።

ናትናኤል ደጃፉ ላይ የቆሻሻ ቦይ ዘሎ ተሻገረና ወደ ትንሿ የጭቃ ቤት መግቢያ ተጠጋ። በሩን በቀስታ አንኳኳው።

"ማነው?" ከውስጥ ድምፅ ተሰማው። ወዲያው አንድ ረጅምና ደልደል ያለ ሰውነት ያላቸው ሴት በሩን መለስ አድርገው ብቅ አሉ። የውጭው ብርሃን ሲወጋቸው ትላልቅ አይኖቻቸውን አሞጨሞጩአቸው።

"አቤት?" አሉት ፊት ፊቱን እየተመለከቱት።

አቋማቸውና ደልደል ያለ ሰውነታቸው...ረዘም ያለ ፊታቸው ትላልቅ አይኖቻቸው ጎርናና ድምፃቸው የምሥራች መጣችበት።

"እንደምን ዋሉ። ከአዲስ አበባ ነው የመጣሁት። የምሥራች ነች የላከችኝ።" አለ እጁን ወደፊት ዘርግቶ።
ሴትየዋ ፈገግ ብለው የዘረጋውን እጁን ጨበጡት።

"ውይ! ግባ-ግባ። አ!ዛሬስ ወንድ ወጣት! በቁልቢው አስታውሳ ሰው ላከች?" አሉ በሩን ከፈት አድርገው ይዘው እያስገቡት። ክፍሏ ጠባብና ጭልምልም ያለች ነች።

ናትናኤል ወደ ውስጥ ከገባ በኋላ ድንገት ቆም አለ። 'ሳይላመዱት ነው ሊያስደነግጣቸው የሚገባ። ድንገት ነው ጭንቅላታቸውን መምታት ያለበት!' ዞር አለና ጨለምለም ባለው ክፍል ውስጥ ትኩር ብሎ ተመለከታቸው።

"የምሥራች የላከችኝ በጅቡቲ በኩል ከአገር እንዳወጣው ነው።የታለ?" አላቸው ድንገት።

"ማ?" አሉ ሴትየዋ ደንገጥ ብለው።
"ካልቨርት የታለ? ጊዜ የለኝም!" አዋከባቸው።

ሴትየዋ አልመለሱለትም።ለአንድ አፍታ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ የተጋቡ መሰሉ።ድንገት አይኖቻቸውን በትከሻው ላይ አሳልፈው ሲመለከቱ ያዛቸው።ፈጠን ብሎ ፊቱን መለሰ። ወደጓዳ ከሚያስገባው በር ጎን አንድ አነስተኛ በር ተመለከተ።

ጊዜ አላጠፋም። በረጃጅም እርምጃዎች የፊተኛውን ክፍል ተሻግሮ ትንሿን በር ወደውስጥ በርግዶ ገባ።

የክፍሉ መጥፎ ጠረን ቀድሞ ተቀበለው።ጠባቧ ክፍል ውስጥ እዚህና እዚያ የተጣሉ የሲጋራ ቁራጮችና የተጨማደዱ ወረቀቶች የክፍሉን ወለል ሞልተውታል። ከበሩ በስተግራ ግድግዳው ስር ያለቁና ያልተነኩ የአረቂ ጠርሙሶች ተደርድረዋል። ከበሩ ፊት ለፊት መሬት ላይ አግድም



በተነጠፈ ፍራሽ ላይ ተቀምጦ በአንድ እጁ ጉልበቶቹን አቅፎ ይዞ በሌላው የአረቄ ጠርሙስ አንገት ጨብጧል!ዓይኖቹ በርበሬ መስለዋል።

ያልተበጠረ ፀጉሩ እርስ በርሱ ተቆጣጥሮ ጥቁር ፊቱ ተነፋፍቶ ጉብት መስሏል። ለአንድ አፍታ ተፋጠጡ በአርባና በሃምሳ ዓመት መሃል የሚገመት ሰው ነው።አጠር ብሎ ትትከሻው ይሰፋል። አራት ማዕዘን አገጩ ባጎፈረው ጺሙ ተሸፍኗል። ከወደትከሻው ከመብዛቱ ጋር የተመጣጠነ ሰውነቱ ጥንካሬውን ያሳያል።

"ቱፍ! አገኛችሁኝ አይደል? አገኛችሁኝ!" የጨበጠውን የአረቂ ጠርሙስ ወርውሮ ግድግዳው ላይ ከሰከሰው። "...ምን ታየኛለህ ! ቀጥል!" ፍራሹ ላይ የተቀመጠው ሰው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከስካር ጋር ይለፈልፍ ጀመር። "ተኩስ! ጨርሰኝ ! ተኩስ!"

ናትናኤል ፊቱን መልሶ የምሥራችን እናት ፈገግ ብሎ ካረጋጋቸው በኋላ ወደ ውስጥ ገባና በሩን ዘጋው። ስካርና እልህ የተሻሙት ፍራሹ ላይ የተቀመጠው ሰው መጨረሻውን በዝምታ መቀበል የመረጠ ይመስል ዝም አለ። ናትናኤል ወደ ጥግ ሄደና ሁለት ያልተነኩ የአረቂ ጠርሙሶች አንስቶ ወደ ሰውየው ተጠጋ።ነጠላ ጫማውን አውልቆ ግራ ተጋብቶ የሚመለከተው ሰው አጠገቢ ተቀመጠና የጠርሙሶቹን ክዳን መክፈት ያዘ።መጀመሪያ የከፈተውን ጠርሙስ ለካልቨርት ካሳለፈለት በኋላ ሁለተኛውን ወደ አፉ አስጠግቶ ተጎነጨለት።

አልኮሉ ጉሮሮውን እንደ እሳት እያቃጠለ እየለበለበ ወደ ሆዱ ሲጣደፍ አይኖቹን ከደነና ከጀርባ ያለውን ግድግዳ ተደገፈው...'አ...ፍ!' አለ ሳይታወቀው።

# III

## ቆንጆዎቹ

-31-

“ማርቆስ” አለ ጀኔራሉ “ጥፋትህ ፍጹም ከይቅርታ በላይ ነው።”

ማርቆስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዘመናት በሚያውቀው አስተማሪው አለቃውና ጓደኛው ፊት ላይ ጽያፌ የተሞላ ቅዝቃዜ የተመለከተ መሰለው።

“በአጭሩ የውጭ ጉዳዩ ሰው ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል።”አለ ጀኔራሉ በንዴት የቀሉ ዓይኖቹን ከማርቆስ ላይ አንስቶ በስተግራ በተቀመጠው ምክትሉ--በሆነው በአንድሬ አማሪ ላይ እየተከለ።

“እኔ መጀመሪያውኑ...” ዣክ ዊልያም ፊቱ ላይ ጎልቶ የሚታየውን ንቀትና ጥላቻ ሳይደብቅ። ዓይኖቹን በኮሎኔል ማርቆስ ላይ ተክሎ ጀመረ።

“በቃ!” አለ ጀኔራሉ አቋርጦት “አሁን ባለፈና በሞተ ነገር ላይ ጊዜዬን ማጥፋት አልፈልግም። ያለን ጊዜ በደቂቃዎች የሚቆጠር ነው። ይህ ሰው ወደ ድሬዳዋ የሄደው እንደምፈራው የካልቨርትን መሸሸጊያ አግኝቶ ከሆነና ምስጢሩንም አስገድዶ እጁ ካገባ ምን እንደሚከተል ልትገምቱ ትችላላችሁ።”

ለአንድ አፍታ የፀጥታው ቡድን ሃላፊ ንግግሩን አቁሞ በረጅሙ ተነፈሰ። በአፍንጫው ላይ ሽፍ ያለው ላብ በክፍሉ ውስጥ ካለው ቀዝቃዛ ካለው አየር ጋር ሲያገናዝቡት ሰውየው በንዳድ የሚሰቃይ ይመስላል።

“ለማንኛውም እናንተን ቢሮዬ ድረስ ከመጥራቴ በፊት ከዚህ ወዲያ ምን ማድረግ እንዳለብን ዝርዝር ዕቅድ አውጥቻለሁ።” አሉ ጀኔራሉ ቀጥሎ “ጉዳዩን ከአሁን በኋላ አንድሬ በቀጥታ እየተከታተልክ በየአንድ አንድ ሰዓቱ ሪፖርት ታደርግልኛለሁ።” አለ ወደምክትሉ ፊቱን መልሶ።

የፀጥታው ክፍል ምክትል አዛዥ ጭንቅላቱን በስምምነት ነቀነቀ።

“በቅድሚያ” አለ ጀኔራሉ ፊቱን የአጥቂ ሰለላ ሃላፊ ወደሆነው ወደ ዣክ ዊልያም መልሶ “በቅድሚያ ዣክ ድሬዳዋ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች...



በገበያ ቦታዎች... እ... የውጭ ዜጎች በሚኖሩበት ክልል... ተከታታይ የፈንጂ አደጋዎችን ትጥላለህ። ይህ በሚቀጥለው አንድ ሰዓት ውስጥ እንዲጠናቀቅ እፈልጋለሁ።” አለ ጀኔራሉ በጣቱ ጠረጴዛውን እየተመተመ። “አንድሬ...” ፊቱን ወደ ምክትሉ መለሰ። “የፈንጂ አደጋዎቹ። እንደደረሱ ወድያውኑ ድሬዳዋ ገብተህ እያንዳንዱን በር ትዘጋለህ። ለጊዜው በማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖስታ አገልግሎቶች ጥብቅ ክትትል አደርጋለሁ። ከዛም ውጪ አራት የኮማንዶ ሃይል ወደዚያው ልኬልሃለሁ ማንኛውም የመጓጓዣ መስመር ከአንድ ሰዓት በኋላ ይዘጋል። አንድሬ አሁኑኑ ቀጥታ ወደ ድሬዳዋ በረሀ ከተማዋን ትመነጥራለህ። ቤት ማፍረስ ካለብህ አፍርስ! ጉድጓድ መማስ ካለብህ ማስ! ያንን ሠይጣን ቀኑ ሳይመሽ በፊት እጅህ ማስገባት አለብህ። ለምናደርገው ሁሉ የፈንጂዎቹን ፍንዳታ የአሸባሪዎች ጥቃት መሆኑን በማጉላት ዣክ በቂ አሳሳች ፕሮፖጋንዳ እያዘጋጀ ለመገናኛ ብዙሃን ያቀርባል።” ፊቱን ወደ ዣክ ዊልያም መልሶ ተናገረ።

“እዚህ ላይ ይቅርታ።” አለ ሩዋንዳዊው አንድሬ አማሪ። “ድሬዳዋ የአሸባሪዎቹ ጥቃት እንደደረሰ እዛ ያሉ የመንግሥት ሃይሎችና ፖሊስም ጣልቃ ሊገቡብን ይችላሉ።”

“ለዚያ አታስብ” አለ ጀኔራሉ እጁን ወደጎን እወናጭፎ “ያ የኔ ስራ ነው። ማንኛውም የመንግሥት ሃይል ጣልቃ አይገባም።ፈንጂዎቹን የምናፈነዳውና አሳሳች ፕሮፖጋንዳ የምንነዛው የሕዝቡን ስነልቦና ለመጠበቅና የጠላትን ጥርጣሬ ላለማነሳሳትና ሽፋን ለመፍጠር ነው።በመንግሥት በኩል ችግር አይኖርም። ድሬዳዋ በእጅህ ናት።”

“እዛ ከተላከው ሃይል ጋር እንዴት ነው የምገናኘው?” አለ አንድሬ አማሪ።

“ወደዛው ትበራለህ። እንዳልኩህ አራት የኮማንዶ ሃይል ከነሙሉ ትጥቁ ወደዛው በሮ ከአውሮፕላኑ ሳይወርድ በተጠንቀቅ ይጠብቅሃል። በተረፈ ከዚህ ከተላከው ሃይል ጋር የሚኖርህ ግንኙነት ቀጥታ በሃይሉ አዛዥ አማካኝነት ይሆናል።”

ጀኔራሉ ተከታታይ ትዕዛዞችን ሲያስተላልፍ ከቆየ በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሲቆም በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ ተነስተው በተጠንቀቅ ቆሙ።

“አሁን” አለ ጀኔራሉ ሰዓቱን እየተመለከተ። “ከጠዋቱ አስራሁለት ከሩብ ነው። ዣክ አንድ ሰዓት ተኩል ከመሆኑበፊት ፈንጂዎች እንዲፈነዱ። አንድሬ ከአንድ ሰዓት ተኩል እስከ ሁለት ድሬዳዋ ታርፋለህ። ከሁለት እስከ ሦስት ባለው ሰዓት ሃይልህን አቀናጅተህ ስራህን ትጀምራለህ...” ጀኔራሉ በረጅሙ ተነፈሰና ያመነታ መሰለ። “ከአሁን ወዲያ ይህን ጉዳይ እዚሁ

ልናቆየው አንችልም:: ዝርዝር ሁኔታውን ለበላዮቼ ማስታወቅ ይኖርብኛል:: ምን ያህል አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለን አስተውሉ:: ለምትሰሩት ማንኛውም ስህተት በቀጥታ ተጠያቂ አድርጌ አቀርባችኋለሁ::" አለ ጀኔራሉ የግርክ ዊልያምን ፊት እየሸሸ:: "መሄድ ትችላላችሁ::"

ሁለቱ ባለስልጣናት ከወጡ በኋላ ጀኔራሉ በወንበሩ ላይ ተቀመጠና ፊቱን በተጠንቀቅ በቆመው ኮሎኔል ማርቆስ ላይ መለሰ::

"ጋዜጠኛዋጋ ሄደህ ጥበቃውን ተከታተል::" አለው ከፊቱ ዘወር እንዲልለት በመፈለግ:: ኮሎኔል ማርቆስ በተጠንቀቅ ሠላምታ ሰጥቶ ፊቱን መልሶ ወደበሩ ሲያመራ "ኮሎኔል" አለ አለቅየው ፊቱ ላይ ንዴት የተቀላቀለበት ጽያፌ እየተነበበ "...እሷም ደግሞ እንዳታመልጥህ::"

ኮሎኔል ማርቆስ በድጋሚ ወታደራዊ ሠላምታ አቅርቦ በፀጥታ ከክፍሉ ወጣ::

-32-

በተከታታይ የፈንጂ ድምጾች ድሬዳዋ ስትናወጥ ናትናኤል ከተኛበት ስስ ፍራሽ ላይ በርግጎ ተነሳ::

ተከታትለው ሌሎች ሁለት ፍንዳታዎች ጠባቧን ከተማ ሲንጧት፣ ያለበትን ክፍል በርና መስኮት ሲያርገፈግፉት ናትናኤል ተነስቶ ቆመና ዙሪያውን ቃኘ:: በፍንዳታው ውስጥ አጉረምርሞ ተገላብጦ መልሶ የተኛው ካልቨርት አሁንም ከገባበት የስካር ባህር ብቅ ያለ አይመስልም::

ናትናኤል ካልቨርትን በጭንቀት ተመለከተው:: ከአንድ ቀን በፊት ሲያገኘው ብስጭት ተስፋ መቁረጥና ስካር የተሻሙት ግማሽ እሬሳ ነበር:: በዛን ሰዓት ናትናኤል ከካልቨርት ጋር ቀጭ ብሎ ለማውራት መሞከር ፍሬቢስ መሆኑን ለመረዳት አልተቸገረም:: ይልቁንም በቅድሚያ የካልቨርትን አመኔታ ሊያገኝበትና ሊያረጋጋውም የሚችልበትን መንገድ መረጠ-ከጎኑ ፍራሹ ላይ ቁጭ ብሎ አረቄ ሲጠጣ ቆየ::

አለፍ... አለፍ እያለ ግራ የተጋባው ካልቨርት...

"ማነህ? ለምን አትገለኝም?... ምንድነው የምትጠብቀው?" እያለ በስካር መንፈስ ቢወተውተውም ናትናኤል መልስ አልሰጠውም::



ከሰዓት በኋላ ናትናኤል ካልቨርት ከተሸሸገበት ጠባብ ክፍል ወጥቶ የምሥራችን እናት አነጋገራቸው::

"ድንገት በመምጣቱ ይቅርታ...የላከችኝ የምሥራች ነበረች:: ግን በዚህን ዓይነት ሁኔታ ላይ ይሆናል ብለን አልገመትንም ነበር::" አላቸው የካልቨርት ስካር ያስደነገጠው መስሎ::

"ምን አባቱ ሳድርገው? ጠዋት ተነስቶ አረቂ ነው...ማታ ተኝቶ አረቂ ነው...ምግብ ሲሉት በሩቁ እጁን ያውለበልባል...አረቂ የከለከልኩት ጊዜ ሲያቃስት ማደር ነው...'ተው' አይሉት ነገር አፉ እንጎዳ...እኔኮ ጨነቀኝ:: አንድ ነገር አድርጊ አልላት ነገር ድምጿ ጠፋ::ሰው አልክባት...ማንም ማወቅ የለበትም ብላኝ እንዴት አድርጌ ለሰው ልናገር?" ሲትየዋ የተማረሩ መሰሉ::

"ግድ የለም:: ዋናው ነገር በህይወት መቆየቱ ነው:: ብቻ እርሶ ትንሽ ተቸገሩ:: የምሥራችን አይሆንም አታስቸግሪያቸው ብያት ነበር:: 'እምቢ' አለች እንጂ::" በተቻለው የልጃቸው የምሥራች የቅርብ ወዳጅ ለመምሰል ጣረ::

"እኔማ ምን ችግር አለብኝ...ቢበላ የገዛ ገንዘቡን፣ ቢጠጣ የገዛ ብሩን ከኔ ሳንቲም አላወጣ...ግን ቢሆንም... ሰው እንዲህ ራሱን በመጠጥ በመርገዝ ልበለው እንጂ ሲገድል ሲያዩ ህሊናም አያርፍ::"

"እውነት አለዎት::" ናትናኤል በስምምነት ጭንቅላቱን ነቀነቀ:: "ምንም ችግር የለም:: እሷም እስባ ነው እኔን መላኳ:: ነገ ከነገ ወዲያ ራሱን ሲገዛ ይገዙው እሄዳለሁ::" አላቸው በራስ የመተማመን ፈገግታ እያሳየቸው::

"ግን እንደው በቁልቢው... እሷ ደህና ነች? እንዲህ የጠፋች?"

"ደህና ነች...ደህና ነች::" ናትናኤል እራሱን ጠሳ "ጊዜ ስላላመቻት እንጂ አብራኝ ልትመጣ ነበር ያሰበችው::"

ናትናኤል ተመልሶ ካልቨርት ካለበት ክፍል ገብቶ እዚያው ፍራሹ ጥግ ተኝቶ አደረ::

ድጋሚ ሦስት የፈንጂ እሩምታ ዙሪያውን ሲያደባልቀው ናትናኤል አይኖቹን ከካልቨርት ላይ ነቅሎ ፈጠን ብሎ ጫማውን አጠለቀና የጠባቧን ክፍል መዝጊያ ከፍቶ ብቅ አለ::

በራፍ ላይ በርካታ ሴቶች ሰብሰብ ብለው ይጯጯሃሉ:: ወደ ፊተኛው በር ጠጋ አለና ወደ ውጪ ተመለከተ:: በየምስራች እናት በራፍ የምታልፈው ኮረኮንች መንገድ ከየቤታቸው ወጥተው በቆሙ እዋቂዎች ተሞልታ

ለች፡፡ ህፃናት ድምፁ ወደ ተሰማበት አካባቢ ሲሮጡ ወላጆች «አትመለስም! አትመጣም!» እያሉ ይጯጯሃሉ፡፡

ከበር ላይ እንደቆመ ሲመለከቱት የምሥራች እናት ፊጠን እያሉ መጡና ከቤት ገቡ፡፡

"ደህና አደርክ የኔ ልጅ...በጠዋት አስደነገጡኸኝ..." አሉ ፍንዳታውን ሰምተው ወደ ውጭ ሲሮጡ እንደነገሩ ደረብ ያደረጉትን ሻል እያስተካከሉ፡፡

"ምንድነው?" አላቸው፡፡

"እንጃ! ብቻ ወዲያ ማዶ ነው... ወደገበያው መሃል፡፡ ደህና አደርክ?"

"ደህና ደህና፡፡ እርሶ ደህና አደሩ?"

"መጣሁ ተጣጥቤ" ብለውት ወደጓሮ ገባ ካሉ በኋላ "... መተጣጠብ ከፈለግህ ወዲህ ና" አሉት መለስ አሉና፡፡ ተከተላቸው፡፡

ናትናኤል በጓሮው በር ወጥቶ ከውጭ ካለች ቧንቧ ስር አጎንብሶ ፊቱን ተጣጥቦ እንደጨረሰ ወደ ቤት ሲመለስ የምሥራች እናት ለባብሰው ብቅ ሲሉ ድጋሚ አገኛቸው፡፡

"እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገረህ!" አሉት የአመት በአል ነጭ የአበሻ ቀሚሳቸውን እንዳጠለቁ በሞቀ ፈገግታ እየተቀበሉት፡፡ "በዓመት በዓል አስደነገጡን አይደል! ገብሬል ያስደንግጣቸው'ቴ!"

"እንኳን አብሮ አደረሰን፡፡" ናትናኤል ፈገግታቸውን በፈገግታ መልሶ፡፡ "ደህና አደሩ?" አላቸው ለረጅም ጊዜ እንደሚያውቃቸው ቤተኛ ሆኖ፡፡

"ደህና ደህና የኔ ልጅ...ቁርስ እዛው ላምጣልህ ከሰውየው ጋር ወይስ ከኛ ጋር ትበላ? መቼም እሱ በጅ ብሎ ከዛ አይወጣም፡፡" ሴትየዋ ከዚህ ቀደም ሞክረው ያቃታቸው መሆኑን ለማሳየት እጃቸውን እወናጨፉ፡፡ "ክፍሉን ለማጽዳት እንኳንኮ አይፈቅድልኝም ሌሊቱን ደህና አደርክ? ሳሳ ቸገረህም? አንዳንዴኮ አይጣልብህ እንድችው ሲያቃስት ነው የሚነጋለት... አበስኩ ገበርኩ!"

"ደህና ነው... አላስቸገረኝም... ደህና ነው..."

"በል ከዚያው አመጣላችኋለሁ ቁርሳችሁን፡፡" አሉ ሴትየዋ ነጠላቸውን ከላያቸው እየገፈፉ ወደ ጓዳ እየገቡ፡፡

ናትናኤል የትንሿን ክፍል መዝጊያ ከፍቶ ሲገባ ካልቨርት ከእንቅልፉ ተነስቶ እጋምሶ ያስቀመጣትን የአረቄ ጠርሙስ ጨብጦ አገኘው፡፡



በእርጋታ ወደፊት ተራምዶ የአረቄውን ጠርሙስ ከካልቨርት እጅ ውስጥ ፈልቅቆ አውጥቶ ጠርሙሱን ወደ ጥግ አስቀመጠና ፊቱን መልሶ ቁልቁል አፈጠጠበት

"ካልቨርት...በቂ ጊዜ የሰጠሁህ መሰለኝ...አዲስ አበባ ውስጥ የሰዎች ነፍስ እንደዋዛ እያለፈ ነው፡፡" አለ ናትናኤል ካልቨርት በሚገባው በእንግሊዝኛ ቋንቋ፡፡

ካልቨርት ከተቀመጠበት ስስ ፍራሽ ላይ ሳይንቀሳቀስ ሽቅብ ተመለከተው፡፡ ፊቱ ላይ የሚነበበው ስሜት የጥርጣሬ ይሁን የጥላቻ፤ የቁጣ ይሁን የግድ የለሽነት ናትናኤል ግራ ተጋባ፡፡

"ስማ ካልቨርት...ነገሩ ምንድነው? እነማን ናቸው እነሱ?" ናትናኤል ጥያቄውን እንዴት አድርጎ እንደሚያስቀምጥ ቸገረው፡፡ "ተናገር ምን ይዘጋሃል?" ወደፊት ተራምዶ ካልቨርት ጎን ፍራሹ ላይ ተቀመጠ፡፡ "...ትሰማኛ ለህ ምንድነው ነገሩ? ሁሉንም ማወቅ እፈልጋለሁ፡፡"

"ማነህ አንተ...ከየትኞቹ ነህ?" አለ ካልቨርት ጥያፌ በተሞላ ገጽ፡፡

"ከማንም አይደለሁም፡፡እውነቱን ለመናገር 'ከየትኞቹ' ስትል ስለነ ማን እንደምታወራም አላውቅም፡፡ ድንገት ወጥመድ ውስጥ የገባሁ ሰው ነኝ፡፡ ወጥመዱን ለመስበር ከአውሬው ለማምለጥ የግድ አንተ ይዘህ የተሰወ ርከውን ምሥጢር ማግኘት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ለዚህ ነው አንተን ፍለጋ የመጣሁት፡፡ ምስጢሩን እፈልጋለሁ... ያን ጊዜ አውሬውን እስንገዋለሁ፡፡"

ካልቨርት ምንም ሳይመልስ በጥርጣሬ ፊት ናትናኤልን ተመለከተው፡፡

"አውሬው ማነው? አውሬው፡፡ ቆይ... ለምን እነግርሃለሁ?"

"ደርሰዋል፡፡ትንሽ ነው የቀራቸው፡፡ ድሬዳዋ ድረስ ተከትለውኛል፡፡ ጊዜ አይወስድባቸውም፡፡ ያገኙናል! ያገኙሃል!"

"እነማን ናቸው እነሱ?" ካልቨርት አይኖቹን አጥብቦ ጠየቀው፡፡

"እሱን ነው ለማወቅ የምፈልገው!"

"አንተን የሚያባርሩህ የትኞቹ መሆናቸውን እንዴት ላውቅ እችላለሁ?" ካልቨርት ወደኋላ ግድግዳውን ተደገፈና እጆቹን ደረቱ ላይ አቆላልፎ ተመለከተው፡፡

"ካልቨርት ጊዜ አታጥፋ! እኔን ያሳደዱኝ ተከላዎች አንተንም የሚያ ነፈንፉ ናቸው፡፡ እነማን መሆናቸውን አላውቅም!"

"ውሸት! ውሸት! ውሸት!" ካልቨርት ጥያፌውን መደበቅ አልቻለም። ፊቱ በጥላቻ ተሞላ። "ልታታልለኝ አትሞክር። የነጮቹ ግልገል ነህ። ባንዳ እንደሆነ እንደምፀየፍህ ባወቅህ። እንዲት ነገር አልነገርህም። ልትነድለኝ ትችላለህ።"

"ወደ አንተ እንድመጣ አምናኝ አድራሻህን የሰጠችኝ የምሥራች ነች።"

"ውሸት!"

"ውሸት አይደለም።ሁሉን በዝርዝር ልነግርህ እችላለሁ። ካልቨርት... ፈቅጄ በዚህ ውሻዮንብር ውስጥ የተዘፈቅሁ ሰው እንዳልመስልህ። ካልቨርት... ትላንት እንደማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ጠዋት ወደ ስራ ማታ ወደቤቴ የምገባ ሰው ነበርኩ። ዛሬ...ዛሬ ቆቅ ነኝ!' ተባራሪ ታዳኝ ቆቅ።" ናትናኤል ከመጀመሪያው ቀን ከአለቃው ትዕዛዝ ከተቀበለባት ቀን ጀምሮ የሆነውን ያደረገውን የተፈፀመውን ሁሉ አንድ በአንድ ይተርክ ጀመር።

"እና የዚህ ጓደኛህ ሞት ብቻ እራስህን ለአደጋ እንድታጋፈጥ አስገደደህ ማለት ነው?" አለ ካልቨርት መሃል ላይ አቋርጦት።

"የጓደኛዬ ሞት ብቻ አልነበረም! እርግጥ የሁኔታውን ጥልቀት ሳልረዳ በፊት ጥቂት ቀናት ውስጥ በአለቃዎቼ እርዳታ በመደገፍ የጓደኛዬን ገዳዮች አጥምጄ ለመያዝ የምችል መስሎኝ ነበር። ሳይሆን ቀረ። ከዛ ወዲህ ግን ለራሴም ህይወት ሰጋሁ። አብርሃምን ድንገት እንዳጠፉት እኔንም ባላሰብኩት ቦታ እንዳይደፉኝ ሰጋሁ። ጭንቀት ወረሰኝ። ከመጨረሻው ሳልደርስ ተገዳዮቼ መኖር እንደማልችል ተረዳሁ... ያንን ለማድረግ ደግሞ አንተን አግኝቼ ምሥጢሩን መረዳት ነበረብኝ... ድንገት ለመሰወር ወሰንኩ።" ናትናኤል አንድ በአንድ ይዘረዝርለት ጀመር። መሃል ላይ እንዴት ወደ የምሥራች ሆቴል እንዳመራ ሲያወራ፣ እንዴት አንድ ክፍል ውስጥ ይዞ የካልቨርትን አድራሻ እንድትነግረው እንደጠየቃት ሲያወጋ፣ እንዴት በቢቷ ጀርባ የስርቆሽ በር አብረው ሾልከው እንደሮጡ ሲተርክ፣ የካልቨርት ዓይኖች ከየጉድጓዶቻቸው እየወጡ ናትናኤል ላይ ተጣብቀው ቀሩ።

ናትናኤል በተቻለው መጠን አለስልሶና አባብሎ የምሥራችን ሞት ሲነግረው ካልቨርት ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳ።

"ውሸት! ውሸትህን ነው!" ሰውነቱ ይቅበጠበጥ ጀመር።



"ውሸቱን አይደለም ካልቨርት። እርግጥ ጥፋቱ የኔው የራሴ ነው። ወደ እርሷ ባልሄድ ምናልባት ያች ሴትዮ አግኝታ አታጠፋትም ነበር።"

ካልቨርት በቆመበት ቁልቁል ናትናኤልን ተመለከተው። ወዲያው የሰማው ቀስ በቀስ እየሰረገ ወደ ሰውነቱ ሲገባ በፍራሿ ላይ ተቀምጦ ፊቱን ጉልበቶቹ መሃል ቀብሮ በፀጥታ ያለቅስ ጀመር። እልህና ንዴት ትከሻውን ሲሰብቁት ናትናኤል ለጥቂት ደቂቃዎች በትዕግሥት ጠበቀውና ቀጠለ።

"ከመሞቷ በፊት እናቷጋ ድሬዳዋ መሆንህን ብቻ ተነፈሰችልኝ።"

ናትናኤል ታሪኩን በሙሉ አንድም ሳያስቀር አውርቶ ሲያበቃ ወደኋላ ፈቀቅ አለና ከፍራሹ ኋላ ያለውን ግድግዳ ተደግፎ ተቀመጠ። ለተከተሉት በርካታ ደቂቃዎች በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ። አልፎ አልፎ ብቻ ካልቨርት መሃረቡን እያወጣ አፍንጫውን ሲያፀዳዳና ሳግ ሲተናነቀው ከሚሰማው ድምፅ በስተቀር ዝምታ ሸፈናቸው።

"ሲገድሏት እዛው ነበርክ ማለት ነው?" አለ ካልቨርት ጉንጮቹን ያረሰረሰውን እንባ እንኳን ለመጥረግ ሳይሞክር ካቀረቀረበት ከጉልበቶቹ መሃል ቀና ብሎ ናትናኤልን እየተመለከተው።

ናትናኤል በዝምታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ- 'አዎ'

ካልቨርት በእንባ የደፈረሱ አይኖቹን ከጣሪያው ላይ ሰቅሎ የሚተናነቀውን እንባ ታገለው።

"እና... ምንድን እንድነግርህ ነው የምትፈልገው?" አለ በተሰበረ ድምፅ ጭንቅላቱን ወደፊት ጉልበቶቹ ላይ ጣል አድርጎ።

"ሁሉን፣ እነማናቸው? ምንድነው የሚሰሩት? አንተስ ለምን ተሰወርክ? ሁሉን ማወቅ እፈልጋለሁ።"

"ዋጋ የለውም።" አለ ካልቨርት ዓይኖቹን በዘዝ አድርጎ።

"እንዴት ዋጋ የለውም? ምስጢሩን ስረዳ ብቻ ነው ራሴንም ሆነ አንተን ልረዳ የምችለው፤ እነዚህን ነፍሰ ገዳዮች ላቆማቸው የምችለው።"

"ነፍሰ ገዳዮች አይደሉም።"

"ታዲያ ምንድናቸው? ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋለህ?"

"ነገርኩህ ነፍሰ ገዳዮች አይደሉም!" በስጨት አለ ካልቨርት። ድጋሚ መሃረብ አውጥቶ አፍንጫውን አጸዳዳ።

“የምሥራችን የገደሏት እነርሱ መሆናቸው እንዳልተዘነጋህ እርግጠኛ ነኝ::”

“እነሱ አይደሉም:: አስታውስ... የገደለቻት ሴት...”

“ያው ነው!” አቋረጠው ናትናኤል::

“ያው አይደለም!” ካልቨርት በስጨት አለ:: “ማነው ስምህ... ናትናኤል ነው ያልከኝ? ብዙ የማታውቀው ነገር አለ:: ምንም አታውቅም ማለት ይቀላል:: ነፍስ ገዳዮች አይደሉም::አዎ ጓደኛህን ገድለውብህ ይሆናል!እንተንም ሊያሳድዱ ይችላሉ ግን አንተ እንደምትለው አይደሉም::”

“የፈለጉትን ይሁኑ:: ብቻ ልናቆማቸው ይገባል:: ትሰማኛለህ?”

“ልናቆማቸው አይገባም:: ተስፋችን እነርሱ ብቻ ናቸው:: የቀረን ጭላንጭል ብርሃን ቢኖር የእነርሱ ዓላማ ብቻ ነው:: ዳር መድረስ አለባቸው::”

ናትናኤል የሚያዳምጠው ሁሉ እንቆቅልሽ ሆነበት::

“ምንድነው የምታወራው የሚሰሩትን ትደግፋለህ ማለት ነው? ወይስ...”

ካልቨርት በመስማማት ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

“ታዲያ ለምን ተሰወርክ...እነሱስ ለምን ያሳድዱሃል... ለምን ለሌሎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆንክ?” ናትናኤል መጥፎ ስሜት ጉሮሮውን ሲተናነቀው ተሰማው:: “ጓደኛዬ የሞተው ለምን ይመስልሃል? ቤቴን ትቼ ጠፍቼ የቀረሁ ለምን ይመስልሃል? አንተ እዚህ አረቄ በምትጋትበት ሰዓት ሌሎች የአንተን ዱካ ሲያፈላልጉ በጥይት እየታደኑ ነበር:: ይገባሃል የምልህ?” በንዴት ተንቀጠቀጠ ናትናኤል::

ካልቨርት ቀና ብሎ በቁጣ የተጨማተረውን የናትናኤልን ፊት ተመለከተና ድጋሚ አቀረቀረ::

የተቀመጡበት ክፍል በር ተከፍቶ የምሥራች እናት በትሪ ላይ ሁለት ሳህኖች ይዘው ገቡ:: በቅመም የሚሰራው ምግብ ሽታ ከጓዳ ተነስቶ በተከፈተው በር አልፎ የተቀመጡበት ድረስ አወዳቸው:: ከተዘጋው መስኮት ጀርባ ከጎሮ ሴቶች ምግብ ሲያሰናዱ ሰቃ ሲያጣጥቡ የሳህን ኳኳታ... ሳቅ ... ጨዋታ... ልጆች ሲጨፍሩ... ልጃገረዶች 'አበባዩ ሆዬ... ለምለም... ' እያሉ ሲዘፍኑ ይሰማል:: ዘመን መለወጫ.... መስከረም አንድ.... አዲስ አመት::

“በሉ ቁርሳችሁን አድርጉ::” አሉ ሴትዮዋ ትሪውን ፍራሹ ጥግ እያስቀመጡ:: ወዲያው በእንባ ያባበጠውን የካልቨርትን ፊት ሲያዩ ደንነግጠው ቆሙ::



“እግዜር ይስጥልን...መቼም አስቸገርንዎት::” አለ ናትናኤል የተፈጠረውን ድንጋጤ ለማርገብ::

የምሥራች እናት ቶሎ ፊታቸውን መለሱና ከክፍሉ ወጡ:: ሴትየዋ ቢወጡም ሁለቱ ሰዎች ምግቡን ለመብላት እጃቸውን አላነሱም::

“ናትናኤል በእኔ ምክንያት ስለተፈጸመው ሁሉ እጅግ አዝናለሁ:: ግን ልነግርህ የምችለው ነገር የለም::” አለ ካልቨርት ሴትየዋ ዘግተውት በሄዱት በር ላይ አፍጥጦ::

“በጣም ጥሩ!” ናትናኤል ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ ተነሳ “ምሥጢሩን አወጣዋለሁ::የማውቀውን ሁሉ በአገርና በውጭ ለሚገኙ ጋዜጦች እበትነዋለሁ:: እርግጠኛ ነኝ... የማወጣው ፍንጭ ምንም ትንሽ ቢሆን ያንተን አድራሻ ይጨምራል::ያ ደግሞ ከትክክለኛው ጆሮ እንደሚደርስ አልጠራጠርም!” ናትናኤል ያለማወላወል ወደ በሩ አመራ::

“ረጋ በል ናትናኤል... ረጋ በል... ምን እያደረግህ እንደሆነ አታውቅም!” አለ ካልቨርት ከተቀመጠበት በርግጎ እየተነሳ:: “ለህይወቴ ፈርቼ ወይ አድራሻዬን እንዳታወጣ ሰግቼ እይምሰልህ... ግን አንተ የማትረዳው የከፋ ጥፋት እንዳትፈጽም ስለምፈራ ነው::”

የካልቨርት መደናገጥ ናትናኤልን የልብ ልብ ሰጠው::

“ጊዜዬን አታጥፋ! ለጓደኛዬ ሞት ምክንያት ሆነሃል:: ከአሁን ወዲያ ግን ለአንዳንተ አይነቱ ጅል ህይወቴን አደጋ ላይ አልጥልም::” ናትናኤል የክፍሉን በር ከፍቶ ቆመ:: “ትነግረኛለህ አትነግረኝም?”

ካልቨርት በተስፋ መቁረጥ ራሱን አወዛወዘና ተመልሶ ከፍራሹ ላይ ዘፍ አለ::

“ቀጥል... እውነቱን ነው የምፈልገው::” አለ ናትናኤለ በሩን ዘግቶ ካልቨርት ጎን ፍራሹ ላይ እየተቀመጠ::

“ከየት እንደምጀምር አላውቅም::” ካልቨርት በባዶው አየር ላይ አፈጠጠ:: “ከኔ ልጀምር ከእነርሱ?” አለ በለሆሳስ ናትናኤልን ሳይሆን እራሱን የሚጠይቅ ይመስል::

“ከሚቀድመው ጀምርልኝ::” ናትናኤል እያበረታታው::

"በወታደራዊ አታሼነት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው የአገሬ ኤምባሲ ውስጥ እንድሰራ ከመመደቤም በፊት በአገሬ የአየር ወለድ ኮማንዶ ሠራዊት ውስጥ በኋላም በተለያዩ አገሮች በወታደራዊ አታሼ የሥራ መደብ ሰርቻለሁ:: በዚሁ የስራ መደብ ሉሳካ በሚገኘው ኤምባሲያችን ውስጥ እየሰራሁ በነበርኩበት ጊዜ ነው... ደቡብ አፍሪካ በነጮች ስር በነበረች ጊዜ... የደቡብ አፍሪካ የነጮች የስለላ ድርጅት ተደራቢ ወኪል አድርጎ የመለመ ለኝ:: ወድጄ አልነበረም:: ያኔ ባለትዳር ነበርኩ:: ባለቤቴ ከመሞቷ በፊት ነው የማይሆን ነገር ሳደርግ ያዙኝ:: የሚፈልጉትን ካላቀበልኳቸው ያደረ ኩት ሁሉ በፎቶግራፍ ከተደገፈ ማስረጃ ጋር ለባለቤቴ እንደሚደርሳት አስጠነቀቁኝ:: እወዳት ነበር::. አሁን ይቆጨኛል...ያኔ ግን ከባለቤቴ ጋር መለያየቱ ሞት መስሎ ታየኝ:: ወጥመዳቸው ውስጥ ገባሁላቸው::"

"ምንድን ነበር ካንተ የሚፈልጉት::"

"ያን ጊዜ ናሚቢያ ነፃነቷን ገና አልተቀዳጀችም ነበር:: የስዋፖ ሽምቅ ተዋጊዎች ከአንጎላና ከዛምቢያ ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣቸው ነበር:: የጦር ሠፈሮችም ነበሯቸው:: በተለይ ከዛምቢያ የሚነሱ የስዋፖ አደጋ ጣዪ ቡድኖች በካፕሪቪ ሰርጥ ውስጥ በተደጋጋሚ በነጮቹ ላይ ጥቃት ያደርሱ ነበር:: ያንን ነበር ከእኔ ለማግኘት የሚሹት-ስዋፖ በዛምቢያ ውስጥ ስለሚያደርገው እንቅስቃሴ:: ለነገሩ እዛ የቆየሁት በጣም ለአጭር ጊዜ ነው - ሁለት ዓመት አይሞላም:: ቢሆንም በጊዜው በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን አስተላልፌላቸዋለሁ::ከዚያ ወዲህ በተመደብኩባቸው አገሮች ሁሉ እየተከታ ተሉ መረጃ እንዳቀብላቸው ይጠይቁኝ ስለነበር የሚፈልጉትን ሳደርግ ቆየሁ:: ከስድስት ዓመታት በፊት አዲስ አበባ በሚገኘው የአገሬ ኤምባሲ ጽህፈት ቤት ስመጣ በድጋሚ ግንኙነቴን እንድቀጥል ጠየቁኝ:: ምርጫ አልነበረኝም ቀጠልኩ:: በደቡብ አፍሪካ ለውጥ ከተደረገና ጥቁሮች ስልጣን ከተጋሩ በኋላ የነጭ ደቡብ አፍሪካ ስለላ ሰዎች ለእንግሊዝ ኤም.አይ. ስድስት ሸጡኝ::"

"ምንድን ነበር የሚፈልጉት እንግሊዞቹ::?"

"አንድ ነገር ላይ ያተኮረ አልነበረም ፍላጎታቸው፤ልሰጣቸው የምች ለውን ሁሉ ይቀበሉኝ ነበር:: የዛን ያህል ጫና አልነበረብኝም...ዋናው ዓላማ ቸው ግንኙነታችን እንዳይሳሳና በእኔ ላይ ያላቸውን የበላይነት እንዳልዘነጋው በየጊዜው ማስታወስ ነበር::"

"የቢላዋ ሴትዮስ?"

"ስለእርሷ ብዙ አላውቅም...ቢሆንም የእሥራኤል ፓስፖርት መያዟን ስለማውቅ የሞሳድ ቅምጥ መሆኗን እጠረጥር ነበር:: ያም ሆነ ይህ የቅብብሎሹን ሠንሠለት የቀየሱት እነሱው ስለነበሩ እኔ መረጃውን ለእርሷ አቀብላለሁ... እርሷ ደግሞ ለእንግሊዝ የምስጢር ሠራተኞችና ያለጥርጥር ለሞሳድም ታቀብላለች::"



"ሹፌሩስ? እዚህ ውስጥ እንዴት ሊገባ ቻለ?"

"በመጀመሪያ እሱ አልነበረም:: እኔ እራሴ ነበርኩ ለቢላዋ ሴት መረጃውን የማቀብላት:: መሃል ላይ ግን ቤላ በምመላለስበት ጊዜ የኢትዮጵያ የፀረ ስለላ ሰዎች በእኔ ላይ ክትትል ማድረጋቸውን ደረስኩበት:: ሁኔታው ስላሰጋኝ የቅብብሎሹን መስመር እንዲቀይሩ ጠየቅኋቸው፤ ከዚያ በኋላ ነው ሹፌሩ በእንግሊዞች የተመለመለ መሆኑንና መረጃውንም በእርሱ በኩል ማስተላለፍ እንደምችል በቢላዋ ሴት በኩል የተነገረኝ:: ሹፌሩ በሽፋን የኢትዮጵያ ፀረ ስለላ ሰው መሆኑን ግን አሁን አንተ ስትነግረኝ ነው ያወቅሁት::"

"እሺ..." አለ ናትናኤል::

"እና ላለፉት ስድስት ዓመታት እንዳልኩህ አልፎ አልፎ አንዳንድ መረጃዎችን ስጥላቸው ቆየሁ::በመሠረቱ የማቀብላቸው መረጃ ያንን ያህል ጥልቀት ያለው አልነበረም::አንደኛ እኔ እራሴም የተጠናከረ ምንጭ አልነበረኝም፤ ሁለተኛ እነርሱም ያንን ያህል አይጫኑኝም ነበር:: ከጥቂት ወራት ወዲህ ግን ሁኔታው በድንገት ተቀየረ::"

"እንዴት?"

"ሰውየው ማን እንደሆን የሚያውቅ የለም:: ብቻ ከሁለት ዓመታት በፊት በተካሄደው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ስብሰባ ላይ ይኸው ሰው መሪዎች ብቻ የተገኙበት ዝግ ስብሰባ ጠይቆ ተፈቀደለት:: ለተገኙት መሪዎች አንድ ምሥጢራዊ ዕቅድ አቀረበ::"

"ማነው ሰውየው? ምንድነው እቅዱ?" ናትናኤል አደራርቦ ጠየቀው::

"እውነቱን ነው የምነግርህ:: ሰውየው ማን እንደሆነ አላውቅም አንዳንዶቹ ከፍተኛ ማዕረግ ያለው በግብጽ የሚገኝ የጦር አዛዥ ነው ይላሉ፤ ሌሎች አይደለም የማሊ ሰው ነው ይላሉ:: በኬንያ ውስጥ በሚገኝ አንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የፖለቲካ ምሁር ነው የሚሉም አሉ:: ብቻ ሁሉም የሚያወራው በሹክሹክታና በይሆናል ነው:: እውነቱን ለመናገር ከጥቂት ሰዎች በስተቀር የሰውየውን ማንነት የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም:: ያም ሆነ ይህ ሰውየው የተባለውን ዕቅድ አቀረበ:: የዕቅዱ መሠረታዊ ሀሳብ ከአፍሪካ አገሮች የተውጣጣ እጅግ ከፍተኛ ቁጥርና ጥራት ያለው የጦር ሠራዊት ማደራጀት የሚል ነበር::"

"እርግጥ እቅዱ ሃሳቡ አዲስ አይደለም፤የዩጋንዳው ኢሚን ሲለፍፈው የቆየው ሃሳብ ነው:: ለአሚን ደቡብ አፍሪካን ነፃ ማውጣት ቀዳሚ ዓላማ ይሁን እንጂ የሰውየው የሩቅ ግብ አንድ አህጉራዊ የመከላከያ ሃይል መፍጠር የሚል ነበር::"

"አፊን ሞልቼ መናገር ባልችልም ይህ ዕቅድ የአስራ ዘጠኝ ዘጠና ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት የአፍሪካ ፖለቲካ ውጤት ነው ለማለት እችላለሁ:: ወደኋላ ካስታወስክ እነዚያ ዓመታት በላይቤርያ፣ በሱማሌ፣ በአልጀሪያ፣ በኢትዮጵያ፣ በሩዋንዳና በብሩንዲ በሌሎችም የአፍሪካ አገሮች የእርስ በርስ ጦርነት የታዩባቸው...በሺህና በሺህ የሚቆጠሩ የሞቱባቸው በሚሊዮንና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተሰደዱባቸው ዓመታት ነበሩ:: ሆኖም እነዛ ዓመታት አስተምረውን ያለፉት ነጥብ ነበር:: በተለይ በላይቤርያ የውስጥ ብጥብጥ የጥቂት ምዕራብ አፍሪካ አገሮች ወታደራዊ ትንጅት የነበረው ኤኮሞግ ያደረገው ሁላም የማስፈን ጥረት 'አፍሪካ አህጉራዊ የመከላከያና የፀጥታ ሃይል ያስፈልጋታል፤ ይህም በተግባር ሊተረጎም የሚችል ነው' የሚለውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነበር:: እና እንዳልኩህ ሰውየው ዕቅዱን አቀረበ:: ካቀረበም በኋላ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ምን ዓይነት ጥናቶች እንደተደረጉና መሪዎችም በምን በምን ነጥብ ላይ እንደተስማሙ አይታወቅም፤ብቻ ሰው የው በአፍሪካ አገሮች ሁሉ በሰውር ጽህፈት ቤቶች ከፍቶ የተመረጡ መኮን ኖች እየተሰበሰቡ የአፍሪካ የመከላከያ ሃይል ጥንስስ 'ቆንጆዎቹ' በሚል መጠ ሪያ ይጠነሰስ ጀመር::"

"ቀጥል::" አለ ናትናኤል ካልቨርት ድንገት ዝም ሲልበት::
"ይቅርታ... ከአረቄው ትንሽ ብትሰጠኝ..."
"አይሆንም... በንፁህ አእምሮ ነው እንድታወራልኝ የምፈልገው::"
"አወራለሁ' አወራለሁ' አንድ መለኪያ ብቻ::" አለ ካልቨርት እጁን እያራገበ::

ናትናኤል ተነስቶ ከአረቄው ጠርሙስ አንድ መለኪያ ቀንሶ ለካልቨርት አቀበለው::

"ሀ!..." አለ ካልቨርት በመጀመሪያው ሙከራ የመለኪያውን ግማሽ ቁልቁል ልኮ:: "እና እንዳልኩህ 'የቆንጆዎቹ' መሠረት በእያንዳንዱ አፍሪካዊ አገር ተጣለ፤የግንባታ እንቅስቃሴውም በስውር ይጣደፍ ጀመር:: እንቅስ ቃሴው በስውር የተደረገው የባዕድ እጅ ከጅምሩ እንዳያኮላሸው ነበር:: በዚህ ጊዜ በየአገሮች ያሉት የአካሉ ቅርንጫፍ ክፍሎች በዚያው በሚገኙበት አገር የመከላከያ ሚኒስቴር ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሲሆኑ መመሪያም የሚሰጣቸው በየአገሮቹ ባሉ የመከላከያ ሚኒስቴሮች ውስጥ ለዚሁ ጉዳዩ በተደራጁ ልዩ ክፍሎች ነበር::



"ዝግጅቱ በተጀመረ በሦስተኛው ወር ምሥጢሩ አፈትልኮ ተገኘ:: ማን አወጣው? እንዴት አወጣው? የሚታወቅ ነገር የለም::ብቻ በእንግሊዞቹ ኦብዘርቨርና በፈረንሳዮቹ አፍሪካን ዲፌንስ ላይ የዕቅዱ ፍንጭ ታትሞ ወጣ:: እውነቱን ንገረኝ ካልክ ምሥጢሩን ያወጣው የዕቅዱ ጠንሳሽ እራሱ ነበር::"

"እንዴት? የገዛ ምሥጢሩን ለምን?"

"ቆይ... ዝም ብለህ ተከተለኝ... እርግጥ ይህ የእኔ መላምት ነው... ግን ዳር ስንደርስ አንተ እራስህ ተመሳሳይ መላምት ላይ እንደምትደርስ እርግጠኛ ነኝ:: እንዳልኩህ ምሥጢሩ አፈተለከ:: ይህ እንደተሰማ የተለያዩ የአፍሪካ ባለሥልጣናት ከወዲያ ወዲህ ሲሯሯጡ ሰነበቱ:: ውጤት - ወታደራዊ ዝግጅቱ እራሱን በቻለ ምስጢራዊ መልክ እንዲካሄድና በማን ኛውም አገር የሚገኝ ቅርንጫፍ ክፍል በቀጥታ ከዋናው ማዘዣ ካልሆነ በስተቀር በሚገኝበት አገር የመከላከያ ሚኒስቴርም ሆነ ሌላ መንግሥታዊ አካል ጣልቃ ገብ ቁጥጥርም ሆነ ተፅዕኖ እንዳይደረግበት ስምምነት ላይ ተደረሰ::

"ዓላማው ዝግጅቱን አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ለማፋጠንና ምሥጢሩም እንዳይባክን ለመጠበቅ ተብሎ የተቀየሰ ነበር:: በሌላ መልኩ ለተመለከተው ደግሞ ስምምነቱ አገሮች በተናጠል በክልላቸው ውስጥ በሚደረገው ወታደራዊ ዝግጅት ላይ መረጃ እንዳያገኙ የሚያግዳቸው ሆነ:: ይህንን ስምምነት ተቃውሞ የሚቆም አገር ደግሞ ቀደም ሲል የተከሰተው አይነት የምሥጢር መዝረክረክ እንደማይፈጠር ማረጋገጫ ማቅረብ ሊኖርበት ሆነ:: የዚህን ዓይነት ዋስትና መስጠት ደግሞ ለማንኛውም አገር አዳጋች ነው:: ያም ሆነ ይህ ምሥጢሩ በጨቅላ ደረጃው በማፈትለኩ ከዛ በኋላ የወታደራዊ አካሉ እቅስቃሴ ሁሉ ከአገሮች ቁጥጥር ውጭ በምስጢር ለመሆን በቃ:: ይህን ነበር የፈለገው የዕቅዱ ባለቤት-እንቅስቃሴውን ያለታዛቢ በቀጥታና በምስጢር መምራት:: ከዚያ ጊዜ በኋላ የአፍሪካ መሪዎች የሚያገኙት መረጃ ሁሉ ከዋናው ማዘዣ በሚተላለፉ ዘገባዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ሆነ:: በሌላ ቋንቋ የአፍሪካ መሪዎች የሚያውቁት የእንቅስቃሴው መሪ እንዲያውቁ የሚፈቅድላቸውን ብቻ ሆነ:: ይህም እያንዳንዱ አገር አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ ኤምባሲው ባስቀመጠው የወታደራዊ አታሼው በኩል ብቻ የሚፈጸም ነበር::

"የወታደራዊ አካሉ መረብ እየሰፋና እየተጠላለፈ በመጣ ቁጥር በየአገሩ የሚገኙ እውቀት ችሎታና ተሰሚነት ያላቸው የጦር ባለሙያዎች በጥንቃቄ እየተጠኑና እየተመዘኑበዚሁ አካል ይዋጡ ጀመር:: ብቻ ምን ልበልህ...በሁለት ዓመታት ውስጥ እጅግ ጠንካራ፤ እጅግ ሰፊ፤ እጅግ ምስጢራዊ ወታደራዊ አካል አፍሪካ ውስጥ በስውር ተገንብቶ አበቃ:: አልፎ አልፎ አንዳንድ ባለስልጣኖች የወታደራዊ አካሉን አለቅጥ ምስጢራዊ መሆንና መግዘፍ የመቃወም ፍንጭ ቢያሳዩም ያለምንም ምህረት በተናጠል

እየተለቀሙ ተወገዱ:: ከዚህ ወዲያ ማንኛውም ምስጢሩን የሚያውቅ ባለሥልጣን ድምፁን ዝቅ አድርጎ መናገርን መረጠ::"

"ይህን 'አካል' የምትለውን ማነው የሚመራው?" ናትናኤል ጠየቀው::

"በትክክል እነማን እንደሆኑ አላውቅም...ግን ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ የተውጣጡ የጦር አባሮች እንደሆኑ አውቃለሁ::"

"እሺ. ቀጥል::"

"ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ ከሁለት ወር በፊት ወደ አገሬ ተጠራሁ:: አገሬ ውስጥ የቆየሁት ግን ለአራት ሰዓታት ብቻ ነበር:: ሞቃዲሾ እንደደረስኩ ወደ መከላከያ ሚኒስቴር ተወስጄ ስለዚሁ አካል መጠነኛ ገለፃ ከተደረገልኝ በኋላ ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት ግልጋሎቴን ለዚሁ አካል እንደምሰጥና ተጨማሪ መመሪያዎችንም ለመቀበል ወደ ሌላ ስፍራ የምወሰድ መሆኑ ተነገረኝ::

"እንዳልኩህ ሞቃዲሾ ከደረስኩ ከአራት ሰዓታት በኋላ በሌላ አነስተኛ አውሮፕላን የሁለት ሰዓታት ጉዞ አድርጌ ከአንድ በረሃማ ቦታ አረፍን:: ቦታው የቱ እንደሆነ ለመናገር ያስቸግራል:: እርግጥ ባንዲራ ተሰቅሎ ይውለበለባል ግን ባንዲራው አንድ ነው፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባንዲራ::

"ከአውሮፕላኑ እንደወረድኩ ማረፊያ ቦታ ተሰጠኝ:: ከእኔ ቀደም ብለው የደረሱ ነበሩ፤ እኔ ከገባሁ በኋላም ሌሎች በተከታታይ ከተለያዩ አገሮች በሄሊኮፕተሮችና በአነስተኛ አውሮፕላኖች እየተጫኑ ገቡ:: በማግስቱ ፕሮግራሙ ተጀመረ:: በአጠቃላይ አስራ አንድ ነበርን:: በኋላ እንደተረዳሁት ሁላችንም በአዲስ አበባ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ኤምባሲዎች ውስጥ እንድንሰራ የተመረጥን ነበርን:: እንደውም አንድ ሁለቱን አዲስ አበባ ውስጥ ቀደም ብዬ አውቃቸው ስለነበር እዛ በረሃማ ቦታ በቆየሁባቸው ጥቂት ቀናቶች ልቀርባቸው ችዬ ነበር:: በነገራችን ላይ የሞሮኮ ወታደራዊ አታሼ የነበረው መሃመድ ባስሪ እኔ በነበርኩባቸው ቀናቶች እዛው ነበር:: ወደ አዲስ አበባ በተመለሰ በወሩ ከጊኒው ሰው ጋር ተገድሎ ተገኘ::"

"ምን ላይ ነበር የፕሮግራሙ አትኩሮት?» ናትናኤል ወደፊት አዝምሞ ጠየቀው::

"ዝርዝር ነጥቦች ውስጥ አልገባም:: በአጠቃላይ የቆየነው ለሁለት ሳምንታት ነበር:: በመጀመሪያው ሳምንት በአፍሪካ ወቅታዊ ችግር ላይ ነበር ያተኮርነው:: በሁለተኛው ሳምንት ግን ስለ 'ቆንጆዎቹ'ና ስለዓላማው፤ ስለአን



ቅስቃሴው ነበር በጥቅሉ:: በአጭሩ ከመጪው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ በኋላ የአፍሪካ መንግሥታት እንደማይኖሩ ነበር የተገለጸልን::»

"ምን ማለት ነው ይሄ?" ናትናኤል ግራ ገባው::

"ነገርኩህኮ ከጥቂት ቀናት በኋላ የምትኖረው አፍሪካ አንድ አፍሪካ ብቻ ትሆናለች::"

"እንዴት? አልገባኝም::" ናትናኤል የሚያዳምጠው ቅዠት መሰለው::

"የስብሰባው ጊዜ ሲደርስ ጠቅላላ የአፍሪካ መሪዎች ተጠቃለው አዲስ አበባ ይገባሉ:: ይህ ከተገባደደ በኋላ በመላው አፍሪካ በየአገሩ ያሉ የአካሉ ቅርጫፍ ክፍሎች በያሉበት አገር ውስጥ መፈንቅለ መንግሥት አድርገው ሥልጣን ይጨብጣሉ:: ከዚያ በኋላ ማንኛውም መመሪያ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ይወጣል:: በአዲስ አበባ በየአገሮች ኤምባሲዎች ውስጥ በሚገኙ ወታደራዊ አታሼዎች አማካኝነት መመሪያዎች እንደአስፈላጊነቱ ለየአገሮች ይተላለፋሉ:: አበቃ::"

"እንዴ! ስንት መፈንቅለ መንግሥት ማለት ነው?" ናትናኤል ካልቨርትን አተኩሮ ተመለከተው:: ሰውየው ድጋሚ የሰከረ መሰለው::

"ሃምሳ ሦስት::"

"የፈጣሪ ያለህ! ይህኮ እልቂት ነው፤ ሃምሳ ሦስት አገሮች ውስጥ ጦርነት መፍጠር እኮ ማለት ነው::መቼም ሁሉም አሜን ብሎ አይቀበልም:: ጦርነት ይኖራል::"

"እልቂት አይደለም:: ይኸው አካል ተብትቦ ያልያዘው ወገን በዝብዞ ያላወቀው ምስጢር በየትኛውም አገር አታገኝም:: ውስጥ ውስጡን በየአገሩ ጠንካራና ተሰሚ ደጋፊዎች አሉት፤ ውስጥ ውስጡን የየአገሩን ደካማ ጎን አብጠርጥሮ ያውቃል፤እነማን መያዝ መታሰር...መወገድ አለባቸው? እነማን ሊታመኑ ይገባል? እነማን ባንዳዎች ናቸው? እነማን ዲቃላዎች ናቸው? እነማን ንፁህ አፍሪካውያን ናቸው? ሁሉ ይታወቃል::"

"አህጉራዊ መከላከያ የተባለውስ? ማለቴ..." ናትናኤል ግራ ገባው::

"ሽፋን ነው:: አየህ... ወታደራዊ አካሉ የአፍሪካ መንግሥታት እያወቁና ሙሉ ድጋፍ እየሰጡት በምስጢር ለመንቃነቅና የዚህን ዓይነት ስፋት ያለው ወታደራዊ ዝግጅት ለማድረግ በየአገሩ የሚገኙትን ከፍተኛ መኮንኖችን በስሩ ለማሰባሰብ አንድ ተቀባይነት ያለው ሽፋን ያስፈልገው ነበር:: አህጉራዊ የመከላከያ ሃይል ተስማሚ ሽፋን ነበረ::"

"እና የአፍሪካ መንግሥታት ሁሉ ስለእንቅስቃሴው ምንም አያውቁም ማለት ነው?"

"ያውቃሉ::ዝግጅቱ ሁሉ ተቀነባብሮ በየአገሩ ያሉ ቅርንጫፍ አካላት በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ያውቃሉ::በእቅዱ መሠረት መሪዎች ለአ.አ.ድ. ዓመታዊ ስብሰባ በሚገናኙበት ዕለት ሌሊት የአፍሪካ አህጉራዊ የመከላከያና የፀጥታ ሃይል መቋቋሙን ለመላው ዓለም ይፋ እንደሚደረግ በማመን ይጠባበቃሉ:: የቀረበላቸውና ያፀደቁት ምስጢራዊ እቅድ ይህ ነው:: የሆነው ግን ይህ ብቻ አይደለም:: መሪዎች ወደ አዲስ አበባ ተጠቃለው እንደገቡ በየአገሩ ያሉ የመከላከያ ሃይሉ ቅርንጫፍ ሃይሎች በያሉበት አገር መፈንቅለ መንግሥት አካሂደው ሥልጣን ይረከባሉ፤ሠላም ያስከብራሉ፤አንድነታችንን ይከላከላሉ:: ይህ እንደተፈፀመ የመከላከያ ሃይሉ ብቻ ሳይሆን የአንዲት አፍሪካ መወለድ ለዓለም ይበሰራል::"

"እብደት! እብደት ነው ይሄ!" ናትናኤል ሊከተል የሚችለው እልቂት ሲታሰበው ጆሮዎቹን ማመን ጠላ:: "በቅድሚያ የአፍሪካ ሕዝብ ስሜት ሳይጤን እንዴት? ይህ ራሱ ዲሞክራሲን ማፈን ነው! እብደት ነው! ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ይህን አያቅድም!"

"ምኑ ላይ ነው እብደቱ?"

"አንድነት በሃይል አይመጣም::ውህደት በጉልበት አይፈጠርም:: ሃይል የሚወልደው ጥላቻን ነው::ጥላቻን ልታዳፍነው ትችላለህ! ልታዘገየው ትችላለህ:: ጊዜውን ጠብቆ ሲገነፍል ግን በተራው ሃይልንና በቀልን ይወልዳል! ጥፋትን ይወልዳል... እብደት ነው ይሄ!"

"እብደት አይደለም:: ይህ ነው የአፍሪካ ተስፋ:: በአንድነት እስካልቆምን ድረስ በተናጠል ለባርነት መሸጥ ነው ዕጣ ፈንታችን:: ምንድነው ዲሞክራሲ? መበታተን? መከፋፈል? የነጮች መሣሪያ መሆን? እርስ በርስ መናቆር ነው ዲሞክራሲ?" አለ ካልቨርት የተቀመጠበትን ፍራሽ እየደበደበ::

"ዲሞክራሲ የሕዝብ ስሜት ነው...ዲሞክራሲ የሕዝብ ፈቃድ ነው... ህሊናቸውን የሳቱ ጠረኞች... መሣሪያ ያነገቱ እብዶች...አንድነትን አያመጡም...ዲሞክራሲን አያስፍኑም!» ናትናኤል በስጨት ብሎ አቋረጠው::

"ዲሞክራሲ የሕዝብ ስሜት ከሆነ የአፍሪካ ሕዝብ ስሜት ምንድነው? ወገን ለይቶ መካሰል? ዘር ተቆጥሮ ጎሳ ተቋጥሮ የጎሪጥ መተያየትና መተላለቅ ነው የአፍሪካ ሕዝብ ስሜት? ወይስ በጋራ ቆሞ የጋራን ችግር መፍታት?"



"ደም የጠማቸው አውሬዎች የአፍሪካን ሕዝብ ችግር አይፈቱም!" አለ ናትናኤል በስጨት ብሎ:: "ይህ እብደት ነው! ታያለህ! ውጤቱም አይሰምርም:: በኃይልና በአፈና የባሰ ውድቀት ማምጣት ነው::"

"ምናልባት እብደት ይሆናል:: ቢሆንም አስተውል:: የአፍሪካ ሕዝብ ካለፈው ውርደትና ጉስቁልና በኋላ ቢያብድና ጠላቶቹን ሊበቀል ቢነሳ ምኑ ላይ ነው ስህተቱ? ውሻ እንኳን ዱላ ከበዛበት የገዛ ጌታውን ሊናከስ ይነሳል! እብድ ይሆናል:: የአፍሪካ ሕዝብ ታግሶ አበደ ... ምናልባት... ግን አስተውል ከዚህ በኋላ የቀድሞዋን አፍሪካ አናያትም:: የቀድሞዋ አፍሪካ ማለፍ ማብቃት ደግሞ ምኞቴ ነው:: አየህ... ጠላቶቻችን ቀድመው ማሰብ ነበረባቸው:: ይህ ጥቁር ህዝብ ታግሶ ታግሶ... ቢያብድስ ቢገነፍልስ ብለው ማስተዋል ነበረባቸው:: ዘገዩ:: አበድን:: ምኑ ላይ ነው ስህተቱ?" ካልቨርት አፈጠጠ::

"አንተም ትደግፋቸዋለህ ማለት ነው?" ናትናኤል የሚያዳምጠውን ማመን አቃተው::

"በደንብ!... ለኔ ይህ ነው ዲሞክራሲ:: በአንድነት መቆም እጅ ለእጅ መያያዝና ካሰንበት ማጥ ተደጋግፎ መውጣት ነው ዲሞክራሲ!"

"ታዲያ ለምን ጥለህ ጠፋህ?" ናትናኤል አፉን ከፍቶ ቀረ::

"አላስጨረስከኝምኮ...ዝም ብለህ ስማኝ...እንዳልኩህ ለሁለት ሳምንታት በዚያው በረሃማ ቦታ ስለእያንዳንዳችን የሥራ ድርሻ ጥንቃቄ የተሞላው ገለፃ ተደርጎልን በስብሰባው ዕለት እያንዳንዳችን በአዲስ አበባ በሚገኙት የየአገሮቻችን ኤምባሲዎች በበላይነት በመቆጣጠር አ.አ.ድ. የሚገኘውን የበላይ አካል በየአገራችን መፈንቅለ መንግሥት አድርጎ ሥልጣን ከሚይዘው ኃይል ጋር የምናገናኝበትን መስመርና ሰዎችን፤ የምስጢር ስሞችን የሬድዮ፤ ሞገዶችን፣ ኮዶችንና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ ተቀብለን በተለያዩ አውሮፕላኖች በመጀመሪያ ወደየአገሮቻችን ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ተመለስን::" ካልቨርት ከተቀመጠበት ተነስቶ መለኪያውን በአረቂ ሞላው::

"ለኔም ስጠኝ::" አለ ናትናኤል እጁን ወደፊት ዘርግቶ::

"እዚህ ከደረስኩ በኋላ ያላሰብኩት ችግር ተፈጠረ::" ካልቨርት የአረቄውን ጠርሙስ ወደ ጥግ አስቀምጦ ናትናኤል አጠገብ ፍራሹ ላይ ተቀመጠ:: "ቀደም ሲል መረጃ አቀብላቸው የነበሩ የእንግሊዝ መረጃ ሰዎች ወጥረው ያዙኝ:: የተጠራሁበት ምክንያት ያን ያህል ምስጢራዊ እንዳልሆነ አድርጌ የሃሰት መረጃ ልመግባቸው ብሞክርም ሊቀበሉኝ አልቻሉም:: አላመኑኝም! አልፈው ተርፈው መረጃውን በፍጥነት ካላቀረብኩ ቀደም ብዬ

የሠራሁትን ጥፋት ለአገሬ መንግሥት እንደሚያሳውቁ አስጠነቀቁኝ:: በዚህ ላይ እንዳለን የጊኒና የሞሮኮ አታሼዎች ተገደሉ::

"አየህ... እኔ ምስጢሩን ሳወጣ አልፈለግሁም:: እርግጥ በአንድ ወቅት በገዛ አገሬ ላይ ስልያለሁ:: በመላው አፍሪካ ላይ ይህን በደል ልፈጽም አልቻልኩም:: የምከዳው አንዲትን አገር ሳይሆን መላውን አፍሪካ ነበር:: እንዳስፈራሩኝ ከዚህ ቀደም የሰራሁትን ወንጀል ቢያወጡ ደግሞ ያለጥርጥር እንደጊኒና ሞሮኮ ወታደራዊ አታሼዎች መሰበሬ ሆነ:: ተሰወርኩ::" ካልቨርት የያዘውን ግማሽ መለኪያ አረቄ ጨለጠው::

"የጊኒና የሞሮኮ አታሼዎች ምስጢር አውጥተው ነው ማለት ነው ለሞት የበቁት?" አለ ናትናኤል ፊቱን አኮማትሮ::

"በእርግጥ አላውቅም... ግን ሊሆን ይችላል:: አየህ... ይኸው አካል የተጠናከረ የመረጃ መረብ አለው:: ከፍተኛ ቁጥጥርም ያደርግብናል:: ምንም እንኳን ቀደም ብሎ ስለእያንዳንዳችን ጥልቅ ጥናት የተደረገ ቢሆንም አንዳንድ ያልታሰቡ ሁኔታዎች ለመቋቋም ሲባል ይከታተሉናል:: አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ በሁለቱ አታሼዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ከፍተኛ የአፍሪካ ባለሥልጣናት ላይም የተፈጸመውን ግድያ ከመፈጸም ወደኋላ የሚል ኃይል አይደለም::ብቻ ሁለቱ አታሼዎች ምስጢር አውጥተዋል ብዬ ለመናገር ያዳግተኛል:: አውጥተውት ቢሆን እስካሁን ብዙ መፍረክረኮች ይከተሉ ነበር:: ቢሆንም እምኔታ እስከታጣብን ድረስና የአንተ መኖር ለአፍሪካ ስጋት እስከሆን ድረስ ያለማመንታት ትወገዳለህ:: ብዙዎቹ ተወግደዋል:: ለዚህ ነው ከሁሉ የተሰወርኩ፤ከምደግፋቸውም ከምፀየፋቸውም የተሰወርኩ::እኔም እንደሌላው አፍሪካዊ አፍሪካ አንድ ሆና ማየት እፈልጋለሁ::"

"በመጀመሪያ ለሌላ ባዕድ ድርጅት መስራትህን እንዴት ሳይደርሱበት ቀሩ?"

"ስህተት ነው:: ስህተት ነው የፈፀሙት:: እርግጥ ጠንቃቃ ነበርኩ፤ ቢሆንም መሳሳታቸው በጊዜው እኔንም ያስደነገጠኝ ጉዳይ ነበር::"

"ከጠፋህስ በኋላ እንዴት ሊያገኙህ አልቻሉም? ማለቴ መንግሥት የሚደግፋቸው እስከሆነ ድረስ አንተን ማደን ያን ያህል አስቸጋሪ አይሆንም... ሌላውን ብንተወው እንኳን አድራሻህን እንድትነግራቸው የምሥራችን ሊያስገድዷት ይችሉነበር:: እኔኮ ግራ የሆነብኝ ይህን ያህል በመላው አፍሪካ እየተርመሰመሰ ያለ ኃይል አድኖ ሊያገኘው ያልቻለውን ሰው እንዴት እኔ ላገኝህ ቻልኩ?"

"ሊያገኙኝ ያልቻሉት ስላልሞከሩ ብቻ ነው::ለመሰወር እንደቆረጥኩ ከዚህ በፊት ያጠፋሁትን ጥፋት በገዛ አገሬ ላይ የሰራሁትን ወንጀል በሙሉ



ዘርዝሬ በጽሁፍ አስተላለፍኩላቸው::ይህንንም ያለፈ ጥፋቴን እንደማስፈራሪያ በመጠቀም የባዕድ የስለላ ድርጅቶች ምስጢሩን ከእኔ ለማግኘት በመጣር ላይ መሆናቸውንና ምስጢሩን አውጥቼ ከዳተኛ ከመሆን አለበለዚያም ነጮቹ ያለፈ ስራዬን ይፋ አውጥተው ለጥፋት ሳይዳርጉኝ በፊት ለመጥፋት መወሰኔን ገለጽኩላቸው:: ሆኖም እኔን አድነው ለማግኘት ቢጥሩ ወይም የምሥራችን ለማስገደድ ቢሞክሩ ደብቄ የያዝኩት ምሥጢር የጋዜጦች ቀለብ እንደሚሆን አስፈራራኋቸው::" ካልቨርት በቀኙ የጨበጠውን ባዶ መለኪያ አተኩሮ ተመለከተው:: "ለዚህ ነው ሳይተናኮሉኝ ባለሁበት ሊተውኝ የመረጡት:: ድምጼን አጥፍቼ ጭንቅላቴን ቀብሬ ሰዓቷ እስክትደርስ ከታገስኩ ከዚያ ወዲያ ሊበቀሉኝ እንደማይሞክሩ እርግጠኛ ነበርኩ:: ምክንያት አይኖራቸውማ:: ለምስጢራቸው ደህንነት ስል ነዋ የተሰወርኩት::"

"ታዲያ የምሥራችን ለምን ገደሏት?"
"እመነኝ እነሱ አይደሉም የገደሏት... ነጮቹ ናቸው::"
"እነማን ናቸው ነጮቹ?"
"እንግሊዞቹ እስራኤላውያኑ... አላውቅም"
"እንዴት... ለምን?"
"እኖህ እንዳልኩህ ከመጥፋቴ በፊት በምሥራች ላይ አደጋ ቢደርስ ምሥጢሩን እንደማወጣ ዝቼ ስለነበር ጥበቃ ይደረግላት ነበር በስውር::"

"በማን?"
"በቆንጆዎቹ::"
"ማን እንዳይጎዳት?"
"በብስጭት ምሥጢሩን ይፋ እንዳደርገው ሲሉ ነጮቹ የምሥራችን ሊያፍኗት ወይ ሊገሏት ይችላሉ ብለው በመፍራት ይመስለኛል:: አንተም ከሆቴሏ ድረስ ሄደህ አንድ ክፍል ውስጥ አስገብተሃት ስትዘጋ የነጮቹ ቅጥረኛ መስለሃቸው አንድ ነገር እንዳታደርጋት በመፍራት ይሆናል ቆንጆዎቹ ሊያቆሙህ የሞከሩት::"

"ግን እንዴት ነው ነገሩ?" ናትናኤል ግራ ተጋባ:: "ያ የባዕድ የሆነ የስለላ ድርጅት ኢትዮጵያውያንን መልምሎ አሰማርቷል ማለት ነው? የገደለቻት ሴትኮ ያለ ጥርጥር ኢትዮጵያዊት ነች::" አለ ናትናኤል ሲቲና ፊቱ ላይ ግጥም ስትልበት::

"አይደለም-አይደለም::" አለ ካልቨርት የናትናኤል ውሱን እውቀት ነገሩን ሁሉእንዳዘበራረቀበት ሲረዳ:: "ለነጮቹ የስለላ ድርጅት በአዲስ አበባ ውስጥ የመስክ ስራ እየሠራለት ያለው ሞሳድ ነው:: እሥራኤል ቀደም ሲል ከዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የኢትዮጵያ አይሁዳውያንን መልሳ ወደ አዲስ አበባ በብዛት አስገብታ የመረጃ ስራ እያሰራቻቸው ነው::"

"ለምን?" ናትናኤል አቋረጠው፡፡ "እሥራኤል ለምን ብላ ለነጮቹ ትሠራለች? ከኢትጵያ ጋር ያላት ግንኙነት መጥፎ አይደለም፤እንደውም ግንኙነታችን ከመቼውም ጊዜ የተሻለ ነው፡፡"

"የስለላ መረብ የምትዘረጋው በጠላትህ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ ስለላ በእጭሩ መረጃዎችን መሰብሰቢያ መንገድ እንጂ የግድ አንዱ ለአንዱ ካለው ጥላቻ የሚመነጭ አይደለም፡፡አስታውስ...እሥራኤል በ1980ዎቹ መጨረሻ በዋንኛ ደጋፊዋ በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ሳይቀር ስለላ ስታካሂድ ተደርሶባታል፡፡ አይደለም፡፡ እሥራኤል ከኢትዮጵያ ጋር ካላት ግንኙነት ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡"

"ታዲያ ለምን?" ናትናኤል አፈጠጠ፡፡

"በመጀመሪያ ነገሩ የተለመደ ነው፡፡የተለያዩ የመረጃ ቤቶች አንዱ ለአንዱ ውለታ መፈጸሙና መረጃ መለዋወጡ የተለመደ ነው፡፡ ግን እሥራኤል እዚህ ውስጥ እጇን የከተተችው ለራሷ ስትል ነው፡፡ አየህ አፍሪካ ተባብራ ለመንቀሳቀስ ከቻለች ምናልባት በግብጽና በጥቂት የሰሜን አፍሪካ አገሮች ገፋፊነት አጥፊ እርምጃ በእርሷ ላይ እንዳይፈጸም የሰጋች ይመስለኛል... ለዚህ ነው ሁኔታውን ከወዲሁ ለመከታተል የመረጠችው፡፡"

"እና... የምሥራችን የገደሏት..."
"ቀንጆዎቹ አይደሉም፡፡ የነጭ ጠላቶቻችን ናቸው፡፡" አለ ካልቨርት አቋርጦ፡፡

"ታዲያ አሁን ምን ልታደርግ ነው? ምሥጢሩን ልታወጣ ነው ወይስ...?"

ካልቨርት ጭንቅላቱን ነቀነቀ፡፡

"ስታየኝ ጅል እመስላለሁ? በፍጹም! ሊያታልሉኝ ሲሞክሩ... እንዳችንን በአንዳችን ላይ ሊያነሳሱ ሲሞክሩ እያየሁ እንዴት እጃጃላለሁ?"

"ጥሩ፡፡ አሁን ምንድነው ማድረግ ያለብን?" ናትናኤል ዙሪያው ድቅድቅ ጨለማ ሆነበት፡፡
"መጠበቅ፡፡"
"ምኑን?"
"ቀኑን፡፡"
"የቱን ቀን?"
"የስብሰባውን ቀን፤ አፍሪካ አንድ የምትሆንበትን..."



"አንችልም!" ናትናኤል ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ ተነሳ፡፡
"ለምንድነው የማንችለው...የቀሩን ሦስት ቀናት ብቻ ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ነፃ ነን፡፡"

"ይይዙናል!" አለ ናትናኤል በጭንቀት ተወጥሮ፡፡
"አያገኙንም፡፡"

"ያገኙናል፡፡ ባቡር ጣቢያው ድረስ ተከታትለውኛል ! አይቼዋለሁ፡፡ ሽጉጡን ከትከሻው በላይ ይዞ ሊቀጥፈኝ ሲንደረደር እነዛን አይኖቹን አይቻቸዋለሁ! ትሰማኛለህ? ! ድጋሚ ካገኘኝ ስሜን እንኳን አይጠራም፡፡ በጆሮ ግንዴ ነው የሚለቅብኝ! ትሰማኛለህ? ! መሞት አልፈልግም፡፡ በጤና ከቤቴ መመለስ ነው የምፈልገው!" ናትናኤል ሰውነቱ ሳይታወቀው ከቁጥጥሩ ውጭ ሲሆንበት ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ግጥም አድርጎ ይዞ መሃል ወለሉ ላይ ቆመ፡፡

"ቁጭ በል..." አለ ካልቨርት በእርጋታ፡፡ "ቁጭ በል ናትናኤል... ለህይወትህ መሳሳት የነበረብህ አሁን አይደለም፡፡ ዘግይተሃል፡፡ እንደነገርከኝ ያኔ ገና ድሮ የጓደኛህን ማስጠንቀቂያ ሰምተህ ከእሳቱ ብትሸሽ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ አሁን ግን መሸሽ የለም፤ ማፈግፈግ አይገኝም፡፡ ከውስጡ ነህ፤ ከረመጡ፡፡"
"ማምለጥ እንችላለንኮ፡፡" አለ ናትናኤል ልመና የተቀላቀለው በሚመስል ድምፅ፡፡

"ወዴት?"
"የትም፡፡ ብቻ ከድሬዳዋ መውጣት አለብን፡፡" ናትናኤል ራመድ ብሎ ፍራሹ ላይ ከካልቨርት ጎን ተቀመጠና አተኩሮ ተመለከተው፡፡ "የትም ይሁን... ብቻ ከዚህ መራቅ አለብን፡፡ አለበለዚያ ያገኙናል፡፡"

"እስካሁን ለምን ሊያገኙን አልሞከሩም? አታስብ፡፡ አሁንም ሊያድኑን አይሞክሩም፡፡"

"ተሳስተሃል! አይተውኛል፡፡ ወደ አንተ መምጣቴን ሊጠረጥሩና እንዳላገኝህም ሊፈሩ ይችላሉ፡፡ምስጢሩን ከአንተ ካገኘሁት ይፋ እንዳላወጣው ሊሰጉ ይችላሉ፡፡ ይህ ፍራቻ ደግሞ ባላቸው ኃይል እንዲያድኑን ያስገድዳቸዋል፤ አትጠራጠር ያገኙናል፡፡"

"መጀመሪያ ነገር ወዲህ እንደምትመጣ እንዴት ሊደርሱበት ቻሉ?" አለ ካልቨርት ዓይኖቹን አጥብቦ፡፡

"አላውቅም! እንደነገርኩህ ነው:: ምናልባት ከፍቅረኛዬ ቤት ሸሽቼ ሳመልጥ አይተውኝ ይሆናል፤ አለበለዚያም ባቡር ጣቢያ ዓይን ነበራቸው ማለት ነው:: አላውቅም::"

"ለፍቅረኛህ ወደዚህ እንደምትመጣ ነግረሃታል?"
"የት አግኝቻት! ነግሬህ የለም እንዴ? ከውጭ ነው የተመለስኩት:: የአፓርትመንቷ በር ላይ አድፍጠው ይጠባበቁኝ ነበር::"

"ወደሷ መሄድ አልነበረብህም:: እሷንም አደጋ ላይ ነው የጣልካት::"
"እሷንስ አይነኳትም::" አለ ናትናኤል እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ::
"ለምን?"
"ምንም አታውቅማ!"
"አለማወቋን የምታውቅ አንተ ብቻ ነህ::"
"ግራ ስትጋባ ሲያዩ ምንም እንደማታውቅ ይረዳሉ::"
"አይመስለኝም:: ምናልባት ከገረፏትና ካሰቃይዋት በኋላ አዎ::"

"የማይሆን ወሬ አታውራ!" አለ ናትናኤል የሚሰማው ወሬ ደስ የማይል ስሜት ሲፈጥርበት ሁኔታውን እንዳለ አለማሰቡን!" መከዳውን መርጦ::

"ምኑ ነው የማይሆን? በአሁኗ ሰዓት በእነሱ አይን ያንተ ፍቅረኛ ከኔ ፍቅረኛ የተለየች ሆና እንደማትገኝ አታውቅም::"
"ምን ለማለት ነው የፈለከው?"

"ምንም ለማለት አልፈለኩም::" አለ ካልቨርት የናትናኤልን ድንገት የተለዋወጠ ገጽ ሲመለከት:: "ብቻ...ወደሷ መሄድህ ጥፋት ነበር ነው ያልኩት:: አሁን ተወው:: ያለፈ ነገር ነው::"

"እንዴት ነው የምተወው? የምትለውኮ 'በአሁኗ ደቂቃ ርብቃን እየገረፉና እያሰቃይዋት ነው::' ነው!" አለ ናትናኤል ፊቱን አባጨጓሬ አስመስሎ::

"ቢሆን አይደንቀኝም::"

ናትናኤል አንጀቱ የተገለባበጠ መሰለው:: እስካሁን በአእምሮው ውስጥ ያልነበረ አዲስ ፍርሃት እንደ ስልባቦት እየረጋ እየተሸበሸበ እየተጠቀለለ ሆድ ዕቃውን ሲደፍነው ትንፋሽ አጠረው:: በባዶው ግድግዳ ላይ አፈጠጠ:: ገጽታዋና የሚወደው ያ ሴታሴት ፊቷ በእንባ ረስርሶ ፊቱ



ላይ ድቅን አለበት... በጥይት የተቀረደደ የየምሥራች ደረት... ታወሰው... ርብቃ!

"የት ነው የምትሄደው?" አለ ካልቨርት፤ ናትናኤል ከተቀመጠበት ድንገት ነጠላ ጫማውን ሲያጠልቅ ሲያየው::

"ስልክ እደውላለሁ::"
"የት?"
"አዲስ አበባ:: ርብቃጋ" አለ ናትናኤል ፊቱ ከስል መስሎ::
"እየመራሃቸው ነውኮ:: ይገባሃል? ስልኩን ጠልፈው በደቂቃዎች ውስጥ የት እንዳለን ሊረዱ ይችላሉ::"

"ይያዙኝ! ከዚህ በላይ መሸከም አልችልም:: ደውዬ አነጋግራታለሁ::"

በሩን ከፍቶ እንደወጣ የየምሥራችን እናት ከጓዳው በር ቆመው አገኛቸው::

"እንደምን አረፈዱ:: እባኮት የምሥራችጋ መደወል ፈልጌ ነበር... ስልክ..." የተረበሸ ስውነቱን በተቻለው መጠን ስመቆጣጠር ታገለ::

"በቁልቢው! ስልክ የት አለኝ ብለህ?"
"ሌላም ቦታ ቢሆን... የሚያውቁት ጎረቤት... ስልክ ያለው::እባኮት... የምሥራች ማወቅ ያለባት ጉዳይ ነው:: አለበለዚያ ችግር ላይ ትወድቅብናለች::"ተንተባተበ::

ሴትየዋ ለአንድ አፍታ በጭንቀት የነጣውን ፊቱን ትኩር ብለው ሲመለከቱት ቆዩ:: ያልተረዱት ስጋት ቀስ በቀስ የተጋባባቸው ይመስል "መጣሁ" ብለውት ወደ ጓዳ ገቡና ወዲያው ነጠላቸውን እያጠፉ ተመለሱ::

"ና... ከነስለሺ አለዚያም ከነአብዱራህማን ቤት ትደውላለህ::" አሉ ጎረቤቶቻቸውን ያውቅ ይመስል በስም እየጠሩቸው::

"ይሰማኛል ይሰማኛል ቀጥል።" አለ ጀነራሉ በሬድዮው መቀበያ ላይ አጎንብሶ።

በሬድዮው ክፍል ውስጥ የክፍሉ ሠራተኞች ያልሆኑ ባለሥልጣናት ከጀኔራሉ ጀርባ ቆመው ይጠባበቃሉ። ክፍሉ ውስጥ ያለው አየር ለክፍሉ ሠራተኞችና ከውጭ ተግተልትለው ለገቡት ለሁሉም የማይበቃ ይመስል እያንዳንዱ ሰው ትንፋሹን ይዞ በጭንቀት ተወጥሯል።

"ጀኔራል" አለ ከድሬዳዋ የቃል ሪፖርት የሚያደርገው አንድሬ አማሪ በሚንኮሻኮሸው የሬዲዮ መልዕክት ማስተላለፊያ ውስጥ "ኦፕሬሽኑ ያለምንም ችግር እየተካሄደ ነው። መውጫ በሮች ተዘግተዋል፤ ቃል የገባህልኝ የስልክ ግንኙነት ግን ገና አልተቋረጠም፤ ሰውየውን በተመለከተ አንዳንድ ፍንጮችን አግኝተናል። ከባቡር ጣቢያ ከሸሸ በኋላ የገባበትን መጠጥ ቤት አግኝተን ወደ አንድ ጋራዥ እንደመሩትና ከጋራዡም ባለቤት ጋር ተገናኝቶ እንደነበር ደርሰንበታል። ጊዜው የዓመት በዓል ስለሆነ የጋራዡን ባለቤት ለማግኘት እቤታቸው ድረስ ልጆቼን ልኬአለሁ። በተረፈ በተቻለኝ መጠን አትኩሮት ሳልስብ ፎቶግራፉን የያዙ ሰዎች በከተማው አሰማርቼ እያሰስኩ ነው።"

ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ የሚለው አንድሬ የደረሰበትን ደረጃ አንድ በአንድ በሬድዮው ውስጥ ሲያስተላልፍ አዲስ አበባ በሬድዮ መቀበያው ክፍል ያሉት ሁሉ በፀጥታ ሲያዳምጡ ቆዩ።

"አንድሬ" አለ ጀኔራሉ "ስልኩን ያላቋረጥኩበት ምክንያት እያንዳንዱን የውጭ ጥሪ እየተከታተልን ስለሆነ መረጃ ለማስተላለፍ ቢሞክር ግንኙነቱን አቋርጠን በስልኩ አድራሻ እንድናጠምደው ስል ነው። የቤት ለቤት ፍተሻ ለምን እንዳልጀመርክ ግን..."

"አስፈላጊ አይደለም።" አለ አንድሬ ጀኔራሉ መጨረሱን እንዳሳወቀው "በቀላሉ እጄ ላስገባው እችላለሁ። ከጋራዡ ከነባ በኋላ በተናጠል የአንድ ሰው አድራሻ ጠይቆ የጋራዡ ባለቤት እንዳመላከቱት ደርሼበታለሁ። የጋራዡን ባለቤት አግኝቼ አድራሻውን እስካገኝሁ ድረስ ምንም አስጊ ሁኔታ ይኖራል ብዬ አልገምትም።"

የሬድዮው መልዕክት ተላልፎ እንዳለቀ ከአንድ ሰዓት በኋላ በድጋሚ የሚቀርበው ሌላ የሬድዮ ሪፖርት እስኪደርስ ድረስ ከሬድዮው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው የነበሩ ሁሉ ጀኔራሉን ተከትለው ወጡ።





ናትናኤልና የየምሥራች እናት ከቤት ወጥተው በጠባቧ የከረኮንች መንገድ በዋናው መንገድ አቅጣጫ ራቅ ብለው ሄዱ። ከአንድ አነስተኛ ቤት እንደደረሱ የየምሥራች እናት ከባለቤቶቹ ጋር በኦሮምኛ ቋንቋ እየወሩ አስከትለውት ገቡ። ከቤት ከገቡ በኋላ የቤቱ ባለቤት ደርባባ ወፍራም ሴትዮ ከፊት ለፊቱ ድክ ድክ እያሉ ስልክ ወዳለበት ክፍል አስገቡት።

ናትናኤል የስልኩን እጀታ አንስቶ አዲስ አበባ ርብቃጋ ደወለ። የደወለበት ስልክ ሲነሳ ሁለት ጊዜ ቃ...ቃ... ሲል ተሰማው።

"ሃሎው..." አለው ወፈር ያለ የወንድ ድምጽ።
"እባኮት ርብቃን ነበር።"
"ናትናኤል ስልኩን እንዳትዘጋው። ልናነጋግርህ እንፈልጋለን።» አለ ያው ወፈር ያለ ድምጽ።
"ማነህ?"
"ማን እንደምሆን መገመት ትችላለህ። አብርሃምን አስታውስ... ሌሎቹንም አስታውስ... ርብቃ በእጃችን ነች።" ለአንድ አፍታ ሰውየው ዝም አለ። "የት ነው ያለኸው? ንገረኝ።"

"ጫፏን ብትነኳት ምስጢራችሁን እንደምነዛው እወቁ! ታዳምጠኛለህ?!" አለ ናትናኤል ድንጋጤውን በቁጣ ለመሸፈን እየታገለ።

"ናትናኤል አትችልም።ምንም መንገድ የለህም። ከድሬዳዋ የሚወጣ ማንኛውም የስልክ ጥሪና ፖስታ ሁሉም በቁጥጥራችን ውስጥ ነው። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በእጃችን ትገባለህ። ይህ ከመሆኑ በፊት በፈቃድህ ያለህበትን ቦታ ንገረኝ...ስማ..."

"ኮሎኔል ትንሽ ድምጽ እንፈልጋለን" አለ ሰውየው በሌላ ስልክ ውስጥ ለሚያዳምጠውና በርብቃ አልጋ ጎን ለቆመው ኮሎኔል ማርቆስ።

ናትናኤል የስቃይ ድምጽ ጆሮው ላይ እንጫረረበት ...እሪታ... የሴት ልጅ... የስቃይ እዬዬ...

"ሰማህ? ርብቃ ነች። ምን እያደረግናት እንደሆነ ልነግርህ አልሞክርም። እመነኝ እራስህን ትጠላለህ። ናትናኤል እመነኝ መፈጠርህን ትጠየፋለህ።ምስጢሩን ከካልቨርት እንዳገኘኸው እንገምታለሁ፤ ዓላማችን ለጋራ ጥቅም ነው። እጅህን ስጠን። ምንም ጉዳት አይደርስብህም።"

"ርብቃ ምንም አታውቅም!" ናትናኤል ስልኩ ውስጥ አምባረቀ።

"እዎ...ስለማታውቅ ነው ያለማቋረጥ የምናሰቃያት...በአንተ ኃጢያት አበሳዋን የምናሳያት። የምታውቀው ነገር ቢኖር በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ ማንኛውንም ምስጢር ደብቃ መያዝ አትችልም ነበር...ግን አሁንም እጅህን እስካልሰጠኸን ድረስ የጀመርነውን አናቋርጥም። አስታውስ...በማህፀኗ የያዘችውን።"

ናትናኤል በስልኩ ውስጥ ድጋሚ የስቃይና የጣር እሪታ ተሰማው።

"ናትናኤል..." ያው ድምጽ ቀጠለ። "ጊዜ የለንም። ያለህበትን ቦታ ንገረን። እዚህ እሷጋ እናመጣሀለን... እመነኝ።" ለሶስተኛ ጊዜ ያው የስቃይ ድምጽ በሩቁ በረጅሙ አንቋረረ። ናትናኤል ጉሮሮውን ተናነቀው፤ ጭንቅላቱን ነዘረው። ዓይኑ ተቁበረበረበት-

"ተዋት! ተዋት! በቃ ... ድሬዳዋ ነኝ"

"አውቃለሁ ድሬዳዋ መሆንህን። ግን ድሬዳዋ የት?"

"ሰፈሩን አላውቀውም። ትንንሽ ቤቶች ያሉበት አካባቢ ነው።" ናትናኤል ጭንቅላቱ ውስጥ የሚነዝረውን ስቃይ መቋቋም አቃተው።

"በአካባቢህ ምን የሚታይህ ነገር አለ? ሆቴል...ህንፃ... ማንኛውም ምልክት።"

"ቤት ውስጥ ነው ያለሁት። መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው።"

"ስልክ ቁጥሩን ንገረኝ።"

ናትናኤል የስልክ ቁጥሩን አነበበለት።

"ጥሩ። የትም ሳትነቃነቅ እዛው ባለህበት ጠብቀን። ካልቨርት አብሮህ ነው ያለው?"

"አይደለም። ግን ቅርብ ነው። ላመጣው እችላለሁ።" አለ ናትናኤል በጭንቀት እየተውተረተረ።

"ጥሩ። በፍጥነት ፈጽመው። ተጠንቀቅ። ካልቨርት ሳይነግርህ እንዳልቀረ እርግጠኛ ነኝ፤ እኛ ብቻ አይደለንም ከተማውን እያሰስን ያለነው። ናትናኤል በእነሱ እጅ መውደቅ የለብህም። በነሙቼ።ተግባባን?"

"እዎ... እዎ... አያገኙኝም... በጥንቃቄ አመጣዋለሁ... ብቻ ርብቃን አታሰቃይዋት። ምንም አታውቅም።"

"ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ማንም የቀሚሷን ጫፍ አይነካም፤ እመነኝ ናትናኤል። ቅሪት የሆነችን ሴት ቀሚስ ገልቦ ማሰቃየት ምን ያህል



አስጠሊታና ሰቅጣጭ እንደሆነ ብታውቅ ችግሬን ትረዳልኝ ነበር። በእጇ ያለችው ሴት ርብቃ እርጉዝ ነች! ለማድረግ የምጠየፈውን እያደረግሁ ነው። አንተ ብቻ ነህ ልታቆመኝ የምትችል።"

ናትናኤል ስልኩን ዘግቶ ለጥቂት ደቂቃዎች ባለበት ፈዝዞ ቆመ። በደም የተጨማለቀ፤ ያበጠና የዘንጎነ ፊት ታየው። የእርጉዝ ሴት ፊት... የርብቃ። ሁለት እጆቹን ዓይኖቹ ላይ ጭኖ ፊቱ ላይ የተደቀነውን አስፈሪ ምስል ሊያጠፋው ታገለ። የዘጎነና የበለዘው ምስል ግን ይብልጡን እየደመቀ ደም እየጎረሰ...እየደፈረሰ... እየረሰረሰ መጣበት። ምንም የማታውቀው የእሱ ርብቃ በሱ ኃጢያት ቀሚሷ ከላይዋ ተበጫጭቆ ጀርባዋ ተገልቦ ራቁቷን በጅራፍ ስትተለተል ታየችው... ሰውነቱን አንቀጠቀጠው።

ፈጠን ብሎ ስልኩ ካለበት ክፍል ወጣና የየምስራችን እናት አስከትሎ በጥድፊያ እየተራመደ ወደ ካልቨርት አመራ።

"ደህና ነች?" አሉት የየምሥራች እናት መንገድ ላይ ከጎን ከጎኑ ሱክ ሱክ እያሉ።

"እ...?"

"ደህና ነች ወይ አልኩ... ምስርዬ... " አሉት ፈገግ ብለው። "ታገናኘኛለህ ብዬ ስጠብቅህ'ኮ ስልኩን ዘጋህብኝ፤ ምነው?»

"እ...እ... እዎ... አ... ደህና ነች" አላቸው። በኮረኮንቿ መንገድ እየተወለካከፈ እየተጣደፈ ወደ ካልቨርት።

እቤት እንደደረሱ ናትናኤል ጊዜ ሳያጠፋ በፍጥነት የትንሿን ክፍል መዝጊያ በርግዶ ገባ።

ካልቨርት በተቀመጠበት እንዳለ ቀና ብሎ የናትናኤልን የበረገገ ፊት ሲመለከት ደነገጠ። ምንም ሳይናገር በጭንቀት ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመ።

"አዝናለሁ ናትናኤል። አዝናለሁ።" አለ የሚለው ሲጠፋው።

"አልሞተችም! ገና አልገደሏትም። እያሰቃይዋት ነው።" አለ ናትናኤል እየተወራጨ፤ "ተነስ... እንሂድ... ስልክ የደወልኩበት ቦታ እንድጠብቃቸው ጠይቀውኛል።"

"እነማን?" ካልቨርት የሰማውን ማመን አቃተው።

"እነሱ... አለበለዚያ ... እጄን ካልሰጠሁ... እንደሚያሰቃይዋት ዝተውብኛል... አልችልም... ፍፁም አልችልም!" አለ ናትናኤል ፊቱን በመዳፉ ሸፍኖ። ስለእርግዝናዋ ላለማሰብ እየታገለ።

“እና ምን ልትሆን ነው?” ካልቨርት አይኖቹን አፈጠጠ።

“እጁን ልሰጥ ነው። አንተንም ይፈልጉሃል።”

“ወዳጄ... እኔን መፈለጋቸውን ከወራት በፊት ነው የማውቀው። ቢይዙን ምን እንደሚያደርጉን ታውቃለህ?” አለ ካልቨርት ናትናኤል ላይ አፍጥጦ።

“ምንም እንደማያደርጉን ቃል ገብተውልኛል።”

“የዚህን ዓይነት ቃል ከሆነማ የምትፈልገው ለምን ከወር በፊት አትጠይቃቸውም ነበር? ! ይሰጡህ ነበርኮ!” ካልቨርት ተናደደ። “በድንገት ጭንቅላትህ ለምን መስራት እንዳቆመ አላውቅም። እኔ ግን ይህን ያህል ጊዜ ተዘግቼ ቆይቼ ነፃነቴን ላገኝ ጥቂት ቀናት ሲቀሩኝ በቃል ኪዳን ሰበብ አንገቴን ለመጋዝ አላቀርብም።”

“ዋጋ የለውም! ያገኙናል።ከተማውን ሁሉ እያሰሱ ነው ነግሮኛል።” አለ ናትናኤል ተስፋ በቆረጠ ድምጽ።

“ነግሮሃል... እውነት?” አለ ካልቨርት ብስጭትና ማሽሟጠጥ በተቀላቀለው ድምጽ። “ድሮ ምን ሲልህ ኖሯል? 'ከቁጥጥራችን ውጪ ናችሁ፤ ልናጠምዳችሁ አይቻለንም።' እንዲልህ ነበር የጠበቅኸው? ደግሞም እንዳሉት የተጠናከሩ ቢሆንም እንኳን አይኔ እያየ አንገቴን ገመድ ውስጥ አልከትም! ሲፈልጉ አባሬው ይያዙኝ፤ ሲሹ ያንጠልጥሉኝ። መጀመሪያ ግን መያዝ አለባቸው፤ አባረው መያዝ አለባቸው።”

“እና ምን ልንሆን ነው?” ናትናኤል ግራ ተጋባ።

“እንሄድማ!” ካልቨርት በስጨት አለ።

“እኔ እሄዳለሁ።”

“አብደሃል እንዴ አንተ ሰው?”

“አልችልም! ካልቨርት አልችልም! ጆሮዎቼ ያንን የስቃይ ጩኸቷን ሰምተው ከአሁን ወዲያ አንዲት ሰዓት መቆየት አልችልም። ምንም በማታውቀው ነገር ነውኮ ጆርባዋ በጅራፍ የሚተለተለው ካልቨርት።” ናትናኤል አይኖቹን ጨፍኖ ጭንቅላቱን በጭንቀት አርገፈገፈው።

“ናትናኤል... ወጥመዳቸው ውስጥ አትግባ። አለማወቋን እስካወቁ ድረስ ሞኞች አይደሉም እሷን ሲደበድቡ የሚውሉ። እጅህን መስጠትህ ደግሞ ከምንም አያድናትም። እጃቸው ውስጥ ከገባህ በኋላ እየቀሰቡ የሚያስቀምጡህ ይመስልሃል? ይመረምሩሃል! ሲመረምሩህ ደግሞ አንተን እየገረፉ አንተን እያሰቃዩ አይምሰልህ...እሷን ነው እፊትህ አስረው የሚጫወቱባት።”



“ድምጿን ሰምቻዋለሁኮ... ስትጮህ።”

“አንተን ለማስጨነቅ ያደረጉት ነው።እርግጥ ለጊዜው ሊያሰቃይዋት ይችላሉ። የፈለጉትን ድምፅ እንድታወጣ። እንዴ ስልኩን ከዘጋኸው በኋላ ግን ትርፍ ዕቃ ነች። ይልቅስ ልትረዳት የምትችለው ለእሷ ግድየለሽ ሆነህ ስትቀርብ ነው። የምልህ ይገባሃል? አሁን ማድረግ ያለብን ድምጻችንን ማጥፋት ብቻ ነው። እጅህን መስጠትህ ዋጋ የለውም። አስረው አስቀምጠው ፊትህ ይጫወቱባታል! ለማየት የምትጠየፈውን ያሳዩሃል! ይገባሃል የምልህ?”

“ነግሬአቸዋለሁኮ ...ያለንበትን።”

“ምን ብለህ?” ካልቨርት የሰማውን ማመን አቃተው። ዓይኖቹ ከየጎሬአቸው ሊወጡ ያሰቡ ይመስል ፈጠጡ።

“ስልክ የደወልኩበትን አድራሻ...ማለቴ የስልክ ቁጥሩን ነግሬአቸዋለሁ። ተመልሼ እዛው ነው እጠብቃችኋለሁ ያልኳቸው።”

“እዚህ ያለንበትንስ ቦታ?”

“አልነገርኳቸውም...ግን ስልክ የደወልኩት ከመኖሪያ ቤት ስለሆነ ባለቤቶቹን ከጠየቋቸው ያለንበትን ያሳይዋቸዋል። የየምሥራችን እናት ያውቋቸዋል።”

ካልቨርት ለጥቂት ሴኮንዶች አፉን ከፍቶ አይኖቹን አፍጥጦ ናትናኤልን ተመለከተው።

“እ...እየመጡ ነው አትለኝም እንዴ ባጭሩ!” አለ ካልቨርት ፊቱ በድንጋጤ በልዞ።

“አዎ።” አለ ናትናኤል ከርፈፍ ብሎ በቆመበት። የርብቃን እሪታ ሲሰማ የተፈጠረበት ድንጋጤ እያለፈለት ሲመጣ ያጠፋው ጥፋት ቀስ በቀስ ወደ ሰውነቱ እየዘለቀና እየሰረገ ሲገባ ተሰማው፤ ህሊናውን እየገዛ ሲመጣ ድንጋጤው ሲያልፍ የሰራው ስህተት ግልጽ ሆኖ ታየው።

ካልቨርት እንደ መብረቅ ተወርውሮ ከጥግ የተቀመጠ ረጅም ቀሚስ አንስቶ በጭንቅላቱ አጠለቀና ሰማያዊ ባለአበባ ሻሽ ሸብ አድርጎ በላዩ ላይ ድርያውን ተከናንቦ ፊቱን ወደ ናትናኤል መለሰ።

“የማትረባ! እጃቸውን ሚስትህ ትከሻ ላይ ሲጭኑ ሰውነትህ ራደ? መጀመሪያውኑ አውቄሃለሁ ከሰው እርሻ ገብተህ የምታስካካ ዝይ ነህ። ይህ ያንተ ቦታ አይደለም። ያንተ ቦታ አዲስ አበባ ቢራ ቤቶች ውስጥ ነው።

ለመሆኑ በደም ስርህ የሚዘዋወረው ምንድነው? ቀይ ደም ወይስ ቢጫ መግል?" ካልቨርት በቁጣ እየተንቀጠቀጠ አንድ ሰፊ የሴት ቦርሳ ውስጥ እቃውን ያጉር ጀመር::

ናትናኤል ባለበት እንደቆመ በእልህ የሚርገበገበውን ካልቨርትን ሲመለከት የፈጸመው ስህተት ወለል ብሎ ታየው::

"እጇን እየጠመዘዙ ሲያስጮኋት መፈረካከስ ጀመርክ... እዬዬዋን ስትሰማ ስለስጡህ ቃልኪዳን መስበክ አማረህ... ናትናኤል የሚወዱት ሰው አደጋ ላይ ሲወድቅ ምን እንደሚሰማ አውቀዋለሁ:: እንዳንተ ለደቂቃዎች ሳይሆን ለቀናት ለሳምንታት አብሮኝ ከርሟል:: ይህ ብቻ አይደለም! የሚወዱትን ማጣት ምን ምን እንደሚልም ቀምሼዋለሁ:: አሁን ድንገት ወጣ ብለህ የፍቅረኛህን ለቅሶ አዳምጠህ ስለመጣህ ካንተ ጋር በአንድ ሲባጎ ተሸብቤ ወደ መቃብሬ እንድነዳ ትጠይቀኛለህ?! አ! ኢየሱስ!"

ናትናኤል ድምፅ ሳያሰማ ባለበት እንደቆመ ቆየ::

"አብረኸኝ ትጠፋለህ ወይስ እጅህን ትሰጣለህ?" አለ ካልቨርት የሴት ነጣላ ጫማውን አጥልቆ ሰፊ የሴት ቦርሳውን ዚፕ ከመዝጋቱ በፊት ድንገት ቀና ብሎ እየተመለከተው::

"አብሬህ እጠፋለሁ::" አለ ናትናኤል ጥርሱን ነክሶ እንባውን እየታገለ::

"ትረፍ ሲልህ ጥሩ መንገድ መርጠሃል::" አለ ካልቨርት ከሰፊው ቦርሳው ውስጥ አንድ ትንሽ ሽጉጥ አውጥቶ እየፈተሸ:: "እጅህን ልትሰጥ ብትወስን ኖሮ እዚሁ ጨርሼህ ልሄድ ነበር የወሰንኩት:: መቼም አይኔ እያየ እየመራህ እንድታሲዘኝ ልተውህ አልችልም:: በል ቶሎ እንውጣ::" አለ ካልቨርት ሽጉጡን ፈትሾ አቀባብሎ መጠበቂያውን ብቻ ባለበት ትቶ መልሶ ቦርሳው ውስጥ እየከተተው::

ካልቨርት የሴት ልብስ ለብሶ በላዩ ላይ ድሪያውን ተከናንቦ ናትናኤል ደግሞ ከወገቡ በታች ሽርጡን እንዳሸረጠ በነጭ ሸሚዝ ከትንሿ ክፍል ተከታትለው ወጡ::

"ወዴት ልትሄዱ ነው?" አሉ የየምሥራች እናት ድምፅ ሰምተው ከጓዳ ብቅ እያሉ::

"ሰላም ነው::ወደ አዲስ አበባ ነው የምንሄደው በላቸው::" አለ ካልቨርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈጠን ብሎ:: "እና ስላደረጉልኝ ሁሉ በደንብ አመስግንልኝ::"



ናትናኤል ካልቨርት ያለውን በአማርኛ ተርጉሞ ለሴትየዋ ተናገረ::

"ውይ...ታዲያ ብትሄዱስ በዓመት በዓል ነው እንዴ! ምነው ዋል አደር ብትሉ::" አሉ የተከፉ የሚመስሉት ሴትዮ ካልቨርት ለብሶት የመጣውን የሴት ልብስ ድጋሚ ለብሶ ሲያዩ ምስጢሩ እያጓጓቸው::

"ብንሄድ ይሻላል:: የምሥራች ትጠብቀናለች:: ዛሬ ከሰዓት መግባት አለብን::"

"በአውሮፕላን ነው የምትሄዱ?" አሉ ሴትየዋ::

"አዎ::" አላቸው ናትናኤል::

"ውይ አፈር በበላሁ! ደብዳቤ እንኳን ሳልጽፍ!" አሉ ሴትየዋ እጃቸውን ሽርጣቸው ላይ እየጠራረጉ "ማነሽ... እሙ... እመቤት... ወረቀት ወዲህ በይ ...ቶሎ..."

"አይ..." አቋረጣቸው ናትናኤል እንዳያዘገይዋቸው ሰግቶ:: "ሰሞኑን ከቻልኩ ተመልሼ እመጣለሁ ከምሥራች ጋር:: መልዕክት ግን እነግርሎታለሁ:: አሁን ቶሎ መሄድ አለብን::"

ሊወጡ ሲሉ ካልቨርት ከቦርሳው ውስጥ በርካታ ገንዘብ አውጥቶ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምሥጋና እየደረደረ ለሴትየዋ ዘረጋላቸው::

"በቁልቢው! ኧረ እኔ'ቴ! እዚህም ሆኖ የተቀበልኩትኮ ሁሉን ሳሟላበት አቅም ስለሌለኝ እንጂ ደግሞ የምን ክፍያ አመጣችሁብኝ? የልጄ ባልንጀሮች ልጆቼም አይደላችሁ? ግድ የለም 'እግዜር ይስጥህ የኔ ልጅ' በልልኝ በአፉ- በቋንቋው::" አሉ ሴትየዋ ፊታቸውን ወደ ናትናኤል መልሰው::

ከየምሥራች እናት ቤት ወጥተው ብዙም ሳይርቁ ከአንድ አነስተኛ ቡና ቤት ገቡና ጥግ ላይ ጨለምለም ያለ ቦታ መርጠው ተቀመጡ::

"አዲስ አበባ ነው ለመሄድ ያሰብኩት::" አለ ካልቨርት ቦታ ይዘው እንደተቀመጡ:: "በዚህ ሰዓት ተመልሰው እመሀከላችን ይገባሉ ብለው አይጠረጥሩንም:: ወደዚያው ማምራታችንን በትክክል አስካልደረሱበት ደግሞ ሁላም ልናገኝ የምንችለው አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ነው::"

"ታዲያ ለምን ለየምሥራች እናት እውነቱን እንድነግራቸው ነገርከኝ?" አለ ናትናኤል::

“አውቄ ነው፡፡ ተባራሪ የሚሄድበትን፣ የሚሸሽበትን በትክክል አይናገርም፡፡ ሴትየዋ ቢያወሩም ዋጋ የሚሰጠው የለም፡፡ ይልቅ እንዴት አድርገን ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንደምንችል ነው ያልተገለፀልኝ፡፡”

“ሦስት አማራጭ ነው ያለን- አውሮፕላን- ባቡር- መኪና፡፡”

“አውሮፕላኑን እርሳው፡፡ ባቡር አንድ አማራጭ ነው፡፡ ቢሆንም በጣቢያዎች ላይ ሰዎች ሊኖሩአቸው ይችላል፡፡ አውቶቡስ ጣቢያዎችም ተመሳሳይ ናቸው፡”

“እያቀራረጥን መጓዝ እንችላለን፡፡” አለ ናትናኤል ዝም ብለው ተቀምጠው ያዘዙትን ሻይ ሲጠጡ ከቆዩ በኋላ፡፡

“እንዴት?”

“ለጊዜው ከድሬዳዋ በእግርም ቢሆን መውጣት... ከዛ በኋላ የጭነት መኪናዎችና የቤት መኪናዎች እየተከራየን እያቀራረጥን መጓዝ እንችላለን፡፡”

“በእግር እስከየት ድረስ እንሄዳለን?” አለ ካልቨርት ትክሻው ላይ ካንገበው ከሰፊው የቤት ቦርሳው ውስጥ አነስተኛ የአገር ጎብኚ ካርታ አውጥቶ አመሃል ከለው ጠረጴዛ ላይ እየዘረጋ፡፡ «እዚህ ነው ያለነው፡፡»አለ ካልቨርት የሌባ ጣቱን ድሬዳዋ ላይ ተክሎ፡፡ «እዚህ ነው መድረስ ያለብን፡፡» ጣቱን ከድሬዳዋ አንስቶ አዲስ አበባ ላይ ጫነው፡፡

“አዎ...ይኸውልህ አንደኛው መንገድ በሐረር አቅጣጫ አድርጎ አሰማይ ከመድረሱ በፊት ወደ ግራ ታጥፎ አሰበ ተፈሪ ይገባና ከዚያ ወዲያ በሚኤሶ አድርጎ ወደ አዲስ አበባ ይደርሳል፡፡ የተለመደው መንገድ ይህ ይመስለኛል፡፡”

“ይመስለኛል? አታውቀውም እንዴ?” አለ ካልቨርት ደንገጥ ብሎ፡፡

“እውነቱን ለመናገር አላውቀውም... የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ድሬዳዋ ስመጣ፡፡”

“በእየሱስ! ከኔ አትሻልማ!” አለ ካልቨርት ወደኋላ ወንበሩ ላይ ተደግፎ፡፡

“አታስብ አማርኛ እስከተናገርኩ ድረስ የትም ይገበህ መሄድ እችላለሁ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ፡፡ ይኸውልህ... ሌላው አማራጭ ደግሞ ከሞላ ጎደል ከባቡር ሃዲዱ ጋር ጎን ለጎን የሚሄደው የየረር ጎታ መስመር ነው፡፡ ይታይሃል በዚህ አድርጎ...” ናትናኤል ወደ አዲስ አበባ ሊያመሩ



የሚችሉባቸውን ሁለት የመኪና መንገዶች አንድ በአንድ ለካልቨርት አሳየው፡፡

“እኔ ሁለተኛውን እመርጣለሁ፡፡ እንዳልከው ብዙም የማይዘወተር ከሆነ...” አለ ካልቨርት፡፡

“ጥሩ፡፡ ግን ከዚያ በፊት ልብሶቻችንን መቀየር አለብን፡፡ ከቤት ስንወጣ የምሥራች እናት አይተውናል፡፡አዳኞቻችን ከጠነከሩባቸው ፈርተው ሊናገሩ ይችላሉ፡፡”

መንገድ ከመጀመራቸው በፊት ናትናኤል ከአንድ የልብስና የጫማ ሱቅ ገብቶ ለካልቨርት የሚሆን ሸርጥና ጫማ፣ ለሁለቱም ደግሞ የእስላም ቆቦች ገዝቶ ተመለሰ፡፡ ከአንድ ቡና ቤት መጸዳጃ ቤት ውስጥ ካልቨርት የለበሰውን የሴት ልብስ በአዲሱ ሸርጥ ከቀየረ በኋላ የወንድ ጫማውን ተጫምቶ መኪና ፍለጋ ወጡ፡፡

“ጎን ለጎን ባንሄድ ጥሩ ነው፡፡ የሚፈልጉት ሁለት ሰዎችን ስለሆነ ዓይናቸው ጥንድ መንገደኞች ላይ ይበልጥ ጠንቃቃ ይሆናል፡፡አንተ ከፊት ከፊቴ ሂድ፤ እኔ በቅርብ ርቀት እከተልሃለሁ፡፡” አለ ካልቨርት፡፡

“እንጠፋፋለና፡፡”

“አንጠፋፋም፡፡ ብቻ አንተ ከጀርባህ መኖሬን ለማረጋገጥ አትገላመጥ፡፡ አማርኛ የምትናገር አንተ ስለሆንክ በተቻለህ መኪናውን ቶሎ ለማግኘት ብቻ ሞክር፡፡ እኔ እከተልሃለሁ፡፡ አታስብ፡፡ ለአንተ አዲስ ነው እንጂ እኔ የኖርኩበት ዓለም ነው፤ድብብቆሽ፡፡” አለ ካልቨርት፡፡ «እ...ናትናኤል ሊይዙን ቢችሉም ቀድመው የሚይዙት አንዳችንን ነው... አንተን ከያዙህ በሩቅ ስለማይህ ችግር የለውም፤ እመልጣለሁ፡፡ እኔን ከያዙኝ ግን የጥይት ድምፅ ስትሰማ ሳትገላመጥ ሳትደናገጥ ለማምለጥ ሞክር፡፡ አንተንም ከያዙህ የምመክርህ የገዛ ሕይወትህን እንድታጠፋ ነው፡፡ አለበለዚያ የሚከተለውን ለመሸከም መምረጥህ ነው፡፡”

“መሣሪያኮ የለኝም፡፡” አለ ናትናኤል መሣሪያ ቢኖረውም የዚህን ዓይነት ዕብደት እንደማይፈጽም እየተማመነ፡፡

“እንዴት?” አለ ካልቨርት በመደነቅ ፊት እየተመለከተው፡፡ «በእየሱስ ያንን ሁሉ ያስለፈለፍከኝ ባዶ እጅህን ነው ማለት ነው?»ካልቨርት ናትናኤል ላይ አፍጥጦ ቆየና ፈገግ አለ፡፡ “‘አትሙት’ ብሎ የፈጠረው ሞኝ ዝንጀሮ አንተን አየሁ፡፡”

ብዙም ሳይቸገሩ በዱርዬዎች እርዳታ ከድሬዳዋ ተነስቶ ቢኬ የሚገባ አሮጌ የቤት ዕቃ የጫነ አነስተኛ የጭነት መኪና አግኝተው በሂሣብ ተስማምተው ተሳፈሩ:: መንገዱ ተዘግቷል እያለ የሚነጫነጨው ሹፌር ሂሳቡን አለቅጥ ቢቆልለውም ካልቨርት ተሽቀዳድሞ ይሁን ስላለ ከጀርባ መኪናው ላይ ወጥተው ጉዞ ጀመሩ::

"አስፋልት መንገዱን ዘግተውታል:: ዙሪያ ጥምጥም በአቧራው በሜዳው አሳብሬ ነው የምወስዳችሁ! እንደውም በእርካሽ ነው ያገኛችሁኝ አቦ!" እያለ እየተነጫነጨ ሹፌሩ ከመሪው ኋላ ገብቶ ከመነቃነቃቸው በፊት በብብቱ ከያዘው ቱባ ጫት ሁለት ዘለላ መዝዞ ወረወረላቸው:: የጭነት መኪናው ከጀርባ የጫነው የሳሎን ፎቴዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ ትናንሽ ሳጥኖች አንዱ በአንዱ ላይ ተነባብረው ተከምረዋል:: እዚያ ውስጥ ናትናኤልና ካልቨርት በትይዩ በተቀመጡ ሁለት የሳሎን ፎቴዎች ላይ ተቀምጠው አስፋልቱን ትተው ሹፌሩ ብቻ በሚያውቀው አቅጣጫ ሜዳ ለሜዳ በአቧራው ላይ እየጋለቡ ተዘጋ ቶተባለውን ኬላ አሳብረው ጋለቡ::

የጭነት መኪናው ያረጀ ብቻ ሳይሆን በጆያያዝ ጉድለት ይሁን ወይ እንደ ወፍ ክንፍ እውጥቶ ሊበር በሚዳዳው የሹፌሩ አነዳድ ብቻ ክፉኛ ወላልቋል:: በእያንዳንዱ ኩርባ ላይ የሚያሰማው ኳኳታ በእያንዳንዱ ጉድባ ላይ የሚለቀው ጓጓታ ከአሁን አሁን ተፈረካክሶ በበረሃው መሃል ተቆለለ ያስብላል::

ከጋቢናው በስተኋላ ባለው መስኮት ውስጥ ጀርባው የሚታያቸው ሹፌር ልጅ እግር አይደለም:: የኮሰሰ ሰውነቱ በጫትና በመጠጥ እንደተጎዳ ያስታውቃል:: አኳኋኑና አነዳዱ፣ በየሰበቡ በየኩርባው ከአፉ የሚወጣ ስድብና ጩኸቱ ግን ወጠምሻ ጎረምሳን ያስንቃል:: ዙርባውን ፊትቶ ከጎኑ ካለው ወንበር ላይ ከበተነው ጫት አሁንም አሁንም እያነሳ አፉን ያጭቃል:: መንገዱን ዘጉ የተባሉትን ወታደሮች ይሳደባል፣ አባቶቻቸውን ይራገማል፣ እናቶቻቸውን ያፈትራል...ሌላም ሌላም ነገር ያደርጋል...ወደፊት ይከንፋል...

ትንሽ እንደሄዱ ካልቨርት ከቦርሳው ውስጥ ትንሹን የአገር ጎብኚ ካርታ አውጥቶ ዘረጋና...

"አሁን የት ድረስ ነው ይህ ሰው የሚያደርሰን?" አለ ባጎነበሰበት ዓይኖቹን ብቻ አቅንቶ ናትናኤልን በግንባሩ እየተመለከተ::

"ይኸውልህ::" አለ ናትናኤል ካርታው ላይ ያለችውን ያቤኬን ከተማ በትንሽ ጣቱ ነካ አድርጎ::

"ከዋናው መንገድ ተገንጥሎ ይወጣል ይሄ ከተማ?" አለ ካልቨርት በካርታው ላይ አፍጥጦ::

"መሆኑ ነው መሰለኝ::"



"ከዚያ በምን መቀጠል እንችላለን?" ካልቨርት ግንባሩን ከስክሶ ጠየቀ::

"ናትናኤል ሰዓቱን ተመለከተ:: «እንጃ ካልቨርት:: ይመሻል:: እዛው ማደር ሳይኖርብን አይቀርም:: አሁን ዘጠኝ ተኩል ሆኗል:: አስራ አንድ... አስራ ሁለት ላይ ብንደርስ ነው:: በዛ ሰዓት ወደ አዲስ አበባ የሚያመራ መኪና ማግኘት አስቸጋሪ ነው የሚሆንብን::»

ለአንድ አፍታ ካልቨርት ሃሳብ ይዞት ጭልጥ አለ:: ናትናኤል ጓደኛውን ምን እንደሚያስብ ባይረዳም ዝም ላለማለት ያህል:-

"አሁን አዲስ አበባ ስንደርስ ምንድነው የምናደርገው?" አለ::

"በመጀመሪያ እዚያ እንድረስ:: በነገራችን ላይ ይህች ቢኬ ወዳልነት ከተማ ከመታጠፋችን በፊት ንገረኝ::" አለ ካልቨርት::

"እሺ. እነግርሃለሁ:: መቼም ባላውቃትም ክፋኛ ወደ ቀኝ ከታጠፈ እሷ መሆን አለባት:: ከዛ ቀድሞ ሌላ የሚገነጠል መንገድ የለም ካርታው ላይ::" አለ ናትናኤል በተቀመጠበት ፎቴ ላይ ሰጠጥ ብሎ:: "አዲስ አበባ ስንደርስ ምን ማድረግ እንዳለብን ብንነጋገር ግን ጥሩ ይመስለኛል:: ቀድሞ ማቀድ ከመሽቀዳደምና ከመደናበር ያድናል- ካለፈው ልምዱ እንዳየሁት::"

"ምንም ዕቅድ አያስፈልግም::" አለ ካልቨርት ፊቱን በዙሪያቸው ወደተንጣለለው በረሃ መልሶ::

"እንዴት?"
"ምንም የምናደርገው ነገር የለማ::"
"ምንም ካልሰራን ለምን ወደዚያ እንሄዳለን?"

"ናትናኤል" አለ ካልቨርት በተሰላቸ ድምፅ:: "ምን ለማድረግ ነው የምታስበው... አዲስ አበባ ውስጥ ተደብቀን ለመቆየት ይበልጥ አመቺ ስለሆነ ብቻ ነው ወደዚያ የምንሄደው:: በቃ::"

"ርብቃስ! የኔስ ፍቅረኛ:: እጃቸው ውስጥ መሆኗን እያወቅሁ የገዛ አንገቴን ለማዳን ስል ድምጼን እንዳጠፋሁ እንድቀይ ነው የምትመክረኝ?" ናትናኤል በስልክ የሰማው ማስጠንቀቂያ አንድ በአንድ ታወሰው::

"ስለዚህ ምን ልታደርግ አሰብክ?"
"አስፈራራቸዋለኋ! እንዲለቋት::" አለ ብስጭት ብሎ::
"በምንህ ነው የምታስፈራራቸው?" አለ ካልቨርት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ ብሎ::

"ደጠዬ አነጋግራቸዋለሁ። እስክልለቀቋትና በሠላም እስካልተዋት ድረስ ዕቅዳቸውን እንደማወጣ አስጠነቅቃቸዋለሁ።"

"እንበልና ሊለቋት ባይስማሙስ?"

"አዝረክርከዋለኋ ጉዳቸውን! እየተለቀመ ይገባታል።" ናትናኤል ንዴት ወረረው።

"አየህ... እዚህ ላይ ነው የማንስማማው። ልንገርህ... ይህን ምስጢር ልታወጣ ብትሞክር ቀድሜ የምቀኝጥስህ እኔ ነኝ።" አለ ካልቨርት ሽጉጥ የከተተበትን ኪሱን በቀኝ እጁ መታ መታ እያደረገ።

"ምን ለማለት ነው?" አለ ናትናኤል ዓይኖቹን አጥብቦ።

"ሰምተኸኛል። ባጭሩ ምስጢሩን ለማውጣት ብትሞክር ቀድሜ እገድልሃለሁ። ናትናኤል አንድ ተስፋ ቢኖረን... አንድ ጭላንጭል ቢታየን እሱንም ልታጨልመው ስትሞክር ዝም ብዬ አልመለከትህም።" ቆፍጠን አለ ካልቨርት።

"ተስፋ... ተስፋ አትበልብኝ ሰባቱ..." ናትናኤል የተሰማውን ንዴት መደበቅ አልቻለም። "የነፍስ ገዳዮች ጥርቅም... የወንበዴዎች ሆያሆዬ አይደለም ተስፋ የሚፈነጥቅብኝ... ተስፋ አይደለም። የሚታየኝ...እልቂት ነው...ጥፋት...ፍጅት... ውድቀት።"

"ታዲያ ለምኑ ፈራህ? ለአፍሪካዊ እልቂትና ፍጅት፣ ጥፋትና ውድቀት ከመቼ ወዲህ ባዳ ሆኑበት? በዘርና በጎሳ፣ በፖለቲካና በሃይማኖት ሰበብ የገዛ ወንድሙን በየጫካው በጥይት እየጠዘጠዘ እየቆላ ላለ አፍሪ-ታዳኝ ሕዝብ እልቂትና ፍጅት አዲስ ናቸው? የገዛ መንጋጋው ሊያላምጠው የሊለው ... የገዛ ጨጓራው ሊሰለቅጠው የሌለው ነጋ ጠባ ከአውሮፓ አራጣ አበዳሪዎች ጓዳ ለማይጠፋ ድሀ ህዝብ ውድቀት ብርቅ ሆነ? ለምኑ ፈራህ ... ምን እንዳይመጣ ሰጋህ? ከዜሮ በታች ቁጥር አለ? ከአፍሪካ በታች ገሃነም አለ? ብንሻውም እንኳን ከዚህ በታች የምንወርድበት የምናዘቅጥበት ስፍራ የለም። አትስጋ።"

"እንደ የተፋጀ ዝንተ ዓለም ቢፋጅ... እንደ የወደቀ ዘለአለም ቢወድቅ ምን ገዶኝ ማለትህ ነው?" አለ ናትናኤል በሃሳቡ የመጣችበት ግን ዘውዲቱ ነበረች... 'ተጎድቼ ያለቀልኝ ሸርሙጣ... ምኑ ይጎዳል?'

"አላልኩም። ለደዌአቸው መድሃኒቱ እዚያው እመሀላቸው አፍሪካ ውስጥ መሆኑን መቀበል ተስኗቸው ከባዕድ ጋር እየተመሳጠሩ... ከመጤ



ጋር እየተሻረኩ የገዛ ወንድሞቻቸውን ስልቀት የሚያራቡ አፍሪካውያን ናቸው። አፍሪካ አንድ መሆን አለባት።"

"አንድነትክ በዘፈቀደ በአየር ላይ አይመሰረትም።" አለ ናትናኤል ስሜቱን ለማስረዳት ተቸግሮ። "እኔኮ ውህደትን አልተቃወምኩም። ግን ፖለቲካዊ አንድነት የኤኮኖሚያዊና የማህበራዊ ዕድገት ጥንቅር ውጤት ነው። ከዚያ ውጭክ ውህደት ጭፍን ውህደት ዲሞክራሲን ችላ ማለት ብቻ ሳይሆን ኢሳይንሳዊ ነው።"

"ፕ!ኢሳይንሳዊ ... ሳይንሳዊ ቅራቅንቦ! በአፍሪካ ውስጥ ከነፃነት ወዲህ ስንት ሳይንሳዊ ፖሊሲዎችና ሳይንሳዊ ዕቅዶች በወረቀት እንደሰፈሩ አንድ ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቅ። የየትኛው አፍሪካዊ አገር ኢኮኖሚ ሲያብብ ሲፈካ... የየትኛው አፍሪካዊ አገር ማህበራዊ ኑሮ ሲለመልምና ሲምንሸነሽ ታየ? በላ ንገረኝ!"

"ታዲያ እኮ የዚህ ምክንያቱ ዲሞክራሲያዊ ሂደት ስለሌለ ነው። ዲሞክራሲና ሠላም በሌለበት ዕድገት የለም..." አለ ናትናኤል።

"ውህደት ነው መልሱ!" ዕልህ ያጨናነቀው የካልቨርት ድምፅ አቋረጠው። "ልክ እንዳንተ በርካታ አፍሪካውያን ከፖለቲካ ውህደት በፊት ኤኮኖሚያዊ ግንባታ ሊቀድም እንደሚገባና የፖለቲካን ውህደት ወደፊት ልንቀዳጀው የምንችል ግብ አድርገው ያቀርቡታል። ነገር ግን ማስተዋል የሚገባን የምንጓጓለት ኤኮኖሚያዊ ጥንካሬ ሊፈጠር የሚችለው ሙሉ ፈቃደኝነት የተሞላበት መደጋገፍና መረዳዳት በአፍሪካ አገሮች መሃከል ሲሰፍን ብቻ ነው። ነገር ግን ይህ መደጋገፍና መረዳዳት በቅድሚያ የሚጠይቀው ነገር አለ- የጋራ ፖለቲካዊ መድረክ።"

"አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ..." አለ ናትናኤል አቋርጦት። "አፍሪካውያንን ምንድነው ሊያስተሳስረን የሚችል? የአፍሪካ አንድነትክ በሥነስርዓቱ የተደከመበት ዓላማ ነው። አልሆነም እንጂ።"

"ከባድ ጥያቄ!" ካልቨርት ጭንቅላቱን ወደኋላ ጥሎ የማሾፍ ሳቅ ሳቀ። "ምንድነው የውህደታችን መሠረት? በእየሱስ ምን እንድልህ ትፈልጋለህ? የሴንጎር ኒግሪትዩድ? የሴኩትሬ አፍሪካዊ ብሄረተኝነት? የንክሩማን የቅኝ ግዛት እከክ ቁስል ጠባሳ? አይደለም። ለእኔ ባዶ ሆዳችን ነው አንድ የሚያደርገን፤ የመሰንበትና ያለመሰንበት ጥያቄ ነው የሚያስተባብረን። ተነጣጥለን ልንሞላው ያልቻልነውን ከርሳችንን ... ለየብቻ ቆመን ልናረጋግጠው ያቃተንን ሰላምና ደህንነታችንን እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንጋፈጠው ይገባል! በእኔና በአንተ እግር ላይ የወደቀን ቋጥኝ ለማንሳት የእኔንና ያንተን የዝምድና ግንድ መቁጠርና መመርመር አያሻንም።

በመጀመሪያ አገሮቻችን ከመጨናነቃቸው በፊት ተረዳድተን ቋጥኙን ከላያችን ማንሳት አለብን:: አለቀ:: 'የአፍሪካ ውህደት የተደከመበት ነው' ላልከው... እርሳው:: ለእኔ አይዋጥልኝም:: በቀንጆ ቀንጆ ከተሞች ቀንጆ ቀንጆ ህንፃዎች እየገነቡ 'የአፍሪካ ድርጅት'፣ 'የአፍሪካ... ኮሚሽን' 'የአፍሪካ... ኢንስቲትዩት' እያሉ ስም ማውጣት... ትንሽ ትንሽ እየሰሩ ብዙ ብዙ የሚከፈላቸውና በሽንጠ ረጃጅም ቀንጆ ቀንጆ የአውሮፓ መኪናዎቻቸው ቀንጆ ቀንጆ ኮረዶችን እየጫኑ መዞር ሥራቸው የሆነ ውድ ውድ ኤክስፐርቶችን ማሰባሰብ አፍሪካን አንድ አያደርጋትም::"

"እኔኮ ሲገባኝ ያልቻለው..." ናትናኤል የጀመረውን ሳይጨርስ ለጥቂት ሰኮንዶች ዝም አለ:: "እሺ ሆነ እንበል:: እንዲያው ድንገት አፍሪካ አንድ ሆናለች ብለህ በመገናኛ መስመሮች ስትለፍፍ ሌላውን ተወው አፍሪካውያን እራሳቸው ምን ይላሉ? ፍጹም ያላሰቡበትና በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህብረት ያላለፉበት ... ወንድማማችነታቸውን አጠናክረው በሚገባ ያልተዋወቁበት... ድንገተኛ ዱብ ዕዳ ሲመጣባቸው ምን ይላሉ?"

"ምን ይላሉ?" ካልቨርት መልሶ ጠየቀ:: "አየህ... አንተ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ያለውን ህዝብ የፖለቲካ አመለካከት አልተረዳህም:: አፍሪካ ውስጥ ፖለቲካ ግለሰብአዊ ነው:: ግለሰቦች ፖለቲካን ይፈጥሩታል እንጂ የፖለቲካ አመለካከት ግለሰቦችን አይቀርጽም:: ምክንያቱም ፖለቲካ ራስን መጠበቂያ መሣሪያ ነው:: አፍሪካ ውስጥ ጥያቄው የትኛው የፖለቲካ መስመር ለዕድገት ይበጃል አይደለም:: ጥያቄው የትኛው የፖለቲካ መስመር ሥልጣን ላይ ያስነባብተኛል ነው:: ለዚህ ነው ፖለቲካ ግለሰብአዊ ነው የምልህ:: ነገ አፍሪካ አንድ ብትሆን አፍሪካውያን የሚሉት 'አፍሪካ አንድ ሆነች ነው::' በቃ::"

ያሉባት መኪና ድንገት ፍጥነቷን አብርዳ ከኋላዋ የአቧራ ቁልል አንስታ ወደ ቀኝ ስትታጠፍ ቢኬ መገንጠያ ላይ ደርሰናል ብለው አሰቡ:: ለአንድ አፍታ ተያዩ:: ወዲያው ካልቨርት ወደጎን አዘምሞ ከሹፌሩ ጀርባ ያለችውን ትንሽ መስኮት እየደበደበ ሹፌሩ መኪናዋን እንዲያቆም በምልክት ይወተውተው ጀመር::

"ምንድነው? ምንድነው የምታደርገው?" አለ ናትናኤል የካልቨርት ፊሲጥ አልገባህ ሲለው::

"አቁም በለው:: እቃ ጥለሃል በለው::" አለ ካልቨርት ፊቱን ወደ ናትናኤል መልሶ::

ናትናኤል ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ለሹፌሩ ዕቃ መጣሉን በምልክት ሲያስረዳው ሹፌሩ መኪናውን አብርዶ ጥግ አስያዛት::



"ምን ሆናችኋል?" ጮኸ ሹፌሩ ጭንቅላቱን ወምዘዞ::

"ምንድነው የፈለከው?" አሉ ናትናኤል በተራው ራሱን ወደ ካልቨርት መልሶ::

"መጣሁ::" አለ ካልቨርት:: ከጭነት መኪናዋ ጀርባ ዘሎ ወረደና ወደ ሹፌሩ ሄደ:: የሹፌሩን በር ከፍቶ ያለሃተታ የሹፌሩን ክንድ ጨመደደና ጎትቶ አወረደው:: የሚንጫጫጨው ሹፌር አግሮች መሬት እንደነኩ ካልቨርት የቀኝ እጁን አንስቶ አንገቱ ስር ቢለው ያ ጫትና መጠጥ የሸረሸሩት ሹፌር ወርዶ እግሩ ስር ተቆለለ::

"ምን ማድረግህ ነው? አብደሃል እንዴ?" ናትናኤል ከተቀመጠበት ወንበር ጋር እንደተጣበቀ ሁሉ ካለበት ሳይንቀሳቀስ ጮኸ::

ካልቨርት የናትናኤልን ጩኸት ችላ ብሎ ብእርጋታ የሹፌሩን እጆች ወደኋላ አዙሮ 'ግጥም' አድርጎ አሰረና አፉን በጨርቅ ጎስጉሶ ሲጨርስ ብቡትና በቡቱ ውስጥ ገብቶ እያንዘላዘለ ከጭነት መኪናው ጀርባ በዕቃዎች መሃል የተከበቀለለ ምንጣፍ ገልጦ ከውስጥ አጋጨመው::

"ውረድና ከፊት ግባ::" አለ ካልቨርት ምንም እንዳልተፈጸመ ሁሉ ናትናኤልን እየተመለከተ:: ወዲያው ፊቱን አዙሮ በሹፌር በር በኩል ገባና መሪውን ጨበጠ::

ናትናኤል ሁኔታውን ሲያይ በፍጥነት ከመኪናው ጀርባ ዘሎ ወረደና ከጎን ያለውን የጋቢና በር ከፍቶ ከካልቨርት ጎን ጋቢናው ውስጥ ገባ:: አብሮት የሚሸሸው ሰው ባህርይ ቀስ በቀስ እየተገለፀለት ሲመጣ ናትናኤል ሲጋት ገባው::

"ምንድነው የሠራኸው? ምን አደረገህ ሰውየው?" አለ ናትናኤል ድንጋጤ ፊቱን አገርጥቶት::

"ናትናኤል ለሁሉ ነገር ጊዜ አለው:: ለግብረገብም ጊዜ አለው:: ገና ለገና መሪውን ስለያዘ የፈለገበት ሲወስደኝ እንደሰንጋ በሬ ከጀርባው ተቆልዬ የምሄድበት ምክንያት የለም:: መሄድ የምፈልገው ወደ አዲስ አበባ ነው:: የአዲስ አበባ አቅጣጫ ደግሞ በዚህ አይደለም::"

ካልቨርት ያለ ጥድፊያ የጭነት መኪናዋን አሽከርክሮ ተገንጥለው ወደ መጡበት መንገድ ተመለሰና ከዋናው መንገድ ሲደርስ ወደ ቀኝ ታጥፎ የመኪናውን አፍንጫ ወደ አዲስ አበባ መለሰው:: ከኪሱ ውስጥ ያችኑ ትንሽ የመንገደኛ ካርታ አወጣና ከመሃላቸው ዘረጋት::

"ስለሚቀጥለው ከተማ ንገረኝ:: ርቀቱን! ፀባዩን የምታውቀውን ሁሉ::" አለ ካልቨርት ቁርጥ ባለ ድምፅ:: ሰውየው - ሰካራሙ ካልቨርት ድንገት ቆፍጣና ወታደር ሲሆንበት ናትናኤል ግራ ተጋባ::

"አ...አፍደም ይላል... አላውቀውም::" አለ ናትናኤል ስለ አፍደም የሚናገረው ግራ ገብቶት::

"ስለእየሱስ ብለህ ርቀቱን ንገረኝ! የያዝከውኮ ካርታ ነው!" አለ ካልቨርት በስጨት ብሎ::

"አ...አርባ.. አርባ አምስት ኪሎ ሜትር ይሆናል::" አለ ናትናኤል ከቢኬ መገንጠያ እስከ አፍደም ያለውን ርቀት ለመገመት እየሞከረ::
"የሚቀጥለው ከተማ ከነርቀቱ?"
"ሚኤሶ:: ርቀቱ... አጥፍ ይሆናል... ዘጠና...መቶ..."

ካልቨርት ሰዓቱን ተመለከተ:: አስራ አንድ ከሃያ ይላል::

"የሚቀጥለውስ ከቶማ?"
"እንጃ:: አይነበብም:: አንድ ነገር አፍስሰህበታል::"
"ተወው አረቂ ይሆናል:: የሚቀጥለውስ ከተማ ከነርቀቱ?"

"አዋሽ:: ርቀቱ እንጃ:: ሩቅ ነው::" አለ ናትናኤል መገመቱ ቢያስቸግረው:: ካርታ እንዴት መነበብ እንዳለበት የሚያውቀው ነገር የለም::

"አምጣ::" አለ ካልቨርት መኪናውን ጥግ አስይዞ:: ካርታውን ከናትናኤል እጅ ተቀብሎ ሲያጠናው ቆየና ቀና አለ-

"ዛሬ ሌሊቱን አዋሽ ደርሰን እናድራለን:: በጠዋት ተነስተን በሌላ ተሽከርካሪ እንቀጥላለን::"
"ነዳጅስ ይበቃናል?"
"እሱን የሚያውቅ አንድ ዲያብሎስ ብቻ ነው::"

ቀኑ እየሸሸ ምሽቱ እየደመቀ ሲመጣ ዝምታ ተጫናቸው:: የሚጓዙበት አሮጌ የቤት ዕቃ የጫነች አሮጌ መኪና ከምታሰማው ኳኳታ በስተቀር ጋቢናው ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ:: ጨለማው ሲጋርዳቸው ሲዳዳው ካልቨርት እንዴ ይህን አንዴ ያንን ሲጫን ከቆየ በኋላ የመኪናውን የፊት መብራት አበራው::የበራው ግን የግራው ወገን አንድ መብራት ብቻ ነበር:: ፍጥነታቸውን ቀንሰው ወደፊት ቀጠሉ::



በመንገዳቸው ላይ ትናንሽና ከፍ ከፍ ያሉ ጥቂት ከተሞች ቢያጋጥሟቸውም ጉዞአቸውን ያለማቋረጥ ቀጠሉ:: ምሽቱ ከገፋ በኋላ አንድ ከፍ ያለች ከተማ አጋጠመቻቸው::

"ሚኢሶ የሚሏት መሆን አለባት ይህች::" አለ ናትናኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ፀጥታውን አደፍርሶ::

ከተማዋን አልፈው ድጋሚ ጭልጥ ባለው በረሃ ውስጥ ሰመጡ:: ከከተማው ብዙም ሳይርቁ ከጀርባቸው ድምፅ ይሰማቸው ጀመር::

"ምንድነው?" አለ ናትናኤል ፊቱን ወደኋላ መልሶ::

ካልቨርት በፍጥነት መኪናዋን ጥግ አስይዞ በሩን ከፍቶ ዘሎ ወረደና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ መጣ::
"ምንድነው?" አለ ናትናኤል
"ሰውየው ነው::"
"ነቅቶ ነው?" አለ ናትናኤል ካልቨርት ሹፌሩን ማለቱ እንደሆነ ሲገባው::
"አዎ::"
"ምን አደረከው?" አለ ናትናኤል ሃሳብ ገብቶት::

"አስተኘሁው መጣሁ::"

ሌሊቱ ከተጋመሰ በኋላ ካሉበት መንገድ በስተቀኝ ተገንጥሎ የሚሄደውን የአሰብን መንገድ ሲያዩ ከፊታቸው የተንጣለለችው አነስተኛ ከተማ የአዋሽ ከተማ እንደሆነች ገመቱ::

ወደ ከተማዋ እየተጠጉ ሲመጡ በግራና በቀኝ ያለው በረሃ ድንገት በትናንሽ ቤቶች የተሞላ መሰለ:: ወደ ከተማዋ ዘልቀው ከመግባታቸው በፊት ካልቨርት መኪናቸውን ጥግ አስያዘና በሮቻቸውን እየከፈቱ ወረዱ:: ጊዜው እጅግ በመግፋቱ ይሆናል በአካባቢው የሚዘዋወር ሰው አይታይም:: ከተማዋን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ የሚያልፈውን መንገድ ይዘው ወደ ትንሿ ከተማ እምብርት በእግራቸው ቀጠሉ::

አልፎ አልፎ ከተዘጉ በሮችና መስኮቶች የሚያመልጥ የብርሃን ጭላንጭል ይታያል:: ልብሳቸውን የሚያርገበግበው ደረቅ ቀዝቃዛ የሌሊት ንፋስ ፊት ፊታቸውን ሲላቸው አይኖቻቸው እምባ አቀረዘዙ::

"በዚህ ሰዓት ማደሪያ ማፈላለግ አትኩሮት መሳብ ይመስለኛል::" አለ ካልቨርት በትከሻው ያነገበውን ቦርሳ አውርዶ ደረት ደረቱን የሚለውን ንፋስ ይከላከልለት ይመስል ደረቱ ላይ ለጥፎ ይዞ::

"እም...እነዛ የጭነት መኪናዎች ይታዩሃል?" አለ ናትናኤል አገጩን ማዶ በጨለማው ውስጥ ጭነታቸውን ጋራ አሳክለው ሸራቸውን ተጀቡነው ወደተደረደሩ ከባድ የጭነት መኪናዎች አሾሎ "...ከነሱ ውስጥ ጠዋት ወደ አዲስ አበባ የሚነቃነቅ አይጠፋም:: አንዳንዶቹን አነጋግረን ከተስማማን አሁኑኑ እንሳፈርና በጠዋት ጉዞ መጀመር እንችላለን::"

በፊት ወዳዩአቸው የጭነት መኪናዎች እንደቀረቡ ናትናኤል ወደ አንደኛው የጭነት መኪና ተጠግቶ በመወጣጫው ላይ ተንጠላጠለና ፊቱን በጎን መስተዋቱ ላይ ለጥፎ ወደ ጋቢናው ውስጥ ተመለከተ:: አንድ ሰው ጋቢ ተጀቡኖ ከመሪው ጎን ባለው ወንበር ላይ ተኝቶአል:: መስኮቱን በዝግታ አንኳኳ:: ሰውየው ባንኖ ተነስቶ እያመነታ መስኮቱን ዝቅ አደረገና "ምንድነው?" አለ በእንቅልፍ ልቡ ጋቢውን ከጭንቅላቱ ላይ እየገፈፈ::

"ይቅርታ ረበሽኩህ:: ባክህ መንገድ ላይ መኪና ተሰብሮብን ነው:: ዛሬ ጠዋት ወደ አዲስ አበባ ለመነሳት ነበር ያሰብነው:: ጠዋት ወደዛው ትነሱ እንደሆነ የምታደርስልኝ ፖስታ ነበር::" አለ ናትናኤል::

"ወደ አዲስ አበባ አይደለም የምንሄደው፤ ሚሌ ነው::" አለ ሰውየው ናትናኤል ከመናገሩ ፊት መስኮቱን እየዘጋበት::

ናትናኤል ተስፋ ሳይቆርጥ ከመኪና መኪና እየቀያየረ መጠየቁን ቀጠለ:: አራተኛው መኪና ውስጥ ያገኘው አውታንቲ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ መሆኑን ሲነግረው መጣሁ ደብዳቤውን ይዤ ብሎት ወደ ካልቨርት ተመለሰ::

ለአውታንቲው ሳይነግሩት ድምፅ ሳያሰሙ ወደ አዲስ አበባ ከሚሄደው የጭነት ጀርባ ላይ እየተንጠላጠሉ ወጥተው ከጭነቱ የፊት ጫፍ ሸራ ገልጠው ገብተው ተደበቁ:: የለበሱት አቧራማ ሸራ ከጨካኙ ንፋስ ቢያተርፋቸውም ሰውነታቸው ተረጋግቶ ለማረፍና እንቅልፍ ለማሸለብ አልቻሉም::

ማለዳ ላይ የተደበቁበት የጭነት መኪና የአዋሽን ከተማ ለቆ እያጓራ እያገሳ አቧራውን እያቦነነ ወደ አዲስ አበባ ለመክነፍ የመጀመሪያ ባይሆንም የኋላ ኋላ የቀደሙትን መኪናዎች ተከትሎ ረጅሙን በረሃማ መንገድ በጠዋቱ ተያያዘው::

አልፎ አልፎ ብቻ የተሸፋፈኑበትን ሸራ ገለጥ እያደረጉ ከፊት ለፊታቸው እየተሽቀዳደመ ወደ መኪናው ሆድ ስር የሚገባውን የአስፋልት መንገድ እያዩ ቆዩ:: ሲረፋፍድ ፀሃይዋ እየጋለች፤ እየጠነከረች ስትመጣ ከሸራቸው ስር የሚፍለቀለቀው ሙቀት ሰውነታቸውን እሳት እንደገላመጠው ጎማ አልፈሰፈሰው:: ከሸራው ውስጥ ለመውጣት ግን አልደፈሩም::



"አልቻልኩትም መቀቀቱን::" አለ ናትናኤል ሸራውን ገለጥ አድርጎ ይዞ በተቻለው መጠን ከፊት የሚከንፈውን ንፋስ ወደ ሸራው ስር ለማስገባት እየሞከረ::

"ለመተኛት ሞክር::"

ወስንጨፊቱን እንዳለፉ የተሳፈሩበት መኪና ድንገት ፍጥነቱን ቀንሶ ጥግ ሲይዝ ሁሉቱም በጥያቄ ተያዩ:: ወዲያው የሌላ መኪና ድምፅ ተሰማቸው:: የተሳፈሩት ከጭነቱ በላይ ስለሆነ እታች ከጭነት መኪናው ጎን ለጎን የሚሄደው መኪና አልታያቸውም:: ወዲያው ያለበት መኪና ጥግ ይዞ እንደቆመ አንድ ጥቁር ሬንጀሮቨር አለፍ ብሎ ከፊት ቆመ::

"እነሱ ናቸው!" አለ ካልቨርት በጥድፊያ ሸራውን መልሶ በጭላንጭል ቁልቁል እየተመለከተ::

ጥግ ይዞ የቆመችው ሬንጀሮቨር የፊትና የኋላ በሮች ተከፍተው አራት ሰዎች ወረዱ:: በእጃቸው አጭጭር አውቶማቲክ ጠመንጃዎች ይዘዋል:: የያዟቸውን መሣሪያዎች ለመደበቅ ሙከራ ሳያደርጉ ወደፊት ደግነው ይዘው በፍጥነት ወደ ጭነት መኪናው ተጠጉና በግማሽ ክብ ቅርፅ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ቆሙ::

"እርግጠኛ ነህ? እነሱ ናቸው?" አንሾካሾከ ናትናኤል ከሸራው ስር::

"ዝም በል!" አለ ካልቨርት ሸራውን በግራ እጁ በስሱ ከፊት አድርጎ እንደያዘ ቀኝ እጁን በሸራው ስር ቁልቁል ሰዶ ሽጉጡን ከኪሱ ውስጥ እያወጣ::

ከሬንጀሮቨሩ ከወረዱት ሰዎች መሃል ሦስቱ ግራና ቀኝ በተን ብለው ሲቆሙ አራተኛው አውቶማቲክ ጠመንጃውን ወደፊት እንደደገነ ወደ ከባድ መኪናው ሹፌር ተጠግቶ እንዲወርድ ምልክት ሰጠው:: ሹፌሩና ረዳቱ ያለክርክር ከጭነት መኪናው ወረዱ::

"እንዳትንቀሳቀሱ!" ራቅ ብሎ የቆመው ሰው ሹፌሩ ላይ ጮኸበት::

ሹፌሩና ረዳቱ ከመኪናው ስር በመሆናቸው ከዓይን ቢከለሉም ካልቨርት አራቱን አዲስ መጤዎች በጥንቃቄ ይከታተላቸው ጀመር::

"የጫናችሁት ሰው አለ?" አለ አራተኛው ሰው በቁጡ ድምፅ የያዘውን አውቶማቲክ መሣሪያ አፈሙዝ በከባድ መኪናው ሹፌር አቅጣጫ ደግኖ::

"የለም። ሁለታችን ብቻ ነን።" የሹፌሩ ድምፅ ከበስተግራ ተሰማ።

"ጭነታችሁን ገልጠን አንድ በአንድ እንፈትሻለን። ሰው ብናገኝ ወየውላችሁ። የምንከታተለው ከፍተኛ ወንጀለኞችን ነው። እውነቱን ንገሩኝ።" አለ መሣሪያውን የያዘው ሰው እየተቆነጠነጠ። "ፖሊሶች ነን... የምንከታተለው የመንግሥት ወንጀለኞችን ነው።"

"እንደፈለጋችሁ ፈትሹ፤ ሁለታችን ብቻ ነን።" አለ ትርፍ ሰው እንዳልጫነ ለአሩሱ እርግጠኛ የሆነው ሹፌር በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

"ጥሩ እንዳትነቃነቅ።" አለ አራተኛው ሰው መሣሪያውን ደግኖ እንደያዘ ወደ ጭነት መኪናው እየተጠጋ። በእርጋታ ወደፊት እየተራመደ በዓይኑ ጭነቱን ይዳብስ ጀመር።

እራቅ ብለው ሁኔታውን በዝምታ ይከታተሉ ከነበሩት ሦስት ሰዎች የመሃሉ ድንገት ተጣራና ጭንቅላቱን ወደኋላ መታ አደረገ። ወዲያው ወደ ጭነት መኪናው የተጠጋው አራተኛው ሰው ፊቱን መልሶ ወደ ጓደኞቹ ሮጥ ብሎ ተመለሰና ሰብሰብ ብለው ይነጋገሩ ጀመር።

"ጠዋት ምን ያህል መኪናዎች ቀድመዋችሁ ወደ አዲስ አበባ ተነስተዋል?" አለ አራተኛው ሰው ፊቱን ወደ ጭነት መኪናው ሹፌር መልሶ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

"አንድ ሶስት - አራት ይሆናሉ።" አለ ከጭነት መኪናው ወርዶ የቆመው ሹፌር።

ወዲያው አራቱ ሰዎች ሮጥ ሮጥ እያሉ ሬንጀሮቨራቸው ውስጥ ገቡና በአዲስ አበባ አቅጣጫ በረሩ።

"ኡፍ ...ፍ!" አለ ካልቨርት ጭንቅላቱን በተኛበት ጆንያ ላይ ጥሎ።
"ሄዱ?" አለ ናትናኤል ሸራውን እንደተከናነበ በሹክሹክታ።
"እዎ። ያለቀልን መስሎኝ ነበር።"

የጭነት መኪናው ሹፌር መኪናው ውስጥ ገብቶ ሲንቀሳቀስ በተቻላቸው መጠን መንፈሳቸውን አረጋግተው መመካከር ያዙ።

"ያለጥርጥር በየከተሞቹ ኬላዎች ላይ ይጠብቁናል። በተለይ ወደ አዲስ አበባ እየቀረብን ስንመጣ አስቸጋሪ ነው የሚሆንብን።" አለ ናትናኤል።



"እዎ። ከአሁን ወዲያ ወደየትኛውም ከተማ መግባት የለብንም። ወደ ከተሞች ስንቀርብ እየወረድን ከጀርባ በግማሽ ክብ ቅርፅ በእግር ማለፍ ነው ያለን አማራጭ።"

"ከናዝሬት ወዲያ ያለውን አካባቢ አውቀዋለሁ፤ መንገዱን በሩቅ እዩታ አስከተከተልን ድረስ ችግር አይገጥመንም።" አለ ናትናኤል።

ናዝሬት ከተማ ሊደርሱ አንድ አምስት ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው ከተደበቁበት ሸራ ውስጥ ብቅ ብቅ እያሉ ከኋላና ከፊት ሌላ ተሽከርካሪ አለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ በጭነቱ ላይ እየዳሁ ወደ መኪናው ኋላ ተጠጉ። ሸራው የተጠፈረባቸውን ወፍራም ገመዶች የሙጢኝ ጨምድደው ይዘው ቁልቁል ተንጠላጠሉ።

"ተጠንቀቅ። አስፋልቱ ላይ እንዳታርፍ። በሁለት እግሮችህ ለማረፍና ለመቆም አትሞክር፤ ከዘለልክ በኋላ ጭንቅላትህን ቀብረህ ተንከባለል። እኔ ስዘል ተመልከት።" አለ ካልቨርት በወጣትነት ዘመኑ በአገሩ ውስጥ ያሳለፋቸውን የኮማንዶ ህይወቱን እያስታወሰ።

በሰላሳ ሜትር ርቀት ልዩነት ሁለቱም የተንጠላጠሉባቸውን ገመዶች አዩለቀቁ ከጭነት መኪናው ላይ ተፈናጠሩ። ካልቨርት አልተጎዳም፤ ናትናኤል ግን ግራ ክንዱ ክፉኛ ተገሸለጠ።

"አስፋልቱ ላይ አትረፍ እያልኩህ እንዲያውም ተርፈሃል።ወደጎን ባትንከባለል ኖሮ ይሄ አስፋልት ጭንቅላትህን ነበር የሚፈረክስልህ።" አለ ካልቨርት እየሮጠ መጥቶ ናትናኤልን ደግፎ እያነሳው።

አውራ መንገዱን እየራቁ፤ እየሸሹ የናዝሬትን ከተማ በስተቀኝ ከጀርባዋ ዞሯት።

"መንገዱ ወደቀኝ የሚታጠፍ ስለሆነ ከዚህ በኋላ በቀጥታ መስመር ብንሄድ በሃያ ወይም በሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ላይ በዱከምና በሞጆ መሃል መንገድ ላይ ብቅ እንላለን።" አለ ካልቨርት ካርታውን አውጥተው ሲያጠኑት ከቆዩ በኋላ።

እንዳለው ከሦስት ሰዓት ተኩል የእግር ጉዞ በኋላ በሞጆ ከተማ አልፈው ከአውራ ጎዳናው ጋር ተገናኙ። ብዙም ሳይቆዩ አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ የነጠር አውቶቡስ እስቁመው ተሳፈሩ።

"አዲስ ፊሊጥ!" ይላሉ አውቶቡሱ ውስጥ ከሹፌሩ ጀርባ የተቀመጡ አዛውንት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው። "ከአውቶብሱ ገብቶ

መፈተሽ የአባት... 'ቀበሆን አውልቅ፤ ኳንቦንባሆን አውርድ' ብሎ ነገር ምንድነው? ወቸጉድ!"

"የሚፈልጉት ሰው አለ መሰለኝ::" አለ ባሻገር የተቀመጠ ልጅ እግር::

"ታዲያ ቢኖርስ! ባለፍንበት ከተማ ሁሉ እየቆምን ቀበና ኳንቦንባችንን መገፈፍ የአባት ነው? ልማድ ነው? ወይ ፈጣሪ!" ሽማግሌው ተቆጡ::

"ምንድነው?" አላቸው ናትናኤል ከጎኑ የተቀመጡትን ሴትዮ::

"እንጃ! ባለፍንበት ከተማ ሁሉ መሣሪያ ደግነው እንደ ሽፍታ ሲበረብሩን ዋሉ::" አሉት ሴትዮዋ መደነቃቸውን፣ መገረማቸውን ለማሳየት እጃቸውን አፋቸው ላይ ጣል አድርገው::

"እነማን ናቸው?" ናትናኤል ግራ የተጋባ መስሎ ጠየቃቸው::

"ምኑን አውቄው! ብቻ ከወለንጭቲ የጀመሩ ሰባቱ እያስቆሙ ሁለት ሁለት፣ሦስት ሦስት እየሆኑ እንዲህ-እንዲህ እያደረጋቸው ሲበረብሩን ዋሉ:: ሆ! እንደ አነሳሳችንክ ገና ቀድሞ ታዲስ አበባ ደርሰን ነበር... ጊዮርጊስ ይይላቸው"

ናትናኤል ዞር ብሎ ካልቨርትን ሹክ አለው::

ደብረዘይት ሊደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ተጠቃቀሱና መጀመሪያ ካልቨርት አራቀ ብሎ ደግሞ ናትናኤል ተከታትለው ወረዱ::

"ምንድነው?" አለ ካልቨርት አውቶቡሱ ውስጥ የተባለውን ሁሉ አጣርቶ ለመረዳት ጓጉቶ::

ናትናኤል አውቶቡሱ ውስጥ የሰማውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገረው::

"ከአሁን ወዲያ መኪና ላይ መውጣት የለብንም::" አለ ካልቨርት::
"ታዲያ እንዴት እናደርጋለን?"
"አሁን ሁለታችንም የተዳከምን ይመስለኛል:: ለጊዜው ከመንገድ ፈቀቅ ብለን እንረፍና ከጨለመ ወዲያ ሌሊቱን መንገዱን ተከትለን በእግራችን እንቀጥላለን:: ከበረታንና በሰዓት አምስት ኪሎ ሜትር ብንጓዝ እንኳን ከምሽቱ አንድ እስከ ጠዋቱ አንድ ሰዓት ስልሳ ኪሎ ሜትር ሸፈንን ማለት ነው:: ፀሐይ ስለማይበረታብን የምንሸነፍ አይመስለኝም::"



ከመንገዱ በስተቀኝ እርቀው ገብተው በአውላላው መሬት ላይ ለብቻዋ በቆመች የግራር ዛፍ ስር በደረታቸው ተደፍተው ለማረፍ ሞከሩ:: እየጠለቀች ያለችው ፀሐይ እንደጌጥ ብታብረቀርቅም ሙቀቷ እየከዳት መጣ:: አውላላው ሜዳ ላይ ብቻውን እየተመላለሰ የሚጋልበው ቀዝቃዛ ነፋስ ሰውነታቸውን ጠዘጠዘው፤ ምግብ ሳያገኝ ሁለተኛ ቀኑን የያዘው ሰውነታቸውም ከፊት የተደቀነውን መንገድ ቁጭ አድርጎ ተዳከመ:: ቢሆንም ፀሐይ ልትሸሸግ ሲዳዳት ከተኙበት ተነስተው የመንገዱን ጥግ ይዘው በአዲስ አበባ አቅጣጫ ጉዞአቸውን በእግር ተያያዙት::

"እርምጃህን አትቀያይር... በአንድ ዓይነት ፍጥነት አንድ አይነት ስፋት ተራመድ... አለበለዚያ ይደክምሃል::" አለ ካልቨርት እጆቹን እያወናጨፈ፤ ከጎን ከጎኑ የሚንቶሰቶሰውን ናትናኤልን ዞር ብሎ ተመልክቶ::

አልፎ አልፎ በሩቁ የመኪና መብራት ሲታያቸው ፈጠን ብለው ከአውራ መንገዱ አራቅ እያሉ መሬቱ ላይ በደረታቸው እየተኙ እያሳለፉ መንገዳቸውን ያለንግግር ቀጠሉ:: ሁለት ጊዜ ጅቦች ቢያጋጥሟቸውም ሁለቱንም ጊዜ የካልቨርት ሽጉጥ የጥይት ጩኸት አተረፋቸው::

እንዳሰቡት እስከጠዋቱ አንድ ሰዓት ድረስ አልተጓዙም:: ከጠዋቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ አቃቂ ከተማ እንደደረሱ ያለዕረፍት መቀጠል እንደማይችሉ ስለተረዱ ከመንገዱ ወጥቶ አራቅ ካለ ጫካ ውስጥ ገብተው ተኙ::

ካልቨርት እንቅልፍ ያዙት ጭልጥ አለ::ናትናኤል እስካሁን ያሳለፋቸውን ሁኔታዎች አንድ በአንድ በህሊናው እየመላለሰ ይቃኝ ጀመር:: ርብቃ... አብርሃም... የቢሮ አለቃው... ወታደራዊ አታሼዎቹ... ነጩዋ ሲትሮይን... የምሥራች... ዘውዲቱ... አዲስ አበባ... ድሬዳዋ...ካልቨርት...ይሄ ሁሉ ውጣ ውረድ... ከርብቃ ስቃይና ከእርግዝናዋ ጋር እየተሰባጠረ ይታየው ጀመር:: ርብቃን ለማዳን ምን ማድረግ አለበት? አውሬዎቹን መጋፈጥ? ከአውሬዎቹ ጋር መደራደር? ካልቨርት ምስጢሬን ይገፍ ልሙት ባይ ነው:: ካልቨርትን እንደገና ማግባባትና ማሳመን ይቻላል? ወይስ የሞተ ነገር ነው? ለማናቸውም ለካልቨርት ምንም ፍንጭ ማሳየት የለበትም... ማናቸውንም ጉዳይ ከካልቨርት መደበቅ ይኖርበታል::

የተጫናቸው ድካም በዙሪያቸው ከነበረው የማለዳ ውርጭ የከበደ ነበር:: ሁለቱም ለበርካታ ሰዓታት ተኝተው አረፈዱ:: በመጀመሪያ ከእንቅልፉ የነቃ ካልቨርት ነበር::

"ረፍዷል... የምንበላው ምናምን ብናገኝ የቀረንን መንገድ ተጠናክረን እንቀጥል ነበር::" አለ ካልቨርት::

ከእንቅልፉ ነቅቶ እግሮቹን እንፈራጦ ከጀርባው ያለ የዛፍ ግንድ ተደግፎ የተቀመጠው ናትናኤል በመዳፉ ፊቱን ሲያሻሽ ቆየና ቀና አለ።

"እስቲ አቃቂ ከተማ ቀስ ብዬ ገብቼ ምናምን እፈልጋለሁ።"

ናትናኤል ከተደበቁበት ጫካ ወጥቶ ሰፊውን ሜዳ አቋርጦ በግራ ጎን በኩል ከተማዋን ለሁለት ከፍሎ ሲገባ የጠበቀውን ያህል ብዙ ችግር አልገጠመውም።

ከአንድ አነስተኛ ኪዎስክ በሞላላ ላስቲክ ውሃ ይዞ ወደሌላ ሱቅ ተሻገረ። ከሱቁ ሁለት የላስቲክ ከረጢቶች ገዛና ዳቦ፣ የላስቲክ ወተትና ፍራፍሬዎች አጭቆባቸው በመጣበት መንገድ ከትንሿ ከተማ ሹልክ ብሎ ወጣ።

"ውሃውን ስጠኝ።" አለ ካልቨርት ናትናኤል ሁለቱን የላስቲክ ከረጢቶች አስቀምጦ ያመጣውን ዕቃ እያወጣ ሲደረድር።

"ብዙ አትጠጣ... ቁርጠት እዚሁ እንዳያውለን።" አለ ናትናኤል የውሃውን ላስቲክ ለካልቨርት እያቀበለው።

ዳቦውንና ፍራፍሬውን ተመግበው ወተቱን ጠጥተው ሲያበቁ ውሃውን ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ አዲስ አበባ በሩቁ ታየቻቸው።

"ከእንግዲህ ነፃ ነን።" አለ ካልቨርት።

"ምን ማለትህ ነው?"

"ከጥቂት ቀናት በኋላ አፍሪካ አንድ ትሆናለች።» አለ ካልቨርት ፊቱን ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ እንዳቀና ፈገግ አለና። «ነፃ እንደመሆን የሚጣፍጥ ምን ነገር አለ።"

"ምንም።" አለ ናትናኤል ካልቨርት ሽጉጥ የከተተባትን ሻንጣውን እየተመለከተ።

-35-

"አሁን ገና ሰው መሰልክ!" አለ ካልቨርት ፊቱ ፈገግታ ለብሶ።

"አይዞህ አንተም ውሃ ሲገላምጥህ ሰው ትመስላለህ።" ናትናኤል ፀጉሩን በፎጣ እያደራረቀ ወደተከራዩት የሆቴል ክፍል ገብቶ ከኋላው በሩን ዘጋው።



"ሀ! ሀ! ሀ! ለሁሉም ጊዜ አለው።" አለ ካልቨርት ከተቀመጠበት ተነስቶ የሚቀይረውን አዲስ ልብስ ተሸክሞ ወደ መታጠቢያ ቤት እየሄደ።

ካልቨርት ከክፍሉ ወጣ እንዳለ ናትናኤል ፈጠን ብሎ ካልቨርት ከጥግ ያስቀመጠውን ቦርሳ ይፈትሽ ጀመር። እንደተመኘውና እንዳሰበው፣ እንዳቀደው የካልቨርትን ሽጉጥ ቦርሳው ውስጥ አገኘው። ሽጉጡን ቶሎ ብሎ ከቦርሳው ውስጥ አወጣና ካርታውን አውጥቶ ጥይቱን ቆጠረ። ሰባት ጥይት በቂ ነው። ካርታውን በቦታው መለሰና ሽጉጡን አቀባብሎ መጠበቂያውን ለቆ በሩን እያየ ካልቨርትን ይጠባበቅ ጀመር። ምርጫ የለውም... ሌላ ምንም ምርጫ የለውም!

'ባይስማማስ? ጭራሽ ባይስማማስ? ፍንክች አልል ቢልስ? የራሱ ጉዳይ። እዚሁ ይጨርሰዋል። አለዛም ትቶት ይሄዳል፤ ብቻውን ይጋፈጣቸዋል። የሚላቸውን ካልሰሙትም ጉዳቸውን ያዝረከርከዋል። ጊዜ የለውም። ነገ ሳይመሽ ርብቃን እጁ ማድረግ አለበት... አለበለዚያ የሚመጣው አይታወቅም...'

ናትናኤል ከአልጋው ግርጌ እንደቆመ የርብቃን መጨረሻ ሲያስብ ሊደርስባት የሚችለውን አደጋ ሲያሰላስል ትንፋሹ አጠረው።

'የነገዋ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ርብቃን እጁ ማግባት አለበት። አለበለዚያ በግርግሩ አንድ ነገር ቢያደርጓት... በማታውቀው ምስጢር የመስዋዕት በግ ቢያደርጓት...እርሱ ነፍሱን ስለወደደ የገዛ ደህንነቱን ስለፈለገ ብቻ ቢያጠፏት... ከዚያ ወዲያ ምን ሊሆን ህይወቱ?' ናትናኤል ሽጉጡን ጨምድዶ እንደያዘ በተከራዩት ክፍል ውስጥ ካሉት አልጋዎች በአንደኛው ጫፍ ላይ ቁጭ አለና ካልቨርትን ይጠባበቅ ጀመር። የራሱ ጉዳይ! ካልተስማማ ትቶት ይሄዳል። ሊቃወመው ወይ ሊያቆመው ከሞከረ ግን... የራሱ ጉዳይ! ሞት ነው የሚጠብቀው። ናትናኤል የጨመደደውን ሽጉጥ ወደግራ እጁ አዙሮ በላብ የተጠመቀውን የቀኝ እጁን ሱሪው ላይ ሞዠቀና ሽጉጡን ጨበጠ።

ብዙም ሳይቆይ ካልቨርት ፎጣውን ትከሻው ላይ ጥሎ መንገድ ላይ ለብሶት የቆየውን በአቧራና በላብ የተበከለ ሸርጥና ሸሚዝ በጥያፌ በሁለት ጣቶቹ አንጠልጥሎ የተከራዩትን ክፍል በር ከፍቶ ሲገባ የገጠመውን ትርዒት ማመን አቃተው።

"ካልቨርት ምርጫ የለኝም... የማይሆን ነገር እንዳደርግ አታስገድደኝ።" አለ ናትናኤል ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ የያዘውን ሽጉጥ ቀና እያደረገ።

"ምንድነው የምትሰራው? ምን ልትሆን ነው?" አለ ካልቨርት የተሸከመውን ቆሻሻ ልብስ ወለሉ ላይ እየዘረገፈ።

"ከአንተ ምንም እርዳታ አልፈልግም:: ርብቃ ያለችበትን ሁኔታ እያወቅሁ በዝምታ መጠበቅ ግን አልችልም:: አዝናለሁ ካልቨርት... ሽጉጥህን ስለሰረቅሁ:: ግን ምርጫ የለኝም:: ይህንን ካላደረግሁ እስረኛህ እንደምታደርገኝ ግልጽ ነው::"

"ስማ!" አለ ካልቨርት በንዴት መንፈስ ወደፊት አንድ እርምጃ እየተራመደ::

"አ! አ!" ናትናኤል የሽጉጡን አፈሙዝ ካልቨርት ላይ ደግኖ ተነስቶ ቆመ:: "እንዳትጠጋኝ:: ምኝ ነገር አትፈጽም:: ክፉ ነገር መፈጸም አልፈልግም:: ግን ምርጫ የለኝም... ካስገደድከኝ ደፍቼህ ነው የምወጣው::"

ካልቨርት ተስፋ በመቁረጥ አልጋው ላይ ቁጭ አለና ፊቱን ሁለት መዳፎቹ ውስጥ ቀበረው::

"ናትናኤል የምትሰራው ጥፋት ነው... ከአሁን ወዲያ ምንም ልትረዳት አትችልም:: እጃቸው ውስጥ ነች::"

"አስፈራራቸዋለሁ! አንተ የምስራችን እንዳይነኩ እንዳስፈራራሯቸው አስፈራራቸዋለሁ::"

"እናስ ከዛስ?"
"ይለቋታላ!"
"ሞኝ አትሁን:: እርግጥ ይለቋት ይሆናል... ግን ከለቀቋት ወዲያ እንደ ወጥመድ ነው የሚጠቀሙባት... ምክንያቱም ወይ በስልክ ወይ በአካል ልትገናኛት መሞከርህ አይቀርም:: አትጠራጠር ይይዙሃል::"

"ከያዙኝ ይያዙኝ... ዝም ብዬ ግን አልቀመጥም"
"ባይስማሙስ? ባይለቋትስ?"
"አወጣዋለሁ-ምሥጢራቸውን::"

ካልቨርት ቀና ብሎ በቁጣ ፊት ናትናኤልን ገላመጠው::

"አታደርገውም... የምትጎዳው እነሱን አይደለም... አፍሪካን ነው:: ነገሮችን አስፍቶ የሚያይ ጭንቀላት ካለህ የምልህ ይገባሃል:: የዚህን ዓይነት ጥፋት ስታጠፋ ደግሞ በዝምታ አልመለከትህም::"

"ሽጉጡ ያለው በእኔ እጅ ነው::"



"ተኩስ! ፈሪ!" ካልቨርት ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ ተነሳ::

"ተጠንቀቅ ካልቨርት... ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ይመስላል ብለህ አታስብ... እንደዛፍ ነው በቁምህ የምጥልህ::" ናትናኤል ጥርሱን ነክሶ አፈጠጠ::

የናትናኤልን አዘማማይ ሲመለከት ካልቨርት ራሱን ነቀነቀና ተመልሶ አልጋው ላይ ተቀመጠ::

"እና አሁን ምን ልታደርግ አሰብክ?" አለ ካልቨርት::
"ጠዋት ስልክ ደውዬ እነግራቸዋለሁ፤ አስጠነቅቃቸዋለሁ:: ከዚያ ወዲያ የራሳቸው ምርጫ ነው::"

"ናትናኤል እስቲ አስበው በቀላሉ ድምፃችንን ብናጠፋ ሁሉ ነገር ጊዜውን ጠብቆ መድኃኒት ያገኛል... እመነኝ ይለቋታል::"

"ባይሳካስ? ዕቅዱ ቢከሽፍስ? ጉዳቸውን ለመስጠር ለመደበቅ እንደሚገድሏት አታውቅም:: ካልቨርት መፍጠን አለብኝ! አንድ ነገር ብትሆን ለራሴ ይቅርታ አላደርግለትም::"

"ናትናኤል ስሜትህ ይገባኛል... ምናልባት እኔም በአንተ ቦታ ብሆን ተመሳሳይ ስህተት ለመፈጸም እገፋፋ ይሆናል:: ለምን እንዲህ አናደርግም... ጥፋት ማጥፋታችን ካልቀረ አንስተኛ ጥፋት ይሻላል::" ካልቨርት ያሰበውን ዕቅድ ለናትናኤል በእርጋታ ተነተነለት::

"አይሆንም! ይይዙናል::"

"ይገባኛል... ሊይዙን ይችላሉ... ግን እንዳልከው በስልክ ልታስፈራራቸው ብትሞክርም መያዝህ አይቀርም:: የእኔ መንገድ ይሻላል:: ሁልጊዜ የተሻለው አስተማማኙ መንገድ ይበልጥ አደገኛና ይበልጥ አስፈሪ፤ ይበልጥ አስደንጋጭ የሆነው፤ ጤነኛ ሰው በጤነኛ አእምሮው የማይመርጠው መንገድ ነው... አትጠራጠር::"

"ግን ቢይዙንስ?"
"አሰቀልና! ምነው ፈራህ እንዴ?" ካልቨርት ፈገግ አለ:: «ቢያዙ ኝም ይያዙኝ አላልክም ዋናው ነገር ፍቅረኛህን ከመዳፋቸው ማውጣታችንና የእነሱንም ዕቅድ አለማደናቀፋችን ነው... ለዚህ ደግሞ የተሻለው መንገድ የእኔ ነው:: ትስማማለህ? "

ናትናኤል በዝምታ ማውጣትና ማውረድ ያዘ::

"አትፍራ።" አለ ካልቨርት ፈገግ ብሎ።
"አልፈራሁም!" በስጨት አለ ናትናኤል።
"እንግዲያው እንስማማ..." ካልቨርት ቀኝ እጁን ዘረጋለት "እንተማመን ናትናኤል ... ደግሞ እሱን ሽጉጥ ዞር አድርገው። ቢባርቅ ሆዴን ነው የምትዘረግፈው።"

"ካልቨርት ልታታልለኝ ብትሞክር..." አለ ናትናኤል በጥርጣሬ ፊት ካልቨርት የዘረጋለትን እጁን እየተመለከተ። "ከአሁን በኋላ ሁለቴ ለማሰብ ጊዜ የለኝም። እንዲት አጉል እንቅስቃሴ ካደረክ አንጉል ነው የምትሆነው።"

"ቃል እገባልሃለሁ።" አለ ካልቨርት እጁን ወደፊት እንደዘረጋ።

ናትናኤል ሽጉጡን ወደግራው አሻግሮ የተዘረጋውን የካልቨርትን እጅ በቀኙ ጨበጠው።

"ጥሩ... አሁን እቅዳችንን አንድ በአንድ ተንትነን እንነጋገርበት... ካጠፋን አይቀር።" አለ ካልቨርት ሁለት ወንበሮች አምጥቶ አንዱን ለናትናኤል አቀብሎት በሁለተኛው ላይ እየተፈናጠጠ።

ፊት ለፊት ቁጭ ብለው በማግስቱ ስለሚፈፅሙት ተግባር አንድ በአንድ ተነጋገሩ ተመካከሩ፤ ተከራከሩ፤ ተስማሙ።

-36-

ሰማዩ ጥርት ብሏል። ለጋዋ ፀሃይ ከእንቅልፏ እንደነቃች ሁሉ ከረጅሙ የክረምት ጨለማ በኋላ በሰማዩ ላይ ብቻዋን ትምነሸነሸበታለች። አለፍ አለፍ እያሉ እንደ እረፍ የተኩረፈረፉት ነጫጭ ደመናዎች ዝናብ ያዘሉ ሳይሆን ለጌጥ የተንጠለጠሉ የጥጥ ንድፎች ይመስላሉ። ንፋሱ ጠንከሯል። በየአውራጎዳናዎቹ ጥግና ጥግ የተሰቀሉት የአፍሪካ አገሮች ባንዲራዎች ያረግዳሉ፤ ያሽበሽባሉ፤ ይጨፍራሉ፤ ያጨበጭባሉ... እርስ በእርስ እየተጎናተሉ ያወካሉ፤ ሊመጣ ያለውን የገመቱ የጠረጠሩ ይመስል... ያንሾካሹካሉ።

የአፍሪካን ታላላቅ መሪዎች ተቀብላ ለማስተናገድ ትንፋሽ አጥታ እላይ እታች ስትል የሰነበተችው አዲስ አበባ ቀኑ ሲደርስ ሰዓቱ ሲቃረብ ለአንድ አፍታ ቆም ረጋ ብላ የገዛ የመስተንግዶ ዝግጅቷን እየጎበኘች እንደምታደንቅ ሴት ወይዘሮ አደብ ገዛታለች። ከወትሮው በርከት ብለው የሚታዩት ፀጥታ አስከባሪ የፖሊስ አባላት የመጥናኛ ሬድዮኖቻቸውን



በየጆሮዎቻቸው ላይ እንደለጠፉ በየኩርባው ባቆሟቸው ተሽከርካሪዎቻቸው ውስጥ ተቀምጠው ዙሪያቸውን ይቃኛሉ።

መሪዎች ወደ ከተማዋ መግባት ጀምረዋል። ከአውሮፕላን ማረፊያው ሜዳ ወደ ከተማዋ የሚወስደውን አንድ አውራ መንገድ ይዘው እየተከታተሉ በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ውስጥ ፒም! ፖም!..... ፒም! ፖም! እያሉ በተራ ወደ ከተማዋ እምብርት ይጎርፋሉ። ለፋሲካ እንደተገዙ ዶሮዎች እያስካኩ አጀብ አጀብ ብለው ይተማሉ... ወደ አዲስ አበባ።

"ማነው ይሀኛው?" ይላል አንዱ መንገደኛ ለአንድ አፍታ ቆም ብሎ አንደኛውን የአፍሪካ መሪ የያዘችው መኪና ከነአጃቢዎቿ ወደ መሃል ከተማ ስትጣደፍ። "የዚህ አገር መሪ... እገሌ ነው።" ይላል ከመኪናዋ አፍንጫ ላይ የሚውለበለበውን ባንዲራ ተመልክቶ የመሪውን ማንነት የለየ ወይ የገመተ ሌላ መንገደኛ። መኪናዎቹ ተከታትለው ሲነጉዱ... ለዓይን ሲርቁ መንገደኛው ሁሉ ፊቱን ወደየእቅጣጫው ይመልሳል። ፒም! ፖም!... ፒም! ፖም! "ይሄ ደግሞ ማነው?" ፒም! ፖም!... ፒም! ፖም! "ይሄኛውስ ደግሞ?"

ቀትር ላይ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ወደ ከተማዋ የገቡትን መሪዎች ዝርዝር ጠቅሶ የተቀሩትም ከሰዓት በኋላ ወደ ከተማዋ ገብተው እንደሚጠቃለሉ ስብሰባውም ምሽት ላይ በወቅቱ ሊቀመንበር የመክፈቻ ንግግር እንደሚከፈት በአድናቆት አወሳ።

ባንዲራዎች ተርገበገቡ... አጨበጨቡ... አወኩ.... አንሾካሾኩ...

እንደተጠበቀው ከሰዓት በኋላም የመላው አፍሪካ መሪዎች ወደ አዲስ አበባ መግባታቸውን ቀጠሉ።

መሃል ፒያሳ ውስጥ ሁለት የቴሌኮሙኒኬሽን ሠራተኞች መንገድ ጥግ የቆመ የስልክ መስመር ማከፋፈያ የብረት ሳጥን ከፍተው ብልሽት ይጠግናሉ። ከመንገድ ባሻገር ሠራተኞቹን ይዛ የመጣችው የቴሌኮሙኒኬሽን አነስተኛ የጭነት መኪና ከጀርባ የብረት መሰላሏን እንደጫነች ጥግ ይዛ ቆማለች። ስራ የፈታው ሹፌር የስራ ባልደረቦቹ ብልሽቱን ጠግነው አስኪጨርሱ ድረስ እዚያው ባለበት መኪናው ውስጥ እንደተቀመጠ ጋዜጣ ያነባል።

አንድ ካኪ የለበሰ ቀጠን ረዘም ያለ ሰው መንገዱን ተሻግሮ ወደ ቴሌኮሙኒኬሽኗ መኪና ተጠጋ። ከጀርባዋ ከዞራት በኋላ ቀልጠፍ ብሎ ከሹፌሩ ባሻገር ያለውን በር ከፍቶ ጥልቅ አለ።

ሹፌሩ ጋዜጣውን ወደጎን ብሎ መኪናው ውስጥ የገባውን እንግዳ ሰው በጥያቄና ግራ በመጋባት ይመለከተው ጀመር።

“ምን ትፈልጋለህ?” አለ ግራ የተጋባው ሹፌር የመኪናዋን በር በርግዶ የገባውን ሰው እብድ እንደሆነ ሁሉ አፍጦ እየተመለከተው:: ወደ መኪናዋ የገባው ሰው እጁን ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ የጨበጠውን ሽጉጥ ሹፌሩ ላይ ደገነበት::

“ለጭቅጭቅና ለማስፈራራት ጊዜ የለኝም የምልህን ብቻ ትፈጽማለህ::” አለ ሽጉጡን የያዘው ሰው ድንገት በፍርሃት በገረጣው ሹፌር ላይ አፍጥጦ:: “መኪናውን አስነስተህ ወደፊት ቀጥል:: ማንም ቢጠራህ ወይም ሊያስቆምህ ቢሞክር እንዳታቆም:: ቀጥል::”

አንድ ጊዜ ሽጉጡን አንድ ጊዜ ከጎኑ የተቀመጠውን እብድ በፍርሃት ሲመለከት የነበረው ሹፌር የማይሰማ ፀሎት እያነበነበ መኪናዋን አስነስቶ ከመንገድ ገባ::

“ፍጥነት ጨምር...አዎ... እየተገላመጥክ እኔን ማየትህን ተውና ዝም ብለህ ንዳ! አቁም::” አለ ሽጉጥ የያዘው ሰው ብዙም ርቀው ሳይሄዱ::

አለቅጥ የተሸበረው ሹፌር የመኪናዋን ፍጥነት ቀነሰ ጥግ ያዘ:: ከመንገድ ጥግ ለጠፍ ብሎ ቆሞ የነበረ አነስተኛ የሸራ ቦርሳ ያነገበና ካኪ ቱታ ያጠለቀ አጠር ብሎ ከትከሻው ሰፋ ያለ ሰው ራመድ ራመድ ብሎ መኪናዋን በፊት በኩል ዞረና በሹፌሩ በኩል ያለውን በር ከፈተው::

“ጠጋ በልለት ወዲህ::” አለ ሽጉጡን የያዘው የመጀመሪያው ሰው የመሣሪያውን አፈሙዝ ሹፌሩ ብብት ውስጥ ደግኖ::

ሹፌሩ በሁለቱ ካኪ ቱታ በለበሱ ሰዎች መሃል ተቀምጦ ሽጉጡን በብብቱ ታቅፎ የሚያደርጉትን በፍርሃት ይከታተል ጀመር::

“የተከተለኝ ሰው አለ?” አለ ሽጉጥ የያዘው ሰው አዲስ መጪውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ::

“ማንም አልተከተለህም::” አለ አዲስ መጪው ጥቁር ሰው የመኪናዋን ሞተር አስነስቶ ወደ መንገድ እየገባ::

የቴሌኮሙኒኬሽኗ መኪና ከጀርባ የብረት መሰላሏን እንደጫነች ከፒያሳ ግርግርታ መሃል ወጥታ ቁልቁል በቸርችል ጎዳና ወርዳ በለገሃር አድርጋ ፊቷን ወደ አስመራ መንገድ መለሰች::

መሃል አስመራ መንገድ ላይ መኪናዋ ወደ ቀኝ ታጥፋ ከአንድ የሆቴል አጥር ግቢ ገባች:: በግቢው ውስጥ ጥቂት መኪናዎች ፈንጠር ፈንጠር ብለው ቆመዋል:: ጥቂቶቹ ተጋባዦች ከየመኪናዎቻቸው ወርደው



ሲገቡ የተቀሩት እዛው በየመኪናዎቻቸው ውስጥ የሚፈልጉትን አስመጥተው ተቀምጠዋል:: የቴሌኮሙኒኬሽኗ መኪና አንድ ጥግ ይዛ ቆመች::

“ለመጮኽ ወይ ለመሮጥ ወይ ሌላ ድላድል ሁኔታ ለመፍጠር ብትሞክር አከርካሪህን ነው የምመነግልልህ::” አለ ሽጉጥ የያዘው ሰው በጓደኛውና በራሱ መሃል ወደተቀመጠው የቴሌኮሙኒኬሽን ሹፌር ፊቱን መልሶ:: ልሳኑ የከዳው ሹፌር በመስማማት ራሱን ነቀነቀ::

ሽጉጡን የያዘው ሰውና ጓደኛው ከተጠቃቀሱ በኋላ በሮቻቸውን እየከፈቱ ወረዱ::

“ውረድ::” አለ ሽጉጡን የጨበጠው ሰው መሣሪያውን ከካኪ ቱታው ኪስ ውስጥ ወሽቆ::

ሹፌሩ እንደታዘዘው ወረደ:: ግራና ቀኝ አጅበውት በሆቴሉ ከጥቂት ሰዓታት በፊት ወደተከራዩት ክፍል ይዘውት ሄዱ:: ከክፍሉ እንደደረሱ ባለሽጉጡ ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ በሩን ከፈተና የሹፌሩን ክንድ በግራው አፈፍ አድርጎ ወደ ውስጥ ገባ:: ከኋላቸው ጓደኛየው ከተል አለና በሩን ከውስጥ ቀረቀረው::

ጊዜ አልወሰደባቸውም:: የቴሌኮሙኒኬሽኑን ሹፌር ከአንድ ወንበር ላይ አስቀምጠው እግሮቹን ከወንበሩ እግሮች ጋር እጆቹን ደግሞ ከድጋፍ ቋሚዎች ጋር የኋሊት ግጥም አድርገው ካሰሩት በኋላ አፉን በጨርቅ ጠቅጥቀው ለጎሙት:: ስራቸውን እንደጨረሱ ከሆቴሉ ክፍል ወጥተው ወደ አነስተኛዋ የጭነት መኪና ተጣደፉ::

* * *

ከዋናው መንገድ ብዙም ሳይርቁ የመኖሪያ ቤቶች ከተደረደሩበት የሠፈር ውስጥ መንገድ ዳር አንድ ጥግ ላይ መኪናቸውን አቆሙ::

መኪናዋ ጥግ ይዛ እንደቆመች ናትናኤል የመኪናዋን ሬድዮ ከፈተው:: ጎርናና የጋዜጠኛ ድምፅ መኪናዋ ውስጥ አስተጋባ::

“... እንዲሁም የአንጎላና የሞሮኮ የሴኔጋልና የቡሩንዲ መሪዎች ከሰዓት በኋላ አቀባበል ሲደረግላቸው እስከሁን ወደ አፍሪካዋ መዲና ያልገቡት ሦስት የአፍሪካ መሪዎች ማለትም የሴራሊዮን የጋቦንና የቡርኪናፋሶ መሪዎች ምሽቱን ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል:: በወጣው ፕሮግራም መሠረት ዛሬ ሰኞ መስከረም አራት ምሽት በሁለት ሰዓት ተኩል

ያልገቡት ሦስት የአፍሪካ መሪዎች ማለትም የሴራሊዮን የጋቦንና የቡርኪናፋሶ መሪዎች ምሽቱን ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። በወጣው ፕሮግራም መሠረት ዛሬ ሰኞ መስከረም አራት ምሽት በሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ጠቅላላ የአፍሪካ መሪዎች የሚገኙበት ስብሰባ ሲከፈት... ይቅርታ አድማጮቻችን አሁን ዘግይቶ የደረሰን ዜና አለ... የሴራሊዮኑን መሪ የያዘችው አውሮፕላን አዲስ አበባ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ማረፊያ አርፋለች... ፕሬዚዳንቱ የክብር ሠላምታ ላቀረበላቸው... አፀፋውን..."

ናትናኤል ሬዲዮኑን ዘጋው።

"ሁለት ቀሩ።" አለ ናትናኤል አይኖቹን አቦዝዞ ለራሱ እንደሚናገር ሁሉ።

ጊዜው እየሄደ ሰዓቱ እየቀረበ ሲመጣ... ተራርቀው የዋሉት ደመናዎች እየተጠራሩ እጅ ለእጅ መያያዝ ጀመሩ። ቀኑን ሙሉ ማን አለብኝ ብላ ያለርህራሄ ምድሪቷን ስትወቃት የዋለችው ፀሃይ የተባበሩትን ደመናዎች ማለፍ ሲያቅታት ዙሪያው ቀዝቀዝ ተንፈስ አለ። ንፋሱ ብቻ እንደ ወሬ ነጋሪ ከወዲያ ወዲህ ይመላለስ ጀመር።

ሁለት ሰዎች የጫነች የቴሌኮሙኒኬሽን የጥገና መኪና ከአስመራ መንገድ ተነስታ በላይኛው ቤተመንግስት አድርጋ ፒያሳን ስሁልት ከፍላ ሲኒማ ኢትዮጵያ አጠገብ ስትደርስ ሊመሻሽ ተቃርቦ ነበር። መኪናዋ ሲኒማ ኢትዮጵያ እንደደረሰች አደባባዩን ዞረችና ቁልቁል ወረደች። ብዙም ሳትርቅ ከአንድ የአፓርትመንት ህንፃ የአጥር በር ፊት ለፊት ቆመች።

"አቤት።" አሉ አፈርማ ካፖርት የደረቡ የአፓርትመንቱ የማታ ዘበኛ የብረቱን በር ከፈት አድርገው ብቅ አሉና።

"እንደሌ ይከፈቱልን አባክዎት።" አለ ከሹፌሩ ጎን የተቀመጠው ሰው ጭንቅላቱን በመስኮት ብቅ አድርጎ። "ስልከኞች ነን... የተበላሸ ስልክ ለመጠገን ነው።"

ሽማግሌው እያቅማሙ የብረቱን በር ወለል አድርገው ከፈቱት። የቴሌኮሙኒኬሽኗ መኪና ወደ አፓርታማው ግቢ ገብታ ጥግ ይዛ ቆመች። ወዲያው ካኪ ቱታ የለበሱ ሠራተኞች ፈጠን ብለው ከመኪናዋ ወርደው የጥገና መሣሪያዎቻቸውን የያዙባቸውን ቦርሳዎቻቸውንና ሌሎችንም ዕቃዎቻቸውን አንግበው ወደ አፓርትመንቱ በር ተጣደፉ።

ከመጀመሪያው ደርብ እንደደረሱ ወደግራ ብለው በጠባቡ መተላለፊያ ፊትና ኋላ ራመድ ራመድ እያሉ ቀጠሉ። '21' የተለጠፈበት በር አጠገብ እንደደረሱ ተያዩ። ወዲያው በሩን አልፈው '22' የሚል ቁጥር የተለጠፈበትን የሚቀጥለውን በር አንኳኩ።



"አቤት?" አለች በሩን የከፈተችው ልጅ እግር ሴት ህፃን ልጅ እንዳቀፈች።

"ከቴሌኮሙኒኬሽን ነው። በአካባቢው የተበላሹ ስልኮች አሉ። የናንተንም ለማየት ነበር።"አላት ቀጠን ቀላ ያለው።

"ደህና ነው የኔ ስልክ።" አለች ሴትየዋ በተራ እያየቻቸው።

"ገብተን እንየው?" አላት የመጀመሪያው ሰው።

"ግቡ-ግቡ።" አለች ሴትየዋ የታቀፈቻትን ህፃን ከመሬት አውርዳ በሩን በሰፊው እየከፈተችላቸው።

ካኪ ቱታ የለበሱት ሁለት ሰዎች ተከታትለው ገቡ።

"ቀድም ስንደውል ያነጋገሩን እርሶ ኖት?" አላት ቀጠን ያለው።

"አይ እዚህ አልደወላችሁም።"

"ምናልባት ሌላ ሰው አንስቶት እንዳይሆን..."

"እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት በቤቱ፤ ከሷ በስተቀር።" አለች ሴትየዋ ፈገግ ብላ የህፃን ልጇን ጭንቅላት እየደባበሰች። "እዚህ አልደወላችሁም።"

ሰዉዬው የፈለገውን ያገኘ ይመስል ጊዜ ሳይወስድ ከቱታው ኪስ ውስጥ ሽጉጥ አውጥቶ ሴትየዋ ላይ ደገነባት። ከጎኑ ቆሞ የነበረው ጥቁር ሰው ያንጠለጠለውን የሸራ ቦርሳ ወደጎን ጥሎ በሚያስደንቅ ፍጥነት አፏን አፍኖ ወንበር ላይ አስቀመጣት። ሽጉጥ የያዘው ሰው ማልቀስ የዳዳትን ህፃን ልጅ ከመሬት አንስቶ ታቀፋት።

"አይዞሽ አንቺንም ሆነ ልጅሽን የመጉዳት ሃሳብ የለንም። ነገር ግን ለመጮህ ወይ ለመሮጥ ብትሞክሪ ጥሩ አይሆንም ውጤቱ።" አለ መሣሪያ የያዘው ሰው የሽጉጡን አፈሙዝ በህፃኗ ለስላሳ አንገት ውስጥ እያፍተለተለ።

ሽጉጡን የያዘው ሰው ምልክት ሲሰጠው አፏዋን አፍኖ የያዛት ሰው ለቀቃት።

"ምንድነው የምትፈልጉት? የምትፈልጉትን ያዙና ውጡልኝ።" አለች ልጇ አንገት ስር የተሸጎጠውን ሽጉጥ የተመለከተችው እናት እየተርበተበተች።

"ሌቦችና ቀማኞች አይደለንም። ጉዳት ልናደርስብሽም አይደለም የመጣነው። እርዳታሽን ብቻ ነው የምንፈልገው።" አላት ቀጠን ያለው ሰው ህፃኗን እንዳቀፈ ከተቀመጠችበት ወንበር አጠገብ በርከክ ብሎ።

"ምንድነው የምትፈልጉት?" አለች ሴትየዋ አይኖቿን በሁለቱ አፋኞች ላይ በተራ እያንከራተተች::

"እዚህ ጎረቤትሽ '21' ቁጥር ውስጥ ያለችውን ሴት ታውቂያታለሽ?" አለ ልጇን የታቀፈው ሰውዬ ማልቀስ የጀመረችውን ህፃን ለማባበል እየጣረ::

"አዎ... ርብቃ ትባላለች... ልጅን ልቀቅልኝ::"

ህፃኗን የታቀፈው ሰው እየተቁነጠነጠች ያስቸገረችውን ህፃን ለእናቷ ካቀበለ በኋላ ወንበር ስቦ አጠገቧ ተቀመጠ::

"ይህን ሰሞን አይተሻታል?" አለ የያዘውን መሣሪያ ከቱታው ኪስ ውስጥ እየጨመረ::

"አላየኋትም:: ረጅም ጊዜ ነው ካየኋት... ግን ሌሎች ሰዎች ወደ ክፍሏ ሲገቡና ሲወጡ አይቻለሁ:: ምንድነው የምትፈልጉት ከኔ?" ሴትየዋ ልጇን እቅፍ አድርጋ ይዛ እያባበለች አፈጠጠችበት::

"ምን ያህል ይሆናሉ ሰዎቹ?" ጠየቃት::

"የቶቹ ሰዎች?" መልሳ ጠየቀችው::

"ክፍሏ ውስጥ ያሉት ሰዎች::"

"እኔ እንጃ... ሲገቡና ሲወጡ ነው ያየኋቸው... ውስጥ ይኑሩ አይኑሩ አላውቅም::"

ቀጠን ያለው ሰው በርከክ ካለበት ተነስቶ በፀጥታ ከቆመው ጓደኛው ጋር በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሹክሹክታ ያወራ ጀመር:: ወዲያው ፊቱን ወደ ሴትየዋ መለሰ::

"እንዳልኩሽ እርዳታሽን እንፈልጋለን:: ጉዳት ላይ እንድትወድቂ አንፈልግም:: የምልሽን ያለማወላወል መፈጸም አለብሽ:: አለበለዚያ ግን ያልጠበቅነው አደጋ ሊደርስ ይችላል::"

"ምንድነው የምትፈልጉት?" አለች ሴትየዋ ግራ ተጋብታ:: ተራ ሌቦችና ቀማኞች አለመሆናቸውን ስታረጋግጥ ድፍረቷ ተሰባሰበላት:: ኮስተር ብላ ተመለከተችው::

"አብረሽን ወደሚቀጥለው ክፍል ትሄጂና በሩን ታንኳኪያለሽ::"

"እኔ የማላውቀው ሰው ቤት ሄጄ አላንኳኳም::". አለች ነገሩ ያልጣማት ሴትዮ የልጇን ጭንቅላት ጡቶቿ መሃል ቀብራ::



"ምርጫ የለሽም:: እምቢ ካልሽን እኛም የማንወደውን እንድንፈጽም እንገደዳለን::" አለ ሽጉጡን የያዘው ሰው ጎንበስ ብሎ የህፃን ልጇን ጭንቅላት እየደባበሰ:: "ተነሽ... የፍርሃት መልክ አታሳዪ:: በሯን ካንኳኳሽ በኋላ ትጠባበቂያለሽ:: በሩ ሲከፈት..." ማድረግ የሚገባትን ሁሉ አንድ በአንድ እያስረዳ ክንዷን ይዞ ከተቀመጠችበት አስነሳት::

ሴትየዋ ህፃን ልጇን እንደታቀፈች ከሁለቱ አፋኞቿ ጋር ከክፍሏ ወጥታ ጭር ባለው መተላለፊያ ወደሚቀጥለው ክፍል አመራች:: ከጎረቤቷ ክፍል መዝጊያ እንደደረሱ ሁለቱ ሰዎች በበሩ ግራና ቀኝ ጀርባቸውን ለጥፈው ቆሙ:: ቀጠን ያለው ሰው ሽጉጡን አውጥቶ ደረቱ ላይ ለጥፎ ያዘው:: በስተግራዋ ያለው ሰው ደግሞ ከሸራ ቦርሳው ውስጥ አውጥቶ የያዘውን ወፍራም የብረት ቱቦ ጫፍና ጫፍ በሁለት እጆቹ ጨብጦ የተጠመጠመ የኤሌክትሪክ ሽቦ በትከሻው ላይ እንዳነገበ ጀርባውን ግድግዳው ላይ ለጠፈው::

ለአንድ አፍታ ፀጥታ ሰፈነ:: ህፃን ልጅ ይዛ በሩ ፊት የቆመችው ሴት በጭንቀትና በፍርሃት በተራ ተመለከተቻቸው::

"አንኳኪ::" አላት በጆሮዋ ቀጠን ያለው ሰው በሽጉጡ ወደ በሩ እያመለከታት::

ሴትየዋ በግራ እጇ ህፃን ልጇን እንቅ አድርጋ እንዳቀፈች ወደ በሩ ጠጋ አለችና በቀስታ በሩን አንኳኳች:: መልስ የለም:: በቀኟ የቆመው ሰው ጭንቅላቱን መታ አድርጎ ድጋሚ እንድታንኳኳ ምልክት ሰጣት:: በግንባሩ ላይ ሽፍ ያለው ላብና ነክሶ የያዘው የታች ከንፈሩ ስሜቱን ያሳጣሉ::

ሴትየዋ ድጋሚ በሩን አንኳኳች:: ከውስጥ የእግር ኮቴ ተሰማ:: የበር ቁልፍ ሲከፈት የሚያሰማው ድምፅ ለሦስቱም ተሰማቸው::

ናትናኤል የሌባ ጣቱን ሽጉጡ ቃታ ላይ ሳለማሳረፍ ከራሱ ጋር ታገለ:: ጥይት መተኮስ የለበትም:: ሁሉንም በፀጥታ መፈጸም አለባቸው:: በተስማሙት መሠረት ቀድሞ መግባት ያለበት ጉልበቱና ልምዱ ያለው ካልቨርት ነው:: ከዚያ በኋላ ነው እሱ ሽጉጡን ደግኖ መከተል ያለበት... ድምፅ መሰማት የለበትም... የአፓርትመንቱ ነዋሪዎች ከየክፍሎቻቸው ብቅ ብቅ ማለት የለባቸውም:: ከራሱ ጋር ሙግት ያዘ::

የበሩ እጀታ ወደታች አዘምሞ በሩ በቀጭኑ ተከፈተ::

"ምንድነው?" አለ የወንድ ድምፅ::

"ናትናኤል ነው የላከኝ::" አለች ህፃን ልጅ የተሸከመችው ሴት በተነገረችው መሠረት::

"ማን?" አለ ሰውየው በቀጭኑ ከፍቶ የያዘውን በር ይበልጥ ከፊት አድርጎ ጭማሪ ለመስማት ወጣ እያለ።

ያን ጊዜ በስተግራ ግድግዳው ላይ ተለጥፎ የነበረው ካልቨርት ወደቀኝ እንደ ወስፈንጥር ተወንጭፎ የያዘውን የብረት ቱቦ በሰውየው መሃል አናት ላይ አሳረፈው። በሩን በትከሻው በርግዶት ገባ። ናትናኤል በድንጋጤ በድን የሆነችውን ሴት ወደፊት ገፍቶ በበሩ አግድም በተዘረረው ሰው ላይ ተሻገረና የሴትዮዋን ክንድ እንደጨመደደ ወደ ውስጥ ተንደረደረ። መጀመሪያ ሲንቀሳቀስ ባየው ነገር ላይ ሽጉጡን ደገኖ ጮኸ...

"እንዳትነቃነቅ!" አለ ናትናኤል ከሳሎኑ መስኮት በስተግራ ፎቴ ላይ የተቀመጠው ሰው ላይ አፍጥጦ።

ማርቆስ ጆሮ ያለው አልመሰለም። ያለማወላወል ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ወደቀኝ ተወርውሮ መሬቱ ላይ እንደዬ ተንከባለለና ለአይን ለመከተል በሚያስቸግር ፍጥነት የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጡን አውጥቶ ተኮሰ። የታፈነውን የጥይት ድምፅ ተከትሎ ናትናኤል ሚዛኑ ከዳው። የግራ ጉልበቱ በገዛ ክብደቱ ስር ዋለለበት። በቁመቱ ሙሉ ተዘረጋ። በስተቀኝ ሽብረክ ብሎ የነበረው ካልቨርት እንደ ነብር ተወርውሮ በርከክ ያለው ማርቆስ ተጨማሪ ጥይት ከመትፋቱ በፊት ተከመረበት።

ካልቨርት በግራ እጁ ከስሩ የተኛውን የማርቆስን ቀኝ እጅ ይዞ ከወለሉ ጋር ሲያጋጨው ሽጉጡ ከማርቆስ እጅ አፈትልኮ በበሩ አቅጣጫ ተፈናጠረ።

ማርቆስ ተስፋ አልቆረጠም።የቀኝ ጉልበቱን እንደ መብረቅ ወርውሮ በካልቨርት ጉልበቶች መሃል አጋጨው። ካልቨርት ለአፍታ ሲቀጣጠረው የማይችለው ስቃይ እስከ ጉሮሮው ተናነቀው። እጆቹን ግን ከማርቆስ አንገት ላይ አላላላም። ማርቆስ ለሁለተኛ ጊዜ ጉልበቱን አወናጭፎ ሲሰድ ካልቨርት በጉልበቶቹ መሃል የተሰማው ስቃይ የሚያየውን ሁሉ አጨለመበት። ማርቆስ ገልብጦት ተነሳ።

ተፋጠጡ። ፊት ለፊት ሽብረክ ሽብረክ ብለው ተፋጠጡ። የመጨረሻ ምት በአንደኛው ላይ አርፎ ዓለም ከማለፏ በፊት ተፋጠጡ። ካልቨርት የሚንቀጠቀጡ ጉልበቶቹ ቢያስቸግሩትም እንደ ግስላ ጥርሱን ገጥሞ ከፊጠጠበት ሰው ጋር እስከመጨረሻው ለመፋለም ቆረጠ። ቢሆንም የባላጋራውን ፍጥነት ሊቋቋመውና ሊስተካከለው አልቻለም። የመጀመሪያው ግራ ቡጢ ቀኝ አገጩ ላይ አርፎ ሳይነሳ ሌላ ቡጢ ልቡን ሲደቁሰው ወደኋላ ተወርውሮ ባለቋሚ የሳሎን መብራት ላይ ተዘረገፈ።



የካልቨርትን ሁኔታ የተመለከተው ማርቆስ እሱን ትቶ ሽጉጡ ወደተፈናጠረበት አቅጣጫ መለስ ሲል የገዛ መሣሪያውን ጠላቱ ናትናኤል እጅ ውስጥ አየው። ለአንድ አፍታ ባለበት ረጋ።

"ትንሽ ተነቃነቅ...እዘረጋሃለሁ።" አለ ናትናኤል መሬት ላይ እንደወደቀ የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን የማርቆስን ሽጉጥ በራሱ በማርቆስ ላይ ደግኖ።

ማርቆስ ለአንድ አፍታ የመሸነፍና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ፊቱን ያለበሰው መሰለ። ወዲያው የጋለበው አጋጣሚ በል እንዳለው ሁሉ ወደ ግራ ተወርውሮ ቀኝ እግሩን ናትናኤል አገጭ ላይ አሳረፈው። የታፈነ የጥይት ድምፅ ተሰማ።በጀርባው የተንጋለለውን ናትናኤልን ቁልቁል ሲመለከት የቆየው ማርቆስ በደም የቀላ ደረቱን እንደጨበጠ እየጉተመተመ ወደመሬት አዘቀጠ... "ባንዳ!... ባንዳ!"

"እያዞህ ተርፈሀል።" አለ ካልቨርት የናትናኤልን ክንድ ይዞ ሊያነሳው እየታገለ። "በርታ ቶሎ ከዚህ መውጣት አለብን። ድምፅ አሰምተናል። አንተ ሂድ። እኔ ይገሮት እመጣለሁ ርብቃን።" ናትናኤል ተነስቶ በፍርሃት የምትንቀጠቀጠውን ሴት ተደግፎ በአንድ እግሩ እንደቆመ ካልቨርት ፊቱን መልሶ በስተግራ ወዳለው የመኝታ ቤት በር ሮጠ።

ናትናኤል የተነደለ ጉልበቱን በግራው እንደጨበጠ ህፃን ልጇን የታቀፈችውን ሴት ተደግፎ ከክፍሉ ወጣና ቀጥሎ ወዳለው ክፍል ተጎተተ።

ካልቨርት የመኝታ ቤቷን መዝጊያ ከፍቶ ሲገባ አልጋዋ ላይ ተኝታ አገኛት። ሆዷ ገፍቷል ከአልጋዋ ላይ አፈፍ አድርጎ አንስቷት እየጎተተ ከመኝታ ክፍሏ አወጣት። ማን መሆኑን ለማስረዳት ጊዜ አልነበረውም። ወደደችውም ጠላችውም እንደ ህፃን ልጅ እየጎተተ ወሰዳት። 'ቶሎ መውጣት አለበት... ቶሎ...'

አልታገለችውም። በግድየለሽነት ተጎተተችለት። እያነከሰች ተሳበች ለት። ገርበብ ያሉ ዓይኖቿ አጥርተው የሚያዩ አይመስሉም። ወደፊት መጥቶ ግንባሯ ላይ የተበተነው ጥቁር ፀጉሯ የተጎሳቆለ ፊቷን ሊሸፍነው አልቻለም። ስስ ብጫ ቀሚስ እንዳጠለቀች ባዶ እግሯን ተጎተተችለት። ከመኝታ ቤቷ ወጥተው ሳሎኑን አልፈው ከመተላለፊያው ሲደርሱ ድምፅ የሰማ አንድ የአፓርትመንቱ ነዋሪ በሩን ከፍቶ ብቅ አለ። ወዲያው የካልቨርትን ደም የጎረሱ ዓይኖች ሲመለከት ከፍቶ የያዘውን መዝጊያ ጠረቀመው። ካልቨርት የርብቃን እጅ እንደያዘ ቀጥሎ ካለው ክፍል ውስጥ ገባና በሩን ዘግቶ በጀርባው ተደግፎት ቆመ። የ ዕብድ አገጩ ላይ ያሳረፈበት ቡጢ መሃል አናቱ ድረስ የተሰነጠቀ ይመስል ሲነዘረው ተሰማው።

ርብቃ አዲስ የገባችበትን ክፍል እስክትለማመደው ድረስ ለአፍታ ፈዘዝ ያለች መሰለች። ወዲያው ከፊት ለፊቷ ባለው የሳሎን ፎቴ ላይ በደም ተበክሎ የተንጋለለው ናትናኤል መሆኑን ስትገነዘብ ራሷን ለመቆጣጠር ተሳናት። ተንደርድራ ሄዳ ተጠመጠመችበት።

ማንም ማንንም ለማባበል ብታርታት አልነበረውም። ድንጋጤ ሲያልፍ መረጋጋት ሲተካ ካልቨርት የርብቃን ክንድ ይዞ በትግል ከናትናኤል ላይ አነሳት። ናትናኤል በጀርባው እንደተንጋለለ ከፊቱ ቆማ ሳግ የሚተናነቃትን እርጉዝ ሴት በጭንቀት ይመለከታት ጀመር...ይቅርታ ለመጠየቅ...ይቅርታ ለመለመን ግን ሃይል አልነበረውም።ዓይኖቹ ብቻ በጭንቅ ግራ በመጋባት ተንቀዋለሉ።

"ያንተ ልጅ ነው...ናትናኤል ሳልነግርህ ቀርቼ ነው... እርግገፎልሃለሁ ናትናኤል..." ርብቃ ፎቴው ስር ተንበርክካ የሚተናነቃትን ሳግ እየታገለች ልታስረዳው ታገለች። በጭንቀት የተወጠረውን ፊቱን ስትመለከት እርግዝናዋ ግራ ያጋባው መሰላት። 'ናትናኤል ያንተ ነው' ወተወተች። ካልቨርት የናትናኤልን ሁኔታ ሲመለከት ርብቃን ጎትቶ ከተንበረከከችበት አንሳትና ህፃን ልጇን እንዳቀፈች እራቅ ብላ ወደቆመችው ሴት ፊቱን መለሰ...

"ደዘሻት ውስጥ ግቢ... ቁስሉን ልደለት።"

ሴትየዋ የርብቃን ክንድ በትግል እየጎተተች ወደ መኝታ ክፍሏ ይዛት ገባች።

ካልቨርት ቀልጠፍ ብሎ ከናትናኤል ጎን በርከክ አለና ቱታ ሱሪውን ቀድዶ ቁስሉን ገለጠው። በጥይት የተነደለውን የጉልበቱን ሎሚ ስቡን ሲመለከት ሳይታወቀው ዓይኖቹን ጨፈነ።

"ሎሚዬን አግኝቶኛል። አይደል? ጉልበቴን አግኝቶኛል።" አለ ናትናኤል በጀርባው እንደተንጋለለ ዓይኖቹን ጣሪያ ላይ እንደሰካ ጥርሱን ነክሶ ስቃዩን ለመቻል እየታገለ።

"አዎ።" አለ ካልቨርት ቁርጥ ባለ ድምፅ። ናትናኤል ያለጥርጥር የዕድሜ ልክ ሽባ መሆኑ ውስጡን እየረበሸው። "አይዞህ ዋናው ህይወትህ መትረፉ ነው።"

ካልቨርት ከተበረገደው ቁስል የሚያገፍውን ደም ለማቆም ይታገል ጀመር። ከናትናኤል እግር ላይ ቀድዶ ያነሳውን ቱታ ለሁለት ተርትሮ ቁስሉን ግጥም አድርጎ አሰረው። እግሩን ወደላይ ሰቅሎ ያዘለት። በቁስሉ ላይ የታሰረው ካኪ ደም እየጠጣ ደም እየጠገበ ቢቀላም ደሙ ቀስ በቀስ መፍሰሱን አቆመ።

ካልቨርት የናትናኤልን እግር ቀና አድርጎ አስደግፎ ወደ መደርደሪያው ሄደና አንድ የውስኪ ጠርሙስ ይዞ ተመለሰ። ናትናኤል ጎን ወንበር



ላይ ተቀምጦ የውስኪውን ጠርሙስ ክዳን ከፍቶ በአፉ ሙሉ ተጎነጨለት። የእንገጩን ስቃይ ሊቋቋመው አልቻለም። እንገጩን ብሎ ከመሬት የደባለቀው ሰው ናትናኤል በተኮሰው ጥይት የተበሳ ደረቱን አፍኖ ሲወድቅ ያለው የተናገረው መጣበት "ባንዳ!"። ራሱን ጠላ ካልቨርት። ድንገት የመኝታ ቤቱ በር ሲከፈት ካልቨርት ድጋሚ ሊጎነጭለት ያነሳውን ጠርሙስ መለስ አድርጎ ፊቱን አዞረ።

"እረ... አመማት!" አለች የህፃኗ እናት እየተርበተበተች።

"ምን?" አለ ካልቨርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሴትየዋ የተናገረችው አማርኛ አልገባህ ሲለው።

"ርብቃ..." አለች ሴትየዋ በእንግሊዝኛ መልሳ። "አመማት።"

"ምነው?" አለ ካልቨርት ከተቀመጠበት ደንግጦ እየተነሳ።

"እንጃ ምጥ መሠለኝ።" አለች ሴትየዋ በፍርሃት።

"በእየሱስ! እርግጠኛ ነሽ?"

"መሰለኝ... ሁኔታዋ እንደዛ ነው።"

"ልትረጃት አትችይም?"

"እኔ... አላውቅበትም።" የሴትየዋ ገፅ በፍርሃት ዋኘ።

ከመኝታ ቤቷ የስቃይ ጩኸት ተሰማቸው።

"እዚህ... ምድር ቤት አንድ አሮጊት አሉ... ግሮሰሪ ያላቸው... ልጥራቸው?" አለች ሴትየዋ የካልቨርትን ግራ መጋባት ስትመለከት ጠንከር ለማለት እየሞከረች።

"ሊረዷት ይችላሉ?"

"እንጃ... ብቻ አሮጊት ናቸው። ከኛ የሚሻሉ ይመስለኛል።"

ድጋሚ የርብቃ ጩኸት በተከፈተው በር አምባረቀ።

"ሂጅ-ሂጅ...ቶሎ በይ አምጫቸው።" አለ ካልቨርት ወደ በሩ እየገፋት።

የህፃኗ እናት እንደወጣች በሩን ቆለፈና ፊቱን መልሶ በጀርባው የተንጋለለውን ናትናኤልን ተመለከተው። ዓይኖቹን ጨፍኖ ተጋድሟል። ወዲያው አላስችልህ ሲለው የተቆራረጠ የማቃሰት ድምፅ ወደሚሰማበት የመኝታ ቤት ተጠጋ።

ርብቃ አልጋው ላይ በጀርባዋ እንደተንጋለለች ሁለት እጆቿን ወደኋላ ልካ የተኛችበትን አልጋ የራስጌ እንጨት ይዛ ታቃስታለች፡፡ በጆሮ ግንዶቿ የሚንቆረቆረውን ላብ ሲመለከት ካልቨርት ጥፋ ጥፋ አለው። ብዙም ሳትቆይ የህፃኗ እናት ባለግሮሰሪዋን ሴት አስከትላ መጥታ በሩን ስታንኳኳ ካልቨርት በድን መስሎ ከቆመበት የመኝታ ቤት በር ሮጥ ብሎ ከፈተላቸው።እንደገቡ በሩን መልሶ ቆለፈው። ሴቶቹ ተከታትለው ወደመኝታ

ቤት ሲያመሩ በዓይኑ ተከተላቸው::ባይገባውም፤ ምን እንደተባባሉ ባይረዳም ሴቶቹ በጥድፊያ እየወሩ እየተነጋገሩ ወደ መኝታ ቤቷ ሲገቡ እፎይታ ተሰማው::

ተጠባበቀ:: ደቂቃዎች እየተከታተሉ አለፉ:: ከመኝታ ቤት የገቡት ሴቶች ግን ብቅ አላሉም:: እንቅስቃሴ ሲሰማው ፊቱን መለሰ:: ናትናኤል ነበር::

"እይዞህ... ድነሃል..." አለ ካልቨርት ወደ ናትናኤል እየተጠጋ "... እምልጠናል::"

ካልቨርት ናትናኤል ጎን በርከክ ብሎ ትከሻውን ጨብጦ ጨብጦ እያደረገ አበረታታው:: ናትናኤል ራሱን መቆጣጠር እንደቻለ ካልቨርት በርከክ ብሎ ከነበረበት ተነሳ:: ሬዲዮኑን ከፈተና ናትናኤል ላይ አፈጠጠ:: የናትናኤል ፊት ከሬድዮኑ ጋር ይቋጠር ይፈታ ጀመር:: ካልቨርት አንዴ የሚለፈልፈውን ሬዲዮ አንዴ ናትናኤልን እየተመለከተ ተጠባበቀ፤ ትዕግስት አጣ::

"ምንድነው የሚለው? ለእኔም ተርጉምልኝ እንጂ!" አለ ካልቨርት ናትናኤል ላይ እንዳፈጠጠ::

"አልገባኝም..." አለ ናትናኤል ካልቨርት ዝም እንዲል አንድ እጁን ብድግ አድርጎ ምልክት እየሰጠው::

"እንዴት? ምን ማለት ነው አልገባኝም?" ትዕግሥት አጣ ካልቨርት::

ለአንድ አፍታ ናትናኤል ቀና ብሎ አይኖቹን ካልቨርት ላይ ተከለ:: ወዲያው ግራ በመጋባት ስሜት ፊቱን መልሶ በሬድዮው ላይ አፈጠጠ::

"ስለ እየሱስ ብለህ ምን እንደሚል ተርጉምልኝ!" አለ ካልቨርት በስጨት ብሎ::

"እየተመለሱ ነው::"

"እነማ?" አለ ካልቨርት ግራ ተጋብቶ "ንገረኝ እንጂ" አለ ናትናኤል ጆሮውን በሬድዮው ላይ ለክቶ ዝም ሲል::

"መሪዎቹ... የአፍሪካ መሪዎች::" አለ ናትናኤል::

"የት ነው የሚመለሱት?"

"የአፍሪካ አንድነት ስብሰባ ዛሬ ምሽቱን በሦስት ሰዓት ይጀመራል ተብሎ ሲጠበቅ ስብሰባውን ለመካፈል ወደ አዲስ አበባ የገቡ የአፍሪካ



መሪዎች ከስብሰባው መክፈቻ ቀደም ብለው ወደየአገሮቻቸው እየተመለሱ ነው' ነው የሚለው ሬድዮኑ::" አለ ናትናኤል ግራ የተጋቡ ዓይኖቹን ካልቨርት ላይ አፍጥጦ::

"ሊሆን አይችልም!" አለ ካልቨርት "ተሳስተሃል... እንዲያ ሊል አይችልም!"

"የሰማሁትን ነው'ኮ የምነግርህ" አለ ናትናኤል ራሱን የተጠራጠረ ይመስል ትከሻውን ሰብቆ:: "ሦስት የአፍሪካ መሪዎች መዲናዋን ለቀው ወደ አገሮቻቸው ተመልሰዋል... ቆይ... ቆይ" አለ ናትናኤል አትኩሮቱን ወደ ሬድዮው መልሶ::

"ምንድነው... ምንድነው የሚለው?" አለ ካልቨርት ናትናኤል ጎን ቁጢጥ እያለ::

"የኢትዮጵያ መንግሥት የስብሰባው መክፈቻ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም ዛሬ ምሽቱን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባለሥልጣናትን መጠየቁን ውስጥ አዋቂዎች ለጋዜጠኞች ገለፁ ነው የሚለው::" አለ ናትናኤል ከፊት ለፊቱ ቁጢጥ ያለውን ካልቨርትን እየተመለከተ::

"ሊያከሽፉት ነው!" አለ ካልቨርት በስጨት ብሎ "ከሃዲዎች!... ምስጢሩ ወጥቷል::"

"ድሮም እብደት ነበር::" አለ ናትናኤል በለሆሳስ:: "አበቃለት!"

"ምናልባት..."

"ምን ማለት ነው ምናልባት?"

"ለጊዜው የጊዜው እብደት አብቅቶለት ይሆናል:: ለአፍሪካ ችግር መልስ እስካላገኘን ድረስ ግን ሌላ እብደት ጊዜውን ጠብቆ እንደሚፈነዳ አትጠራጠር::" አለ ካልቨርት ዓይኖቹን ቦዝዝ አድርጎ::

ከተዘጋው የመኝታ ቤት ጀርባ ጩኸት ተሰማቸው:: በድንጋጤ ተፋጠጡ:: የህፃኗ እናት በሩን ከፍታ ብቅ አለች:: ካልቨርት በፍርሃትና በጥያቄ መልክ አፈጠጠባት::

"ደህና ነች...ምጥ ነው:: አለጊዜው ነው የመጣው:: ሰባት ወሩ ነው አለችን:: ግን ምንም አትልም::" አለች የህፃኗ እናት ተረጋግታ:: ናትናኤል የሚሰማውን የሚያየውን ሁሉ መሸከም አቃተው:: ድንገት የመኪና ፍሬን በፍጥነት ሲያዝ ያሰማው ሲጥታ ከውጭ ተሰማቸው:: ካልቨርት ቶሎ ብድግ ብሎ ወደ መስኮቱ ተጠጋና መጋረጃውን በስሱ ገለጥ አድርጎ ወደ ውጭ ተመለከተ::ውጭው ቢጨልምም ከአፓርታማው አጥር ግቢ መግቢያ

ላይ ከደረሰችው መኪና ውስጥ ሦስት ሰዎች በጥድፊያ ወጥተው ሽማግሌውን በረኛ ወደጎን ገፍትረው እየሮጡ ወደ አፓርትመንቱ ሲጠጉ ታየው። ካልቨርት ፊጠን ብሎ ፊቱን መለሰና የህፃኗን እናት ርብቃ ወዳለችበት ክፍል እንድትገባና ድምፃቸውን እንዲያጠፉ ነገራት። ሴትየዋ ወደ መኝታ ክፍሏ ስታመራ ካልቨርት በፍጥነት ወደ ዋናው በር ሄዶ መዝጊያው መቆለፉን አረጋገጠ። ወዲያው መብራቱን አጥፍቶ በስሷ የጨረቃ ብርሃን እየተመራ ወደ ናትናኤል ተጠጋ።

"እነሱ ናቸው።" አለ ካልቨርት ስማቸውን መጥራት እንደፈራ ሁሉ በሹክሹክታ።

በጨለማው ውስጥ አንዳቸው የአንዳቸውን ትንፋሽ እያዳመጡ ተጠባበቁ። ከተቆለፈው በር ጀርባ በመተላለፊያው ላይ የእግር ኮቴዎች ተሰማቸው።ተከትሎም ከጎን ያለው ክፍል በር ተበርግዶ ሰዎች ተከታትለው ሲገቡ አዳመጡ። ካልቨርትና ናትናኤል በጨለማው ውስጥ በፍርሃት ተያዩ።

የርብቃ ጩኸት ድንገት አስተጋባ።

ናትናኤልና ካልቨርት በድንጋጤ ደርቀው ቀሩ። በመተላለፊያው የእግር ኮቴ ተሰማቸው። ተጠባበቁ። የመኪና ድምፅ ሲጥ... ጥ! አለ። ካልቨርት በቀስታ ወደ መስኮቱ ተጠጋ። ቀደም ብለው ከአፓርትመንቱ አጥር ግቢ በር ላይ ከቆሙት ሁለት ተደርበው ከቆሙ ሌሎች ሁለት መኪናዎች የወረዱ ስምንት ሰዎች የያዙትን የጦር መሣሪያ ለመሸሸግ እንኳን ሳይሞክሩ ወደፊት እንደደገኑ የአፓርትመንቱን የአጥር በር አልፈው ተከታትለው ገቡ። ከግቢው መሃል እንደደረሱ ከአፓርትመንቱ ከወጣ አንድ ሰው ጋር ሰብሰብ ብለው ተነጋገሩ። ወዲያው ሁለቱ ሰዎች ወደ መጡባቸው መኪናዎች ሲመለሱ የተቀሩት ወደ አፓርትመንቱ ተጣደፉ። ካልቨርት ወደ ናትናኤል ተመልሶ ያየውን ሁሉ ለናትናኤል አንሾካሾከለት።

"አፓርትመንቱን የሚፈትሹ ይመስልሃል?"አለ ናትናኤል ጨለማው ላይ አፍጥጦ።

"ፈጣሪ አያድርገው።"
"ስንት ሰዓት ነው?" ናትናኤል ጠየቀ።
"ሁለት ከሰላሳ።" አለ ካልቨርት ሰዓቱን ወደ አይኑ አስጠግቶ።

የመኝታ ቤቱ በር ተከፈተ። ከውስጥ የሚወጣው ደብዛዛ ብርሃን የሳሎኑን ጨለማ ወገግ አደረገው የህፃኗ እናት አንድ ነገር ታቅፋ ተጠጋቻቸው።

"ተገላገለች።" አለች በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።



ባለ ሶስራዊም አሮጊት ቀረብ ብለው የህፃኑን ፊት ትኩር ብለው ተመለከቱ። ካልቨርትና ናትናኤል የሚመለሱት ግራ ገብቷቸው በጨርቅ በተጠቀለለው አዲስ ህይወት ላይ አፈጠጡ።

"ወንድ ልጅ ተገላገለች።" አለች የህፃኗ እናት ድጋሚ. ወንዶቹ ያለስሜት የመሰለ ዝም ሲሏት፤ አሁንም ከወንዶቹ መልስ አላገኘችም። ሁለቱም ዝም ብለው እሩቅ ሄዱባት።

"ቆንጆ ልጅ አይደለም?" አለች ከተደናገጡት ወንዶች መልስ ያጣችው ሴት ፊቷን ወደ አሮጊቷ መልሳ በአማርኛ።

"የዛሬ ልጆች ቆንጆዎች ናቸው።" አሉ አሮጊቷ አይኖቻቸውን ከህፃኑ ፊት ላይ ሳይነቅሉ።

ሴትዮዋ በአማርኛ ቋንቋ የተመላለሱት ያልገባው ካልቨርት ወደ ናትናኤል ፊቱን መልሶ ጠየቀው።

"ምንድነው ያሉት?"

"የዛሬ ልጆች ቆንጆዎች ናቸው ነው ያሉት" አለው ናትናኤል የሚታገለውንና የሚተናነቀውን የደስታ እንባ እየታገለ።